

# የምስራቹን ለሙስሊሞች ለማድረስ ከየት እንጀምር?



ሳሙኤል ግሪን

# የምሥራቹን ለሙስሊሞች ለማድረስ ከየት እንጀምር?

በቄስ ሳሙኤል ግሪን

የአዘጋጁ መብት በሕግ የተጠበቀ ነው

Rev. Samuel Green ©2024

www.engagingwithislam.org

ትርጉም፡- እውነት ለሁሉ ክርስቲያናዊ አገልግሎት

www.ewnetlehulu.net

መስከረም 2017

# ማውጫ

መግቢያ ........................................................................ II

ፍቅር ለሰው ልጆች ሁሉ ........................................................................5

እስልምናን መረዳት ........................................................................16

ወንጌል ........................................................................29

ኢየሱስ አምላክ ነውን? ........................................................................44

ሥላሴና ተውሒድ ........................................................................68

ደህንነት ........................................................................94

መቅደስ እና እስላማዊ አስተምህሮ ........................................................................117

የኢየሱስ ሞት ........................................................................123

ሙሐመድ ማን ነበር? ........................................................................146

ሙስሊሞችና መጽሐፍ ቅዱስ ........................................................................167

ታሪክ ........................................................................201

የስብከት ምሳሌዎች እና እስልምና ........................................................................231

# መግቢያ

ክርስትናን የተቀበልኩት በ1986 ክሪስ ሙር የተሰኘ ሰው እሠራበት ወደነበረው የነዳጅ ማደያ ገብቶ ክርስቲያን መሆን አለመሆኔ ከጠየቀኝ በኋላ ነበር። ስለ እግዚአብሔርና ከእርሱ ጋር ስላለኝ ሕብረት እያሰብኩ የነበረበት ጊዜ ነበርና ክሪስ ወንጌልን ሲያብራራልኝ ሁሉንም ነገር ተረዳሁ። ከዚህ በኋላ ብዙም ሳይቆይ ወደ ቤተ ክርስቲያን መሄድ ጀመርኩ፤ ኢየሱስ ያደረገው ለእኔ ብቻ ሳይሆን ለሁሉም የሰው ልጆች እንደሆነ ማወቅ በመቻሌ ከትንሽ ማንገራገር በኋላ የፍርሃት ስሜቶቼን ድል በመንሳት ወንጌልን ለሌሎች ማካፈል ጀመርኩ።

አንዳንድ ጓደኞቼ ለወንጌል ልባቸው የተዘጋጀ ስለነበረ በእግዚአብሔር ቸርነት ክርስቲያን ሆኑ፣ አንዳንዶቹ ችላ ብለውኝ ነበር፣ የተናደዱብኝም ነበሩ፤ ነገር ግን በሙስሊም ጓደኞቼ ዘንድ የታዘብኩት ቀድሞውንም በኢየሱስ ማመናቸውን ነበር፣ ነገር ግን ፍጹም በተለየ መንገድ ነው። በእምነታቸው ደግሞ እርግጠኞች ነበሩ። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ከብዙ ሙስሊሞች ጋር ፊት ለፊት እንዲሁም በበይነ መረብ ላይ ተነጋግሬያለሁ። በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ያለውን ይዘት ያዳበርኩት ከነዚህ ልምዶች ነው።

ይህንን መጽሐፍ የጻፍኩት ክርስቲያኖች እስልምናን ለመረዳት ከየት መጀመር እንዳለባቸውና ከሙስሊም ጓደኞቻቸው ጋር እንዴት መነጋገር እንዳለባቸው እንዲያውቁ ለመርዳት ነው። በእኔ ልምድ ክርስቲያኖችና ሙስሊሞች እርስ በርሳቸው መግባባትና ውይይታቸውን ማሻሻል ከፈለጉ ከየት መጀመር እንዳለባቸው ማወቅ ቁልፍ ነገር ነው። አለማወቅ አንዳንድ ጊዜ ጥሩ ነው ሊባል ይችል ይሆናል፣ እግዚአብሔር ለወንጌልና ለቤተክርስቲያን የሚጓጓ አንተን የሚሰማ ሰው አዘጋጅቶ እንደሆነስ። በቅርቡ ወደ ቤተክርስቲያን ጎራ በማለት ክርስቲያን የሆነና ተሳትፎ እያደረገ የሚገኝ አንድ የሙስሊም ቤተሰብ አውቃለሁ። ይሁን እንጂ ለአብዛኞቹ ሙስሊሞች ጉዳዩ እንዲህ አይደለም። በመሆኑም ከየት መጀመር እንዳለበት ማወቅ ጠቃሚ ነው። አለማወቅ የሚከተሉትን አሉታዊ ውጤቶች ሊያስከትል ይችላል።

በመጀመሪያ ፣ በጭራሽ አትጀምሩም እንበል። ሙስሊም ጓደኛ አላችሁ፤ ለዚህ ጓኛችሁ ስለ እግዚአብሔር መናገር ትፈልጋላችሁ፣ ነገር ግን ከየት እንደምትጀምሩ እርግጠኛ ስላልሆናችሁ እንዳትሳሳቱ ደግሞ ትንሽ ስለምትፈሩ በጭራሽ አትጀምሩም። ይህ መጽሐፍ ከየት መጀመር እንደሚገባችሁ ያመላክታችኋል።

በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ ትጀምሩ ይሆናል፤ ነገር ግን ከተሳሳተ ቦታ ትጀምራላችሁ ምክንያቱም ለውይይታችሁ እንቅፋት የሚሆኑ ጉዳዮችንና ቅድመ ሐሳቦችን አታውቁም። ከተሳሳተ ቦታ ስትጀምሩ ለጥያቄዎቻቸው መልስ ባልሰጣችሁበት ሁኔታ መልስ እየሰጣችሁ ያላችሁ ሊመስላችሁ ይችላል። እኔ በግሌ ከተሳሳተ ቦታ ስጀምር የተወሰነ ለውጥ ይታያል ነገር ግን እጅግ ቀርፋፋ ሒደት ይሆንብኛል። እርስ በርስ መግባባት ያልቻልነው ለምን እንደሆነ

ለማወቅ ረጅም ጊዜ በመውሰድ የጠለቀ ምርምር ማድረግ አስፈልጎኛል። በዚህ ወቅት ከብዙ ሙስሊም ጓደኞቼ ጋር ግንኙነታችን ተቋርጦ የነበረ ሲሆን ከዚያ በኋላ ምንም የተለየ ለውጥ አልታየም። ከስህተቶቼ መማር ትችላላችሁ። ይህ መጽሐፍ ሙስሊሞች ያላቸውን ቅድመ ግምት እንድትረዱና ይበልጥ ፍሬያማ የሆነ ውይይት እንድታደርጉ ይረዳችኋል።

በሦስተኛ ደረጃ፣ ከየት መጀመር እንዳለባችሁ እርግጠኛ ካልሆናችሁ ሙስሊም ጓደኛሁ ከሆነ ቦታ ይጀምራል! ይህ ሁኔታ በእኔ ላይ የደረሰ ሲሆን ሙስሊም ጓደኛዬ የውይይታችንን አጀንዳ ሲያዘጋጅና ውይይቶችን ሲቆጣጠር አገኘው ነበር። ሙስሊሞች የሚናገሩትን ማዳመጥና ለጥያቄዎቻቸው መልስ መስጠት መልካም ነው ነገር ግን ስሜታዊ መሆንና ሁሉንም ነገር እንዲቆጣጠሩ ማድረግ ተገቢ አይደለም። ለሚያነሷቸው ጥያቄዎች መልስ መስጠት ብቻ ሳይሆን ክርስቲያናዊ አቋማችንን ለእስልምና መልእክት በሚያስተላልፍ መንገድ ማስቀደም መቻል ይኖርብናል። ይህ መጽሐፍ በእስላማዊ አጀንዳ እንዳትመሩ ያዘጋጃችኋል።

አብዛኞቹ ምዕራፎች ተመሳሳይ አወቃቀሮች አሏቸው፤ እነርሱም ክርስቲያኖች በአንድ ርዕሰ ጉዳይ ከየት መጀመር እንዳለባቸው እንማማራለን፣ ከዚያም ርዕሰ ጉዳዩን በዝርዝር እንመረምራለን፣ በመጨረሻም አተገባበር ላይ ተወያይተን አንዳንድ ተደጋግመው የሚነሱ ጥያቄዎችን እንመልሳለን።

ይህንን መጽሐፍ በተግባር ላይ ለማዋል እንዲረዳ፣ ከአብዛኞቹ ምዕራፎች በተጓዳኝ የተዘጋጁ engagingwithislam.org/evangelistic-resources/ ከተሰኘ ገጽ አውርዳችሁ ለሙስሊም ጓደኞቻችሁ ልትሰጡ የምትችሏቸው የወንጌል ቡክሌቶች ተዘጋጅተዋል። ድረ ገጹ መጽሐፉን ሊደግፍ የሚያስችል የመስመር ላይ የስልጠና ኮርስም አለው። ድረ ገጹን መጎብኘታችሁን አረጋግጡ።

ወንጌልን በዓለማዊው ባሕል ውስጥ ስናካፍል ባሕሉ የእግዚአብሔር መኖር፣ ሳይንስ፣ ስቃይ፣ ጾታ እና ታሪክ በሚሉ ጥያቄዎች ወንጌልን ወደ ኋላ ይገፋል ይህ ደግሞ በእነዚህ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ እንድናተኩር ያስገድደናል።

ወንጌልን ለሙስሊሞች ስናካፍል ስለ ሥላሴ፣ ስለ ኢየሱስ ማንነትና ሥራ፣ እንዲሁም ስለ ድነት ጥያቄዎችን በማንሳት ወንጌሉን ወደ ኋላ ይገፋል። እነዚህ በጣም ጥሩ ጥያቄዎች ናቸው። እስልምና ትኩረትን የሚከፋፍል ሳይሆን ዋና ዋና አስተምህሮቻችንን የምንማርበት ዕድል ነው።

ይህ መጽሐፍ ለህትመት እንዲበቃ በማድረግ ረገድ ድጋፍ ያደረጉትን ወገኖች አስቀድሜ ለማመስገን እወዳለሁ። ይህንን ሥራ መሥራት የቻልኩት በእናንተ ድጋፍ ብቻ በመሆኑ እናንተን ወክዬ የምሠራ ሰው ነኝ። አመሰግናለሁ።

ለጄይ ስሚዝ፣ ለጆኬን ካዝ እና ለእስልምና መልስ ቡድን ምስጋናዬ የላቀ ነው።[1] የዚህ ቡድን አባላት ከተለያየ የዓለም ክፍል የተውጣጣን የመንግሥቱ ሠራተኞች ነን። በዚህ ረገድ ስላሳያችሁት ጽናት እንዲሁም ከእናንተ ስለተማርኩት ነገር ላመሰግናችሁ እወዳለሁ። ይህ ዓለም አቀፍ ኅብረት በእጅጉ ጠቅሞኛል።

እንዲሁም ሙስሊም ጓደኞቼንና ወዳጆቼን ላመሰግናቸው እፈልጋለሁ። ዌሳም ቻርካዊ፣ አብዱላህ ኩንዴ፣ ሙስጠፋ አርጃ፣ ዛኪር ሑሴን፣ ሙስጠፋ አል ሻካርጂ፣ ዲያሳ ሙሐመድ፣ ሻቢር አሊ፣ አብዱላህ አል አንዳሉሲ፣ ፋራዝ ኖማሚ፣ ኡሥማን በደር፣ ሻሂር ናጋ፣ ኢጃዝ አሕመድ፣ ኬይሳር ትራድ፣ አብዱል ጀሊል አሕመድ፣ ቤይላል ራኬሃ፣ ዋሲም ራዝቪ፣ ብራዘር ኢምራን እና አድናን ረሺድ። ለሁሉም ክርክሮችና ተከታታይ ውይይቶች አመሰግናለሁ። ያለፉትን 15 ዓመታት ወደ ኋላ መለስ ብዬ ሳስበው አንዳንችን ሌላችንን በመረዳት ረገድ ዕድገት እንዳሳየን እገነዘባለሁ።

ለፊሊፕ ጄንሰን፣ ግሬም ጎልድስዎርዝ፣ ስቱዋርት ቢንስ፣ ማርክ ዱሪ፣ አንድሪው ሙዲ፣ ዴቪድ ሆህን፣ እና ሪቻርድ ሹማከ ልዩ ምስጋና አለኝ። ሁላችሁም በተለያየ መንገድ ረድታችሁኛል።

በመጨረሻም፣ አባቴንና እናቴን እንዲሁም ቤተሰቦቼን ሁሉ ለማመስገን እፈልጋለሁ። ስላደረጉልኝ ድጋፍ፣ ስላሳዩት ጽናት፣ ስላስተማሩኝ ድፍረት እና ስለነበረን የደስታ ጊዜያት ሁሉ ምስጋና ይገባቸዋል።

በክርስቶስ ወንድማችሁ ሳሙኤል ግሪን።

2024 ዓ.ም

## በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ጥቅም ላይ የዋሉ የቁርአንና የሐዲስ ማጣቀሻዎች

ቁርአን በእስልምና ውስጥ ዋናው መጽሐፍ ሲሆን quran.com ድረ ገጽ ላይ ይገኛል። በውስጡ ያሉት ምዕራፎች ሱራ ይባላሉ።

በእስልምና ሁለተኞቹ ቅዱሳት መጻሕፍት ሐዲስ ይባላሉ። ሐዲስ የሚለው ቃል 'አጭር ትረካ' ማለት ነው።

በ sunnah.com ላይ የሚገኙትን የሐዲስ የቁጥር ሥርዓቶች ተጠቅሜያለሁ።

[1] answering-islam.org

# ምዕራፍ 1

## ፍቅር ለሰው ልጆች ሁሉ

እስልምና በመላው ዓለም እየተስፋፋ ያለ ሃይማኖት ነው። ይህንን በብዙ መንገዶች መታዘብ እንችላለን፤ ሙስሊም አገራት በዓለም የፖለቲካ መድረኮች ላይ ወሳኝ ሚናዎችን ይጫወታሉ፤ ዩኒቨርሲቲዎች እስልምናን የተመለከቱ የትምህርት ዘርፎችን እየከፈቱ ነው፤ ሙስሊም ወዳልሆኑ አገራት የሚደረጉ የሙስሊም ስደቶች ቀላል ግምት የሚሰጣቸው አይደሉም፤ ጂሃዳውያን ወታደራዊ ጥቃቶችን ያደርሳሉ፤ ሙስሊም ጎረቤቶች፣ ጓደኞች፣ የሥራ ባልደረቦችና ደንበኞች ያሏቸው ክርስቲያኖች ቁጥር የትየለሌ ነው።

ለዚህ እስላማዊ ማንሠራራት ሰዎች በተለያዩ መንገዶች ምላሽ ይሰጣሉ። አንዳንዶች ንግዳቸውን ለማጧጧፍ እንደ ጥሩ የኢኮኖሚ ዕድል ይቆጥሩታል፤ አንዳንዶች ሕብረ ባሕላዊነትን ለመለማመድ እንደ ጥሩ አጋጣሚ ይቆጥሩታል፤ አንዳንዶች የትዳር አጋር የማግኛ አጋጣሚ ያደርጉታል፤ አንዳንዶች ደግሞ ምንም ግድ ላይላቸው ይችላል። ብዙ መንግሥታት ሙስሊሞችን ለመቀበልና ለማስተናገድ እየተጠነቀቁ በአካባያቸውና በውጪ አገራት የሚገኙትን ጂሃዳውያን ጥቃቶች በጦር ኃይል ለመመከት ሲሞክሩም ይስተዋላል። ጉዳዩ የሚያሳስባቸው፣ የሚፈሩ፣ የሚቆጡ፣ ግራ የተጋቡና በጉዳዩ ውስጥ ጣልቃ መግባት የማይፈልጉ ችግሩ ግን እንዲወገድ የሚመኙ ብዙ ሰዎች አሉ።

በዚህ የመክፈቻ ምዕራፍ ክርስቲያኖች በዙሪያችን ካለው ዓለማዊ አካሄድ በተቃራኒው ለእስልምና ክርስቲያናዊ ምላሽ ሲሰጡ ከየት መጀመር እንደሚገባቸው እጠቁማለሁ። እንደ ክርስቲያኖች በዙርያችን የሚገኘውን ዓለም ልማድ ከመከተል ይልቅ ክርስቲያናዊ በሆነ መንገድ ምላሽ መስጠት እንዳለብን እናውቃለን። መረዳታችን የጠራ እንዲሆንና ልባችንና የውስጥ ሐሳባችን በእግዚአብሔር ፊት የቀና እንዲሆን እንሻለን። ስለዚህ የክርስቲያን ምላሽ ምን መሆን አለበት? ከየት እንጀምር?

እግዚአብሔር ከጀመረበት ቦታ መጀመር ያሻናል፤ እርሱም ሁሉን ሰው መውደድ ነው:-

> “በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዶአልና።” (ዮሐ. 3፡16)

> “ይህን ስለቆረጥን የክርስቶስ ፍቅር ግድ ይለናልና፤ አንዱ ስለ ሁሉ ሞተ፤ እንግዲያስ ሁሉ ሞቱ።” (፲ቆሮ. 5፡14)

ይህ የእግዚአብሔር ፍቅር ሙስሊሞችን ጨምሮ ሁሉንም ሰዎች እንዴት አድርገን ማስተናገድ እንዳለብን ጥሩ ተምሳሌት ነው ።

ሰዎችን መውደድና ለሰዎች መጠንቀቅ እንደሚገባን ኢየሱስና ሐዋርያው ጳውሎስ ግልፅ አድርገዋል።

> "ባልንጀራህን ውደድ ጠላትህንም ጥላ እንደ ተባለ ሰምታችኋል። እኔ ግን እላችኋለሁ፥ በሰማያት ላለ አባታችሁ ልጆች ትሆኑ ዘንድ ጠላቶቻችሁን ውደዱ፥ የሚረግሙአችሁንም መርቁ፥ ለሚጠሉአችሁም መልካም አድርጉ፥ ስለሚያሳድዱአችሁም ጸልዩ፤ እርሱ በክፎዎችና በበጎዎች ላይ ፀሐይን ያወጣልና፥ በጻድቃንና በኃጢአተኞችም ላይ ዝናቡን ያዘንባልና።" (ማቴ. 5፡43-45)
>
> "ባልንጀራህን እንደ ራስህ ውደድ።" (ማር. 12፡31)
>
> "እንግዲያስ ጊዜ ካገኘን ዘንድ ለሰው ሁሉ ይልቁንም ለሃይማኖት ቤተ ሰዎች መልካም እናድርግ።" (ገላ. 6፡10)

ኢየሱስ ስለ ደጉ ሳምራዊ በሉቃስ 10 ላይ የተናገረውም ምሳሌ ሙስሊሞችን ጨምሮ ለሰዎች ሁሉ መልካም ማድረግ እንደሚገባን ያስተምረናል። ከዚህም በመነሳት ሙስሊሞችን ትወዳላችሁን? ብዬ እጠይቃችኋለሁ።

## ሙስሊሞችን ትወዳላችሁን?

ገሚስ አገልግሎቴ ወደ ተለያዩ አካባቢዎች በመጓዝ ክርስቲያኖችን ስለ እስልምና ማስተማርን ያጠቃልላል። በነዚህ ጉዞዎቼ ወቅት ይህንን ጥያቄ ለክርስቲያኖች ሳቀርብ አዎንታዊ ምላሽ አገኛለሁ። ሙስሊም ጓደኞች ስላሏቸው ሊሆን ይችላል። ባይኖራቸው እንኳ እንደ ማንኛውም ሰው ለሙስሞች ይጠነቀቃሉ፤ ፍቅርን ያሳይዋቸዋል። ሙስሊም ስደተኞች በአውስትራሊያ ውስጥ ቦታ እንዲያገኙ ጥረት የሚያደርጉ ክርስቲያኖችን አውቃለሁ። ማረፍያ ቦታ፣ ምግብና መንግሥታዊ ሰነዶችን በማዘጋጀት እንዲሁም ቋንቋ በማስተማር ይረዷቸዋል። ሌሎች ክርስቲያኖች ደግሞ ሙስሊሞችን ያለገደብ ሲወዳጁ አይቻለሁ። ይጸልዩላቸዋል፣ በጋራ ይሠራሉ፣ ገፊ ከሆኑ አስተያየቶችም ይከላከሏቸዋል። ወዳጅነትን ለማጎልበትና ለበለጠ ትውውቅ ማሕበራዊ መርሃ ግብሮችን በማዘጋጀት ሙስሞችን የሚጋብዙ የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች አሉ። በተወሰኑ አጋጣሚዎች ደግሞ ክርስቲያኖቹ ሳያስቡበት ቤተክርስቲያንን የሚጎበኙ ሙስሊሞች አጋጥመውኛል። እንዲህ ያሉ የፍቅርና የመቀባበል ተግባራትን ማየት በእጅጉ አበረታች ነው። ማድረግ ያለብን ይህንን ነው።

ሆኖም ሙስሊሞችን ይወዱ እንደሆን ስጠይቃቸው አሉታዊ ምላሽ የሚሰጡ ክርስቲያኖችም አጋጥመውኛል። በሙስሊሞች ሁኔታ የመሸማቀቅና የእስልምናን ሃይማኖት አሳሳቢ ሆኖ አግኝተውታል። በእስልምና ስም በየጊዜው የሚፈፀሙ ጥቃቶችን ይመለከታሉ። ምዕራባውያን ሰለምቴዎች የገዛ አገራቸውን ማጥቃታቸውን፣ ግላዊ ጉዳዮቻቸው መነካታቸውን፣ የአገር በቀል የሽብር ጥቃቶች መስፋፋትን እንዲሁም ከመሰል የሽብር

ጥቃቶች ዜጎችን ለመከላከል የሚወጣውን ብዙ ገንዘብ የስባሉ። በሙስሊም አገራት ውስጥ በሌሎች ሃይማኖቶችና በሴቶች ላይ የሚደርሰውን ጭቆና ያስባሉ፤ አንዳንዶቻቸውም የጥቃቱ ሰለባዎች የነበሩ ናቸው። አንዳንድ ሙስሊሞች አውስትራሊያን በመሳሰሉ አገራት ውስጥ የሚገኘውን ነፃነት ሽፋን በማድረግ እስላማዊ ሕግጋትን አስርገው እንደሚያስገቡና በተመሳሳይ ጊዜ ደግሞ እስልምና ላይ የሚሰነዘሩ ትችቶችን ዝም ለማሰኘት እንደሚሠሩ ያስባሉ። ይህ ደግሞ ያስቆጣቸዋል። እናንተ እንደዚያ ትሆኑ? ስለ ሙስሊሞች የሚሰማችሁ ስሜት እንደዚያ ይሆንን?

የደረሰባችሁን ነገር የማስተባበል ፍላጎት የለኝም፤ ነገር ግን በጥላቻም ሆነ በፍርሃት መነዳት የለብንም ለማለት ያህል ነው። በእግዚአብሔር መታመን፣ የኢየሱስን ምሳሌነት መከተልና የእግዚአብሔርን ቃል ልንታዘዝ ይገባናል።

> “ጌታ ቅርብ ነው። በነገር ሁሉ በጸሎትና በምልጃ ከምስጋና ጋር በእግዚአብሔር ዘንድ ልመናችሁን አስታውቁ እንጂ በአንዳች አትጨነቁ።” (ፊልጵ. 4፡6)
>
> “ነገር ግን ስለ ጽድቅ እንኳ መከራን ብትቀበሉ ብፁዓን ናችሁ። ማስፈራራታቸውንም አትፍሩ አትናወጡም፥ ዳሩ ግን ጌታን እርሱም ክርስቶስ በልባችሁ ቀድሱት። በእናንተ ስላለ ተስፋ ምክንያትን ለሚጠይቁአችሁ ሁሉ መልስ ለመስጠት ዘወትር የተዘጋጃችሁ ሁኑ፥ ነገር ግን በየዋህነትና በፍርሃት ይሁን።” (1ጴጥ. 3፡14-15)
>
> “እኔ ግን እላችኋለሁ፥ በሰማያት ላለ አባታችሁ ልጆች ትሆኑ ዘንድ ጠላቶቻችሁን ውደዱ፥ የሚረግሙአችሁንም መርቁ፥ ለሚጠሉአችሁም መልካም አድርጉ፥ ስለሚያሳድዱአችሁም ጸልዩ፤ እርሱ በክፎዎችና በበጎዎች ላይ ፀሐይን ያወጣልና፥ በጻድቃንና በኃጢአተኞችም ላይ ዝናቡን ያዘንባልና።” (ማቴ. 5፡44-45)
>
> “የሚያሳድዱአችሁን መርቁ፥ መርቁ እንጂ አትርገሙ።” (ሮሜ 12፡14)
>
> “ለማንም ስለ ክፉ ፈንታ ክፉን አትመልሱ፤ በሰው ሁሉ ፊት መልካም የሆነውን አስቡ።
>
> ቢቻላችሁስ በእናንተ በኩል ከሰው ሁሉ ጋር በሰላም ኑሩ።” (ሮሜ 12፡17-18)
>
> “ክፉውን በመልካም አሸንፍ እንጂ በክፉ አትሸነፍ።” (ሮሜ 12፡21)
>
> “ማንም ለሌላው በክፉ ፈንታ ክፉ እንዳይመልስ ተጠንቀቁ፥ ነገር ግን ሁልጊዜ እርስ በርሳችሁ ለሁሉም መልካሙን ለማድረግ ትጉ።” (1ተሰ. 5፡15)

እስልምና አሳሳቢ ከሆነባችሁ በጸሎት በጌታ ፊት መቅረብና ስለ ጉዳዩ መጸለይ ያስፈልጋችኋል። በሌላው ክርስቲያናዊ ሕይወታችሁ ማደግ እንደሚገባችሁ ሁሉ በዚህም ረገድ ማደግ ይኖርባችኋል። እንደ ክርስቲያኖች በእምነታችን ማደግ፣ በመጽሐፍ ቅዱስ

ንባባችን ማደግ፣ በጸሎት ማደግ፣ በቅድስና ሕይወት ማደግ፣ ወንጌልን በማሰራጨት ማደግ እንዲሁም ሌሎችን በማገልገል ማደግ ይኖርብናል። በስለ እስልምና ስታስብ የምትፈራ ወይም የምትቆጣ ከሆነ የሚያሳስቡህን ነገሮች ወደ እግዚአብሔር በጸሎት ልታቀርብ፣ መጽሐፍ ቅዱስ የሚልህን ልታነብና ይህን ጉዳይ በተመለከተ ሌሎች ሰዎች የሚሰጡትን ምሥክርነት ልትሰማ ይገባል። ክርስቲያኖች እግዚአብሔርን በመታመንና ሙስሊሞችን በመውደድ ማደግ ይጠበቅባቸዋል።

ሙስሊሞችን መውደድ ከምታስቡት በላይ ቀላል እንዲሆን የሚያደርጉ ብዙ ምክንያቶች አሉ። ብዙ ሙስሊሞች ሃይማኖታቸውን እንደ ባሕል እንጂ እንደ ሃይማኖት ስላልያዙት እናንተን መወዳጀት ይፈልጋሉ። እነዚህን ሙስሊሞች ለመውደድ ፈቃደኞች ናችሁን? በእስልምና መኖር የሚፈልጉት ሁሉም ሙስሊሞች አይደሉም። በወጥመድ ውስጥ እንዳሉ እንሚሰማቸውና ከእምነቱ መውጣት እንደሚፈልጉ የሚናገሩ ብዙ ሙስሊሞች አጋጥመውኛል። እነዚህን ሙስሊሞች ለመውደድ ፈቃደኞች ናችሁን? ብዙ ሙስሊሞች በፈጣሪ ያምናሉ፤ ስለ ፈጣሪያቸው ለማውራት ጉጉት አላቸው፤ ከናንተ ጋርም ለመነጋር ፈቃደኞች ናቸው። ከእነርሱ ጋር ለመነጋገር ፈቃደበኞች ናችሁን?

ክርስቲያኖች ስለ ሙስሊሞች አንድ ዓይነት ስጋት አላቸው። እርሱ ከባሕላችን ጋር ተዋሕደው ለመኖር ፈቃደኞች አይደሉም የሚል ነው። ይህ እውነት ቢሆንም ሁሉም ባሕሎቻችን ክርስቲያናዊ ናቸው ማለት አይደለም።

> “የእግዚአብሔር ፈቃድ እርሱም በጎና ደስ የሚያሰኝ ፍጹምም የሆነው ነገር ምን እንደ ሆነ ፈትናችሁ ታውቁ ዘንድ በልባችሁ መታደስ ተለወጡ እንጂ ይህን ዓለም አትምሰሉ።” (ሮሜ 12፡2)

የምዕራቡ ዓለም የነፃነት፣ የግልፅነትና የእኩልነት ባሕል መልካም ቢሆንም እንደ ቁማር ያሉ በመንግሥታት የሚደገፉ ከፉ ተግባራትን ምን ልንላቸው ነው? የመጠጥ ባሕላችን፣ ልቅ የወሲብ ፊልሞች፣ ዘማዊነት፣ ያታን ማምታታትና የመሳሰሉትም አሉ። በሺዎች የሚቆጠሩ ህፃናት የውርጃ ሰለባዎች ናቸው። በየትምሕርት ቤቱ፣ በየመዝናኛ ተቋማትና በሚድያዎቻችን የእግዚአብሔር ስም ይሰደባል። በዚህ ረገድ ከታሰበ ሙስሊሞችና ክርስቲያኖች የጋራ የሆነ ስጋት አላቸው። በሁሉም ረገድ የማንስማማና ክርስቲያኖች በባሕላችን ውስጥ የሚገኙ ነገሮችን ሁሉ ከትችት የመከላከል ግዴታ እንዳለብን ማሰብ የለብንም። ስለ እነዚህ ስጋቶቻችሁ ከሙስሊሞች ጋር መነጋገር ትችላላችሁ። ከዚህም የተነሳ ከሙስሊሞች ጋር ወዳጅነትን መፍጠር ከምታስቡት በላይ ቀላል ነው።

በመጨረሻም ክርስቲያኖችን የሚጠሉትን ሙስሊሞች በተመለከተ እንኳ የኢየሱስን ምሳሌነትና ጠላቶቹን እንደወደዳቸው ልናስብ ያስፈልገናል። በፍርሃት መነዳት ሳይሆን በእግዚአብሔር በመታመንና የኢየሱስን ምሳሌነት በመከተል ሙስሊሞችን መውደድ ያስፈልገናል።

ሙስሊሞችን ለመወዳጀት ተከታዮቹን ዘዴዎች ልትጠቀሙ ትችላላችሁ፡-

1. በፈገግታ በዙርያችሁ የሚገኙትን ሙስሊሞች ሰላም በሏቸው። መንገድ ላይ ስትሄዱ አንድን ሰው ላለማየት ፊታችሁን ማዞር ቀላል ሊሆን ይችላል። በተለይም ሙስሊሞችን ስታዩ እንደርሱ ታደርጉ ይሆናል። ነገር ግን ፈገግታን እንድታሳዩዋቸው ላበረታታችሁ እወዳለሁ። በትምህርት ቤታችሁ ሙስሊም ልጆች ካሉ ወላጆቻቸው ሊቀሏቸው ሲመጡ በፈገግታ ሰላምታ ስጧቸው። ሙስሊሞችን ማራቅ ሳይሆን በወዳጅነት ስሜት ተቀበሏቸው።
2. ማንኛውንም ሰው እንደምታወሩት ከእነርሱ ጋር አውሩ። ክፉዎች እንደሆኑ አታስቡ። ሁሉም ሙስሊሞች የተለያዩ በመሆናቸው ከእነርሱ ጋር በመነጋገር ማንነታቸውን ለማወቅ ሞክሩ። ሙስሊሞች ምን ያህል ልዩነቶች እንዳሏቸው ለማሳየት ያህል ከግል ልምዴ አንዳንድ ምሳሌዎችን ልስጣችሁ፡-
    - ስለ ሃይማኖት ግድ የሌለውና ሙስሊም መሆኑ እንኳ እንዲታወቅ የማይፈልግ ሙስሊም አውቃለሁ።
    - አንዲት የስድስት ልጆች እናት ባሏ ጥሏት ስለኮበለለ የሚረዳን አጥታ ስትቸገር አጋጥማኛለች።
    - ስለ እስልምና ምንም ዕውቀት ያልነበራት ባሕሏ ስለሆነ ብቻ ራሷን ሸፍና የምትሄድ ሴት ደግሞ አለች።
    - ትኩረቷ ሙሉ በሙሉ ትምሕርቷ ላይ ብቻ የሆነ ያላገባች ሙስሊም ወጣት ሴት።
    - ከክርስቲያን ሚስቱ ጋር ቤተክርስቲያን የሚሄድ ሁሉም ሃይማኖታት እኩል እንደሆኑ የሚያስብ ሙስሊም ወንድ።
    - አባቱ ሙስሊም እናቱ ደግሞ ክርስቲያን የሆነች ሙስሊምም ክርስቲያንም መሆን የሚፈልግ ወጣት ልጅ።
    - መስጊድ የሚያዘወትር ከክርስቲያኖች ጋር ለመነጋገር የሚፈልግ ሙስሊም።
    - ወደ እስልምና የተለወጠ ክርስቲያን።
    - እስልምና በዓለም ላይ እየፈፀማቸው የሚገኙትን ክፉ ነገሮች በማየት እስልምናን የጠላ ሙስሊም።
    - በአውሮፓ ሊጎች ውስጥ የሚጫወቱ ተጫዋቾችን አንድ በአንድ የሚያውቅ የእግር ኳስ ሱሰኛ።
    - ኤቲየስት (ኢ-አማኝ) ሆኖ ራሱን እንደሙስሊም የሚኖር ሰው።
    - ራሱን ሙስሊም ብሎ የሚጠራ ነገር ግን በፈጣሪ መኖር የማያምን ሰው።
    - በክርስትና አስተምሕሮ የሚደነቅ ሙስሊም።

ከማንኛውም ሰው ጋር እንደምትነጋገሩት ሁሉ በዙርያችሁ ከሚገኙት ሙስሊሞች ጋር ተነጋገሩ። ስለ ቤተሰብ፣ ሥራ፣ ትምሕርት ቤት፣ ስፖርት፣ ስለሚወዱት የቲ ቪ ፕሮግራም፣ ስለ ዓለም ሁኔታ፣ ወይንም ስለ ስጋቶቻቸው አውሩ። አትከራከሩ ነገር ግን በማዳመጥ ማንነታቸውን ተረዱ። ጠንካራ ሙስሊሞችና የእምነቱን ትዕዛዛት በጥብቅ የሚከተሉ መሆን አለመሆናቸውን ጠይቋቸው። ግምታዊ አትሁኑ። ይህ እነርሱን የምንወድበት አንዱ መንገድ ነው።

3. ለሙስሊም ወዳጆቻችሁ ጸልዩ። ስለ ምን መጸለይ እንዳለባችሁ በመጠየቅ እነዚህ ጸሎቶች መመለስ አለመመለሳቸውን ተከታተሉ። እግዚአብሔር ልባቸውን ለወንጌል እንዲከፍት ጸልዩላቸው።
4. ነገሮችን በጋራ ማድረግ ጀምሩ። በሆነ ጉዳይ እርዳታን ከፈለጋችሁ ሊያግዟችሁ ይችላሉ። ጠይቋቸው። እንረሱ ደግሞ እርዳታችሁን የሚፈልጉ ከሆነ ልትረዷቸው ትችላላችሁ። እርዳታችሁን ለግሷቸው። ልጆቻቸውን ወደ ልጆቻችሁ ዝግጅቶች ጋብዟቸው። ለሻይ ጋብዟቸው። ጓደኛሞች ሁኑ።

ከምታውቋቸው ሙስሊሞች ሁሉ ጋር ምርጥ ጓደኛሞች መሆን አለባችሁ እያልኩ አይደለም። ጊዜያችንን የምናሳልፈው መጥነን ነው። ነገር ግን በሕይወታችን ውስጥ የሚያጋጥሙንን ሙስሊሞች ለመወዳጀት፣ ለመቀበልና ለማገልገል ፍላጎት ሊኖረን እንደሚገባ እያስገነዘብኩ ነው። እንደ ክርስቲያኖች የምንጀምረው ከዚህ ነጥብ መሆን አለበት።

ለአንዳንዶቻችን ሙስሊሞችን በዚህ መንገድ መውደድ ቀላል ሲሆን አንዳንዶቻችን ደግሞ ልንቸገር እንችላለን። በሙስሊሞች እጅ መከራ ተቀብላችሁ ከሆነ እነርሱን መውደድ ቀላል ባይሆንም እግዚአብሔር ከኛ የሚጠብቀው ጉዳይ መሆኑን ማስታወስ ያስፈልገናል። የኢየሱስን ምሳሌነት ልንከተል ያስፈልገናል። በዚህ መንገድ መከራን ተቀብላችሁ ከሆነ ከመጋቢያችሁ ወይንም ከክርስቲያን ወዳጃችሁ ጋር እንድትመካከሩ እመክራችኋለሁ። ምናልባትም ከደረሰባችሁ ስነ ልቦናዊ ጫና ለማገገም ከአማካሪ ወይንም ከስነ ልቦና ባለሙያ ጋራ ማሳለፍ ሊያስፈልጋችሁ ይችላል።

በዚህ ክፍል እግዚአብሔር ሁሉን ሰው እንድንወድ እንደሚጠብቅብን ተመልክተናል፤ ሙስሊሞችን ትወዳላችሁን? የሚል ጥያቄም ተጠይቀናል። እንዲህ ያለው ጥያቄ ይህን በሚመስል መጽሐፍ ውስጥ የሚጠበቅ ቢሆንም ሁሉንም ሰው ውደዱ የሚለው የእግዚአብሔር ትዕዛዝ ሌላ ገፅታም አለው፤ ክርስቲያኖችን ትወዳላችሁን?

## ክርስቲያኖችን ትወዳላችሁን?

መጽሐፍ ቅዱስ ሰዎችን ሁሉ እንድንወድ ሲነግረን ብዙ ጊዜ ቅድሚያ እንድንሰጥ ከማሳሰብ ጋር ነው።

እንግዲያስ ጊዜ ካገኘን ዘንድ ለሰው ሁሉ ይልቁንም ለሃይማኖት ቤተ ሰዎች መልካም እናድርግ። (ገላ. 6፡10)

ክርስቲያኖች ሁሉንም ሰው በተለይም የእምነት ወንድሞቻቸውንና እህቶቻቸውን መውደድ ይገባቸዋል። የአንድ ቤተሰብ አባላት በመሆናችን ለክርስቲያን ወንድሞቻችንና እህቶቻችን እውነተኛ የሆነ ቤተሰባዊ ፍቅር ሊኖረን ይገባል።

"በወንድማማች መዋደድ እርስ በርሳችሁ ተዋደዱ፤ እርስ በርሳችሁ ተከባበሩ።" (ሮሜ 12፡10)

ስለዚህ እኔ ደግሞ በእናንተ ዘንድ ስለሚሆን በጌታ በኢየሱስ ስለ ማመንና ለቅዱሳን ሁሉ ስለሚሆን መውደድ ሰምቼ፥ ስለ እናንተ እያመሰገንሁ ስጸልይ ስለ እናንተ ማሳሰብን አልተውም።" (ኤፌ. 1፡15-16)

"እናንተ ራሳችሁ እርስ በርሳችሁ ልትዋደዱ በእግዚአብሔር ተምራችኋልና ስለ ወንድማማች መዋደድ ማንም ይጽፍላችሁ ዘንድ አያስፈልጋችሁም።" (1ተሰ. 4፡9)

"የወንድማማች መዋደድ ይኑር።" (ዕብ. 13፡1)

ለእውነት እየታዘዛችሁ ግብዝነት ለሌለበት ለወንድማማች መዋደድ ነፍሳችሁን አንጽታችሁ እርስ በርሳችሁ ከልባችሁ አጥብቃችሁ ተዋደዱ።" (1ጴጥ. 1፡22)

ይህ ለክርስቲያን ወገኖቻችን ያለን ፍቅር በተለይም ክርስቲያኖች ችግር ውስጥ በሚገቡበት ጊዜ መገለጥ ይኖርበታል። በእስልምና ምክንያት ብዙ ክርስቲያን ወገኖቻችን ችግር ውስጥ ናቸው።

በታሪክ፣ በሥነ መለኮትና በሕግ ረገድ እስልምና በክርስቲያኖች ላይ መከራን ሲያደርስ የኖረ ሃይማኖት ነው። ይህን ሃቅ ዕውቅና በመስጠት በእርሱ ስር እየተሠቃዩ የሚገኙትን ክርስቲያን ወገኖቻችንን ለመርዳት መነሳት ያስፈልገናል። ስለ እስልምና ግድየለሾች መሆን ሳይሆን መረጃን የሰነቅን ልንሆን ይገባናል። ቁርአን ክርስቲያኖች ኢየሱስ የእግዚአብሐየር ልጅ መሆኑን በማመናቸው ምክንያት ከሃዲያን እንደሆኑ በግልፅ ይናገራል፡-

ከእነዚያ መጽሐፍን ከተሰጡት ሰዎች እነዚያን በአላህና በመጨረሻው ቀን የማያምኑትን፣ አላህና መልክተኛው እርም ያደረጉትንም እርም የማያደርጉትንና እውነተኛውንም ሃይማኖት የማይቀበሉትን እነርሱ የተዋረዱ ኾነው ግብርን በእጆቻቸው እስከሚሰጡ ድረስ ተዋጉዋቸው። አይሁድ ዑዘይር የአላህ ልጅ ነው አለች። ክርስቲያኖችም አልመሲሕ የአላህ ልጅ ነው አሉ። ይህ በአፎቻቸው (የሚናገሩት) ቃላቸው ነው። የእነዚያን ከነሱ በፊት የካዱትን ሰዎች ቃል ያመሳስላሉ። አላህ ያጥፋቸው። (ከእውነት) እንዴት ይመለሳሉ! (ቁርአን 9፡30)

የዚህ ፍረጃ ውጤቱ ክርስቲያኖችን መውረርና በእስልምና ስር መግዛት ያስፈልጋል የሚል ነው፡-

በ7ኛው ክ.ዘ. ሙሐመድ የእስላማዊ ጂሃድ ሠራዊቶችን አደራጀ። እነዚህ ሠራዊቶችም በፍጥነት የክርስትናውን ዓለም ወረሩ። ክርስቲያኖችና ሌሎች ሙስሊም ያልሆኑ ሕዝቦች ለሚቀጥሉት ሺህ ዓመታት ተገዢዎች ሆኑ። ይህ በታክ በትክክል የተመዘገበ ሲሆን የምሥራቅ አፍሪካ፣ የመካከለኛው ምሥራቅና የኢስያን ክርስቲያናዊ ስልጣኔዎች እንዲያከትሙ ያደረገ ነበር። በዚህ ረገድ እውቀት ሊጎድለን አይገባም፤ ወይንም ዕውቀት ስለሌለን ብቻ እንዳልተፈፀመ መቁጠር የለብንም።

በጣም መልካምና ሰላማዊ የሆነ ሙስሊም ወዳጅ ሊኖራችሁ ይችላል። ይህ መልካም ቢሆንም ነገር ግን ከእርሱ ባሕርይ በመነሳት የእስልምና ታሪክ መልካምና ሰላማዊ እንደሆነ መደምደም አትችሉም። ብዙ ዓይነት ሙስሊሞች ስላሉ ጉዳዩ ያንን ያህል ቀላል አይደለም። አንዱ ሙስሊም መልካምና ሰላማዊ ቢሆን ሌላኛው ደግሞ እርሱና በዙርያው የሚገኙት ሰዎች እስልምና በጥብቅ እንዲከተሉ የሚፈልግ ሊሆን ይችላል። የትኛውን ነው ትክክለናውን እስልምና እየተገበረ ያለው? ይህንን ጥያቄ ለመመለስ መጠነኛ ጥናት ማድረግ ያስፈልጋችኋል ነገር ግን አንድን ሙስሊም በመመልከት ብቻ ልትመልሱት አትችሉም።

በታሪክ መካከል ክርስቲያኖች ከእስላማዊ አስተምሕሮ የተነሳ ብዙ መከራ ደርሶባቸዋል፤ ዛሬም እየደረሰባቸው ይገኛሉ። ክርስትናን የሚቀበሉ ሙስሊሞች ግድያና እሥራት ስለሚደርስባቸው ከአገር ለመሰደድ ይገደዳሉ።

በዚህ ዘመን እንኳን እስልምና በሚያስተምረው ትምህርት ምክንያት ከእምነታቸው የተነሳ ብዙ መከራን የሚቀበሉ ክርስቲያኖች አሉ። ከኢንዶኔዢያውያን ክርስቲያን ጓደኞቼ መካከል አንዱ ለትምሕርት ወደ አውስትራሊያ ዩኒቨርሲቲ መጥቶ ነበር። የእርሱ ፎቶግራፍ ዛሬም ድረስ ጠረጴዛዬ ላይ አለ። ይህ ሰው ለጉዞ ከመውጣቱ በፊት ንብረቱን ለሁለት በመክፈል በተለያዩ ሁለት ከተሞች ውስጥ እንዲቀመጡ አደረገ። ለዚም ምክንያቱ ጂሃዳውያን አንዱን ከተማ ቢያጠቁ በሌላኛው ከተማ ውስጥ የሚገኝ ንብረቱ እንደሚተርፍለት ስላሰበ ነበር። ወደ አገሩ ከተመለሰ በኋላ ስጠይቀው ጂሃዳውያን ሁለቱንም ከተሞች በመዝረፋቸው ምክንያት ንብረቱን በሙሉ እንዳጣ ነገረኝ። ጠረጴዛዬ ላይ የተቀመጠው ፎቶግራፉ በጂሃዳውያኑ ወረራ ወቅት በተገደሉት ክርስቲያኖች መቃብር ውስጥ ቆሞ የሚያሳይ ነው።

ሌላ ፋርማሲ የሚያጠና ግብፃዊ ወዳጄ በከተማው የሚገኙ ሙስሊሞች ከአርብ ጸሎት መልስ የክርስቲያኖችን ንብረት በሙሉ እንደዘረፉ ነገረኝ። ሙስሊሞቹ በመስጊድ ውስጥ ይማሩ የነበሩት ትምሕርት ክርስቲያኖቹ ጂዝያ[2] ባለመክፈላቸው ምክንያ የጥበቃ

[2] ጂዝያ ሙስሊም ያልሆኑ ሰዎች ከእስላማዊ ጦርነት ለመትረፍ ለሙስሊሞች የሚከፍሉት ግብር ነው። ቁርኣን 9፡29

መብታቸውን አጥተዋል የሚል ነበር። እርሱና ቤተሰቡ እንደ ሌሎች ክርስቲያኖች ሁሉ በዚህ ሁኔታ ስለተማረሩ በቋሚነት በአውስትራሊያ ውስጥ ሰፍረዋል።

ናይጄሪያዊያን ክርስቲያን ጓደኞች አሉኝ ፤ በእነርሱ ላይ በየቀኑ ጂሃድ ይፈጸማል። በዚህ አካባቢ በአሥር ሺዎች የሚቆጠሩ ክርስቲያኖች ተገድለዋል። ከነዚህ አገራት የመጡትን እነዚህን ክርስቲያኖች በመጠየቅ ስለደረሰባቸው ነገር ተረዱ። ታሪኮቻቸውን አንብቡ።

ምናልባት በእነዚህ አካባቢዎች የሚኖሩ ሰዎች ሁሉ መጽናት አለባቸው ብላችሁ መከራዎቻቸውን እንደ ሌሎች ፖለቲካዊ ችግሮች አስባችሁት በእስላማዊ ትምህርት ምክንያት የሚመጣ እንዳልሆነ ቆጥራችሁ ትንቁት ይሆናል። ምናልባት እነዚህ ክርስቲያኖች ከሌሎች ክርስቲያኖች የተለየ እርዳታ ሊያገኙ እንደማይገባ ይሰማችሁ ይሆናል ። ነገር ግን ይህ ከተከታዩ ጥቅስ ጋር እንዴት ይስማማል?

> እንግዲያስ ጊዜ ካገኘን ዘንድ ለሰው ሁሉ ይልቁንም ለሃይማኖት ቤተ ሰዎች መልካም እናድርግ። (ገላ. 6፡10)

ክርስቲያኖችን በተለየ ሁኔታ መርዳት ያስፈልገናል። ክርስቲያኖች ለሁሉም የጋራ በሆነ ችግር በእስላም አገራት ውስጥ እየተሰቃዩ ቢገኙ እንኳ ፍቅራችንና ርዳታችን ለክርስቲያኖቹ የተለየ መሆን እንደሚገባው ይህ ጥቅስ ይነግረናል። ለዚህ ሁለት ጥሩ ምክንያቶች አሉ፡- የመጀመርያው ቤተሰቦቻችን በመሆናቸው ወንድማዊ ፍቅራችንን የምንገልፅበት መንገድ ስለሆነ ነው። ሁለተኛው መከራቸው ከእንርሱ ጋር በጋራ ሆነን የእግዚአብሔርን ፍቅር ለሙስሊሞች እንድንገልፅ ዕድልን ይሰጠናል። በአካባቢያቸው የሚገኙትን ሙስሊሞች ለመርዳት ክርስቲያኖችን መርዳትና በእነርሱ አማካይነት መሥራት ያስፈልገናል። የክርስቶስን ፍቅር መመስከር እንዲችሉ አቅማቸውን ማሳደግ ያስፈልገናል። ይህ የገዛ ወገኖቻችንን መንከባከብና ሌሎችን እንዲንከባከቡ ማስቻል በመሆኑ ምንም ችግር የለበትም።

ሙስሊሞችን መፍራትና መጥላትን መተው የሚገባቸው ክርስቲያኖች እንዳሉ ሁሉ ክርስቲያኖች በእስልምና ስር የሚደርስባቸውን ሥቃይና እንግልት በቸልታ ማየታቸውንና መካዳቸውን ማቆም የሚገባቸው ክርስቲያኖችም አሉ። ለክርስቲያን ወንድሞቻችንና እህቶቻችን ያለንን ኃላፊነት በሚያስረሳ ሁኔታ ሙስሊሞችን በመውደድ መታወር አይገባንም። እስልምና በክርስቲያን ወንድሞቻችንና እህቶቻችን ላይ እያደረሰ የሚገኘውን ሥቃይ እስከመካድ ድረስ ሙስሊሞችን መውደድ የለብንም። ከሙስሊሞች ጋር ስንወዳጅ በክርስቲያን ወንድሞቻችን ሥቃይ ማፈር የለብንም። ለምቾታችን ስንል መስዋዕት ልናደርጋቸው አይገባም።

የበርናባስ ፈንድን የመሳሰሉት ተቋማት ክርስቲያኖች በሙስሊም አገራት የሚደርስባቸውን እንግልት እንድታውቁ መረጃዎችን ይሰጣሉ። በእነዚህ ተቋማት ተመዝግባችሁ ከምታገኟቸው መረጃዎች በመነሳት በቤታችሁና በቤተክርስቲያን ለክርስቲያኖች ጸልዩ። እነዚህ ተቋማት ለክርስቲያኖች ተግራዊ በሆነ መንገድ ፍቅራችሁን እንዴት ማሳየት

እንደምትችሉም ይጠቁሟችኋል። ቤተክርስቲያናችሁ ከእነዚህ አብያተ ክርስቲያናት ጋር በመተባበር ለሙስሊሞች የክርስቶስን ፍቅር ማካፈል እንድትችልም ይረዷችኋል።

ሰዎች እስልምና የሰላም ሃይማኖት መሆኑንና በታሪክ ውስጥ ለክርስቲያኖች ትክክለኛ ጥበቃና አያያዝ ሲያደርግ እንደነበር ሲነጋሩ እውነቱ እንደርሱ እንዳልሆነ መግለፅ ያስፈልገናል። ይህ ከታሪክና ከእስላማዊ አስተምሕሮ ጋር እንደሚጣረስ መግለፅ ያስፈልገናል። ሙስሊም መሪዎች እነዚህን አግላይ ሕግጋት እንዲሰርዙና ሙስሊሞችም ጭቆናን እንዲያቆሙ መንገር ያስፈልገናል። ይህንንም ለማድረግ በቂ መረጃዎችን በማግኘት፣ በጥበብ፣ በሃቅና በኃላፊነት ስሜት ልንናገር ይገባናል።

ስለ እስልምና ስናስብ እግዚአብሔር ከሚጀመርበት ቦታ መጀመር ያስፈልገናል፤ እርሱም ሰዎችን ሁሉ መውደድ ነው። ሙስሊሞችን መውደድ ይገባናል ነገር ግን ደግሞ በእስልምና ስር የሚሠቃዩትንም ክርስቲያኖች መውደድ ይገባናል። ክርስቲያን ወገኖቻችሁን ትወዳላችሁን? እነርሱንስ ለመርዳት ፈቃደኞች ናችሁን?

## ይህንን ሚዛናዊ ማድረግ የምትችሉት እንዴት ነው?

ሙስሊሞችን መውደድና በሌላ ወገን ደግሞ በእስልምና ስር የሚሠቃዩትን ክርስቲያኖች መውደድ የምትችሉት እንዴት ነው? ሙስሊሞችን መውደድን እስልምና በታክ ሁሉ ውስጥ በክርስቲያኖች ላይ ያደረሰውን ሰቆቃ መማርን ሚዛናዊ ማድረግ የምትችሉት እንዴት ነው? ይህንን ማድረግ ቀላል ባለመሆኑን እንደ ቀላል መቁጠር የለብንም። ከልምዴ በመነሳት ሰዎች አንደኛውን ወይንም ሌላኛውን እንደሚያደርጉ አይቻለሁ፤ አንዳንድ ክርስቲያኖችም ሙስሊሞችን መውደድ እንዳለባቸው ስለሚሰማቸው ይህንን ለማድረግ እስልምና በክርስቲያኖች ላይ ያደረሰውን መከራ መካድ እንደሚገባቸው ያምናሉ። ሌሎች ደግሞ ክርስቲያኖችን መርዳት እንደሚገባቸው ያምኑና ሙስሊሞችን በመጥላት ይደመድማሉ። ስለዚህ ሙስሊሞችን መውደድን በእስልምና ስር የሚሠቃዩትን ክርስቲያኖች ከመውደድ ጋር ሚዛን ማስጠበቅ የምትችሉት እንዴት ነው?

መንገዱ አንድ ብቻ ሲሆን እርሱም የወንጌል ኃይል ነው። ወንጌል እውነታን የመጋፈጥና ሰዎችን የመውደድን አቅም ይሰጣችኋል። በሐሳብ የማትስማሟቸውን ሰዎች መውደድ እንድትችሉ ይረዳችኋል። ኢየሱስ ጌታችን ይህንን አድርጓል። እውነትን እየተናገረ ሰዎችን ይወድድ ነበር።

የኛ ዓለም ይህ ኃይል የለውም። ጠላቶቹን መውደድን አያውቅም። ለዚህ ነው አንዳንዶች እስልምና የሰላም ሃይማኖት መሆኑን አጥብቀው የሚናገሩት። ሙስሊሞችን መቀበልና መውደድ የሚችሉት በዚያ መንገድ ብቻ ነው። ነገር ግን ይህ ስለ እስልምና ታክም ሆነ ስለ አስተምሕሮው እውነታን መጋፈጥ አይደለም። አንዳንዶች ደግሞ እስልምና ሽብርን

ስለሚያስተምር ሙስሊሞችን መጥላት ይኖርብናል ይላሉ። ነገር ግን ይህኛውም ክርስቲያናዊ ምላሽ አይደለም።

ወንጌል ስለ እስልምና እውነቱን እንድንጋፈጥና ሙስሊሞችን እንድንወዳቸው ያስችለናል። በዙርያችን ያሉ ክርስቲያኖች ላይረዱን ይችላሉ ነገር ግን ልንከተለው የሚገባው አቀራረብ ይህ ነው። አንዳንዶች በክርስቲያኖች ላይ ለሚደርሰው መከራ ዕውቅና በመስጠታችን ምክንያት ፍቅር የጎደለን መስሎ ሊሰማቸው ይችላል። ሌሎች ደግሞ ሃይማኖቱ እኛን የሚጠላን ሆኖ ሳለ ሙስሊሞችን እንዴት መውደድ እንደምንችል ግራ ሊገባቸው ይችላል። ሁለቱመረ ቡድኖች እንዲህ የሚሰማቸው ወንጌሉን ስለማያምኑት ነው። ይህ በዚህ ምዕራፍ ልጠይቀው ወደምፈልገው የመጨረሻ ጥያቄ ይመራናል፤ ወንጌሉን ታምኑታላችሁን?

## ወንጌሉን ታምኑታላችሁን?

እናንተ ኃጢአተኞች መሆናችሁንና በእግዚአብሔር ጸጋ ብቻ የዳናችሁ መሆናችሁን ታምናላችሁን?

> "እኛ ደግሞ አስቀድመን የማናስተውል ነበርንና፤ የማንታዘዝ፥ የምንስት፥ ለምኞትና ለልዩ ልዩ ተድላ እንደ ባሪያዎች የምንገዛ፥ በክፋትና በምቀኝነት የምንኖር፥ የምንጣላ፥ እርስ በርሳችን የምንጠላላ ነበርን። ነገር ግን የመድኃኒታችን የእግዚአብሔር ቸርነትና ሰውን መውደዱ በተገለጠ ጊዜ፥ እንደ ምሕረቱ መጠን ለአዲስ ልደት በሚሆነው መታጠብና በመንፈስ ቅዱስ በመታደስ አዳነን እንጂ፥ እኛ ስላደረግነው በጽድቅ ስለ ነበረው ሥራ አይደለም።" (ቲቶ 3፡3-5)

ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ ኃጢአታችሁ ስለሞተ ምሕረትን ያገኛችሁት ከእርሱ የተነሳ ብቻ ነው። ከሙስሊሞችም ሆነ ከማናቸውም ሰዎች የተሻላችሁ እንደሆናችሁ ማሰብ የለባችሁም። ሁላችንም የእግዚአብሔር ፍቅርና ምሕረት የሚያሻን ኃጢአተኞች ነን። ይህንን ማወቅ የእግዚአብሔርን ፍቅር ለሰዎች ሁሉ እንድናካፍል ይረዳናል። ይህ ፍቅር ልባችንን ስለሚለውጥ ለሌሎች ሰዎች ደህንነት እንድናስብ ይረዳናል። ይህ ወንጌል ነው ሁሉንም ሰው እንድንወድ አቅምን የሚሰጠን።

### የትግበራ ማጠቃለያ

1. በፈገግታ፣ ሰላምታ በመስጠት የምታውቁትን ሙስሊም አናግሩት።
2. በሙስሊም አገራት በክርስቲያኖች ላይ እየተፈፀመ ስላለው ነገር መረጃ ይኑራችሁ። ጸልዩላቸው። ቤተክርስቲያናችሁ በምን መንገድ ልትረዳቸው እንደምትችል ጠይቋቸው።

# ምዕራፍ 2

## እስልምናን መረዳት

ባለፈው ምዕራፍ ሙስሊሞችን ጨምሮ ሰዎችን በሙሉ መውደድ እንደሚገባን ተመልክተናል። እግዚአብሔር ሥራውን የሚጀምረው ከዚህ በመሆኑ እኛም ከሙስሊሞች ጋር ያለንን ግንኙነት ከዚህ መጀመር ያስፈልገናል። ለፍርሃት፣ ለቁጣ፣ ለቸልተኝነት ወይንም ለጥላቻ ቦታን ባለመስጠት ሰዎችን ሁሉ በፍቅር መቅረብ ይገባናል። በዚህ ምዕራፍ ማተኮር የምፈልገው ስለ እስልምና ሃይማኖት መረጃዎችን ከየት እናግኝ በሚለው ጥያቄ ላይ ነው።

ከመገናኛ ብዙኀን መጀመር ያስፈልገን ይሆን? ስለ ሙስሊሞች ተግባር በየዕለቱ በሚድያ እንሰማለን። አንዳንድ ተግባራት በጎ ሲሆኑ ሌሎች ደጌሞ እኩይ ናቸው። እያንዳንዱ የመገናኛ አውታር የየራሱ አድሎአዊ አመለካከት አለው።ሙስሊም መሪዎች በቴሌቪዥኖች ብዙ ጊዜ ቃለ መጠይቅ ይደረግላቸዋል። እስላማዊ ድርጅቶችም ለእስልምና ኃይማኖታቸው ማስታወቂያዎችን ይሠራሉ። ሆኖም ይህ ሁሉ የሚድያ ጋጋታ ባለበት ሁኔታ ሰዎች አሁንም ድረስ የእስልምና ሃይማኖት ምን እንደሚያስተምር ይጠይቃሉ። ስለ እስልምና መማር የምትፈልጉ ከሆነ አሁን ያለው ማሕበራዊ የመረጃ መስተጋብር ጥሩ ቦታ አይደለም።

ምናልባት ሙስሊም ጓደኛ ይኖራችሁ ይሆናል። ስለ እስልምና እነርሱን መጠየቅ ጥሩ የጅማሬ ቦታ ሊሆን ይችላል። እነርሱ የሚያምኑትን በማሳወቅ ከእነርሱ ጋር ውይይት ለማድረግ በር ከፋች ስለሚሆን በጣም ጠቃሚ ነው። ነገር ግን ደግሞ እስልምናን በትክክል ትረድተውታል ወይ የሚል ጥያቄ መነሳት ይኖርበታል። ምናልባት ደግሞ ሙስሊም ጓደኛ ላይኖራችሁ ይችላል።

ክርስቲያኖች ስለ እስልምና ሃይማኖት ለማወቅ የሚያስችላቸው ጥሩ ቦታ የዓለም ሃይማኖታት ጥናት ነው። ይህ ምናልባት ስለ ዓለም ሃይማኖታት የሚያወራን መጽሐፍ ማንበብ ወይንም በትምህርት ቤት መማር ወይንም ደግሞ አንድ ሃይማኖት ምን እንደሚያስተምር በኢንተርኔት ላይ ፍለጋን ማድረግ ሊሆን ይችላል። ይህ አካሄድ አንድን ሃይማኖት በኢንሳይክሎፒድያዎች ውስጥ በሚነበበው መንገድ ለማጥናት ያግዛል። መረጃዎችን፣ ካርታዎችን እንዲሁም የቃላት ትርጉሞችን ያሳውቃሉ። በዚህ ሁኔታ የምናጠና ከሆነ *እስልምና* የሃይማኖት ስም መሆኑን፣ *ሙሐመድ* የእምነቱ ዋና ነቢይ መሆኑን፣ *ቁርኣን* የሙስሊሞች ዋና ቅዱስ መጽሐፍ መሆኑን፣ *አላህ* የሙስሊሞች አምላክ ስም መሆኑን እንዲሁም ይህ ሁሉ የተከናወነው በ600 ዓ.ም. አካባቢ በመካና መዲና ከተሞች ውስጥ መሆኑን ማወቅ እንችላለን።

የሙስሊሞች መሠረታዊ እምነቶች በፈጣሪ አንድነት ማመን፣ በመላእክት፣ በጅንና ሰይጣን መኖር ማመን፣ ከቁርኣን ብፊት በነበሩት መጻሕፍት ማመን፣ በነቢያት ሁሉ ማመን፣ በፍርድ

ቀን ማመን መሆናቸውን ማወቅ ይቻላል። ስለ አምስቱ የእስልምና አዕማዳት፡ ማለትም እምነትን መመስከር፣ ወደ መካ ሃይማኖታዊ ጉዞን ማድረግ፣ በቀን አምስት ጊዜ መጸለይ፣ በረመዳን ወር መጸለይ እንዲሁም ለእስላማዊ ተግባራት ምፅዋትን መስጠትን በተመለከተ መማር ይቻላል። እነዚህን ሁሉ የተመለከቱ ማስረጃዎችን ከቁርኣን፣ ከሐዲስ ወይንም በእስልምና ምሑራን ከተጻፉት መጻሕፍት ማግኘት ይቻላል።

እነዚህ ሁሉ እውነታዎችና ዝርዝሮች አስፈላጊ ቢሆኑም እነዚህን ነገሮች ማስተማር ለክርስቲያኖች ጥሩ የጅማሬ ቦታ እንዳልሆነ ከራሴ ልምድ በመነሳት መረዳት ችያለሁ። ለዚህ ሦስት ምክንያቶች ይጠቀሳሉ፤ የመጀመርያው ምክንያት ብዙ ክርስቲያኖች ከሕይወታቸው ጋር ቀጥተኛ ተያያዥነት የሌለውን ሃይማኖት በዝርዝር ለማጥናት ፍላጎት ማጣታቸው ነው። የሚያገኙትንም መረጃ ያን ያህል ጥቅም ላይ ላያውሉት ስለሚችሉ በፍጥነት ከትውስታቸው ይፋቃል። ሁለተኛው ክርስቲያኖች እነዚህን ዝርዝር ጉዳዮች በጥሩ ሁኔታ ለመጠቀም የሚያስችል በቂ ዕወቀት ማጣታቸው ነው። ሦስተኛው ደግሞ አንድ ክርስቲያን ሙስሊም ጓደኛ ቢኖረው እንኳ ሙስሊሞች ከክርስቲያኖች ጋር ሲወያዩ በነዚህ ጉዳዮች ላይ አለማተኮራቸው ነው። እነዚህ ዝርዝር ጉዳዮች አስፈላጊ እንዳልሆኑ እየተናገርኩ ሳይሆን ለክርስቲያኖች ጥሩ የጅማሬ ርዕሶች እንዳልሆኑ እያስረዳሁ ነው።

እኔ አንድ አዲስ መንገድ ለመጠቆመ እፈልጋለሁ። እርሱም በክርስትና ላይ ማተኮር ነው። ቁርኣን ስለ እስልምና እምነት መሠረቶች ይናገራል። ከዚህ በተጨማሪም ስለ ክርስተቲያኖችና ስለ ክርስትና እምነትም በስፋት ይናገራል። ክርስቲያኖችና ክርስትና በቁርኣን ውስጥ ብቻ ሳይሆን በሐዲስ፣ በሸሪኣና በእስላማዊ ባሕል ውስጥ አበይት ርዕሳን ናቸው። ሙስሊም ሰባኪያን በየመስጊዱ ስለ ክርስትና የሚሰብኩ ሲሆን ወላጆችም ከልጆቻቸው ጋር ይወያያሉ። ሙስሊሞች የእስልምናን መሠረቶች እንደሚማሩት ሁሉ ስለ ክርስትናም ይማራሉ ስለዚህ ክርስቲያኖች ‹ሙስሊሞች ስለ ክርስቲያኖችና ስለ ክርስትና የሚማሩት ምንድነው?› ከሚለው ጥያቄ እንዲጀምሩ የምመክረው ከዚህ አንፃር ነው።

እስልምና ስለ ክርስትና ከሚያስተምረው መጀመር አራት ዕድሎች አሉት። የመጀመርያው በክርስትናና በእስልምና መካከል ቀጥተኛ ተያያዥነት እንዲኖር ያደርጋል። ለምሳሌ ያህል አንድ ዓይነት አምላክ ነው የምናመልከው? ሁሉም አብረሃማውያን ሃይማኖታት ናቸውን? እነዚህ ትክክለኛ ተያያዥነቶች የመሆናቸው ጉዳይ ሌላ ጥያቄ ቢሆንም እስልምና ስለ ክርስትና የሚያስተምራቸው ነገሮች ተያያዥነት እንዲኖር ማድረጋቸው አጠያያቂ አይደለም። ሁለተኛው ስለ እነርሱ እየተወራ ስለሆነ ክርስቲያኖች በቀላሉ እንዲያስታውሱት ከማስቻሉም በተጨማሪ በተመሳሳይ ጊዜ ስለ እስልምና ወሳኝ ጉዳዮችን እንዲማሩ ይረዳቸዋል። ሦስተኛው ሙስሊሞች ስለ ክርስትና አስቀድመው ስለሰሙ ክርስቲያኖች ከሙስሊሞች ጋር ሲወያዩ የሚያጋጥማቸው የውይይት አውድ በመሆኑ ነው። በመጨረሻም እስልምናን በገዛ ራሱ የንግግር አውድ ብቻ ሳይሆን ለክርስቲያኖች ተጨባጭ በሆነ መንገድ ለመወያየት ያግዛል። ስለዚህ በዚህ ምዕራፍ በሚገኙት ቀጣይ ክፍሎች እስልምናን

የምናጠናው ቁርኣን ስለ ክርስቲያኖችና ስለ ክርስትና በሚናገረው ላይ ተመሥርተን ሲሆን ይህም ደግሞ ክርስቲያኖች ከሙስሊሞች ጋር እነዲወያዩ በምን ሁኔታ እንደሚያዘጋጃቸው እናያለን። ስለ ክርስትና እምነት፣ ስለ ፍቅርና ስለ ፖለቲካ እናያለን።

## ቁርኣን ስለ ክርስትና የሚናገረው

## የኢየሱስ ሞት

> እኛ የአላህን መልክተኛ የመሬምን ልጅ አልመሲሕ ዒሳን ገደልን በማለታቸው (ረገምናቸው)፤ አልገደሉትም፤ አልሰቀሉትምም ግን ለነሱ (የተገደለው ሰው በዒሳ) ተመሰለ እነዚያም በርሱ ነገር የተለያዩት፣ ከርሱ (መገደል) በመጠራጠር ውስጥ ናቸው፤ ጥርጣሬን ከመከተል በስተቀር በርሱ ነገር ምንም ዕውቀት የላቸውም፤ በእርግጥም አልገደሉትም። (ቁርኣን 4፡157)

የኢየሱስ ሞት በክርስትና እምነት ውስጥ ወሳኝ በመሆኑ ቁርኣን ሙስሊሞችን ስለ ጉዳዩ ዝግጁ አድርጓቸዋል። አንዳንድ ቦታዎች ላይ ቁርኣን የኢየሱስን ሞት የሚናገር ሲሆን (19፡33 ስለ ሞቱ በዋናነት በተናገረበት ቦታ ላይ (4፡157) የሞተ ወይንም የተሰቀለ መምሰሉን ብቻ ይናገራል። የተከሰተውን በተመለከተ በሙስሊሞች መካከል መግባባት የለም። ይሁዳ ወይንም የቀሬናው ስምዖን በእርሱ ፋንታ ተሰቅሏል ከሚለው ጀምሮ የተሰቀለው በርባን ነው እስከሚለው ድረስ ሐሳቦች ይሰነዘራሉ። አንዳንዶች ደግሞ ስቅለቱ ኢየሱስን በመግደል ሊሳካ ስላልቻለ ኢየሱስ ከሞት ተርፏል ይላሉ። አንዳንዶች ደግሞ ይህ ጉዳይ ሚስጢር በመሆኑ ማወቅ አይቻለንም ይላሉ። ይህ ጥቅስ ለብዙ ጭቅጭቅ የተጋለጠ ሲሆን በአጠቃላይ ሙስሊም ሊቃውን ኢየሱስ በመስቀል ላይ አልሞተም በሚለው ይስማማሉ።

ለክርስትና የኢየሱስ ሞት ማዕከላዊ ጉዳይና የደህንነታችን መንገድ ነው። የእግዚአብሔር ፍቅርና ባሕርይ መገለጫም ነው። በጸጋ የመዳን መሠረት እርሱ ነው። በእስልምና ግን አልተከሰተም። በእስልምና ፈጣሪ እናንተን ለማዳን የሠራው የሚታይ ሥራ የለም። ሙስሊሞች ስለ መስቀሉ የተማሩት ይህንን ሲሆን በዚህ ዙርያ የሚያስለጥኗቸው የታወቁ መጻሕፍትና ሰባኪያን ይገኛሉ። ይህ ዝግጅት የኢየሱስን ስቅለት ለማስተባበል የታለሙ ከመጽሐፍ ቅዱስ የተመረጡ ጥቅሶችንና በክርስቲያኖች ውስጥ ጥርጣሬን ለማጫር የተዘጋጁ ጥያቄዎችን ይጨምራል።

## ሥላሴና ምስጢረ ሥጋዌ

> እነዚያ አላህ የሦስት ሦስተኛ ነው (*) ያሉ በእርግጥ ካዱ፤ ከአምላክም አንድ አምላክ እንጅ ሌላ የለም፤ ከሚሉትም ነገር ባይከለከሉ፣ ከነሱ እነዚያን የካዱትን አሳማሚ ቅጣት በእርግጥ ይነካቸዋል። (ቁርኣን 5፡73-75 እና 5፡116)

> እላንተ የመጽሐፉ ሰዎች ሆይ! በሃይማኖታችሁ ወሰንን አትለፉ፤ በአላህም ላይ እውነትን እንጂ አትናገሩ፤ የመርየም ልጅ አልመሲሕ ዒሳ፣ የአላህ መልክተኛ፣ ወደ መርየም የጣላት (የሁን) ቃሉም ከርሱ የሆነ መንፈስም ብቻ ነው፤ በአላህና በመልክተኞቹም እመኑ (አማልክት) ሦስት ናቸው አትበሉም፤ ተከልከሉ ለናንተ የተሻለ ይሆናልና፤ አላህ አንድ አምላክ ብቻ ነው። ለርሱ ልጅ ያለው ከመሆን የጠራ ነው። በሰማያትና በምድር ያለ ሁሉ የርሱ ነው። መመኪያም በአላህ በቃ። (ቁርአን 4፡171)

ቁርአን በግልፅ ሥላሴን የሚቃወም ሲሆን በተደጋጋሚ ጠቅሶታል። ከነዚህ ጥቅሶች እንደምንመለከተው ሙሐመድ ከተሳሳተ መረጃ በመነሳት ሥላሴ ማለት እግዚአብሔር፣ ማርያምና ኢየሱስ እንደሆኑ በማስመሰል ቢናገረም ሙስሊሞች ግን የትኛውንም የሥላሴ ፅንሰ ሐሳብ ለመቃወም ዝግጁዎች ናቸው። ሙስሊሞች ክርስቲያኖች ሥላሴን እንዲተረጉሙ በመጠየቅ ይገዳደሯቸዋል። ይህ የሙስሊሞች የተለመደ ተግበር ሲኾን ተዘጋጅተውበት ይንቀሳቀሳሉ። ሥላሴን እንዳብራራለት የጠየቀኝ ሒንዱ፣ ቡዲስት ወይንም ኢ-አማኒ የሆነ ሰው አላጋጠመኝም። ነገር ግን ሙስሊሞች ሁል ጊዜ ይጠይቁኛል። የዚህ ምክንያ ደግሞ ቁርአን ስለሚያዛቸው ነው።

ከዚህ ጋር ተያያዥ የሆነው ደግሞ ሚስጢረ ሥጋዌ የምንለው ሲሆን ኢየሱስ ፍፁም አምላክ ፍፁም ሰው ነው የሚል አስተምሕሮ ነው። ቁርአን ይህን አስተምሕሮ በግልፅ ስለሚቃወም ለሙስሊሞች ተሠግዎና ሥላሴ ሐሰት፣ ኢ-አመክንዮአዊና ክህደት ናቸው። ሙስሊሞች ስለ ሥላሴና ስለ ተሠግዎ የተማሩት ይህንን ሲሆን በዚህ ዙርያ የሚያሰለጥኗቸው የታወቁ መጻሕፍትና ሰባኪያን ይገኛሉ። ይህ ዝግጅት ሥላሴና ተሠግዎ መጽሐፍ ቅዱሳዊ አለመሆናቸውን ለማሳየት ከመጽሐፍ ቅዱስ የተመረጡ ጥቅሶችን እንዲሁም ስለ ኒቅያ ጉባኤ የተሳሳተ መረጃንና በክርስቲያኖች ውስጥ ጥርጣሬን ለማጫር የተዘጋጁ ጥያቄዎችን ይጨምራል።

## አባትነትና የኢየሱስ ልጅነት

> ለአልረሕማን ልጅን መያዝ አይገባውም። በሰማያትና በምድር ያለዉ ሁሉ (በትንሣኤ ቀን)፣ ለአልረሕማን ባሪያ ኾነዉ የሚመጡ እንጂ ሌላ አይደሉም። (ቁርአን 19፡92-93)

ቁርአን የወልደ እግዚአብሔርን አስተምሕሮ የሚክድ ሲሆን በውጤቱም የእግዚአብሔርን አባትነት ክዷል። ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ አለመሆኑ ብቻ ሳይሆን 5፡18 ላይ ክርስቲያኖችም ራሳቸውን የእግዚአብሔር ልጆች ብለው መጥራት እንደማይችሉ ይናገራል። የእስልምናው አምላክ ጌታ ብቻ ሲሆን እናንተ መሆን የምትችሉት የመጨረሻው ነገር ተወዳጅ ባርያዎች ብቻ ነው። ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ አለመሆኑ በቁርአን በተደጋጋሚ

የተነገረ ሲሆን እንደርሱ ማመን የከፋውን ኃጢአት ከመፈፀም ይቆጠራል። ከዚህ የተነሳም ሙስሊሞች ክርስቲያኖችን “ፈጣሪ እንዴት ልጅ ሊኖረው ይችላል?” በማለት ይጠይቃሉ።

ቁርኣንን በማንበብ ብቻ እስከ አሁን ያየናቸውን የኢየሱስ ሞት፣ በፀጋ መዳን፣ ሥላሴ፣ ተሠግዎ እና የእግዚአብሔር ልጅ የሚሉትን ነጥቦች ልብ በሉ። እነዚህን ነገሮች ሲናገር ሙሐመድ ክርስትናን ተረድቷል እያልኩ አይደለም። የተሳሳተ መረጃና በብዙ መልኩ ለክርስትና አስተምሕሮ እንግዳ የሆነ አመለካከት ነበረው። ቁርኣን መጽሐፍ ቅዱስን በቀጥታ በመጥቀስ ክርስቲያናዊ አስተምሕሮዎችን የሚገዳደር ባይሆንም ነገር ግን ሙስሊሞች ዋና ዋና የወንጌል አስተምሕሮዎችን እንደዲገዳደሩና እንዲጠራጠሩ ያዘጋጃቸዋል። እነዚህ መሠረታዊና ልዩ የኾኑ አስተምሕሮዎቻችን ናቸው። እነዚህ ለመማርና ለማስተማር ብዙ ጊዜን የሚፈልጉ ወሳኝ ጉዳዮች ናቸው። ሙስሊሞች ስለነዚህ አስተምሕሮዎች መረዳት የላቸውም ነገር ግን ቁርኣን እንዲቃወሙ፣ እንዲጠራጠሩና እንዲያስተባብሏቸው ያስተምራቸዋል።

## መጽሐፍ ቅዱስ

ቀደም ሲል እንዳየነው ቁርኣን ሙስሊሞችን ለክርስቲያናዊ አስተምሕሮዎች ዝግጁ ያደርጋቸዋል፤ ከዚህ የከፋው ደግሞ ለመጽሐፍ ቅዱስ ዝግጁዎች እንዲሆኑ ማድረጉ ነው።

ቁርኣን ለመጽሐፍ ቅዱስ አዎንታዊ አመለካከት አለው፡-

> እላንተ ያመናችሁ ሆይ! በአላህና በመልክተኛው በዚያም በመልክተኛው ላይ ባወረደው መጽሐፍ፣ በዚያም ከበፊቱ ባወረደው መጽሐፍ፣ እመኑ፤ በአላህና በመላክቱም፣ በመጽሐፎቹም፣ በመልክተኞቹም፣ በመጨረሻውም ቀን የካደ ሰው፣ (ከሰውነት) የራቀን መሳሳት በእርግጥ ተሳሳተ። (ቁርኣን 4፡136)

በቁርኣን ውስጥ ክርስቲያኖች መጽሐፍ ቅዱስን እንዲታዘዙ ተነግሯቸዋል፡-

> የኢንጅልም ባለቤቶች በውስጡ አላህ ባወረደው ሕግ ይፍረዱ፤ አላህም ባወረደው የማይፈርድ ሰው፣ እነዚያ አመጠኞች እነርሱ ናቸው። (ቁርኣን 5፡47)

ነገር ግን በተግባር ሙስሊም መሪዎች ሙስሊሞችን ከዚህ በጣም የተለየ ነገር ያስተምሯቸዋል። ሙስሊሞች መጽሐፍ ቅዱስ መለወጡንና እንዳይቀበሉት ይማራሉ።

> እኛ የምናምነው ቶራህ አይሁድና ክርስቲያኖች የሚያምኑት “ቶራህ” አይደለም... በተመሳሳይ መዝሙራት ፈጣሪ ለዳዊት የሰጣቸው መገለጥ መሆኖቻቸውን ብናምንም ዛሬ ግን ከስሙ ጋር የተያያዙት መዝሙራት የእርሱ አይደሉም። ... ወንጌልስ? ... በሕይወት ዘመኑ ኢየሱስ አንድም ቃል አልጻፈል። ሌሎችም እንዲጽፉ አላዘዘም።ዛሬ የተላለፉት ወንጌላት በማይታወቁ ሰዎች የተዘጋጁ ናቸው! (Ahmed Deedat, Is the Bible God's Word?, ch. 3, pp. 7-8)

እስልምና ስለ መጽሐፍ ቅዱስ የሚያስተምረው ይህ ሲሆን በዚህ ረገድ ሙስሊሞችን የሚያሰለጥኑ መጻሕፍትና ሰባኪያን ብዙ ናቸው። ይህ ስልጠና የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪኮችን ማንቋሸሽና በውስጡ ግጭት እንዲሁም ስህተት እንዳለ መናገርን ይጨምራል። ሙስሊም በመጽሐፍ ቅዱስ ጽሑፍ ተዓማኒነት ላይ ጥርጣሬን ለማጫር ማርቆስ 16፡9-20፣ ዮሐንስ 8፡ 1-11 እና 1ዮሐንስ 5፡7 ላይ የሚገኙትን የንባብ ልዩነቶች እንዲጠቅሱ ሊሰለጥኑ ይችላሉ። ሙስሊም መሪዎች የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ርዕሰ ጉዳዮችን በመማር መጽሐፍ ቅዱስነን ለማጥቃጥ ይጠቀማሉ።

ነገር ግን ጉዳዩ ከዚህም ያለፈ ነው። ሙስሊም መሪዎች ሙስሊሞች መጽሐፍ ቅዱስን እንዳይቀበሉ ማስተማር ብቻ ሳይሆን አንዳንዶች መጽሐፍ ቅዱስን ከልሶ እስከመጻፍ ደፍረዋል። ከነዚህ መካከል ሁለቱ *የበርናባስ ወንጌል* እና *የእስልምና ወንጌል* የተሰኙት ይገኙበታል። የበርናባስ ወንጌል በ14ኛው ክ.ዘ. የተጻፈ ሲሆን ተከታዩ ምሳሌ ሙስሊሙ ደራሲ የመጽሐፍ ቅዱሱ ወንጌል ላይ ምን እንደፈጸመ ያሳያል። መጀመርያ ዮሐንስ 1፡19-23 እናንብብ፡-

> አይሁድም፡- አንተ ማን ነህ? ብለው ይጠይቁት ዘንድ ከኢየሩሳሌም ካህናትንና ሌዋውያንን በላኩበት ጊዜ፥ የዮሐንስ ምስክርነት ይህ ነው። መሰከረም አልካደምም፤ እኔ ክርስቶስ አይደለሁም ብሎ መሰከረ። እንኪያስ ማን ነህ? ኤልያስ ነህን? ብለው ጠየቁት። አይደለሁም አለ። ነቢዩ ነህን? አይደለሁም ብሎ መለሰ። እንኪያስ፡- ማን ነህ? ለላኩን መልስ እንድንሰጥ፤ ስለራስህ ምን ትላለህ? አሉት። እርሱም፡- ነቢዩ ኢሳይያስ እንዳለ፡- የጌታን መንገድ አቅኑ ብሎ በምድረ በዳ የሚጮኽ ሰው ድምፅ እኔ ነኝ አለ።

አሁን ደግሞ የበርናባስን ወንጌል እናንብብ፡-

> “አንተ ማነህ?” ብለው እንዲጠይቁት ሌላውያንና ጸሐፍትን ላኩበት። ኢየሱስም እንዲህ በማለት እውነትን መሰከረ፡- “እኔ መሲሁ አይደለሁም።” እንዲህ ብለው ጠየቁት፡- “አንተ ኤልያስ ወይንም ኤርሚያስ ወይንም ከጥንት ነቢያት መካከል አንዱ ነህን?” ኢየሱስም “አይደለሁም” ብሎ መለሰ። ለላኩን ሰዎች እንድንነግር እንግዲያውስ አንተ ማነህ?” ኢየሱስም መለሰ እንዲህ ሲል፡- እኔ በይሁዳ ውስጥ እንዲህ ብሎ የሚጮኽ ድምፅ ነኝ፡- «ለጌታ መልእክተኛ መንገድ አዘጋጁ» ይህም በኢሳይያስ ውስጥ እንደተጻፈው ነው።” (የበርናባስ ወንጌል ምዕራፍ 42)

የበርናባስ ወንጌል ደራሲ ዮሐንስ 1፡19-23 ላይ የሚገኘውን ከቁርኣን ጋር ለማስማማት እንደለወጠው ግልፅ ነው። የመጥምቁ ዮሐንስን የሥራ ድርሻ ለኢየሱስ በመስጠት ኢየሱስ ለሙሐመድ መንገድን ለመጥረግ የመጣ አስመስሎታል። የበርናባስ ወንጌል በእስላማዊ የመጽሐፍት መደብሮች ውስጥ ይሸጣል።

አሕመድ ሻፋት የተሰኘ ሰው *የእስልምና ወንጌል* የተሰኘ መጽሐፍ የጻፈ ሲሆን መነሻውን እንዲህ ሲል ይገልፃል፡-

> በፊታችሁ ያለው መጽሐፍ ወንጌል ነው። ፈጣሪ ለነቢዩ ሙሐመድ ከሰጠው መገለጥ በመነሳት የተጻፈ ነው። … ይህ ማውጫ በተወሰኑ አጋዥ ጽሑፎች ድጋፍ ያለው ነው (በአብዛኛው ከአዲስ ኪዳን የተወሰደ ሲሆን አንዳንዴ በቁርኣን መገለጥ መሠረት ተለውጧል)። ይህም የማርቆስን ወንጌል የሚያክል ወንጌል ለመፍጠር ነው። … ቀደም ሲል እንዳልነው ይህ መጽሐፍ እንደ አዲስ ወንጌል የቀረበ ነው። ከነባሮቹ ወንጌላት ጋር የሚመጣጠን አማራጭ የሙስሊም ወንጌል ነው። (Ahmad Shafaat, The Gospel According to Islam, New York: Vantage Press, 1979, pp. 1-2)

እስልምና መጽሐፍ ቅዱስን ከእንደገና ጽፎታል፤ ወንጌልን እንደገና ጽፎታል! የሌላውን ሃይማኖት መጽሐፍ ከእንደገና መጻፍ ትልቅ ድፍረት ቢሆንም እስልምና ሙስሊሞችን ክርስቲያኖች ጋር ለሚኖራቸው ሙግት ለማዘጋጀት እስከዚህ ጥግ ሄዷል። ነገር ግን ከዚህም የከፋ አለ።

## ዮታዊ ፍቅር

ቁርኣን ሙስሊም ወንዶች ክርስቲያኖችን እንዲያጠምዱ ለዖታዊ ፍቅርም አዘጋጅቷቸዋል።

> ዛሬ መልካሞች ሁሉ ለናንተ ተፈቀዱ፤ የነዚያም መጽሐፍን የተሰጡት ሰዎች ምግብ (ያረዱት) ለናንተ የተፈቀደ ነው፤ ምግባችሁም ለነሱ የተፈቀደ ነው፤ ከምእምናት ጥብቆቹም ከነዚያ ከናንተ በፊት መጽሐፍን ከተሰጡት ሴቶች ጥብቆቹም ዘማዊዎችና የሚስጢር ወዳጅ ያዢዎች ሳትሆኑ ጥብቆች ሆናችሁ መህሮቻቸውን በሰጠችኋቸው ጊዜ (ልታገቡዋቸው የተፈቀዱ ናቸው)፤ ከእምነትም የሚመለስ ሰው በእርግጥ ሥራው ተበላሸ። በመጨረሻም ቀን እርሱ ከከሳሪዎቹ ነው። (ቁርኣን 5፡5)

በነዚህ ጥቅሶች መሠረት ሙስሊም ወንዶች ክርስቲያን ሴቶችን ማግባት ይችላሉ። ሙስሊም ወንዶችና እናቶቻቸው ይህንን ያውቃሉ። ሙስሊም ቤተሰቦች ወጣት ክርስቲያን ሴቶችን ለመቀበል ዝግጁዎች ናቸው። የሴቶቹን እምነት ለማናጋት ምን ጥያቄ ማቅረብ እንዳለባቸውና ምን ርዕስ ላይ መወያየት እንዳለባቸው ያውቃሉ። በምዕራብ አገራት ወደ እስልምና የሚቀየሩት አብዛኞቹ ሰዎች ከሙስሊም ወንዶች ጋር በፍቅር የወደቁ በእምነታቸው ደካማ የሆኑ ሴት ክርስቲያኖች ናቸው። ሙስሊም ወንዶች ክርስቲያን ሴቶች ጥሩ ስነ ምግባር ስላላቸውና ትዳር ፈላጊ ስለሆኑ ሊያጠምዷቸው ይቋምጣሉ። ክርስቲያኖች ይህንን ማወቅና መጠንቀቅ ያስፈልጋቸዋል።

ሙስሊም ወንዶች ክርስቲያን ሴቶችን ማግባት መቻላቸው እስልምና ሳይታወቅ በአዳዲስ አካባቢዎች በፍጥነት ስር እንዲሰድ ያደርጋል። እስልምና ሙሽሊምንዶችን በፆታዊ ፍቅር ረገድ ዝግጁዎች እንዲሆኑ ያደርጋቸዋል።

## ፖለቲካዊ

ቁርኣን ሙስሊም መሪዎችና መንግሥታት በፖለቲካ ረገድ ለክርስቲያኖች ዝግጁዎች እንዲሆኑ ያደርጋቸዋል። በቁርኣን ውስጥ በክርስቲያኖችና በሙስሊሞች መካከል የነበረው ግንኙነት እየተለወጠ የሚመጣው የሙሐመድ ሕይወት ሁኔታ ሲለዋወጥ ነው። ሙሐመድ ክርስቲያኖች የሙስሊሞች ወዳጆች መሆናቸውን የተናገረበት ቀዳሚ ጊዜ ነበር።

> ይሁዶችንና እነዚያን ያጋሩትን፣ ለነዚያ ለአመኑት በጠላትነት ከሰዎች ሁሉ ይበልጥ የበረቱ ሆነው በእርግጥ ታገኛለህ፤ እነዚያንም እኛ ክርስቲያኖች ነን ያሉትን ለነዚያ ለአመኑት በወዳጅነት በእርግጥ ይበልጥ የቀረቧቸው ሆነው ታገኛለህ፤ ይህ ከነሱ ውስጥ ቀሳውስትና መነኮሳት በመኖራቸውና እነሱም የማይኮሩ በመሆናቸው ነው። (ቁርኣን 5፡82 እንዲሁም 60፡8)

ይህ ብዙ ሙስሊሞች ሊኖሩ የሚፈልጉበት መንገድ ነው። ዝም ብለው ብቻ ጓደኞቻችሁ በመሆን ሕይወትን መኖር ይፈልጋሉ። ክርስቲያኖችን በተመለከተ የሰጠው የመጨረሻ ትዕዛዙ ግን የተለየ ነው። በመጨረሻም እስልምና ዋናው ሃይማኖት በመሆኑ በክርስቲያኖች ላይ ትልቅ ተፅዕኖ አለው። ተከታዩ የሙሐመድ ታላቁ ተልዕኮ ነው፡-

> ከነዚያ መጽሐፍን ከተሰጡት ሰዎች፣ እነዚያን በአላህ በመጨረሻዉ ቀን የማያምኑትን፣ አላህና መልክተኛዉ እርም ያደረጉትንም እርም የማያደርጉትንና እዉነተኛዉንም ሃይማኖት የማይቀበሉትን እነርሱ የተዋረዱ ሆነዉ ግብርን በእጆቻቸው እስከሚሰጡ ድረስ ተዋጉዋቸው። አይሁድ ዑዘይር የአላህ ልጅ ነዉ፣ አላችሁ፤ ክርስቲያኖችም አልመሲሕ የአላህ ልጅ ነዉ አሉ፤ ይህ በአፎቻቸዉ (የሚናገሩት) ቃላቸው ነው፤ የነዚያን ከነሱ በፊት የካዱትን ሰዎች ቃል ያመሳስላሉ፤ አላህ ያጥፋቸዉ (ከእዉነት) እንዴት ይመለሳሉ! ከርሱ በቀር ሌላ አምላክ የሌለዉን አንድን አምላክ ሊገዙ እንጂ ያልታዘዙ ሲሆኑ ሊቃውንቶቻቸውንና መነኮሳታቸዉን የመርየምን ልጅ አልመሲሕንም ከአላህ ሌላ አማልክት አድርገው ያዙ፤ ከሚያጋሩት ሁሉ የጠራ ነው። የአላህን ብርሃን በአፎቻቸዉ ለማጥፋት ይፈልጋሉ፤ አላህም ከሐዲዎች ቢጠሉም እንኳ ብርሃኑን መምላትን እንጂ ሌላን አይሻም። እርሱ ያ አጋሪዎቹ ቢጠሉም መልክተኛዉን (ሙሐመድን) በቅን መንገድና በእውነተኛ ሃይማኖት ላይ ከሃይማኖት ሁሉ በላይ ይፋ ያደርገው ዘንድ የላከው ነዉ። (ቁርኣን 9፡29-33፣ እንዲሁም 48፡28-29፣ 61፡9)

ሙሐመድ ለተከታዮቹ የሰጠው ታላቁ ተልዕኮ የእርሱን አምላክ፣ ትምህርት ወይንም ነቢይነቱን የማይቀበሉትን ሕዝቦች እንዲዋጉና እንዲያስገዙ ነው። በተለይ ክርስቲያኖችና አይሁድ ስለ እግዚአብሔር ልጅ ከሚያስተምሩት አስተምሕሮ የተነሳ ትኩረት ተደርጎባቸዋል። የእርሱም ተከታዮች ይህንኑ በስኬት ፈፅመዋል። የአረብ ባሕረ ሰላጤን፣ መካከለኛው ምሥራቅን፣ ሰሜን አፍሪካን፣ እስፔንን፣ ፋርስን እስከ ቻይና ጠረፍ ድረስ በመውረር ያዙ። የምሥራቃዊ ሮማና የፋርስ ግዛተ መንግሥታት የእስልምናን መምጣት ተከትሎ ህልውናቸው አከተመ። እስልምና ለ1200 ዓመታት ያህል ዓለምን ሊገዛ ችሏል። ከወራራው በኋላ በአጭር ጊዜ ውስጥ ብዙ ክርስቲያኖች እስልምናን ተቀበሉ። ሙስሊሞች ይህንን ወርቃማ የእስልምና ዘመናት በማለት ይጠሩታል። ስለዚህ ቁርአን ለሙስለሊመም መሪዎች ፖለቲካዊ አጀንዳና ግልፅ ግቦችን በመስጠት ወደ ክርስቲያኖች ይልካቸዋል።

ይህንን ክፍል የጀመርነው ቁርኣን ስለ ክርስቲያኖችና ስለ ክርስትና ምን ይላል? የሚል ጥያቄን በማንሳት ነው። ቁርኣን የወንጌልን ዋና ዋና አስተምሕሮዎች በሙሉ እንደሚቃወም፣ በሙስሊም ወንዶችና በክርስቲያን ሴቶች መካከል ግንኙነት እንዲኖር እንደሚያበረታታ እንዲሁም ክርስቲያኖችን በተመለከተ ለሙስሊም መንግሥታት ፖለቲካዊ አጀንዳን እንደሚሰጥ ተመልክተናል። ይህ ዝግጅት ምን ያህል ሁሉን አቀፍ እንደሆነ በማሰብ ተገርማችሁ ሊሆን ይችላል ነገር ግን እስከ አሁን ድረስ የተመለከትነው ቁርኣንን ብቻ ነው! ስለ ክርስትና መማር እምነታቸውን ለሚማሩት ሙስሊሞች መሠረታዊ ጉዳይ ነው። በዚህ ዘመን ስለ ክርስትና መማር ለእነርሱ እንደ ጌዴታ የሚቆጠር ነው።

ይህ ምዕራፍ ሁሉም ሙስሊሞች ቁርኣን ስለ ክርስትና የሚያስተምረውን በማወቅ ያምናሉ የሚል መልእክት የለውም። ነገር ግን ይህ እስልምና የሚያስተምረውና የእስልምናን ባሕል የሚቃኝ ጉዳይ ነው።

## መጽሐፍ ቅዱስ ስለ እስልምና ምን ይላል?

አሁን ደግሞ የጫወታ ሜዳውን በመለወጥ መጽሐፍ ቅዱስ ስለ እስልምና ምን ይላል? ብሎ ለመጠየቅ ጊዜው ነው።

የሐዋርያት ሥራን መጽሐፍ ስናነብ የኢየሱስ ሐዋርያት የተለያዩ ሕዝቦችን በወንጌል ሲደርሱ እንመለከታለን። አይሁድ፣ ሳምራውያን፣ ሮማውያን፣ የአይሁድ መሪዎች፣ አስማተኞች፣ ፈላስፎች፣ ጣዖት አምላኪያን፣ የዜውስ ተከታዮች፣ የአርጤምስ አምላኪዎች፣ የመጥምቁ የሐንስ ተከታዮች ... ነገር ግን ሙስሊሞች በወቅቱ አልነበሩም። ይህን የሆነበት ግልፅ ምክንያት እስልምና ከክርስቶስ በኋላ 600 ዓመታት ያህል ቆይቶ ስለመጣ ነው። ስለዚህ አዲስ ኪዳንን ስታነቡ የእስልምና ርዕስም ሆነ የሙሐመድ ማንነት አይጠቀስም።

በወንጌል ውስጥ ኢየሱስ ስለ ሐሰተኞች ነቢያን ማስጠንቀቂያ ሰጥቷል።እንዲህ አለ፡-

> የበግ ለምድ ለብሰው ከሚመጡባችሁ በውሥጣቸው ግን ነጣቂዎች ተኵላዎች ከሆኑ ከሐሰተኞች ነቢያት ተጠንቀቁ። ከፍሬያቸው ታውቋቸዋላችሁ። ከእሾህ ወይን ከኩርንችትስ በለስ ይለቀማልን? (ማቴ. 7፡15-16)

> ሐሰተኞች ክርስቶሶችና ሐሰተኞች ነቢያት ይነሣሉና፥ ቢቻላቸውስ የተመረጡትን እንኳ እስኪያስቱ ድረስ ታላላቅ ምልክትና ድንቅ ያሳያሉ። እነሆ፥ አስቀድሜ ነገርኋችሁ። (ማቴ. 24፡24-25)

ይሁን እንጂ ይህ የኢየሱስ ማስጠንቀቂያ አጠቃላይ እንጂ በእስልምና ላይ ብቻ በተናጠል ያተኮረ አይደለም። የእስልማና ሃይማኖትና ሙሐመድ የተባለ ሰው በኢየሱስ አልተጠቀሱም።

ብሉይ ኪዳንስ? ሙስሊሞች ሙሐመድ የእስማኤል ዘር እንደሆነ ስለሚናገሩ ሙስሊሞችና አንዳንድ ክርስቲያኖች ለእስልመናና ለሙሐመድ መሠረት ለማግኘት የዘፍጥረትን መጽሐፍና የእስማኤልን ማንነት ለመመልከት ሞክረዋል። ይህ ክርክር ምን ያህል ውኀ የሚቋጥር ነው የሚለው ሌላ ጥያቄ ሆኖ በግል መታወቅ ያለበት ነገር ቢኖር በዘፍጥረት ውስጥ የተጠቀሰው የእስማኤል ታሪክ በምንመም መንገድ እስልምናንና የሙሐመድን ማንነት የሚጠቅስ አለመሆኑ ነው። እስልምናንም ሆነ ሙሐመድን እንድንጠባበቅ የሚያሳሰብ ምንም ነገር በውስጡ አልያዘም።

ቁርአን ስለ ክርስትና በሚናገረው ሁኔታ መጽሐፍ ቅዱስ ስለ እስልምናም ሆነ ስለ ሙሐመድ አይናገርም። ይህ ደግሞ የራሱ መዘዝ አለው።

## ውጤቱ

ቁርአን ስለ ክርስቲያኖችና ስለ ክርስትና ብዙ ነገሮችን በመናገር ሙስሊሞች በአስተምህሮ፣ በፆታዊ ፍቅርና በፖለቲካ ለክርስቲያኖች ዝግጁዎች እንዲሆኑ እንደሚያደርጋቸው ቀደም ሲል ተመልክተናል። በአንፃሩ ደግሞ መጽሐፍ ቅዱስ እስልምናንም ሆነ ሙሐመድን በቀጥታ አይጠቅስም። የዚህ ልዩነት ውጤቱ ምንድነው?

የዚህ ውጤቱ ስለ ሃይማኖታቸው የተማሩ ሙስሊሞች ለክርስትና ዝግጁዎች ሲሆኑ ከየት መጀመር እንዳለባቸው ያውቃሉ። ሁሉንም የወንጌል አስተምህሮዎችና መጽሐፍ ቅዱስን ለመቃወም ዝግጁዎች ናቸው። በክርስቲያኖች መካከል ለመኖር ራሳቸውን ያዘጋጁ ሲሆን መንግሥታታቸው ከክርስቲያኑ ዓለም ጋር ስላላቸው መስተጋብር ዝግጁዎች እንደሆኑ ታሪካቸው ያሳያል። ክርስትና ስህተት ስለመሆኑና ስለ ኢየሱስ እውነቱን ለክርስቲያኖች የማስተማር ኃላፊነት እንዳለባቸው በራስ በመተማመን ያስባሉ። ክርስቲያኖችን ጥያቄዎችን ለመጠየቅ በሚያስችሏቸው መጽሐፍትና ቪድዮዎች የታጠቁ ናቸው። ለሙስሊሞች ስለ ክርስትና መማር ግዴታ ሲሆን ዝግጁዎች ናቸው።

ለክርስቲያኖች ጉዳዩ የተገላቢጦሽ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ስለ እስልምና በቀጥታ ምን ስለማይል ለክርስቲያኖች ስለ እስልምና መማር የምርጫ ጉዳይ ነው። አንድ ክርስቲያን ክርስቲያን ለመሆን መሠረታዊ የእስልምና አስተምሕሮዎችን ማወቅ ስለማይጠበቅበት እምነታቸውን ጠንቅቀው የተማሩ ክርስቲያኖች እንኳ እስልምናን ላያውቁ ይችላሉ። የዚህም ውጤቱ ክርስቲያኖች ከሙስሊሞች ጋር ለመነጋገር ዝግጁዎች እንዳይሆኑ አድርጓቸዋል። ሙስሊሞች በወንጌል ላይ ለሚያቀርቧቸው ተቃውሞዎች ዝግጁዎች አይደሉም። በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ ለሚሰነዘሩት የተጠኑ ትችቶች ዝግጁዎች አይደሉም። ስለ ታሪክ ሙስሊሞች ለሚናገሯቸው ሐሳቦች ዝግጁዎች አይደሉም። አንድ ዓይነት አምላክ ስለ ማምለክ አለማምለካችን እንኳ እርግጠኞች አይደሉም። ከክርስቲያኖች ጋር እንዴት መነጋገር እንዳለበት ከተማረ ሙስሊም ጋር መነጋገር ለክርስቲያኖች ቀላል አይደለም። ለብዙ በምዕራብ አገራት ለሚኖሩ ክርስቲያኖች እስልምና የማይታወቅ፣ እንግዳና ያልተዘጋጁበት ነገር ነው።

መጽሐፍ ቅዱስ በቂ እንዳልሆነ እየተናገርኩ አይደለም። በቂ እንደሆነ አምናለሁ፤ ይህንንም በቀጣዩ ምዕራፍ እገልጣለሁ። እኔ እያልኩ ያለሁት ቁርኣን ሙስሊሞችን ለክርስቲያኖች ዝግጁ የሚያደርግበት መንገድ መጽሐፍ ቅዱስ ክርስቲያኖችን ለሙስሊሞች ዝግጁ ከሚያደርግበት መንገድ የተለየ መሆኑ መታወቅ እንዳለበት ነው።

ይህንን በምሳሌ ለመግለጥ ያህል ስለ አንድ ወዳጄ እውነተኛ ታሪክ ልንገራችሁ። ይህ ወዳጄ ያደገው መጽሐፍ ቅዱስን በጥሩ ሁኔታ በምታስተምር ቤተክርስቲያን ውስጥ ነበር። ይህንንም ዕድል በመጠቀም በአንድ ጥሩ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ውስጥ የመጀመርያ ዲግሪውን ተማረ። አሁን ዕድሜው 30 ዓመት ያህል ይሆናል። ትምህርቱን ካጠናቀቀ በኋላ በዩኒቨርሲቲ ካምፓስ ውስጥ እንዲያገለግል ተመድቦ የነበረ ሲሆን በዚህን ወቅት አንድ የ 18 ዓመት ሙስሊም ተማሪ አገኘ። ይህ ሙስሊም ወጣት መጽሐፍ ቅዱስ መበረዙን ለማሳየት የመጽሐፍ ቅዱስን የንባብ ሕየሳ ጠቀሰ፣ ክርስቲያኖች ከብለይ ኪዳን ጋር ያላቸውን ግንኙነት ተቸ፣ ጳውሎስ ክርስትናን  እንዴት እንደበረዘ ተናገረ። ይህንን ሁሉ ሲያደርግ ደግሞ ሰፋፊ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎችን በመጥቀስ ነበር። ይህ ወዳጄ እንዲህ ሲል ጻፈልኝ፡-

> ይህ ሙስሊም ወጣት የንግግር ክህሎቱ ከፍተኛ ሲሆን የዕውቀቱም ልክ ከእኔ ጋር የሚመጣጠን ነው። የርሱ ጥያቄዎች ለኔ እንዲህ ከከበዱ ለሌሎች ተማሪዎች ደግሞ ምን ያህል ሊከብዱ እንደሚችሉ አሰብኩ። የኮሌጅ ትምህርቴ እስልምናን ለመገዳደር ምን ያህል ጎደሎ እንደሆነ ተረድቻለሁ።

አሁንም ሙስሊሞች በሙሉ በዚህ ልክ ዝግጁዎች ናቸው እያልኩ አይደለም ነገር ግን እስልምና ሙስሊሞችን ዝግጁዎችና ተጠራጣሪዎች እንዲሆኑ እንደሚያደርጋቸው ክርስቲያኖች እንዲያውቁ እያሳሰብኩ ነው።

# ማጠቃለያና ዕድሎች

በዚህ መረጃ ላስደነግጣችሁ አልሻም ነገር ግን አውዳችንን እንድትገነዘቡ እፈልጋለሁ። ለክፍለ ዘመናት ቤተክርስቲያን በምዕራቡ ዓለም የሃይማኖት ትምህርት ምንጭ ሆና ኖራለች። ራሳችንንና የምዕራቡን ዓለም ስለ ክርስትና አስተምረናል ነገር ግን ስለ እስልምና አላስተማርንም። ለዚህ ነው ስለ እስልምና ያለን ዕውቀት አናሳ የሆነው። ከዚህም የተነሳ እስልምና በዓለም መድረክ ላይ በፍጥነት በመታየቱ ተደናግጠናል። ለዚህ ነው የትምህርት ተቋሞቻችን ስለ እስልምና የሚያስተምሩት ትምህርት ጥልቀት የሌለው የሆነው። ከዚህም የተነሳ የመገናኛ አውታሮቻችንና የፖለቲካ መሪዎቻችን ስለ እስልምና ቂላቂል ንግግሮችን እያደረጉ ነው።

እስልምና ከዓለም ዋና ዋና የሥነ መለኮት አስተምሕሮዎች መካከል አንዱ ነው። ከዚህ በኋላ የምርጫ ጉዳይ መሆኑ አክትሟል። በሁሉም ረገድ ለቤተክርስቲያን ተግዳሮት ነው። ይህ ተግዳሮት ነገሮችን ከተቆጣጠረ በኋላ አማራጭ ድምፆችን በሙሉ በኃይል ዝም ያሰኛል።

ይህንን ምዕራፍ የምናጠቃልለው እስልምና ያመጣቸውን ተግዳሮቶች በመናገር ብቻ ሳይሆን ዕድሎችንም በመጠቆም ጭምር ነው።

የመጀመርያው ዕድል ወንጌልን ከማዳረስ አኳያ ነው። ስለ ክርስትና ማውራት ከሙስሊሞች የሚጠበቅ ጉዳይ ነው። ይህ ደግሞ ለክርስቲኖች በር ከፋች በመሆኑ ትልቅ ዕድል ነው፤ “ስለ ክርስትና የሰማችሁት ምንድነው?” ብሎ መጠየቅ ቀላል ነው። ስለ ክርስትና የተማሩት ጥቂትም ይሁን ብዙ ይህ ጥያቄ ትክክለኛ ጥያቄ ነው። ሙስሊም ጓደኛ ኖሯችሁ ስለ እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ለመነጋገር እንዴት መጀመር እንዳለባችሁ ግራ ከገባችሁ ይህንን ጥያቄ እንድትጠይቁ አበረታታችኋለሁ። መልሶቻቸው እንረሱንና እስላማዊ አስተምሕሯቸውን እንድትረዱ በማገዝ ስለ ክርስትና በተሻለ ሁኔታ እንድታብራሩላቸው በርን ይከፍትላችኋል።

ሁለተኛው ዕድል ለዝግጅታችን የሚሆን ነው። እስልምና ሙስሊሞችን የሚያዘጋጅባቸውን የተለመዱ ርዕሰ ጉዳዮች ስለምንረዳ በነዚህ ርዕሶች ዙርያ ራሳችንን እናዘጋጃለን። ይህ በጣም ጠቃሚ ነው። ለሁሉም ነገሮች መባከን ይቀርና ለተወሰኑ ነገሮች እንዘጋጃለን። ከሙስሊሞች ጋር ስንነጋገር ምንም ዓይነት ርዕሶች ሊነሱ ይችላሉ ነገር ግን እስልምና ስለ ሥላሴ፣ ስለ ተሠግዎና ስለ መጽሐፍ ቅዱስ ተዓማኒነት ከሚያስተምራቸው ነገሮች የተነሳ እነዚህ ርዕሶች የመነሳታቸው ዕድል ሰፊ ነው። ለነዚህ ዝግጁዎች መሆን እንችላለን።

በመጨረሻም እስልምና ስለ ገዛ እምነታችን የበለጠ እንድናውቅ አዲስ ዕድልን ፈጥሮልናል። በዙርያችን ካለው ዓለም የሚደርስብን ግፊት ብዙ ጊዜ በየትኞቹ የክርስትና ትምሕርቶች ላይ እንድናተኩር ተፅዕኖ ያሳድርብናል። እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ግፊቱ ይመጣ የነበረው ከምዕራቡ የዓለማዊነት እሳቤ ነበር። ስለ እግዚአብሔር መኖር፣ ስለ መከራና ስለ

እግዚአብሔር መልካምነት፣ ስለ ቤተክርስቲያን ግብረገብነት፣ ስለ ሃይማኖትና ስለ ሳይንስ የመሳሰሉትን ጉዳዮች በማንሳት ክርስትናን ተገዳድሯል። ነገር ግን የምዕራቡ የዓለማዊነት አስተሳሰብ ሥላሴ፣ ተሠግዎና ደህንነትን ለመሳሰሉት ክርስቲያናዊ አስተምሕሮዎች የሚሰጠው ትኩረት አናሳ ነው። ነገር ግን እስልምና እነዚህን አስተምሕሮዎች በመገዳደር ክርስቲያኖች እንዲያብራሩና እንዲከላከሉ ይገዳደራል። ስለዚህ እስልምና ማዕከላዊ አስተምሕሮዎቻችንን ለአዲስ አውድና ትውልድ በጥሩ ሁኔታ እንድናብራራ ያስገድደናል ማለት ነው። ሥላሴና ተሠግዎ ክርስቲያኖች ብዙ ጊዜ ችላ ከሚሏቸው ርዕሶች መካከል በመሆናቸው ይህ መልካም ነገር ነው።

**ትግበራ**

1. ክርስቲያናዊ አስተምህሮህን ተማሩ። በሚቀጥሉት ምዕራፎች ውስጥ ይህንን እናደርጋለን።

2. “እስልምና ስለ ክርስትና ምን ያስተምራል?” በማለት የወንጌል ውይይት መጀመር ትችላላችሁ። አታርሟቸው ዝም ብላችሁ አዳምጡ። ከዚያም “ስለ ክርስትና አንድ ነገር ላሳይህ እችላለሁን?” በማለት ጠይቁ።

# ምዕራፍ 3

## ወንጌል

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ለሙስሊሞች ወንጌልንም መናገር ከየት መጀመር አለብን በሚለው ሐሳብ ላይ አተኩራለሁ። ለሙስሊሞች ወንጌልን የምናካፍልባቸው ብዙ መንገዶች መኖራቸውን ገና ከጅምሩ ዕውቅና ለመስጠት እፈልጋለሁ። የመጽሐፍ ቅዱስን እውነት የሚያንፀባርቁ ታሪኮችን መናገር ይቻላል። ዝም ብለን ወደ ቤተክርስቲያን ልንጋብዛቸው እንችላለን። የግል ምስክርነቶቻችሁን በመናገር ስለ ደህንነት ያላችሁን ማረጋገጫ ልትነግሯቸው ትችላላችሁ። የክርስቲያን መዝሙሮችን፣ ፊልሞችን ወይንም የኢየሱስን ፊልም በስጦታ መስጠት ትችላላችሁ። ሌላው ደግሞ እስልምናን ማጋለጥ የተሰኘው ዘዴ ነው። ይህም ሙስሊሞች እምነታቸውን እንዲመረምሩ ለማድረግ እስልምና ስለ ጂሃድ፣ ሴቶችና ሙሐመድ፣ ወዘተ. የሚያስተምረውን መናገር ነው። እስልምናንና አስተምሕሮዎቹን ፍልስፍናዊ በመሆነ መንገድም መመርመር ይቻላል። ቁርኣን ስለ መጽሐፍ ቅዱስ ታሪኮችና ስብዕናዎች ጥቆማዎችን ስለሚሰጥ የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪኮችን እንደ ድልድይ መጠቀም ይቻላል። እነዚህ ሁሉ መንገዶች ጥሩዎችና ፍሬያማ ሊሆኑ የሚችሉ ናቸው። ሆኖም፣ በዚህ ምዕራፍ ውስጥ በመጨረሻው ምዕራፍ ላይ ባየነው ሐሳብ ላይ መገንባት እፈልጋለሁ። በመጨረሻው ምእራፍ ላይ ሙስሊም ወዳጃችሁን ስለ ክርስትና የሰሙትን ጠይቃችሁ እንድታዳምጡት ሐሳብ አቅርቤ ነበር። የወንጌል ውይይት ለመጀመር ቀጥሎ ምን ማለት እንዳለብን እንመለከታለን።

## ወንጌልን ማስተዋወቅ

ሲጀመር ዝም ብለን ወንጌልን እናካፍላለንን? መልሱ አዎንና አይደለም የሚል ነው። አዎ ስንል የማቴዎስ፣ ማርቆስ፣ ሉቃስና ዮሐንስ ወንጌላት ለሁሉም ሰው እኩል በሆነ ሁኔታ ተመዝግበዋል ማለታችን ነው። አገራችሁ የትም ቢሆን፣ የምትናገሩት ቋንቋ ምንም ቢሆን፣ የምትኖሩበት የታሪክ ዘመን መቼም ቢሆን ስለ ኢየሱስ ሕይወት የምታነቡት ምስክርነት በነዚህ አራት መጻሕፍት ውስጥ የሚገኘው ነው። ስለዚህ ለሙስሊሞችም ተመሳሳይ ነው። ልክ እንደማንኛውም ሰው ማቴዎስ፣ ማርቆስ፣ ሉቃስና ዮሐንስን ማንበብ ይጠበቅባቸዋል።

ነገር ግን መልሱ አይደለም የሚልም ነው። ለሁሉም ሰው ተመሳሳይ በሆነ መንገድ ወንጌልን አናካፍልም። ለምሳሌ ያህል የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍን ተመልከቱ። በሐዋርያት ሥራ ውስጥ ሐዋርያው ጳውሎስ ለተለያዩ ወገኖች ወንጌልን ሲያካፍል በተለያዩ መንገዶች ነበር። ይህንንም አይሁድንና ጣዖት አምላኪያን የሆኑትን አሕዛብ ካናገረበት መንገድ መረዳት ይቻላል። ለአይሁድና እግዚአብሔርን ለሚፈሩ የግሪክ ሰዎች ሲናገር እግዚአብሔር

ለአይሁድ አበው በነቢያት አማካይነት የሰጣቸውን ተስፋዎች በመናገር ይጀምራል። በማስከተልም ስለ ኢየሱስ በመናገር እግዚአብሔር በእርሱ ስትሣኤ አማካይነት ይህንን ተስፋ እንዴት እንደፈፀመ ያብራራል።

> እኛም ለአባቶች የተሰጠውን ተስፋ የምሥራቹን ለእናንተ እንሰብካለን፤ ይህን ተስፋ እግዚአብሔር በሁለተኛው መዝሙር ደግሞ፡- አንተ ልጄ ነህ እኔ ዛሬ ወለድሁህ ተብሎ እንደ ተጻፈ፥ ኢየሱስን አስነሥቶ ለእኛ ለልጆቻቸው ፈጽሞአልና። (ሐዋ. 13፡32-33)

> ጳውሎስም እንደ ልማዱ ወደ እነርሱ ገባ፥ ሦስት ሰንበትም ያህል ከእነርሱ ጋር ከመጻሕፍት እየጠቀሰ ይነጋገር ነበር፤ ሲተረጉምም ክርስቶስ መከራ እንዲቀበልና ከሙታን እንዲነሣ ይገባው ዘንድ እያስረዳ፡- ይህ እኔ የምሰብክላችሁ ኢየሱስ እርሱ ክርስቶስ ነው ይል ነበር። (ሐዋ. 17፡2-3)

ነገር ግን ጳውሎስ አቴንስ በነበረ ጊዜ ጣዖታትን ያመልኩ ለነበሩት ሰዎች ወንጌልን ያካፈለው ለየት ባለ መንገድ ነበር። እግዚአብሔር ሕይወትን የሰጠን ፈጣሪ መሆኑንና ጣዖታት እርሱን እንደማይወክሉ ነበር የነገራቸው። ከዚያም ኢየሱስ እውነኛው የእግዚአብሔር ወኪል መሆኑን በመናገር ስለ ኢየሱስ አስረዳቸው።

> በሕዝብም ዘንድ ምስክሮቹ ለሆኑት ከእርሱ ጋር ከገሊላ ወደ ኢየሩሳሌም ለወጡት ብዙ ቀን ታያቸው። (ሐዋ. 17፡31)

ስለዚህ ጳውሎስ ወንጌልን ለተለያዩ ሰዎች በተለያዩ መንገዶች ያደርስ ነበር። ጥያቄው ጳውሎስ ወንጌልን ለሙስሊሞች የሚያካፍለው በምን ምንገድ ሊሆን ይችላል የሚል ነው። ሙስሊሞች የብሉይ ኪዳንን ተስፋዎች የተቀበሉ አይሁድ አይደሉም ስለዚህ በዚያ መንገድ ሊሆን አይችልም። ጣዖትን የሚያመልኩ አሕዛብም ስላልሆኑ በዚያም መንገድ አይሆንም። ሙስሊሞች በሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ውስጥ ከምንመለከታቸው ቡድኖች ጋር አንድ አይደሉም። የራሳቸው ማንነት ያላቸው፣ ስለ ኢየሱስና ስለ ክርስትና የራሳቸው መረዳት ያላቸው ለየት ያሉ ቡድኖች ናቸው። ለነዚህ ለየት ያሉ ቡድኖች ጳውሎስ ወንጌልን የሚያካፍለው እንዴት ሊሆን ይችላል? የሚል ነው ጥያቄው።

ለዚህ ምላሽ ለመስጠት ጳውሎስ ለተለያዩ ቡድኖች ወንጌልን ሲያደርስ ምን ሲያደርግ ነበር? የሚል ጥያቄ መጠየቅ ያስፈልጋል። በነዚህ የተለያዩ መንገዶች እንዲናገር ምን አነሳሳው? ምን ምን ጉዳዮችን ነበር ከግምት ሲያስገባ የነበረው?

የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ጳውሎስ ከማን ጋር ሲነጋገር እንደነበር፣ የባሕል ገፅታዎቻቸውንና ምን እንደተናገራቸው ነግረናል። ከነዚህ ዝርዝር ጉዳዮች በመነሳት ጳውሎስ ሁለት ነገሮችን ያደረገ ይመስላል፡- የመጀመርያው ስለሚያናግራቸው ሰዎች ሃይማኖት ጠንቅቆ የሚያውቅ ይመስላል። እነዚያ ሰዎች ስለ ፈጣሪ የነበራቸው እሳቤ ምን ነበር? ሃይማኖታዊ

ልምምዶቻቸው ምን ነበር? ሃይማኖታዊ ፅንሰ ሐሳቦቻቸውና ክፍፍሎቻቸው ምን ነበር? ሁለተኛው ደግሞ ወንጌልን ከየት በመጀመር ቢነግራቸው ትርጉም ሊሰጣቸው እንደሚችልና ከባሕላቸው ጋር ሊያያዝ እንዲሁም ትገዳሮቶቹን ሊጋፈጥ እንደሚችል ጠንቅቆ ያውቃል።

ስለዚህ ወንጌልን በተሳካ ሁኔታ ለሙስሊሞች ለማድረስ ክርስቲያኖች የትኞቹን እስላማዊ አስተሳሰቦችና ባሕሎች ከግምት ውስጥ ማግባት ያስፈልጋቸዋል? ከሙስሊሞች ጋር ካደረኳቸው ውይይቶችና ሙግቶች በመነሳት ሁለት ወሳኝ የሆኑ እስላማዊ ገፅታዎችን መንካት እንደሚገባን ተረድቻለሁ። የመጀመርያው በነቢያት ሁሉ እናምናለን የሚለው እስላማዊ አመለካከት ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ መጽሐፍ ቅዱስ ተበርዟል የሚለው ነው።

## በነቢያት ሁሉ እናምናለን!

ከእስልምና መሠረታውያን እምነቶች መካከል አንዱ በነቢያት ሁሉ ማመን ነው። ሙስሊሞች በሙሐመድ ብቻ ሳይሆን በፈጣሪ ነቢያት ሁሉ የማመን ግዴታ አለባቸው። ይህ እምነት በመላው ሙስሊሞች ዘንድ ቅቡል ሲሆን የእስላማዊ ባሕል አካል ነው እንደሁም በቁርአን ውስጥ ተዟል።

> መልካም ሥራ ፊቶቻችሁን ወደ ምሥራቅና ምዕራብ አቅጣጫ ማዞር አይደለም። ግን መልካም ሥራ በአላህና በመጨረሻው ቀን፣ በመላእክትም፣ በመጻሕፍትም፣ በነቢያትም፣ ያመነ ሰው ገንዘብንም ከመውደዱ ጋር ለዝምድና ባለቤቶችና ለየቲሞች ለምስኪኖችም፣ ለመንገደኞችም፣ ለለማኞችም፣ ለጫንቃዎችም (ማስለቀቅ) የሰጠ ሰውና ሶላትንም ደንቡን ጠብቆ የሰገደ፣ ዘካንም የሰጠ፣ ቃል ኪዳንም በገቡ ጊዜ በኪዳናቸው የሞሉ (ሰዎች ሥራ) ነው። በችግር በበሽታና በጦር ጊዜም ታጋሾችን (እናወድሳለን)። እነዚህ እነዚያ እውነትን የያዙ ናቸው። እነዚያም ተጠንቃቂዎቹ እነርሱ ናቸው። (ቁርአን 2፡177)

ሙስሊሞች ስለ ነቢያት የሚያምኑት ሙሐመድ መልአክ እንደነገረው በተናገረው መሠረት ነው። በቁርአን ውስጥ ሙሐመድ የአብርሃም፣ ይስሐቅ፣ እስማኤል፣ ያዕቆብ፣ ሙሴ፣ ዳዊት፣ ሰለሞን፣ ኢዮብ፣ ዮናስ፣ ኢየሱስና የሌሎች ብዙ ስብዕናዎችን ታሪክ ይተርካል። እነዚህ ሁሉ ሰዎች ነቢያት እንደሆኑ የሚታሰቡ ሲሆን ሙስሊሞች ታሪኮቻቸውንና መልእክቶቻቸውን ይማራሉ። ሙሐመድ የነዚህን ሰዎች መጻሕፍትንም ይጠቅሳል፡-

ከርሱ በፊት ያሉትን መጻሕፍት የሚያረጋግጥ ሲሆን መጽሐፉን (ቁርአንን) ባንተ ላይ ከፋፍሎ በዉነት አወረደ። ተዉራትንና ኢንጅልንም አውርዷል። (ቁርአን 3፡3)

ይልቁንም በዚያ በሙሳ ጽሁፎች ውስጥ ባለው ነገር አልተነገረምን? (ቁርአን 53፡ 36)

> ጌታህም በሰማያትና በምድር ያለውን ሁሉ ዐዋቂ ነው፤ ከፊሉንም ነቢያት በከፊሉ ላይ በእርግጥ አብልጠናል፤ ዳውድንም ዘቡርን ሰጥተነዋል። (ቁርአን 17፡55)

የዚህ ትምህርት ውጤቱ ሙስሊሞች ብዙ ጊዜ ኢየሱስን ጨምሮ በነቢያት ሁሉ እንደሚያምኑ ለክርስቲያኖች መንገራቸው ነው። ሙስሊሞች ኢየሱስንና ሁሉንም የፈጣሪ ነቢያት ካልተቀበሉ ሙስሊም መሆን እንደማይችሉ አበክረው ይናገራሉ። ሙስሊሞች ብዙ ጊዜ በክርስቲያኖች ዘንድ ተቀባይነትን ለማግኘት ሲሉ ይህንን ይናገራሉ። ሙስሊሞች በሁሉም ነቢያት እንደሚያምኑ መናገራቸው እስልምና ለየት ያለ ሃይማኖት እንደሆነ እንዲሰማቸውና ሌሎችም ሰዎች እንደዚያ እንዲያስቡ ያደርጋቸዋል።

ይህ በነቢያት ሁሉ የማመን አስተሳሰብ በእስልምና ወሳኝ የሆነ እምነት ሲሆን ክርስቲያኖች ይህ ለሙስሊሞች ምን ያህል ወሳኝ እንደሆነ ማወቅ ያስፈልጋቸዋል። የክርስቶስ ሞት ለክርስቲያኖች ወሳኝ የሆነውን ያህል ይህም እምነት ለሙስሊሞች ወሳኝ ነው። ይህ የነርሱ መለያ ነው። ማንነታቸውንና ልዩ የሚያደርጋቸውን የሚገልጥ እምነት ነው። ሙስሊምን ሙስሊም የሚያደርገው ነው፡- “እኛ በነቢያት ሁሉ የምናምን ነን። ከፈጣሪ የሆኑትን መልእክተኞች በሙሉ የምንቀበል ነን። የነቢያትን ዓላማ የምናሳካው እኛ ነን!” እስልምና ነቢያትን በሙሉ ስለሚቀበል ትክክል ነው ብለው እንዲተማመኑበት የሚያደርጋቸው ይህ እምነት ነው። ሙሐመድ ስለ ኢየሱስ ያስተማረው እውነት እንደሆነ ማረጋገጫ የሰጣቸው ይህ እምነት ነው። ሙስሊም መሆን ማለት ነቢያት በሙሉ ያስተማሩትን መቀበል ሲሆን ይህንንም የሚያደርጉት ሙስሊሞች ብቻ ናቸው። ይህ መለያቸው ነው። ይህ ኩራታቸው ነው።

ክርስቲያኖች ወንጌልን ለሙስሊሞች ሲያቀርቡ ይህንን የእስልምና እምነት ገፅታ ከግምት ማግባት የሚገባቸው ለምንድነው? ለዚህ ምክንያቱ አብዛኞቹ ሙስሊሞች ኢየሱስና ሌሎች ነቢያት ያስተማሩትን እንደሚያውቁ ስለሚያስቡ ነው። ይህንንም ከሙሐመድ ነው የተማሩት። ስለዚህ ክርስቲያኖች ሙስሊሞች ወንጌልን እንዲቀበሉ ሲነግሯቸው ያንን ማድረግ እንደማያስፈልጋቸው ይሰማቸዋል ምክንያቱም ኢየሱስን እንደሚወዱት ያስባሉና። በነቢያትና በትምህርቶቻቸው አስቀድመው እንደሚያምኑ ስለሚሰማቸው የክርስትናን ወንጌል አለመቀበላቸው ትክክል እንደሆነ ያምናሉ። እንዲያውም ክርስቲያኖች ሊቀበሉት የተገባውን ትክክለኛ የኢየሱስ መልእክት አስቀድመው እንደተቀበሉ ያምናሉ። አብዛኞቹ ሙስሊሞች ወንጌልን እንዳይሰሙ የሚያግዳቸው በነቢያት ሁሉ እናምናለን የሚለው እስላማዊ ትምህርት ነው። ይህ ለወንጌል እንቅፋት ነው። ስለዚህ ክርስቲያኖች ወንጌልን ለሙስሊሞች ሲያቀርቡ ይህንን ከግምት ማስገባት ይኖርባቸዋል።

## መጽሐፍ ቅዱስ ተቀይሯል

ክርስቲያኖች ለሙስሊሞች ወንጌልን ሲያቀርቡ ከግምት ማስገባት የሚኖርባቸው ሌላው ጉዳይ መጽሐፍ ቅዱስ ተበርዟል የሚለው እስላማዊ ትምህርት ነው። ይህ ትምህርት በቀጥታ በቁርኣን ውስጥ የማይገኝ ሲሆን በእስልምናው ዓለም ውስጥ ግን በሰፊው ይናፈሳል። ሙስሊሞች ስለ ክርስትና ሲማሩ እንደ ዝግጅት አካል አድርገው የሚወስዱት ነው።

የእስልምና ባሕል አካል ነው። ሙስሊሞች የሚማሩት ከሙሐመድ በፊት የነበሩት ነቢያት ከፈጣሪ መጻሕፍትን እንደተቀበሉ ነው፤ ሙሴ ቶራን አመጣ፣ ዳዊት መዝሙራትን፣ ኢየሱስ ደግሞ ወንጌልን። ይሁን እንጂ በጊዜ ሒደት አይሁድና ክርስቲያኖች መጻሕፍታቸውን ለወጡት። አሁን ፈጣሪ ሙሐመድን በቁርኣን ልኮታል። ቁርኣን በትክክል ተጠብቋል። የነቢያትን እውነተኛ መልእት በትክክለ ጠብቆ የያዘ መጽሐፍ ነው። ቶራ፣ መዝሙርና ወንጌልን የመሳሰሉት መጻሕፍት የተወሰነ እውነት በውስጣቸው ሊኖር ይችላል ነገር ግን ከስህተት ጋር የተቀላቀለ ነው። ሙስሊሞች በሌሎች መጻሕፍት ውስጥ የሚገኙትን ስህተትና ትክክል የሆኑ ነገሮችን ለመለየት ቁርኣንን መጠቀም ይኖርባቸዋል (ቁርኣን 5፡48)።

ክርስቲያኖች ለሙስሊሞች ወንጌልን ሲያካፍሉ ይህንን እስላማዊ ገፅታ ከግምት ማስገባት ያስፈልጋቸዋል። ሙስሊሞች መጽሐፍ ቅዱስ የማይታመን እንደሆነ የሚያስቡ ከሆነ ስለ ወንጌል የምንነግራቸውን ሊቀበሉ አይችሉም ማለት ነው። መጽሐፍ ቅዱስ እንደተለወጠ ማመናቸው የመጽሐፍ ቅዱስን ወንጌል እንዳያምኑ ያደርጋቸዋል። የመጽሐፍ ቅዱሱን ወንጌል የማይቻል ያደርገዋል። ስለዚህ ክርስቲያኖች ለሙስሊሞች ወንጌልን ለማቅረብ ሲያቅዱ ይህንን ጉዳይ ከግምት ማግባት ይጠበቅባቸዋል።

## ትክክለኛው መንገድ ምንድነው?

እስልምና የመጽሐፍ ቅዱሱን ወንጌል በሙስሊሞች ዘንድ ተቀባይነት እንዳያገኝ የሚያደርጉ ሁለት ገፅታዎች እንዳሉት ተመልክተናል። እነዚህም በነቢያት ሁሉ እናምናለን የሚለው እስላማዊ አስተሳሰብና መጽሐፍ ቅዱስ ተበርዟል የሚሉት ናቸው። መጽሐፍ ቅዱስን ትኩረት የሚስብና የሚያስደንቅ ልናደርግላቸው ይገባል፤ በዚህ ሁኔታም የተማሩትን እንደገና እንዲያጤኑት ልናደርጋቸው እንችላለን። ይህንን ማድረግ ቀላል ነው።

## ወንጌልን ማስተዋወቅና መናገር

ሙስሊሞች በነቢያት ሁሉ እንደሚያምኑ ቢናገሩም ነገር ግን አያምኑም። በተግባር ሙሐመድ ስለ ነቢያት የነገራቸውን ብቻ ነው የሚያምኑት። ይህ ነቢያትን ከማመን ጋር አንድ አይደለም። አንዱን ሰው ሙሐመድን ማመን ነው። ሙስሊሞች “ግን እኮ ሙሐመድ የፈጣሪን ቃል ነው የተናገረው” ይላሉ። ይህ ከነጥቡ ያፈነገጠ ነው። አሁንም ቁርኣን ከአንድ ሰው የተገኘ ነው።

ቁርኣን የትኛውንም የመጽሐፍ ቅዱስ መጽሐፍ አልያዘም። ይህንን የምልበት ምክንያት አንዳንድ የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት በቁርኣን ውስጥ አንደተካተቱ የሚያስቡ ክርስቲያኖች ስለገጠሙኝ ነው። እነዚህ ክርስቲያኖች ቁርኣንን ጭራሹኑ ያላነበቡ ሲሆን ሙስሊሞች በሙሴ እንደሚያምኑ ስለተነገራቸው ዘፍጥረትና ዘጸአትን የመሳሰሉት የሙሴ መጻሕፍት በቁርኣን ውስጥ እንደተካተቱ ያስባሉ። ነገር ግን እውነቱ እንደርሱ አይደለም። ቁርኣን የያዘው ሙሐመድ መልአክ እንደነገረው የተናገረውን ብቻ ነው። ቁርኣን የአንድ ግለሰብ

ሥራ ሲሆን ሙስሊሞችም የሚያምኑት አንዱ ግለሰብ ሙሐመድ ስለ ነቢያት የነገራቸውን ነው።

ይህ ማለት ሙስሊሞች ስለ ሙሴ የተማሩት የሙሴ መጽሐፍ የሆነውን ቶራን በማንበብ ሳይሆን ከሙሐመድ ነው። ሙስሊሞች ስለ ዳዊት የተማሩት መዝሙረ ዳዊትን በማንበብ ሳይሆን ከሙሐመድ ነው። ስለ ኢዮብ፣ ስለ ዮናስና ስለመሳሰሉት ሰዎች የተማሩት የእነርሱን መጻሕፍት በማንበብ ሳይሆን ከሙሐመድ ነው። ሙስሊሞች በኢየሱስ እናምናለን ሲሉ ሙሐመድ ስለ ኢየሱስ የነገራቸውን ሁሉ እንደሚያምኑ እየተናገሩ ነው። የትኛውንም የወንጌል ትራኬ አንብበዋል ማለት አይደለም። እስልምና ሙሉ በሙሉ የተመሠረተው በአንድ ግለሰብና ያ አንዱ ግለሰብ ስለ ሌሎች በተናገረው ላይ ነው። ሙስሊሞች በነቢያት ሁሉ እናምናለን ሲሉ ይህንን ማለታቸው ነው።

በዚህ ረገድ እስልምና ከበሃኢ እምነት ጋር ተመሳሳይ ነው። የበሃኢ እምነት በሃኡላ በተባለ ሰው በ1863 በኢራን አገር የተመሠረተ ነው። ይህ ሰው ከፈጣሪ ዘንድ የተላከ ነቢይ መሆኑንና የሃይማኖታትን ሁሉ አንድነት እንዲሁም የነቢያትን ሁሉ ወንድማማችነት አስተማረ። የበሃኡላ ተከታዮች በሃኢዎች በመባል የሚታወቁ ሲሆን ነቢያትን በሙሉ እንደሚቀበሉ ይናገራሉ። በእርግጥ ሙሐመድን፣ ሙሴን፣ ዳዊትን ኢየሱስን፣ ወዘተ. ካልተቀበላችሁ በሃኢ ልትሆኑ አትችሉም። በሃኢዎች በነቢያት ሁሉ እንደሚያምኑ ቢናገሩም እንደ እውነቱ ከሆነ ግን የእነርሱ ነቢይ ስለ ነቢያት የነገራቸውን ብቻ ነው የሚያምኑት። በሙሐመድ ያምናሉ ነገር ግን ቁርአንን አያነቡም፤ በኢየሱስ ያምናሉ ነገር ግን ወንጌልን አያነቡም፤ በሙሴ ያምናሉ ነገር ግን ቶራን አያነቡም። አንድ ሰው ስለ ሁሉም ሰው እንዲያምኑ የነገራቸውን ብቻ ነው የሚያምኑት። ሙስሊሞች የሚያደርጉት ተመሳሳይ ነገር ነው። የተለያዩ ነቢያትን መጻሕፍት አያነቡም ነገር ግን አንድ ሰው ስለ ነቢያቱ የነገራቸውን ብቻ በጭፍን ተቀብለዋል። እስልምና በመሠረቱ ከበሃኢ ሃይማኖት ጋር ተመሳሳይ ነው። ሙስሊሞች በነቢያት የሚያምኑ በተግባር ሳይሆን በአፍ ብቻ ነው። በብቸኛነት የሚያምኑት በሙሐመድና እርሱ ስለ ነቢያት የነገራቸውን ነው።


ክርስትናስ እንዴት ነው? ከእስልምና ጋር አንድ ዓይነት ሃይማኖት ነውን? መጽሐፍ ቅዱስ አንድ መጽሐፍ ብቻ ሳይሆን በተለያዩ ነቢያት፣ በተለያዩ ቦታዎችና በተለያዩ ቋንቋዎች በ1500 ዓመታት ውስጥ የተጻፉ የተለያዩ መጻሕፍት ስብስብ ነው። የሙሴን ሕግ (ቶራ)፣ የዳዊትን መዝሙር፣ የሰለሞንን መጻሕፍት፣ ኢሳይያስ፣ ኤርምያስ፣ ሕዝቅኤል፣ ዳንኤል፣ ሆሴዕ፣ ኢዩኤል፣ አሞፅ፣ አብድዩ፣ ዮናስ፣ ኢዮብ፣ ሚክያስ፣ ናሆም፣ ዕንባቆም፣ ሶፎንያስ፣ ሐጌ፣ ዘካርያስ፣ ሚልክያስና የመሳሰሉትን ነቢያት መጻሕፍት አካቷል። በማቴዎስ፣ ማርቆስ፣ ሉቃስና ዮሐንስ የተጻፈውን የኢየሱስን ወንጌል ይዟል። የሐዋርያትም ጽሑፎች በውስጡ ይገኛሉ።

| መጽሐፍ ቅዱስ | | | |
| --- | --- | --- | --- |
| የሙሴ ሕግ (ቶራ) | የነቢያት መጻሕፍት | መዝሙራት | ወንጌል |
| «------------------------ 1500 ዓመታት ---------------------------» | | | |

ክርስቲያኖች እነዚህን ሁሉ መጻሕፍት የተቀበሉት ለምንድነው? መልሱ ቀላል ነው። ያነቧቸው ዘንድ ነው። ክርስቲያኖች በሁሉም ነቢያት ስለሚያምኑ ያነቧቸዋል። ክርስቲያኖች ስለ እግዚአብሔር የሚያምኑት በአንድ ግለሰብ ላይ ተመሥርተው ሳይሆን ነቢያትን በሙሉ በማንበብ ነው። ይህም ማለት በተግባር በነቢያት ሁሉ የሚያምኑት ሙስሊሞች ሳይሆኑ ክርስቲያኖች ናቸው ማለት ነው።

ክርስቲያኖች ግን የተለየና ከባዱን መንገድ መርጠዋል። ነቢያትን በሙሉ እናነባለን። አንድ ሰው የተናገረውን ብቻ መቀበል ለኛ ቀላል ቢሆንም ነገር ግን ከዚያ ይልቅ ነቢያት በሙሉ ያስተማሩትን ማንበብና መቀበልን የክርስትና መንፈሳዊነት አካል አድርገን ተቀብለናል። በእውነቱ ከሆነ ነቢያትን በሙሉ የምናከብረው እኛ ነን። የመጽሐፍ ቅዱስም ይዘት እንደሚያሳየው የአንድ ሰው ሥራ ከመሆን ይልቅ ከብዙ ነቢያት የተገኙ ብዙ መጻሕፍትን በውስጡ ይዟል። በዚህ መነሻነት ሙስሊሞች ነቢያትን በሙሉ እንደማያምኑ በማሳየት ወንጌልን ልናቀርብላቸው የምንችለው እንዴት ነው?

ይህን ሁሉ ግምት ውስጥ በማስገባት ሙስሊሞች ነቢያትን እንደማያምኑ በሚያሳይ መንገድ ወንጌልን ማስተዋወቅ እና መጽሐፍ ቅዱስን እንዲስብ እና እንዲስብ ማድረግ የምንችለው እንዴት ነው? መልሱ ቀላል ነው፣ የመጀመሪያው የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናትህ የይዘት ሠንጠረዥ ነው።




በዚህ ረገድ እንዲያግዛችሁ “መጽሐፍ ቅዱስ ምንድነው?” በሚል ርዕስ ያዘጋጀሁት ጽሑፍ አለ (አባሪ 1 ተመልከቱ)። ለሙስሊም ወዳጃችሁ ይህንን ስጡ ወይንም በጋራ አንብቡ።

በተጨማሪም የመጽሐፍ ቅዱስ ሽፋን ሙስሊሞች ቅዱሳት መጻሕፍታችን ምን እንደሚመስሉ እንዲያውቁ ሊያግዛቸው ይችላል። ብዙ ጊዜ እኛ ክርስቲያኖች መጽሐፍ ቅዱስን ለሙስሊሞች ስናዘጋጅ እንዲቀበሉት

በማሰብ ከቁርአን ጋር ለማመሳሰል እንሞክራለን። ነገር ግን ይህ አቀራረብ ተቃውሟቸውን ከመመለስ ይልቅ ሁለቱም መጻሕፍት ተመሳሳይ እንደሆኑ እንዲያስቡና ቁርኣን የተሻለ እንደሆነ እንዲያምኑ ያደርጋቸዋል። ማድረግ ያለብን ግን መጽሐፋችን በምንም መንገድ ከቁርአናቸው ጋር ተመሳሳይ እንዳልሆነ እንዲያውቁ በሚያደርግ መንገድ ነው። እኔ ቶራ፣ ነቢያት፣ መዝሙራትና ወንጌል የሚለውን በመጽሐፉ ሽፋን ላይ በማተም ይህንን አድርጌያለሁ። ሌላው ከድረገፅ ላይ አውርዳችሁ መለበጃ ላይ በማተም መጽሐፍ ቅዱሳችሁን መለበድ ነው።[3] ይህ ማውጫውን በሽፋን ላይ እንደማስቀመጥ ሲሆን ትልቅ ልዩነትን ይፈጥራል።

## ከሙስሊሞች ጋር መጽሐፍ ቅዱስን ማንበብ

ቅዱሳት መጻሕፍታችን ምን እንደሆኑ ካብራራችሁና በኋላ ቀጣዩ እርምጃ ከመጽሐፍ ቅዱስ ወንጌልን ማቅረብ ነው። ልታሳዩዋቸው የምትፈልጓቸው የራሳችሁ የተመረጡ ጥቅሶች ሊኖሩ ይችላሉ። በተለይም ዳግመኛ የማታገኟቸው ከሆነ ይህ ጥሩ ነው። ነገር ግን ወንጌልን ከናንተ ጋር ወይንም ለግላቸው እንዲያጠኑና ከዚያም ከናንተ ጋር እንዲወያዩ እንድትጋብዟቸው እመክራችኋለሁ። አጠቃላዩን ወንጌል ማንበብ ለሙስሊም የተለየ ልምምድ ነው። በምዕራፍ 2 ላይ እንደተመለከትነው አንድ የሰለጠነ ሙስሊም ለነጠላ ጥቅሶች ዝግጁ ሊሆን ይችላል ነገር ግን ለአጠቃላዩ ወንጌል ዝግጁ አይደለም። ይህ ለእነርሱ አዲስና አስገራሚ ልምምድ ነው። የብሉይ ኪዳን ነቢያት በተደጋጋሚ ከመጠቀሳቸው አንፃር ወንጌል አጠቃላዩን መጽሐፍ ቅዱስን ለማስተዋወቅ ጥሩ የጀምር ቦታ ነው። በርግጥ ጥቅሶቹ አጫጭርና ተጨማሪ ማብራርያዎችን የሚሹ ሊሆኑ ይችላሉ። ከነዚህ ምክንያቶች በመነሳት አንድን ሙስሊም ወንጌልን ከናንተ ጋር እንዲያነብ እንድትጋብዙት እመክራችኋለሁ።

የትኛውም ወንጌል ለሙስሊም ተስማሚ ነው። ማቴዎስ በሙስሊሞች የሚታወቁ ብዙ ርዕሶችን ስላካተተ በግሌ እርሱን እመርጣለሁ። አባሪ 2 ለሙስሊሞች አስፈላጊ የሆኑ ጥያቄዎችን በማካተት ማቴዎስን በቀላሉ ለማንበብ በሚያመቹ ክፍሎች ይከፍላል። ይህንን እንደ መምርያ ልትጠቀሙት ትችላላችሁ። ነገር ግን ወንጌልን ከሙስሊሞች ጋር ለማንበብ ኤክስፐርት መሆን እንደማያሻችሁ አፅንዖት መስጠት እፈልጋለሁ። ዝም ብላችሁ በጋራ በማንበብ ምን እንደሚያስቡ ጠይቋቸው። አስፈላጊ ናቸው የምትሏቸውን ነጥቦች አውጥታችሁ ጻፉ። የማታውቁትን ጥያቄ ከጠየቋችሁ እንደማታውቁና መልሱን እንደምታዘጋጁ ንገሯቸው። ይህ ምንም ማለት አይደለም። በሚቀጥለው ትወያዩበታላችሁ። ከሙስሊም ጓደኛችሁ ጋር ማቴዎስን እንዴት ማንበብና መወያየት እንደምትችሉ በማስከተል እቅድ ተቀምጧል።

---

[3] http://engagingwithislam.org/leaflets/EwI_Bible_Dust_Jacket.docx

| ከሙስሊም ጋር የማቴዎስ ወንጌል ማንበብ | |
|---|---|
| ኢየሱስን በታሪክ ውስጥ ማግኘት 1፡1-17 | በካርታው ላይ የተጠቀሱትን የቦታዎች መገኛ ቦታ አሳዩ። ዳራ፡ ዘፍጥረት 12፡1-3 እና 2ሳሙ 7፡11-17ን አንብቡና ስለ እግዚአብሔር ቃል ኪዳኖችና በኢየሱስ በኩል እንዴት እንደተፈጸሙ ተናገሩ። |
| የኢየሱስ ልጅነት 1፡18-2፡23 | እግዚአብሔር አምላክ ልጁን ኢየሱስን ሲጠብቀው እንዴት እናየዋለን? ስለ ኢየሱስ ስሞች ምን እንደሚያስቡ ጠይቁ? ማስጠንቀቂያ፡- አዳምም ሰብዓዊ አባት ስላልነበረው በድንግልና መወለዱ ኢየሱስ አምላክ መሆኑን አያረጋግጥም ይሉ ይሆናል። እግዚአብሔር የሁለቱም አባት ነው ግን በተለያየ መንገድ ነው።<br>ሆኖም በድንግልና መወለድ ኢየሱስ አምላክ መሆኑን አያረጋግጥም ነገር ግን እግዚአብሔር የሰውን ተፈጥሮ ወደ ራሱ ለመውሰድ የተጠቀመበት ዘዴ ነው። |
| መጥምቁ ዮሐንስ 3፡1-17 3፡1-17 | የዮሐንስ መልእክት ምን እንደሆነ ጠይቁ? ዮሐንስና ሁሉም ነቢያት ኢየሱስን እንዴት እንደሚጠቁሙ አሳዩ። ኢሳይያስ 53 |
| የኢየሱስ ፈተና 4፡1-11 | ሁላችንም ኃጢአት እንሠራለን ኢየሱስ ግን አይሠራም። ዲያብሎስ ኢየሱስን የእግዚአብሔርን ጥበቃ በተመለከተ እንዴት ነበር የፈተነው? ኢየሱስ እግዚአብሔር ጥበቃ እንደሚያደርግለት ተናግሯልን? |
| ስብከት 5- 7 | ይህ እግዚአብሔር የሚፈልገውን መስፈርት ያሳያል ስለዚህ ለሙስሊሞች አስገራሚ እና ተግዳሮት ነው። ሙስሊሞች የኃጢአትን ከባድነት እንዲረዱ ይረዳቸዋል። |
| የኢየሱስ ኃይል 8-9 | በቁርአን ኢየሱስ ምልክቶችን አድርጓል ነገር ግን ዝርዝሮቹ ጥቂት ናቸው። ራሳቸው እንዲያነቡት ፍቀዱላቸው። ኢየሱስ ምን ዓይነት ስልጣን አለው? |
| ቤተሰብ 10 | ከእግዚአብሄር በላይ ቤተሰባችሁ ታከብራላችሁን? |
| ምሳሌዎች 13 | የኢየሱስ ምሳሌዎች የትምህርቱ ትልቅ ክፍል ናቸው ነገር ግን በቁርአን ውስጥ የሉም። እነዚህ ምሳሌዎች እግዚአብሔር ሕዝቡን እንዴት እንደሚሰበስብ ምን ያስተምራሉ? |
| ንፁህ እና ርኩስ 15 | የሙስሊሙ ዓለም በውጫዊ ንፅህና ላይ ያተኩራል። ሀላል ምግብ ብቻ መመገብ የሚችሉት። በቀን ቢያንስ አምስት ጊዜ በሥርዓት መታጠብ አለባቸው። ኢየሱስ ይህን የንጽሕና ሐሳብ በመቃወም የውጭ መመሪያዎች የልባችንን ንጽሕና ፈጽሞ ሊለውጡ እንደማይችሉ አሳይቷል። ጠይቁ፡- ክፋት ከየት ነው የሚመጣ? |
| ኢየሱስ ማነው? 16 | ኢየሱስ ማነው? "የእግዚአብሔርን ልጅ" የሚለውን በኦሪት፣ በነቢያት፣ በመዝሙርና በወንጌል ውስጥ ማሳየት ያስፈልጋችሁ ይሆናል። |
| ኃጢአትና ይቅርታ 18 | ስለ ይቅርታ ምን እንማራለን? |
| ጋብቻ 19 | ይህ የእግዚአብሔርን መስፈርትና ኢየሱስ እንዴት ወደ እግዚአብሔር የመጀመሪያ የፍጥረት እቅድ እንደሚመልሰን ያሳያል። ስለ ፍቺ እና ከአንድ በላይ ማግባት ምን እንደሚያስቡ ጠይቁ። |
| ኢየሱስ በኢየሩሳሌም 20-23 | ኢየሱስ የሞቱን ትርጉም 20፡20-28 ላይ ገልጿል። |
| የሰው ልጅ 24-25 | ኢየሱስ ወደፊት ምን ሚና አለው? |
| የኢየሱስ ሞትና ትንሣኤ 26-28 | ኢየሱስ ሞቶ ከሙታን መነሣቱን በተመለከተ ቅዱሳት መጻሕፍት ግልጽ መሆን አለመሆናቸውን ጠይቅ |

## ስለ ወንጌል የሚነሱ ጥያቄዎችን መመለስ

ወንጌልን ከሙስሊሞችም ሆነ ከማንኛውም ሰው ጋር ስታነቡ በምንባቡ ውስጥ የሚገኙ አንዳንድ ነገሮችን ማብራራት ያስፈልጋችኋል። ለምሳሌ ያህል ሰዎቹ ማን እንደሆኑ፣ ባሕላቸውና እምነታቸውን፣ የአንዳንድ ቃላት ትርጉም፣ የብሉይ ኪዳኑ ጥቅስ የሚገኝበትን ቦታ፣ ወዘተ። ከየት እንጀምር?

ከደርዛዊ ነገረ መለኮት በመጀመር ትምህርቱን ማብራራት ትችላላችሁ። ክርስቲያኖች መጽሐፋቸውን ቶራ፣ ነቢያት፣ መዝሙራትና ወንጌላት በማለት ሲገለፁና ሲያብራሩ በነቢያት ሁሉ እናምናለን ለሚለው እስላማዊ አስተሳሰብ ምላሽ እየሰጡ ነው። ይህ አቀራረብ በተጨባጭ በሁሉም ነቢያት የሚያምኑት ክርስቲያኖች መሆናቸውን ያረጋግጣል። ስለ ኢየሱስ ሕይወት፣ ሞት፣ ትንሣኤና ዕርገት በዚህ ሁኔታ እንድታስረዱ እመክራችኋለሁ።

ሙስሊሞች ስለ ኢየሱስ ልጅነት ሲያነሱ ደስ ይለኛል ምክንያቱም ይህ ጉዳይ የክርስቲያኖች ፈጠራ እንዳልሆነ ለመንገር ዕድልን አገኛለሁና።

የእግዚአብሔር ልጅ የሚለው ሐሳብ በክርስቲያኖች የተጀመረ አይደለም። ሐዋርያው ጳውሎስም አልጀመረውም። በኒቅያ ጉባኤም አልተጀመረም። ከኢየሱስ በፊት የነበሩት ነቢያት የሚያውቁት ጉዳይ ነው። በቶራና በነቢያት ውስጥ እግዚአብሔር የሕዝቡ አባት እንደሆነና እነርሱም ልጆቹ እንደሆኑ ተነግሯል።

> ፈርዖንንም፡- እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፡- እሥራኤል የበኵር ልጄ ነው፤ ይገዛልኝ ዘንድ ልጄን ልቀቅ አልሁህ፤ አንተም ትለቅቀው ዘንድ እንቢ አልህ፤ እነሆ እኔ የበኵር ልጅህን እገድላለሁ ትለዋለህ። (ዘጸአት 4፡22-23)
>
> ደንቆሮ ብልሃተኛም ያልሆንህ ሕዝብ ሆይ፥ ለእግዚአብሔር ይህንን ትመልሳለህ? የገዛህ አባትህ አይደለምን? የፈጠረህና ያጸናህ እርሱ ነው። (ዘዳግም 32፡6)
>
> በልቅሶ ወጡ እኔም በማጽናናት አመጣቸዋለሁ፤ በወንዝ ዳር በቅን መንገድ አስኬዳቸዋለሁ፥ በእርሱም አይሰናከሉም፤ እኔ ለእሥራኤል አባት ነኝና፥ ኤፍሬምም በኵሬ ነውና። (ኤርምያስ 31፡9)
>
> ሕፃን በነበረ ጊዜ ወደድሁት፥ ልጄንም ከግብጽ ጠራሁት። (ሆሴዕ 11፡1)

በነቢያት መጻሕፍት ውስጥ በብዛት የተጠቀሰው አብያ የሚለው ስም ያሕዌ አባቴ ነው የሚል ትርጉም አለው።

አሁንም ስለ አባትነትና የእግዚአብሔር ልጅነት በነቢያትና በመዝሙራት ውስጥ እናነባለን። ይህ የተነገረው ግን የዳዊት ልጅ ስለሆነው ስለ መሲሁ ነው፡-

ዕድሜህም በተፈጸመ ጊዜ ከአባቶችህም ጋር ባንቀላፋህ ጊዜ፥ ከወገብህ የሚወጣውን ዘርህን ከአንተ በኋላ አስነሣለሁ፥ መንግሥቱንም አጸናለሁ። እርሱ ለስሜ ቤት ይሠራል፤ የመንግሥቱንም ዙፋን ለዘላለም አጸናለሁ። እኔም አባት እሆነዋለሁ፥ እርሱም ልጅ ይሆነኛል፤ ክፉ ነገርም ቢያደርግ፥ ሰው በሚቀጣበት በትርና በሰው ልጆች መቀጫ እገሥጸዋለሁ፤ (2ሳሙኤል 7፡12-14)

እርሱም፡- ልጅ ይሆነኝ ዘንድ መርጬዋለሁና፥ እኔም አባት እሆነዋለሁና ልጅህ ሰሎሞን ቤቴንና አደባባዮቼን ይሠራል። (1ዜና 28፡6)

ትእዛዙን እናገራለሁ፤ እግዚአብሔር አለኝ፡- አንተ ልጄ ነህ፥ እኔ ዛሬ ወለድሁህ። (መዝሙር 2፡7)

ይህ የሚያሳየው የእግዚአብሔር ልጅ የሚለው አስተምሕሮ ከኢየሱስ በፊት በነበሩት ነቢያት ሲሰበክ እንደነበረ ነው። ክርስቲያኖች ይህንን ሐሳብ አልፈጠሩትም። የነቢያት ትምህርት የነበረ ሲሆን ኢየሱስ ወደ ፍፃሜ አምጥቶታል።

| **መጽሐፍ ቅዱስ** | | | | **ቁርኣን** |
|---|---|---|---|---|
| ብሉይ ኪዳን | | | አዲስ ኪዳን | ሙሐመድ |
| ቶራህ | ነቢያት | መዝሙራት | ወንጌል | |
| <-------------------------- 1500 ዓመታት --------------------------> | | | | 23 ዓመታት |
| የሰው ልጅ በእግዚአብሔር አምሳል የተፈጠረ ነው። | | | | አይ |
| የእግዚአብሔር አባትነትና ወልድ | | | | አይ |
| እግዚአብሔር ከሕዝቡ ጋር ሊያድር ይመጣል | | | | አይ |
| የሰው ልጅ በኃጢአት ተበላሽቷል | | | | አይ |
| ክህነትና የኃጢአት ስርየት መስዋዕትነት | | | | አይ |
| የኖህ፣ የአብርሃም፣ የሙሴ እና የዳዊት ቃል ኪዳኖች | | | | አይ |
| አንድ የቤዝዎት ታሪክ | | | | አይ |

የነቢያት መጻሕፍት አንዳቸው በሌላቸው ላይ የተገነቡ ሲሆን በጋራ መጠናት ይኖርባቸዋል። በጋራ የተሟላውን የእግዚአብሔርን መልእክት ይሰጡናል። ሳጥን 1 ይህንን የቅዱሳት መጻሕፍት ተግባቦት ያሳየናል።

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ብዙ መጻሕፍት ቢኖሩም አንድ የመዋጀት ታሪክ ብቻ ነው ያለው። የእግዚአብሔር ሕዝብና የታዋቂ ሰዎቻቸው ታሪክ የተጠቀሰው ሕግጋት፣ ተግባራትና

ተስፋዎችን በአውድ ውስጥ መረዳት እንዲቻል ነው። ቃላትና ማዕረጋት በጊዜ ሒደት ተፈጥረው ተያያዥ ከሆኑ ታሪኮች ጋር ቀርበዋል። ቃል ኪዳናት ተሰጥተው እስከ ፍፃሜያቸው ድረስ ተተግብረዋል። እነዚህ ቃል ኪዳናት ትንቢታትንና ፍፃሜያቸውን ቅርፅ ያስይዛሉ። እነዚህን ሁሉ በጋራ አጣምረው የያዙ ታላላቅ የነገረ መለኮት ፅንሰ ሐሳቦች አሉ። ከቶራ፣ ነቢያትና መዝሙራት ውጪ ወንጌልን መረዳት አይቻልም፤ ከወንጌል ውጪ ቀደምት ነቢያት መቋጫ የላቸውም። ወንጌል አዲስ ነው ነገር ግን አዲስ ፈጠራ አይደለም። በነቢያት ሁሉ መሠረት ላይ የተመሠረተ ነው። አንድ አምላክና አንድ መልእክት ብቻ ነው ያለው።

ይህንን ሳጥን ስትመለከቱ ትኩረታችሁን ከመሳብ ያለፈ ነገር በውስጣችሁ እንደፈጠረ ተስፋ አደርጋለሁ። ትኩረትን የሚስብ ብቻ ሳይሆን ግሩም ነው! ውብ ነው! ይህ የቅዱሳት መጻሕፍት ተግባቦት መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል ስለመሆኑ አንዱ ማስረጃ ነው። በ1500 ዓመታት ውስጥ የተለያዩ ነቢያት፣ ከተለያዩ ቦታዎች የተገኙና የተለያዩ ቋንቋዎችን የሚናገሩ ቢሆኑም በኢየሱስ አማካይነት ወደ ፍፃሜ የመጣ አንድ መልእክት ነበራቸው። በዓለም ላይ እንዲህ ያለ ሌላ ሃይማኖት የለም። ይህንን የመጽሐፍ ቅዱስ ተግባት በመውሰድ የዓለም ሃይማኖታት ሁሉ ተመሳሳይ ባሕርይ እንዳላቸው እንዳታስቡ። እንደርሱ አይደለም። የዓለም አብዛኞቹ ሃይማኖታት ምን ማመን እንደሚገባችሁ የሚነግራችሁ አንድ ሰው ብቻ ነው ያላቸው። በክርስትና ግን እንደርሱ አይደለም። ነቢያትን ሁሉ የምንከትል ሲሆን ስለ እግዚአብሔር የምናምነው ሁሉ ነቢያትን ሁሉ ከማመን የተገኘ ነው። ክርስትና ለየት ያለ ነው።

## መጽሐፍ ቅዱስን እና ቁርኣንን አንድ ላይ ማንበብ

በዚህ ምእራፍ ውስጥ አንድ ሙስሊም ወንጌልን እንዲያነብ እንዴት እንደምንጋብዝ ተመልክተናል ነገር ግን ቁርኣንን እንድታነቡ ቢጋብዛችሁ ምን ማድረግ አለባችሁ? ይህ በስብከተ ወንጌል ጊዜ ሊከሰት ይችላል።

ክርስቲያኖች ቁርኣንን ከማንበባቸው በፊት መጠንቀቅ አለባቸው። እውነት ነው ሐዋርያው ጳውሎስ በስብከቱ ላይ የግሪክ ፈላስፎችን ሲጠቅስ እናያለን።

> በእርሱ እንኖራለን እንንቀሳቀሳለን እንኖራለንና። አንዳንድ ገጣሚዎችህም “እኛ የእርሱ ዘሮች ነንና” እንዳሉት ነው። (የሐዋርያት ሥራ 17:28)

ይህ የሌሎች ሃይማኖታትን መጽሐፍት የማንበብ ምሳሌ ይሆነናል። ሆኖም የቁርኣን ንባብ አዲስ ክርስቲያንን ግራ ሊያጋባና እናንተ እስልምናን እንደምትቀበሉ በማሳሰብ እንዲሰናከሉ ሊያደርጋቸው እንደሚችል ማጤን ይኖርብናል።

እነዚህን ነገሮች ከግምት ውስጥካስገባችሁና ቁርኣንን ማንበብ ምንም ችግር እንደሌለው ከተሰማችሁ አንድ ሙስሊም ቁርኣንን እንድታነቡ ቢጋብዛችሁ ምን ማድረግ ይኖርባችኋል? ጥቂት ጥቆማዎች እነሆ።

ሙሐመድ የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪኮችን ደግሞ የተናገረባቸው አጋጣሚዎች በመኖራቸው ሁለቱን ማነጻጸር አስፈላጊ ነገር ነው። ለምሳሌ ያህል የዮናስን ታሪክ ከቁርኣን ማንበብ ትችላላችሁ።

> ዩኑስም በእርግጥ ከመልክተኞቹ ነው። እነሆ! ወደ ተመላው መርከብ በኮበለለ ጊዜ (አስታውስ)። እርሱም ተወቃሽ ሲሆን ዐሳው ዋጠው። እርሱ ከአመስጋኞች ባይኾንማ ኖሮ እስከ ትንሣኤ ቀን ድረስ በሆዱ ውስጥ በቆየ ነበር። እርሱ በሽተኛ ሆኖ በቃይ በሌለው (በባሕር) ዳርቻ ላይ ጣልነውም። በእርሱም ላይ (በአጠገቡ) ከቅል የሆነችን ዛፍ አበቀልን። ከዚያም ወደ አንድ መቶ ሺህ ወይም ከዚያ በላይ ላክነው። አመኑም። እስከ ጊዜ ድረስም አጣቀምናቸው። (ቁርኣን 37 ፡ 139-148)

ምን አስተዋላችሁ? ታሪኩ ያልተሟላ ነው። ለምሳሌ ዮናስ የሸሸው ለምንድን ነው? ለምን ዕጣ ተጣጣሉ? ዮናስ ለምን ተጠያቂ ሆነ? ዮናስ እግዚአብሔርን ያከበረው መቼና የት ነው? ለምንድነው የቅል ዛፍ በእርሱ ላይ የበቀለችው? ቁርኣን ምንም አይልም። ይህን ታሪክ ለመረዳት የቻላችሁበት ብቸኛው ምክንያት የመጽሐፍ ቅዱስን ዘገባ ስለምታውቁና የጎደለውን መረጃ መሙላት ስለምትችሉ ነው።

የዮናስንም ታሪክ ካነበባችሁ በኋላ መጽሐፉን አንብቡ። ምን አስተዋላችሁ?

- መጽሐፍ ቅዱስ የመጀመሪያውን የነቢዩ መጽሐፍ ይዟል ።
- መጽሐፍ ቅዱስ ሙሉውን የነቢዩ መልእክት ይዟል ።
- ቁርኣን ጥቂት ብቻ ዝርዝር ጉዳዮችን ይዟል።
- ቁርኣንን ለመረዳት መጀመርያ መጽሐፍ ቅዱስን ማወቅ ያስፈልጋል።

እነዚህ ከሙስሊም ጓደኞችሁ ጋር ለመወያየት ጥሩ ነጥቦች ናቸው፤ በተጨማሪም መጽሐፍ ቅዱስ ምን እንደሆነና ለምን ማንበብ እንዳለበት ያሳያሉ። ተመሳሳይ ነጥቦችን ለማንሳት ልታነቧቸው የምትችሏቸው ሌሎች ንጽጽሮችን እነሆ።

- ዘፍጥረት፡- ቁርኣን 7፡54 ከዚያም ዘፍጥረት 1ን አንብቡ።
- ዮናስ፡- ቁርኣን 37፡139-148 የዮናስን መጽሐፍ አንብቡ።
- ኢዮብ፡- ቁርኣን 21፡83-84፤ 38፡41-44። በመቀጠል ኢዮብ 1-2 እና 40-42ን አንብቡ።
- የኢየሱስ ትምህርትና ተአምራት፡- ቁርኣን 3፡48-49 በመቀጠል ማቴዎስ 5-7 እና 8-9።
- የኢየሱስ መመለስ በቁርኣን ውስጥ የለም ነገር ግን አብዛኞቹ ሙስሊሞች ያምናሉ። ርዕሰ ጉዳዩን አንብቡና ማቴዎስ 24-25ን አንብብ።

## 2. በቁርኣን ውስጥ ጠቃሚ ጥቅሶች

ሙሐመድ ኃጢአቱን መናዘዝ አለበት የሚል የቁርኣን አንቀጽ አለ።

> “እነሆ ከአላህ ሌላ አምላክ አለመኖሩንም ዕወቅ። ስለ ስህተትህም ለምእመናንም ምሕረትን ለምን። (ቁርኣን 47፡19)

ይህ በእርግጥ ሙሐመድ እንደ ኢየሱስ እንዳልሆነ ለማሳየት ይጠቅማል። ሙሐመድም ሲሞት ምን እንደሚገጥመው አያውቅም ነበር።

> "ከመልክተኞች ብጤ የሌለኝ አይደለሁም። በእኔም በእናንተም ምን እንደሚሥሠራም አላውቅም። ወደእኔም የሚወረደውን እንጅ አልከተልም። እኔ አስፈራሪ ብቻ ነኝ።” (ቁርኣን 46፡9)

ሙሐመድ በእርሱ ላይ ምን እንደሚደርስበት ካላወቀ እስልምና ኢየሱስ የሰጠንን ዓይነት ድነት የመስጠት ብቃት እንደሌለው በራሱ ላይ መስከሯል ማለት ነው።

በመጨረሻም መጽሐፍ ቅዱስን የሚያረጋግጡ ብዙ ጥቅሶች አሉ።

> እናንተ ያመናችሁ ሆይ! በአላህና በመልክተኛው በዚያም በመልክተኛው ላይ ባወረደው መጽሐፍ በዚያም ከበፊቱ ባወረደው መጽሐፍ እመኑ። (ቁርኣን 4፡136)
>
> በአላህም ወደኛም በተወረደው (ቁርኣን) ወደ ኢብራሂምም፣ ወደ ኢስሐቅም፣ ወደ ኢስማዒልም፣ ወደ ያዕቆብም፣ ወደ ነገዶችም በተወረደው፣ ለሙሳም፣ ለዒሳም በተሰጡትም፣ በዚያም ውስጥ በተወረደው አመንን በላቸው። ለነቢያቶች ከጌታቸው የተሰጡ ናቸው። (ቁርኣን 2፡136)

ሙሐመድ መጽሐፍ ቅዱስን ለማስረጃነት ማየት አለበት

> በአንተም ላይ ባወረድነው በመጠራጠር ውስጥ ብትኾን ከአንተ በፊት መጽሐፉን የሚያነቡትን ጠይቅ። (ቁርኣን 10 ፡ 94)

ክርስቲያኖች ወንጌሉን መታዘዝ አለባቸው

> በፈለጎቻቸውም (በነቢያቶቹ ፈለግ) ላይ ኢንጂልን በውስጡ ቀጥታና ብርሃን ያለበት በስተፊቱ ያለችውን ተውራትንም የሚያረጋግጥ ለጥንቁቆችም መሪና ገሳጭ ሲኾን ሰጠነው። የኢንጅልም ባለቤቶች በውስጡ አላህ ባወረደው ሕግ ይፍረዱ። አላህም ባወረደው ሁሉ ውስጠ ዐዋቂ ነው። (ቁርኣን 5፡46-47)

ከመጽሐፍ ቅዱስ ማስረጃ ማቅረብ አለባቸው "ገነትንም አይሁድን ወይም ክርስቲያኖችን የኾነ ሰው እንጂ ሌላ አይገባትም" አሉ። ይህ (ዕውነት ነው)። "እንግዲያውስ ከእውነተኞች እንደኾንክ (አስረጁን) አምጣው" በላቸው። (ቁርኣን 2፡111)

## ትግበራና ማጠቃለያ

1. ሙስሊም ጓደኞችሁን ስለ ክርስትና የሰማውን ጠይቃችሁ እርማት ሳትሰጡት አዳምጡት። ማን እንደሆኑና እምነታቸውን እወቁ።

2. ካዳመጣችሁ በኋላ ስለ ክርስትና አንድ ነገር ልታሳዩዋቸው ትችላላችሁ። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የትኞቹ መጻሕፍት እንደሚገኙ ጠይቁ። ከመጽሐፍት ማውጫው ሰንጠረዥ የነቢያትን መጽሐፍት አሳይታችሁ ይህንን የአንድ ሰው ብቻ ሥራ ከሆነው ከቁርአን ጋር አነጻጽሩ። ነቢያትን ሁሉ የሚያምኑት ሙስሊሞችን ሳይሆኑ ክርስቲያኖች እንዴት እንደሆኑ አስረዱ። 'መጽሐፍ ቅዱስ ምንድን ነው?' የሚለውን በራሪ ጽሑፍ ቅጂ ከድረ-ገጹ አውርዳችሁ ልትሰጧቸው ትችላላችሁ።

3. ከእናንተ ጋር ወንጌልን እንዲያነቡ ጋብዟቸው።

4. እንደ እግዚአብሔር ልጅ ወይም ስርየት ያሉ ሐሳቦችን ማስረዳት ካስፈለጋችሁ የነቢያት ሁሉ መልእክት መሆኑን በማሳየት አስረዷቸው።

5. ቁርኣንን እንድታነቡ ከተጋበዛችሁ ይህን እንዴት ማድረግ እንዳለባችሁ በጥንቃቄ አስቡበት። ይህን ለማድረግ በራስ የመተማመን ስሜት ከተሰማችሁ ቁርኣን ሰዎችን ወደ መጽሐፍ ቅዱስ እንዴት እንደሚያመለክት ያሳዩ።

## የሚደጋገሙ ጥያቄዎች

1. ሙስሊም: - ክርስትናን የፈለሰፈው ጳውሎስ ነበር።

ክርስቲያን:- መጽሐፍ ቅዱስ ምን እንደሆነ አልገባህም። ጳውሎስ የመጽሐፍ ቅዱስ 7% ብቻ ነው። ክርስቲያኖች ሁሉንም ነቢያት ያነባሉ; ስለ እግዚአብሔር የሚያምኑትm ሁሉንም ነቢያት በማንበብ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ እንደ ቁርኣን አይደለም።

2. ሙስሊም:- የነብያትን ስም ባነሳሁ ቁጥር "ሰላም በእርሱ ላይ ይሁን" በማለት አከብራለሁ።

እኔ የነቢያትን መጻሕፍት በማንበብ አከብራቸዋለሁ። መጽሐፍ ቅዱስ የብዙ ነቢያት መጻሕፍትን ይዟል። ነብይን የማክበር ትክክለኛው መንገድ እነርሱን ማንበብ ነው። ነቢያትን በስም ታከብራለህ በተግባር ግን አታከብርም።

3. ሙስሊም:- እስልምና የነቢያት ሁሉ ሃይማኖት ነው።

ክርስቲያን :- በፍጹም፤ እስልምና የሙሐመድ ሃይማኖትና አንዱ ግለሰብ ሙሐመድ ስለ ነቢያት የተናገረው ነገር ነው። የነቢያት ሁሉ ሃይማኖት ቢሆን ኖሮ ታነባቸው ነበር ።

# ምዕራፍ 4

## ኢየሱስ አምላክ ነውን?

በምዕራፍ 2 ላይ እንደተመለከትነው ሙስሊሞች የኢየሱስን አምላክነት እንዳይቀበሉ ቁርኣን ያዛቸዋል። የዚህም ውጤቱ ክርስቲያኖች ለሙስሊሞች ሲመሰክሩ ወይንም መጽሐፍ ቅዱስን አብረው ሲያነቡ የኢየሱስን አምላክነት እንዲያብራሩ ማስገደዱ ነው። በዚህ ምዕራፍ ይህንን ርዕሰ ጉዳይ ከየት ጀምረን የት መፈፀም እንዳለብን አብረን እንመለከታለን።


### ምስጢረ ሥጋዌ

ኢየሱስ ማነው? ይህ ጥያቄ ብዙ ጊዜ ሙስሊሞችና ክርስቲያኖችን የሚያወያይና የማይስማሙበት ነው። በክርስቲያኖች እምነት መሠረት ኢየሱስ ፍጹም አምላክ ፍጹም ሰው ነው። ይህም ተሠግዎ በመባል ይታወቃል። ተሠግዎ የሚለው የግዕዝ ቃል ሲሆን ሥጋ መሆን የሚል ትርጓሜ አለው። ይህም እግዚአብሔር በአምሳለ ሰው ወደ እኛ መምጣቱን ያመለክታል። በተሠግዎ አስተምሕሮ መሠረት ኢየሱስ ያልተፈጠረ መለኮት የሆነ ባሕርይና የተፈጠረ ሰው የሆነ ባሕርይ አለው። በማንነቱ አንድ ሲሆን ሁለት ባሕርያት አሉት። ለሙስሊሞች ኢየሱስ ታላቅ ሰው ነው፣ ነቢይና ሰው ብቻ ነው። ስለዚህ ስለ ኢየሱስ ያለን መረዳት የተለያየና የማይታረቅ ነው።

ብዙ ክርስቲያኖች ተሠግዎ ለመረዳት ቀላል ነው፤ ለመጠራጠር ምክንያት የለንም። እግዚአብሔር ሁሉን ቻይ ነው፤ ይወደናል፤ ሊያድነን መጥቷል። ስለዚህ ተሠግዎ ቀላል ነው። ነገር ግን ለብዙ ሙስሊሞች ይህ የሚዋጥ አይደለም። እስልምና ተሠግዎን እንዲቃወሙ ስለሚያዛቸው ለማመን ምክንያት የላቸውም። ስለዚህ ክርስቲያን ለሙስሊም እንዲያምን ምክንያትን መስጠት አለበት ማለት ነው። ክርስቲያን ተሠግዎች የሚቻል መሆኑን፣ በፈጣሪ ከማመን ጋር የሚስማማ መሆኑንና እውነት መሆኑን መግለጥ መቻል አለበት። ይህ ጊዜን፣ ጥረትንና ልምምድን የሚጠይቅ ነገር ነው። ከዚህ ቀደም ይህንን ርዕሰ ጉዳይ ካላጠናችሁት ማጥናት ይኖርባችኋል። ትልቅ ርዕሰ ጉዳይ ነው። ከሁሉ በላይ ደግሞ ስለ ፈጣሪያችን ማጥናት ስለሆነ ጊዜና ጉልበታችንን መሠዋት አስፈላጊ ነው።

ክርስቲያኖች ስለ ተሠግዎ ለመማር ጊዜ እንደሚወስድባቸው ሁሉ ሙስሊሞችም ለመረዳት ጊዜ ያስፈልጋቸዋል። ይህንን ከሙስሊም ወዳጃችሁ ጋር መወያየት ያስፈልጋችኋል። የአንድ አረፍተነገር መልስ የሚጠብቁ ከሆነ ለርዕሱ ተገቢውን ትኩረት አልሰጡትም ወይንም የርዕሱን ባሕርይ አልተገነዘቡም ማለት ነው። ተሠግዎ ሉኣላዊና ዘላለማዊ የሆነው አምላክ ከፍጥረቱ ጋር የፈጠረውን ግንኙነት የሚያስረዳ ነው። ይህ በጣም ወሳኝና ውብ ርዕሰ ጉዳይ ነው፤ ስለዚህ ከየት እንጀምር?


ወጣት ሳለሁ ስለ ኢየሱስ አምላክነት ጥያቄ ሲቀርብልኝ የኢየሱስን አምላክነት የሚያሳዩ የአዲስ ኪዳን ጥቅሶችን እጠቅስ ነበር። እነዚህን ጥቅሶች አሳማኝ ሆነው ባገኛቸውም ሙስሊም ወዳጆቼ ግን አይቀበሏቸውም ነበር። የምጠቀምበት ምሳሌም ነበረኝ፤ ቅዱሳት መጻሕፍት። ቅዱሳት መጻሕፍት መለኮታዊ ቃልና ከወረቀትና ከቀለም የተሠራ የዚህ ዓለም ተፈጥሮ እንዳላቸው ሁሉ ኢየሱስም አምላክም ሰውም ነው እል ነበር። ይህ ጥሩ ምሳሌ ቢሆንም ሙስሊሞች ግን ሊረዱት የማይችሉት ምሳሌ ነው። እነዚህን ነገሮች ማድረግ የለባችሁም እያልኩ ሳይሆን እንደዚህ ያለውን ታላቅ ርዕስ ለማስረዳት ከጥቂት ጥቅሶችና ከምሳሌ ያለፈ ነገር ያስፈልገናል እያልኩ ነው።




ምስል 1

በአዲስ ኪዳን የመጀመር ችግሩ ብዙ ቅድመ ግንዛቤዎችን መጠየቁ ነው። ክርስቲያኖችና ሙስሊሞች ስለ ፈጣሪ፣ ስለ ፍጥረትና ስለ ሰው ስምምነት እንዳላቸውና በኢየሱስ ላይ ብቻ ልዩነት እንዳላቸው በመቁጠር ውይይት እንጀምራለን። (ምስል 1)

ነገር ግን ክርስቲያኖችና ሙስሊሞች ስለ ፈጣሪ፣ ስለ ፍጥረትና ስለ ሰው የተለያዩ መረዳቶች አሏቸው፤ ለዚህ ነው ስለ ኢየሱስ የተለያዩ መረዳቶች የኖሯቸው። ከነዚህ መረዳቶች የተነሳ ተሠግዎ ለክርስቲያኖች ትክክለኛ ሲሆን ለሙስሊሞች ደግሞ ስህተትና ትርጉም አልባ ነው። (መስል 2)




ምስል 2

ይህ ማለት ክርስቲያኖችና ሙስሊሞች አንዳቸው ሌላቸውን ተረድተው ስለ ኢየሱስ ባላቸው ውይይት የተሻለ ዕድገት ማሳየት ከፈለጉ ስለ ፈጣሪ፣ ስለ ፍጥረትና ስለ ሰው ባለን መረዳት

ዙርያ መወያየት ያስፈልገናል። ከዚህ ነው መጀመር ያለብን። ሉኣላዊ የሆነው አምላክ ከፍጥረት ጋር ስላለው ግንኙነትና ሰው መሆን ማለት ምን ማለት እንደሆነ ከተወያየን በኋላ ነው ስለ ኢየሱስ መወያየት የምንችለው። ፈጣሪ ከፍጥረቱ ጋር ስላለው ግንኙነትና ሰው መሆን ማለት ምን ማለት እንደሆነ ካልተወያየን በስተቀር ኢየሱስ አምላክም ሰውም በመሆኑ ላይ ላንግባባ እንችላለን። ስለ ፈጣሪ፣ ስለ ፍጥረትና ስለ ሰው ባለን መረዳት ዙርያ በተወያየን መጠን በምን ጉዳዮች ላይ እንደምንስማማና ያሉንን ልዩነቶች መረዳት እንጀምራለን። በዚህ ሒደት ለተሠግዎ መሠረት እንጥላለን። ልንወያይባቸው የሚገቡን ነጥቦች የሚከተሉት ናቸው:-

- ፈጣሪና ፍጥረት
- ፈጣሪ ለፍጥረቱ ያለው ስፍራ
- ፈጣሪ ከሕዝቡ ጋር ለመኖር ስለመምጣቱ
- የፈጣሪ ምስል

እነዚህን መሠረቶች ከግንዛቤ ካስገባን በኋላ ቅዱሳት መጻሕፍት ስለ ኢየሱስ የሚሰጡትን ምስክርነቶች እንመለከታለን።

## ፈጣሪና ፍጥረት

ሉኣላዊ የሆነው አምላክ ከፍጥረቱ ጋር ሕብረት የሚያደርገው እንዴት ነው? ለብዙ ክርስቲያኖችና ሙስሊሞች ይህ አዲስ ርዕስ ሊሆን ይችላል ነገር ግን መሠረታዊ ጉዳይ ስለሆነ ልንወያይበት ይገባል። ተሠግዎ ማለት እግዚአብሔር ከፍጥረቱ ጋር የሚያደርገው ሕብረት ነው። ስለዚህ እግዚአብሔርን የበለጠ ማወቅ እንችል ዘንድና የተሳሳቱ ቅድመ ግንዛቤዎቻችንን ለማስተካከል ክርስቲያኖችም ሆኑ ሙስሊሞች ይህንን ርዕሰ ጉዳይ ማጥናት ይጠበቅባቸዋል። በዚህ ምዕራፍ ጠጠር ያለው ክፍል ይህ በመሆኑ ተስፋ አትቁረጡ።

ክርስቲያኖች ኢየሱስ አምላክ ነው ሲሉ ፈጣሪ ከፍጥረቱ ጋር ሕብረት ፈጥሯል እያሉ ነው። ፈጣሪ ከፍጥረቱ ጋር እንዴት ነው ሕብረት የፈጠረው ወይንም ሕብረት ፈጥሯል ወይ የሚሉትን ጥያቄዎች ሁሉም ሃይማኖታትና ፍልስፍናዎች ሊመልሷቸው ይገባል፤ የሚሰጡትም ምላሽ የተለያየ ነው። አንዳንዶች ፈጣሪ ሉኣላዊ፣ ከፍጥረት የተነጠለ፣ የማይለወጥና ፍፁማዊ የሆነ አንድነት



ምስል 1



ምስል 2

ስላለው ከሚለዋወጠውና ብዝሐነት ካለው ዓለም ጋር ሊቆራኝ አይችልም። በዚህ ሁኔታ ፈጣሪ ራሱን ከፍጥረቱ ጋር ሕብረት ለማድረግ መካከለኛ ያስፈልገዋል (ምስል 1)። ጥንታውያን የግሪክ ፈላስፎች በዚህ ምድብ ውስጥ ናቸው።[4]

ሌሎች ሃይማኖታትና ፍልስፍናዎች ደግሞ በተቃራኒው ፈጣሪ ፍጥረት ነው፤ ሁሉም አንድ ነው ይላሉ። ይህ መድብለ አማልክታዊነት ነው። እነዚህ ሁለት የተለያዩ የሥነ ፍጥረት ትራኬዎች ናቸው። ሌሎች የሥነ ፍጥረት ትራኬዎች ቢኖሩም ለጊዜው ሁለቱን ብቻ እንመለከታለን።

ይህንን ርዕሰ ጉዳይ በሚገባ ማጤን ያስፈልገናል ምክንያቱም እዚህ ጋ የምንወስደው ቅድመ ግንዛቤ ስ ተሠግዎ ባለን ምልከታ ላይ ተፅዕኖ አለውና። ፈጣሪ ሉኣላዊና የማይለወጥ በመሆኑ ምክንያት ከሚለዋወጠውና ብዝሐ ከሆነው ፍጥረቱ ጋር ምንም ዓይነት ሕብረት ሊኖረው እንደማይችል የምናምን ከሆነ ተሠግዎ የማይቻል እንደሆነ እናስባለን። ፈጣሪ ፍጥረት መሆኑን ካመንን ተሠግዎ የሚቻል ነገር ግን ልዩ ያልሆነ ክስተት ይሆናል ምክንያቱም ሁሉም ነገር ተሠግዎ ነውና። ስለዚህ ሙስሊሞችና ክርስቲያኖች የሚያምኑት ምንድነው?

ክርስቲያኖችም ሆኑ ሙስሊሞች በፈጣሪና በፍጥረት ያምናሉ። ፈጣሪ ሉኣላዊ፣ ሃያል፣ ፍጥረትን የፈጠረና ከፍጥረት የተለየ መሆኑን እንዲሁም ያልተፈጠረና የማይለዋወጥ መሆኑን ያምናሉ። ፍጥረት በባሕርዩ ከፈጣሪ የተለየ መሆኑን በጊዜ የተገደበና ለመለወጥ የተዳረገ ጥገኛ መሆኑን እናምናለን። ለሁለታችንም የሚቀርብ ጥያቄ ሉኣላዊና ያልተፈጠረው ፈጣሪ እንዴት ከፍጥረት ጋር ሕብረት ይኖረዋል? የሚል ነው። እንደ ምስል 1 ና 2 ነው ወይንስ የተለየ? ስለ ተሠግዎ ስንነጋገር መግባባት እንችል ዘንድ በዚህ ላይ ግልፅነት ያሻናል። ከዚህ ሐሳብ በመነሳት ክርስትና ስለ ተሠግዎ የሚሰጠውን ማብራርያና የጠለመደውን የሙስሊሞች ምላሽ አቀርባለሁ።

ፈጣሪ ሰው ሆኖ እንደመጣ ክርስቲያኖች ሲናገሩ ሙስሊሞች ፈጣሪ እንደተለወጠ የተናገሩ ይመስላቸዋ። ፈጣሪ ከሉኣላዊ፣ ያልተፈጠረ፣ የማይለወጥና ኢ-ውሱን ከሆነው ባሕርዩ ወደ ፍጡር፣ ውሱን፣ ተለዋዋጭና ጊዜያዊነት እንደተለወጠ የሚያምኑ ይመስላቸዋል። ተከታዩ ጥቅስ ይህንን መረዳት ያንጸባርቃል።

> አት-ተፍታዛኒ እንደተናገረው ክርስቲያኖች እንዲህ ይላሉ፡- መለኮት ከባሕርዩ ተለውጦ በኢየሱስ አካል ራሱን ገለጠ። ስለዚህ መለወጥን በመፍቀድ አንዱን

[4] Search: The Chain/Ladder of Being and Classical Theism

አንዱን የመለኮት ባሕርይ ያጎድላሉ። ስለዚህ መለኮት በነርሱ ዕይታ ተለዋጭ ነው።[5]

ፈጣሪ ደግሞ ስለማይለወጥ ተሠግዎ በሙስሊሞች ዕይታ ኢ-አመክንዮአዊ፣ የማይቻልና የማይለዋወጠውን የመለኮት ዘላለማዊ ባሕርይ የሚያመቻምች ነው።

ሆኖም ሙስሊም ሊቃውን የክርስቲያኖችን እምነት በተሳሳተ መንገድ ተረድተውታል። እኛ ፈጣሪ ከአንዱ ባሕርይ ወደ ሌላው ተለውጧል የሚል እምነት የለንም፤ ነገር ግን ኢየሱስ ሁለት ባሕርያት አሉት፤ መለኮትና ሰው። ፍፁም አምላክ ፍፁም ሰው ነው። መለኮታዊ ባሕርዩ አልተለወጠም ነገር ግን እግዚአብሔር ከሰብአዊ ባሕርይ ጋር ተጣመረ። በኢየሱስ ውስጥ የመለኮታዊና ሰብአዊ ባሕርያት ጥምረት ይገኛል።

በመሆኑም በሙስሊሞችና ክርስቲያኖች መካከል ያለው ጥያቄ ፈጣሪ ይለወጣል ወይ? የሚል ሳይሆን ክርስቲያኖች በሚሉት መንገድ ፈጣሪ ከፍጥረት ጋር ሕብረት ማድረግ ይችላል ወይ? የሚል ነው። ሉአላዊ፣ ያልተፈጠረ፣ የማይለወጥና ኢ-ውሱን የሆነው ባሕርይ ያለው አምላክ ፍጡር፣ ውሱንና በጊዜ ከተገደበው ፍጥረት ጋር ሕብረት ሊኖረው ይችላልን? መለኮታዊ ባሕርይ ከፍጡር ባሕርይ ጋር በኢየሱስ ማንነት ውስጥ መጣመሩን ክርስቲያኖች ማመናቸው ምክንያታዊና የሚቻል ነውን? መልሱ አዎን የሚል ነው፤ ምክንያቱም ፈጣሪ በየትኛውም መንገድ ከፍጡራን ጋር ሕብረት ሲያደርግ ጥምረት ይፈጠራልና። ተከታዮቹን ምሳሌዎች ልብ በሉ፡-

የመፍጠር ተግባር። እግዚአብሔር ከፍጥረቱ ጋር ሕብረት ያደረገበት የመጀመርያው አጋጣሚ ሲፈጥር ነው። ልዑልና ያልተፈጠረው አምላክ  በቃሉ ብቻ ፍጥረትን ካለመኖር ወደ መኖር እንዳመጣ እንመለከታለን። በዚህም ሁለት የተለያዩ ባሕርያት የሆነ ዓይነት ግንኙነት ሲኖራቸው እንመለከታለን። ግንኙነት ከሌለ ፈጣሪ ለፍጥረት መፈጠር ምክንያት አይደለም ማለት ይሆናል። ይህ ግንኙነት የፈጣሪን ባሕርይ መለወጥ ወይንም ማመቻመች ይችላልን? አይችልም። ይህ ግንኙነትን ፍጥረትን መለኮት ያደርጋልን? አያደርግም። ስለዚህ በፍጥረት ተግባር ሁለት ባሕርያት ግንኙነት ሲኖራቸውና አንዳቸውም ባሕርያቸው አለመለወጡን እንመለከታለን።

ፍጥረትን ማኖር። ፈጣሪ ፍጥረትን ከመፍጠር ባለፈ ህልውናውንም ያስቀጥላል። ህያዋን ሆነን የምንኖረው ፈጣሪያችን ሕያዋን ሆነን አንድንኖር ስላደረገን ነው። ከሞትም በማስነሳት ዘላለማውያን ያደርገናል።

መላዔ ኩሉ - በሁሉም ቦታ መገኘት። እግዚአብሔር ሁሉንም ነገሮች ፈጥሮአል፤ ሁሉንም ነገር ያኖራል፤ እናም በመላው ፍጥረት ውስጥ ይገኛል።

---


[5] Muhammad Salih Farfur, *The Beneficial Message & The Definitive Proof in the Study of Theology*, (Trans: Wesam Charkawi) 2010, p. 95.

ከመንፈስህ ወዴት እሄዳለሁ? ከፊትህስ ወዴት እሸሻለሁ? ወደ ሰማይ ብወጣ አንተ እዚያ አለህ! ወደ ሲኦልም ብወርድ አንተ በዚያ ትገኛለህ! (መዝሙር 139 7-8)

እግዚአብሔር በሁሉም ቦታ ይገኛል። ይህ እንደገና መለኮትና ፍጥረት በተወሰነ መልኩ መገናኘቱን ያመለክታል። ግንኙነት ከሌለ እግዚአብሔር የለም ማለት ይሆናል። ይህ ግንኙነት የእግዚአብሔርን ባሕርይ የሚለውጥ ወይንም የሚያመቻምች ነውን? በፍፁም። ይህ ግንኙነትን ፍጥረትን መለኮት ያደርጋልን? አያደርግም። ስለዚህ ፈጣሪ በሁሉም ቦታ መገኘቱ ሁለት ባሕርያት አንዳቸውም ሳይለወጡ መገናኘት እንደሚችሉ አመላካች ነው።

መገለጥና ቅዱሳት መጻሕፍት። እግዚአብሔር በቃሉ በኩል ለፍጥረት ራሱን ይገልጣል። ክርስቲያኖችና ሙስሊሞች ስለ ፈጣሪ ቃል ያላቸው መረዳት ይህ ነው። ቅዱሳት መጻሕፍት በፍጥረት ውስጥ የተገለጡ የመለኮት ቃል ናቸው። ይህም መለኮታዊና ፍጥረታዊ ባሕርያት በተወሰነ መንገድ መገናኘታቸውን አመላካች ነው። ግንኙነት ከሌላ ፈጣሪ ራሱን ለኛ ስለማይገልጥ ፈጣሪ በሉአላዊነቱ ተነጥሎ የሚኖር ነው። ይህ ግንኙነት ሁለቱንም ባሕርያት የሚያመቻምች ነውን? በፍፁም። ይህ ግንኙነትን ፍጥረትን መለኮት ያደርጋልን? አያደርግም። ስለዚህ ፈጣሪ በቃሉ ራሱን በመግለጡ ሒደት ውስጥ ሁለት ባሕርያት ተገናኝተው እንመለከታለን።

የነዚህ ምሳሌዎች ነጥብ ፈጣሪ ከፍጥረተ ዓለሙ ጋር በሚኖረው መስተጋብር መለኮታዊና ፍጥረታዊ ባሕርያት ሕብረት ፈጥረዋል። የሆነ ዓይነት ግንኙነት ያለ ሲሆን ሁለቱም ባሕርያት አልተለወጡም። ይህ የነቢያት ሁሉ መልእክት ነው። ይህ ክርስቲያኖችና ሙስሊሞች ሊስማሙበት የተገባ ጉዳይ ነው።



ምስል 3

እነዚህ ምሳሌዎች እንደሚያስረዱት ክርስቲያኖችና ሙስሊሞች ፈጣሪ ከፍጥረተ ዓለሙ ጋር ያለውን ግንኙነት በተመለከተ ከምስል 1 ጋር አይስማሙም። ፈጣሪ የፍጥረት አካል ነው ከሚለውም የምስል 2 መረዳት ጋር አይስማሙም። እምነታችን የሚያስተምረው ፈጣሪ ሉአላዊ ቢሆንም በተለያዩ መንገዶች በመንፈሱና በቃሉ አማካይነት ከፍጥረተ ዓለሙ ጋር መስተጋብር እንዳለው ሲሆን ይህ ሁኔታ ባሕርዩን አያመቻምችም።[6] ነገር ግን ብዙ ሙስሊሞች ምስል 1ን ስለሚያስቡ ተሠግዎን ይቃወማሉ።

[6] ዘፍ. 1, 2:7, መዝ. 33:6, 139:7, ዮሐ. 1, ዕብ. 1:3, ወዘተ.

ይህ ማለት ፈጣሪ በቃሉና በመንፈሱ አማካይነት የራሱ ወኪል በመሆን በፍጥረት ውስጥ ሊኖር ይችላል። በሉአላዊነቱ ውስጥ ተቆልፎበት የሚኖርና በመላእክትና በሌሎች ወኪሎች ላይ የተደገፈ አይደለም።

ስለዚህ ይህንን ከሙስሊሞች ጋር ልትወያዩ የምትችሉት እንዴት ነው?

ፈጣሪ ከፍጥረቱ ጋር አይገናኝም የሚለውን ቅድመ ግንዛቤያቸውን ልትወያዩበት ይገባል። ተሠግዎን እንዳይቀበሉ የሚያደርጋቸው ይህ ቅድመ ግንዛቤያቸው ነው። ስለዚህ ይህንን ጉዳይ ማንሳት ያስፈልጋችኋል። ምናልባትም ከዚህ ቀደም ይህንን ጉዳይ አስበውበት ላይሆን ስለሚችል ይህንን ጉዳይ መጠቆም ግዴታ ነው። ይህ ርዕሰ ጉዳይ በመጀመርያ ዕይታ ቴክኒካዊ ቢሆንም አጨቃጫቂ ግን አይደለም። ሙስሊሞች ይህንን የማይቀበሉበት ምክንያት የለም። እንዲያውም በጣም አጓጊ ርዕስ ሆኖ ሊያገኙት ይችላሉ። ይህንን የማድረጊያ የተወሰኑ መንገዶች አሉ።

መጀመርያ እግዚአብሔር ከፍጥረት ጋር መገናኘት እንደሚችል በግልፅና በራስ መተማመን ተናገሩ። እግዚአብሔር ፈጣሪያችንና አኗሪያችን ነው። ሕይወታችንና መኖራችን በእርሱ ላይ የተደገፈ ነው። እርሱ በሁሉም ቦታ የሚገኝና ራሱን ለኛ ለመግለጥ ዝግጁ የሆነ አምላክ ነው። እግዚአብሔር ይህንን ሁሉ የሚፈፅመው በቃሉና በመንፈሱ አማካይነት ነው። ይህ ማሰላሰልን የሚፈልግ ውብ እውነት ነው። ደረቅ አስተምሕሮ ሳይሆን ተጨባጭ እውነት ነው። ነቢያት ሁሉ ያስተላለፉልን መልእክት ነው።

ሁለተኛ ይህንን ርዕሰ ጉዳይ በማንሳት ፈጣሪ ሁሌም ከፍጥረቱ ጋር እንዴት እንደሚገናኝ ከሙስሊም ወዳጃችሁ ጋር ተነጋገሩ። ፈጣሪ እጅግ የከበረ በመሆኑ ምክንያት ከፍጥረት ጋር ሊገናኝ እንደማይችል ከተናገሩ ይህንን ቅድመ ግንዛቤ አስተካክሉ። እንዲህ ማለት ትችላላችሁ፡- “ፈጣሪ ከፍጥረት ጋር እንደማይገናኝ ቅድመ ግንዛቤ የያዝክ ይመስላል ነገር ግን ፈጣሪ ሁሌም ከፍጥረቱ ጋር እንደተገናኘ ነው።” ፈጣሪ ሲፈጥር፣ ሲያኖር፣ በሁሉም ቦታ ሲገኝ ወይንም ራሱን ሲገልጥ የሆነ አይነት ግንኙነት እንደሚከሰት ንገሯቸው። ፈጣሪ ከፍጥረት ጋር ፈፅሞ እንደማይገናኝ ከተናገሩ (ምስል 1) ፈጣሪነቱን እንደ ካዱ አስረዷቸው።[7] አሁን እግዚአብሔር ራሱ ከሰው አካል ጋር እንደተገናኘና ወደ እኛ እንደመጣ ንገሯቸው፤

---

[7] በቤተክርስቲያን ታሪክ መጀመሪያ ውስጥ ስለ ኢየሱስ ተፈጥሮ እና ስለ ትስጉቱ ብዙ ውይይቶች ነበሩ። እነዚህ የጥንት ክርስቲያኖች ስለ ኢየሱስ የሚከራከሩ ቢመስልም ነገር ግን አብዛኛዎቹ የሚከራከሩዋቸው ስለ ፍጥረት እና ሉኣላዊው ፈጣሪ ከፍጥረቱ ጋር እንዴት መስተጋብር ሊኖረው እንደሚችል ነበር። እንደ አርዮስ እና ዶክስቶሳውያን ያሉ ሰዎች እግዚአብሔርን እጅግ የላቀ ከመሆኑ የተነሳ ከፍጥረት ጋር ፈጽሞ ሊገናኝ አይችልም የሚል የግሪክ ፍልስፍና አመለካከት ነበራቸው። ሆኖም ግን እንደተመለከትነው መጽሐፍ ቅዱሳዊው አመለካከት ከፍጥረት ጋር ሊገናኝ እንደሚችል እና ከእሱ ጋር እንደሚገናኝ የሚገልፅ ነው። ስለ ፍጥረትና ስለ ፈጣሪ ያለው ይህ የተለያየ አመለካከት ነበር ስለ ኢየሱስም የአመለካከት ልዩነት እንዲኖር ምክያት የሆነው። ለዚህ ነው ክርስትያኖችና ሙስሊሞች ፈጣሪ እንደ ሰው ወደ እኛ መምጣት መቻል አለመቻሉን ከመወያየታቸው በፊት አስቀድመው ስለ ፈጣሪና ስለ ፍጥረት መነጋገር የሚያስፈልጋቸው።

ይህ ትሥጉት ነቢያት ካስተማሩት ትምሕርት ጋር አብሮ እንደሚሄድና ፈጣሪ ከፍጥረቱ ጋር ስለሚኖረው ግንኙነት የተናገሩትን ውብ በሆነ መንገድ የሚገልጥ መሆኑን ነገሯቸው።

በአራተኛ ደረጃ ቁርኣንን ለማመልከት በራስ መተማመን ካላችሁ ቁርኣን 75፡22-23 ጥቀሱ። ይህ ጥቅስ ሙስሊም አማኞች በፍርድ ቀን ፈጣሪን እንደሚያዩና ይህም ታላቅ የደስታ ምክንያት እንደሚሆን ይናገራል። ያም ማለት በጥቅሱ መሠረት ያልተፈጠረው ድንቅ የሆነው ፈጣሪ በተፈጥሮ ውስጥ በተወሰነ መልክ ይኖራል ማለት ነው። ይህም ማለት በእግዚአብሔርና በፍጥረት መካከል አንድ ዓይነት ግንኙነት መኖር አለበት። ስለሆነም ሙስሊሞች በየትስጉት ሥጋ መልበስ እንደማይቻል ሊናገሩ አይችሉም።

**ፈጣሪ በፍጥረት ምህዳር**

እግዚአብሔር ከእሱ ፍጥረት ጋር ሊገናኝ እንደሚችልና ከእሱ ጋር በተለያዩ መንገዶች እንደተገናኘ ተመልክተናል። ይህም ለትስጉትነት አንድ መሠረት ሆኖናል። በእግዚአብሔር እና በፍጥረት መካከል ስላለው ግንኙነት ልናስብበት የሚገባ ሌላ ገፅታ አለ። እርሱም እግዚአብሔር በፍጥረት ውስጥ ያለው ምህዳር ሲሆን ለትስጉት ሌላኛው መሠረት ነው። በርካታ ሙስሊሞች እና የይሖዋ ምሥክሮች ኢየሱስ እግዚአብሔር ሊሆን አይችልም ምክንያቱም እግዚአብሔር ገደብ የሌለው፣ ሁሉን ቻይ፣ ሁሉን አዋቂ እና ገደብ የለሽ ስለሆነ በሰብዓዊ ማንነት ብቻ ሊወሰን አይችልም ይሉኛል። አይበቃውም! ይህ ሙግት መጀመሪያ ላይ ምክንያታዊ ይመስላል። አንድ ያልተገደበ ነገር በአንድ ጊዜ ሊገደብ አይችልም ብሎ ማለቱም ምክንያታዊ ይመስላል። ሆኖም ይህ ሙግት ፈጣሪ ከኛ ጋር ስላለው ግንኙነት አንድ ወሳኝ ገፅታን የዘነጋ ነው። ፈጣሪ በፈጣሪነቱ በሚኖርበት ሁኔታና ከኛ ጋር ባለው ግንኙነት መካከል ልዩነት አለ። የማይገደበው አምላክ በተገደበው ፍጥረቱ ምህዳር ራሱን ይገልጣል።[8] እግዚአብሔር በራሱ አቻ የሌለውና ከእኛ የመረዳት በላይ መሆኑ እውነት ነው።

> "እነሆ፥ እግዚአብሔር ታላቅ ነው፥ እኛም አናውቀውም። የዘመኑም ቍጥር አይመረመርም።" (ኢዮብ 36፡26)
>
> "ጌታችን ታላቅ ነው፥ ኃይሉም ታላቅ ነው፥ ለጥበቡም ቍጥር የለውም።" (መዝ. 147፡5)
>
> "መቼም ቢሆን እግዚአብሔርን ያየው አንድ ስንኳ የለም፤ በአባቱ እቅፍ ያለ አንድ ልጁ እርሱ ተረከው።" (ዮሐ. 1፡18)

---

[8] John Calvin, *Institutes of the Christian Religion*, ed. John T. McNeill, trans. Ford Lewis Battles (Philadelphia: Westminster, 1960), 1.13.1; p. 120ff. ካልቪን የእግዚአብሔር በፍጥረት መኖር እግዚአብሔር እራሱን ለመግለጽ ከሚጠቀምበት ቋንቋ ጋር ያያይዛል። እኔ ግን እግዚአብሔር ከፍጥረት ጋር ግንኙነት ሲኖረው በፍጥረት ምህዳር ውስጥ እንደሚገባ ሙግት እያቀረብኩ ነው።

“እርሱ ብቻ የማይሞት ነው፤ ማንም ሊቀርበው በማይችል ብርሃን ይኖራል፤ አንድ ሰው እንኳ አላየውም ሊያይም አይቻለውም፤ ለእርሱ ክብርና የዘላለም ኃይል ይሁን፤ አሜን።” (1ጢሞ. 6፡16)

ቅዱሳት መጻሕፍት ብዙ ይናገራሉ። እግዚአብሔር በኛ ምሕዳር ራሱን እንደገለጠ ይናገራሉ። እግዚአብሔር የመኖሪያ ስፍራውን በመካከላችን ማድረጉን በብዙ መንገዶች እንመለከታለን። በመጀመሪያ እግዚአብሔር ራሱን ለእኛ ገልጦልናል፤ እናም ይህንን ሲያደርግ በማይቀረብ ብርሀን የሚኖረው አምላክ ለፍጥረታቱ በውሱን መንገድ ራሱን አሳይቷል። ለምሳሌ ያህል ያልተገደበው አምላክ በነቢያቱና በቅዱሳት መጻሕፍት በኩል ለኛ ሲናገር ውሱን በሆነ መንገድ ነው። አላቂ የሆኑ ቃላት በአላቂ ገፆች ላይ ተጽፈዋል ነገር ግን በነዚህ አላቂ ቃላት አማካይነት ያልተገደበውን አምላክ እናውቀዋለን። የተገደበው ያልተገደበውን ይገልጠዋል። በዚህ መንገድ ፈጣሪ ውሱን በሆነው በኛ ዓለም ራሱን ለኛ አሳወቀ። በርግጥ እግዚአብሔር ከፍጥረቱ ጋር በተገናኘ ቁጥር ውሱን በሆነ መንገድ ራሱን ይገልጣል።

ያልተገደበውን የእዚአብሔርን ኃይል እስኪ አስቡ። እውነት ነው፣ እግዚአብሔር በራሱ ኃይሉ ያልተገደበ ነው ነገር ግን ለኛ የሚገልጠው የተወሰነውን የእርሱን ኃይል ብቻ ነው። ይህንን በመፍጠር ሒደት ውስጥ እናስተውላለን። በፍጥረት ውስጥ እውነተኛው የእግዚአብሔር ኃይል ተገልጦ ብንመለከትም ነገር ግን ውሱን በሆነ መንገድ ነው። እግዚአብሔር የዚህን አፅናፈ ዓለም እጥፍ የሆነ ወይንም ግማሽ ያህል ሊፈጥር ይችላል ወይንም ከነጭራሹ ላይፈጥር ይችላል፤ ሆኖም ውሱን በሆነ መንገድ ቢሠራም በዚህ ሁሉ ሁኔታ በራሱ እኩል በሆነ መንገድ ሃያል ነው።

የእግዚአብሔርን ያልተገደበ ነፃነት እስኪ አስቡ። እግዚአብሔር ሉኣላዊና የፈቀደውን ማድረግ የሚችል ቢሆንም በኖኅ፣ አብረሃም፣ ዳዊት እና ኢየሱስ አማካይነት ቃልኪዳንን አድርጓል፤ ይህም ለተወሰነ ነገር በመታመን እንዲፈፅም ያደርገዋል።

ስናጠቃልል ፈጣሪ ሦስት ፅንፍ ካለው የጊዜና የቦታ ዓለም ሊሸከመው የማይችል ልውል ቢሆንም በዚህ በተፈጠረው ዓለም ውስጥ በመግባት ውሱን በሆነ መንገድ ራሱን ለኛ ይገልጣል።

እነዚህን ምሳሌዎች ስጠቅስ ለማለት የፈለኩት ነገር ቢኖር ያልተገደበው አምላክ ከፍጥረተ ዓለም ጋር መስተጋብር ባደረገ ቁጥር ራሱን በመወሰን በተገደበ መንገድ ከኛ ጋር ግንኙነት ያደርጋል የሚል ነው። ውሱን ቢሆንም ትክክለኛው የእርሱ ማንነት ነው። ፈጣሪ በቸርነቱ በፍጥረቱ ልክ ራሱን ገድቧል። ይህ በምንም መንገድ የእግዚአብሔርን ግርማ ሞገስ የሚቀንስ አይደለም፤ ያልተገደበው አምላክ ከኛ ጋር በምን መንገድ ግንኙነት እንደሚኖረው ብቻ ዕውቅና የሚሰጥ ነው።

ተሠግዎ ልበ ወለድ አይደለም፤ ነቢያት እግዚአብሔር በፍጥረቱ ምሕዳር ስለ መገኘቱ የተናገሩትን አዲስ፣ ውብና ምሉዕ በሆነ መንገድ የሚገልጥ ነው።

ፈጣሪ በኛ ምሕዳር ራሱን መግለጡ ኢየሱስ እንዴት አምላክ እንደሆነ ለመረዳት ወሳኝ ነው ምክንያቱም ያልተገደበው አምላክ በኢየሱስ ማንነት ራሱን በኛ ምሕዳር ገልጧልና።

> "እርሱ በእግዚአብሔር መልክ ሲኖር ሳለ ከእግዚአብሔር ጋር መተካከልን መቀማት እንደሚገባ ነገር አልቈጠረውም፥ ነገር ግን የባሪያን መልክ ይዞ በሰውም ምሳሌ ሆኖ ራሱን ባዶ አደረገ፥ በምስሉም እንደ ሰው ተገኝቶ ራሱን አዋረደ፥ ለሞትም ይኸውም የመስቀል ሞት እንኳ የታዘዘ ሆነ።" (ፊል. 2፥6-8)

ያልተገደበው አምላክ በውሱንና የተገደበ መንገድ ራሱን መግለጥ አይችልም የሚለውን ቅድመ ግንዛቤያቸውን ማረም ያስፈልጋችኋል። ይህ ቅድመ ግንዛቤያቸው ነው ተሠግዎን እንዳይቀበሉ የሚያግዳቸው። ስለዚህ ይህንን ጉዳይ በማንሳት በዚህ ቅድመ ግንዛቤ ላይ መወያየት ያስፈልጋችኋል። ስለዚህ ጉዳይ ምናልባትም ከዚህ ቀደም አስበው ላያውቁ ይችላሉ፤ እናም የእነርሱን ቅድመ ግንዛቤ በመረዳት ልትወያዩበት ይገባል። ይህ ርዕሰ ጉዳይ የተወሰነ ያህል ሙያዊ ቢሆንም አጨቃጫቂ ግን አይደለም። እግዚአብሔር በፍጥረት ምህዳር መኖር መቻሉን እንዲክዱ ስለማይማሩ ለመወያየት ትኩረታቸውን የሚስብ ሆኖ ሊያገኙት ይችላሉ።

ስለዚህ ምንድነው ማድረግ የምትችሉት?

መጀመርያ እናንተ ራሳችሁ እግዚአብሔር በፍጥረት ምህዳር መኖር ስለመቻሉ እርግጠኞች ሁኑ። አምላካችን ገደብ የሌለው ቢሆንም ነገር ግን ለሕዝቡ ሲል በፍጥረት ውስጥ ራሱን ይገልጣል። ይህ ልናስብበት የሚገባ ውብ ነገር ነው። ይህ የሆነ ዓይነት ደረቅ ሥነ መለኮት ሳይሆን እኛ ከአምላካችን ጋር ያለን ቀጥተኛ ግንኙነት ነው። የነቢያት ሁሉ መልእክት ነው። በዚህ መረዳት ዕደጉ።

ሁለተኛ የእግዚአብሔርን በፍጥረት ምህዳር መገለጥ ከሙስሊም ወዳጆቻችሁ ጋር ተወያዩበት። በዚህ ክፍል የተጠቀሱትን ምሳሌዎች ተጠቀሙ። ከዚያም የክርስቶስ በሥጋ መምጣት ገደብ የሌለው አምላክ ከፍጥረት ጋር ሕብረት ከማድረጉ ጋር እንደማይፃረር ንገሯቸው። ይህ ልምምድን ይፈልጋል። ይህንን ለማድረግ ልበ ሙሉ ካልሆናችሁ *ኢየሱስ አምላክ ነውን?* የሚለውን የኔን ቡክሌት ከሙስሊም ወዳጆቻችሁ ጋር አንብቡ።

ሦስተኛ ተሠግዎ ለምን የማይቻል እንደሆነ እንደሚያስቡ ጠይቋቸው። ፈጣሪ ገደብ ስለሌለው በተገደበ መንገድ አይገለፅም የሚሉ ከሆነ እንዲህ በሏቸው፡- "እግዚአብሔርን ባልተገደበ መንገድ ብቻ ልናየው እንደምንችል የምታስብ ይመስላል፤ ነገር ግን እውነቱ እንደርሱ አይደለም።" ከዚያም በዚህ ክፍል ውስጥ የተጠቀሱትን ምሳሌዎች ተጠቀሙ።

በመጨረሻም ተሠግዎ ያልተገደበው አምላክ ሁል ጊዜ ከፍጥረት ጋር ባለው መስተጋብር ከመገለፁ ጋር እንደማይጣረስ አስረዷቸው።

አራተኛ ቁርኣንን ለመጥቀስ ልበ ሙሉ ከሆናችሁ 75፡22-23 ጥቀሱ። ይህ ጥቅስ ሙስሊም አማኞች በፍርዱ ቀን አላህን እንደሚያዩትና ይህም ታላቅ ደስታ እንደሆነ ይናገራል።

ፊቶች በዚያ ቀን አብሪዎች ናቸው። ወደ ጌታቸው ተመልካቾች ናቸው። (ቁርኣን 75፡22-23)

ይህ ጥቅስ ያልተገደበው አምላክ በተወሰነ መንገድ በፍጥረቱ መካከል እንደሚገኝ ነው። ይህ ፈጣሪ በፍጥረቱ ምህዳር የሚገለፅበት አንዱ መንገድ ነው። ስለዚህ ሙስሊሞች ተሠግዎ የሚቻል እንዳልሆነ ሊናገሩ አይችሉም።

## የእግዚአብሔር ምስል

ባለፉት ሦስት ክፍሎች ስለ እግዚአብሔር ያለንን አስተምሕሮ ተመልክተናል። እግዚአብሔር ከፍጥረቱ ጋር ያለውን መስተጋብር፣ ራሱን በፍጥረት ምህዳር እንዴት እንደሚገልፅና ከሕዝቡ ጋር እንዴት እንደሚኖር ዐይተናል። እነዚህ ደግሞ ምስጢረ ሥጋዌን ለመረዳት እንደሚያግዙ ተመልክተናል። ይህ እግዚአብሔርን የበለጠ እንድታውቁትና ስለ ምስጢረ ሥላሴ ያላችሁን መረዳት እንዳዳበረ ተስፋ አደርጋለሁ። አሁን ደግሞ የኛን ትምሕርተ ሰብዕ ወይንም የኛን አንትሮፖሎጂ እንመለከታለን፤ ሰው መሆን ማለት ምን ማለት ነው?

ቶራህ፣ ነቢያት፣ መዝሙራትና ወንጌል እግዚአብሔር በአምሳሉ እንደፈጠረን ይናገራሉ፡-

> እግዚአብሔርም አለ፡- ሰውን በመልካችን እንደ ምሳሌአችን እንፍጠር፤ የባሕር ዓሦችንና የሰማይ ወፎችን፥ እንስሳትንና ምድርን ሁሉ፥ በምድር ላይ የሚንቀሳቀሱትንም ሁሉ ይግዙ። እግዚአብሔርም ሰውን በመልኩ ፈጠረ፤ በእግዚአብሔር መልክ ፈጠረው፤ ወንድና ሴት አድርጎ ፈጠራቸው። (ዘፍ. 1፡26-27)

ሰው መሆን ማለት ምን ማለት ነው? በእግዚአብሔር መልክና ምሳሌ መፈጠር ማለት ነው። የዚህ ብዙ ገፅታዎች አሉ። በመጀመርያ ሰዎች የእግዚአብሔርን አገዛዝ በምድር ላይ ይወክላሉ ማለት ነው (ቁ. 26)። ሰዎች የእግዚአብሔርን አገዛዝ እንዲወክሉ ነው የታሰቡት።

ሁለተኛ በእግዚአብሔር አምሳል መፈጠር ማለት የእግዚአብሔርን ባሕርይ እናሳያለን ማለት ነው።

> ለእሥራኤል ልጆች ማኅበር ሁሉ እንዲህ በላቸው፡- እኔ እግዚአብሔር አምላካችሁ ቅዱስ ነኝና እናንተ ቅዱሳን ሁኑ። (ዘሌ. 19፡2)
>
> እንግዲህ እንደ ተወደዱ ልጆች እግዚአብሔርን የምትከተሉ ሁኑ። (ኤፌ. 5፡1)

ዳሩ ግን፡- እኔ ቅዱስ ነኝና ቅዱሳን ሁኑ ተብሎ ስለ ተጻፈ የጠራችሁ ቅዱስ እንደ ሆነ እናንተ ደግሞ በኑሮአችሁ ሁሉ ቅዱሳን ሁኑ። (1ጴጥ. 1፡16)

ሰዎች የእግዚአብሔርን ባሕርይ ማሳየትና በዚያም ምክንያት የእግዚአብሔርን ክብር መግለጥ ይችላሉ። ሰውን ዝቅ አድርጋችሁ አትመልከቱ።

በመጨረሻም በአምሳለ እግዚአብሔር መፈጠር ማለት እንደ አምሳሎቹ በመሆናችንን ተስፋን በመቀበላችን በእርሱ ክብርና ሕይወት ውስጥ ውስጥ ተካፋዮች እንሆናለን ማለት ነው።

... በገነትም መካከል የሕይወትን ዛፍ፥ መልካምንና ክፉን የሚያስታውቀውንም ዛፍ አበቀለ ... (ዘፍ. 2፡9)

ስለዚህ ክፉዎች በፍርድ፥ ኃጢአተኞችም በጻድቃን ማኅበር አይቆሙም። እግዚአብሔር የጻድቃንን መንገድ ያውቃልና፥ የክፉዎች መንገድ ግን ትጠፋለች። (መዝ. 8፡5-6)

የሰው ልጆች የክብሩ ተካፋዮች ይሆኑ ዘንድ የእግዚአብሔር ዕቅድ ነው። ይህ ማለት እግዚአብሔር በአምሳሉ ሲፈጥረን በእርሱና በኛ መካከል ልዩ ግንኙነት እንዲኖር አድርጎ ነው ማለት ነው። ሰው የእግዚአብሔርን አገዛዝ ሊወክል ይችላል፣ የእግዚአብሔርን ባሕርይ ማንፀባረቅ ይችላል፣ የክብሩም ተካፋይ መሆን ይችላል። ኃጢአት እነዚህን ነገሮች ከማድረግ ያግደናል ነገር ግን ኃጢአት አልባ የሆነ ሰው ሙሉ በሙሉ ይገልጣቸዋል። እግዚአብሔርን ማሳየት ይችላል።

ይህ ተሠግዎን ለመረዳት ሌላኛው መሠረት ነው፤ እግዚአብሔር ሰው ሆኖ ወደኛ ሲመጣ ተያያዥነት በሌለው ድንገቴ መንገድ አይደለም። ነገር ግን እርሱን ወካይ፣ ባሕርዩን ገላጭና ክብሩን ተካፋይ የሆነውን አስቀድሞ የፈጠረውን ሰብዓዊነት ተላብሶ ነው የመጣው። እግዚአብሔር ሰብዓዊነትን ለተሠግዎ ተስማሚ አድርጎ ቀድሞውኑ ፈጥሮታል። ይህ ቁልፍ ነጥብ ነው፤ እግዚአብሔር ሰብዓዊነትን ለተሠግዎ ተስማሚ አድርጎ ፈጥሮታል።[9]

ሙሐመድ ይህንን የነቢያትን መልእክት አላስቀጠለም፤ ለዚህ ነው በቁርአንና በተለመደው እስላማዊ እምነት መሠረት[10] የሰው ልጅ በአምሳለ እግዚአብሔር እንደተፈጠረ የማይታመነው። የቁርአን ብቸኛ መልእክት፡-

---

[9] ይህንን ርዕሰ ጉዳይ ከዚህ በላይ አንተነትነውም ምክንያቱም እየተመለከትን ያለነው ተሠግዎ የሚቻል መሆኑን ብቻ ነውና፤ ነገር ግን አንድሪው ሙዲ *In Light of the Son,* p. 58 በሚለው መጽሐፉ እንደጻፈው እግዚአብሔር ሁሉን ነገር ሲፈጥር ተሠግዎን ታሳቢ በማድረግ ነበር ምክንያቱም የልጁ ውርስ ስለሆነ ልጁ የሚወርሰው በተሠግዎ በኩል ስለሆነ ነው። ሁሉም ነገር ለእርሱ ነው የተፈጠረው።

[10] አንድ የሱኒ ሐዲስ (Sahih Muslim: bk. 40, no. 6809) አዳም በአላህ አምሳል 30 ሜትር ረዝሞ እንደተፈጠረ ቢናገርም በተለመደው እስላማዊ እምነት ላይ ያለው በገረ መለኮታዊ ተፅዕኖ ኢምንት ነው።

... የሚመስለው ምንም ነገር የለም ... (ቁርአን 42፡11)

በእስልምና ኸሊፍ[11] እንደ ፈጣሪ ወኪል ሆኖ ምድርን ይገዛል ነገር ግን ይህ በአምሳል አልተገለጸም፤[12] ከፈጣሪ ጋር የሚደረግ ማንኛም ተያያዥነት ተክዷል።

... ለነርሱ ከርሱ በቀር ምንም ረዳት የላቸውም፤ በፍርዱም አንድንም አያጋራም። (ቁርአን 18፡26)

ቁርአን "እኔ ቅዱስ ነኝና ቅዱሳን ሁኑ" የሚል ቃል የለውም። አላህን የሚመስል ምንም ነገር የለም፣ ስለዚህ የሰው ልጆች የእግዚአብሔርን ባሕርይ አያንጸባርቁም።

በመጨረሻም ቁርአን የሰው ልጆች በእግዚአብሔር ክብር ውስጥ ተካፋዮች ይሆኑ ዘንድ የእግዚአብሔር ዓላማ እንደሆነ አይናገርም። የሰው ልጆች ግብ በገነት ውስጥ ደስታን ማጣጣምና ወደ አምላካቸው የመቅረብ ዕድልን ማግኘት ነው። ይህ ማለት ክርስቲያኖችና ሙስሊሞች ሰው መሆን ማለት ምን ማለት እንደሆነ ፈፅሞ የተለያየ መረዳት አላቸው ማለት ነው። ለክርስቲያኖች ሰውነ መሆን እግዚአብሔርን ይወክላል፣ የእግዚአብሔርን ባሕርይ ያንጸባርቃል፣ በክብሩም ውስጥ ተካፋይ ነው። እግዚአብሔር በእርሱና በኛ መካከል ግንኙነትን ፈጥሯል ስለዚህ ሰብዓዊነት ለተሠግዎ ተስማሚ ነው። የሰው ልጆች በአምሳለ እግዚአብሔር ነው የተፈጠሩት የሚለው አስተምሕሮ ለተሠግዎ መሠረትን ይጥላል። ለሙስሊሞች ሰብዓዊነት እግዚአብሔርን አይወክልም፣ የእርሱን ባሕርይ አያንጸባርቅም፣ በእርሱም ክብር ውስጥ ተካፋይ አይደለም። እግዚአብሔር በኛና በእርሱ መካከል ልዩ ግንኙነት አልመሠረተም፣ ስለዚህ ሰብዓዊነት ለተሠግዎ ተስማሚ አይደለም። የእስልምናው አስተምሕሮ ሰብዕ ለተሠግዎ ምንም መሠረት አይሰጥም። በክርስትናና በእስልምና መካከል የሚገኘውን ይህንን ልዩነት መረዳት ያስፈልገናል።

ብዙ ጊዜ ሙስሊሞችና ክርስቲያኖች ስንወያይ በብዙ ነገሮች ላይ የምንስማማ ይመስለናል እውነታው ግን አለመስማማታችን ነው። ሰው መሆን ማለት ምን ማለት እንደሆነ እንኳ አንስማማም! ስለዚህ ስለ ተሠግዎ ከማውራታችሁ በፊት ሰው መሆን ማለት ምን ማለት እንደሆነ ማብራራት ያስፈልጋችኋል።

ስለዚህ ይህንን ከሙስሊም ጋር መወያየት የምትችሉት እዴት ነው? ዝም ብላችሁ ብቻ ርዕሱን ለውይይት አቅርቡ። ሰው መሆን ማለት ምን ማለት ነው? ከእንስሳት የምንለየው በምንድነው? ብላችሁ ጠይቁ። የአምሳለ እግዚአብሔርን አስተምሕሮ ከቶራህ፣ ከነቢያት፣ ከመዝሙራትና ከወንጌል አሳዩዋቸው። የነቢያት ሁሉ አስተምሕሮ መሆኑን አስረዷቸው። በዚህ ክፍል የተጠቀሱትን ነጥቦች ጥቀሱ፤ ሰው የእግዚአብሔር ወኪል ነው፣ ባሕርዩን

11 ኸሊፍ የእስላማዊ ማሕበረሰብ መሪ ነው። ሙሐመድ በአላህ ክብር ተካፋይ እንደሆነ መሟገት ይቻላል ነገር ግን እዚህ ነጥብ ላይ አናነሳውም።

12 ቁርአን 2፡30፣ 38፡26

ያንጸባርቃል፣ እግዚአብሔር ለኛ ያለው ዓላማ የክብሩ ተካፋዮች እንሆን ዘንድ ነው። ይህ ማለት እግዚአብሔር ሰውን ለተሥግዎ ተስማሚ አድርጎ ፈጥሯል ማለት እንደሆነ አስረዷቸው።

ቁርኣን ኢየሱስ አምላክ አለመሆኑን በግልጽ ይናገራል። ነገር ግን አምላክ ወደ ፍጥረታቱ ከመግባት አላገደውም። ከዚህ ይልቅ አማኞች በትንሳኤ ቀን አምላክን በፍጥረት ውስጥ እንደሚያዩት እና ይህም ታላቅ የደስታ ምክንያት እንደሚሆን ይነግረናል። ይህ ሀሳብ በሚከተለው ሐዲስ ውስጥ የበለጠ ተብራርቷል፡-

አቡ ሰዒድ አል-ኩድሪ እንደተረከው፡- “የአላህ መልእክተኛ ሆይ! የትንሣኤ ቀን ጌታችንን እናየዋለንን?" ብለን ጠየቅነው። እርሱም "ሰማዩ በጠራ ጊዜ ፀሐይንና ጨረቃን ለማየት ይከብዳችኋልን?" ብሎ ጠየቀን" እኛም "አይከብደንም" ብለን መለስንለትን። እርሱም "ፀሐይንና ጨረቃን (በጠራራ ሰማይ ውስጥ) ለማየትም እንደማይቸግራችሁ በዚያ ቀን ጌታችሁን ለማየት አትቸገሩም" አለን። [...] ከዚያም አላህ እነርሱ በማያውቁትና ቀደም ብለው ባላዩት ቅርጽ ይመጣል። መጥቶም እኔ ጌታችሁ ነኝ ይላል። (ሳሂህ አል-ቡኻሪ 7439፡ ቅጽ 9 መጽሐፍ 93 ቁጥር 532s)

ስለዚህ በቁርኣን እና በሐዲስ መሰረት እግዚአብሔር ቅርጽ አለው እናም በፍጥረት ውስጥ ተገልጦ ይታያል ማለት ነው። ይህ ማለት እስልምና የራሱ የትስጉት ትምህርት አለው ማለት ነው። ስለዚህ በቁርኣን እና ሀዲስ መሰረት ትስጉት ሊከሰት የሚል ነገር ነው። ይህንን ሀሳብ ከሙስሊም ጓደኛዎ ጋር ለመወያየት ጠቃሚ ሆኖ ሊያገኙት ይችላሉ።

ልህቀት ምንድነው?

በእስልምና አንድ የተለመደ አባባል አለ። እርሱም ‘አላሁ አክበር’ ሲሆን ትርጉሙም ‘አላህ ታላቅ ነው’ ተብሎ ይተረጎማል። ለብዙ ሙስሊሞች ከዚህ የአላህ ታላቅነት የተነሳ ሰው ሆኖ መምጣት ለእርሱ ውርደት አድርገው እንዲያስቡት አድርጓቸዋል። በርካታ ሙስሊሞች “አምላክ ሽንት ቤት ገባ እያልከኝ ነው? ምንኛ ወራዳ አነጋገር ነው? ይሉኛል"

ይሁን እንጂ ታላቅነት ምን ማለት ነው? የኢየሱስ ደቀ መዛሙርት በዓለማችን እንዳሉት ብዙ ሰዎች ታላቅነትን በትክክል አልተረዱም ነበር። ታላቅ መሆን ሌሎች አናንተን ሲያገለግሉ እንደሆነ አሰቡ ነበር።

> ደግሞም ማናቸውም ታላቅ ሆኖ እንዲቈጠር በመካከላቸው ክርክር ሆነ። እንዲህም አላቸው። የአሕዛብ ነገሥታት ይገዙአቸዋል፥ በላያቸውም የሚሠለጥኑት ቸርነት አድራጊዎች ይባላሉ። እናንተ ግን እንዲህ አትሁኑ፤ ነገር ግን ከእናንተ ታላቅ የሆነ በመካከላችሁ እንደ ታናሽ፥ የሚገዛም እንደሚያገለግል ይሁን። ሉቃ 22፡24-26

> በእናንተስ እንዲህ አይደለም፤ ነገር ግን ማንም ከእናንተ ታላቅ ሊሆን የሚወድ የእናንተ አገልጋይ ይሁን፥ከእናንተም ማንም ፊተኛ ሊሆን የሚወድ የሁሉ ባሪያ ይሁን፤ ማር 10፡43-44

በኢየሱስ ትምህርት መሰረት ታላቅ ሰው ኃያል ሆኖ ሌሎችን ለማገልገል ራሱን ዝቅ የሚያደርግ ሰው ነው። ይህንን ታላቅነት በኢየሱስ ሕይወት ውስጥ እናያለን። አንድ ቀን ምሽት በኢየሩሳሌም መታጠቂያውን አውልቆ የደቀ መዛሙርቱን እግር አጠበ። እነርሱም ደነገጡና ሊያስቆሙት ሞከሩ። እርሱ ግን እንዲህ አላቸው፡-

> እናንተ መምህርና ጌታ ትሉኛላችሁ፤ እንዲሁ ነኝና መልካም ትላላችሁ። እንግዲህ እኔ ጌታና መምህር ስሆን እግራችሁን ካጠብሁ፥ እናንተ ደግሞ እርስ በርሳችሁ እግራችሁን ትተጣጠቡ ዘንድ ይገባችኋል። እኔ ለእናንተ እንዳደረግሁ እናንተ ደግሞ ታደርጉ ዘንድ ምሳሌ ሰጥቻችኋለሁና። ዮሐ 13፡13-15

ኢየሱስ እውነተኛ ታላቅነት ምን እንደሆነ አሳይቶናል። እርሱም ኃያላን ሌሎችን ለማገልገል ሲመርጡ ነው። እግዚአብሔርም ያደረገልን ይህንኑ ነው። እግዚአብሔር ራሱን ለኛ ሰጥቶናል። ትስጉት የአምላክ ክብሩን አይገፈውም። ከዚያ ይልቅ በተቃራኒው ታላቅነቱን ያሳያል። ምክንያቱም አምላክ ይህንን ያደረገው እኛን ስለወደደን ነው። በዚህም ኢየሱስ የአምላክን ታላቅ ፍቅር ገለጠልን።

ጠቃሚ ሆኖ ሊታገኙት የሚችሉትን ምሳሌ ላሳያችሁ። ሕዝባቸው እየተሰቃዩ እና እርዳታ የሚያስፈልጋቸው ሁለት ነገሥታት እንዳሉ እናስብ። አንደኛው ንጉሥ በቤተ መንግሥቱ ውስጥ ተቀምጦ ነገሮችን እንዴት ማስተካከል እንዳለባቸው መመሪያ ለሕዝቡ ላከ። ሌላኛው ንጉሥ ቤተ መንግሥቱን ትቶ ከሕዝቡ ጋር ተቀላቅሎ ራሱ ረዳቸው። ከሁለቱ ታላቅ ንጉስ የትኛው ነው? የትስጉት ትምህርት በምንም መልኩ የእግዚአብሔርን ታላቅነት አይነግፍም። እንደ እውነቱ ከሆነ የእግዚአብሔር ታላቅነት ማሳያ ነው።

## የብሉይ ኪዳን ነቢያት

እዚህ ነጥብ ላይ ስትደርሱ በቀጥታ ወደ አዲስ ኪዳን በመሄድ ስለ ኢየሱስ ምን እንደሚል ማሳየት ትችላላችሁ፤ ይህንኑ እንድታደርጉም እመክራችኋለሁ። እነዚህን መሠረታዊ ፅንሰ ሐሳቦች ከተመለከታችሁ ቅድመ ግንዛቤያቸውን ለማጥራት በቂ ጊዜ ወስዳችኋል ማለት ነው። እነዚህ ቅድመ ግንዛቤዎች ሊጸዱ ይገባል ነገር ግን አሁን ኢየሱስን የመገናኛ ጊዜ ነው። በዚህ ምዕራፍ ቀጣይ ክፍል ይህንን እናደርጋለን። ነገር ግን ነገሮችን ምሉዕ ለማድረግ ያህል ስለ ተሠግዎ የተነገሩ የብሉይ ኪዳንን ትንቢቶች መመልከት ያስፈልገናል። እነዚህ በክርስቲያን-ሙስሊም ውይይት ወቅት ሊነሱ ስለሚችሉ ማወቅ አስፈላጊ ነው።

> ብሉይ ኪዳን በምን ዓይነት መንገዶች ነው ስለ ተሠግዎ የሚተነብየው? ሁለት ዓይነት መንገዶች እንዳሉ አስባለሁ። የመጀመርያው በብሉይ ኪዳን ጠቅላላ ታሪክ

ነው። ሁለተኛው ደግሞ መሲሁ ከሰው በላይ መሆኑን የሚጠቁሙ ዝርዝር ትንቢቶች ናቸው። አንድ በአንድ እንያቸዋለን።

ከክርስቶስ በፊት የነበሩ ነቢያት የሰው ልጅ በአምሳለ እግዚአብሔር ስለመፈጠሩ፣ የእርሱን ባሕርይ እንደሚያንጸባርቅና የክብሩ ተካፋይ እንደሆነ በግልፅ ይናገራል። የእሥራኤል ሕዝብና ነገሥታቱ ለተመሳሳይ ዓላማ ተጠርተዋል፤ ሕጉም የተሰጣቸው ለዚሁ ዓላማ ነበር። ይሁንና ብሉይ ኪዳን የሰው ልጆችን ውድቀትና እሥራኤል በዚህ መንገድ መኖር አለመቻሏን ይዘግባል። ውድቀቱ በረጅም ዘመናት፣ በተለያዩ ሁኔታዎች ውስጥ፣ በተለያዩ የመንግሥታት ዓይነቶችና በተለያዩ ነገሥታት ዘመናት ታይቷል። የእግዚአብሔርን መንፈስ የተቀበሉ ነገሥታት እንኳ ጉድለት ነበረባቸው! እግዚአብሔር በረከትን፣ ሕይወትንና ክብርን ቢሰጥም ነገር ግን የሰው ልጆችና የእሥራኤል ባሕርይ ፍርድን፣ ውርደትንና ሞትን አመጣ። ሁላችንም ኃጢአተኞች ነን። የእግዚአብሔርም ስም በእኛ ምክንያት ጎድፏል።

> ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል። የእሥራኤል ቤት ሆይ፥ በመጣችሁባቸው በአሕዛብ መካከል ስላረከሳችሁት ስለ ቅዱስ ስሜ ነው እንጂ ስለ እናንተ የምሠራ አይደለሁም። ሕዝ 36፡22

ከምርኮ ዘመን በኋላ እንኳ እሥራኤል የኃጢአት እስረኛ ነበረች። ስለዚህ ብሉይ ኪዳን የሰው ልጆች በራሳቸው ጥረት አንድ ቀን ነገሮችን እንደሚያስተካክሉ የሚሰጠው ምንም ተስፋ የለም። ብሉይ ኪዳን የሰው ልጆች ምንም ያህል የተራዘመ ጊዜ ቢሰጣቸው ከኃጢአት ራሳቸውን በማፋታት ለእግዚአብሔር ክብር ሊኖሩ ስለመቻላቸው ምንም ተስፋ አይሰጥም። ብሉይ ኪዳን የሚጠናቀቀው የሰው ልጆች የኃጢአት እስረኛ፣ በእግዚአብሔር ፍርድ ስር ያሉ፣ ተልኳቸውን ከግብ ማድረስ ያልቻሉና አዳኝ የሚያሻቸው መሆናቸውን በመግለፅ ነው።የሰው ልጆችንና የእሥራኤልን ዓላማ ከግብ ማድረስ የሚችል ከሰው ልጆች መካከል አልተገኘም። በዚህ ሁኔታ ውስጥ ነበር እግዚአብሔር ራሱ በመምጣት እኛ መፈፀም ያልቻልነውን እንሚፈፅም ተስፋን የሰጠው። እርሱ ራሱ ፍትህን፣ መዳንንና ለስሙ ክብርን ያመጣል፡-

> እውነትም ታጥቶአል፥ ከክፋትም የራቀ ሰው ለብዝበዛ ሆኖአል። እግዚአብሔርም አየ ፍርድም ስለሌለ ተከፋ። ሰውም እንደሌለ አየ፥ ወደ እርሱ የሚማልድ እንደሌለ ተረዳ ተደነቀም፤ ስለዚህ የገዛ ክንዱ መድኃኒት አመጣለት፥ ጽድቁም አገዘው። ... ለጽዮን ታዳጊ ይመጣል፥ በያዕቆብም ዘንድ ከኃጢአት ለሚርቁ፥ ይላል እግዚአብሔር። (ኢሳ. 59፡15-16፣ 20)

ይህንኑ ሐሳብ ኢሳይያስ 40 ላይ እናገኛለን። ይህ እግዚአብሔር ራሱ ወደ ፍጥረቱ በመምጣት ኃጢአተኛ ሰዎች መፈፀም ያልቻሉትን እንደሚፈፅም የተተነበየበት ነው፡-

> የአዋጅ ነጋሪ ቃል፡- የእግዚአብሔርን መንገድ በምድረ በዳ ጥረጉ፥ ለአምላካችንም ጐዳና በበረሀ አስተካክሉ። ሸለቆው ሁሉ ከፍ ይላል፥ ተራራውና ኮረብታውም

> ሁሉ ዝቅ ይላል፤ ጠማማውም ይቃናል፥ ስርጓጉጡም ሜዳ ይሆናል፤ የእግዚአብሔርም ክብር ይገለጣል፥ *ሥጋ* ለባሹም ሁሉ በአንድነት ያየዋል፥ የእግዚአብሔር አፍ ይህን ተናግሮአልና። (ኢሳ. 40፡3-5)

ሰው የእግዚአብሔርን ክብር እንዲገልጥ ነበር የታሰበው። ነገር ግን ይህንን ማድረግ አልቻልንም። ኢሳይያስ 40 እግዚአብሔር ራሱ በመምጣት ክብሩን እንደሚገልጥ ይናገራል። ስለዚህ እግዚአብሔር እኛ ማድረግ ያልቻልነውን ሊያደርግ ሊመጣ ዘንድ አለው። እግዚአብሔር ሰዎችንና እሥራኤልን የፈጠረበት ዓላማ ከግብ ይደርሳል ነገር ግን በመምጣት ይህንን የሚያደርገው እግዚአብሔር ራሱ ነው። ቁጥሮቹ እግዚአብሔር ይህንን ያደርጋል ብቻ አይሉም ነገር ግን *በመምጣት* ያደርጋል ነው የሚሉት።

ሚልኪያስ 3፡1 ከኢሳይያስ 40፡3-5 ጋር ተመሳሳይ ሲሆን እግዚአብሔር እንደሚመጣ ይናገራል ነገር ግን በዚህ ጊዜ እግዚአብሔር አስቀድሞ ማንነቱ በመተዋወቅ ይመጣል። መልእክተኛን ይልካል፣ ይህ መልእክተኛ ነቢዩ ኤልያስ[13] ነው፣ እርሱም መንገድን ያዘጋጅለታል፡-

> እነሆ፥ መልእክተኛዬን እልካለሁ፥ መንገድንም በፊቴ ያስተካክላል፤ እናንተም የምትፈልጉት ጌታ በድንገት ወደ መቅደሱ ይመጣል፤ የምትወዱትም የቃል ኪዳን መልእክተኛ፥ እነሆ፥ ይመጣል፥ ይላል የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር። (ሚል. 3፡1)

ከዚህ እንደምናየው ከክርስትና ቀደም ብሎ በነበረው የአይሁድ እምነት ውስጥ በዘመን ፍጻሜ አምላክ እንደ ወደ ሕዝቦቹ መካከል እንደሚወርድ ይታመናል። ከዚህ ቀደም ያየናቸው ጥቅሶች እግዚአብሔር ሰዎች ማድረግ ያልቻሉትን ለማድረግ እንደሚመጣ ይናገራሉ። ይሁንና ሌሎች ጥቅሶች የእግዚአብሔርን መምጣት ከሰው መምጣት ጋር ያያይዛሉ፡-

> ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላልና፡- እነሆ፥ እኔ ራሴ በጎቼን እሻለሁ እፈልግማለሁ። እረኛ በተበተኑት በጎች መካከል ባለ ጊዜ መንጋውን እንደሚፈልግ፥ እንዲሁ በጎቼን እፈልጋለሁ፤ በደመናና በጨለማ ቀን ከተበተኑት ስፍራ ሁሉ አድናቸዋለሁ። … በላያቸውም አንድ እረኛ አቆማለሁ እርሱም ያሰማራቸዋል፥ እርሱም ባሪያዬ ዳዊት ነው፤ ያሰማራቸዋል እረኛም ይሆናቸዋል። (ሕዝ. 34፡11-12፣ 23)

እዚህ ቦታ ላይ እንደምናየው እግዚአብሔር ሕዝቡን ለመሰብሰብና ለመንከባከብ ሲመጣ ይህ “ባርያውን ዳዊትን” ያካትታል። እዚህ ቦታ ላይ ደዊትን የጠቀሰው መሲሃዊ ነው። እዚህ ነጥብ ላይ ስንደርስ እግዚአብሔር ለዳዊት የገባለትን ቃል ኪዳን ማየት ያስፈልገናል።

---

[13] ሚል. 4፡5

በእግዚአብሔር መንግሥት ላይ ዘላለማዊ ንግሥና ያለው የዳዊት ልጅ እንደሆነ እግዚአብሔር ለዳዊት ኪዳን ገብቶለታል፡-

ዳዊት ስለዚህ ስልለሚመጣው መሲህ ሲናገር በቃል ኪዳኑ መሠረት ልጄ ብሎ አልጠራውም ነገር ግን ጌታዬ ብሎ ጠርቶታል፤ እርሱ በእግዚአብሔር ቀኝ የሚቀመጥ እውነተኛ የእግዚአብሔር ልጅ ነውና።

> እግዚአብሔር ጌታዬን፡- ጠላቶችህን ለእግርህ መቀመጫ እስካደርግልህ ድረስ በቀኜ ተቀመጥ አለው። (መዝ. 110፡1)

ኢሳይያስ 9 የእግዚአብሔርን መንግሥት ለዘላለም የሚመሠርተው እውነተኛውል ልጅ መሲሁ እንደሚመጣ ይናገራል፡-

> ሕፃን ተወልዶልናልና፥ ወንድ ልጅም ተሰጥቶናልና፤ አለቅነትም በጫንቃው ላይ ይሆናል፤ ስሙም ድንቅ መካር፥ ኃያል አምላክ፥ የዘላለም አባት፥ የሰላም አለቃ ተብሎ ይጠራል። (ኢሳ. 9፡6-7)

መሲሁ እዚህ ጋ “ኃያል አምላክ” የሚለውን ጨምሮ ብዙ ማዕርጋት ተሰጥተውታል። ይህ ሃያል አምላክ የሚለው ቃል በሚቀጥለው ምዕራፍ ውስጥ እንደገና ጥቅም ላይ ውሏል፡-

> የያዕቆብም ቅሬታ ወደ ኃያል አምላክ ይመለሳሉ። (ኢሳ. 10፡21)

በመጨረሻ የምንመለከተው የብሉይ ኪዳን ትቅስ ዳንኤል 7 ነው።

> በሌሊት ራእይ አየሁ፤ እነሆም፥ የሰው ልጅ የሚመስል ከሰማይ ደመናት ጋር መጣ በዘመናት ወደ ሸመገለውም ደረሰ፤ ወደ ፊቱም አቀረቡት። ወገኖችና አሕዛብ በልዩ ልዩ ቋንቋም የሚናገሩ ሁሉ ይገዙለት ዘንድ ግዛትና ክብር መንግሥትም ተሰጠው፤ ግዛቱም የማያልፍ የዘላለም ግዛት ነው፥ መንግሥቱም የማይጠፋ ነው። (ዳን. 7፡ 13-14)
>
> መንግሥትም ግዛትም ከሰማይም ሁሉ በታች ያሉ የመንግሥታት ታላቅነት ለልዑሉ ቅዱሳን ሕዝብ ይሰጣል፤ መንግሥቱ የዘላለም መንግሥት ነው፥ ግዛቶችም ሁሉ ይገዙለታል ይታዘዙለትማል። (ዳን. 7፡27)

የዳንኤል ትንቢት በአራት አራዊት ይጀምራል። አራዊቱ የሰው መንግሥታትን የሚወክሉ ናቸው (ቁ. 17)። እነዚህ መንግሥታት የእግዚአብሔርን መንግሥት ስለሚቃወሙ የእግዚአብሔር ምስል አይደሉም። ኢ-ሰብዓዊና አውሬያዊ እንዲሆኑ ያደረጋቸው ይህ ሲሆን እርባና ቢስ ናቸው። ነገር ግን የእግዚአብሔር ምስል የሰው ልጅን እናያለን፤ እርሱ ደግሞ ተገቢ ነው። ሰዎች በብሉይ ኪዳን ውስጥ እግዚአብሔርን በዙፋኑ ላይ ሲያዩት የማይበቁና

ወደ እርሱ መቅረብ እንደማይገባቸው ይናገራሉ።[14] ይህ ግን እንደርሱ አይደለም። በኃጢአተኞች ከተሞላው የሰው ልጆች ዓለም ይህ የሰው ልጅ ወደ እግዚአብሔር ዙፋን የመቅረብ ብቃት አለው! ይህ የሰው ልጅ ማን ነው? እርሱ የሕዝበ እሥራኤል ተምሳሌት ነውን? አይደለም ምክንያቱም እንደ ሰው ልጆች ሁሉ የእግዚአብሔርን ዙፋን የመቅረብ ብቃት የላትምና። ይሁንና ተምሳሌታዊ ስላልሆነ እሥራኤልንና የሰው ልጆችን በእግዚአብሔር ዘንድ በመወከል መካከለኛ ሊሆንላቸው ይችላል። ይህ ጻድቅ የሰው ልጅ ሰዎችና እሥራኤል ማድረግ ያልቻሉትን ያደርጋል። የሰው ልጆችን ዓላማ ከግብ ለማድረስ ወደ እግዚአብሔር መገኘት የመቅረብ ብቃት አለው። በእግዚአብሔር ሕዝብ ፋንታ በመሆን የእግዚአብሔርን መንግሥት ይረከባል (ቁ. 27)።[15] የሰው ልጅ የእሥራኤልና የሰው ልጆች ሁሉ ተስፋ ነው፤ እርሱ አዳኛችን ነው፤ እርሱ በእግዚአብሔር ፊት ጽድቃችን ነው።

የሰው ልጅ የተባለው የእግዚአብሔር የብቻው የሆኑ ባሕርያት አሉት። ይህ ሰው የሚያደርገውን ማድረግ የሚችለው እግዚአብሔር ብቻ ነው። ስለዚህ ዳንኤል 7፡13-14 ስለ ተሠግዎ የተነገረ ትንቢት አለበለዚያም ለተሠግዎ በር ከፋች ነው።

## የወንጌል ምስክርነት

ስለ ኢየሱስ የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት ከሆኑት ከወንጌል ዘገባዎችና ከሐዋርያት ጽሑፎች እንማራለን። እነዚህም የኢየሱስን ፍፁም አምላክነትና ፍፁም ሰውነት ይገልጣሉ።

ኢየሱስ ተወልዷል፣ አድጓል፣ ተምሯል፣ በልቷል፣ ጸልዮዋል፣ መከራን ተቀብሏል፣ ተፈትኗል፣ ሞቷል፣ ከሙታንም ተነስቷል። ይህ ሁሉ ሰው መሆኑን የሚገልጥ ነው።

> ኢየሱስም ደግሞ በጥበብና በቁመት በሞገስም በእግዚአብሔርና በሰው ፊት ያድግ ነበር። (ሉቃ. 2፡52)

> ማለዳም ተነሥቶ ገና ሌሊት ሳለ ወጣ ወደ ምድረ በዳም ሄዶ በዚያ ጸለየ። (ማር. 1፡35)

> በዚያም የያዕቆብ ጕድጓድ ነበረ። ኢየሱስም መንገድ ከመሄድ ደክሞ በጕድጓድ አጠገብ እንዲህ ተቀመጠ፤ ጊዜውም ስድስት ሰዓት ያህል ነበረ። (ዮሐ. 4፡6)

> እንግዲህ ልጆቹ በሥጋና በደም ስለሚካፈሉ፥ እርሱ ደግሞ በሞት ላይ ሥልጣን ያለውን በሞት እንዲሽር፥ ይኸውም ዲያብሎስ ነው፥ በሕይወታቸውም ሁሉ ስለ ሞት ፍርሃት በባርነት ይታሰሩ የነበሩትን ሁሉ ነጻ እንዲያወጣ፥ በሥጋና በደም እንዲሁ ተካፈለ። (ዕብ. 2፡14-15)

---

14 ኢሳ. 6

15 2ሳሙ. 5፡12

እርሱ ራሱ ተፈትኖ መከራን ስለ ተቀበለ የሚፈተኑትን ሊረዳቸው ይችላልና። (ዕብ. 2፡18)

በክርስትና የቀደመው ዘመን ኢየሱስ ፍፁን ሰው መሆኑን የሚክዱ ሰዎች ነበሩ። ይሁንና ይህ ለሙስሊሞች ችግር አይደለም። ኢየሱስ ፍፁም ሰው መሆኑን ይቀበላሉ። ስለዚህ አዲስ ኪዳን ኢየሱስ ፍፁም አምላክ መሆኑን እንዴት እንደሚያረጋግጥ እናያለን። ማጣቀሻዎቹ ከመብዛታቸው አንፃር አጥር ባለ መንገድ አጠቃላዩን ማስረጃ እናቀርባለን።

1. ከድንግል መወለዱ *እግዚአብሔር ከእኛ ጋር* ተብሎ ተገልጿል (ማቴ. 1፡23)፤ ልዩ የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን እንደሚያሳይም ተነግሯል (ሉቃ. 1፡35)።
2. ኢየሱስ እግዚአብሔር ወደ እኛ ስለመምጣቱ በኢሳ. 40፡2-3 እና ሚል. 3፡1፣ ማቴ 3፡3 ላይ የተገባው ተስፋ ፍፃሜ ነው። ማር. 1፡1-3 እና ሉቃ. 19፡44፣ ሉቃ 3፡4-6፣ 19፡44 እና ዮሐ 1፡23 ይመልከቱ።
3. ኢየሱስ መለኮታዊ ቅድመ ኑባሬ አለው። መጥምቁ ዮሐንስ ስለ ኢየሱስ ከተናገረው መረዳት ይቻላል።

ኢየሱስ ቅድመ ዓለም እንደነበረ ዮሐ. 1፡1፣ ፊል. 2፡5-11፣ ቆላ. 1፡15 እና ዕብራውያን 1፡3 ላይ ተገልጿል።

4. ኢየሱስ ፈጣሪ ነው፤ ዮሐ. 1፡1-3፣ ቆላ. 1፡16፣ ዕብ. 1፡1-3።
5. ኢየሱስ እግዚአብሔር የሚያደርገውን ልክ በዚያው መንገድ ያደርጋል።
    - የሰዎችን ኃጢአት ይቅር ብሏል፤ ማር. 2፡5-7።
    - የእርሱ መገኘት ሰዎች ኃጢአተኞች መሆናቸውን እንዲገነዘቡ አድርጓል፤ ሉቃ. 5፡8።
    - በቃሉ ማዕበሉን ፀጥ አሰኝቷል፤ መዝ. 89፡9-10፣ 104፡7፣ 107፡23-30 › ማር. 4፡35።
    - በውኀ ላይ ተራምዷል፤ ኢዮብ 9፡8 » ማር. 6፡45-።
    - መናፍስትን አዟል፤ 1ነገ. 22 › ማር. 5፡7-8።
    - የሚድነው ማን እንደሆነ መርጧል፤ ማቴ. 11፡27።
    - በፍርድ ቀን በደመና ላይ ሆኖ ይመጣል፤ ኢሳ. 19፡1፣ መዝ. 68፡4፣ 104፡ 1-3 › ማር. 14፡62
6. ኢየሱስ መለኮታዊ ማዕርጋት ተሰጥተውታል።

- የእግዚአብሔር ሕዝብ አስተዳዳሪ ወይንም ባል ነው፤ ኢሳ. 54፡5፣ ኤር. 3፡14፣ ሕዝ. 16፡32፣ ሆሴዕ 1-2 (2፡19-20) › ማር. 2፡19፣ ዮሐ. 3፡29።
- “እኔ ነኝ” ብሎ ዘጸ. 2፡19 ላይ የተናገረው ነው › ዮሐ. 8፡58።
- የሕይወት ራስ ነው፤ ሐዋ. 3፡15።

- ያሕዌ ነው ኢሳ 6 ፣ ዮሐ. 12፡38-42፣ ኢዩ. 2፡32 ፣ ሐዋ 2፡21 እና 38፣ 4፡12፣ ሮሜ 10፡12-13።
- ሕዝቡን ሰብሳቢ እንደሆነው አንደ እግዚአብሔር ይናገራል፤ ኤር. 23፡3፣ ሶፎ. 3፡20 ፣ ማቴ. 23፡37፣ ሉቃ. 13፡34።
- የመጀመርያና የመጨረሻ፤ ኢሳ. 44፡6 ፣ ራዕይ 1፡17-18፣ 22፡13።

7. ኢየሱስ ዳንኤል 7 ላይ የተነገረው መለኮታዊ የሰው ልጅ ነው ፣ ማቴ. 26፡63-66፣ እንዲሁም የመዝሙር 110 መለኮታዊ ልጅ ነው ፣ ማር. 12፡35።
8. እርሱን ካያችሁት እግዚአብሔር አብን አይታችሁታል ማለት ነው፤ ዮሐ. 14፡8-9።
9. ኢየሱስ እንደ እግዚአብሔር ይሠራል፤ ዮሐ. 5፡16-30።
10. እንደ እግዚአብሔር አምልኮን ተቀብሏል፤ ዮሐ. 5፡23፣ 20፡28፣ ራዕይ 5፡13።

ኢየሱስ አምላክ ነው!

ስለዚህ ኢየሱስ ፍፁም አምላክ ፍፁም ሰው መሆኑን አይተናል። አዲስ ኪዳን እነዚህን ሁለቱን ገፅታዎች አንድ ላይ አጣምሮ ይዟል።

ይህንን ለሙስሊም ማሳየት የምትችሉት እንዴት ነው?

በዚህ ክፍል የተጠቀሱትን ጥቅሶች ኢየሱስ ፍፁም አምላክ ፍፁም ሰው መሆኑን ለማሳየት ተጠቀሙበት። ብዙ ጊዜ ኢየሱስ አምላክ መሆኑን የሚያሳዩ ጥቅሶችን ብቻ ለማሳየት እንጓጓለን። ይህንን እንዳታደርጉ። እርሱ አምላክም ሰውም መሆኑን ነው ማሳየት ያለብን ምክንያቱም የምናምነው እርሱን ነውና። የኢየሱስን አምላክነት የሚሳዩ ጥቅሶችን ብቻ የምትጠቅሱ ከሆነ ሙስሊሞች አቋማችሁን ለማጣጣል ሰውነቱን የሚያሳዩ ሌሎች ጥቅሶችን ሊጠቅሱ ይችላሉ። የኢየሱስን ሁለቱንም ገፅታዎች ማሳየት ያስፈልጋችኋል።

## የኢየሱስ አምላክነትና ቁርአን

ቁርአንን ለመጥቀስ ልበ ሙሉ ከሆናችሁ የኢየሱስን አምላክነት ለማሳየት ልትጠቀሙበት ትችላላችሁ። ይህንንም በቁርአን ውስጥ የተጠቀሱ የፈጣሪ ባሕርያትን ኢየሱስ በወንጌል ውስጥ ከተናገረው ጋር በማነፃፀር በማሳየት ነው። እነዚህን ጥቅሶች አነፃፅሩ፡-

- ኃጢአትን ይቅር ሊል የሚችል ፈጣሪ ብቻ ነው፤ ቁርአን 3፡135 ፣ ማር. 2፡1
- ፈጣሪ ሕይወት ነው፤ ቁርአን 2፡255 ፣ ኢየሱስ ሕይወት እርሱ መሆኑን ተናግሯል፤ ዮሐንስ 14፡6።
- ፈጣሪ የመጀመሪያውና የመጨረሻው ነው፤ ቁርአን 57፡3 ፣ ኢየሱስ የመጀመሪያውና የመጨረሻው፤ ራዕይ 1፡17-18፣ 22፡13።
- ፈጣሪ ማዕበሉን ጸጥ ያደርጋል፤ ቁርአን 42፡32-33 ፣ ኢየሱስ ማዕበሉን ጸጥ አደረገ፤ ማርቆስ 4፡35።

- *ፈጣሪ በደመና ሆኖ በመምጣት ይፈርዳል፤ ቁርኣን 2፡210፣ 89፡21-23* › ኢየሱስ ለፍርድ በደመና ሆኖ እንደሚመጣ ተናግሯል፤ ማር. 8፡38፣ 13፡26።

እነዚህን ጥቅሶች ከተመለከታችሁ በኋላ እንዲህ ብላችሁ ጠይቋቸው፤ *ኢየሱስ ስለ ራሱ ምን እያለ ነው?* ከዚያም መጽሐፍ ቅዱስን ከናንተ ጋር እንዲያነቡ ጋብዟቸው።

በቁርኣን ውስጥ ፈጣሪ ብቻ እንደሚያደርጋቸው የተነገሩትን ኢየሱስ እንዴት እንዳደረጋቸው ማሳየትም ትችላላችሁ። ይሁን እጂ በቁርኣን ውስጥ ኢየሱስ ይህ የፈጣሪ ልዩ ባሕርይ እንዳለውና በተመሳሳይ መንገድ ሲፈፅም እንመለከታለን።[16] ይህ እግዚአብሔር አዳምን ከአፈር አበጅቶት የሕይወትን እስትንፋስ እፍ ካለበት ጋር ተመሳሳይ ነው።

> ጌታህ «ለመላእክት እኔ ሰውን ከጭቃ ፈጣሪ ነኝ ባለ ጊዜ» (አስታውስ)። «ፍጥረቱንም ባስተካከልኩና ከመንፈሴ በነፋሁበት ጊዜ ለእርሱ ሰጋጆች ኾናችሁ ውደቁ» (አልኩ)። (ቁርኣን 38፡71-75)

## ትግበራና ማጠቃለያ

1. እግዚአብሔር ከፍጥረት ጋር ራሱን አቆራኝቷል።
2. እግዚአብሔር በፍጥረቱ ምሕዳር በመኖር ራሱን ይገልጣል።
3. እግዚአብሔር በመምጣት ከሰው ዘር ለመኖር እቅድ አለው።
4. ሰዎች በእግዚአብሔር መልክ ተፈጥረዋል።
5. በቁርኣን መሰረት አምላክ ወደ ፍጥረቱ መግባት ይችላል።
6. አምላክ በሰውነት ወደ እኛ መምጣቱ ታላቀቱን ይገልጣል።
7. ብሉይ ኪዳን አምላክ ወደ ሕዝቡ መምጣትና በመካከላቸው የመሆን ዕቅድ እንደነበረ ያስረዳል።
8. የወንጌል ምስክርነት እንደሚያሳየው ኢየሱስ ፍፁም አምላክና ፍፁም ሰው ነው።

በመጨረሻም ለሙስሊም ወዳጃችሁ ልትሰጡት የምትችሉት ወይንም በጋራ ልታጠኑት የምትችሉን የወንጌል ስርጭት ቡክሌት ድረገፅ ላይ ይገኛል።

## የተለመዱ ጥያቄዎች

1. *ሙስሊም፡* ዘኍልቁ 23፡19 "እግዚአብሔር ሰው አይደለም" ይላል፤ ስለዚህ መጽሐፍ ቅዱስ ተሠግዎን ይክዳል።

[16] አንዳንድ ሰዎች ሙሴ በትሩን በወረወረና እባብ በሆነች ጊዜ ተመሳሳይ ተዓምር እንደሠራ ይነግሩኛል (ዘጸ. 4)፤ ነገር ግን ሙሴ እግዚአብሔር በሠራው ተዓምር በመደናገጥ ከእባቡ ሸሽቷል። ይህ ታሪክ እግዚአብሔር አዳምን በፈጠረበት በዚያው ሁኔታ ኢየሱስ መፍጠሩን ከሚናገረው *የቶማስ ወንጌል* ከተሰኘው የአፖክሪፋ መጽሐፍ ከተቀዳው የቁርኣን አፈታሪክ ሙሉ በሙሉ የተለየ ነው።

*ክርስቲያን፡* የጥቅሱን የተወሰነ ክፍል ብቻ ነው ቆርጠህ የጠቀስከው። ሙሉ ጥቅስ እንዲህ ይላል፡-

> ሐሰትን ይናገር ዘንድ እግዚአብሔር ሰው አይደለም፥ ይጸጸትም ዘንድ የሰው ልጅ አይደለም። እርሱ ያለውን አያደርገውምን? የተናገረውንስ አይፈጽመውምን? (ዘኍ. 23፡19)
> እግዚአብሔር እንደ ሰው የመጣበት ሌሎች በርካታ ክፍሎ አሉ። ዘፍ 3፡8፣ 18፡1

አምልክ ሰው እንዳይደለ ክርስቲያኖችም ይስማማሉ። አምላክ አምላክ ነው ሰውም ሰው ነው። እኛ የምንለው ግን ኢየሱስ አምላክም ሰውም ሁለቱንም ነው። ሙሉ ጥቅሱ ሲነበብ እግዚአብሔር ሰው ሆኖ ወደ እኛ መምጣት አለመቻሉን ሳይሆን እግዚአብሔር እንደ ሰው ልጆች ሐሰትን እንማይናገርና የተናገረውን ቃል እንደሚጠብቅ የሚናገር ነው። ይህ ጥቅስ የያዝነውን ርዕስ የተመለከተ አይደለም፤ ለዚህ አንዱ ማስረጃ እግዚአብሔር ወደ አብርሃም በሰው አምሳል መምጣቱ ነው (ዘፍ. 18)። የተቀረው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍልም ኢየሱስ ፍፁም አምላክ ፍፁም ሰው መሆኑን ይመሰክራል።

2. *ሙስሊም፡* ወንጌል ኢየሱስ ምግብ እንደበላና እንደደከመው ይናገራል። አምላክ እነዚህ ነገሮች ሊፈራረቁበት አይችሉም። ስለዚህ ወንጌላት ኢየሱስ ሰው ብቻ መሆኑን ይመሰክራሉ።

*ክርስቲያን፡* ኢየሱስ ፍፁም ሰው መሆኑን ካንተ ጋር እስማማለሁ ነገር ግን የማስረጃውን ግማሽ ብቻ ነው እያየህ ያለኸው። አምላክ መሆኑን ደግሞ የሚናገሩ ሌሎች ጥቅሶች አሉ። ኢየሱስ ፍፁም አምላክ ፍፁም ሰው ነው። ማስረጃውን በሙሉ ማገናዘብ ይኖርብሃል።

3. *ሙስሊም፡* ወንጌል ኢየሱስ ስለ ኃጢአታችን መሞቱን ይናገራል። ኢየሱስ አምላክ ከሆነ አምላክ እንዴት ሊሞት ይችላል? ፍጥረት ፈጣሪውንና ገዢውን መግደል አይቻለውም።

*ክርስቲያን፡* ይህ ጥሩ ጥያቄ ነው። መልሱ ሁለት ዓይነት ነው፤ መጀመርያ ሞት ማለት አለመኖር ማለት አይደለም። እግዚአብሔር መኖር አቆመ እያልን አይደለም። ሁለተኛ በዚህ ምዕራፍ ውስጥ እንዳየነው ኢየሱስ በአንድ ማንነት ሁለት ባሕርያት አሉት። በሰብዓዊ ማንነቱ ነው የሞተው።

4. *ሙስሊም፡* ኢየሱስ እኔ አምላክ ነኝ አምልኩኝ ብሎ የተናገረው የቱ ጋ ነው?

*ክርስቲያን፡* ኢየሱስ መለኮታዊ ወልደ እግዚአብሔር መሆኑን ከአባቱ ጋርም እኩል መሆኑን፣ ከእርሱ ጋር የሚመለክ መሆኑን ተናግሯል (ማቴ 26፡63-64፣ ዮሐ 5፡16-23፣ 10፡33-36)፤ በተግባርም አረጋግጧል። ነገር ግን ወደዚህ ምድር የመጣው የተላከበትን ሥራ ለመፈጸም እና እኛን ለማዳን ስለእኛ መከራን ሊቀበል ነው። ከዚያም በኋላ ወደመጣበት ክብሩ ተመልሷል። ይህንንም በሞቱና በትንሳኤው አረጋግጧል።

5. *ሙስሊም፡* ማርቆስ ላይ እንዲህ ይላል፡-

እርሱም በመንገድ ሲወጣ አንድ ሰው ወደ እርሱ ሮጦ ተንበረከከለትና፡- ቸር መምህር ሆይ፥ የዘላለም ሕይወትን እወርስ ዘንድ ምን ላድርግ? ብሎ ጠየቀው። ኢየሱስም፡- ስለ ምን ቸር ትለኛለህ? ከአንዱ ከእግዚአብሔር በቀር ቸር ማንም የለም። ትእዛዛትን ታውቃለህ፤ አታመንዝር፥ አትግደል፥ አትስረቅ፥ በሐሰት አትመስክር፥ አታታልል፥ አባትህንና እናትህን አክብር አለው። (ማር. 10፡17-19)

ስለዚህ ኢየሱስ አምላክ አለመሆኑን ተናግሯል።

*ክርስቲያን፡* መጀመርያ አውዱን ስንመለከት ይህ ሰው መልካም በመሆን መዳኑን ማግኘት ይፈልግ ነበር። ኢየሱስ ራስህን በራስህ ማዳን እንድትችል የሚያስተምር መልካም አስተማሪ እንደሆነ እየነገረው ነው። የእግዚአብሔር ቃል ያንን ቀደም ሲል ግልጽ አድርጓል። ኢየሱስ ሕይወትን እናገኝ ዘንድ ልንከተለው የሚገባን መልካም አዳኝ መሆኑን በቀጣይነት አሳይቶታል። ሁለተኛ መላውን ማርቆስን ስናነብ ኢየሱስ አምላክነቱን ማሳየቱን እናያለን፣ ለምሳሌ 2፡7፣ 4፡41፣ 12፡35።

6. *ሙስሊም፡* ኢየሱስ አምላክ አለመሆኑን የሚያረጋግጠውን ሙግቴን ላቅርብልህ።

- አምላክ ሁሉን አዋቂ ነው።
- ኢየሱስ የምፅዓቱን ሰዓት አያቀውቅም (ማቴ. 26፡36)
- ስለዚህ ኢየሱስ አምላክ አይደለም።

*ክርስቲያን፡* ይህ በመጀመሪያ ጥሩ ይመስላል ነገር ግን ችግሩ የምትፈልገውን መደምደሚያ ለማግኘት የክርክርህን ወሰን ገድበሃል። ክርክሩ መምሰል ያለበት ይህ ነው።

- እግዚአብሔር ሁሉንም ነገር ያውቃል።
- በእግዚአብሔር የላቀ እውቀት እና በፍጥረት ውስጥ በሚኖረው አገላለጽ መካከል ልዩነት አለ (ዘፍ 18፡20-21፣ 11፡5፣ ቁርኣን 5፡94)።
- እግዚአብሔር ወልድ ሰው ሆኖ ሲወለድ፣ ሲያድግ፣ ሲማር፣ ሲጸልይ፣ ሲሞት፣ ሲነሳና ሲከበር በጊዜ ሂደት እየተገለጠ ነው።
- ኢየሱስ የሚመጣበትን ሰዓት አያውቅም።
- ስለዚህ፣ ይህ መለኮታዊ ልጅ በጊዜ ሂደት ራሱን የሚገልጥበት ምሳሌ ነው።

(ከእነዚህ ነጥቦች ውስጥ አንዳንዶቹን ማስተካከል ትፈልጉ ይሆናል ፣ ነገር ግን ተጨማሪ ማስረጃዎችን በማቅረብ የተለየ መልስ መስጠት ትችላላችሁ።)

# ምዕራፍ 5

## ሥላሴና ተውሒድ

እግዚአብሔር ማነው? ደግሞስ ምን ይመስላል? ይህ ሁሉም እምነቶችና ፍልስፍናዎች መልስ ሊሰጡበት የሚገባ ጉዳይ ነው። በክርስቲያኖች መረዳት መሠረት እግዚአብሔር አንድነትም ብዝሐነትም አለው። ይህም ማለት አንዱና የማይከፋፈለው የፈጣሪ ባሕርይ አብ፣ ወልድ እና መንፈስ ቅዱስ የተሰኙ ሦስት ልዩ አካላት አሉት። ጠርጡሊያኖስ የተሰኘ ቀዳሚ የቤተክርስቲያን አባት ይህንን የእግዚአብሔር አንድነትና ሦስትነት በመውሰድ "አሐዱ ሥሉስ" (Trinity) የሚል ቃል ፈጠረ። ሙስሊሞችም የፈጣሪን ማንነትና ባሕርይ በተመለከተ የራሳቸው መረዳት አላቸው። በእነርሱ መረዳት ፈጣሪ አንድነት ብቻ ያለው ሲሆን ይህ አንድነት ፍፁማዊ ነው። የእነርሱ የፈጣሪ መረዳት *ተውሒድ* ይሰኛል። በእስልምና መረዳት መሠረት አምላክ አባት አይደለም፣ ወልድም የለም፣ መንፈስ ቅዱስ መልአኩ ገብርኤል ነው።

በምዕራፍ 2 እንደተመለከትነው ቁርኣን ሙስሊሞች ሥላሴን እንዲቃወሙና ክርስቲያኖችንም እንዲገዳደሩ ስለሚያዛቸው ክርስቲያኖች ብዙ ጊዜ ይህንን አስተምሕሮ እንዲያብራሩና እንዲመክቱ በሙስሊሞች ይጠየቃሉ። በሌላ ወገን ደግሞ አብዛኞቹ ክርስቲያኖች ስለ ተውሒድ አስተምሕሮና ተያያዥ ስለሆኑት ጉዳዮች ሰምተው ስለማያውቁ ሙስሊሞች እንዲያብራሩና እንዲመክቱ አይጠይቁም። የሥላሴና የተውሒድ ርዕስ ሲነሳ ውይይቱ ወደ አንድ ወገን ብቻ ሲሆን ሙስሊሞች ብቻ ክርስቲያኖችን እንዲያብራሩና እምነታቸውን እንዲጠራጠሩ ይገዳደሯቸዋል።

ሙስሊሞች ሥላሴ ውስብስብ ነው፣ ምንም ትርጉም አይሰጥም፣ የአምላክንም አንድነት ያመቻምቻል፣ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥም የለም፤ ነገር ግን ተውሒድ ግልጽና እውነተኛ አሓዳዊነት ነው በማለት ክርስቲያኖችን ይሞግታሉ። ይህ ዓይነቱ ተግዳሮት ሲገጥማቸው ክርስቲያኖች እርግጠኝነት ማጣትና የዝግጅት ማነስ ስሜት ሊሰማቸው ይችላል። ሥለዚህ ክርስቲያን ከሙስሊም ጋር መወያየት ከፈለገ በሥላሴ ለምን እንደሚያምንና እንዴት ማብራራት እንዳለበት ማወቅ ይኖርበታል ማለት ነው። ይህ ደግሞ እንደ ማንኛውም አስፈላጊ ጥናት ጊዜን፣ ጉልበትንና ልምምድን የሚጠይቅ ነው። ይህንን ርዕሰ ጉዳይ ከዚህ ቀደም ካላጠናችሁት ማጥናት ይኖርባችኋል። ከሁሉም በላይ ደግሞ ስለ ፈጣሪያችን የማወቅ ጥረት በመሆኑ ጊዜ መስጠት አስፈላጊ ነው፤ ደግሞም አስደሳች ነው። ስለ እግዚአብሔር ባለን ዕውቀት ማደግ ከሕዝበ እግዚአብሔር የሚጠበቅ ነው። ስለዚህ በቀሪው ምዕራፍ ስለ ትምህርተ ሥላሴና ተውሒድ እንማማራለን፣ ከሙስሊም ጋርም እንዴት መነጋገር እንደምንችል እንመለከታለን።

# ከየት እንጀምር?

ሙስሊም ስለ ሥላሴ ቢጠይቃችሁ ከየት ነው የምትጀምሩት? ብዙ ጊዜ ስለ ሥላሴ ስንወያይ ከመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ እንጀምራለን። "ሰውን በመልካችን እንደ ምሳሌያችን እንፍጠር" ከሚለው እንጀምር ይሆናል (ዘፍ. 1፡26)። ወይንም ደግሞ የኢየሱስንና የመንፈስ ቅዱስን አምላክነት ከሚገልፁት ጥቅሶች እንጀምር ይሆናል። ከዚህም በመነሳት አንዱ አምላክ በብዝሐነት ራሱን እንደገለጠ እናስረዳ ይሆናል። ወይንም ደግሞ በስልታዊ ነገረ መለኮት ተጠቅመን በእግዚአብሔር ባሕርይና አካላት መካከል ያለውን ግንኙነት እናብራራ ይሆናል። የቅዱስ አትናቴዎስ የእምነት መግለጫ እንዲህ ያለ ሲሆን ማጥናት በእጅጉ አስፈላጊ ነው። በመጨረሻ አንድነትና ብዝሐነት እንዴት በአንድ ላይ ሊኖር እንደሚችል ለማስረዳት ምሳሌዎችን እንጠቀም ይሆናል።

እነዚህ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች፣ የስልታዊ ነገረ መለኮት ማብራሪያዎችና የእምነት መግለጫዎች እንዲሁም እነዚህ ምሳሌዎች ከሙስሊሞች ጋር ለምናደርጋቸው ውይይቶች ጠቃሚ ሊሆኑ ይችላሉ ነገር ግን ውይይት ለመጀመር የተሻሉ ቦታዎች እንዳልሆኑ መረዳት ችያለሁ። የነዚህ ችግሮች በተጠናቀቀ የሥላሴ አስተምሕሮ መጀመራቸውና ለማብራራት መሞከራቸው ነው። ይህ ብዙ ነገሮችን እንደ ቅድመ ግንዛቤ ያቀፉ ናቸው። መጀመርያ ግን መሆን ያለበት ለአስተምሕሮተ ሥላሴ መሠረታዊ የሆኑ የተወሰኑ ፅንሰ ሐሳቦችን መወያየት ነው። እነዚህን መሠረታዊ ፅንሰ ሐሳቦች መወያየት ካልቻልን በነዚህ ጉዳዮች ላይ ያለን ቅድመ ግንዛቤያዊ መረዳት አንዳችን ሌላችንን በትክክል እንዳንረዳ ጋሬጣ ይሆኑብናል። ስለ ሥላሴ ከማውራታችን በፊት የጋራ መሠረት ማነፅ ይኖርብናል።

ይህንን የጋራ መሠረት ለማስቀመጥ መወያየት ያሉብን እነዚህ መሠረታዊ ፅንሰ ሐሳቦች የሚከተሉት ናቸው፡-

- ስለ ሥላሴ ከየት ነው የምንማረው?
- የእግዚአብሔር አንድነትና ልዩነት።
- ፈጣሪ ራሱን መግለጥ አለበት።
- አካላዊ ኑባሬነት

ከዚያ መጽሐፍ ቅዱስ ስለ አብ፣ ወልድ መንፈስ ቅዱስ ምን እንደሚል ማየት እንችላለን።

አሁን እነዚህን መሠረታዊ ፅንሰ ሐሳቦች አንድ በአንድ እንመለከታቸዋለን። እነዚህን ከተመለከትን በኋላ ሥላሴን የሚገልጡ ማስረጃዎችን እናያለን።

# ስለ ሥላሴ ከየት ነው የምንማረው?

ስለ እስልምና መማር ከፈለግን ቁርአንና ሐዲስን ማንበብ እንደሁም ሙስሊሞችን መጠየቅ ያስፈልገናል። ስለ ቡዲሒዝም መማር ከፈለግን የቡድሃን ስብከቶች ማንበብና ቡዲሂስቶችን

መጠየቅ ያስፈልገናል። ስለ ክርስትናም መማር ከፈለግን መጽሐፍ ቅዱስን ማንበብና ክርስቲያኖችን መጠየቅ ያስፈልገናል። ይህ ግልፅ ቢሆንም ነገር ግን ብዙ ሙስሊሞች ቁርኣንን በማንበብ ክርስትናን መረዳት የሚችሉ ይመስላቸዋል።

ቁርኣን ስለ ክርስቲያኖችና ስለ እምነታቸው በብዙ ቦታዎች ላይ ይናራል። ሙስሊሞች ክርስቲያኖችን እንዲያናግሩ ስለሚዘጋጃቸው ሙስሊሞች ቁርኣንን በማንበብ ክርስትናን መረዳት የሚችሉና ለምን ስህተት እንደሆነ የሚውቁ መስሎ ሊሰማቸው ይችላል። ሆኖም ግን ቁርኣን ለክርስትና ያለው ዕይታ ውጪያዊ ሲሆን ክርስቲያናዊ አስተምሕሮዎችን በትክክል አያብራራም። የሥላሴ አስተምሕሮ ለዚህ ጥሩ ማሳያ ነው። በቁርኣን ውስጥ የአብ፣ የወልድና የመንፈስ ቅዱስ ጥምረት በፍፁም አልተጠቀሰም፤ በዚህ ፋንታ ቁርኣን ስለ ሦስት ሲናገር ፈጣሪ፣ ማርያምና ኢየሱስን ይጠቅሳል።

> እነዚያ አላህ የሦስት ሦስተኛ ነው ያሉ በእርግጥ ካዱ፤ ከአምላክም አንድ አምላክ እንጅ ሌላ የለም፤ ከሚሉትም ነገር ባይከለከሉ፣ ከነሱ እነዚያን የካዱትን አሳማሚ ቅጣት በእርግጥ ይነካቸዋል። ወደ አላህ አይመለሱምና ምሕረትን አይለምኑትምን? አላህም መሐሪ አዛኝ ነው። (ቁርኣን 5:73-75)[17]
>
> አላህም፡- የመርየም ልጅ ዒሳ ሆይ አንተ ለሰዎቹ ፡- እኔንና እናቴን ከአላህ ሌላ ሁለት አምላኮች አድርጋችሁ ያዙ ብለሃልን? በሚለው ጊዜ (አስታውስ)፤ ጥራት ይገባህ፤ ለኔ ተገቢዬ ያልሆነን ነገር ማለት ለኔ አይገባኝም፤ ብዬው እንደሆነም በእርግጥ አውቀኸዋል፤ በነፍሴ ውስጥ ያለውን ሁሉ ታውቃለህ፤ ግን ዘንድ ያለውን አላውቅም፤ አንተ ሩቆችን ሁሉ በጣም ዐዋቂ አንተ ብቻ ነህና ይላል። (ቁርኣን 5:116)

ይህ የሥላሴ መረዳት በቁርኣን ውስጥ እንዴት ሊገኝ እንደቻለ ምሑራን ከመግባባት አልደረሱም።[18] ምክንያቱ ምንም ይሁን ምን ሥላሴ እግዚአብሔር፣ ማርያምና ኢየሱስ ከመሆን ይልቅ አብ፣ ወልድና መንፈስ ቅዱስ ነው። ይህ የሚያሳየው ሙስሊሞች ቁርኣንን በማንበብ የክርስትናን አስተምሕሮ መረዳት እንደማይችሉ ነው። ክርስትናንና ሥላሴን በትክክል መረዳት ከፈለጉ መጽሐፍ ቅዱስን ማንበብና ክርስቲያኖችን መስማት ይኖርባቸዋል። ይህ ነጥብ ለክርስቲያን ግልፅ ቢሆንም ለሙስሊሞች ግን ግልፅ አይደለም። ክርስትናን ከቁርኣን መማር እንደሚችሉ ያስባሉ። ይህ በፅኑ የሚያምኑት ቅድመ ግንዛቤያቸው ነው።

---

17 ሁቱም ምግብን የሚበሉ የሚለው ሟች መሆናቸውን ያሳያል።

18 ትክክለኛው ክርስትና ለማደነ አስተምሕሮ ከሰጠው ማርያም የአምላክ እናት ናት ከሚለው ወይንም ከቆሊራዳውያን አመለካከት የመጣ ሊሆን ይችላል።

## የእግዚአብሔር አንድነትና ልዩነት

የአንድነትና የብዝሐነት ፅንሰ ሐሳብ ስለ ሥላሴ ከሚያወሩ ብዙ መጻሕፍት መካከል ጥቂቶቹ ብቻ የሚጀምሩበት ርዕሰ ጉዳይ ነው። ሆኖም ስለ ሥላሴ ከቤተክርስቲያን ውጪ ከሚገኙ ወገኖች ጋር ለመነጋገር መሠረታዊው ፅንሰ ሐሳብ ነው። እያንዳንዱ ሃይማኖትና ፍልስፍና ስለ አንድነትና ስለ ብዝሐነት የየራሱ መረዳት አለው።

በቡዲሂዝም[19] ውስጥ በዙርያችን የሚገኘው ብዝሃነት ምኞታችንን የሚበትን ነው። እነዚህን ፍላጎቶች መግደልና መነጠል ያስፈልገናል። ስንነጠል ወደ አንድነት እንገባለን።

ሂንዱኢዝምም ተመሳሳይ ነው። ሁሉም ብዝሐነት ሐሳባዊ እንጂ ተጨባጭ አይደለም። ሁሉም አንድ ነው። ይህንን አንድነት ለማግኘት ማሰላሰልና ከዓለም የሐሳብ ብተና መላቀቅ ያስፈልጋል።

ፊዚክስ የአንድነትና የብዝሐነት ጉዳይ ነው። በፊዚክስ መሠረት በመጀመርያ ሁሉም ነገር ነጠላ አንድ የነበረ ሲሆን ከዚያም በመስፋት ይህንን ታላቅ አፅናፈ ዓለም አስገኘ። የሒሳብ ግብ ይህንን ብዝሐነት በበማብራራት ለሁሉም የሚሆን አንድ ትወራ ማዘጋጀት ነው።

በክርስትና ውስጥ የመጨረሻው እውነታ የሆነው እግዚአብሔር የባሕርይ አንድነትና የማንነት ልዩነት እንዳለው እናምናለን። አንድነትና ልዩነትን በጋራ እንይዛለን።

በሕዝብ ደረጃ እስልምና አንድ አምላክ እንዳለ ብቻ ሳይሆን ይህ አምላክ በአንድነት መሆኑን ያስተምራል በአንድነትም ሊገለጽ ይገባዋል ይላል።

> የአላህ ፍጹም አንድነት አስተምህሮ የእስልምና ዋና ነገር ነው። ሁሉም ሌሎች የእስልምና ሕግጋት፣ እምነቶችና ትእዛዛት በዚህ መሠረት ላይ የተገነቡ ናቸው። እርሱን ከወሰዳችሁት ከሃይማኖት የሚቀር ነገር አይኖርም።[20]

ሙስሊሞች ብዙ ጊዜ ሲናገሩት ከምንሰማው በተጻራሪ ከአፍታ በኋላ እንደምንመለከተው እስልምናም ለብዝሐነትና ለአንድነት የራሱ ትርጓሜ አለው። እንደዚሁ ክርስትና የእግዚአብሔርን አንድነትና ብዝሐነት የተመለከተ ፅንሰ ሐሳብ አለው። ይህም የማይከፋፈለውን አንዱን መለኮታዊ ባሕርይ የሚጋሩ ሦስት አካላት አሉ የሚል ነው።

እነዚህን ምሳሌዎች የጠቀስኩበት ምክንያት የትኛውም ሰው ክርስቲያን ሆነም አልሆነም አንድነትና ብዝሐነት እንዴት በጋራ እንደሚኖሩ ማብራራት እንዳለበት ለማመልከት ያህል ነው። ችግሩ ግን ክርስቲያኖችም ሆኑ ሙስሊሞች ይህንን ፅሰ ሐሳብ የማብራራት ግዴታ ያለባቸው ክርስቲያኖች ብቻ እንደሆኑ ማሰባቸው ነው።

---

19 Buddha’s *Sermon of Fires* ይመልከቱ።

20 God is One, Dublin: Discover Islam, Information Pamphlet.

ይህ እውነት አይደለም። ሁሉም ሰው ምላሽ መስጠት አለበት። ይህንን ስትገነዘቡ ከሙስሊሞች ጋር የምታደርጉት ውይይት ይቀየራል። ክርስቲያኖች የፈጣሪን አንድነትና ብዝሐነት አብራርተው ሙስሊሞች ከዚህ ኃላፊነት ነፃ የሚሆኑበት መንገድ አይኖርም። ሁላችንም ኃላፊነት አለብን - ሙስሊሞች ግን በዚህ ረገድ ድክመት አለባቸው።

ስለ ሥላሴ ከማውራታችን በፊት መወያየት የሚገባን ሁከተኛው ፅንሰ ሐሳብ ይህ ነው። ይህም ክርስቲያኖችም ሆኑ ሙስሊሞች ስለ ፈጣሪ አንድነትና ብዝሐነት የየራሳቸው መረዳት ስላላቸው ሁለቱም ማብራርያ መስጠት አለባቸው። ለአብዛኞቹ ክርስቲያኖችና ሙስሊሞች ይህ አዲስ ርዕስ ነው። ስለዚህ ጉዳይ የማሰብም ሆነ የመናገር ልማድ የለንም። አሁን ይህ ርዕሰ ጉዳይ ለክርስቲን ሙስሊም ውይይት ያለውን አንድምታ እንመለከታለን።

የሥላሴ አስተምሕሮ እግዚአብሔር አንድነትና ብዝሐነት እንዳለው ይናገራል። ይህም ማለት አንዱ የማይከፋፈለው መለኮታዊ ባሕርይ ልዩ የሆኑ ሦስት አካላት አሉት ማለት ነው። ክርስቲያኖች ይህንን አንድነትና ልዩነት በተለያዩ ምሳሌዎችና መጽፍ ቅዱሳዊ ማብራርያዎች ሲያሳዩ የተለመደው የሙስሊሞች ምላሽ በሁለት ምክንያቶች ይህንን ማብራርያ አለመቀበል ነው።

1. በሙስሊሞች እምነት መሠረት የፈጣሪ አንድነት የትኛውንም ልዩነት ወይም ብዝሐነት የማይቻል ስለሚያደርግ ሥላሴ የፈጣሪን አንድነት ያመቻምቻል።
2. ክርስትና ለሥላሴ የሚሰጠው ማብራርያ ለመረዳት የሚያዳግት ውስብስብ ሲሆን ተውሒድ ግን ቀላልና ለመረዳት የማይከብድ ነው።

እነዚህ ሁለቱ ምክንያቶች ሙስሊም መሪዎች በክርስትና ላይ ተቃውሞዎችን በሚያቀርቡባቸው መድረኮች ሁሉ ላይ በተደጋጋሚ የሚደመጡ ናቸው። ሆኖም ሙስሊም መሪዎች ይህንን በአደባባይ ቢናገሩም ሙስሊም ሊቃውንትና ፈላስፎች ግን ጉዳዩ እንደዚያ ቀላል እንዳልሆነ ያውቃሉ። ፈጣሪ ያለምንም ብዝሐነት አንድነት ብቻ ያለው እንደሆነ መናገር ሙስሊም ሊቃውንት ሊያስቡባቸው የሚገቡ በቀላል የማይታዩ አመክንዮአዊ ችግሮችን ያስከትላል። ችግሩ ቁርኣን (እንዲሁም መጽሐፍ ቅዱስ) ፈጣሪን በአንድነት ብቻ ሳይሆን በብዝሐነትም ጭምር መግለጻቸው ነው።

በቁርኣን ውስጥ ይህ የተገለጠው በሚከተሉት መንገዶች ነው፡- ፈጣሪ መንፈሱን በሰው ውስጥ መተንፈሱ፣[21] የተለያዩ ባሕርያተ መለኮት ያሉት በመሆኑ (ኃይል፣ ሉኣላዊነት፣ ዕውቀት፣ ንግግር፣ ሕይወት፣ ፈቃድ፣ ዕይታ፣ መስማት፣ እጆች፣ ፍቅር፣ ፍትህ፣ ትዕግስት፣ ቁጣ)፣ እንዲሁም በተለያዩ መንገዶች መሥራቱ ናቸው። እነዚህ ሁሉ የብዝሐነትና የልዩነት መገለጫዎች ናቸው። ስለዚህ ፈጣሪን በአንድነት ብቻ መግለፅ የማይሆን ነው።

---

[21] ቁርኣን 38፡71 ጀምሮ

እስልምና እንደሚያስተምረው እያንዳንዱ በቁርኣን ውስጥ የተገለጡት የአላህ ባሕርያት የተለያዩ ሲሆኑ አንዱን የፈጣሪ ማንነት በሙላት ይካፈላሉ። ይህ አንድነትና ብዝሐነት እንዴት ነው መታየት ያለበት? ተከታዩ ጥቅስ እንደሚያመለክተው በፈጣሪ አንድነት ላይ የሚያተኩረው የተውሒድ አስተምሕሮ ይህንን ብዝሐነት ማብራራት አስቸጋሪ ሆኖበታል፡-

> የዚህ መጽሐፍ ርዕስ ትኩረት የሚስብ ቢሆንም ውስብስብ ሊሆን የሚችል ነው፤ ጉዳዩን መወያየት ግን ቀላል አይደለም [...] የአላህ አንድነት፣ ባሕርያትና ተግባራትን የተመለከተውን ይህንን ርዕሰ ጉዳይ ማለት ነው።[22]
>
> አሽአሪዎች እንደሚናገሩት የፈጣሪ ባሕርያተ መለኮት የእርሱ ምንነት (essence) አይደሉም፤ ከምንነቱም የተለዩ አይደሉም። እነዚህ ባሕርያተ መለኮት የፈጣሪ ምንነት ናቸው ከተባለ (ሙዕተዚላዎችና ፈላስፎች እንደሚናገሩት)፣ ይህ ማለት የፈጣሪ ምንነት ባሕርያተ መለኮት የሉትም ምክንያቱም ከምንነቱ ጋር አንድ ስለሆኑ ለማለት እንገደዳለን (ባሕርያተ መለኮትና ምንነት የተለያዩ እንደሆኑ ይታሰባል)። ይሁን እንጂ የፈጣሪ ባሕርያተ መለኮት ከምንነቱ የተለዩ እንደሆኑ መናገር እነዚህ ባሕርያት ለብቻቸው መኖር የሚችሉና ሊጠፉ የሚችሉ እንደሆኑ ስለሚያሳስብ ችግር ይፈጥራል። እነዚህ ባሕርያት በእርግጠኝነት ዘላለማዊ ናቸውና። እንደ እውነቱ ከሆነ በምንነቱና በባሕርያቱ መካከል <u>ልዩ የሆነ ግንኙነት አለ።</u> ባሕርያቱ በምንነቱ ውስጥ የሚገኙ ናቸው፣ በዘላለማዊነቱ ውስጥ ዘላለማውያን ናቸው። ሁል ጊዜም በዚያ ሁኔታ ከእርሱ ጋር ኖረዋል፤ ለዘላለምም ይኖራሉ። (Muhammad Salih Farfur, *The Beneficial Message & The Definitive Proof in the Study of Theology*, (Trans: Wesam Charkawi) 2010, p. 119, underline added.)

ይህ ጥቅስ ሙስሊም ሊቃውንት የፈጣሪን ብዝሐነት ከአንድነቱ ጋር ለማስታረቅ የሚያደርጉትን ጥረት በምሳሌነት የሚያሳይ ነው። ይህ ማለት ሙስሊም ሊቃውንት ፈጣሪ አንድነት ያለው ብቻ መሆኑን አያምኑም ማለት ነው፤ ፈጣሪ የብዝሐነት ገፅታም እንዳለው ዕውቅና ይሰጣሉ። ይህ ነጥብ በእጅጉ ወሳኝ ነው ምክንያቱም ሙስሊሞችም የፈጣሪን አንድነትና ብዝሐነት አስታርቀው ማብራራት ሲጠበቅባቸው ብዙ ጊዜ ግን እንዲያብራሩ የሚጠበቅባቸው ክርስቲያኖች ብቻ ስለሚሆኑ።

ከላይ የተጠቀሰው ጸሐፊ ፈጣሪ አንድ ሆኖ ሳለ ብዙ ባሕርያት ሊኖሩት እንዴት ቻሉ የሚለውን አስቸጋሪ ጥያቄ ለመመለስ በሁለቱ መካከል ልዩ የሆነ ግንኙነት እንዳለ ገልጿል። ነገር ግን *ልዩ የሆነ ግንኙነት አለ* ብሎ መናገር ማብራርያ አይደለም። አንድነትና ብዝሐነት እውነት እንደሆኑና የሆነ ዓይነት ግንኙነት እንዳላቸው ብቻ አምኖ መቀበል ነው። የተለያዩ የሙስሊም የአመለካከት ጎራዎች ይህንን ችግር ለመፍታት የተለያዩ ዘዴዎችን ዘርግተዋል ፤

---

[22] Yassin Roushdy, Allah - The Divine Nature, London: Dar Al Taqwa, 1999, p. 1.

ይህም ውጤቱ የተለያዩ የተውሒድ ግንዛቤዎችን ፈጥሯል፡ ፡ አራቱ ቡድኖች የአሽአሪ፣ የሙታዚላ ፣ የቀጥታ ተርጓሚዎች፣ የሱፊና የኢርፋኒ ዋነኛ ቡድኖች ናቸው። የሙስሊም መሪዎች ሥላሴን ይነቅፋሉ ፣ በሌላ በኩል ደግሞ በተውሒድ ለመስማማት አልቻሉም!

አንዱ ታዋቂ ምሳሌ የቁርኣንን ባሕርይ የተመለከተ ነው። ሙስሊሞች ቁርኣን የፈጣሪ ንግግር ነው ይላሉ ስለዚህ የአምላክ ባሕርይ ነው። ስለዚህ ቁርኣን የተፈጠረ ነው ያልተፈጠረ? ሙዕተዚላውያን ቁርኣን የፈጣሪን ያለመፈጠር ባሕርይ እንዲካፈል ስላልፈለጉ ቁርኣን ፍጡር እንደሆነ ይናገራሉ። ይሁን እንጂ አሽዓሪዎች ቁርኣን የፈጣሪ ንግግር በመሆኑ ከባሕርያቱ መካከል አንዱ ነው ስለዚህ ፈጣሪ ባሕርያቱን ስላልፈጠረ ቁርኣን ፍጡር ሊሆን አይችልም የሚል እሳቤ አላቸው።

አሽአሪዎች በዚህ ምላሽ ላይ መመራመርን በታወቀው የአረብኛ አባባል *ቢ ላ ካይፍ* (እንዴት ተብሎ ሳይጠየቅ) በማለት ይዘጉታል። የአሽዓሪዎች አቋም በዚህ ዘመን የእስልምና ትክክለኛው አቋም እንደሆነ ታምኖበት ተቀባይነትን አግኝቷል። እንግዲህ አስቡት። የአምላክ እስላማዊ ግንዛቤ ዋና ጉዳይ እንዴት ይሆናል ብላችሁ እንድትጠይቁ አይፈቀድም። ይህንን ስትረዱ በሥላሴ ላይ የሚሰነዘሩት ኢስላማዊ ትችቶች መሠረተ ቢስ እንደሆኑ ይገባችኋል።

የዚህ ሐተታ ዋናው ነጥብ ይህ ነው፤ ሙስሊሞች ሥላሴ የፈጣሪን አንድነት እንደሚያመቻምችና ለመረዳት ውስብስብ እንደሆነ ይነግሯቸዋል። ነገር ግብ እኔ እንደገለጥኩት እስልምና በአንድነትም በብዝሐነትም የሚያምን ቢሆንም ይህንን እንደ ማመቻመች አይቆጥርም። ሙስሊሞች ይህንን አንድነትና ብዝሐነት ማስታረቅ ተወሳስቦባቸዋል። በርግጥ ስምምነትም የላቸውም።

ስለዚህ እስልምና በፈጣሪ አንድነት ብቻ ያምናል በሚለው የሙስሊሞች ብሒል አትታለሉ። እንደርሱ አያምንም። እስልምናም እንደ ክርስትና ሁሉ ስለ ፈጣሪ አንድነትና ብዝሐነት የራሱ የሆነ እሳቤ አለው። ስለዚህ ሙስሊሞች ሥላሴን ለመቃወም ምንም ዓይነት አመክንዮአዊ መሠረት የላቸውም።

ሙስሊም፡- ሥላሴ ትርጉም አይሰጥም፤ የፈጣሪን አንድነት ያናጋል። እስልምና ግን ቀላል ነው።

ክርስቲያን፡ እስልምና ቀላል አይደለም። በቢላ ካይፍ ላይ የተመሠረተ ሲሆን የእስልምና መሪዎች ተውሒድን እንዴት መረዳት እንዳለባቸው አይስማሙም። ሥላሴ እንዴት ትርጉም እንደሚሰጥ ላሳይህ።

# ፈጣሪ ራሱን መግለጥ አለበት

እስልምና አመክንዮአዊ ሃይማኖት እንደሆነ በመናገር ይኮፈሳል። በተለይም በአንድ አምላክ ማመኑን በዚህ መንገድ ይመለከታል። በቁርኣን 6፡74-82 ላይ ይህንን የሚገልጥ የታወቀ ታሪክ አለ። ይህ ታሪክ አብርሃም ከዋክብትን፣ ጨረቃንና ፀሐይን ማምለክ ከጀመረ በኋላ እውነተኛ አማልክት አለመሆናቸውን በመረዳት ወደ እውነተኛው ፈጣሪ እንደተመለሰ ይናገራል። ታሪኩ እስልምና ስለ አምላክ ያለውን አመለካከት እንዴት እንደሚያረጋግጥ ለማሳየት የታለመ ነው።

ሙስሊሞች ተውሒድና እስልምና ምክንያታዊ እንደሆኑ ከመማር አልፈው ሥላሴ አመክንዮአዊ እንዳልሆነና ከምክንያታዊነት ጋር እንደሚጣረስ ይማራሉ። የሰው ምክንያታዊ አስተሳሰብ ደግሞ ይህንን እንደሚያረጋግጥ ያምናሉ። ይህ እንግዲህ የሰው አእምሮ ፈጣሪን መመርመርና ማንነቱና ባሕርዩ ምን እንሚመስል ሙሉ በሙሉ መረዳት ይችላል የሚል ቅድመ ግንዛቤ ላይ የተመሠረተ ነው። ይህ ቅድመ ግንዛቤ ሐሰት ነው፤ ይህንን ደግሞ ለሙስሊም ጓደኞችሁ ማሳየት መቻል አለባችሁ። ፈጣሪ ከፍጥረት ውጪ ስለሆነ በኛ አእምሮ አይመረመርም። ፈጣሪ ከጊዜና ከቦታ ሦስትዮሻዊ ፅንፍ የመጠቀ በመሆኑ በምርመራችን ስር ሊገባ አይችልም። ፈጣሪ ምስጢር ነው። ስለዚህ ከሰው አስተሳሰብ በመነሳት ፈጣሪን ሙሉ በሙሉ እንገነዘባለን ማለት አመክንዮአዊ አይደለም።

> እነሆ፥ እግዚአብሔር ታላቅ ነው፥ እኛም አናውቀውም። የዘመኑም ቍጥር አይመረመርም። (ኢዮብ 36፡26)
>
> ሰማይ ከምድር ከፍ እንደሚል፥ እንዲሁ መንገዴ ከመንገዳችሁ አሳቤም ከአሳባችሁ ከፍ ያለ ነው። (ኢሳይያስ 55፡9)
>
> በእግዚአብሔር ጥበብ ምክንያት ዓለም እግዚአብሔርን በጥበብዋ ስላላወቀች፥ በስብከት ሞኝነት የሚያምኑትን ሊያድን የእግዚአብሔር በጎ ፈቃድ ሆኖአልና። (1ቆሮንቶስ 1፡21)
>
> ዓይኖች አያገኙትም፤ (አያዩትም)። እርሱም ዓይኖችን ያያል። እርሱም ርኅራኄው ረቂቁ ውስጠ ዐዋቂው ነው። (ቁርኣን 6፡103)

ፈጣሪ በፍጥረቱ ውስጥ ከሚሠራው ሥራ በመነሳት ስለ እርሱ የተወሰነ ነገር ማወቅ እንችላለን ነገር ግን ስለ እርሱ አካላዊ ኑባሬ፣ ሐሳብ፣ ዕቅድ፣ ዓላማና መለኮታዊ ባሕርይ ለማወቅ እርሱ ራሱን ለእኛ መግለጥ ያስፈልገዋል። እግዚአብሔር በነቢያቱና ሐዋርያቱ በተነገረው የመጽሐፍ ቅዱስ ቃሉ ይህንን አድርጓል።

ምሥጢሩ ለአምላካችን ለእግዚአብሔር ነው፤ የተገለጠው ግን የዚህን ሕግ ቃሎች ሁሉ እናደርግ ዘንድ ለእኛ ለዘላለምም ለልጆቻችን ነው። (ዘዳግም 29፡29)

በእውነት ጌታ እግዚአብሔር ምሥጢሩን ለባሪያዎቹ ለነቢያት ካልነገረ በቀር ምንም አያደርግም። (አሞፅ 3፡7)

ስለዚህ ፈጣሪያችን ምንደሚመስል ለማወቅ ስለ ራሱ የተናገረውን መስማት ያስፈልገናል። ፈጣሪ ምን መምሰል እንዳለበት ከራሳችን እሳቤ በመነሳት መደምደም ሳይሆን እርሱ ራሱ ምን እንደሚመስል እንዲነግረን ልናደምጠው ይገባል።

ሙስሊም፡- እስልምና አመክንዮአዊ ሃይማኖት ነው።

ክርስቲያን፡- የሰው አእምሮ ስለ እግዚአብሔር ሁሉንም ነገር ሊያውቅ ይችላል እያልክ ነው?

ሙስሊም፡- አይ መገለጥ ያስፈልገናል።

ክርስቲያን፡ እስማማለሁ ለዚህም ነው ክርስቲያኖች ሁሉንም ነቢያት የሚያነቡት። እግዚአብሔርን ለማወቅ እግዚአብሔርን መስማት አለብን።

## ማንነታዊ ኑባሬነት

ክርስቲያኖች እንደሚናገሩት አንዱ መለኮታዊ ባሕርይ በሦስት ልዩ አካላት ይኖራል። ሙስሊሞች ደግሞ እንዲህ በማለት የተለመደውን ምላሻቸውን ይሰጣሉ፤ "ሦስት እንዴት አንድ ይሆናል? ይህ ትርጉም የሚሰጥ አይደለም።" መጋቢዎች እንኳ ለጉባኤያቸው እንዲህ ሲሉ ሰምቻቸዋለሁ፤ ይህ ደግሞ ያስደነግጠኛል ምክንያቱም እውነት ስላልሆነ።

ምላሽ ሊሰጥበት የሚገባው ቅድመ ግንዛቤ እንዲህ የሚለው ነው፤ *አንድ ማንነት አንድ አካል ብቻ እንዳለው ግልፅ ስለሆነ ሦስት በአንድ የሚለው ሐሳብ ትርጉም የማይሰጥ መሆኑ ግልፅ ነው።* ይህ በብዙ ሰዎች ዘንድ የሚገኝ ቅድመ ግንዛቤ ሲሆን በተለይም ሙስሊሞች ሥላሴን ቦታ እንዳይሰጡት አድርጓቸዋል። ይህ ቅድመ ግንዛቤ በአንክሮ እስከታጤኑት ድረስ ትክክል መምሰሉ አያስገርምም ምክንያቱም ማንነቶችና አካላት ያላቸው ቁርኝት ግልፅ አይደለምና። ይህንን ርዕሰ ጉዳይ የበለጠ በጥልቀት ለመረዳት አራት አካላዊ ኑባሬዎችን ከግምት አስገብተን እንመለከታለን።

1. መጽሐፍ ቅዱስም ሆነ ቁርኣን የሰውን ማንነት ሲገልፁ እንደ ነጠላ ሳይሆን የአካል፣ የነፍስ፣ የመንፈስ፣ የአእምሮና የልብ ጥምረቶች እንደሆነ ነው። ይህ ማለት የሰብዓዊነት የተለያዩ ማዕከላት አሉ ማለት ነው። በእርግጥ ቁርኣን ነፍሳችን ለኛ መናገር እንደምትችል ይናገራል።

> የሰውን ልጅ የፈጠርነው እኛው ነን። ነፍሱ የምትጐተጉተውን (እንኳ ሳይቀር) ጠንቅቀን እናውቃለን። እኛ ለርሱ ከደም ጋን ጅማቱ ይበልጥ የቀረብን ነን። (ቁርኣን 50፡16)

ስለዚህ የሰው ሰብዓዊነት አንድነትና ብዝሐነትን ያቀፈ ነው ማለት ነው።

2. አሁንም የሰውን ኑባሬ ከተለየ አቅጣጫ እናስብ። ቁርኣንም ሆነ መጽሐፍ ቅዱስ የሰዎች ኑባሬ ፈጣሪንም የሚያካትት እንደሆነ ይገልጣሉ። ክርስቲያኖች እግዚአብሔር አምላካችን በውስጣችን እንደሚኖር እናውቃለን፡

> ብትወዱኝ ትእዛዜን ጠብቁ። እኔም አብን እለምናለሁ ለዘላለምም ከእናንተ ጋር እንዲኖር ሌላ አጽናኝ ይሰጣችኋል። (ዮሐንስ 14፡16)

> ኢየሱስም መለሰ አለውም፡- የሚወደኝ ቢኖር ቃሌን ይጠብቃል፤ አባቴም ይወደዋል ወደ እርሱም እንመጣለን በእርሱም ዘንድ መኖሪያ እናደርጋለን። (ዮሐንስ 14፡23)

> በእርሱም እናንተ ደግሞ ለእግዚአብሔር መኖሪያ ለመሆን በመንፈስ አብራችሁ ትሠራላችሁ። (ኤፌሶን 2፡22)

> ልጆች ሆይ፥ እናንተ ከእግዚአብሔር ናችሁ አሸንፋችኋቸውማል፥ በዓለም ካለው ይልቅ በእናንተ ያለው ታላቅ ነውና። (1ዮሐንስ 4፡4)

እግዚአብሔር በመንፈስ በኛ ውስጥ ስለሚኖር ክርስቲያኖች በዚህ ደስ እንሰኛለን።

እኛ ነጠላ አይደለንም፤ እግዚአብሔር በማንነቱ በውስጣችን ይኖራል፣ በሐሳባችን ውስጥ፣ በማንነታችን ውስጥ ይገኛል። ቁርኣንም ፈጣሪ በውስጣችን ስለመኖሩ የራሱ የሆነ እሳቤ ያለው ይመስላል። ምክንያቱም ፈጣሪን የሩቅ ሳይሆን ለሰው ልጆች በቅርበት የሚገኝ እንደሆነ ይናገራልና።

> የሰውን ልጅ የፈጠርነው እኛው ነን።ነፍሱ የምትጐተጉተውን (እንኳ ሳይቀር) ጠንቅቀን እናውቃለን።እኛ ለርሱ ከደም ጋን ጅማቱ ይበልጥ የቀረብን ነን። (ቁርኣን 50፡16)

ስለዚህ በሰውኛ ልምምዳችን በውስጣችን ከአንድ በላይ አካል እንዳለ እንገነዘባለን። ይህ የሰብዕ እሳቤ የመጽሐፍ ቅዱስም ሆነ የቁርኣን መረዳት ነው።

ስለዚህ አንድ ማንነት አንድ አካል ብቻ አለው የሚለው ቅድመ ግንዛቤ ትክክል አይደለም።

3. በመጨረሻም ከሰው ልጆች የላቀና ያለፈ ኑባሬ ስላላቸው መንፈሳውያን ፍጥረታት አስቡ። ይህንን መናፍስት በሰው ውስጥ በማደራቸው ማየት እንችላለን። በዚህ ሁኔታ አንድ ወይም ከዚያ በላይ መናፍስት አንዱን ሰው ተቆጣጥረውት በውስጡ ሊኖሩ ይችላሉ። ይህም

ብዙ በአንድነት ማለት ነው። ስለዚህ አሁንም ስለ ማንነታዊ ኑባሬ ስናስብ አንድ ማንነት አንድ አካል ብቻ እንዳለው ግልፅና የተረጋገጠ አይደለም።

እነዚህ ምሳሌዎች ለሥላሴ እንደ ማሳያ የቀረቡ አይደሉም። እግዚአብሔር ልዩ ነው፤ እርሱን የሚመስል ምንም ነገር የለም። የእርሱ አካላዊ ኑባሬ ፈፅሞ የተለየ ነው። ይልቁኑ እነዚህ ምሳሌዎች ማንነቶችና አካላት በተለያየ መልክ መኖር መቻላቸውን ለማሳየት የታለሙ ናቸው። ይህንን መረዳት ሥላሴን ለመረዳት መሠረታዊና ወሳኝ ነው። ከሙስሊም ጓደኞቻችሁ ጋር ስለ ምንነቶች ተፈጥሮ ልትነጋገሩ ያስፈልጋል። አንድ ማንነት አንድ አካል ብቻ እንዳለው የተረጋገጠና ግልፅ አለመሆኑን ለማስረዳት ቀደም ሲል የተጠቀሱትን ምሳሌዎች መጠቀም ትችላላችሁ። ሥላሴ ከአመክንዮ አንፃር የሚያስኬድ መሆኑንና ሥላሴን ለመቃወም የሚያስችል አመክንዮአዊ መሠረት እንደሌላቸው አሳዩአቸው።

አካላት የተለያየ ኑባሬ ሊኖራቸው ይችላል የሚለው ሦስተኛው መሠረት ነው።

## አብ፣ ወልድ፣ መንፈስ ቅዱስ

በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ የሚያምኑት ክርስቲያኖች ብቻ እንደሆኑ በሙስሊሞች ቢታሰብ አይገርምም ነገር ግን ከክርስትና የቀደመ እምነት ነው። ከኢየሱስ በፊት በነበሩት ነቢያት ዘመን የነበረ አስተምሕሮ ነው። ተከታዮቹ ጥቅሶች ከኢየሱስ ዘመን ከነበሩት ቅዱሳት መጻሕፍት የተወሰዱ ጥቅሶች ናቸው።

መጀመርያ ሕዝበ እሥራኤል የእግዚአብሔር ልጅ መባሉንና እግዚአብሔርም በመንፈሱ አማካይነት በመካከላቸው መመላለሱን እንመለከታለን።

> ፈርዖንንም፦ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ እሥራኤል የበኵር ልጄ ነው፤ ይገዛልኝ ዘንድ ልጄን ልቀቅ አልሁህ፤ አንተም ትለቅቀው ዘንድ እንቢ አልህ፤ እነሆ እኔ የበኵር ልጅህን እገድላለሁ ትለዋለህ። (ዘጸአት 4፡22)
>
> ደንቆሮ ብልሃተኛም ያልሆንህ ሕዝብ ሆይ፥  ለእግዚአብሔር ይህንን ትመልሳለህ? የገዛህ አባትህ አይደለምን?  የፈጠረህና ያጸናህ እርሱ ነው። (ዘዳግም 32፡6)
>
> በልቅሶ ወጡ እኔም በማጽናናት አመጣቸዋለሁ፤ በወንዝ ዳር በቅን መንገድ አስኬዳቸዋለሁ፥ በእርሱም አይሰናከሉም፤ እኔ ለእሥራኤል አባት ነኝና፥ ኤፍሬምም በኵሬ ነውና። (ኤርምያስ 31፡9)
>
> ሕፃን በነበረ ጊዜ ወደድሁት፥ ልጄንም ከግብጽ ጠራሁት። (ሆሴዕ 11፡1)
>
> እርሱም እንዲህ ብሎ የቀደመውን ዘመን አሰበ፦ የበጎቹን እረኛ ከባሕሩ ያወጣው ወዴት ነው ያለ? ቅዱስ መንፈሱንም በመካከላቸው ያኖረ ወዴት ነው ያለ? (ኢሳይያስ 63፡11)

ስለዚህ ከክርስትና በፊት በነበሩት ነቢያት ዘመን አብ፣ ወልድ እና መንፈስ ቅዱስ እግዚአብሔር ፈጣሪ ከሕዝቡ ጋር የነበረውን ሕበርት የገለጠበት መንገድ ሆኖ እናገኛለን።

ሁለተኛ የእሥራኤል ንጉሥ፣ የዳዊት ልጅ፣ የተቀባው፣ የእግዚአብሔር ልጅ ተብሎ ተጠርቷል፣ እግዚአብሔርም አምላኩ እንደሆነና በመንፈስ የተሞላ መሆኑ ተገልጧል።

> ዕድሜህም በተፈጸመ ጊዜ ከአባቶችህም ጋር ባንቀላፋህ ጊዜ፥ ከወገብህ የሚወጣውን ዘርህን ከአንተ በኋላ አስነሣለሁ፥ መንግሥቱንም አጸናለሁ። እርሱ ለስሜ ቤት ይሠራል፤ የመንግሥቱንም ዙፋን ለዘላለም አጸናለሁ። እኔም አባት እሆነዋለሁ፥ እርሱም ልጅ ይሆነኛል፤ ክፉ ነገርም ቢያደርግ፥ ሰው በሚቀጣበት በትርና በሰው ልጆች መቀጫ እገሥጸዋለሁ፤ (2ሳሙኤል 7፡12-14)

> እርሱም፡- ልጅ ይሆነኝ ዘንድ መርጬዋለሁና፥ እኔም አባት እሆነዋለሁና ልጅህ ሰሎሞን ቤቴንና አደባባዮቼን ይሠራል። (1ዜና 28፡6)

> ከፊትህ አትጣለኝ፥ ቅዱስ መንፈስህንም ከእኔ ላይ አትውሰድብኝ። (መዝሙር 51፡ 11)

> ትእዛዙን እናገራለሁ፤ እግዚአብሔር አለኝ፡- አንተ ልጄ ነህ፥ እኔ ዛሬ ወለድሁህ። (መዝሙር 2፡7)

ስለዚህ ከክርስትና ዘመን በፊት በነበሩት ነቢያት ዘመን አብ፣ ወልድ፣ መንፈስ ቅዱስ የሚሉት እግዚአብሔር ከተቀባው ንጉሥ ጋር የነበረውን ግንኙነት ለመግለጥ አገልግሏል ማለት ነው።

የእግዚአብሔር ልጅ መሆን ትርጉሙ ምንድነው? ፈጣሪ አባትህ ነው፣ አንተ በምድር ላይ እርሱን የምትወክል ወኪል ነህ፣ ምስሉን ታሳያለህ፣ ባሕርዩን ልታሳይና ክብሩን ልትገልጥ ይገባሃል ማለት ነው። ልክ እንደ እኛው ሁሉ እራኤል ይህንን ማድረግ ተስኗታል። ስለዚህ እግዚአብሔር እውነተኛ ልጁን፣ የእርሱን ትክክለኛ ምሳሌና በፍፁምነት እርሱን መግለጥ የሚችለውን እንሚልክ ተስፋን ሰጠ። ይህ የቅዱሱ መሲህ መምጣት ተስፋ ነው።

> ሕፃን ተወልዶልናልና፥ ወንድ ልጅም ተሰጥቶናልና፤ አለቅነትም በጫንቃው ላይ ይሆናል፤ ስሙም ድንቅ መካር፥ ኃያል አምላክ፥ የዘላለም አባት፥ የሰላም አለቃ ተብሎ ይጠራል። ከዛሬ ጀምሮ እስከ ዘላለም ድረስ በፍርድና በጽድቅ ያጸናውና ይደግፈው ዘንድ በዳዊት ዙፋንና በመንግሥቱ ላይ አለቅነቱ ይበዛል፥ ለሰላሙም ፍፃሜ የለውም። የእግዚአብሔር ቅንዓት ይህን ያደርጋል። (ኢሳይያስ 9፡6-7)

> ለአሕዛብም ምልክትን ያቆማል፥ ከእሥራኤልም የተጣሉትን ይሰበስባል፥ ከይሁዳም የተበተኑትን ከአራቱ የምድር ማዕዘኖች ያከማቻል። (ኢሳይያስ 11፡2)

እግዚአብሔር ቅዱሱን መሲህ እንደሚልክ ቃል ሲገባ በመንፈስ የተሞላ እውነተኛ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ ተነግሮናል። ይህ ብሉይ ኪዳን የሚደመድምበት ተስፋ ነው። ስለዚህ የነቢያትን መጻሕፍት ስናነብ እግዚአብሔር ስለ አብ፣ ወልድና መንፈስ ቅዱስ ደረጃ በደረጃ እንደገለጠና የበለጠ ደግሞ ለመግለጥ እንዳቀደ እንመለከታለን።

የነዚህ ምሳሌዎች ዓላማ ትርጉማቸው ምንም ይሁን ምን የአብ፣ የወልድና የመንፈስ ቅዱስ ግንኙነቶች መኖራቸውን መግለጥ ነው። በቤተክርስቲያን ታሪክ ጅማሬ አካባቢ ስለ ኢየሱስ ማንነትና ባሕርይ የተለያየ አመለካከት የነበራቸው ቡድኖች ነበሩ ነገር ግን ሁሉም የአብ፣ የወልድና የመንፈስ ቅዱስን ሕብር ተቀብለዋል። ማንም ይህንን የካደ አልነበረም። ልዩነታቸው የዚህን ሕብር ባሕርይ እንዴት እንረዳ በሚለው ላይ ነበር። ነገር ግም ሙሐመድ ይህ ሕብር መኖሩን ክዷል። በቁርአን ውስጥ ፈጣሪ አባት አይደለም፣ ማንም ደግሞ በየትኛውም መልኩ የፈጣሪ ልጅ በተብሎ ሊጠራ አይችልም፤ መሆን የምትችሉት ነገር ባርያ ብቻ ነው።

> ይሁዶችና ክርስቲያኖችም እኛ የአላህ ልጆችና ወዳጆቹ ነን አሉ። ታዲያ በኀጢአቶቻችሁ ለምን ያሰቃያችኋል? አይደላችሁም እናንተ ከፈጠራችሁ ሰዎች ናችሁ፣ በላቸው፤ ለሚሻው ሰው ይምራል፤ የሚሻውንም ሰው ይቀጣል፤ የሰማያትና የምድርም በመካከላቸውም ያለው ሁሉ ንግሥና የአላህ ብቻ ነው። መመለሻም ወደርሱ ብቻ ነው። (ቁርኣን 5፡18)
>
> እላንተ የመጽሐፉ ሰዎች ሆይ! በሃይማኖታችሁ ወሰንን አትለፉ፤ በአላህም ላይ እውነትን እንጂ አትናገሩ፤ የመርየም ልጅ አልመሲሕ ዒሳ፣ የአላህ መልክተኛ፣ ወደ መርየም የጣላት (የሁን) ቃሉም ከርሱ የሆነ መንፈስም ብቻ ነው፤ በአላህና በመልክተኞቹም እመኑ (አማልክት) ሦስት ናቸው አትበሉም፤ ተከልከሉ ለናንተ የተሻለ ይሆናልና፤ አላህ አንድ አምላክ ብቻ ነው። ለርሱ ልጅ ያለው ከመሆን የጠራ ነው። በሰማያትና በምድር ያለ ሁሉ የርሱ ነው። መመኪያም በአላህ በቃ። (ቁርኣን 4፡171)
>
> ለአልረሕማን ልጅን መያዝ አይገባውም። በሰማያትና በምድር ያለዉ ሁሉ (በትንሣኤ ቀን)፣ ለአልረሕማን ባሪያ ኾነዉ የሚመጡ እንጂ ሌላ አይደሉም። (ቁርኣን 19፡92-92)

የአብ፣ የወልድ፣ የመንፈስ ግንኙነት በነቢያት እና በሐዋርያት ሁሉ የተሰበከ ሲሆን ሥላሴን ለመረዳት አስፈላጊ መሠረት ነው። ከሙስሊም ወዳጃችሁ ጋር የሚከተለውን ጥያቄ መወያየት ትችላላችሁ፡- ነብያት ያስተማሩት ትምህርት ሆኖ ሳለ ቁርኣን ስለ አብ፣ ወልድና መንፈስ የማይናገረው ለምንድን ነው?

## አንድ አምላክ

የተለያዩ ቅድመ ግንዛቤዎችን በማየት በቂ ጊዜ ወስደናል። አሁን ደግሞ ክርስቲያኖች ለምን በሥላሴ እንደሚያምኑ እንመለከታለን። መጽሐፍ ቅዱስ አንድ አምላክ ብቻ መኖሩንና አምላካችንን አባት ብለን ልንጠራው እንደሚገባ በግልፅ ይናገራል።

> እኔ እግዚአብሔር ነኝ ከእኔም በቀር አምላክ የለም። (ኢሳይያስ 45: 5)

ክርስትና አሃዳዊ ሃይማኖት ነው። መጽሐፍ ቅዱስም የሚለው ይህንኑ ነው። የሃይማኖታችን መግለጫ ይህ ነው።

ሁለተኛው ነጥብ ይህ እግዚአብሔር በጊዜ ሂደት ራሱን ለህዝቡ የሚገልጥ መሆኑ ነው።

> እግዚአብሔርም ሙሴን ተናገረው አለውም። እኔ እግዚአብሔር ነኝ፤ ለአብርሃምም ለይስሐቅም ለያዕቆብም ሁሉን እንደሚችል አምላክ ተገለጥሁ፤ ነገር ግን ስሜ እግዚአብሔር አልታወቀላቸውም ነበር። (ዘጸአት 6፡2-3)

ቅዱሳት መጻሕፍትን ስናነብ እግዚአብሔር ራሱን እንደ አብ፣ ወልድ እና መንፈስ ሲገልጥ እናያለን። አሁን እያንዳንዳቸው ለምን እግዚአብሔር እንደሆኑ በማስረጃ እናያለን። ሙስሊም ወዳጆችሁን አብ፣ ወልድ፣ መንፈስ ቅዱስ የሚለው የነቢያት ትምህርት ሆኖ ሳለ በእስልምና ተቀባይነት የሌለው ለምንድነው? ብላችሁ ልትጠይቁት ትችላላችሁ።

## አብ

> ለእኛስ ነገር ሁሉ ከእርሱ የሆነ እኛም ለእርሱ የሆንን አንድ አምላክ አብ አለን፥ ነገር ሁሉም በእርሱ በኩል የሆነ እኛም በእርሱ በኩል የሆንን አንድ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ አለን። (1ቆሮንቶስ 8፡6)
>
> እንግዲህ እናንተስ እንዲህ ጸልዩ፡- በሰማያት የምትኖር አባታችን ሆይ … (ማቴዎስ 6፡9)

መጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ አባትነትን ለእግዚአብሔር ይሰጣል።

## መንፈስ ቅዱስ

መንፈስ ቅዱስም የፈጣሪ ባሕርያት ሁሉ እንዳሉት ተገልጿል፡- አእማሬ ኩሉ (ሁሉን አዋቂ) ነው (ኢሳ. 40፡13-14)፣ ምሉዕ በኩላሄ (በሁሉም ቦታ ይገኛል) (መዝ. 139፡7) እንዲሁም የእግዚአብሔር የመፍጠር፣ የማኖር፣ የማነቃቃትና የማስነሳት ችሎታ ሁሉ በእርሱ አማካይነት ነው - እርሱ ከሃሊ ኩሉ (ሁሉን የሚችል) ነው። መንፈስ ቅዱስ በእግዚአብሔር እንደተፈጠረ ሆኖ አልተገለጸም ነገር ግን የእግዚአብሔር የራሱ እስትንፋስ እንደሆነ ነው። ይህ ማለት እግዚአብሔር የገዛ ራሱን እስትንፋስ ፈጥሯል ለማለት ስለማንችል ከእግዚአብሔር ባሕርይ ጋር አንድ ነው ማለት ነው።

“እግዚአብሔር አምላክም ሰውን ከምድር አፈር አበጀው፤ በአፍንጫውም የሕይወት እስትንፋስን እፍ አለበት ሰውም ሕያው ነፍስ ያለው ሆነ።” (ዘፍ. 2፡7)

“የእግዚአብሔር መንፈስ ፈጠረኝ፥ ሁሉንም የሚችል የአምላክ እስትንፋስ ሕይወት ሰጠኝ።” (ኢዮብ 33፡4)

“በእግዚአብሔር ቃል ሰማዮች ጸኑ፥ ሠራዊታቸውም ሁሉ በአፉ እስትንፋስ።” (መዝ. 33፡6

መንፈስ ቅዱስ የሆነ ዓይነት ኃይል ብቻ አይደለም፤ አካል እንዳለው ተገልጿል። አፅናኝ ተብሏል (ዮሐ. 14፡16-17)፣ ይናገራል ይልካል (ሐዋ. 13፡2-4)፣ ይመርጣል (ሐዋ. 20፡28)፣ ያስተምራል (ዮሐ. 14፡26)፣ ይሠራል ይሰጣል (1ቆሮ. 12፡11)፣ ሰዎች ሊዋሹትና ሊፈትኑት ይችላሉ (ሐዋ. 5፡3፣ 9)፣ ያዝናል (ኢሳ. 63፡10፣ ኤፌ. 4፡30)፣ ሰዎች ሊሰድቡት ይችላሉ (ማቴ. 12፡31)፣ ይመሰክራል (ዮሐ. 15፡26፣ ሮሜ 8፡16)፣ ይማልዳል (ሮሜ 8፡26-27)፣ ወደ ቅድስና ይጠራል (ያዕ. 4፡5)፣ ይመረምራል ያውቃል (1ቆሮ. 2፡10-11)፣ ጌታ ነው (2ቆሮ. 3፡ 18)።

ስለዚህ መጽሐፍ ቅዱስ መንፈስ ቅዱስን ኃይል ብቻ እንደሆነ አይናገርም። ልዩ የሆነ የእግዚአብሔር አካል እንደሆነ ይናገራል።

## መለኮታዊው አምሳል፣ መልእክተኛና ልጅ

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ካሉት አስደናቂ ገጽታዎች አንዱ እግዚአብሔርን ማየት የሚችል የለም መባሉ ነው።

መቼም ቢሆን እግዚአብሔርን ያየው አንድ ስንኳ የለም፤ (ዮሐ 1፡18)

እርሱ ብቻ የማይሞት ነው፤ ማንም ሊቀርበው በማይችል ብርሃን ይኖራል፤ አንድ ሰው እንኳ አላየውም ሊያይም አይቻለውም፤ ለእርሱ ክብርና የዘላለም ኃይል ይሁን፤ አሜን። (1 ጢሞቴዎስ 6:16 እና 1:17)

ሆኖም መጽሐፍ ቅዱስ ሰዎች አምላክን እንዳዩት ይናገራል።

በቀትርም ጊዜ እርሱ በድንኳኑ ደጃፍ ተቀምጦ ሳለ እግዚአብሔር በመምሬ የአድባር ዛፍ ተገለጠለት። (ዘፍ 18፡1)

ሙሴም አሮንም ናዳብም አብዩድም ከእስራኤልም ሰባ ሽማግሌዎች ወጡ፤ የእስራኤልንም አምላክ አዩ፤ ከእግሩም በታች እንደ ሰማይ መልክ የሚያበራ እንደ ብሩህ ሰንፔር ድንጋይ የሚመስል ወለል ነበረ። (ዘጸ 24፡9-10)[23]

---

[23] እንዲሁም፣ ዘፍጥረት 3፡8፣ ዘኍልቍ 12፡6-8፣ ሕዝቅኤል 1

> ንጉሡ ዖዝያን በሞተበት ዓመት እግዚአብሔርን በረጅምና ከፍ ባለ ዙፋን ላይ ተቀምጦ አየሁት፥ የልብሱም ዘርፍ መቅደሱን ሞልቶት ነበር። (ኢሳ 6፡1)

ስለዚህም ከዘላለም በላይ የሆነው እግዚአብሔር ወደ ፍጥረት የሚልከው ሌላ ወኪል እንዳለው እናያለን፤ ይህም መለኮታዊ መልክ ወይም መልክተኛው ነው።[24] ይህ መለኮታዊ ምስል እንደ እግዚአብሔር የሚመለክና የሚናገር ሲሆን ከማይታየው ከእግዚአብሔር አብ የተለየ ነው። ይኸውም፣ ለብሉይ ኪዳን የእግዚአብሔር ሰዎች፣ ስለ እግዚአብሔር የነበራቸው መረዳት ሦስትዮሽ እንጂ ነጠላዊ አልነበረም፤ እግዚአብሔር አብ፣ መንፈሱ፣ እና መለኮታዊ መልእክተኛው ወደ ፍጥረት ይገቡ ነበረ። ወንጌል ይህ መለኮታዊ መልእክተኛ መሆኑን እውነተኛው ልጅ ኢየሱስ መሆኑን ይገልጻል። የኢሳይያስን ራዕይ በማጣቀስ (ኢሳ 6) ዮሐንስ እንዲህ ሲል ጽፏል፡-

> ክብሩን ስለ አየ ኢሳይያስ ይህን አለ፥ ስለ እርሱም ተናገረ። ከዚህም ጋር ከአለቆች ደግሞ ብዙዎች በእርሱ አመኑ፤ ነገር ግን ከምኵራብ እንዳያስወጡአቸው በፈሪሳውያን ምክንያት አልመሰከሩለትም፤ ከእግዚአብሔር ክብር ይልቅ የሰውን ክብር ወደዋልና። (ዮሐንስ 12፡41-43)

ሐዋርያው ጳውሎስ እንዲህ ሲል ጽፏል፡-

> እርሱም የማይታይ አምላክ ምሳሌ ነው። የሚታዩትና የማይታዩትም፥ ዙፋናት ቢሆኑ ወይም ጌትነት ወይም አለቅነት ወይም ሥልጣናት፥ በሰማይና በምድር ያሉት ሁሉ በእርሱ ተፈጥረዋልና ከፍጥረት ሁሉ በፊት በኵር ነው። ሁሉ በእርሱና ለእርሱ ተፈጥሮአል። (ቆላስይስ 1፡18))

በኢየሱስ መምጣት ይህ እውነተኛ ልጅ ተገልጧል። ከድንግል መወለዱ ኢየሱስ ልዩ ልጅ መሆኑን ያሳያል። ማንም ልጅ በዚህ መንገድ አልመጣም፡-

> መልአኩም መልሶ እንዲህ አላት፡- መንፈስ ቅዱስ በአንቺ ላይ ይመጣል፥ የልዑልም ኃይል ይጸልልሻል ስለዚህ ደግሞ ከአንቺ የሚወለደው ቅዱስ የእግዚአብሔር ልጅ ይባላል። (ሉቃስ 1፡35)

ኢየሱስ እራሱ ከተለመደው የዳዊት ልጅ በላይ መሆኑን ተናግሯል።

> ኢየሱስም በመቅደስ ሲያስተምር መልሶ እንዲህ አለ፡- ጻፎች ክርስቶስ የዳዊት ልጅ ነው እንዴት ይላሉ? ዳዊት ራሱ በመንፈስ ቅዱስ፡- ጌታ ጌታዬን፡- ጠላቶችህን

---

[24] አንቶኒ ሮጀርስ በመጋቢት 2, 2019 በ Know Reformed Presbyterian ባደረገው ንግግር ይህን ግልጽ ሆኖልኛል https://knoxreformedpres.org/sermon-library/

የእግርህ መረገጫ እስካደርግልህ ድረስ በቀኜ ተቀመጥ አለው አለ። (ማርቆስ 12፡ 35-37)

ወንጌላት የኢየሱስን ፍጹም አምላክነት በተለያዩ መንገዶች ያውጃሉ። በመጀመሪያ ነቢያቱን ኢሳይያስንና ሚልክያስን በመጥቀስ እንዲሁም እነዚህ ጥቅሶች ለኢየሱስ የተነገሩ መሆናቸውን በማስረዳት ነው፡-

> የአዋጅ ነጋሪ ቃል። የእግዚአብሔርን መንገድ በምድረ በዳ ጥረጉ፥ ለአምላካችንም ጐዳና በበረሀ አስተካክሉ። (ኢሳ 40፡3)

> እነሆ፥ መልእክተኛዬን እልካለሁ፥ መንገድንም በፊቴ ያስተካክላል፤ እናንተም የምትፈልጉት ጌታ በድንገት ወደ መቅደሱ ይመጣል፤ የምትወዱትም የቃል ኪዳን መልእክተኛ፥ እነሆ፥ ይመጣል፥ ይላል የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር። (ሚል 3፡1)

እነዚህ ጥቅሶች ያህዌ ወደ ህዝቡ እንደሚመጣ ይናገራሉ። ወንጌላት ኢየሱስን ለመግለጽ ይጠቀሙባቸዋል (ማቴ 3፡3፣ 11፡10፣ ማርቆስ 1፡2-3፣ ሉቃስ 3፡4-6፣ ዮሐ. 1፡23)። ኢየሱስ ወደ እስራኤል የሚመጣው ያህዌ ነው።

በሁለተኛ ደረጃ በወንጌላት መሠረት ኢየሱስ እግዚአብሔር የሚያደርገውን ልክ እግዚአብሔር በሚያደርገው መንገድ ያደርጋል፡-

- ሰዎችን ኃጢአት ይቅር ብሏል፡ ማር. 2፡7-5
- የእርሱ መገኘት ሰዎች ኃጢአታቸውን እንዲረዱ አድርጓል፡ ሉቃ 5፡8
- በቃሉ ብቻ ማዕበሉኝ ፀጥ አሰኝቷል፡ መዝ. 89፡9-10፣ 104፡7፣ 107፡23-30 › ማር. 4፡35
- በውኀ ላይ ተራምዷል፡ ኢዮብ 9፡8 › ማር. 6፡43-
- መናፍስትን አዟል፡ 1ነገ. 22 › ማር. 5፡7-8
- የዳኑትን መርጧል፡ ማቴ. 11፡27
- በደመና ላይ ሆኖ ለፍርድ ይመጣል፡ ዘጸ. 33፡26፣ ኢሳ. 19፡1፣ መዝ. 68፡4፣ መዝ. 104፡1-3 › ማር. 14፡62

በሦስተኛ ደረጃ፣ አብ የሚያደርገው ሁሉ በወልድ በኩል ብቻ የሚደረግ ነው (ዮሐ. 1፡3፣ 3፡ 34-35፣ 5፡19-20፣ 16፡15)። ወልድ ከአብ ጋር እኩል ይከበራል (ዮሐ. 5፡23)። 20፡28፣ ራእይ 5፡13)።

በአራተኛ ደረጃ ኢየሱስ የእግዚአብሔር ማዕርጋት ተሰጥቶታል።

- እርሱ የእግዚአብሔር ሕዝብ ባል ነው፡ ኢሳ. 54፡5፣ ኤር. 3፡14፣ ሕዝ. 16፡32፣ ሆሴ. 1፡2 (2፡19-20) › ማር. 2፡19፣ ዮሐ. 3፡29

- እርሱ የዘጸአት 3፡14ቱ “እኔ ነኝ” ነው ፣ 8፡58
- የሕይወት ራስ ነው፡ ሐዋ. 3፡15
- ያሕዌ፡ ኢሳ. 6 ፣ ዮሐ. 12፡38-42፤ ኢዩ. 2፡32 ፣ ሐዋ. 2፡21፤ 38፤ 4፡12፤ ሮሜ 10፡ 12-13
- የመጀመርያና የመጨረሻ፡ ኢሳ. 44፡6 ፣ ራዕይ 1፡17-18፤ 22፡13

እነዚህ ጥቅሶች የኢየሱስን አምላክነት ያሳያሉ። ቅዱስና እውነተኛ የእግዚአብሔር ልጅ ለሆነው ለጌታችን ለኢየሱስ ክርስቶስ ማንነት ምስክሮች ናቸው። ነገር ግን ይህ ሌላ ጥያቄን ያጭራል፤ አብና ወልድ ሁለቱም አምላክ ሆነው እንዴት አንድ አምላክ ብቻ ሊኖር ይችላል? ወንጌል ለዚህ ምላሽን የሚሰጠን የኢየሱስን የልጅነት ባሕርይ በማብራራት ነው።

> በመጀመርያው ቃል ነበረ፤ ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ፤ ቃልም እግዚአብሔር ነበረ። … ቃልም ሥጋ ሆነ ፀጋንና እውነትን ተሞልቶ በእኛ ዘንድ አደረ። (ዮሐንስ 1፡1፤ 14)

ኢየሱስ *የእግዚአብሔር ቃል* ተብሏል። ይህ አገላለፅ የሚከተለውን ያሳያል፡-

- አሓዳዊነት ነው፡ እግዚአብሔርና ቃሉ ናቸው።
- ኢየሱስ በፍጥረት ከእግዚአብሔር አልመጣም ምክንያቱም እግዚአብሔር ቃሉን አልፈጠረምና፤ ይልቁኑ ኢየሱስ የእግዚአብሔር ቃል በሚመጣበት መንገድ ከእግዚአብሔር መጥቷል፤ ይህም በባሕርዩ ነው። ኢየሱስ በባሕርይ ከእግዚአብሔር ጋር አንድ ነው።
- ኢየሱስ ልዩ የሆነ አካል አለው።

ሌላው ወሳኝ የኢየሱስ ገለፃ በሚከተለው ጥቅስ ውስጥ ይገኛል፡-

> እርሱም (ልጁ) የክብሩ መንጸባረቅና የባሕርዩ ምሳሌ ሆኖ ሁሉን በስልጣኑ ቃል እየደገፈ ኃጢአታችንን በራሱ ካነፃ በኋላ በሰማያት በግርማው ቀኝ ተቀመጠ … (ዕብራውያን 1፡3)

በዚህ ቦታ ኢየሱስ የእግዚአብሔር ክብር መንጸባረቅ እንደሆነ ተነግሯል። አሁንም ሦስቱን ተመሳሳይ ነጥቦች እንመለከታለን፡-

- ሓዳዊነት ነው፤ እግዚአብሔርና ክብሩ።
- ኢየሱስ በፍጥረት ከእግዚአብሔር አልመጣም ምክንያቱም እግዚአብሔር ክብሩን አልፈጠረምና፤ ይልቁኑ ኢየሱስ የእግዚአብሔር ክብሩ በሚመጣበት መንገድ ከእግዚአብሔር መጥቷል፤ ክብሩ ከባሕርዩ የሚመነጭ ነው። ስለዚህ ኢየሱስ በባሕርይ ከእግዚአብሔር ጋር አንድ ነው።
- ኢየሱስ ልዩ የሆነ አካል አለው።

ስለዚህ ኢየሱስ ከእግዚአብሔር ጋር ያለው ግንኙነት የአሓዳዊነትን እምነት የጠበቀ ሲሆን በአካል ግን ልዩ ነው።

## ሁሉንም ማዋሓድ - ሥላሴ

እግዚአብሔር ራሱን ሲገልጥ የአብ፣ የወልድና የመንፈስ ቅዱስ መገለጥ በመሆን ነው። አንዱን የእግዚአብሔርን ባሕርይ የሚካፈሉ ሦስት ልዩ አካላት። ክርስቲያኖች ከዚህ የመጽሐፍ ቅዱስ መገለጥ የተነሳ ነው እግዚአብሔርን በሥላሴነት ለመረዳት የቻሉት። ይህ መረዳት ነቢያትን ሁሉ ከማንበብ የመነጨ ሲሆን የእግዚአብሔርን አንድነትና በአንድነቱ ውስጥ ያለውን ብዝሐነት የሚያሳይ ነው።

የአንዱ እግዚአብሔር ተግባር ከአብ፣ በወልድ እና በመንፈስ ቅዱስ በኩል ነው። አብ ያቅዳል፣ ወልድ ይሠራል፣ መንፈስ ፍጹም ያደርጋል። ሦስቱም ያልተከፋፈለ መለኮታዊ ባሕርይ ሙሉ በሙሉ ስለሚካፈሉ የአካል ቅደም ተከተል ዝቅተኛነትን ወይም መገዛትን አያመለክትም።

## ቁርኣንና ሥላሴ

ቁርኣን ሥላሴን ሲቃወም የፈጣሪ፣ የማርያምና የኢየሱስን ጥምረት እየተቃወመ ነው፡-

> እነዚያ አላህ የሦስት ሦስተኛ ነው (*) ያሉ በእርግጥ ካዱ፤ ከአምላክም አንድ አምላክ እንጅ ሌላ የለም፤ ከሚሉትም ነገር ባይከለከሉ፣ ከነሱ እነዚያን የካዱትን አሳማሚ ቅጣት በእርግጥ ይነካቸዋል። ወደ አላህ አይመለሱምና ምሕረትን አይለምኑትምን? አላህም መሐሪ አዛኝ ነው። የመርየም ልጅ አልመሲሕ ከበፊቱ መልክተኞች በእርግጥ ያለፉ የሆነ መልክተኛ እንጅ ሌላ አይደለም፤ እናቱም በጣም እውነተኛ ናት፤ (ሁለቱም) ምግብን የሚበሉ ነበሩ፤ አንቀጾችን ለነርሱ (ለከሐዲዎች) እንዴት እንደምናብራራ ተመልከት፤ ከዚያም (ከውነት) እንዴት እንደሚመለሱ ተመልከት። (ቁርኣን 5፡73-75)

ይህ ክርስቲያኖች የሚያምኑት ሥላሴ አይደለም ነገር ግን አጠቃላይ ፅንሰ ሐሳቡን ይከዳል። ይሁን እንጂ ቁርኣን ሥላሴን ቢክድም ጠቂት የሥላሴ አስተምሕሮ ቅሪቶች በቁርኣን ውስጥ ይገኛሉ።

የመጀመርያው ምሳሌ ኢየሱስ በጭቃ ወር መሥራቱን የሚናገረው የቁርኣን ትረካ ነው። ልዩ ከሆኑ እግዚአብሔር ባሕርያት መካከል አንዱ ፈጣሪነት ነው። ፈጣሪነቱ ከሁሉም ነገር ልዩ የሚያደርገው ሲሆን መታወቂያው ነው። ይሁን እጂ በቁርኣን ውስጥ ኢየሱስ ይህ የፈጣሪ

ልዩ ባሕርይ እንዳለውና በተመሳሳይ መንገድ ሲፈፅም እንመለከታለን።[25] ይህ እግዚአብሔር አዳምን ከአፈር አበጅቶት የሕይወትን እስትንፋስ እፍ ካለበት ጋር ተመሳሳይ ነው።

> ጌታህ «ለመላእክት እኔ ሰውን ከጭቃ ፈጣሪ ነኝ ባለ ጊዜ» (አስታውስ)። «ፍጥረቱንም ባስተካከልኩና ከመንፈሴ በነፋሁበት ጊዜ ለእርሱ ሰጋጆች ኾናችሁ ውደቁ» (አልኩ)።መላእክትም መላውም ባንድነት ሰገዱ። ኢብሊስ ብቻ ሲቀር። ኮራ፤ ከከሓዲዎቹም ነበር። (አላህም) «ኢብሊስ ሆይ! በሁለት እጆቼ (በኃይሌ) ለፈጠርኩት ከመስገድ ምን ከለከለህ? (አሁን) ኮራህን? ወይስ (ፊቱኑ) ከትዕቢተኞቹ ነበርክ?» አለው። (አላህም) አለው «አንተ ከሚቆዩት ነህ።» (ቁርኣን 38፡71-75)

ኢየሱስ ከፈጠረበት መንገድ ጋር ፍፁም ተመሳሳይ ነው፡-

> ወደ እሥራኤልም ልጆች መልክተኛ የደርገዋል፤ (ይላልም) ፡-እኔ ከጌታዬ ዘንድ በታምር መጣኋችሁ። እኔ ለናንተ ከጭቃ አንደ ወፍ ቅርጽ እፈጥራለሁ፤ በርሱም እተነፍስበታለሁ፤ በአላህም ፈቃድ ወፍ ይሆናል። በአላህም ፈቃድ ዕዉር ሆኖ የተወለደን፥ ለምጻኛንም፥ አድናለሁ፤ ሙታንንም አስነሳለሁ። የምትበሉትንና በቤታችሁ የምታደልቡትንም ሁሉ እነግራችኋለሁ፤ የምታምኑ እንደሆናችሁ ለእናንተ በዚህ ዉስጥ በእርግጥ ታምር አለበት። (ቁርኣን 3፡49)

ኢየሱስ ወፎችን ከጭቃ የመፍጠሩ ትረካ ከጥንታዊ የክርስቲያን አፈታሪክ የተቀዳ በመሆኑ[26] የኢየሱስን አምላክነት ያሳያል፤ እናም ትምህርተ ሥላሴን በመጠኑ የሚያንጸባርቅ ነው።

በቁርኣን ውስጥ ኢየሱስ በፈጣሪ ፈቃድ መሠረት ይህንን እንደፈፀመ ቢናገርም ዳሩ ግን መፍጠር ፈጣሪ ከማንም ጋር የማይጋራው መለያው በመሆኑ ምክንያት ይህ የኢየሱስን አምላክነት ውድቅ አያደርግም። ፈጣሪ ይህንን ችሎታ ለኢየሱስ ካጋራው ኢየሱስ የፈጣሪን ልዩ ችሎታ ተጋርቷል ማለት ነው። ፈጣሪ ይህንን ችሎታ ለሌሎች የሚያጋራ ከሆነ ልዩ መሆኑ ይቀራል። ስለዚህ የሥላሴ አስተምሕሮ ቅሪት በቁርኣን ውስጥ ይገኛል።

ከሙስሊም ወዳጆችሁ ጋር እነዚህን ጥቅሶች በማንበብ ኢየሱስ የመፍጠሩን ጉዳይ ልትወያዩበት ትችላላችሁ። ሆኖም ግን እናንተ ራሳችሁ ፅንሰ ሐሳቡን በትክክል መረዳታችሁን አስቀድማችሁ እርግጠኞች ሁኑ።

ሁለተኛው ምሳሌ ኢየሱስ “የአላህ ቃል” የሚለውን ማዕርግ ማግኘቱ ነው።[27]

---

[25] አንዳንድ ሰዎች ሙሴ በትሩን በወረወረና እባብ በሆነች ጊዜ ተመሳሳይ ተዓምር እንደሠራ ይነግሩኛል (ዘጸ. 4)፤ ነገር ግን ሙሴ እግዚአብሔር በሠራው ተዓምር በመደናገጥ ከእባቡ ሸሽቷል። ይህ ታሪክ እግዚአብሔር አዳምን በፈጠረበት በዚያው ሁኔታ ኢየሱስ መፍጠሩን ከሚናገረው *የቶማስ ወንጌል* ከተሰኘው የአፖክሪፋ መጽሐፍ ከተቀዳው የቁርኣን አፈታሪክ ሙሉ በሙሉ የተለየ ነው።

[26] የቶማስ ወንጌል

እርሱም በጸሎት ማድረሻው ክፍል ቆሞ ሲጸልይ መላእክት ጠራቻው። "አላህ በየሕያ ከአላህ በኾነ ቃል [ኢየሱስ][28] የሚያረጋግጥ ጌታም ድንግልም ከደጋጎቹ ሲኾን ያበስርሃል" በማለት (መላእክት ጠራቻው) (ቁርኣን 3፥39)

የመርየም ልጅ አልመሲሕ ዒሳ፣ የአላህ መልክተኛ፣ ወደ መርየም የጣላት (የሁን)[29] ቃሉም ከርሱ የሆነ መንፈስም ብቻ ነው። (ቁርኣን 4፥171)

በባለፈው ክፍል እንደተመለከትነው ኢየሱስን የእግዚአብሔር ቃል ብሎ መጥራት የሥላሴ አስተምሕሮ አካል ነው። ይህ የሚያሳየው በመፈጠር ከእግዚአብሔር መምጣቱን ሳይሆን እንደ ቃሉ ከእግዚአብሔር ጋር በባሕርይ አንድ መሆኑን ነው። ኢየሱስን የእግዚአብሔር ልጅ ብሎ የመጥራት ቀዳሚው ሐሳብ ይህ ነበር (ዮሐ. 1፥1)። በቁርኣን ውስጥ ያለው ፅንሰ ሐሳብ የተለየ ነው። ቁርኣን ኢየሱስን የአላህ ቃል ብሎ ሲጠራው የእርሱ መፈጠር የአላህ ቃል ወደ ማርያም የመምጣቱ ውጤት እንደነበር ለመግለፅ ነው። የዚህ ችግሩ የሰው ልጆች በሙሉና ሁሉም ነገር በፈጣሪ ቃል/ትዕዛዝ የተፈጠሩ በመሆኑ[30] ኢየሱስን የፈጣሪ ቃል ብሎ መጥራት ምንም የጠለየ ነገር የለውም - ነገር ግን በግልፅ እንደሚታየው ልዩ ማዕርግ ነው። ኢየሱስን የእግዚአብሔር ቃል ብሎ ለመጥራት ተቀባይነት ያለው ምክንያት ቀዳሚው የሥላሴ አስተምሕሮ ብቻ ነው። እናም ይህ በቁርኣን ውስጥ የሚገኝ የአስተምሕሮተ ሥላሴ ሌላኛው ቅሪት ነው።

አሁንም ስለ አላህ ቃል የሚናገሩትን እነዚህን የቁርኣን ጥቅሶች ከሙስሊም ወዳጃችሁ ጋር በማንበብ ጥያቄዎችን ማንሳት ትችላላችሁ።

የመጨረሻው ምሳሌ ስለ መንፈስ ቅዱስ የተነገረው ነው። በእስልምና ውስጥ መንፈስ ቅዱስን በተመለከተ የተለያዩ ሐሳቦች አሉ። አብዛኞቹ እርሱ መልአኩ ገብርኤል እንደሆነ ቢናገሩም ቁርኣን ግን ይህንን አይልም።

በቁርኣን ውስጥ ቅዱሱ መንፈስ የአላህ እስትንፋስ ሲሆን ለአፋም ሕይወትን የሰጠበ ት ነው (ቁርኣን 15፥29)

ፈጣሪ መንፈሱን ከመገለጥ ጋር ልኳል (ቁ. 16፥102)፣ የኢየሱስን ልደት ለማብሰር የፈጣሪ ወኪል በመሆንም ወደ ማርያም መጥቷል (ቁ. 19፥17)። ስለዚህ በቁርኣን መሠረት መንፈስ ቅዱስ በዓለም ላይ የእርሱ ወኪል የሆነ አካል ያለው የፈጣሪ እስትንፋስ ነው። ይህም የሥላሴ አስተምሕሮ ቅሪት ነው።

---

27 ዮሐንስ ለኢየሱስ መንገድ ማሳየቱን የሚገልፅ ነው።

28 Mustafa Akyol, The Islamic Jesus, New York: St. Martin’s Press, 2017, p. 162.

29 የሁን የምትለዋ በቅንፍ የገባችዋ ቃል በአረብኛ የለችም። የተርጓሚዎቹ ጭማሬ ነው

30 ቁርኣን 2:117, 3:59, 6:73, 16:40, 36:82, 40:68

ሙሐመድ ስለ መንፈስ በተጠየቀ ጊዜ መልስ እንዳልነበረው ከተከታዩ ጥቅስ መረዳት ይቻላል፡-

> ከሩሕም ይጠይቁሃል፤ ሩሕ ከጌታዬ ነገር ነው ከዕውቀትም ጥቂትን እንጂ አልተሰጣችሁም፤ በላቸው። (ቁርኣን 17፡85-86)

ይህ የሚያሳየው ሙሐመድ ስለ ጉዳዩ ዕውቀት እንዳልነበረው ነው።

በድጋሜ እነዚህን ጥቅሶች ከሙስሊም ወዳጆች ጋር በማንበብ ስለ መንፈስ ቅዱስ እነዚህን ጉዳዮች ማንሳት ትችላላችሁ። ለእነርሱ ጠቃሚ ማረጋገጫ ሊሆን ይችላል።

በዚህ ምዕራፍ በቁርኣን ውስጥ የሚታዩትን የአስተምሕሮተ ሥላሴ ቅሪቶች ተመልክተናል። እነዚህ ምናልባትም ስለ ሥላሴ ከሙስሊሞች ጋር ስትወያዩ ጠቃሚ ሊሆኑ ይችላሉ።

## ሥላሴን መካድ ምን ያስከትላል?

ሙስሊሞች፣ ሰባሊዮሳውያን፣ አርዮሳውያንና ሌሎችም ሥላሴን አይቀበሉም፣ ነገር ግን ለቅዱሳት መጻሕፍት እውነት የሆነ አማራጭ ማቅረብ አለባቸው። ሥላሴን ብቻ መቃወም አይችሉም። አማራጭ መስጠት ይኖርባቸዋል። አማራጮቹን ስናጤን ደግሞ ሁሉም ውድቅ ይሆናሉ። ለቅዱሳት መጻሕፍት በብቸኛነት እውነት የሆነው ሥላሴ በመሆኑ ክርስቲያኖች ሙሉ በሙሉ እርግጠኞች መሆን አለባቸው። ለይሖዋ ምስክሮች፣ አብ አምላክ ነው፣ ወልድ መልአክ ሚካኤል ነው፣ መንፈስ ቅዱስ ደግሞ ኃይል ብቻ ነው። ይህ ትርጓሜ በፍፁም አይሠራም። ዕብራውያን ምዕራፍ 1 እና ቆላስይስ 2፡18 ላይ ኢየሱስ መልአክ አይደለም፣ መንፈስ ቅዱስም ወደ አብ ስለ እኛ ይማልዳል ተብሏል፤ ስለዚህ ይሄ ማለት ኃይል አይደለም ማለት ነው። ለእስልምና ደግሞ እግዚአብሔር አብ (አባት) አይደለም፣ ኢየሱስ ሰው ብቻ ነው፣ መንፈስ ቅዱስ ደግሞ መልአኩ ገብርኤል ነው። በድጋሚ ይሄ ትርጓሜ አይሠራም። ምክንያቱም በቁርኣን ውስጥ አላህ መንፈሱን በአዳምና በማርያም እፍ እንዳለ እናነባለን (21፡91)፤ ይህ ማለት አላህ ወደ አዳምና ማርያም መልአክን እፍ አለባቸው እንደ ማለት ነው። ስለዚህ ገብርኤል የሕይወት እስትንፋስ ይሆናል።

ሙሐመድ ስለ መንፈስ በተጠየቀ ጊዜ መልስ እንዳልነበረው ከተከታዩ ጥቅስ መረዳት ይቻላል፡-

> ከሩሕም ይጠይቁሃል፤ ሩሕ ከጌታዬ ነገር ነው ከዕውቀትም ጥቂትን እንጂ አልተሰጣችሁም፤ በላቸው። (ቁርኣን 17፡85-86)

ይህ የሚያሳየው ሙሐመድ ስለ ጉዳዩ ዕውቀት እንዳልነበረው ነው።

ሙሐመድ አምላክን ምን አደረገው? ሙሐመድ አምላክን ገነጣጥሏል። እግዚአብሔር ከመንፈሱና ከቃሉ የተለየ አይደለም። ሁለቱም የእግዚአብሔር ማንነት አካል ናቸው፣ ነገር ግን ስለ አምላክ አንድነት ያለውን አስተምህሮ ለማዳበር ሲል ሙሐመድ የእግዚአብሔርን

መንፈስና ቃል ቆርጧል። ይህ የደማስቆው ዮሐንስ ለጠየቁት ሙስሊሞች የሰጠው ምላሽ ነበር። የሙስሊም መሪዎች ክርስቲያኖች የአምላክን አንድነት ያመቻምቻሉ ሲሉ ይከሳሉ እኛ ግን አምላክን ቆራርጠዋል ብለን ልንመልስላቸው እንችላለን።

## ሥላሴና አመክንዮ

የሥላሴን አስተምሕሮና አመክንዮን ስንመለከት ከግምት ውስጥ ሊገባ የሚገባው ጉዳይ ቢኖር የማሰብ ችሎታችንንና አመክንዮን በመጠቀም ስለ ፈጣሪያችን ሙሉ ግንዛቤን እንደምናገኝ ማሰብ እንደማይገባን ነው። እንዲህ ያለ ሐሳብ እንዲያድርባችሁ ፍላጎት የለኝም። እግዚአብሔር ከሕዋሶቻችን ያለፈና የመጠቀ ነው። ከፍጥረት በመነሳት ስለ እግዚአብሔር የተወሰነ ነገር ማወቅ ብንችልም በፍፃሜው ፈጣሪያችን ማን መሆኑንና ምን እንደሚመስል ለማወቅ እርሱ ስለ ራሱ ሊገልጥልን ያስፈልገናል። ይህንን ካልን ዘንዳ ፈጣሪያችን ለኛ ራሱን ሲያሳውቅ ይህ መገለጥ ምክንያታዊ እንዲሆን እንጠብቃለን።

ሙስሊም መሪዎች ብዙ ጊዜ ሥላሴን አመክንዮን የሚያፋልስና ትክክለኛውን እሳቤ የሚፃረር በማስመሰል ሲቀልዱበት ይታያል። የፈጣሪን አንድነት ስለሚያመቻምች ኢ-አመክንዮአዊ ነው ይላሉ ነገር ግን ቀደም ሲል እንደተመለከትነው ክርስትናም ሆነ እስልምና የፈጣሪን አንድነትና ብዝሐነት አንድነቱን ጥያቄ ውስጥ ሳይከቱ ይቀበላሉ። ሦስቱ አንድ መሆናቸው እንደማይቻል በማስመሰል ቢናገሩም ዳሩ ግን አካላዊ ኑባሬዎች እንደሚለያዩና ሦስቱ አንድ ሊሆኑ እንደሚችሉ ተመልክተናል። ስለዚህ ሥላሴ ከነዚህ ክሶች በተፃራሪ ምክንያታዊ መሆኑን አረጋግጠናል። አሁን ግን ማንነነት ያለውና የተብቃቃ የሆነውን አምላክ ለመግለፅ ሥላሴ ጥሩ መንገድ መሆኑን የሚያሳይ ሌላ ጉዳይ ለማንሳት እፈልጋለሁ።

በመጽሐፍ ቅዱስ ሁሉ ውስጥ እግዚአብሔር ማንነታዊ አካል ያለው ሆኖ ነው የተገለጸው። ኃይል ወይንም እምቅ ጉልበት ሳይሆን በማንነቱ የሚሠራና ሕብረት የሚያደርግ እንደሆነ ነው። ፈጣሪ ራሱን ቻይ (የተብቃቃ) ነው። ይህ ማለት ፈጣሪ ፍጥረት የማያስፈልገውና ለምንም ጉዳይ በውጪያዊ ነገር ላይ ጥገኛ ያልሆነ ነው ማለት ነው። ፈጣሪ ሁሉን ነገር የፈጠረው ወዶና ፈቅዶ እንጂ ስለሚጠቅመው ወይንም ስለሚያስፈልገው አይደለም።

እነዚህ ሁለቱ እውነታዎች አንድ ላይ ሲታዩ የሥላሴ አስተምሕሮ ምክንያታዊ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል። የዚህም ምክንያቱ ፈጣሪ ራሱን ቻይ (የተብቃቃ) ከሆነና በማንነቱ ንቁና ሕብረት የሚያደርግ ከሆነ ይህ ንቃትና ሕብረት በሌላ ውጪያዊ ነገር ላይ ጥገኛ ያልሆነና በገዛ ማንነቱ ውስጥ የሚፈፀም መሆን አለበት። ይህም ማለት ፈጣሪ ራሱን ቻይ ከሆነ ሕብረት ለማድረግ ፍጥረት አያሻውም ማለት ነው። የሥላሴ አስተምሕሮ ይህንን ያረጋግጣል። እግዚአብሔር አብ፣ ወልድና መንፈስ ቅዱስ ሆኖ ከዘላለም ዘመናት ጀምሮ በማንነቱ ውስጥ ሕብረት ነበረው። ሥላሴ ዘላለማዊ የሆነውን የእግዚአብሔርን ንቁ ሕብረት ያረጋግጣል። እግዚአብሔር ፍቅር ነው ከሚለው እምነታችን አንፃር ትርጉም የሚሰጥ ነው

(፲ዮሐ. 4፡8) ምክንያቱም ፍቅር በእግዚአብሔር ማንነት ውስጥ ከዘላለም ጀምሮ እንዴት ሕያው እንደነበር ያሳያልና።

በተፃራሪው ግን ተውሒድ በዚህ ረገድ ችግር ይገጥመዋል ምክንያቱም ፈጣሪ ከዘላለም አንስቶ በማንነቱ ውስጥ ብዝሐነት ከሌለው ንቁ የሆነ ሕብረት ሊኖረው የሚችለው እንዴት ሆኖ ነው? ነጠላ አሓዳዊ ማንነት ያለው አምላክ ፍጥረት ከተፈጠረ በኋላ ሕብረት የማድረግ እምቅ አቅም ሊኖረው ይችላል ነገር ግን ይህ አምላክ ከዘላለም አንስቶ ሕብረት ሊኖረው አይችልም። ሕብረት ለማድረግ በፍጥረት ላይ ጥገኛ የሆነ አምላክ ራሱን ቻይ አይደለም። ስለዚህ ሥላሴ የፈጣሪን ማንነታዊ ራሱን ቻይነት ማብራራት ሲችል ተውሒድ ግን አይችልም።

ይህ ሙግት ሥላሴ ምክንያታዊ መገለጥ መሆኑን ለሙስሊሞች ለማብራራት ይረዳል።

## ማጠቃለያ

1. ሙስሊሞች ስለ እግዚአብሔር መልስ ሊያገኙ የሚገቧቸው ብዙ ቅድመ ግንዛቤ ስላላቸው በአዲስ ኪዳን መጀመር ጥሩ ቦታ ላይሆን ይችላል። እነዚህ ቅድመ ግንዛቤዎች መልስ ካልተሰጠባቸው የእግዚአብሔርን ባሕርያት ለመወያየት ምንም የጋራ መሠረት አይኖረንም።

2. ሥላሴ እግዚአብሔር፣ ኢየሱስና ማርያም አይደሉም። ስለ ሥላሴ ከቁርአን አንማርም ነገር ግን ከቶራህ፣ ከነቢያትና ከወንጌል እንማራለን።

3. ሙስሊሞችም ስለ እግዚአብሔር አንድነትና ብዛሐነት የራሳቸው የሆነ እሳቤ ስላላቸው ያላቸው ሲሆን ተውሒድ ይሰኛል። የተለያዩ ዓይነት የተውሒድ መረዳቶች ያሉ ሲሆን ብዙዎች የሚቀበሉት ቢ ላ ከይፍ ወይም መጠየቅ አይቻልም በሚል የእግድ ቃል ላይ የተመሠረተ ነው።

4. የሰው ልጆች አእምሯዊ መረዳት በቂ አይደለም፤ ፈጣሪ ራሱን ሊገልጥልን ያስፈልገናል።

5. ሰዎች በአሓዱ ሥሉስ የሚሰናከሉበት ምክንያት ከሰው ልጅ ተሞክሮ ያካበቱትን አመክንዮ በመጠቀም ስለ አምላክ አመክንዮአዊ የሆነ ዳኝነት ለመስጠት ስለሚሞክሩ ነው።

6. ሦስት አካላት ያሉት አንድ አምላክ መኖሩን ቅዱሳት መጻሕፍት ያስተምራሉ።

7. ቁርአን የአስተምሕሮተ ሥላሴ ቅሪት አለው።

8. ሙሐመድ ሥላሴን አልተቀበለም፤ ነገር ግን ስለ አምላክ የነበረው ዕውቀት የአምላክ እስትንፋስ የሆነውን መንፈስ ቅዱስን መልአኩ ገብርኤል የሚያደርግ በመሆኑ ውድቅ ሆኗል።

9. ሥላሴ ምክንያታዊና በቅዱሳት መጻሕፍት ድጋፍ ያለው አስተምሕሮ ነው።

በመጨረሻም በድረ-ገጹ ላይ በዚህ ጉዳይ ላይ የሚያጠነጥን የወንጌል ስርጭት ቡክሌት አለ፤ ከላይ ያሉትን ሁሉንም ሐሳቦች ጠቅለል አድርጎ ያቀርባል። ከሙስሊም ጓደኞችሁ ጋር ማንበብ ወይም እንዲያነቡ ልትሰጡት ትችላላችሁ።

## የሚደጋገሙ ጥያቄዎች

1. *ሙስሊም፡* የነቢያት ማዕከላዊ መልእክት አንድ አምላክ ብቻ አለ የሚል ነው። በአንድ አምላክ ካመንክ ሁሉም ነገር አለህ። ቁርኣን ይህንን ያረጋግጣል። የእስልምና መልእክት ይህ ነው።

*ክርስቲያን፡* ነቢያት በእርግጠኝነት አንድ አምላክ መኖሩን አስተምረዋል ነገር ግን በዚያ ብቻ አላቆሙም። ይህ አምላክ ማን እንደሆነ፣ ዕቅዶቹ ምን እንደሆኑና ለእርሱ ምላሽ በመስጠት እንዴት መኖር እንዳለብን አስተምረዋል። አንድ አምላክ ማኖሩንማ ሰይጣንም ያምናል (ያዕ. 2፡19)።

2. *ሙስሊም፡ ሥ*ላሴ በጳውሎስ ወይም በኒቅያ ጉባኤ ወይንም ከአረማውያን ሃይማኖታት የተፈጠረ ነው።

*ክርስቲያን፡* በፍፁም። *ሥ*ላሴ ከኢየሱስ በፊት በነበሩት ነቢያት ትምሕርቶች ላይ ጠልቆ የተመሠረተ ነው። ጳውሎስ እነዚህን ነገሮች አስተምሯል ነገር ግን *ሥ*ላሴ የነቢያት ሁሉ ትምሕርት መቋጫ እንጂ የጳውሎስ ብቻ አይደለም።

3. *ሙስሊም፡* 1+1+1=3 ይሆናል እንጂ 1 አይሆንም። በሦስት አማልክት ነው የምታምኑት አለበለዚያም ከአመክንዮ ጋር ትጣረሳላችሁ።

*ክርስቲያን፡* እኛ የምንለውን በተሳሳተ መንገድ ነው ያቀረብከው። እኛ እያልን ያለነው አንዱን ግፃዌ መለኮት የሚካፈሉ ሦስት አካላት 1+1+1=3 ይሆናሉ ነው።

4. *ሙስሊም፡ ታዲያ ለምን ሦስት ብቻ*? *ለምን አራት፣* አምስት ወይም ስድስት አይደሉም?

*ክርስቲያን፡* እግዚአብሔር ስለ ራሱ የገለጠው ይህ ነው።

5. *ሙስሊም፡* ዘዳግም 6፡4 የእስልምናን ፅንሰ-ሀሳብ የሚያስተምረው የአምላክ (ተውሂድ) ፍፁም አንድነት የሚደግፍ ነው።

> እስራኤል ሆይ፥ ስማ፤ እግዚአብሔር (ያህዌ) አምላካችን እግዚአብሔር አንድ እግዚአብሔር ነው። (ዘዳግም 6:4)

*ክርስቲያን፡* ዘዳግም 6፡4 ተውሂድን አያስተምርም፤ ምክንያቱም መለኮታዊ መንፈሱንና መልኩን ወደ ዓለም የላከውን አባት የተባለውን ያህዌን ስለሚያመለክት። ዘዳግም 6፡4 ይህንን አንድነት እያስታወሰን ነው ነገር ግን የእግዚአብሔርን ሌሎች ገጽታዎች መካድ አይደለም።

6. *ሙስሊም፡* ‘ሥላሴ’ የሚለው ቃል በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አይገኝም። ከኢየሱስ ከብዙ መቶ ዓመታት በኋላ የተፈጠረ ሐሳብ ብቻ ነው።

*ክርስቲያን፡* እውነት ነው ሥላሴ የሚለው ቃል በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አይገኝም ነገር ግን ተውሂድ የሚለው ቃልም በቁርኣን ውስጥ አይገኝም። እነዚህ ሁለቱም ቃላቶች የዳበሩት ክርስቲያናዊና እስላማዊ የፈጣሪን ግንዛቤ ለመግለጽ ከሥነ-መለኮት ሐተታ አንጻር ነው፤ በመሆኑ ይህ ምንም ስህተት የለበትም።

# ምዕራፍ 6

## ደህንነት

እስምናና ክርስትና ስለ ደህንነት የተለያየ መረዳት ነው ያላቸው። የተለያዩ ከመሆናቸውም ባለፈ ሙስሊሞ ክርስቲያናዊውን መረዳት እንዲቃወሙ ይማራሉ። ስለዚህ ክርስቲያኖች ኢየሱስ ለደህንነታቸው ሲል እንደሞተ ሲናገሩ ሙስሊሞች ለመገዳደር ዝግጁዎች ናቸው። በዚህ ምዕራፍ እስልምና ስለ ደህንነት ምን እንደሚያስተምር፣ ስለ ወንጌልና ታሪካዊ ዳራው ምን አመለካከት እንዳለው እንዲሁም ከየት መጀመር እንዳለብንና ለነዚህ ተቃውሞዎች እንዴት መልስ መስጠት እንዳለብን እንመለከታለን።

### ኢየሱስና ሙሐመድ

ኢየሱስ የሚለው ስም “እግዚአብሔር ያድናል” ማለት ሲሆን ኢየሱስ ምድር ላይ በነበረበት ዘመን ሁሉ በዙሪያው ላሉት ሰዎች መዳንን ሲያመጣ እንመለከታለን። አጋንንት ያደሩባቸውን ከአጋንንት እሥራት ነፃ አውጥቷል። ዓይነ ስውራንን፣ ሽባዎችን፣ ለምጻሞችንና ሙታንን አድኗል። የሰዎችን ኃጢአት ይቅር ብሏል፤ በመስቀል ላይ ሲሞትም በእርሱ ለሚታመኑት ሁሉ መዳንን አምጥቶላቸዋል። ኢየሱስ ያድናል!

በሌላ ወገን ሙሐመድ ማንንም አላዳነም። የእርኩሳን መናፍስት እስረኛ ነበር፡-

> አኢሻ እንደተረከችው፡- ነብዩ (ሶ.ዐ.ወ) ላይ ድግምት ተሠራበት ስለዚህ እያደረገ ያልነበረውን ነገር እያደረገ እንደሆነ ማሰብ ጀመረ። (ሳሂህ አል-ቡኻሪ 3268፣ ቅጽ 4፣ መጽ. 54፣ ቁ. 490)

ከኃጢአቱ መዳን ነበረበት።

> "እነሆ ከአላህ ሌላ አምላክ አለመኖሩንም ዕወቅ። ስለ ስህተትህም ለምእመናንም ምሕረትን ለምን። አላህም መዘዋወሪያችሁን፣ መርጊያችሁንም ያውቃል።" (ቁርአን 47፡19)።

እንዲሁም ሲሞት ምን እንደሚደርስበት አያውቅም ነበር።

> … ኡም አል-ዓላ እንዳወራችው፡- ኡሥማን ቢን መዝዑን ከእነርሱ ጋር (ማለትም ከኡም አል-ዓላ ቤተሰብ ጋር) ለመኖር ወሰነ፤ ኡሥማን ታመመና እስከሞተበት ጊዜ ድረስ አጠባሁት፤ ከዚያም በልብሶቹ ሸፈንነው። ከዚያም ነቢዩ ወደ እኛ በመጣ ጊዜ (አስከሬኑን) እንዲህ አልኩት፡- “አቡ አስ-ሳዒብ ሆይ የአላህ እዝነት ባንተ ላይ ይሁን! አላህ እንዳከበረህ እመሰክራለሁ።” ከዚያም ነቢዩ እንዲህ አሉ፡- “አላህ እዳከበረው እንዴት አወቅሽ?” እንዲህ ስል መለስኩ “አላውቅም። እናቴና አባቴ

> መሥዋዕት ይሁኑልዎ የአላህ መልእክተኛ ሆይ! (ኡሥማን ካልሆነ በስተቀር) ይህ የተገባው ማን ነው?” እሳቸውም እንዲህ አሉ፡- “እርሱ እንደሆን በአላህ ይሁንብኝ ሞት አሸንፎታል፤ መልካሙንም እመኝለታለሁ። በአላህ ይሁንብኝ እኔ የአላህ መልእክተኛ ብሆንም አላህ ምን እንደሚያደርግብኝ አላውቅም።” በአላህ ይሁንብኝ ከሱ ወዲያ ማንንም ጻድቃል ብዬ መናገር አልችልም… (ሳሂህ አል-ቡኻሪ፣ ቅፅ 5፣ መጽሐፍ 58፣ ቁጥር 266)

ኢየሱስና ሙሐመድ የኖሩት ሁለት ዓይነት ሕይወት ሲሆን ይህም ሁለቱም ለዓለም ባመጡት መልእክት ውስጥ ተንጸባርቋል።

## የኢየሱስና የሙሐመድ መልእክቶች

በክርስትና ውስጥ እንደሆነው ደህንነት የእስልምና ዋነኛ ትምህርት አይደለም። የክርስትና ዋና መልእክት እግዚአብሔር ለሁሉም ሕዝቦች ይቅርታና መዳንን ለማምጣት በኢየሱስ በኩል እርምጃ መውሰዱ ነው። የእስልምና መልእክት አላህ የተሰኘ አንድ አምላክ ብቻ አለ፤ ሙሐመድም የእርሱ ነቢይ ነው፤ እናንተም ሦስት አማራጮች አሏችሁ፡- እስልምናን መቀበል፣ የሽንፈት ግብር (ጂዝያ) መክፈል ወይም መዋጋት የሚል ነው።

> ሙሐመድ እንዲህ ይላል፡- በአላህ ስምና በአላህ መንገድ ተዋጉ። እነዚያን በአላህ የካዱትን ተዋጉ። የተቀደሰ ጦርነት አድርጉ […] ጠላቶቻችሁን ሙሽሪኮችን ስታገኟቸው ወደ ሦስት ሁኔታዎች ጋብዟቸው። [… 1] ወደ እስልምና ጋብዟቸው (እንዲቀበሉ)። ቢመልሱላችሁም ከነሱ ተቀበሉ። ከመዋጋትም ተቆጠቡ። ለመክፈል ከተስማሙ ከእነሱ ተቀበሉና እጆቻችሁን መልሱ። (3) ጂዝያን ለመክፈል እምቢ ካሉ የአላህን እርዳታ ጠይቁና ተዋጉዋቸው። (ሳሂህ ሙስሊም 1731፣ መጽሐፍ 19፣ ቁጥር 4294)

የእስልምና ዋና መልእክት የድነት መልእክት ሳይሆን ሁሉን ጠቅልሎ የመግዛት መልእክት ነው።

ታዲያ እስልምና ስለ ድነት ምን ያስተምራል? ይህ ቀላል ጥያቄ ሊመስል ይችላል ነገርግን ማወቅ ቀላል አይደለም ምክንያቱም የሙስሊም መሪዎች በይፋ የሚናገሩት በማህበረሰቡ ውስጥ የሚነገረው ትምህርት አይደለምና።

### ድነት በእስልምና ውስጥ

የእስልምና መሪዎች መዳን ቀላል እንደሆነ በአደባባይ ያስተምራሉ። ሰው ለመዳን ትክክለኛ እምነትና አምልኮ ሊኖረው፣ ንስሃ ሊገባ እንዲሁም መልካም ሥራ ሊሠራ ይገባዋል። ይህ ቀላልና ተግባራዊ ይመስላል፣ ነገር ግን ሙስሊሞች በግል የሚማሩትን በከፊል ብቻ የሚገልፅ ነው። በክርስትና እና በእስልምና ስለ ድነት ጉዳይ ብዙ የአደባባይ ክርክሮችን አድርጌያለሁ፣ ብዙ ክርክሮችንም ተመልክቻለሁ። በነዚህ ክርክሮች ውስጥ እኔና ሌሎች

የሠራነው ስህተት በእስልምና መሪዎች የተሰጠውን ይህንን ከፊል የመዳን ማብራሪያ በመቀበልና በዚህ ጉዳይ ተወስነን እስልምና በሚያስተምረውን የተሟላ ሐሳብ ችላ ማለታችን ነው። ስለዚህም ያሳየነው ለውጥ ኢምንት ነው። እስልምና ስለ ድነት የሚያስተምረውን ስንረዳ የጫወታ ሜዳው ሙሉ በሙሉ ይቀየራል። ለልባቸው ለመናገር፣ ድርጊቶቻቸውን ለመረዳትና ኢየሱስ እንዴት ለኃጢአታቸው መሞት እንደሚችል ለማስረዳት የተሻለ ሁኔታ ዕድል ይፈጠርልናል። በማስከተል የተሟላውን ኢስላማዊ የመዳን ግንዛቤን እንመረምራለን።

## አጠቃላይ መርሆ

ደህንነት በእስልምና ፈጣሪ ይቅር ብሏችሁ ከሚያወርድላችሁ ምህረት ይገኛል። ይህ ምህረትና ይቅርታ ልትፈልጉት የሚገባ ነገር ነው።

> መጥፎም የሚሠራ ሰው ወይንም ነፍሱን የሚበድል ከዚያም (ተጸጽቶ) አላህን ምሕረት የሚለምን አላህን መሐሪ አዛኝ ሆኖ ያገኘዋል። (ቁርኣን 4፡110)

ይቅርታ የወደፊት የገነት ስጦታ ነው። ይህ ስጦታ ትክክለኛ ነገር በማመንና መልካምን በመሥራት የሚሰጥ ነው።

> እነዚያንም ያመኑትንና በጎ ሥራዎችን የሠሩትን አላህ (ገነትን) ተስፋ አደረገላቸው። ለነርሱ ምሕረትና ታላቅ ምንዳ አላቸው። (ቁርኣን 5፡9)
>
> የዚያች ጥንቁቆች ተስፋ የተሰጧት ገነት ምስል በውስጧ ሺታው ከማይለወጥ ውሃ ወንዞች ጣዕሙ ከማይለውጥ ወተትም ወንዞች ለጠጪዎች ሁሉ ጣፋጭ ከኾነች የወይን ጠጅም ወንዞች,ከተነጠረ ማርም ወንዞች አሉባት፤ ለነሱም በውስጧ ከፍሬዎች ሁሉ (በያይነቱ) ከጌታቸው ምሕረትም አላቸው፣ (በዚች ገነት ውስጥ ዘውታሪ የሆነ ሰው) እርሱ በእሳት ውስጥ ዘውታሪ የሆነ ሰው ሞቃትንም ውሃ እንደ ተጋቱ፣ አንጀቶቻቸውንም ወዲያውኑ እንደ ቆራረጠው ነውን? (አይደለም)። (ቁርኣን 47፡15)

መልካም ሥራዎች ፍላጎታችሁን የሚገልጡ ሲሆን የፈጣሪን ምህረትና ይቅርታ ያስገኛል። መጥፎ ሥራዎች ከምህረትን ይቅርታ እንድትርቁ ያደርጓችኋል። ፈጣሪ ዝም ብሎ ይቅር አይልም። ስለዚህ የሙስሊሞች ግብ በሕይወት ዘመናቸው ከመጥፎ ሥራዎቻቸው የበዙ መልካም ሥራዎችን ማጠራቀም ነው። በፍርድ ቀንም ሥራቸው ሲመዘን መዳን ይችሉ ይሆናል።

> ሚዛኖቹም የከበዱለት ሰው እነዚያ እነርሱ ፍላጎታቸውን ያገኙ ናቸው። ሚዛኖቹም የቀለሉበት ሰው እነዚያ እነርሱ ነፍሶቻቸውን ያከሰሩ ናቸው። በገሀነም ውስጥ ዘመውታሪዎች ናቸው። (ቁርኣን 23፡102-103)

እነዚህ ሰው እንዴት እንደሚድን የሚያሳዩ የእስልምና አጠቃላይ መርሆች ናቸው። ይሁንና እነዚህ መርሆች ለአንድ ሙስሊም መሥራት የሚችሉበት ሁኔታ ይለያያል። ይህ ደግሞ ሙስሊም ሊድንባቸው የሚችሉ ሦስቱ መንገዶችን ያመለክታል፡

## መንገድ ፩፡ ምርጥ ሙስሊም – በቀጥታ ወደ ገነት የሚሄድ

በእስልምናው አምላክ ፊት መልካም ሥራዎች ሁሉ እኩል አይደሉም።

> ካዕባን ጎብኝዎችን[31] ማጠጣትንና የተከበረዉን መስጊድ መሥራትን፣ በአላህና በመጨረሻዉ ቀን እንዳመነና በአላህ መንገድ እንደታገለ ሰው (እምነትና ትግል) አደረጋችሁን? አላህ ዘንድ አይተካከሉም፤ አላህም በዳዮች ሕዝቦችን አይመራም። እነዚያ ያመኑት ከአገራቸዉም የተሰደዱት በገንዘቦቻቸውና በነፍሶቻቸዉም በአላህ መንገድ ላይ የታገሉት አላህ ዘንድ በደረጃ በጣም የላቁ ናቸው፤ እነዚያም እነሱ ፍላጎታቸውን ያገኙ ናቸው። (ቁርኣን 9፡19-20)

በፈጣሪ ዘንድ ከፍተኛ ቦታ የተሰጠው አንድ መልካም *ሥራ* ቢኖር *ለፈጣሪ ሥራ በፈጣሪ መንገድ* በመጋደል የእስልምናን አገዛዝ ለማስፈን ጥረት ማድረግ ነው። ይህ በእስልምና ትግል ወይም *ጂሃድ* የሚባለው ነው። ይህ ማለት ወደ መካ ከመሄድ ይልቅ ጂሃዳዊ መሆን የበለጡ ነጥቦችን ያስገኛል ማለት ነው። በተከታዮቹ ጥቅሶች ውስጥ ይህንን የሚደግፍ ሐሳብ እናገኛለን።

> ከምእመናን የጉዳት ባለቤት ከሆኑት በቀር ተቀማጮቹና[32] በአላህ መንገድ በገንዘቦቻቸውና በነፍሶቻቸው የሚታገሉት አይስተካከሉም፤ በገንዘቦቻቸውና በነፍሶቻቸው የሚታገሉትን አላህ በተቀማጮቹ ላይ በደረጃ አበለጠ፤ ለሁሉም አላህ መልካሚቱን (ገነት) ተስፋ ሰጠ። ታጋዮቹንም በተቀማጮቹ ላይ አላህ በታላቅ ምንዳ አበለጠ። ከርሱ ዘንድ በሆኑ ደረጃዎች (አበለጠ) ምሕረትንም አደረገ፤ እዝነትም አዘነላቸው፤ አላህም መሐሪ አዛኝ ነው። (ቁርኣን 4፡95-96)
>
> ፊላቸውን በከፊሉ ላይ እንዴት እንዳበለጥን ተመልከት፤ የመጨረሻይቱም አገር በማዕረጎች በጣም የከበረችና በመብለጥም የተለቀች ናት። (ቁርኣን 17፡21)[33]

የዚህ ውጤቱ በቀጥታ ወደ ገነት የሚሄዱ ሙስሊሞች አሉ ማለት ነው። በቁርኣን ውስጥ እነዚህ የእስልምና ሰማዕታት እንሆኑ ተገልጧል።[34] እነዚህ በአላህ መንገድ ሲጋደሉ የሞቱ ሰዎች ናቸው። የእነርሱ መሥዋዕት መሆን በጣም መልካም ስለሆነ ፍርድን ማየት አያሻቸውም። በአንፃሩ ሙሉ መዳንን በማግኘት ወደ ፈጣሪ ዘንድ ወደ ገነት ይሄዳሉ።

---

31 ይህ ለሐጅ መጓዝ ሲሆን ከእስልምና አዕማዳት መካከል አንዱ ነው።

32 ይህ ማለት ለጂሃድ ያልሄዱና ዝም ብለው ቤታቸው የተቀመጡ ማለት ነው።

33 ቁርኣን 2:253, 6:132, 46:19, 58:11, *Sahih al-Bukhari* 3769; vol. 5, bk. 57, no. 113.

34 ነቢያትም በቀጥታ ወደ ገነት ይገባሉ።

> በአላህም መንገድ ብትገደሉ ወይም፤ በትሞቱ፥ ከአላህ የሆነዉ ምሕረትና እዝነት (ከእነርሱ) ከሚሰበስቡት ሀብት በእርግጥ በላጭ ነው። ብትሞቱም፥ ወይም ብትገደሉ፣ በእርግጥ ወደ አላህ ብቻ ትሰበሰባላችሁ። (ቁርኣን 3፡157-158)

> እነዚያን በአላህ መንገድ የተገደሉትን ሙታን አድርገህ አትገምታቸዉ። በእርግጥ እነርሱ እጌታቸዉ ዘንድ ሕያዋን ናቸዉ፤ ይመገባሉ። (ቁርኣን 3፡169)

> አላህንና መልክተኛውንም የሚታዘዝ ሰው፤ እነዚህ ከነዚያ አላህ በነርሱ ላይ ከለገሰላቸው ከነቢያት፣ ከጻድቃንም፣ ከሰማዕታትም ከመልካሞቹ ጋር ይኾናሉ። የነዚያም ጓደኝነት አማረ! (ቁርኣን 4፡69)

> በአላህ መንገድ (ለሃይማኖቱ) የሚገደሉትን ሰዎችም «ሙታን ናቸው» አትበሉ። በእውነቱ ሕያዋን ናቸው፤ ግን አታውቁም። (ቁርኣን 2፡154)

> እላንተ ያመናችሁ ሆይ! ከአሳማሚ ቅጣት የምታድናችሁ የሆነች ንግድ ላመላከታችሁን? (በላቸው)።(እርሷም) በአላህና በመልክተኛው ታምናላችሁ፣ በአላህ መንገድም በገንዘቦቻችሁ በነፍሶቻችሁም ትታገላላችሁ፤ ይሃችሁ የምታውቁ ብትሆኑ ለናንተ የተሻለ ነው። ኃጢአቶቻችሁን ለናንተ ይምራል፤ ከሥሮቻቸው ወንዞች የሚፈሱባቸውንም ገነቶች ያገባችኋል፤በመኖሪያ ገነቶችም በሚያማምሩ ቤቶች ውስጥ (ያስቀምጣችኋል)፤ ይህ ታላቅ ዕድል ነው። (ቁርኣን 61፡10- 12)

> ጃቢር ቢን አብዱላህ እንዳስተላለፈው በኡሑድ ጦርነት ወቅት አንድ ሰው ወደ ነቢዩ መጥቶ እንዲህ አላቸው፡- "ሰማዕት ብሆን ወዴት እንደምሄድ ሊነግሩኝ ይችላሉ?" ነቢዩም እንዲህ ሲሉ መለሱ፡- "ወደ ገነት"። ሰውየው በእጁ የያዛቸውን ተምሮች ወዲያ ወርውሮ ሰማዕት እስኪሆን ድረስ ተዋጋ። (ሳሂህ አል-ቡኻሪ ቅፅ 5፣ መጽሐፍ 59፣ ቁጥር 377)

> የሰማዕታት ነፍሳት ሁሉን ቻይ በሆነው አላህ ዙፋን ላይ በተንጠለጠሉ ጎጆዎች ውስጥ በሚኖሩ አረንጓዴ ወፎች አካል ውስጥ ይኖራሉ። የገነትን ፍሬዎች በሚፈልጉበት ስፍራ ሁሉ ከእርሷ በይዎች ይኾናሉ። (ሳሂህ ሙስሊም 1887፣ መጽ. 20፣ ቁ. 4651)

እንደ እስላም ሰማዕት መሞት የፈጣሪን ምህረት ያስገኛል፣ ከኃጢአትም ያነፃል - ቀጥተኛው መንገድ ይህ ነው - ነገር ግን ከዚህም ያለፈ ነው። ለሰማዕት በመቃብርም ሆነ በገሃነም ውስጥ መሰቃየት የለም።

> አቡ ደርዳዕ እንዳወራው ነቢዩ እንዲህ አሉ፡- "የሰማዕት ምልጃ ለሰባ የቤተሰቡ አባላት ተቀባይነት አለው። (ሱናን አቡ ዳውድ 2522፣ መጽሐፍ 14፣ ቁጥር 2516)

ስለዚህ እስልምና ብዙ አዳኞች አሉት። ወደዚህ ነጥብ ኋላ ላይ የምንመለስ ቢሆንም በእስልምና ኢየሱስ አዳኝ መሆኑን - ከብዙ አዳኞች መካከል አንዱ መሆኑን እንጠቁማለን።

ሰማዕት መሆን ወደ ገነት የመግቢያ የመጀመርያው መንገድ ነው።

## መንገድ 2፡ ጥሩ ሙስሊም - ወደ መቃብር የሚሄዱ፣ ከዚያም ወደ ፍርድ ከዚያም ወደ ገነት የሚሄዱ

አብዛኞቹ ሙስሊሞች በአላህ መንገድ ሰማዕት አይሆኑም። ይህ ማለት ወደ ገነት የሚገቡት በሌላ መንገድ ነው ማለት ነው። የሙስሊም መደበኛ መልካም ሥራዎችን መሥራት ማለትም አምስቱን የእስላም አዕማዳት መጠበቅ ያስፈልጋቸዋል። እነርሱም፡- የእምነት መግለጫን መናገር (አረብኛ፡ ሸሃዳ)፤ ከአላህ በስተቀር አምላክ የለም ሙሐመድም መልእክተኛው ነው ብሎ ማወጅ፣ በቀን አምስቴ መጸለይ (ሰላህ)፣ ለእስልምና ዓላማ ገንዘብ መስጠት( ዘካት)፣ በረመዳን ወር መጾም (ሰውም)፣ ወደ መካ መሄድ (ሐጅ) ናቸው። በተለይም ረመዳን የአምላክን ምሕረት ለማግኘት ይበልጥ የሚጥሩበት ጊዜ ነው። ሲሞቱ ቀድመው ወደ መቃብር ይሄዱና በኋላ ላይ በገነት የመኖር ተስፋ አላቸው። አብዛኞቹ ሙስሊሞች በሚሞቱበት ጊዜ ወደ ገነትነት ሳይሆን ወደ መቃብር እንደሚሄዱ ይጠብቃሉ።

> እስከሚቀሰቀሱበት ቀን ድረስም ከስተፊታቸው ግርዶሽ አልለ። (ቁርኣን 23፡100፤ 15፡92)

> የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡- “በእርግጥ መቃብር ከመጨረሻው ዓለም የመጀመሪያ ደረጃ ነው። ስለዚህ አንድ ሰው ከሱ የዳነ ከሆነ ከዚያ በኋላ የሚመጣው ከእሱ የበለጠ ቀላል ነው. አንድም ሰው ከሱ ካልዳነ ከዚያ በኋላ የሚመጣው ከሱ የከፋ ነው። (ጃሚ አል-ቲርሚዚ 2308)

እነዚህንና ሌሎች መልካም ሥራዎችን መሥራት መልካም ሥራችሁን ከፍ ከማድረግም ባለፈ አንዳንድ ክፉ ሥራዎቻችሁን ይሰርዛሉ።

> ሶላትንም በቀን ጫፎች፤ ከሌሊትም ክፍሎች ፈጽም፤ መልካም ሥራዎች ኀጢአቶችን ያስወግዳሉና፤ ይህ ለተገሣጮች ግሣጤ ነው። (ቁርኣን 11፡114)[35]

> አቡ ሁረይራ እንዳስተላለፈው የአላህ መልእክተኛ እንዲህ ብለዋል፡- “ያለ ምንም ሸሪክ «ከአላህ በስተቀር አምላክ የለም፤ እሱ ከሁሉ በላጭ ነው፣ ገነት የእርሱ ናት፣ እርሱ በሁሉ ላይ ኃይል አለው» የሚል ሰው አሥር ባርያዎችን ነፃ ከማውጣት በላይ መቶ እጥፍ ምንዳ ያገኛል። መቶ መልካም ሥራዎችም ይጻፍለታል። መቶ ኃጢአቶችም ይሰረዙለታል። (ሳሂህ አል-ቡኻሪ ቅፅ 8፣ መጽሐፍ 75፣ ቁጥር 412)

---

35 እንዲሁም ቁርኣን 2:183-4, 2:196, 2:271, 4:31, 5:45, 5:89.

*መጥፎ ሥራዎች የመልካም ሥራዎችን ቁጥር ይቀንሳሉ*

> አቡ ሁረይራ እንዳስተላለፈው የአላጅ መልእክተኛ እንዲህ አሉ፡- "ውሻን ለእርሻ ወይም ከብት ለመጠበቅ ካልሆነ በስተቀር የሚያሳድግ ሰው በእያንዳንዱ ቀን ከመልካም ሥራው አንድ ቂራት[36] ይቀነስበታል።" (ሳሂህ አል-ቡኻሪ ቅፅ 4፣ መጽሐፍ 54፣ ቁጥር 541)

በዚህ መንገድ ላይ የተገኘ ሙስሊም ሲሞት ወደ ገነት ሳይሆን ወደ መቃብር ይሄዳሉ (አረብኛ በዛኽ)። መቃብር በሞትና በትንሣኤ መካከል የሚገኝ ሲሆን ምናልባትም የሥቃይ ቦታ ሊሆን ይችላል። ሰዎች ከመነሳታቸውና ለፍርድ ከመቅረባቸው በፊት የሚጠብቁበት ቦታ ነው።

> … የአላህ መልእክተኛ እንዲህ አሉ፡- "በእርግጥ መቃብር በቀጣዩ ሕይወት የመጀመርያው ደረጃ ነው። ስለዚህ አንድ ሰው ከእርሱ ካመለጠ የሚመጣው ነገር ከእርሱ የቀለለ ነው። አንድ ሰው ከእርሱ ካላመለጠ የሚመጣው ከእርሱ የከፋ ነው።" (ጃሚዕ አት-ትርሚዚ ፡ 2308)[37]

ሰዎች በመቃብር ውስጥ ንቁዎች ሲሆኑ ስለ ሙሐመድ ምን እንደሚያምኑ ይጠየቃሉ።[38] አብዛኞቹ ሙስሊሞች ወደ መቃብር ይሄዳሉ ነገር ግን ትኩረት የሚስበው ጉዳይ እናንተ መቃብር ውስጥ ሳላችሁ በሕይወት ያለ ሌላ ሰው ለእናንተ መልካም ሥራዎችን ማስመዝገብ ይችላል።

> ሀ. ኢብን አባስ እንዳወራው አንድ ሰው ወደ ነቢዩ መጥቶ እንዲህ አላቸው፡- "የአላህ መለእክተኛ ሆይ! እናቴ የረመዳንን ወር መፆም ቢገባትም ሳታካክስ ሞተች። በእርሷ ፋንታ ልጹምን?" ነቢዩም አዎንታዊ ምላሽ በመስጠት እንዲህ አሉ "የአላህ ዕዳ ሊከፈል ይገባል"። (ሳሂህ አል-ቡኻሪ ቅ 3፣ መጽሐፍ 31፣ ቁጥር 174)
>
> ለ. ኢብን አባስ እንዳወራው፡- ከጁሃይና ጎሣ የሆነች አንዲት ሴት ወደ ነቢዩ በመምጣት እንዲህ ሰለቻቸው፡- "እናቴ ሐጅ ለማድረግ ምላ ነበር ነገር ግን ሳይሳካላት ሞተች። በእናቴ ፋንታ ሐጅ ላድርግን?" ነቢዩም እንዲህ ሲሉ መለሱ፡- "በእርሷ ፋንታ ሐጅ አድርጊ። በእናትሽ ላይ ዕዳ ቢኖርባት ኖሮ አትከፍይም ነበርን? ስለዚህ የአላህን ዕዳ ክፈይ ምክንያቱም የእርሱ ዕዳ የመከፈል የበለጠ መብት አለውና።" (ሳሂህ አል-ቡኻሪ ቅፅ 3፣ መጽሐፍ 29፣ ቁጥር 77)

---

36 ቂራት መመዘኛ ነው።

37 ሳሂህ ነው። እንዲሁም ሱናን ኢብን ማጃህ 4408

38 *Sahih Bukhari*: vol. 2, bk. 23, no. 422

ሐ. አይሻ እንዳወራችው የአላህ መልእክተኛ እንዲህ ብለዋል፡- "መፆም ሲገባው ሳይፆም የሞተ ሰው የእርሱ ወኪል ሊፆምለት ይገባል።" (ሳሂህ አል-ቡኻሪ ቅፅ 3፣ መጽሐፍ 31፣ ቁጥር 173)

ስለዚህ በእስልምና አንድ ሰው ለእናንተ ሲል መልካም ሥራ ከሠራ ያ መልካም ሥራ ለናንተ ይመዘገብላችኋል። ይህንን ነጥብ ኋላ ላይ እናነሳዋለን ነገር ግን ይህ ከወንጌል ጋር የሚገጣጠም ጠቃሚ ነጥብ መሆኑን ለመጠቆም እንወዳለን።

በመቃብር ውስጥ ያሉት እስከ ዕለተ ትንሣኤ ድረስ በዚያ ይቆያሉ። በዚያን ዕለት መልካምና ክፉ ሥራቸው ይመዘናል። ከሰማዕታት በተፃራሪ የገሃነምን ፍርሃት ያያሉ።[39] በፍርድ ቀን ሊሆን የሚችል አራት ዓይነት ውጤት ወይንም ድብልቅ ውጤት አለ፡-

1. አንድ ሰው በራሱ ተግባር ወይንም በሌሎች ሰዎች በተሠራለት ሥራ የፈጣሪን ምህረት ለማግኘት በቂ መልካም ሥራዎች አሉት ስለዚህ ወደ ገነት ይሄዳል። (ማጣቀሻዎች ሀ፣ ለ፣ ሐ)
2. አንድ ሰው የእርሱን መጥፎ ሥራ የሚሸከምለት ሌላ ሰው ስላለ ወደ ገነት ይሄዳል።

   መ. (ይህንንም የሚሉት) በትንሣኤ ቀን ኃጢአቶቻቸውን በሙሉ ከነዚያም ያለ ዕውቀት ኾነው ከሚያጠሟቸው ሰዎች ኃጢአቶች ከፊሉን ሊሸከሙ ነው፤ ንቁ የሚሸከሙት ኀጢአት ምንኛ ከፋ! (ቁርኣን 16፡25)

   ሠ. አቡ ሙሳ እንዳወራው የአላህ መልእክተኛ እንዲህ አሉ፤ በዕለተ ትንሣኤ የኔ ኡማህ (እስላማዊ ማሕበረሰብ) በሦስት ቡድን ይሰበሰባል። አንዱ ወገን ስለ ሥራቸው ሳይጠየቅ ገነት ይገባል። ሌላው ወገን በቀላል ጉዳይ ተጠይቆ ገነት ይገባል። ሦስተኛው ደግሞ እንደ ተራራ የከበዱ ኃጢአቶችን ተሸክሞ ይመጣል። አላህ ስለ እነርሱ የበለጠ አዋቂ ቢሆንም መላእክቱን እንዲህ ሲል ይጠይቃል፡- እነዚህ እነ ማን ናቸው? እንዲህ ሲሉ ይመልሳሉ፡- ያንተ ትሁት ባርያዎች ናቸው። እርሱም እንዲህ ይላል፡- ከእነርሱ ላይ ኃጢአቶቻቸውን በማውረድ በአይሁድና በክርስቲያኖች ላይ ጫኑ። የኔ ትሁት ባርያዎች በኔ ምህረት ወደ ገነት ይግቡ። ሐዲሱ ተዓማኒ ሲሆን በሐኪም ሙስተድራክ ተጠቅሷል። (*110 Ahadith Qudsi*, trans.: Syed Masood-ul-Hasan, pp. 20-21.)[40]

---

[39] ቁርኣን 3:185, 19:66-73

[40] እንዲሁም *Sahih Muslim*, bk. 37, no. 6665-6668

ይህ ማለት በፍርድ ቀን አንድ ሰው የሌላውን ኃጢአት ይሸከማል ማለት ነው። አሁንም ይህንን ሐሳብ ወደ ኋላ የምናነሳው ሲሆን ከወንጌል ጋር የሚገጣጠም ጠቃሚ ነጥብ መሆኑን ለመጠቆም እንወዳለን።

3. አንድ ሰው ሌላ ሰው የፈጣሪን ምሕረት ለምኖለት ሊድን ይችላል። በዚያ ሰው ምልጃ ምክንያት ወደ ገነትም ይሄዳል።
   አነስ እንዳስተላለፈው ነቢዩ እንዲህ ሲሉ ሰማሁ፡- በትንሣኤ ቀን እንዲህ ብዬ ምልጃ አቀርባለሁ፡- “ጌታዬ ሆይ! በልባቸው ውስጥ የሰናፍጭ ቅንጣት ታክል እምነት ያላቸውን ሰዎች እንኳ ወደ ገነት አግባ።” እነዚያም ሰዎች ወደ ገነት ይገባሉ፤ እኔም እንዲህ እላለሁ፤ “አላህ ሆይ የመጨረሻ ትንሽ የሆነ እምነት ያላቸውን ሰዎች እንኳ ወደ ገነት አግባ።” (ሳሂህ አል-ቡኻሪ ቅፅ 1፣ መጽሐፍ 93፣ ቁጥር 600)

የተለያዩ ሰዎች ስለ እናንተ ሊማልዱ ይችላሉ ነገር ግን የሙሐመድ ምልጃ ከሁሉ የተሻለ ነው።[41] የሙስሊሞች ተስፋ ሙሐመድ ለእነርሱ እንደሚማልድና በዚያም እንደሚድኑ ነው።

4. በመጨረሻም አንድ ሰው ወደ ገሃነም ሊሄድ ይችላል። ይህ ሰው ሙስሊም ሊሆንም ላይሆንም ይችላል። ይህ በቀጣይ የምንመለከተው መንገድ ነው።

## ሦስተኛ መንገድ፡ መጥፎ ሙስሊም - ወደ መቃብር የሚሄዱ፣ ከዚያም ወደ ፍርድ፣ ከዚያም ወደ ገሃነም፣ መከዚያም ወደ ገነት የሚሄዱ

የመጨረሻው ወደ ገነት የመሄጃ ሥቃይ ያለበት መንገድ በገሃነም በኩል ወደ ገነት መሄድ ነው። በዚህ ሁኔታ አንድ ሰው ሲሞት ወደ መቃብር ይሄዳል። በፍርድ ቀን በቂ መልካም ሥራ ወይንም ምልጃ ስለሌላቸው ወደ ገሃነም ይሄዳሉ። በገሃነም ስለ ክፉ ሥራቸው ሊሠቃዩ ይችላሉ፤ ምልጃ በእነርሱ ምትክ ሊደረግ ይችላል፤ ነገር ግን የመጨረሻ ትንሹ ትክክለኛ እምነት ካላቸው ፈጣሪ ምህረት አድርጎላቸው ወደ ገነት ሊያመጣቸው ይችላል።[42]

> “ከአላህ በስተቀር ሊመለክ የሚገባው ማንም የለም” ብሎ የተናገረ ሰው፤ በልቡም ውስጥ የገብስ ዱቄት ያህል ክብደት ያለው እምነት ያለው ሰው ከገሃነም ይወጣል። (ሳሂህ አል-ቡኻሪ ቅፅ 1፣ መጽሐፍ 2፣ ቁጥር 42/43)

## የፍርድ ቀን


አንድ ሙስሊም ምን ያህል እንደተሳካለት የሚያውቀው በፍርድ ቀን ነው። ቁርአን ከሰማዕታት በስተቀር ሁሉም ሰዎች ወደ ገሃነም አፋፍ በመሄድ እጣ ፈንታቸውን እንደሚያገኙ ይናገራል።

---

41 *Sahih al-Bukhari*: vol. 6, bk. 60, no. 3.

42 Ahmad ibn Naqib al-Misri, *Reliance of the Traveller - A Classic Manual of Islamic Sacred Law*, v2.7, p. 824

## ድነት በእስልምና




> ከእናንተም ወደ እርሷ ወራጅ እንጂ አንድም የለም። ይህም (ጊዜ) ያ ወደ ጌታህ የኾነ ሕግ ነው። ከዚያም እነዚያን የተጠነቀቁትን እናድናለን። አመጸኞቹንም የተንበረከኩ ኾነው በውስጧ እንተዋቸዋለን። (ቁርኣን 19፡71-72፣ 21፡101-102)

በዚህ ላይ ብዙ ማለት ይቻላል ነገር ግን በእስልምና ወደ ገነት የመሄጃ ሦስቱ መንገዶች እነዚህ ናቸው።

## ትግበራ

የእስልምናን የደህንነት አካሄድ ከተረዳን ዘንዳ ከዚህ ቀደም ከተነገረን በላይ ርዕሱን የተመለከቱ ብዙ ጉዳዮች መኖራቸውን እንደተረዳችሁ ተስፋ አደርጋለሁ። የእስልምና አምላክ ሊያድነን ምንም ነገር አላደረገም፤ እንዲያውም እስልምና መዳንን አያመጣም፤ ከዚህ ይልቅ የአምላክን ምሕረት ለማግኘትና ራሳችሁን ለማዳን የተለያዩ መንገዶችን መጠቀም ይኖርባችኋል። ይህንን ማወቅ ለወንጌል ሥራ የሚጠቅመን እንዴት ነው?

1. አሁን የመጫወቻው ሜዳ ስለተደላደለ አንድ ሙስሊም በትክክል ከሚያምንበት ነገር ተነስተን ውይይት ውስጥ ልንገባ እንችላለን። ከአሁን በኋላ አንድ ሙስሊም “በእስልምና መዳን ቀላል ነው፣ አላህ ይምራል፣ ክርስትና ግን ውስብስብ እና ከባድ ነው” ሊላችሁ አይችልም።

ሙስሊሞች በቂ መልካም ሥራዎችን ሠርተው እንደሆነ መጠየቅ ትችላላችሁ፣ ነገር ግን ስለተለያዩ መንገዶች ማውራት ትችላላችሁ፣ ምናልባትም የቀደመውን ሥዕላዊ መግለጫ ብታሳዩዋቸው መልካም ነው። እኔ ሥዕላዊ መግለጫው በስልኬ ላይ አለኝ። በሥዕላዊ መግለጫው ካልተስማሙ የተሻለ እንዲስሉ ይጠይቋቸው።

3. በየትኛው መንገድ ላይ እንደሚገኙ ጠይቋቸው። እንደማያውቁ ሊነግሯችሁ ይችላሉ። እናንተም እንዲህ ያለ ምላሽ ልትሰጡ ትችላላችሁ፡- አዎን ሰዎች ወደ አምላክ ለመድረስ ብዙ ጎዳናዎችን ለመከተል ይሞክራሉ፣ እግዚአብሔር ሊያድነን ሲመጣ ግን በአንድ መንገድ ብቻ ነው፣ እርሱም ኢየሱስ ለኃጢአታችን መሞቱ ነው። እኔ ያለሁበት መንገድ ይህ ነው። አንተም ወደዚህ መንገድ መምጣት ትችላለህ። እንደምትድን እርግጠኛ መሆን ትችላለህ።"

4. ዋስትና አለኝ ብሎ ከመለሰ፡- ሙሐመድ ምን እንደሚደርስበት እንደማያውቅ የሚያሳዩ የቀደሙትን ሁለት ማጣቀሻዎች ጥቀሱና ሙሐመድ ካላወቀ ማወቅ አትችልም ብላችሁ ንገሩት።

## ድነት በክርስትና

በክርስትና መዳን በኢየሱስ ማንነት ላይ ያተኮረ ነው፤ ወንጌል ደግሞ ክርስቲያኖች ሊሰብኩትና ሊመሩበት የተገባ የኢየሱስ መልእክት ነው። ስለዚህ ስለ ወንጌል ግልጽ መሆን አለብን።

ወንጌል እግዚአብሔር ለዚህ ዓለም ያለውን እቅድ በኢየሱስ ማንነት እንደፈጸመ የሚያውጅ መልእክት ነው። በኢየሱስ በኩል እግዚአብሔር ለስሙ ክብርና ለሕዝቡ መዳንን አምጥቷል። እግዚአብሔር የሰውን ልጅ በአምሳሉ የፈጠረው ክብር እንዲያመጣለትና የሕይወቱ ተካፋይ እንዲሆን ነው። ይሁን እንጂ የፈጣሪያችንን አገዛዝ ውድቅ አድርገን ለእርሱ ክብር ሳናመጣ ቀርተናል። አሁን በኃጢያት እና በሞት መዘዝ እንሰቃያለን፣ ስለዚህ እንደ ኃጢአተኛ ይፈረድብናል፣ እንኮንናለን።

ወደዚህ የኃጢአትና የሞት ዓለም እግዚአብሔር መጥቶ ለኛ የተሳነውን እንደሚያደርግ ቃል ገብቷል።

> እውነትም ታጥቶአል፥ ከክፋትም የራቀ ሰው ለብዝበዛ ሆኖአል። እግዚአብሔርም አየ፥ ፍርድም ስለሌለ ተከፋ። ሰውም እንደሌለ አየ፥ ወደ እርሱ የሚማልድ እንደሌለ ተረዳ ተደነቀም፤ ስለዚህ የገዛ ክንዱ መድኃኒት አመጣለት፥ ጽድቁም አገዘው። (ኢሳ 59፡15-16)
>
> የአዋጅ ነጋሪ ቃል። የእግዚአብሔርን መንገድ በምድረ በዳ ጥረጉ፥ ለአምላካችንም ጐዳና በበረሀ አስተካከሉ። ሸለቆው ሁሉ ከፍ ይላል፥ ተራራውና ኮረብታውም ሁሉ ዝቅ ይላል፤ ጠማማውም ይቃናል፥ ስርጓጕጡም ሜዳ ይሆናል፤ የእግዚአብሔርም ክብር ይገለጣል፥ ሥጋ ለባሹም ሁሉ በአንድነት ያየዋል፥ የእግዚአብሔር አፍ ይህን ተናግሮአልና። (ኢሳ 40፡3-5)
>
> ስላደረግሽውም ሁሉ ይቅር ባልሁሽ ጊዜ፥ ታስቢ ዘንድ ታፍሪም ዘንድ ስለ እፍረትሽም ደግሞ አፍሽን እንዳትከፍቺ፥ ቃል ኪዳኔን ከአንቺ ጋር አጸናለሁ እኔም

እግዚአብሔር እንደ ሆንሁ ታውቂያለሽ፥ ይላል ጌታ እግዚአብሔር። (ሕዝ 16፡62-63)

እርሱም እሥራኤልን ከኃጢአቱ ሁሉ ያድነዋል። (መዝ 130፡8)

ይህንንም መፈፀም የቻለው ጌታ ኢየሱስ ነው። ሁሉም ወንጌላት የሚጀምሩት ኢየሱስ ወደ እኛ የመጣው አምላክ መሆኑን ለማሳየት ኢሳይያስ 40ን በመጥቀስ ነው። መንፈስ ቅዱስ ለእግዚአብሔር ልጅ ሰብዓዊ አካል ሲሰጥና በዚህ አካል አማካኝነት ወልድ ፍጹም ታዛዥ ሕይወትን፣ ኃጢአት የሌለበት ሕይወትን፣ ያልኖርነውን ሕይወት ሲኖር እናያለን ። ወልድ ታዛዥ በመሆን ለአባቱ ክብር አምጥቷል፤ እኛ መስጠት ያልቻልነውን ክብርም እርሱ ለአባቱ ሰጥቷል። ኢየሱስ ሰብዓዊነታችንን ፍጹም ያደርጋል፣ አዲሱን ሰው ፈጥሯል፣ እንዲሁም የጽድቅ ሕይወቱ በእምነት የተሰጠን ስጦታ ነው።

የልጁ ታዛዥነት በመስቀል ላይ በመሞት ተደምድሟል። ለኃጢአት ፍጹም መሥዋዕት ሆኖ ቀርቧል። ይህንን ያደረገው ለአባቱ ክብር ለማምጣትና ስለሚወደን ነው። እንደ አዳም ወኪላችን ስለሆነ ከእርሱ ጋር አንድነት አለን። እርሱ ራሱ ኃጢአት ስለሌለ ኃጢአታችንን ሊሸከም ይችላል። የእግዚአብሔር መለኮታዊ ልጅ በመሆኑ የእርሱ ዋጋ ሊተመን የማይችልና ገደብ የለሽ ነው፤ በመሆኑም የእርሱ መሥዋዕት ኃጢአታችንን ሊያጠብን ይችላል።

እግዚአብሔር ዓለምን በፈጠረ ጊዜ መልካም ነበር። ቁሳዊው ፍጥረት መልካም ነበር፣ እንዲሁም እንደ ቁሳዊ ፍጡር ከሕይወት ዛፍ የዘለአለም ሕይወት እንካፈል ነበር። የዘላለም ሕይወት መንፈሳዊ ብቻ ሳይሆን ሥጋዊም ነው፤ ስለዚህ አዲሱ አዳም ኢየሱስ የዘላለም ሕይወት ምንጭ እንዲሆንልን በአካል ከሞት ተነስቷል። ከሞት መነሳቱ ተልዕኮው የተሳካ እንደነበር ያረጋግጣል። የኢየሱስ ትንሣኤ አብ ሕይወቱንና ሞቱን እንደተቀበለ ያሳያል። ትንሣኤው ወደ እርሱ የሚመጡትን ሁሉ ለማዳን የሚያስችል ኃይል እንዳለው ያሳያል። ኢየሱስ ከሞት መነሳቱ፣ በእግዚአብሔር የፍጥረት ሥራዎች ላይ የሚፈርደው መሲሕ፣ ማለትም የሚገዛውና የሚዳኘው እርሱ እንደሆነ ያሳያል።

አሁን እንደ ሰው፣ ወልድ ወደ ወደ አብ ቀኝ አርጓል፣ ስለዚህ የሰው ልጅ ወደ እግዚአብሔር ፊት እንዲገባ ምክንያት ይሆናል። የሰው ልጅ ራሱን ማዳን አይችልም፣ የሚያድነን ሰው ሆኖ ወደ እኛ የመጣው እግዚአብሔር ነው።

በመንፈስ ቅዱስና በእምነት ከኢየሱስ ጋር አንድ ሆነናል ስለዚህም ያደረገውን ሁሉ ያደረገው ለእኛ ነው። ይህ ወንጌል ነው። ለወንጌል የምንሰጠው ምላሽ ንስሐ መግባትና ለኢየሱስ ጌትነት መገዛት እንዲሁም እርሱ በሚያመጣው መዳን ላይ እምነት መጣል ነው።

ጊዜ ወስደን ወንጌልን በደንብ መማር ይኖርብናል።

## ነቢያት መሠረት በመጣል የኢየሱስን ሞት አስቀድመው ተናግረዋል

በምዕራፍ ሁለት እና ሦስት ላይ ለሙስሊም ጓደኞችሁ በመጀመሪያ ስለ ክርስትና የሰሙትን በመጠየቅ፣ ከዚያም መጽሐፍ ቅዱስ ከይዘቱ ምን እንደሆነ በማብራራትና በመጨረሻም ማቴዎስን እንዲያነቡ በመጋበዝ ወንጌሉን እንድታስተዋውቁ ሐሳብ አቅርቤ ነበር። ማቴዎስን ወይም የትኛውንም ወንጌላት ስታነቡ፣ ሁሉም የቀደሙትን ነቢያት ለመልእክታቸው መሠረት አድርገው ሲጠቅሷቸው ታስተውላላችሁ። ስለዚህ የምንሰብከው ወንጌል አዲስ ነገር ሳይሆን መነሻውና መሠረቱ ቀደምት ነቢያት እንዴት እንደሆኑ ለሙስሊሞች ማሳየቱ ጠቃሚ ነው።

ሙስሊሞች በሁሉም ነቢያት እንደሚያምኑ ይናገራሉ። በዚህ ምክንያት ነቢያት እንዴት መንገድን እንዳመላከቱ በማሳየት የኢየሱስን ሞት ማብራራት የኢየሱስን ሞት ለማስረዳት በጣም ጥሩ መንገድ ነው። ይህንን በመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት፣ የነቢያትን ጉዞ እንዲመለከቱ ታሪኮችን በማሳየት፣ እያንዳንዱን መሥዋዕት በማሳየት እንዲሁም ይህ ሁሉ የኢየሱስን ሞት ለመረዳት እንዴት እንደሚያግዝ በማስረዳት ማድረግ እንችላለን። እነዚህ መሥዋዕቶች ለኢየሱስ መንገድን የጠረጉ የመጀመርያ አስተምሕሮዎች ናቸው።

በማስከተል የሚገኙት የብሉይ ኪዳን መሥዋዕቶችና ከእነርሱ ጋር ልትወያዩዋቸው የምትችሏቸው ነጥቦች ናቸው። ከሙስሊም ወዳጃችሁ ጋር ከማንበባችሁ በፊት በግላችሁ አንብባችሁ በሚገባ ተረዷቸው። ጊዜ የሚያጥራችሁ ከሆነ በቀጥታ ወደ ትንቢተ ኢሳይያስ 53 መሄድ ትችላላችሁ።

እግዚአብሔር ያዘጋጃል - የአብርሃም መሥዋዕት - ዘፍጥረት 22፡1-19

- ይህ ምንባብ ከሙሴ ሕግ ከቶራህ መሆኑን አብራሩ።
- ይህ መሥዋዕት እግዚአብሔር ትክክለኛውን መሥዋዕት በማዘጋጀት የአብርሃምን ልጅ ማዳኑን ያሳያል፤ የወደፊቱንም ያመለክታል፣ ዘፍ. 22፡14
- መሥዋዕቱ በይስሐቅ ቦታ ነው፤ ምትክ ወይም ቤዛ ነው።
- በአብርሃም ለመሥዋዕት የቀረበው ልጅ እስማኤል እንደሆነ ከነገሯችሁ ቁርአን[43] የልጁን ስም እንደማይጠቅስና መጽሐፍ ቅዱስ በጉዳዩ ላይ ግልፅ መሆኑን ንገሯቸው።
- ይህ መሥዋዕት የኢየሱስን የመስቀል ላይ ሞት እንድንረዳ ያግዘናል ምክንያቱም እርሱ እግዚአብሔር እኛን ለማዳን ያዘጋጀው መሥዋዕት ነውና፤ ዮሐ. 3፡16፣ ሮሜ 3፡25

ከፍርድ መዳን - ፋሲካ - ዘጸአት 12፡1-30

[43] ቁርአን 37:83-113

- ስለ ግብፅ መቅሠፍትና ስለ ዘጸአት ተናገሩ። ቁርኣን ስለ ጸአት ቢናገርም የፋሲካውን በግ ግብ አይጠቅስም - ይህ ግን ወሳኝና በመጨረሻው መቅሠፍት ወቅት ነበር።
- ይህ ምንባብ ከሙሴ ሕግ ማለትም ከቶራህ መሆኑን አብራሩ።
- ይህ መሥዋዕቱ፣ ማለትም የበጉ ደም የእግዚአብሔርን ፍርድ እንደሚመልስና ከመቅሠፍት እንደሚያድን ያሳያል።
- በጉ በቤተሰቡ ምትክ ነው የሞተው፤ ምትክ ነው።
- የፋሲካ መሥዋዕት የኢየሱስን የመስቀል ላይ ሞት እንድንረዳ ያግዘናል ምክንያቱም እርሱ የእግዚአብሔርን ፍርድ ከኛ ላይ በመመለስ አድኖናልና፣ ማር. 14፡12-25

ቅዱሱን አምላክ መቅረብ - የስርየት ቀን - ሌዋውያን 16

- ይህ ምንባብ ከሙሴ ሕግ ከቶራህ መሆኑን አብራሩ።
- መቅደሱ የእግዚአብሔር መገኘት እንዳለበት አብራሩ።
- ይህ የሚያሳየው እግዚአብሔር ወደ እርሱ ለመቅረብና በኃጢአት ላይ ያለውን ቁጣውን እንዲመልስ የስርየት መሥዋዕት እንደሚፈልግ ነው።
- መሥዋዕቶቹ በሕዝቡ ፈንታ ይሞታሉ፤ ምትክ ናቸው።
- የስርየት ቀን የኢየሱስን የመስቀል ላይ ሞት እንድንረዳ ያግዘናል ምክንያቱም በእርሱ ሞት ምክንያት የእግዚአብሔር ቁጣ ከኛ ላይ ስለተመለሰ በደ ቅዱሱ አምላካችን መቅረብ ይቻለናል፣ ማር. 15፡38፣ ዕብ. 10፡19-22።

ቃል ኪዳን ማድረግ

- እግዚአብሔር ከኖኅ ጋር እንዴት ነው ቃል ኪዳን ያደረገው? ዘፍ. 8፡20 እና 9፡8-11
- እግዚአብሔር ከአብርሃም ጋር እንዴት ነው ቃል ኪዳን ያደረገው? ዘፍ. 15
- እግዚአብሔር ከሙሴ ጋር እንዴት ነው ቃል ኪዳን ያደረገው? ዘጸ. 24፡8
- መልስ፡ ከላይ ያሉት ቃል ኪዳኖች ሁሉ በመሥዋዕት አማካይነት የተደረጉ ናቸው።
- ኢሳ. 55፡3፣ ኤር. 31፡31-33 በማንበብ እነዚህን መጻሕፍት ማን እንደጻፈ አብራሩ። እግዚአብሔር ቃል የገባው ምንድነው?
- ኢየሱስ በደሙ አማካይነት አዲሱን ቃል ኪዳን በማምጣት እነዚህን ተስፋዎች ፈፅሟል፣ ማቴ. 26፡19-28።

ኢሳይያስ 53

- ኢሳይያስ ማን እንደሆነ፣ መቼ እንደኖረና የራሱ መጽሐፍ እንዴት ሊኖረው እንደቻለ አብራሩ።

- ምዕራፉን ለሙስሊም ወዳጃችሁ ጋር በዝግታ እያነበባችሁ ምን እንደሚሆን ቃል እንደተገባ ጠይቁት። ምዕራፉ ራሱ ይናገራል፤ ኢየሱስ ለኃጢአታችን ሲል እንዴት ባለ ሁኔታ እንደሚሞት በመቶዎች ከሚቆጠሩ ዓመታት በፊት ተነግሯል።

ማስጠንቀቂያ፡ ኢይያስ 53 በጣም ኃይለኛ ምዕራፍ ከመሆኑ የተነሳ ሙስሊም መሪዎች ስለ ኢየሱስ እንዳልሆነ ያስተምራሉ። የሰማኋቸው ሙግቶች የሚከተሉት ናቸው፡-

- *የኢሳይያስ 53 መከራ ተቀባይ አገልጋይ በክፉ ሕዝቦች እጅ መከራ የሚቀበለውን የእሥራኤልን ሕዝብ ያሳያል።* ነገሩ እንደዚያ አይደለም ምክንያቱም ምዕራፉ እንደዚያ አይልምና። በምዕራፉና በትንቢተ ኢሳይያስ ውስጥ እሥራኤላውያን ኃጢአተኞች ሲሆኑ አገልጋዩ ለእሥራኤላውያን ኃጢአት ይማልዳል።
- *አገልጋዩ ለኃጢአታቸው ሲሉ የሚሠቃዩትን ሕዝበ እሥራኤልን ያመለክታል።* ነገሩ እንደርሱ አይደለም ምክንያቱም በመጽሐፉ ውስጥ በግለሰቡና በሕዝበ እሥራኤል መካከል ልዩነት ተደርጓልና። በኢሳይያስ ውስጥ ሁለት አገልጋዮች ናቸው ያሉት፤ አንዱ ታማኝ ያልሆነው ሕዝበ እሥራኤል ሲሆን ሌላኛው ደግሞ የእሥራኤልን ፍፃሜ ወደ ግብ በማምጣት ሕዝቡን ያሚያድን ታማኙ አገልጋይ ነው (ኢሳ. 49፡1-6)፤፤
- *ንፁህ የሆነው አገልጋይ ኢሳይያስ ራሱ ነው።* ይህ ትክክል አይደለም ምክንያቱም ኢሳይያስ ንፁህ አልነበረምና። እንደ ማንኛውም ሰው የኃጢአት ስርየት አስፈልጎታል (ኢሳ. 6፡5-7)።
- *መከራ ተቀባዩ አገልጋይ የበደል መሥዋዕት ነው፤ የበደል መሥዋዕት ደግሞ ላልታሰበ ኃጢአት እንጂ ለሁሉም ዓይነት ኃጢአት አይደለም።* በመጀመርያ ደረጃ ጉዳዩ እንደዚያ ቢሆን እንኳ ምዕራፉ አንድ ሰው ስለሌሎች ኃጢአት መሥዋዕት መሆኑን ያሳያል። ሁለተኛ ያልታሰቡ ኃጢአቶች ከተካተቱ ጉዳዩ የበለጠ የከረረ ይሆናል። ሦስተኛ በበደል መሥዋዕት ውስጥ በማወቅ የሚሠሩ ኃጢአቶች ተካትተዋል፣ ሌዋ. 5፡1፣ ቁ. 5-6፣ 6፡1-7፣ 19፡20-፣ ዘኁ. 5፡5-10።
- *አገልጋዩ ልጆች/ዘር አሉት 53፡10፤ ኢየሱስ ግን ልጆች አልነበሩትም።* ይሁንና አገልጋዩ ከሞት ተነስቷል (ቁ. 9)፤ ስለዚህ የሥጋ ልጆችን አያሳይም። የትንሣኤ ልጆች ናቸው ያሉት። ኢየሱስ ሁለተኛው አዳም በመሆኑ ይህንን አምጥቷል፣ 1ቆሮ. 15፡45-49 ተመልከቱ።

በተጨማሪም የጥንቱ የአይሁድ እምነት ኢሳይያስ 53 ስለ መሲሑ መሆኑን ይስማማ ነበር ።

- እነሆ ፥ ባሪያዬ የተቀባውም መሲሕ ይከናወንለታል፤ እርሱ ከፍ ከፍ ይላል፥ ይበዛል፥ እጅግም ይበረታል። የእሥራኤልም ቤት ብዙ ቀን እንደ ጠበቀው ሁሉ። (Targum of Isaiah 52:13-14)

- [ስለ] መሲሑ [...] ረበናት እንዲህ አሉ፥ የረቢ ይሁዳ ሐናሲ ቤት ለምጻም መጠርያው ነው፤ እንዲህ እንደተባለ "በእርግጥ ሕመማችንንና ሥቃያችንን ተሸክሞአል፤ ነገር ግን በእግዚአብሔር የተመታንና የተጎሳቆለ እንደ ሆነ አስበን ነበር" (ኢሳይያስ 53 ፥ 4)። (Babylonian Talmud Sanhedrin 98b)

ኢሳይያስ 53 በጣም ግልፅ ነው። ለሌሎች ኃጢአት መከራን ተቀብሎ ከሞት የሚነሳ ግለሰብ አለ። ይህንን የፈፀመው ደግሞ ኢየሱስ ብቻ ነው። ጥያቄው፡ ነቢያትን ታምናላችሁን? የሚል ነው።

> እርሱም፦ እናንተ የማታስተውሉ፥ ነቢያትም የተናገሩትን ሁሉ ልባችሁ ከማመን የዘገየ፤ ክርስቶስ ይህን መከራ ይቀበል ዘንድና ወደ ክብሩ ይገባ ዘንድ ይገባው የለምን? አላቸው። ከሙሴና ከነቢያት ሁሉ ጀምሮ ስለ እርሱ በመጻሕፍት ሁሉ የተጻፈውን ተረጐመላቸው። (ሉቃ. 24፡25-27)

ቁርኣን ራሱ ኢየሱስ ነቢያትን እንዳረጋገጠ ስለሚናገር ሙስሊሞች ይህንን ሐሳብ መቃወም የለባቸውም።

> ከተዉራትም ከኔ በፊት ያልለዉን ያረጋገጥሁ ስሆን ... (ቁርኣን 3፡50)

## ኢየሱስ ከማንነቱ የተነሳ የኃጢአት ዕዳችንን ሊከፍል ይችላል

ኢየሱስ እንደ ማንኛውም ሰው አይደለም። እርሱ አምላክም ሰውም ነው። ፍፁም አምላክ ፍፁም ሰው ስለሆነ የዓለምን ሁሉ የኃጢአት ዕዳ መክፈል ይችላል።

## ኢየሱስ ፍፁም አምላክ ፍፁም ሰው ነው

ኢየሱስ ወደ እኛ የመጣ አምላክ በመሆኑ አንድ ተራ ሰው ለሌላ ሰው እንደ መክፈል አይደለም፤ እግዚአብሔር ራሱ ነው ኃጢአታችንን የተሸከመው።

> እግዚአብሔር ሙላቱ ሁሉ በእርሱ እንዲኖር፥ በእርሱም በኩል በመስቀሉ ደም ሰላም አድርጎ በምድር ወይም በሰማያት ያሉትን ሁሉ ለራሱ እንዲያስታርቅ ፈቅዶአልና። (ቆላ. 1፡19-20)

ኢየሱስ ሩቅ ቆሞ ተመልካች ወይንም ጉዳዩ የማይመለከተው ሦስተኛ ወገን አይደለም። ኃጢአታችንን ለማስወገድ የመጣ አምላክ ነው። ወንጀል ከተሠራ ወንጀል ሠሪው ይከፍላል አለበለዚያም ደግሞ ወንጀል የተሠራበት ሰው የወንጀሉን ውጤት ይሸከማል። ኢየሱስ ኃጢአታችንን የተሸከመልን አምላክ ነው።

ኢየሱስ መለኮታዊ ወልደ እግዚአብሔር ነው። እርሱ ያልተገደበ ዋጋ አለው። ከዚህ የበለጠ መሥዋዕት ሊቀርብ አይችልም ስለዚህ ሁሉንም የኃጢአት ዕዳ የመክፈል ብቃት አለው።

በእስልምና አንድ ሰው የሌላውን ኃጢአት መሸከም የሚችል ከሆነ[44] እግዚአብሔር በኢየሱስ በኩል ይልቁኑ ይህንን እንዴት አያደርግልን!

ኢየሱስ ፍፁም ሰውም ነው። በአንክሮ ልናጤናቸው የሚገቡ የሰውነቱ ሁለት ገፅታዎች አሉ፤ እርሱ ወኪላችን ነው እንዲሁም ኃጢአት አልባ ነው።

በመጀመርያ ደረጃ ኢየሱስ ፍፁም ሰው ነው፤ ከሰው ልጆች ጋር ባለው አንድነት እኛን ይወክለናል፡-

> እንግዲህ ልጆቹ በሥጋና በደም ስለሚካፈሉ፥ እርሱ ደግሞ በሞት ላይ ሥልጣን ያለውን በሞት እንዲሽር፥ ይኸውም ዲያብሎስ ነው፥ በሕይወታቸውም ሁሉ ስለ ሞት ፍርሃት በባርነት ይታሰሩ የነበሩትን ሁሉ ነጻ እንዲያወጣ፥ በሥጋና በደም እንዲሁ ተካፈለ። (ዕብ. 2፡14-15)
>
> ስለዚህ የሕዝብን ኃጢአት ለማስተስረይ፥ ለእግዚአብሔር በሆነው ነገር ሁሉ የሚምርና የታመነ ሊቀ ካህናት እንዲሆን፥ በነገር ሁሉ ወንድሞቹን ሊመስል ተገባው። (ዕብ 2፡17)

እግዚአብሔር ወደ ሰዎች ሲመጣ አንዳንድ ሰዎች የውክልና ቦታ አላቸው። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በተለይም ይህ ውክልና ያላቸው ሁለቱ ሰዎች አዳምና ካህኑ ናቸው። ኢየሱስ እንደ ኃጢአት አልባ ሰው ሁለቱንም ሚናዎች ይጫወታል። እስልምና የክህነት ፅንሰ ሐሳብ ባይኖረውም ስለ አዳም መረዳት ስላለው ይህንኑ እንመለከታለን።

ኢየሱስ እንደ አዳም የኛ ወኪል ነው ስለዚህ እኛ ከእርሱ ጋር አንድ በመሆናችን አዳም ያደረገው በኛ ላይ ተፅዕኖ እንዳመጣ ሁሉ ኢየሱስም ያደረገው ለኛ ይሆናል። ክርስቲያኖች ከክርስቶስ ጋር አንድ ሆነዋል፤ እርሱ የአካሉ ማለትም የቤተክርስቲያን ራስ ነው፤ ስለዚህ ያደረገውን ሁሉ ያደረገው ከእርሱ ጋር አንድ ለሆኑት ሁሉ ነው፤ ሲሞት ለኃጢአታችን ነው የሞተው።

ይህ የኢየሱስ የውክልና ሚና ኢየሱስ ለኃጢአታችን ሊሞት እንዴት እንደቻለ ለማብራራት ይጠቅማል። የኢየሱስን የውክልና ሚና መጀመርያ ከመጽሐፍ ቅዱስ በማጣቀስ ሁለተኛ ደግሞ ከቁርአንና ከሐዲስ በማጣቀስ ለሙስሊሞች ማስረዳት ይቻላል ምክንያቱም በነዚህ መጻሕፍት ውስጥ አዳም ወኪላችን እንደሆነ ተገልጿልና።[45]

> ጌታህም ከአደም ልጆች ከጀርባቸቸው ዘሮቻቸውን ባወጣና ጌታችሁ አይደለሁምን? ሲል በነፍሶቻቸው ላይ ባስመሰከራቸው ጊዜ (የሆነውን

[44] ማጣቀሻ መ እና ሠ ይመልከቱ።

[45] ቁርአን 7:172, *Sahih al-Bukhari*: vol. 4, bk. 55, no. 551

> አስታውስ)፤ ጌታችን ነህ መሰከርን አሉ፤ በትንሳኤ ቀን ከዚህ (ኪዳን) ዘንጊዎች ነበርን እንዳትሉ። (ቁርአን 7፡172)
>
> አነስ እንዳወራው ነቢዩ እንዲህ አሉ፡- "ትንሹን ቅጣት በገሃነመ እሳት የሚቀጣውን ሰው አላህ እንዲህ ይለዋል «በምድር ላይ ያለው ሁሉ ያንተ ቢሆን ኖሮ ራስህን (ከገሃነም) ነፃ ለማውጣት ትሰጥ ነበር?» እርሱም እንዲህ ይላል «አዎን»። ከዚያም አላህ እንዲህ ይለዋል «በአዳም የጀርባ አጥንት ውስጥ በነበርክ ጊዜ ከዚህ ያነሰ ነበር የጠየኩህ፣ ማለትም ከኔ ሌላ እንዳታመልክ፣ ነገር ግን አንተ ከኔ ሌላ በማምለክ ላይ በረታህ»"። (ሳሂህ አል-ቡኻሪ ቅፅ 4፣ መጽሐፍ 55፣ ቁጥር 551)

በቁርአንና በሐዲስ መሠረት በሁላችንም አባት በአዳም ውስጥ ሳለን ፈጣሪ ለሁሉም የሰው ልጆች ተናግሮ ነበር። ከእርሱ ሌላ እንዳናመልክ ነግሮናል ስለዚህ ይህንን ካላደረግን ማመካኛ የለንም። ይህንን የአዳምን የውክልና ሚና ለሙስሊሞች ለማሳየት እነዚህን ማጣቀሻዎች ልታነቡላቸው ትችላላችሁ። ከዚያም በወቅቱ የመስማት አቅም የነበረው አዳም ብቻ መሆንኑና ነገር ግን አዳም የኛ ወኪል በመሆኑ ምክንያት ለእርሱ የተነገሩት ቃላት ለኛ እንደተነገሩ ይቆጠራል፣ ይህም ማለት ለአዳም የሆነው ሁሉ ለኛም ሆኗል። ከዚያም ኢየሱስ በአዲስ መንገድ ለመዳናችን የኛ ወኪል መሆኑን ከመጽፍ ቅዱስ አሳዩዋቸው።

> በአንዱም በደል ሞት በአንዱ በኩል ከነገሠ፥ ይልቁን የጸጋን ብዛትና የጽድቅን ስጦታ ብዛት የሚቀበሉ በአንዱ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል በሕይወት ይነግሣሉ። እንግዲህ በአንድ በደል ምክንያት ፍርድ ለኵነኔ ወደ ሰው ሁሉ እንደ መጣ፥ እንዲሁም በአንድ ጽድቅ ምክንያት ስጦታው ሕይወትን ለማጽደቅ ወደ ሰው ሁሉ መጣ። በአንዱ ሰው አለመታዘዝ ብዙዎች ኃጢአተኞች እንደ ሆኑ፥ እንዲሁ ደግሞ በአንዱ መታዘዝ ብዙዎች ጻድቃን ይሆናሉ። (ሮሜ 5፡17-19)

ኢየሱስ እንደ አዳም ተወካያችን ነው፤ ከአዳም ጋር እንደተባበርን ከኢየሱስ ጋር አንድ ሆነናል። እርሱ የአካሉ ማለት የቤተ ክርስቲያን ራስ ነውና ያደረገውን ሁሉ ከእርሱ ጋር ለተባበሩት ሁሉ ነው ያደረገው። እርሱ የሞተው ስለ ኃጢአታችን ነው።

1. *ሙስሊም፡-* አምላክ ለኛ ይቅርታ ለማድረግ መሥዋዕት አያስፈልገውም።

*ክርስቲያን፡-* እስልምና የሚያስተምረው ይህንን አይደለም። ሙስሊሞች የአላህን እዝነት በራሳቸው ጥረት ማግኘት አለባቸው። የአላህን እዝነት ማግኘታቸውን እርግጠኛ የሚሆኑት ሙስሊም ሰማዕታት ብቻ ናቸው።

2. *ሙስሊም፡-* ሕዝቅኤል 18፡20 አንድ ሰው ስለሌላው ኃጢአት እንደማይጠየቅ ይናገራል፤ ስለዚህ ኢየሱስ ለኃጢአታችን ሲል ሊሞት አይችልም።

*ክርስቲያን፡-* አዎ አንዱ ኃጢአተኛ የሌላውን ኃጢአት መሸከም አይችልም ነገር ግን ኢየሱስ ኃጢአት የሌለበት ነው ስለዚህም የተለየ ነው። በሁለተኛ ደረጃ፣ ሕዝቅኤል የኃጢአትን

ስርየት መስዋዕትነት አይከድም፣ እንዲያውም ያስተምራል 40:39፣ 42:13፣ 44:29፣ 45:17, 25። በመጨረሻም፣ በሕዝቅኤል እግዚአብሔር ለእኛ ስርየት እንደሚሰጥ ተስፋ ሰጥቷል።

> ስላደረግሽውም ሁሉ ይቅር ባልሁሽ ጊዜ፥ ታስቢ ዘንድ ታፍሪም ዘንድ ስለ እፍረትሽም ደግሞ አፍሽን እንዳትከፍቺ፥ ቃል ኪዳኔን ከአንቺ ጋር አጸናለሁ እኔም እግዚአብሔር እንደ ሆንሁ ታውቂያለሽ፥ ይላል ጌታ እግዚአብሔር። (ሕዝ 16፡62-63)

3. *ሙስሊም፡-* ቁርአን ማንም የማንንም ኃጢአት መሸከም እንደማይችል ይናገራል፡-

> **ተሸካሚም** (ነፍስ) የሌላይቱን ሸክም (ኃጢአት) አትሸከምም። (ቁርኣን 6፡164)
>
> Every soul earns only to its own account; no soul **laden** bears the load of another. (Qur'an, 6:164, Arberry)

*ክርስቲያን፡-* እባክህን ጥቅሱን በአስተውሎት አንብብ። ይህ ማለት ኃጢአተኛ የሆነ ሰው የራሱ ሸክም ስላለበት የሌላውን ሸክም መሸከም አይችልም ማለት ነው። ክርስቲያኖች ከዚህ ጋር የስማማሉ። ኢየሱስ የኛን ኃጢአት መሸከም የቻለበት አንዱ ምክንያት ከኃጢአት ነፃ መሆኑ ነው።

> እኛ በእርሱ ሆነን የእግዚአብሔር ጽድቅ እንሆን ዘንድ ኃጢአት ያላወቀውን እርሱን ስለ እኛ ኃጢአት አደረገው። (2ቆሮ. 5፡21)

ሁለተኛ እስልምና አንዱ የሌላውን ኃጢአት መሸከም እንደሚችል ያስተምራል።

> (ይህንንም የሚሉት) በትንሣኤ ቀን ኃጢአቶቻቸውን በሙሉ ከነዚያም ያለ ዕውቀት ኾነው ከሚያጠሟቸው ሰዎች ኃጢአቶች ከፊሉን ሊሸከሙ ነው፤ ንቁ የሚሸከሙት ኀጢአት ምንኛ ከፋ! (ቁርኣን 16፡25)

አንድ ሰው ደግሞ መልካም ሥራ ሊሠራላችሁ ይችላል፡-

> ኢብን አባስ እንዳወራው፡- ከጁሃይና ጎሣ የሆነች አንዲት ሴት ወደ ነቢዩ በመምጣት እንዲህ ሰለቻቸው፡- “እናቴ ሐጅ ለማድረግ ምላ ነበር ነገር ግን ሳይሳካላት ሞተች። በእናቴ ፋንታ ሐጅ ላድርግን?” ነቢዩም እንዲህ ሲሉ መለሱ፡- “በእርሷ ፋንታ ሐጅ አድርጊ። በእናትሽ ላይ ዕዳ ቢኖርባት ኖሮ አትከፍይም ነበርን? ስለዚህ የአላህን ዕዳ ክፈይ ምክንያቱም የእርሱ ዕዳ የመከፈል የበለጠ መብት አለውና።” (ሳሂህ አል-ቡኻሪ ቅፅ 3፣ መጽሐፍ 29፣ ቁጥር 77)

ስለዚህ እስልምና የምትካዊ ቤዝዎት አስተምህሮ አለው።

4. *ሙስሊም፡-* ነቢያት ሁሉ ኃጢአት የለሽ ናቸው፤ ኢየሱስ ብቻ አይደለም። ሙሴ ወይም ሙሐመድ ለኃጢአታችን ሊሞቱ ይችሉ ነበር እያልክ ነው?

*ክርስቲያን፡-* እንደ ኢየሱስ ያለ ማንም የለም። ቁርአን ሙሐመድ እንደሌላው ሰው ኃጢአቱን መናዘዝ ነበረበት ይላል።

> እነሆ ከአላህ ሌላ አምላክ አለመኖሩን ዕወቅ፤ ስለ ስሕተትም ለምእመናንም ምሕረትን ለምን፤ አላህም መዘዋወሪያችሁን መርጊያችሁንም ያውቃል። (ቁርአን 47፡19)[46]

5. *ሙስሊም፡* ኢየሱስ ለኃጢአታችን ሲል ከሞተና ለመዳን መልካም *ሥራ መሥራት* ካላስፈለገን ለምን መልካም *ሥራ* እንሠራለን?
*ክርስቲያን፡* መልካም *ሥራ* ስለሠራን አልዳንንም ነገር ግን መልካም *ሥራ* እንድንሠራ ድነናል። የክርስቲያኖች መልካም *ሥራ* ለሌሎች ምክንያቶች ነው፤ ለምሳሌ ሰዎችን ለመርዳት፣ እግዚአብሔርን ስለምንወድና ለእርሱ ምስጋና፣ ትክክለኛና ፍትሃዊ *ሥራዎች* በመሆናቸው እንዲሁም እግዚአብሔርን ስለሚያስደስቱ ነው። ክርስቲያኖች ነጥብ ለማስመዝገብ ሳይጨነቁ በነፃነት ያገለግላሉ።
6. *ሙስሊም፡* መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር ይቅርታ ለማድረግ *መሥዋዕት* እንደማያስፈልገው ይናገራል። ንስሐ ከገባህ ይቅር እንደሚልህ ይናገራል፡-

> *መሥዋዕትን* ብትወድድስ በሰጠሁህ ነበር የሚቃጠለውም *መሥዋዕት* ደስ አያሰኝህም። (*መዝሙር* 51፡16)

ስለዚህ መጽፍ ቅዱስ የኢየሱስ ሞት ለኃጢአታችን አስፈላጊ እንዳልሆነ ይናገራል።
*ክርስቲያን፡* ንስሐ የሚገቡትን ሰዎች እግዚአብሔር ይቅር እንደሚልና *መሥዋዕትን* እንደማይፈልግ የሚናገሩ ጥቅሶች በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አሉ፣ ነገር ግን በአውድ ውስጥ ልታነባቸው ይገባል። ለምሳሌ ያህል *መዝሙር* 51፡16 እግዚአብሔር *መሥዋዕትን* እንደማይፈልግ ቢናገርም *መዝሙሩ* በዚያ *መንገድ* አያልቅም፡-

> አቤቱ፥ በውዴታህ ጽዮንን አሰማምራት፤ የኢየሩሳሌምንም ቅጽሮች *ሥራ*። የጽድቁን *መሥዋዕት* መባውንም የሚቃጠለውንም *መሥዋዕት* በወደድህ ጊዜ፥ ያን ጊዜ በመሠዊያህ ላይ ፍሪዳዎችን ይሠዋሉ። (*መዝሙር* 51፡18-19)

በአውድ ማንበብ ይገባናል እንጂ እስላማዊውን አመለካከት በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ መጫን የለብንም።

መጽሐፍ ቅዱስ በሌላ ቦታ እግዚአብሔር ግብዛዊ በሆነ *መሥዋዕት* ደስ እንደማይሰኝ ይናገራል፤[47] ሆኖም ይህ ማለት ምንም ዓይነት የኃጢአት *መሥዋዕት* መኖር የለበትም ማለት

---

46 እንዲሁም ቁርአን 4:106, 40:55, 48:1-2, 94:1-3, 110:3

47 ሚልክያስ 1፡10

አይደለም። ኃጢአትን ባንሠራና መሥዋዕት አስፈላጊ ባይሆን ኖሮ የተሻለ ነበር[48] ነገር ግን ኃጢአትን ስለምንሠራ ወደ እግዚአብሔር መቅረብ እንችል ዘንድ መሥዋዕት የንስሐ አካል መሆኑን ነቢያት ግልፅ አድርገዋል።[49]

7. *ሙስሊም:* እግዚአብሔር የሰው መሥዋዕት አያስፈልገውም።

> ከዘርህም ለሞሎክ በእሳት አሳልፈህ አትስጥ፥ የአምላክህንም ስም አታርክስ፤ እኔ እግዚአብሔር ነኝ። (ዘሌዋውያን 18፡21)

*ክርስቲያን:* እሥራኤላውያን ልጆቻቸውን ለጣዖት እንዳይሠው እግዚአብሔር ማስጠንቀቁ እውነት ነው፤ ነገር ግን ደግሞ እግዚአብሔር አብርሃምን ልጁን ይስሐቅን እንዲሠዋለት ማዘዙ እውነት ነው፤ ቁርአንም ይህንኑ ያረጋግጣል (ቁርአን 37:83-113)። እግዚአብሔር ይህንን እንዲያደርግ አብርሃምን ሲያዝዘው ኃጢአትን እንዲፈፅም እያዘዘው አልነበረም፤ በእርሱ ዘንድ ተቀባይነት ስለነበረው ነው።

አምላክ ግብረ ገባዊ ያልሆኑ ድርጊቶችን አያዝዝም። (ቁርኣን 7፡28)

8. *ሙስሊም:* ስለ እስልምና ድነት የተናገርከው ልክ አይደለም። ሙሐመድ ትልቁ ጂሃድ ከኃጢአት ጋር የምናደርገው ትግል እንደሆነ ተናግሯል። አነስተኛው ጂሃድ ግን ለእስልምና መዋጋት ነው፡-

> ነቢዩ ከጦርነት ከተመለሱ በኋላ እንዲህ አሉ፡- “ወደ ተሻሉ ቦታዎች ተመልሰናል፣ እናንተም ከትንሹ ጂሃድ በትልቁ ጂሃድ ውስጥ ለመታገል ተመልሳችኋል”። አጃቢዎች እንዲህ ሲል ጠየቁ፡- “የአላህ መልእክተኛ ሆይ ትልቁ ጂሃድ ምንድነው?” እሳቸውም እንዲህ ሲሉ መለሱ “አንድ ሰው በምኞቱ ላይ የሚያደርገው ጂሃድ ነው”። (Tarikh al-Baghadadi 13/493)

*ክርስቲያን:* ጂሃዳውያን ሰማዕታት በቀጥታ ወደ ገነት አይሄዱም ነው እያልክ ያለኸው? ይህ የጠቀስከው አባባል/ሐዲስ ከቁርኣን ጋር አይስማማም፤ ተዓማኒ ሐዲስ አይደለም።

9. *ሙስሊም:-* መጽሐፍ ቅዱስ እርስ በርሱ ይጋጫል። ጳውሎስ ድናችኋል ያለው በእምነት ብቻ ነው (ገላ 2፡15-16) ያዕቆብ 2፡14 ግን ለመዳን እምነት እና ሥራ ሊኖርህ ይገባል ይላል።

*ክርስቲያን:-* በጳውሎስና በያዕቆብ መካከል እርስ በርሱ የሚጋጭ ነገር የለም። ተመሳሳይ ነገር ቢናገሩም የሚጻፉት ተቃራኒ አመለካከት ለነበራቸው አውዶች ነው ። ጳውሎስ እየጻፈ ያለው ለመዳን ሕጉን መጠበቅ እንዳለባቸው ለሚሰማቸው ሰዎች ሲሆን ያዕቆብ ደግሞ ሕጉን ችላ ብለው እምነት እንዳላቸው ለሚሰማቸው ሰዎች ነው። ጳውሎስና ያዕቆብ ለእነዚህ ሁለት የተለያዩ ሁኔታዎች አንዱን ወንጌል ሥራ ላይ አውለዋል። ሁለቱም እንዲህ ይላሉ፡-

---

48 መዝሙር 40:6-8

49 የነነዌ ሕዝቦች ንስሐ ገብተው ያለ መሥዋዕት ምህረትን አግኝተዋል ነገር ግን በመቅደሱ አማካይነት ለእግዚአብሔር ኃልዎት ቅርበት አልነበራቸውም። ወደ እግዚአብሔር መቅረብ ቢያስፈልጋቸው ኖሮ መሥዋዕት ያስፈልጋቸው ነበር።

- አሮጌውን ሕግ መጠበቅ አንችልም፣ ገላ 3፡10፣ 5፡3 እና ያዕቆብ 2፡10።
- በአዲሱ የጸጋና የምሕረት ሕግ ወንጌል መኖር አለብን፣ ገላ 6፡2 እና ያዕቆብ 2፡12።
- በሕይወታችን ውስጥ ከመንፈስ ቅዱስ ሥራ ጋር መራመድ አለብን፣ ገላ 5፡25 እና ያዕቆብ 4፡5።

10. *ክርስቲያን:* - ወደ እግዚአብሔር የሚያደርሰው ብቸኛው መንገድ ኢየሱስ እንደሆነ ተናግሯል ።

> ኢየሱስም። እኔ መንገድና እውነት ሕይወትም ነኝ። በእኔ በቀር ወደ አብ የሚመጣ የለም "(ዮሐ. 14፡6)።

*ሙስሊሞች፡-* ኢየሱስ የተናገረው ነገር በነቢዩ ባለበት ዘመን ለማንኛውም ነቢይ የሚሠራ ነው። ሙሐመድ የመጨረሻው ነቢይ ስለሆነ ወደ አምላክ የሚወስደው መንገድ እሱ ነው።

ክርስቲያን: - ይህ እውነት አይደለም። ማንኛውም ነቢይ እንዲህ ማለት አይችልም። ከኢየሱስ በፊት የነበሩት ነቢያት ራሳቸውን ሳይሆን የአምላክን ማዳን በጉጉት ይጠባበቁ ነበር። መጥምቁ ዮሐንስ ሰዎችን ወደ ኢየሱስ አመለከተ እንጂ እኔ መንገድ ነኝ አላለም (ማርቆስ 1፡7)። ሙሐመድም እኔ መንገድ ነኝ ብሎ አያውቅም። እንዲያውም ሙሐመድ ምን እንደሚደርስበት ግራ ገብቶት ነበር።

> "ከመልክተኞች ብጤ የሌለኝ አይደለሁም። በእኔም በእናንተም ምን እንደሚሥሠራም አላውቅም። ወደእኔም የሚወረደውን እንጅ አልከተልም። እኔ አስፈራሪ ብቻ ነኝ።" (ቁርአን 46፡9)
>
> እሳቸውም [ሙሐመድ] እንዲህ አሉ፡- "እርሱ እንደሆን በአላህ ይሁንብኝ ሞት አሸንፎታል፤ መልካሙንም እመኘለታለሁ። በአላህ ይሁንብኝ እኔ የአላህ መልእክተኛ ብሆንም አላህ ምን እንደሚያደርግብኝ አላውቅም።" በአላህ ይሁንብኝ ከሱ ወዲያ ማንንም ጻድቋል ብዬ መናገር አልችልም… (ሳሂህ አል-ቡኻሪ፣ ቅፅ 5፣ መጽሐፍ 58፣ ቁጥር 266)

11. *ሙስሊም፡-* ኃጢአት የፈጣሪ እቅድ አካል ነው። ትልቅ ጉዳይ አይደለም። ለአላህ ይቅር ማለት ቀላል ነው።

> አቡ አዩብ አንሷሪ እንዳስተላለፉት የአላህ መልእክተኛ እንዲህ አሉ፡- "ኃጢያትን ባትሠሩ ኖሮ አላህ ከህልውናችሁ ጠራርጎ ያጠፋችሁ ነበር፤ ኃጢአትንም በሚሠሩ ሰዎችን ይተካችሁ ነበር፤ ከዚያም እነዚያ ሰዎች አላህን ምህረትን ለምነው ይቅር ባላቸው ነበር። (ሳሂህ ሙስሊም፡ 2748b፣ መጽ. 37፣ ቁ 6621)

*ክርስቲያን፦* አዎ፣ ክርስትናና እስልምና ስለ ኃጢአት ያላቸው ግንዛቤ በጣም የተለያየ ነው። በክርስትና ውስጥ ኃጢአት በጣም ከባድ ነገር ነው። እግዚአብሔር ኃጢአት እንድንሠራ አይፈልግም።

## ትግበራና ማጠቃለያ

1. አለ ክርስቶስ ሞት እየተወያያችሁ ሙስሊም ወዳጃችሁ "አላህ እንዲሁ ይቅር ስለሚለን መስቀል አያስፈልገንም" ቢላችሁ በእስልምና ያሉትን የተለያዩ የመዳን መንገዶች በመዘርዘር ስለ መዳናቸው እርግጠኛ መሆን አለመሆናቸውን ጠይቁ። እስልምና መዳን እንደማይሰጥ አሳዩ። ሙሐመድም እንኳ ምን እንደሚደርስበት አያውቅም ነበር።

2. ከኢየሱስ በፊት የነቢያትን መጻሕፍት ስለ መስዋዕት እንደሚያስተምሩ አሳዩ። ኢየሱስ እንደ አዳም እንዴት ወኪላችን እንደሆነ ግለጹ።

3. ካስፈለገ እስልምና የቤዝዎት ሐሳብ እንዳለው አሳዩ።

4. ሙሐመድ እንዴት ይቅርታ እንደሚያስፈልገውና እንደ ኢየሱስ እንዳልሆነ አሳዩ።

5. በረመዳን ፆም ላይ ከሆኑ ረመዳን ሊያድናቸው እንደማይችል አስረዷቸው።

በመጨረሻም ለሙስሊም ወዳጃችሁ ልትሰጡት ወይም አብራችሁ ልታነቡት የምትችሉት በዚህ ርዕሰ ጉዳይ ላይ የተጻፈ ቡክሌት ዌብሳይቱ ላይ አለ ።

# ምዕራፍ 7

## መቅደስ እና እስላማዊ አስተምህሮ

ይህ ምዕራፍ በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ካሉት ሌሎች ምዕራፎች የተለየ ነው። በሌሎች ምእራፎች እስልምና የሚያስተምረውንና ምን ዓይነት መስተጋብር ሊኖረን እንደሚገባ ተመልክተናል። በዚህ ምእራፍ ማየት የምፈልገው እስልምና ምን እንደሚያደርግ ሳይሆን የሚሠራውን ለምን እንደሚያስተምር ነው። ይህንን ለማድረግ መጽሐፍ ቅዱሳዊውን ቤተመቅደስና ጥፋቱ በእስላማዊ ሥነ-መለኮት ላይ እንዴት ተጽዕኖ እንዳሳደረ እንመለከታለን።

በኢየሩሳሌም የሚገኘው ቤተ መቅደስ የመጽሐፍ ቅዱስ ማዕከል ነው። የዘፀአትና ዘሌዋውያን መጻሕፍት በቤተ መቅደሱ ውስጥ ይከወኑ የነበሩትን ሥነ-መለኮት እና ሥርዓታት ይገልጻሉ። የነገሥት፣ የዜና መዋዕል እና የዕዝራ መጻሕፍት ቤተ መቅደሱን እንደ ዋና ጭብጥ ይዘዋል። ነቢያትና መዝሙራት ስለ መቅደሱ አዘውትረው ይጠቅሳሉ። የመጀመሪያው ቤተመቅደስ በባቢሎናውያን በ587 ዓ.ዓ ፈርሷል። እንደገና ከተሠራ በኋላ ኢየሱስና ሐዋርያቱ የጎበኙትና የተናገሩለት ይህ ቤተ መቅደስ ነበር። በኢየሱስና በሐዋርያቱ ዘመን የነበረው የአይሁድ እምነት የቤተ መቅደሱ ይሁዲነት ይሰኛ። ይህ ሁለተኛው ቤተ መቅደስ በ70 ዓ.ም. በሮማ ወታደራዊ መሪ በቲቶ የፈረሰ ሲሆን ከዚያ ወዲህ እንደገና አልተሠራም።

ይህ ወሳኝ ጉዳይ ነው ምክንያቱም የቤተ መቅደሱ መጥፋት ይሁዲነትን ከቤተመቅደስ ይሁዲነት ወደ ራቢያዊ ይሁዲነት ለውጦታልና። ቤተ መቅደሱ የአይሁድ እምነት ማዕከል ነበር፣ ነገር ግን በመጥፋቱ ሳቢያ የአይሁድ እምነት ልማዶቹን ከእንደገና ማስተካከል ነበረበት። በቤተ መቅደሱ ውስጥ ያለው ሊቀ ካህን ዋና አካል ከመሆኑ ይልቅ፣ አሁን በምኩራብ ውስጥ ያሉት ረቢዎች ይበልጥ አስፈላጊ ሆኑ። አይሁዳውያን በቤተ መቅደሱ የእንስሳትን መሥዋዕት ከማቅረብ ይልቅ ጸሎትን መሥዋዕት አድርገው እንዲያቀርቡ ተምረዋል። ወደ ቤተ መቅደሱ ከመሄድ ይልቅ ምኩራቦች ትኩረት አግኝተዋል። የአይሁድ እምነት በቤተ መቅደሱ መፍረስ ምክንያት አቅጣጫውን ቀይሯል። የቤተመቅደስ ይሁዲነት ራቢያዊ ይሁዲነት ሆነ። ራቢያዊ ይሁዲነት የተባለበት ምክንያት ያዳበሩት ረቢዎች በመሆናቸው ነው። ሳይለወጥ የቀረው አንድ ነገር ቢኖር የጸሎት አቅጣጫ ነበር። አይሁድ ቤተ መቅደሱ በአንድ ወቅት ቆሞ ወደ ነበረው ወደ መቅደሱ ተራራ ዞረው መጸለያቸውን ቀጠሉ።

ይህ ለምን አስፈላጊ ሆነ? ትኩረት የሚሻ ጉዳይ ነው ምክንያቱም ሙሐመድ የተወለደው በ 570 ዓ.ም ነው፤ ይህም ማለት ለ 500 ዓመታት ቤተመቅደስና ተያያዥ ልምምዶች አልነበሩም። ሙሐመድ አይሁዶች የቤተ መቅደሱን ይሁዲነት ሲለማመዱ አላየም ነገር ግን

ረቢያዊ ይሁዲነትን ሲከተሉ ተመልክቷል። ይህ ጉዳይ ትኩረት የሚሻው ሙሐመድ የአይሁዶችን ድርጊት በመኮረጁ ነው።

> ኢብኑ አባስ እንደተረከው፡- ነቢዩ (ሙሐመድ) ከአላህ ዘንድ ትዕዛዝ በሌለበት ጉዳይ ላይ የቅዱሳት መጻሕፍትን ሰዎች (አይሁዶችና ክርስቲያኖች) ይቀዱ (ይኮርጁ) ነበር። የቅዱሳት መጻሕፍት ሰዎች ፀጉራቸውን ይለቁ የነበረ ሲሆን አረማውያንም ፀጉራቸውን ይከፋፍሉ ነበር። ስለዚህ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) መጀመርያ ላይ ጸጉራቸውን ወደ ታች ይለቁ ነበር፤ በኋላ ግን ከፋፈሉት። (ሳሂህ አል ቡኻሪ 5917፣ ቅጽ 7፣ መጽ. 72፣ ቁ. 799፣ ሳሂህ ሙስሊም 2336a)

ሙሐመድ አይሁዶች ወደ ቤተ መቅደሱ ዞረው የሚሰግዱበትን ስርዓት ቀድቷል።

> አል-በራ እንደተረከው፡- ከነቢዩ ጋር ወደ እየሩሳሌም ትይዩ ለአሥራ ስድስት ወይም ለአሥራ ሰባት ወራት ሰገድን። ከዚያም አላህ ፊቱን ወደ ቂብላ (መካ) እንዲያዞር አዘዘው (ሳሂህ አል ቡኻሪ 4492፣ ቅጽ 6፣ መጽ. 60፣ ቁ. 19)

ነገር ግን፣ ሙሐመድ የመቅደሱን ይሁዲ ሳይሆን ረቢያዊ ይሁዲን በመቅዳት ሲከውን ነበር። ይህ አስፈላጊ ነው ምክንያቱም በመቅደሱ አሠራር አማካይነት መንፈስ ቅዱስ አበይት እውነቶችን አመላክቶናልና።

> “በሁለተኛይቱ ግን ሊቀ ካህናት ብቻውን በዓመት አንድ ጊዜ ይገባባታል፥ እርሱም ስለ ራሱና ስለ ሕዝቡ ስሕተት የሚያቀርበውን ደም ሳይዝ አይገባም፤ ፊተኛይቱም ድንኳን በዚህ ገና ቆማ ሳለች፥ ወደ ቅድስት የሚወስደው መንገድ ገና እንዳልተገለጠ መንፈስ ቅዱስ ያሳያል።” ( ዕብራውያን 9:7-8 )

መንፈስ ቅዱስ በቤተ መቅደሱ ያስተማረውን ትምህርት አሁን እንመለከታለን።

1. እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ሊያድር ይመጣል። የእግዚአብሔር እቅድ ሁል ጊዜ መጥቶ ከሕዝቡ ጋር መኖር ነው። እግዚአብሔር ከአዳም ጋር በገነት ነበረ (ዘፍ 3፡8)። ሙሴ የማደሪያውን ድንኳን ከሠራ በኋላ እግዚአብሔር በእሥራኤላውያን መካከል አደረ (ዘጸአት 25: 8)፤ እንዲሁም በሰሎሞን ቤተ መቅደስ አደረ (1ኛ ነገ 8፡10-11)። እኛ ከፍጥረት ዓለም ተነስተን ወደ እግዚአብሔር በመጓዝ ላይ አይደለንም። እግዚአብሔር ወደ እኛ ይመጣል። ቤተ መቅደሱ እግዚአብሔርና ሰው የሚገናኙበት ቦታ ነው። ቤተ መቅደሱ የሚያስተምረን ይህንን ነው።

2. ካህን ያስፈልገናል። ቅዱሱ አምላክ መጥቶ በኃጢአተኛ ሕዝብ መካከል ሲኖር ሁኔታው ጥሩ አይደለም። የእግዚአብሔር ቁጣ በሕዝቡ ላይ ይነድዳል። በዚህ ምክንያት እግዚአብሔር ለእሥራኤላውያን ካህናትን ሰጣቸው። ካህናቱ ቅዱሱን እግዚአብሔርን በመወከል ለሕዝብ ሕዝቡንም በመወከል ለእግዚአብሔር ይቆሙ ነበር። ካህናቱ አስታራቂዎች ነበሩ።

3. የስርየት መሥዋዕት ያስፈልገናል። ኃጢአተኞች ከቅዱሱ አምላክ ጋር ለመገናኘት እንዲችሉ ቍጣውን ለመመለስ ለኃጢአት ዋጋ የሚከፍልበትን መሥዋዕት እንዲያቀርቡ እግዚአብሔር አዘዘ። ካህናቱ እነዚህን መሥዋዕቶች በቤተ መቅደሱ ውስጥ ሕዝቡን ወክለው ያቀርቡ ነበር። ቤተ መቅደሱ የሚያስተምረን ይህንን ነው።

4. የጸሎት አቅጣጫ። ቤተ መቅደሱ የእግዚአብሔር መገኘት ያደረበት ቦታ ስለሆነ የጸሎት አቅጣጫ ነበር። ከእግዚአብሔር ጋር የሚገናኙበት መንገድ ነበር።

5. እሥራኤል ለዓለም ክህነታዊ ሕዝብ ነው፣ ዘጸ 19፡6። ይህ ማለት ቤተ መቅደሱ ለዓለም ህዝቦች ሁሉ ፋይዳ ነበረው ማለት ነው። ሕዝቦች ሁሉ ወደ ቤተ መቅደሱ እንዲመጡና እንዲጸልዩ፣ ስለ እግዚአብሔር እንዲማሩና ወደ እርሱ እንዲቀርቡ ተጋብዘዋል።

6. መሲሑ እግዚአብሔርንና የሰው ልጆችን አንድ የሚያደርግ ቤተ መቅደስ ሠሪ ነው። እግዚአብሔር ከንጉሥ ዳዊት ጋር ቃል ኪዳን አድርጎ ነበር። በዚህ ቃል ኪዳን እግዚአብሔር የዳዊት ልጅ በእግዚአብሔር መንግሥት ላይ ይነግሣል፣ እግዚአብሔር አባቱ ይሆናል፣ የእግዚአብሔር ልጅ ይሆናል፣ ይህም ልጅ ቤተ መቅደሱን ይሠራል በማለት ተናገረ። ይህ የመሲሑ ቃል ኪዳን ነው።

“ዕድሜህም በተፈጸመ ጊዜ ከአባቶችህም ጋር ባንቀላፋህ ጊዜ፥ ከወገብህ የሚወጣውን ዘርህን ከአንተ በኋላ አስነሣለሁ፥ መንግሥቱንም አጸናለሁ። እርሱ ለስሜ ቤት ይሠራል፤ የመንግሥቱንም ዙፋን ለዘላለም አጸናለሁ።” (2 ሳሙኤል 7:12-14)

ስለዚህ መሲሑ እግዚአብሔርንና የሰው ልጆችን አንድ ላይ የሚያገናኝ ቤተ መቅደስ ሠሪ ነው። ኢየሱስ ስለ ቤተመቅደስ ግንባታ የተናገረው ለዚህ ነው፣ ዮሐ 2፡12።

7. አዲሱ ፍጥረት ከመቅደስ ጋር ተገልጿል። ነቢያት አዲሱን ፍጥረት፣ የትንሳኤውን ጊዜ፣ መጻዒውን ዘመን ሲገልጹ የቤተመቅደስ ቋንቋ ይጠቀሙ ነበር። ይህንንም በሕዝቅኤል 40-48 እና በራዕይ 21-22 እንመለከታለን። አዲሱ ፍጥረት ፍጹም ተብሎ ተገልጿል፤ እግዚአብሔርና የሰው ልጆች በአንድነት የሚኖሩበት እንዲሁም የሰው ልጅ እግዚአብሔርን በፍጽምና የሚያመልኩበት መቅደስ ተብሏል።

እነዚህ ሰባት ነጥቦች መንፈስ ቅዱስ በቤተ መቅደሱ ያስተማራቸው ሲሆን እነዚህ ሰባት ነጥቦች የቤተመቅደሱ ይሁዲነት ይለማመደው የነበረ ነው፤ ማለትም የቤተመቅደስ ይሁዲነት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ይሁዲነት፣ የነቢያት ይሁዲነት ነው። ነገር ግን፣ ረቢያዊ ይሁዲነት እነዚህን ነገሮች አይተገብረውም ምክንያቱም ቤተመቅደስ ስለሌለ፣ እናም ሙሐመድ የተመለከተው እና የቀዳው ረቢያዊ ይሁዲነትን ነው። ቁርአንን ስናነብ ረቢያዊ ይሁዲነትን እናያለን፤ ይህ የቤተ መቅደሱ ይሁዲነት አይደለም።

## የቤተመቅደስ ሥነ-መለኮት እና ቁርኣን

ቁርኣንን የቤተመቅደስን ስነ መለኮት በልቡናችን ይዘን ስናነበው ምን እናስተውላለን?

1. በቁርኣን ውስጥ እግዚአብሔር ከሕዝቡ ጋር ለመኖር ወደ ፍጥረት አልመጣም። በቁርኣን አላህ አዳምን ሲፈጥረው አዳም በሰማይ በገነት ነበር፣ በምድር ላይ አልነበረም። ቁርኣን ስለ ሙሴ ሲናገር ስለ ማደሪያውና ስለ እግዚአብሔር ከሕዝቡ ጋር ስለመኖሩ ፈጽሞ አይጠቅስም። ሰለሞንንም እንዲሁ ነው። በቁርኣን ውስጥ ወደ አላህ ጉዞ ላይ ነን፣ አላህ ወደ እኛ አይመጣም። ሙሐመድ ለምን እንዲህ አስተማረ? ምክንያቱም ሙሐመድ የቀዳው የረቢያዊ ይሁዲነት ልምምዶችን እንጂ የቤተመቅደሱ ይሁዲነትን ስላልነበረ ነው።

“አላህ መፍጠርን ይጀምራል። ከዚያም ይመልሰዋል፤ ከዚያም ወደርሱ ትመለሳላችሁ።” (ቁርኣን 30፡11)

2. በእስልምና ክህነት የለም። ይህ አንዳንድ ሙስሊሞች የሚኮሩበት ነገር ነው ነገር ግን የሚያኩራራ አይደለም። በሁሉም የነቢያት መጻሕፍት ውስጥ ካህናት አሉ። አብርሃም ካህን መልከ ጼዴቅ ነበረው፣ ለእሥራኤላውያን የአሮን ክህነት ነበር፣ እሥራኤል የክህነት ሕዝብ ነበር፣ እንዲሁም ኢየሱስ የክህነት ፍጻሜ ነው። እግዚአብሔር ቅዱስ እንደሆነና ሰዎች ኃጢአተኞች እንደሆኑ ካመንክ ነቢያት ካህን ያስፈልግሃል ይላሉ። በእስልምና ግን ክህነት የለም። ለምን? ምክንያቱም ሙሐመድ የገለበጠው የረቢያዊ ይሁዲነት ልምምዶችን እንጂ የቤተመቅደስ አይሁዶች ስላልሆነ።

3. በእስልምና የስርየት መስዋዕትነት የለም። እስልምና መስዋእት አለው ነገር ግን አላማው በፍፁም አልተገለፀም። እናንተን ወደ እግዚአብሔር ፊት ለማቅረብ በቁርኣን ውስጥ የማስተሰረያ መስዋዕት ለማቅረብ ምንም ትእዛዝ አልተሰጠም። ለምን? ምክንያቱም ሙሐመድ የገለበጠው የረቢያዊ ይሁዲነት ልምምዶችን እንጂ የቤተመቅደሱ ይሁዲን ስላልሆነ።

4. በቁርኣን ውስጥ፣ እሥራኤል እግዚአብሔር ለዓለም የሚናገርበትና ዓለም ወደ እርሱ የሚመጣበት ልዩ የክህነት ሕዝብ አይደለም። ይልቁንም እያንዳንዳቸው ሕዝቦ የራሳቸው ነቢያት አሏቸው (ቁርኣን 16፡36)።

5. በቁርኣን ውስጥ ኢየሱስ መሲህ ተብሎ ተጠርቷል ነገር ግን መሲሑ ቤተ መቅደሱን የሠራ እንዲሁም አምላክንና የሰውን ልጅ ያገናኘ እንደሆነ ምንም መረዳት የለም።

6. ቁርኣን ስለ ጀነትና ስለ አዲስ ፍጥረት ሲናገር ፍጹም በሆነው ቤተ መቅደስና አምልኮ አይገልጸውም (ቁርኣን 56፡1-56)። ይልቁንም አምልኮ የሌለበት የደስታ ቦታ ብቻ እንደሆነ በማመላከት ያልፈዋል።

7. በቁርአን ውስጥ አብርሃም በመካ ካዕባን ሠራ፣ የአላህ መገኘት ግን በካዕባ ላይ አልወረደም። አምላክ በዚያ አያድርም። ባዶ ነው። ወደ እሱ ለመጸለይ ምንም ምክንያት የለም። ካዕባ ቤተ መቅደስ አይደለም።

8. ሙሐመድ ኢየሩሳሌም የሚገኘውን ቤተመቅደስ ሲጠቅስ መስጊድ ብሎ ይጠራል (ቁርአን 17፡7)። እንደ ቤተመቅደስ ያለውን ግልጋሎት መረዳቱን የሚያሳይ ፍንጭ የለም።

9. በቁርአን ውስጥ ሙሐመድ ስለ ሙሴ፣ አሮንና ኢየሱስ ብዙ ታሪኮችን ተናግሯል፣ ነገር ግን አንዳቸውም ቢሆኑ ከቤተመቅደስ ተግባራት ጋር ግንኙነት የላቸውም። በቁርአን ውስጥ ሙሴ፣ አሮንና ኢየሱስ ረቢያዊ አይሁዶች እንጂ የቤተመቅደሱ አይሁዶች አይደሉም። ይህንን በተለይ ከአሮን አኳያ እናያለን። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ፣ የአሮን ዋና ተግባር የእሥራኤል ካህን መሆን ነው። በቁርአን ግን አሮን ነቢይ ብቻ ነው። ኢየሱስ ነቢይ ብቻ ነው ከማለት አልፎ አሮንንም ነቢይ ብቻ ያደርገዋል።

እነዚህ ዘጠኝ ነጥቦች ሙሐመድ ከመጽሐፍ ቅዱሳዊው የቤተመቅደስ ይሁዲነት ይልቅ የረቢያዊ ይሁዲነት ልምምዶችን በመኮረጅ ሥነ መለኮቱን እንዴት እንደተማረ ያሳያሉ።

ቁርአን ሥላሴንና ሥጋዌን ለማስተባበል እንደሚሞክር ሁሉ መጽሐፍ ቅዱሳዊውን የቤተ መቅደሱን አስተምህሮ ለማስተባበል እንደማይሞክር ልብ በሉ። ለዚህም ምክንያቱ ሙሐመድ ስለ ጉዳዩ ምንም ዓይነት ዕውቀትና መረዳት ስላልነበረው ነው። ስለዚህ ቁርአን ብዙ የነብያት ዋና ዋና አስተምህሮዎች የጎደሉት መጽሐፍ ነው። እግዚአብሔር ከሕዝቡ ጋር ሊያድር ይመጣል የሚለው ይጎድላል። ክህነት እና መስዋዕትነት የለም። የእሥራኤልን ሕዝብ ያለው ልዩ ቦታ የለም። እግዚአብሔርንና የሰው ልጆችን አንድ የማድረግ የመሲሑን ሚና ይጎድለዋል። እስልምና የሚያስተምረውን ለምን እንደሚያስተምር አሁን መረዳት እንደቻላችሁ ተስፋ አደርጋለሁ።

መጽሐፍ ቅዱስን ወደ ቁርአን መቀየር ፈለጋችሁ እንበል። እንዴት ነው የምታደርጉት? ድንኳኑን/መቅደሱን፣ ከሕዝቡ ጋር ለመኖር ወደ ማደሪያው የሚመጣውን እግዚአብሔርን፣ ካህናቱን፣ የማስተሰረያውን መሥዋዕት፣ የመሲሑንና የቤተ መቅደሱን ግንኙነት፣ አዲሱን ፍጥረትና የመቅደሱን የሚያመለክቱ ማጣቀሻዎችን በሙሉ ከውስጡ በመቅደድ ማውጣት ይጠበቅባችኋል። ይህን ብናደርግ ምን ይቀረናል? የረባ ነገር አይኖረንም። ውስጡ ባዶ የሆነ ሽፋን ብቻ ይቀርልናል። እንግዲህ ቁርአን ማለት ይህ ነው።

## ትግበራ

መጀመሪያ፣ ክርስትናን ለመረዳት መጽሐፍ ቅዱሳዊውን የቤተመቅደስ ይሁዲነት መረዳት ያስፈልጋችኋል።

በሁለተኛ ደረጃ፣ እስልምናን ለመረዳት የረቢያዊ ይሁዲነት ልምምዶችን መረዳት ያስፈልጋችኋል ምክንያቱም የሙሐመድ ታሪካዊ አውድ መጽሐፍ ቅዱሳዊ የቤተመቅደስ ይሁዲነት ሳይሆን ረቢያዊ ይሁዲነት ነበርና።

በሦስተኛ ደረጃ፣ ቁርአንን አንብባችሁ የምታውቁ ከሆነ አሁን የምታነቡትን መረዳት ትችላላችሁ። የቤተመቅደስ ሥነ-መለኮት የሌለው መጽሐፍ ነው።

በአራተኛ ደረጃ፣ ስለ መቅደሱ ግንዛቤ እስከሌላቸው ድረስ ሙስሊሞች ኢየሱስንና ወንጌሉን ለመረዳት መሠረት የላቸውም፡- እግዚአብሔር በመቅደሱ እንዳደረገው ሁሉ ኢየሱስ ከእኛ ጋር ለመኖር የመጣ አምላክ ነው። ኢየሱስ ሰውነቱን በቤተመቅደስ መስሏል (ዮሐ. 2፡19)። እግዚአብሔርና የሰው ልጆች ፍጹም የተገናኙበት እውነተኛ ቤተ መቅደስ እርሱ ነው። ኢየሱስ እግዚአብሔርን ለሕዝቡ እንዲሁም ሕዝቡን ለእግዚአብሔር የሚወክል እውነተኛ ካህን ነው። እርሱ የእግዚአብሔርን ቁጣ የሚመልስ እውነተኛ መስዋዕት ነው። ኢየሱስና ወንጌልም በቤተ መቅደሱ ትምህርት ውስጥ መሠረታቸው አላቸው። ቤተመቅደስን ለሙስሊሞች ማስተማር ከወንጌል ጋር የማስተዋወቅ ጥሩ መንገድ ሊሆን ይችላል።

አምስተኛ፣ ብዙ ሙስሊሞች እስልምና ከአይሁድ እምነት ጋር ይመሳሰላል ብለውኛል። እውነትም ከረቢያዊ ይሁዲነት ጋር ተመሳሳይ ነው ነገር ግን ከመጽሐፍ ቅዱሳዊው የነቢያት ይሁዲነት ከሆነው የቤተመቅደስ ይሁዲነት ጋር አይደለም።

በመጨረሻም፣ ስለ ቤተመቅደስ መማርና ማስተማር ክርስቲያኖች የእስልምናን አስተምህሮ እንዲያውቁ ከማዘጋጀት አኳያ መሠረታዊ የክርስትናን አስተምህሮ እንዴት ማስተማር እንደምትችሉ ጥሩ ምሳሌ ነው።

# ምዕራፍ 8

## የኢየሱስ ሞት

> እኛ የአላህን መልክተኛ የመሬምን ልጅ አልመሲሕ ዒሳን ገደልን በማለታቸው (ረገምናቸው)፤ አልገደሉትም፤ አልሰቀሉትምም ግን ለነሱ (የተገደለው ሰው በዒሳ) ተመሰለ እነዚያም በርሱ ነገር የተለያዩት፣ ከርሱ (መገደል) በመጠራጠር ውስጥ ናቸው፤ ጥርጣሬን ከመከተል በስተቀር በርሱ ነገር ምንም ዕውቀት የላቸውም፤ በእርግጥም አልገደሉትም። ይልቁኑስ፣ አላህ ወደርሱ አነሳው፤ አላህም አሸናፊ ጥበበኛ ነው። ሱረቱል አል-ኒሳእ (4) ፡157-158

የኢየሱስ ክርስቶስ ሞት እውነተኛ የታሪክ ክስተት እንደመሆኑ መጠን ለወንጌል ማዕከላዊ ነው። አዲስ ኪዳን የዚህ ክስተት ምስክር መሆኑን ይነግረናል። ይሁን እንጂ ሙስሊሞች በተለምዶ ይህ ፈጽሞ እንዳልተከሰተ፣ በኢየሱስም ፈንታም ሌላ ሰው እንደተሰቀለ ይህም ሰዎች ኢየሱስ የተሰቀለ እንደመሰላቸው ያስተምራሉ። የክርስቶስ ስለኃጢአታችን በመስቀል ላይ መሞት የወንጌሉ መልእክት ሲሆን የእርሱን ሞት መካድ ለሙስሊሞች ወንጌሉን እንዳይሰሙ ትልቅ እንቅፋት ነው። በዚህ ምዕራፍ በዚህ ርዕስ ዙርያ እንዴትና መቼ ውይይት መጀመር እንደምንችል እናያለን።

### የኢየሱስ ስቅለትና ኢስልምና

ክርስቲያኖች ኢየሡስ ስለኃጢአታቸው እንደሞተ እየሰሙ ያድጋሉ ስለዚህ የእርሱ መሞት ለኛ ግልጽ ይመስላል። ስለ አሟሟቱም ከመጽሐፍ ቅዱስ እናነባለን፣ እንደ እምነት መግለጫችን እንመሰክራለን፣ አንዳንድ ጊዜ ክስተቱን የሚያረጋግጡልንን ከመጽሐፍ ቅዱስ ውጪ ያሉ ታሪካዊ ዳራዎችን እናጠናለን። እንድንጠራጠረው የሚያደርገን ምንም ምክንያ የለንም። ቢሆንም ሙስሊሞች ደግሞ ኢየሱስ እንዳልተሰቀለና የተሰቀለ እንደተመሰለ እየሰሙ ያድጋሉ። በጊዜው ምን እንደተከሰተ የተለያዩ ትወራ አሉ። ነገር ግን ለቀደሙ ሙስሊሞች ስቅለት በፍጹም አልተከናወነም። እንደ ሙስሊም ኢየሱስ እንዳልተሰቀለ ማመን ሃይማኖታዊ ግዴታ ነው። ይህም እስልምና የራሱ የሆነ እምነትና መረዳትን ቀድሞ የያዘ እምነት ነው። ይህም ደግሞ ለመስቀሉ ሚዛናዊ (neutral) አይደለም።

ይህንን ማወቁ በጣም ጠቃሚ ነው። ምክንያቱም ይህ ርዕስ በክርስቲያኖችና በሙስሊሞች ዘንድ ለውይይት መነሳቱ አይቀርምና። ወንጌልን እንመሰክርላቸው የኢየሱስን ሞት እንናገራለን። መጽሐፍ ቅዱስን ለሙስሊች ስናነብላቸው የኢየሱስን ሞት እናነብላቸዋለን። ወደ ቤተ-ክርስቲያንም ሆነ ወደ ቤት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ስንጋብዛቸው ስለኢየሡስ ሞት እንነግራቸዋለን። የኢየሱስን ፊልም ሲያዩም ኢየሱስ ሲሞት ያዩታል። መዝሙሮችንም ሲሰሙ የኢየሡስን ሞት ይሰማሉ። የኢየሱስ ሞት ጉዳይ ያለምንም ጥርጥር የሚነሳ

አንገብጋቢ ጉዳይ ሲሆን ሙስሊም ወገኖችም ስለእርሱ ምን እንደሚያምኑ ማወቅ ጠቃሚ ነው።

ስለዚህ የስቅለቱ ጉዳይ ሲነሳ *“ስለ ኢየሱስ ሞት ምንድነው ከዚህ በፊት የሰማሄው ደግሞስ ምንድነው የምታምነው?”* ብሎ መጠየቅ አስፈላጊ ነው።

ይህን ጥያቄ መጠየቅ አስላጊ ነው። ምክንያቱም ይህን ሁሉ ጊዜ ኢየሱስ ፈጽሞ አይሞትም ብለው እያመኑ በትሕትና ይመልሱ የሆናል አልያም ምንም ላይናገሩ ይችላሉ። በዚህ ጊዜ የምትመሰክሩትን ወንጌል ግልጽ ሆኖ ላይረዱት ይችላል። በሌላ በኩል ደግሞ ኢየሡስ እንዳልተሰቀለ በኩራት ሊናገሩና ሊከራከሩም ይችላሉ። በየትኛውም መንገድ ቢሆን እነሱ ስለመስቀሉ የሚያምኑትን ማወቅ ይኖርብሃል።

መጽሐፍ ቅዱስን ማንበብ ኢየሱስ እንደተሰቀለ ለማመን ድምዳሜ ላይ ይደርሱ ይሆናል፤ ካልሆነ ግን ወደዚያ ድምዳሜ እንዲደርሱ ተጨማሪ ማስረጃዎችን ማቅረብ ይኖርብሃል።

## ኢየሱስ እንደተሰቀለ ማሳየት

ሙስሊሞች የኢየሱስን ስቅለት ሲክዱ ክርስቲያኖች የሚመልሷቸው በርካታ ምላሾች አሏቸው። እነዚህም ታሪካዊ፣ ትንቢታዊ፣ የቁርአንን ታሪካዊ ተዓማኒነት እና ዶሰቲዝም ናቸው። እነዚህንም በዝርዝር የምንመለከት ቢሆንም ከዚህም ይልቅ ለመጀመር ጥሩ ቦታ አለ ብዬ አስባለሁ።

በመጀመርያ ክርስቲያኖች ኢየሡስ እንደተሰቀለ ለማመልከተ ወደ ታሪካዊ መረጃ ያቀናሉ። ይህም እጅግ በጣም ጥሩ ሙግታዊ አካሄድ ነው። ምክንያቱም የኢየሱስን ስቅለትና ሞት እውነት የተከሰተ እንደሆነ የሚያስረዱ እጅግ የበዙ ታሪካዊ መረጃዎች አሉ። አዲስ ኪዳን በራሱ የአንድ ብቻ ሳይሆን የብዙ ሰዎችን ምስክርነት የያዘ ማስረጃ ሲሆን ከመጽሐፍ ቅዱስ ውጪ የሆኑ ታሪካዊ ምንጮችም ማስረጃዎቻችን ናቸው። በዚህም ርዕሰ ጉዳይ የተጻፉ በርካታ ግሩም መጻሕፍት መኖራቸው ነገሩን ተጨባጭና ሊገኝ የሚችል ያደርገዋል።[50] በመጨረሻም ሁሉም የታሪክ ምሁራን ኢየሱስ በመስቀል ላይ እንደተሰቀለና እንደሞተ ይስማማሉ። ይህ ደግሞ ኢየሡስ በመስቀል ላይ እንደተሰቀለና እንደሞተ ለማመን እጅግ አሳማኝና ጥሩ ምክንያት ነው። አንዳንድ ሙስሊሞች ይህንን አሳማኝ ሆኖ ያገኙታል። ቢሆንም ግን ይህ ለብዙ ሙስሊሞችና ለቀድምት ሙስሊሞች ኢየሱስ አልተሰቀለም፤ ይህ ደግሞ መጽሐፍ ቅዱስን ብቻ ሳይሆን ታሪክ የሚነግረንን ጭምር መካድ ነው። ስለዚህ ከዚህም ይልቅ ለመጀመር ጥሩ ቦታ አለ ብዬ አስባለሁ።

---

50 Paul Barnett, *Is the New Testament History?* F.F. Bruce, *The New Testament Documents - Are The Reliable?* John Dickson, *The Christ Files*. Book and DVD, www.thechristfiles.com.au

በሁለተኛ ደረጃ ክርስቲያኖች ትንቢታዊ ማስረጃዎችን ያቀርቡ ይሆናል። ለሙስሊሞች መዝሙር 22 ወይም ኢሳያስ 53ን በማንበብ እነዚያ ትንቢቶች እንዴት የኢየሱስን ሞት እንደሚተነብዩ ይነግሯቸዋል። ይህም ቢሆን እጅግ በጣም ትክክለኛ ሙግታዊ አቀራረብ ነው። የኢየሱስ ሞት በታሪክ ብቻ የተረጋገጠ ሳይሆን እግዚአብሔር ራሱ አስቀድሞ በነቢያቱ አማካኝነት የተናገረው እውነት ነው። ቢሆንም ሙስሊሞች ይህንንም ሊቃወሙና ትንቢቶቹ ስለ ኢየሱስ አይደሉም የተነገሩት ይሉ ይሆናል።

በሦስተኛ ደረጃ ክርስቲያኖች ወደ ቁርኣን የታሪክ ኢ-ተዓማኒነት ማስረጃ ያልፍ ይሆናል። ለምሳሌ ቁርኣን ሐማ ፈርዖን እግዚአብሔርን ማየት እንዲችል የባቢሎንን ግንብ እንደገነባለት ይነግረናል፤[51] ወይም ሙሴ በሲና ተራራ ላይ በነበረ ጊዜ እሥራኤላዊያን የጥጃ ጣዖት እንዲያመልኩ ያታለሏቸው ሳምራዊያን ናቸው የሚለውን፤[52] እና ማርያም የኢየሱስ እናት በዘጸአት ዘመን የነበሩት የኢምራን ልጅ፣ የአሮንና የሙሴ እህት እንደሆነች ይነግረናል።[53] ሙሐመድ ለመሰረታዊ የታሪክ እውነታዎች ምንም ታማኝነት ሊጣልበት አይችልም። ታድያ ስለ ስቅለቱ የሚነግረንን ለምን እንመነው? ይህም ቢሆን ከሙስሊም ወገኖቻችን ጋር ስንወያይ ልናነሳው የሚገባ ጥሩ ሙግት ነው። ቢሆንም እነርሱ ቁርኣን ታሪካዊ ስህተት እንዳለበት በተለያዩ ምክንያቶች ላያምኑና ላይቀበሉ ይችላሉ። ስለዚህ ከዚህም ይልቅ ለመጀመር ጥሩ ቦታ አለ ብዬ አስባለሁ።

በመጨረሻም ስነ-መለኮታዊ ትምህርቶችን የተከታተላችሁ ክርስቲያኖች የቁርአኑ ዘገባ የደሶቲዝም ትምህርት እንደሚመስል በመግለጥ የኢየሱስን መሰቀልና መሞት ትሞግቱ ይሆናል። ዶሰቲዝም በጥንቷ የቤተ-ክርስቲያን ዘመን የነበረ እምነት ሲሆን አምላክ ይህን ዓለም ሊነካው እንኳ እስከማይችል ድረስ ከፍ ያለና ድንቅ ነበር። ስለዚህ ኢየሡስ አምላክ እንደመሆኑ ሰው ሊሆን አይችልም ብለው ያምናሉ። በእነርሱ እምነት ኢየሱስ ሲራመድ፣ ሲበላ፣ ሲተኛና ሲሰቀል እውነተኛው ኢየሱስ ሳይሆን የሆነ አካሉ ነበር እያደረገ ይመስል ነበር እንጂ በውል እርሱ እያደረገ አልነበረም ይላሉ። ስለዚህ የቁርአኑ ዘገባ የዚህ የተሳሳተ ግንዛቤ የተቀዳ ስሁት ግንዛቤ ነው። በዚህ አቀራረብ ጥሩ ነጥብ ይኖረዋል ግን እኔ በሚከተሉት ሁለት ምክንያቶች ይህን የሙግት አቀራረብ አልመክርም። መጀመርያ ይህን ለሙስሊሞች ለማስረዳት እጅግ ጥንቃቄንና ብዙ መትጋት ይጠይቃል። ሲቀጥል ሙስሊሞች ኢየሱስ አምላክ መሆኑንና አካል እንዳልነበረው አያምኑም። ለእነርሱ ኢየሱስ ስጋዊ አካል ያለው ሰው ነው። ስለዚህ ከዚህም ይልቅ ለመጀመር ጥሩ ቦታ አለ ብዬ አስባለሁ።

እንግዲህ የምትፈለፍጉ ከሆነ ከላይ ያየናቸውን ሙግቶች ትጠቀሚቸው ይሆናል። ሁሉም ትክክለኛና እውነተኛ ተገቢም ስለሆኑ መጠቀም ትችላላችሁ። ከላይ ያሉትን ሙግቶች

---

51 ቁርኣን 28:38? 40:36-37

52 ቁርኣን 20:85-88, 95

53 ቁርኣን 3:35-51? 19:27, 34, 53? 66:12

እንዳትጠቀሟቸው የምመክራችሁ ከእነርሱ የተሸለና ሙስሊም ወገናችሁን ስለመስቀሉ በተሻለ አዲስ አስተሳሰብ እንዲያስብ የሚያደርግ የተሻለ ምክንያት እንዳለ ስለማምን ነው። ለማሳየትም እጅግ ቀላል ነው። ይህም ቁርኣን በእርግጥ የኢየሱስን መሰቀልና መሞት እንደማይክድ ለማሳየት ነው።

በዚህ ምዕራፍ መጀመርያ ላይ ምዕራፍ 4፡157-158 በማንበብ ስለጀመርን ክፍሉ የኢየሱስን ሞት ቁርጥ ባለ ሁኔታ እንደሚክድና ግልጽም ሊሆን እንደማይችል ታስቡ ይሆናል። ነገር ግን ይህንን ክፍል በዚህ መልኩ ከተረዳነው ቁርአኑን በአውዳዊ ፍቺው እያነበብነው እንዳልሆነ ከዚያ ይልቅ በራሳችን ታሪካዊ ጥያቄዎች እያነበብን እንደሆነ ላሳስብ እወዳለሁ። ይህንን ክፍል በቁርኣን “ንፅረተ ዓለም” አውድ ካነበብን በቁርኣን ውስጥ ስቅለቱ ትክክል መሆኑን እናገኛለን፤ የክፍሉ ሐቲት የነቢያትና የሰማዕታት ሞት እንዴት እንደሆነ የሚገልጽ ሆኖ እናገኘዋለን። ይህንን ለሙስሊሞች ማሳየት በጣም ቀላልና አዲስ ወንጌል የመመስከሪያ ዘዴ ይፈጥርልናል። በመጀመርያ ግን ሙስሊሞች ቁርኣንን እንዴት እንደሚፈቱት ማወቅ ይኖርብናል።

## የቁርኣን አተረጓጎም

ቁርኣን ሙሐመድ የቀራቸውና ከአምላክ ዘንድ ወርደውልኛል ያላቸው ንግግሮች ስብስብ ነው። እነዚህን ንግግሮች በተለያዩ ሁኔታዎችና ምክንያቶች ተናግሯቸዋል። ይህ ማለት ደግሞ ቁርኣን በሙሐመድ ሕይወት ዛቢያ የሚዞር ነው ማለት ነው። እነዚያ እርሱ የተናገረባቸው ሁኔታዎችና ምክንያቶች ምን እንደሆኑ በቁርኣን ውስጥ አልተካተቱም። በኋላ ግን የእስልምና የታሪክ መጻሕፍት ሆነው ሲራ እና ሐዲስ ተብለው መጡ።

ሙሐመድ ቁርኣንን በሃያ ሦስት(23) ዓመታት ውስጥ ተናገ፤ በነዚያ ጊዜያት በሕይወቱ ብዙ ነገሮች ተቀይረዋል። ስለዚህም ምክንያት እርሱ የተናገራቸውም ነገሮች ተቀይረዋል። ስለዚህ ቁርኣን በሙሐመድ ሕይወት ዛብያ የሚዞር ብቻ ሳይሆን በሙሐመድ ሕይወት ምክንያት የሚሻሻልና የሚለወጥ ነው።

በመሆኑም የሙሐመድን ሕይወት ማወቅ ቁርኣንን ለመረዳት እጅግ አስፈላጊና የመጀመርያ እርምጃ ነው። ይህም ማለት አንድ የቁርኣን ሱራ[54] ለማንበብ ስትዘጋጅ በመጀመርያ ሙሐመድ ይህንን መቼ እና በምን ሁኔታ እንደተናገረው ማወቅ ይኖርብሃል። አብዛኛው የቁርኣን ትርጉሞች እንደመግቢያ በእያንዳንዱ ሱራዎች መጀመርያ ላይ ለብቻቸው አስቀምጠዋቸዋል።

የእያንዳንዱን ሱራ ታሪካዊ ዳራውን ማወቅ በጣም አስፈላጊ ነገር ሆኖ ሳለ በተመሳሳይም ቁርኣንን ሌሎች መጻሕፍትን በምንተረጉምበት መንገድ መተርጎም በጣም ጠቃሚ ነው ። ይህ ማለት ደግሞ አንድ ቁጥር ሊተረጎም የሚገባው አጠገቡ ባሉ ቁጥሮች አውድና ስነ-

[54] ሱራ ማለት የቁርኣን ምዕራፍ አረብኛ አጠራር ነው።

አፈታት መሰረት፤ ቁጥሩ ለሙሉ ሱራው በሚኖረው ፋይዳና በሌላ ቦታ የሚገኙ ቁርአናዊ ሱራዎች በዚህ ርዕሰ ጉዳይ ላይ በሚያስተምሩት ትምህርት ይሆናል ማለት ነው። ይህ አተረጓጎም ቁርኣን ራሱን በራሱ እንዲተረጉም መፍቀድ ነው። በዓለም አቀፍ ደረጃ ሁሉም ኢስላማዊ ምሁራን አተረጓጎም መጀመር ያለበት በዚህ ሂደት እንደሆነ ይስማማሉ።

> ቁርኣን ለአንድ ዓላማ በአንድነት የተሰባሰበ እንደሆነ ይታመናል። ይህም ማለት ለመረዳት ከባድ የሆኑ የቁርኣን ክፍሎች ወይም ቁጥሮች ግልጽ በሆኑ ሌሎች የቁርኣን ክፍሎች ይብራራሉ። … አንድን ክፍል በሌላው ክፍል መፍታት ቁርኣንን በቁርኣን ማብራራት ሲባል በብዙ ፈቺዎችም (ሙፈሲሮች) ዘንድ የተሸለና የላቀ ስልጣናዊ ስነ-ፍታቴ እንደሆነ ይታመናል። ኢብን ታይሚያህ (ዲ.728/1328) እንዲህ ይላል፡-

የተሸለው ተፍሲር[55] ቁርኣንን በቁርኣን መፍታት ነው። በአንድ ቦታ የቁርኣን ክፍል የተነገቋጨ በሌላ ቦታ ይብራራል። በአንዱ ቦታ በስፋት የተገጠቀሰ በሌላ ቦታ ይብራራል።[56]

ቁርኣንን በቁርኣን አፈታት የተፍሲር ከፍተኛው ምንጭ ነው። በአንዳንድ የቁርኣን አንቀጾች ላይ የሚነሱ ጥያቄዎች በራሱ መጽሐፍ በሌላ ክፍል የሚብራሩ በመሆኑ በራሱ ተፍሲር ከያዘው ከአላህ ቃል በቀር ወደ ሌላ ማጣቀሻ[57] መሄድ አያስፈልገንም፤ የአንዱን የቁርኣን አያ[58] ማብራርያ ፍለጋ ወደ ሌላ የቁርኣን አያ መሄድና አተረጓጎሙን መፈለግ የሙሰፊሮች[59] የመጀመርያ ሃላፊነታቸው ነው። ይህም የማይበቃ ከሆነ ነው ወደ ሌላ የተፍሲር[60] ምንጮች የሚጠቁመው።

> አንተንም በነዚህ (ሕዝቦች) ላይ መስካሪ አድርገን የምናመጣህን ቀን (አስታውስ)፤ መጽሐፉንም በነገር ሁሉ አብራሪ መሪመረ እዝነትም ለሙስሊሞችም አብሳሪ ኾኖ ባንተ ላይ አወረድነው። (ቁርኣን 16፡89)

እንግዲህ ቁርኣን ራሱ በራሱ እንዲፈታ ከተፈቀደ ሌላ ስነ-አፈታት ይከተለዋል። የሚከተለውም ወደ ኢስላማዊ የታሪክ ድርሳናት በመሄድ ሙሐመድ ይህንን ክፍል እንዴት

---

55 ተፍሲር የቁርኣን ማብራርያ ነው።

56 Abdullah Saeed, *Interpreting the Qur'an - Towards a Contemporary Approach*, Oxon, U.K.: Routledge, 2006, p. 43.

57 ልክ እንደ ሐዲሰቱ

58 በአንድ ምዕራፍ ውስጥ የሚገኙ ቁጥሮች አረብኛ አጠራር

59 ተፍሲር የሚያዘጋጁ ኢስላማዊ ምሁራን በክርስትናው ማብራርያ አዘጋጅ እንደሚባለው

60 Ahmad von Denffer, *'Ulum al-Qur'an - An Introduction to the Sciences of the Qur'an*, U.K.: The Islamic Foundation, 1994, p. 124.

እንደፈታው በመጠየቅ[61] ይሆናል። ከዚህም ቀጥሎ የሙሐመድ ወዳጅ እንዴት እንደተረጎሙት ማየት እንችላለን። ከዚህ ሚከተሉት የቁርኣን ስነ-አፈታት መርሆች ናቸው።

1. ቁርኣንን በቁርኣን መፍታት
2. ሙሐመድ ቁርኣንን የፈታበት መንገድ
3. ከሙሐመድ ወዳጆች ቁርንን የፈቱበት መንገድ

ቶድ ላውሰን[62] እና ደብሊው ሪቻርድ ኦክስ ጁኒየር[63] እንደሚሉት ከሆነ በኢየሱስ ፈንታ ሌላ ሰው ተሰቀለ የሚለው የሙስሊሞች የተለምዶ አስተሳሰብ ቁርኣንን በቁርኣንና በሙሐመድ የአፈታት ዘዴ ሳይሆን በአንዳንድ የሙሐመድ ወዳጆችና ሌሎች ሰዎች መሰረት ያደረገ ሆኖ እናገኛዋለን። ይህ የሙስሊሞች ተለምዷዊ ስነ-አፈታት ምርጥና የመጀመርያ ከሚባለው የቁርኣን ስነ-አፈታቶች የመጡ አይደሉም። በሚገረርም ሁኔታ ከሁለተኛው ምርጥ የአፈታት ዘዴም የመጡ አይደሉም፤ ምክንያቱም ሙሐመድ ይህንን ክፍል ያብራራበት የታሪክ ድርሳን ስለማይገኝ።[64][65] ነገር ግን ከሦስተኛው የአፈታት ዘዴ ሲገኝ እናያለን።

የተላያዩ ሙስሊም ምሁራን 4፡157-158ን የሚተረጉሙበት የተለያየ ስነ-አፈታት አንመለከትም። የአብዛኞቹ ምሁራን ድምዳሜ ከቁርአኑ ጋር እንደማይስማማ ልብ ይሏል። እናም እያንዳንዱ ቃላት በሌሎች የቁርኣን ቦታዎች እንዴት እንደተብራራ በማሳየት ይፈቱታል።

## የሙስሊሞች የስቅለቱ ቁርአናዊ ስነ-አፈታት

እኛ የአላህን መልክተኛ የመሬምን ልጅ አልመሲሕ ዒሳን ገደልን በማለታቸው (ረገምናቸው)፤ አልገደሉትም፤ አልሰቀሉትምም ግን ለነሱ (የተገደለው ሰው በዒሳ) ተመሰለ

---

61 The hadith of *Sahih al-Bukhari* and a book devoted to Muhammad’s commentary on the Qur’an. https://sunnah.com/bukhari/65 and so too do other collections of Hadith.

62 Todd Lawson, *The Crucifixion and the Qur’an - A Study in the History of Muslim Thought,* London, England: Oneworld, 2013, p. 13.

63 W. Richard Oakes, Jr., *The Cross of Christ: Islamic Perspectives*, unpublished Ph.D. thesis, The University of Edinburgh, 2013, p. 392.

64 Lawson, p. 47

65 *ሙሐመድ እነዚህ ቅሶች ስለማብራራቱ የሚገልፅ ምንም ነገር ባይኖርም ነገር ግን ከእርሱ የተላለፈ አንድ አስገራሚ ሐዲስ አለ። እንዲህ ይላል፡- አብዱላህ እንዲህ አለ፡- “ነቢዩ ሙሐመድ ስለ አንድ ወገኖቹ ስለመቱትና ቆስሎ ስለደማ ነቢይ የተናገሩት ይታወሰኛል። ደሙ ፊቱ ላይ እየፈሰሰ ሳለ ‹‹አላህ ሆይ የሚያደርጉትን አያውቁምና ይቅር በላቸው›› ብሎ ጸለየ።* (*Sahih al-Bukhari*: 3290/3477 vol. 4, bk. 56, no. 683. Translated: Aisha Bewley, https://bewley.virtualave.net/bukhari26.html#prophets Accessed June 28, 2018.) ይህ ሉቃስ 23 ላይ ኢየሱስ በመስቀል ላይ ተሰቅሎ ሳለ ከጸለየው ጋር ይመሳሰላል።

እነዚያም በርሱ ነገር የተለያዩት፣ ከርሱ (መገደል) በመጠራጠር ውስጥ ናቸው፤ ጥርጣሬን ከመከተል በስተቀር በርሱ ነገር ምንም ዕውቀት የላቸውም፤ በእርግጥም አልገደሉትም። ይልቁኑስ፣ አላህ ወደርሱ አነሳው፤ አላህም አሸናፊ ጥበበኛ ነው።

ሱረቱል አል-ኒሳእ (4) ፡157-158

እነዚህ ጥቅሶች ኢየሱስ አልተሰቀለምም አልተገደለምም የሚሉ ቢሆን ኖሮ በማያሻማ መልኩ ለመተርጎምና በቀጥታ ለመረዳት አያዳግቱም ነበር። ነገር ግን እነርሱ እነደዚያ አይሉም። ክፍሎቹ የሚሉት፡- አይሁዳዊያን ኢየሱስን ሰቅለው አልገደሉትም፣ እርሱም ተሰቅሎ የሞተ መሰላቸው፣ ግን አምላክ ወደራሱ አነሳው። እንደ እስልምና ይህን አነጋገር ለመረዳት በቀጥታ መረዳት አይኖርብንም። ትልቁ ማወቅ ያለብን ነገር "ለእነርሱ ተመሰለላቸው" የሚለው አባባል ምን ማለቱ እንደሆነ ነው። የሚከተሉቱ ሙስሊሞች ሊሆን ይችላል ብለው ያሰቀመጧቸው አፈታቶች ናቸው። ምንጮቹም ከታች ከተቀመጡ ማጣቀሻዎችና እኔ ከተካፈልኩባቸው ክርክሮች የተወሰዱ ናቸው።

- የሆነ ሰው በኢየሱስ ፈንታ ተሰቅሎ ነበር።
- ማንም አልተሰቀለም ነበር።
- ኢየሱስ ነበር የተሰቀለው።
- ኢየሱስ ስቅለትን ተቋቁሞ በሕይወት ተርፏል
- አይሁዳዊያን ሳይሆኑ ሮማዊያን ነበሩ ኢየሱስን የሰቀሉት።
- የኢየሱስ ነፍሱ ከስጋው ተለይታ ነበር።
- ምን እንደተከሰተ አናውቅም።

ከዚህ ቀጥሎ እነዚህን አንድ በአንድ በዝርዝር እናያለን።

## 1. የሆነ ሰው በኢየሱስ ፈንታ ተሰቅሎ ነበር

በምትክዮሽ ትወራ መሰረት ስቅለት ተካሂዷል፤ ኢየሱስ የተሰቀለም መስሏል፤ እንደ እውነቱ ከሆነ ግን ሌላ ሰው ነበር የተሰቀለው። ይህ ነው በብዙ ምስሊሞች አመለካከት በተለምዶ የሚታሰበው። ይህ አስተሳሰብ ከቁርአን የመጣ ሳይሆን ክፍሉን ለምፍታት ተብለው ከሚጠቀሱ ከብዙ ታሪኮች መነሻነት የሚመጣ ነው። ለምሳሌ፡-

> ኢብን አቢ ሐቲም እንደመዘገበው ኢብን አባስ እንዲህ ብሏል። አላህ ኢሳን[66] ወደ ሰማይ ከመውሰዱ ትቂጥ ቀደም ብሎ ወደ አሥራ ሁለት ሆነው አንድ ቤት ውስጥ

---

[66] ኢሳ ቁርአን ለኢየሱስ የሰጠው ስም ነው።

እያሉ ወደ ወዳጆቹ ሄዶ ነበር። ወደ ቤቱ ስደርስም ከጸጉሩ ውሃ እየተንጠባጠበ እንዲህ አለ “እናንተ መካከል በእኔ የማያምኑ አሉ አሥራ ሁለት ጊዜ በእኔ ካመነ በኋላ።” እንዲህም ብሎ ጠየቃቸው “ከእናንተ የእኔን መልክ እንዲመስል ፈቃደኛ የሚሆን እና በእኔ ፈንታ የሚገደል ማን ነው? እርሱ ከእኔ ጋር በገነት ይሆናል።” ከእነርሱ መካከልም አንዱ ወጣት ፈቃደኛ ሆኖ ተነሳ ኢሳም እንዲቀመጥ ጠየቀው። ኢሳ እንደገና ፈቃደኛነታቸው ጠየቃቸው፤ ያም ወጣት አሁንም ፈቃደኝነቱን ማሳየቱን ቀጠለ፤ ኢሳም እንዲቀመጥ ጠየቀው። ከዚያም ያ ወጣት እንደገና ፈቃደኛ ሆነ ኢሳም አንተ እርሱ ነህ አለው። ኢሳም ወደ ሰማይ በተወሰደ ጊዜ የኢሳ መልክ ቤት ውስጥ ካሉ ሰዎች ሁል በወጣቱ ልጅ ላይ ሆነ። አይሁድም ኢሳን ፈልገው ሲመጡ ያንን ወጣት ሰው አገኙት ወስደውም ሰቀሉት።[67]

ይህንን የመሰሉ ብዙ ታሪኮችን እናገኛለን ግን ሐቲታቸው በብዙ ይለያያል።[68] አንዳንዶቹ የተተካው ይሁዳ[69] ወይም ፈቃደኛ የሆነ ደቀ-መዝሙር ወይም ተቀላቅለው ስለነበር ሮማዊያን ተሳስተው በርባን[70] ወይም የቀሬናው ስምዖን[71] ነው ይላሉ።

## 2. ማንም አልተሰቀለም

በዚህኛው አፈታት ደግሞ የተሰቀለ ማንም ሰው አልነበረም ነገር ግን ህዝቡ በአጠቃላይ የሆነ ምዕናባዊ ወይም በህልም[72] ዓለም የተሰቀለ መሰላቸው። የዚህ አቋም ጥንካሬው በውጪ ባሉ የታሪክ ድርሳናት ላይ አለመደገፉ ሲሆን ግን አምላክ ራዕይን[73] ስለሚሰጥ መልሱን ከቁርኣን ይፈልጋል። ይሁን እንጂ አይሁዳዊያን አይተነዋል ብለው ሳይሆን አድርገነዋል ብለው የሚኮሩበትን ነገር ራዕይ ነበረ ማለት ከባድ ነው። እነርሱም ቁርኣን የደረጉ መስሏቸዋል የሚለውን ነገር አድርገናል ይላሉ። ስለዚህ “ማንም አልተሰቀለም ነበር” የሚለው ትወራ በርዕሰ ጉዳዩ ላይ አጥጋቢ መልስ የለውም ግን ቢያንስ ከቁርኣን መልስ ለማግኘት ይጥራል።

## 3. ኢየሱስ ነበር የተሰቀለው

እርሱ በአይሁዳዊያን ተከዳ ተሰቀለም፤ አላህ ወደራሱ ወደ ሰማይም ወሰደው።[74]

---

67 Ismail Ibn Kathir, *Tafsir ibn Kathir* (Abridged), ed. Abdul Malik Mujahid, et al., Riyadh, KSA: Darussalem, 2000, vol. 3, p. 28.
68 Al-Tabari records eleven such stories. Lawson, p. 71
69 *The Gospel of Barnabas*, chap. 216.
70 *The Gospel According to Islam*, 26:21.
71 Commonly used in debates.
72 Lawson, p. 23
73 ቁርኣን 12፡43
74 Prof. Masud ul Hasan, *History of Islam*, Delhi, India: Adam Publishers & Distributors, 2002, vol. 1, p. 29.

በመጨረሻም ስለናዝሬቱ ኢየሱስ በሙሉ ልብ መደገፍ የምንችልባቸው ሁለት እጅግ ከባድ ታሪካዊ እውነታዎች አሉ። የመጀመርያው ኢየሱስ በመጀመርያው ክፍለ ዘመን በፍልስጥኤም ውስጥ ትልቅ አይሁዳዊ እንቅስቃሴን ያካሄደ አይሁዳዊ መሆኑ ነው፤ ሁለተኛው ደግሞ ኢየሱስ እንደዚያ በማድረጉ እርሱን መስቀላቸው ነው።[75]

ይህ አፈታት ከቁርኣን ጋር የማስማማት ሥራ ሳይሰራ ታሪካዊ የሆነውን እውነት በቀጥታ ይቀበላል። የዚህ ሙግት ደካማ ጎኑ ከቁርአኑ ጋር ጭራሽ አይገናኝም።

## 4. ኢየሱስ ስቅለትን ተቋቁሞ በሕይወት ተርፏል

አህመዲያ[76] የሚባሉ የእስልምና ክፍሎች ራስን የመሳት ትወራን ይቀበላሉ። ይህም ኢየሱስ ተሰቅሎ ነበር ነገር ግን መከራውን ሁሉ ተቋቁሞ በምድር ላይ በሕይወት ነበር የሚለው ነው። ስለዚህ ኢየሱስ ተሰቅሏል ነገር ግን እስኪሞት አልነበረም የተሰቀለው፤ በዚህም ምክንያት ስቅለቱ በተሳካ ሁኔታ የተጠናቀቀ መሰላቸው። የዚህ አፈታት ትልቁ ችግር ቁጥሩ ኢየሱስ ተሰቅሎ መከራውን ተቋቁሞ በምድር በሕይወት ሊቆይ ችሏል ሳይሆን የሚለው ወደ አምላክ ተወስዷል ነው የሚለው። ይህም ቢሆን ቁርኣንን በቁርኣን መፍታት አይደለም።

## 5. አይሁዳዊያኑ ሳሆኑ ሮማዊያኑ ነበሩ ኢየሱስን የሰቀሉት

ይኼኛው ማብራርያ ጥቅሱ አይሁዳዊያን ኢየሱስን መስቀላቸውን መካዱ ላይ ትኩረት ያደርጋል። እርሱ ግን በሌላ ሰው አልነበረም የተገደለው።

> ቁርኣን ራሱ አይሁዳዊያን ኢየሱስን እንዳልሰቀሉት ያረጋግጣል፤ ይህ ደግሞ ኢየሱስ አልተሰቀለም ከማለት እንደሚለይ ግልጽ ነው።[77]

በዚህኛው አካሄድ ሮማዊያን ወታደሮች እንጂ አይሁዳዊያን አልነበሩም ኢየሱስን የሰቀሉት ይላሉ። እናም አይሁዳዊያኑ ኢየሱስን ለመስቀል ነበር በቦታው የነበሩት። በዚህኛው እይታ ኢየሱስ በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ በተጻፈበት ሁኔታ ተሰቅሏል።[78] የዚህ አቋም ጠንካራ ጎኑ ክፍሉን በጥንቃቄ ማንበቡና የማይለውን አለማስባሉ ነው። ቢሆንም ግን ክፍሉ በአይሁድ ገዢዎች ፈንታ ሌላ ሰው ሰቅሎታል አይልም። ሮማዊያን ቢያደግሩት እንኳ በኢየሱስ መገደል መመካታቸውን አያስቀርላቸውም ምክንያቱም ነገሩን ያቀነባበሩት አይሁዳዊያን ስለሆኑ። ያም ሆነ ይህ እቅዳቸው ነበርና ኢየሱስን ያስደግሉታል። እነሱ አላማቸው እስከተሳካ ድረስ በእውነቱ ማንስ ቢያደርገው ይህን ያህል አንገብጋቢ ጉዳይ ነው; ይህን

---

[75] Reza Aslan, *Zealot - The Life and Times of Jesus of Nazareth*, New York, U.S.A.: Random House, 2013 p. xxviii

[76] Mustafa Akyol, *The Islamic Jesus*, New York: St. Martin's Press, 2017, p. 153.

[77] Lawson, p. 12

[78] Akyol, p. 154

ክፍል በጥንቃቄ መፍታት ካሰብን ክፍሉ በበቂ ሁኔታ ጥቅሱን በዝርዝር ማብራራት ይችላል።

## 6. የመለያየት ትወራ

የመለያየት ትወራ ኢየሱስ ሳይሞት ነፍሱ ከሥጋው ተለይታ ሥጋው ብቻ ነበር በመስቀል ላይ የተሰቀለው የሚል ነው።[79][80] ስለዚህም ኢየሱስ ሰቅሎ የሞተ መስሏቸው እርሱ ሳይሞት የእርሱ ነፍስ ግን ሄዳ ነበር። ይህ ትወራ በተለያዩ ቁርአናዊ ክፍሎች ላይ መሰረት ያደረገ ነው። በመጀመርያ ከፈጣሪ ፍቃድ ውጪ ማንም ሰው አይሞትም፤ በመሆኑም ሞትም ሆነ ሕይወት በፈጣሪ እጅ ነው፤ በዚህም ምክንያት ኢየሱስን ገደልኩት ብሎ ማንም ሰው ሊኮራ አይችልም።

> ለማንኛይቱም ነፍስ በአላህ ፍርድ ቢኾን እንጅ ልትሞት አይገባትም፤ (ጊዜውም) ተወስኖ ተጽፏል፤ (ቁርአን 3፡145)
>
> እኛ እኛው ሕያው እናደርጋለን፤ እንገድላለንም፤ መመለሻም ወደኛ ብቻ ነው። (ቁርአን 50፡43)

በመቀጠል አምላክ ሳይገድልህ ነፍስህን ሊወስድ ይችላል።

> አላህ ነፍሶችን በሞታቸው ጊዜ ይወስዳል፤ ያችንም ያልሞተችውን በእንቅልፏ ጊዜ (ይወስዳታል)፤ ታድያ ያችን ሞትን የፈረደባትን ይይዛታል፤ ሌላይቱንም እስከ ተወሰነ ጊዜ ድረስ ይለቃታል፤ (ቁርአን 39፡42)

ስለዚህ ኢየሱስ 4፡157-158 እንደሚለው አልሞተም ነበር፤ አምላክ ነፍሱን ወሰዶት ነበርና።

የዚህ አቋም ጠንካራ ጎኑ ከቁርአን ሳይወጣ የሞትን ምንነት ከሌላ የቁርአን ክፍል መተርጎም መቻሉ ነው። ክርስቲያኖች የሞት ምንነት ሙስሊሞቹ በሚረዱበት መንገድ እንረዳዋለን ብለው ማሰብ አይኖርባቸውም። በዚ አቋም ላይ ያለኝ ብቸኛ ትችት ቁርአን ሰው ሲሞት ምን እንደሚሆን ሌሎች ተጨማሪ ነገሮችንም ይነግረናብ ብየ አስባለሁ።

## 7. ምን እንደተከሰተ አናውቅም

---

[79] *Jesus' death according to the Quran*, (Accessed March 7, 2018) www.quran-islam.org/main_topics/quran/new_information/jesusand039s_death_(P1261).html

[80] Lawson, p. 23

በዚህ በመጨረሻው አፈታት ክፍሉ ከሚነግረን ክስተት ውጪ በሰዓቱ ምን እንደተከሰተ አናውቅም የሚል አቋም ይሆናል። ማለት የምንችለውም አይሁዳዊ መሪዎች ኢየሱስን ሰቅለውታል ወይም ደግለውታል ነው። በቃ! ይህ አመለካከት በ20ኛው ክፍለ ዘመን የቁርኣን ማብራሪያ በሆኑት በሳይድ ቁጥቢ[81] እና ማኡዱዲ የሚጠቀስ ነው።

> ቁርኣን ግልጽ በሆነ መንገድ አይሁድ ኢየሱስን የመግደል ኣላማቸው እንዳልተሳካላቸው እና አላህም ወደራሱ እንዳነሳው ይነግረናል። ነገር ግን ስለነበረው ሁኔታና ዝርዝር መረጃ ዝም ብሏል። በግልጽም ከምድር በስጋና በነፍስ ወደ ራሱ ወደ ሰማይ እንደወሰደውም አይነግረንም። እንደሌሎቹ ሟቾችም ሞቶ ነፍሱ ብቻ ወደ ሰማይ ሄዷልም አይለንም። ስለዚህ በቁርኣን መሰረት ይህንን ጉዳይ ቁርጥ ባለ መልኩ መቃወምም መቀበልም አይቻልም።[82]

የዚህም አቋም ጠንካራ ጎኑ መልስ ፍለጋ ከቁርኣን አለመውጣቱ ነው። ደካማ ጎኑ ደግሞ መልሱን ወደ ቁርኣንም ጠልቆ አለመፈለጉ ነው። በቁርአኑ የስቅለቱ ሁኔታ የተነገረው ሃሳብ በሌላ የቁርኣን ቦታ ተነግሯል። ይህንንም ከግንዛቤ ውስጥ ባለማስገባት ቁርኣን ራሱን በራሱ እንዲፈታ አለመፍቀድ ነው።

በዚህ ክፍል ስቅለቱን አስመልክቶ ቁርኣን የሚያትተው እስላማዊ ምሁራንን ወደ ተለያዩ አተረጓጎሞች እንዲገቡ አንዳደረጋቸው አይተናል። የብዙዎቻቸው ችግር ቁርአኑን በቁርአኑ ከመፍታት ይልቅ በውጪ ባሉ ታሪኮች ተመስርተው መተርጎማቸው ነው። በኢየሱስ ምትክ ሌላ ሰው ሞቷል የሚለው የተለመደ አመለካከት ነው። ቁርኣንን በቁርኣን የሚተረጉሙ ሰዎች ይህን በግልጽ የሚያደርጉ አይመስልም ግን ቢያንስ ከፍተኛውን ተዓማኒ የአፈታት ዘዴ ሊጠቀሙ ይጥራሉ።

ለዚህም ሁለት ተግባራዊ ትግበራዎች አሉት፡- መጀመርያ ሙስሊሞች ኢየሱስ በመስቀል ላይ በጭራሽ አልሞተም የሚሉ ከሆነ ከሰባቱ የትኛውን አፈታት እንደሚያምኑ ጠይቋቸው። ኢየሱስ እንደተሰቀለ የሚያምኑ ሌሎች ሙስሊሞች እንዳሉም አሳስቧቸው። በሁለተኛ ደረጃ የወዳጃችሁ አፈታት ቁርኣንን በቁርኣን ከመፍታት ይልቅ በውጪ ታሪኮች ላይ መሰረት እንደሚያደርግ ጠቁሙት። ከዚያም ቁርኣንን ይህንን ክፍል እንዴት እንደሚፈታው እንዲያውቅ ጋብዙት። ይህም ቀጥሎ የምናየው ነው።

---

81 Sayyid Qutb, *In the Shade of the Qur'an*, *Surah 4*, p. 318 https://tafsirzilal.files.wordpress.com/2012/06/an-nisa-eng.pdf

82 S. Abdul A`La Maududi, *The Meaning of the Qur'an*, Lahore: Islamic Publications, 2007, fn 195 for Q. 4:157, vol. 1, p. 399.

## 4፡157-158ን በቁርአን መፍታት

> እኛ የአላህን መልክተኛ የመሪምን ልጅ አልመሲሕ ዒሳን ገደልን በማለታቸው (ረገምናቸው)፤ አልገደሉትም፤ አልሰቀሉትምም ግን ለነሱ (የተገደለው ሰው በዒሳ) ተመሰለ እነዚያም በርሱ ነገር የተለያዩት፣ ከርሱ (መገደል) በመጠራጠር ውስጥ ናቸው፤ ጥርጣሬን ከመከተል በስተቀር በርሱ ነገር ምንም ዕውቀት የላቸውም፤ በእርግጥም አልገደሉትም። ይልቁኑስ፣ አላህ ወደርሱ አነሳው፤ አላህም አሸናፊ ጥበበኛ ነው። (ሱረቱል አል-ኒሳእ (4) ፡157-158)

የመጀመርያው አፈታት ቁርአንን በቁርአን መፍታት እንደሆነ አይተናል። ስለዚህ ቁርአን የሚሞትንና ወደ ፈጣሪ የሚወሰድን ሰው እንዴት ነው የሚገልጸው; መቅድምያ ሲሪል ግላሴ የጻፈውን ለመጥቀስ እወዳለሁ፡-

> በእስልምና በቁርአን ውስጥ በዓለም ከሚታዩ ገሃድ ከሆኑት ነገሮች ይልቅ ይበልጥ አስፈላጊ ተብሎ ሚወሰደው ከፍተኛ አስፈላጊ ነገር ሞት ወይም ሕይወት የሚለው እውነታ ነው። ሰማዕታት ያለበትን ሁኔታ ለመረዳት ቁልፉ ይህ ክፍል ነው። “አልገደሉትም”፣ “በአላህ መንገድ (ለሃይማኖቱ) የሚገደሉትን ሰዎችም «ሙታን ናቸው» አትበሉ። በእውነቱ ሕያዋን ናቸው፤ ግን አታውቁም” (2፡154) ወይም “እነዚያን በአላህ መንገድ የተገደሉትን ሙታን አድርገህ አትገምታቸዉ። በእርግጥ እነርሱ እጌታቸዉ ዘንድ ሕያዋን ናቸዉ፤ ይመገባሉ።” (3፡169)[83]

ግላሴ ወደ ሁለት ጥቅሶች ይመራናል። ወደ 2፡154 እና 3፡169። እነዚህ ክፍሎች ስለ ጂሃዲስቶች የሚናገሩ ናቸው።እነርሱም በአላህ መንገድ ሰማዕት የሆኑ ሰዎች ናቸው። ስለእነሱ ምን እንደተባለ ልብ በሉ፡-

> በአላህ መንገድ (ለሃይማኖቱ) የሚገደሉ ሰዎችንም ሙታን ናቸው አትበሉ፤ በውኑ ሕያዋን ናቸው፤ ግን አታውቁም። (ቁርአን 2፡154)

ስለዚህ ሙስሊሞች ሰማዕታት ሞተዋል ብለው እንዲያወሩ አይፈቀድላቸውም። ምንም እንኳ በሕይወት ባይኖሩም ንግ ሕያው እንደሆኑ ሊታሰብ ይገባል። ሙስሊሞች ከራሳቸው እይታ አንጻር ሳይሆን መናገር ያለባቸው ለእነርሱ የማይታየውን አላህ በገለጠው መሰረት መናገር ይኖርባቸዋል። ይህ ደግሞ በቁርአን ውስጥ እጅግ ጠቃሚ ገጽታ ነው። ቁርአን አንተ ማየት የምትችለውንም ሆነ ማየት የማትችለውን ነገር የሚገልጥ መለኮታዊ መገለጥ እንደሆነ ያስተምራል።

> ሩቁንና ቅርቡን ዐዋቂ ታላቅ የላቀ ነው። (ቁርአን 13፡9)

---

[83] Cyril Glasse, “Jesus”, *The New Encyclopedia of Islam*, Maryland, U.S.A: Rowman & Littlefield, 4th ed., 2013, p. 268.

> እርሱ በሩቁ ወሬ ላይ ሰሳች (ንፉግ) አይደለም። (ቁርአን 81፡24)

ቁርአንና ሙሐመድ አንተ ማየት የማትችለውን ይነግሩሃል። በዚህም ጉዳይ ሰማዕታት የሞቱ ቢመስልም ሙስሊሞች እንደዚያ እንዲሉ አይፈቀድም ምክያም በማይታየው እውነታ መሰረት ሰማዕታቱ ከአምላክ ጋር ስለሚኖሩ። ይህንኑ ሃሳብ መልሰን በሚቀጥለው ክፍል እናገኛለን።

> እነዚያን በአላህ መንገድ የተገደሉትን ሙታን አድርገህ አትገምታቸዉ። በእርግጥ እነርሱ እጌታቸዉ ዘንድ ሕያዋን ናቸዉ፤ ይመገባሉ። (ቁርአን 3፡169)

በድጋሚ ሙስሊሞች ስለ ሰማዕታት ከሚያዩት እይታ አንጻር እንዲናገሩ አልተፈቀደላቸውም። ሊናገሩም የሚገባቸው አላህ በገለጠው መሰረት ነው: ሳይድ ቁጥቢ እንዲ ያብራራዋል፡-

> በሁሉም አግባብ ሰማዕታቱ ሕይወት የሌላቸው ሊመስሉ ይችላሉ ነገር ግን ሕይወትና ሞት በውጪ በሚታየው አካላዊ ይዘት ብቻ አይፈረድም። እንደ እስልምና ባሕል በፈጣሪ መንገድ የሞቱ ሰዎች ለቀብር ዝግጅት ሰውነታቸውን አይታጠቡም፤ ከሞቱበት ልብሳቸው ጋር ይቀበራሉ። ይህም ንጹሃንና ጻድቃን እንደሆኑ ስለሚታሰብና በእውነታው በእርግጥ ስላልሞቱ ነው። ግን እነዚያ በሕይወት ያሉ ሰማዕታት እነማን ናቸው; እነዚያ በፈጣሪ መንገድ የሞቱቱ ብቻ![84]

ስለኢየሱስ ስቅለት በተነረው የቁርአን ክፍል ያሉትን አገላለጾች በሙሉ እነዚህ ሁለት ክፍሎች (2፡154፤ 3፡169) ውስጥ እናገኛለን። ሰማዕታት እንደሞቱ ሊወራ እንደማይገባው ሁሉ ኢየሱስም እንደሞተ ሊወራ አይገባም። ሰማእታት የሞቱ እንደሚመስሉ ሁሉ ኢየሱስም የሞተ መስሏል። ሰማዕታት ወደ ፈጣሪ እንደሚወሰዱ ሁሉ ኢየሱስም ወደ ፈጣሪ ተወስዷል። ቁርአን ስለ ሰማዕታት የሚያስተምረውን በሚገባ ከተረዳን የኢየሱስመ መሰቀል እንደ ክስተት የሚጠበቅ ነው። ቁርአን የሰማዕታትን መሞት በሚቃወምበት ልክ የኢየሱስንም ሞት ይቃወማል። የኢየሱስ መሞት በቁርአን ውስጥ የሃጥአት ስርየት ሳይሆን የስነ መለኮት ትንታኔ አለው። ይህም የሰማዕታት አሟሟት ተምሳሌት ነው። ለዚህም ነው በዚህ ሁኔታ ተብራርቶ የተቀመጠው።

በተጨማሪም ቁርአን ቁርአን ማንም ማንንም በመግደሉ ሊኮራ እንደማይገባ ይናገራል። የዚህም ምክንያት በማይታየው እውነታ መሰረት ሰውን መግደልና ነፍስን የሚወስደው ፈጣሪ ብቻ በመሆኑ ነው።

> ለማንኛይቱም ነፍስ በአላህ ፍርድ ቢኾን እንጂ ልትሞት አይገባትም። (ጊዜውም) ተወስኖ ተጽፏል። (ቁርአን 3፡145)

---

[84] Sayyid Qutb, *In the Shade of the Qur'an*, (Sura 2:154), pp. 164-167 https://tafsirzilal.files.wordpress.com/2012/06/al-baqarah-eng.pdf

እኛ እኛው ሕያው እናደርጋለን። እንገድላለንም። መመለሻም ወደእኛ ብቻ ነው። (ቁርኣን 50፡43)

አላህ ነፍሶችን በሞታቸው ጊዜ ይወስዳቸዋል። ያችንም ያልሞተችውን በእንቅልፏ ጊዜ (ይወስዳታል)። ታድያ ያችን ሞትን የፈረደባትን ይይዛታል። ሌላይቱንም እስከ ተወሰነ ጊዜ ድረስ ይለቅቃታል። በዚህ ውስጥ ለሚያስተነትኑ ሕዝቦች ምልክቶች አሉበት። (ቁርኣን 39፡42)

በመሆኑም ሰውን የገደልን ይመስለናል እንደ እውነታው ከሆነ ግን እርሱን የገደለው ፈጣሪ ነው።

አንገደላችኋቸውም ግን አላህ ገደላቸው። (ጭብጥን ዐፈር) በወረወርክ ጊዜ አንተ አልወረወርክም። ግን አላህ ወረወረ። (ቁርኣን 8፡17)

ስለዚህ የአይሁድ መሪዎች ኢየሱስን ገድለነዋል እያሉ መኩራራት አይችሉም፤ ምክንያቱም እንደ እውነታው ከሆነ እነሱ አይደሉም የገደሉት ፈጣሪ ነው ወደራሱ የወሰደው እንጂ።

በዚህ ክፍል ቁርኣንን በቁርኣን በመተርጎም በ4፡157-158 ውስጥ የኢየሱስ ሰማዕታዊ ሞት ስሜት የሚሰጥ እንደሆነ አይተናል። ከቁርኣን ወጥተው ከተለያ ታሪኮች በመቀነጫጨብ ሊተረጉሙ ከሚሞክሩት አተረጓጎሞች ይልቅ ይበልጥ ስሜት የሚሰጥ አፈታት ነው።

ሙስሊሞች እስልምና ኢየሱስ አልሞተም ይላል ካሏችሁ በ8፡17፣ 2፡154፣ 3፡169 ላይ ያሉ ሃሳቦች አሳዩአቸውና የኢየሱስ ሰማዕታዊ ሞት በ4፡157-158 ላይ ያለውን የበለጠ በተሻለ መንገድ እንደሚያብራራው በማሳየት ተግባራዊ ማድረግ ትችላላችሁ።

ከዚህም በኋላ መጽሐፍ ቅዱስ እና የታሪክ ድራሳናትን በመጥቀስ ስለኢየሱስ ሞት ማስረጃዎችን ማሳየት ትችላላችሁ። ይህን ከማየታችን በፊት በሌሎች የቁርኣን ክፍሎች የኢየሱስ ሰማዕታዊ ሞት ስሜት እንደሚሰጥ ለማሳየት እወዳለሁ።

## ኢየሱስ በሌሎች የቁርኣን ክፍሎች

ባለፈው ክፍል በቁርኣን ያለው የስቅለቱ መግለጫ በኢየሱስ ሰማዕታዊ ሞት መተርጎም የተሻለ መንገድ መሆኑን አይተናል። በዚህ ክፍል ደግሞ ይህ አተረጓጎም ከሌሎቹ የቁርኣን ክፍሎች ጋር እንደሚጣጣም እንመለከታል።

## ወንጌልና ሰማዕትነት

ቁርኣን ኢየሱስ ወንጌልን እንደሰበከ ይነግረናል።[85] የወንጌሉንም ዝርዝር በሚቀጥለው ቁጥር አስቀምጧል።

85 ቁርኣን 5፡46

አላህም ከምእመናን ነፍሶቻቸውንና ገንዘቦቻቸውን ገነት ለእነሱ ብቻ ያላቸው በመኾን ገዛቸው። በአላህ መንገድ ላይ ይጋደላሉ። ይገድላሉ፤ ይገደላሉም። በተውራት በኢንጂልና በቁርኣን (የተነገረውን) ተስፋ በእርሱ ላይ አረጋገጠ። (ቁርኣን 9፡111)

ይህ ክፍል አላህ ለጂሃዲስቶችና ለሰማዕታት ስለገባውን ቃል ይነግረናል። በቶራህ፣ በወንጌልና በቁርኣን በአላህ መንገድ የሚደግሉ ወይም የሚሞቱ ነገትን እንደሚገቡ አላህ ቃል ገብቶላቸዋል ይለናል። እንደ ቁርኣን አስተምህሮ ኢየሱስ የጂሃድና የሰማዕትነት ወንጌልን ሰብኳል። እንግዲህ ኢየሱስ የጂሃድና የሰማዕትነትን ወንጌል ከሰበከ የእርሱ ሰማዕትነት ሊታመን የሚችል ነው ምክንያቱም ነቢያት እንዳስተማሩት መልእክት ነው የሚኖሩት።

## ኢየሱስና መጥምቁ ዮሐንስ

መጥምቁ የሐንስ በቁርኣን ውስጥ ተጠቅሶ እናገኘዋለን። ኢስላማዊ ምሁራን ሰማዕት እንደሆነም ይስማማሉ።[86] ነገሩን ይበልጥ ሳቢ የሚያደርገው ቁርኣን ስለ ዮሐንስ ሕይወት የሚሰጠው መደምደሚያ ለኢየሱስ ከሚሰጠው መደምደሚያ ጋር ተመሳሳይ መሆኑ ነው። የሚገርመው ደግሞ እንዲህ አይነቱ መደምደሚያ ለዮሐንስና ለኢየሱስ ብቻ የተሰጠ መሆኑ ነው።

በተወለደበት ቀንና በሚሞትበት ቀን፣ ሕያው ሆኖ በሚነሳበትም ቀን ሰላም በእርሱ ላይ ይሁን። (ቁርኣን 19፡15)

ሰላም በእኔ ላይ ነው። በተወለድሁ ቀን፣ በምሞትበትም ቀን፣ ሕያው ኾኜ በምቀሰቀስበትም ቀን። (ቁርኣን 19፡33-34)

እንግዲህ ቁርኣን ስለ ዮሐንስና ስለ ኢየሱስ የሕይወት መደምደሚያ የሚሰጠው መግለጫ ከተመሳሰለ፤ ዮሐንስ ደግሞ የሰማዕትነት ሞት ከሞተ ኢየሱስም የሰማዕትነት ሞት ሞቷል ብሎ ማመን አሳማኝ አተረጓጎ ነው።

## የኢየሱስ ወደ አምላክ መወሰድ

በቁርኣን የስቅለት ሂደት መሰረት ኢየሱስ ወደ አምላክ ተወስዷል። ነገር ግን ይህ የኢየሱስ ወደ ሰማይ መወሰድ ብቸኛው ክፍል አይደለም። በሚቀጥለውም ክፍል ጭምር ተጠቅሶ እናገኘዋለን።

---

86 Ismail Ibn Kathir, *Stories of the Prophets*, (trans. Rashad Ahmad Azami), KSA: Riyadh, 2003, p. 537.

(አይሁዶችም) አደሙ፤ አላህም አድማቸዉን መለሰባቸዉ፤ አላህም ከአድመኞች ሁሉ በላጭ ነዉ።አላህም ባለ ጊዜ (አስታውስ)፤ ዒሳ ሆይ! እኔ ወሳጂህ፣ ወደ እኔም አንሺህ ነኝ፤ ከነዚያም ከካዱት ሰዎች አጥሪህ ነኝ፤*** እነዚያንም የተከተሉህን እስከ ትንሣኤ ቀን ድረስ፥ ከነዚያ ከካዱት በላይ አድራጊ ነኝ፤ ከዚያም መመለሻችሁ ወደኔ ነዉ፤ በርሱ ትለያዩበትም በነበራችሁት ነገር በመካከላችሁ እፈርዳለሁ። (ቁርኣን 3:54-55,)[87]

ይህ ክፍል አይሁድ መሪዎች ኢየሱስን ለመግደል እንዴት እንዳቀዱና አምላክም እንዴት ወደራሱ ለመውሰድ እንዳቀደው ይነግረናል። ይህም ሌላው የስቅለቱ ሂደት የተብራራበት ክፍል ነው። የኢየሱስ ሰማዕትነት ከዚህ ክፍል ጋር ይጣጣማል; አዎ! ምክንያቱም በዚህ ክፍል ወሳጅ ተብሎ የተተረጎመው አረብኛ ቃል ሙታዋፊ በቁርኣን አምላክ ሰዎችን በሞት ሲወስድ ጥቅም ላይ የሚውል ቃል ነው።

> ወሳጅህ ነኝ በሚለው ውስጥ ወሳጅ ተብሎ የተተረጎመው ሙታዋፊ፤ በአብዛኛው አምላክ ሰዎችን በመግደል ወደራሱ የሚወደውን የሚያመለክት ነው። ብዙ ተንታኞች እና ተርጓሚዎች በዚህ ክፍል አውድ በመግደል መውሰድን የሚያመለክት አይደለም ነገር ግን ከዚህ ዓለም መወሰድን ያመለክታል ይላሉ። ቢሆንም አንዳንዶቹ ይህ ክፍል አምላክ ኢየሱስን በመግደል ወደራሱ እንደወሰድ ያመለክታል ይላሉ።[88]
>
> ሙታዋፊ የሚለውን ቃል በትክክለኛ ትርጉሙ የተረጎሙ የቁርኣን ሁለት ትርጉሞች እነሆ፡-
>
> አላህም አለው፡- ኢየሱስ ሆይ እኔ እንድትሞት አደርግሃለሁ፣ እኔም ወደ ራሴ እወስድሃለሁ። (ቁርኣን 3፡54)[89]
>
> አምላክም አለ፡- ኢየሱስ ሆይ እኔው እንድትሞት አደርግሃለሁ፤ እኔም ወደ ራሴ አነሳሃለሁ። (ቁርኣን 3፡55)[90]

ስለዚህ የኢየሱስን ሰማዕታዊ ሞት በሚገባ የምንረዳበት ተጨማሪ ቁርአናዊ ማጣቀሻ አግኝተናል።

የኢየሱስ ወደ ሰማይ መወሰድ በ5፡110-117ም ተጠቅሶ እናገኘዋለን። ይህ ክፍል አምላክ ከኢየሱስ "የእሥራኤልን ልጆች አገደ"[91] ይላል። ነገር ግን ሙስሊም ምሁራን ይህንን አምላክ

---

[87] ቁርኣን 5፡117
[88] *The Study Quran*, ed. Seyyed Hossein Nasr, et al., HarperOne, 2015, fn. for 3:55, p. 146.
[89] Maulana Muhammad Ali, *The Holy Qur'an*, Lahore, Pakistan, 1951.
[90] Muhammad Asad, *The Message of the Qur'an*, Gibraltar, Dar Al-Andalus, 1984.
[91] ቁርኣን 5፡110

ኢየሱስን እንዳይገድሉት ከልክሏቸዋል ብለው ይረዳሉ። ይሁን እንጂ ይህ ክፍል በኢስላማዊው የመጨረሻው እራት ኢየሱስ እንዲህ ብሎ ይቋጫል።

> በርሱ ያዘዝከኝ ቃል ጌታዬንና ጌታችሁን አላህን ተገዙ ማለትን እንጂ ለነርሱ ሌላ አላልኩም፤ በውስጣቸውም እስካለሁ ድረስ በነርሱ ላይ ተጠባባቂ ነበርኩ፤ በተሞላኸኝም ጊዜ፣ (ባነሳኸኝም ጊዜ) አንተ በነሱ ላይ ተጠባባቂ ነበርክ፤ አንተም በነገሩ ሁሉ ዐዋቂ ነህ። (ቁርኣን 5:117)

በዚህ ክፍል "ባነሳኸኝ" ተብሎ የተጠቀሰው አረብኛ ቃል በ3፡55 ላይ ከተጠቀሰው ጋር አንድ አይነት ሲሆን አምላክ ሰዎችን በሞት መውሰዱን የሚያመለክት ነው። ይህም ክፍል የኢየሱስ ሰማዕታዊ ሞት ተቀባይነት ያለው እንዲሆን ተጨማሪ ማጣቀሻ ይሰጣል።

## የሰማዕታት አካል

ቁርኣን ሰማዕታት ሲሞቱ ነፍሳቸው ከአምላክ ጋር እንዲሆን እንደሚወሰድ ስጋዊ አካላቸው ግን በምድር ላይ እንደሚቀር አይተናል። ይህ ታድያ ኢየሱስ እንደሰማዕት ሞቷል ለሚለው መረዳት ተገቢና ተደጋጋፊ ነው; መልሱ አዎን ነው። ምክንያቱም የቁርኣን የስቅለት ትምህርት ኢየሱስ በስጋዊ አካሉ ወደ ሰማይ እንደተወሰደ እንቅጩን አይነግረንም፡ ከዚህ ይልቅ "አላህ ወደራሱ ወሰደው" ብቻ ነው የሚለን። ይህም ደግሞ ለማንኛውም ሰማዕት የሚሆን አነጋገር ነው። የኢየሱስ ስጋ ወደሰማይ ተወስዶ ከሆነ ሰማዕት አይደለም ማለት ነው። የሚገርመው ግን የእርሱ ስጋ ለመወሰዱ ምንም ጠቋሚ መረጃ የለም። ስለዚህ ኢየሱስ እንደ ሰማዕት ሞቷል የሚለው አፈታት ቁርኣን ስለ ሰማዕታት ከሚሰጠው ዝርዝር መረጃ ጋር ተገቢ፣ ተደጋጋፊና ተቀባይነትም ያለው አፈታት ነው።

## የኢየሱስ ዳግም ምጽአት

እንግዲህ ስለ ኢየሱስ ሰማዕት ለመሆኑ ከቁርኣን ምንም ተቃውሞ የለም። ነገር ግን ኢየሱስ ተመልሶ ይመጣል፣ መጥቶም ይሞታል የሚል ተቃውሞ አላቸው። በአመለካከት መሰረት ኢየሱስ በመስቀል ላይ አልሞተም ነገር ግን በስጋ ተወስዷል፣ የዓለም መጨረሻ ምልክት እንዲሆን ተመልሶ ይመጣል፣ ከዚያም ይሞታል። የዚህ አመለካከት ችግሩ ቁርኣን ፈጽሞ ኢየሱስ ተመልሶ ይመጣል አለማለቱ ነው።

> የኢየሱስ ዳግም ምጽአት ግልፅ በሆነ መንገድ የተጠቀሰው በሐዲሳቱ ነው ብንል የተሻለ ነው።[92] ቁርኣን ግን ጥቂት አከራካሪ የሆኑ ጥቅሶች አሉት። በመጀመርያ እስቲ ቁርአኑን እንመልከት። በቁርኣን ውስጥ ኢየሱስ በመጨረሻው ዘመን ወደ ምድር ተመልሶ እንደሚመጣ የሚገልፅ ግልፅ የሆነ ጥቅስ የለም። ነገር ግን የቁርኣን ሐታቾች በጥቂት አከራካሪ ጥቅሶች ላይ ተመሥርተው ያንን ትርጓሜ ይሰጣሉ።

---

92 ከቁርኣን ውጪ የሚገኙ ታሪኮች

ስለዚህ ቁርኣን በግልፅ ኢየሱስ ወደ ምድር ተመልሶ ይመጣል አይልም። ሆኖም ሙስሊም ሊቃውን የኢየሱስን ተመልሶ መምጣት እንደሚያመለክት የሚናገሯቸው ሁለት ጥቅሶች አሉ፤ ፡159 እና 43፡61።

ሱራ 4፡159ን በተመለከተ፡-

> "ከመጽሐፉም ሰዎች ከመሞቱ በፊት በርሱ (በዒሳ) በእርግጥ የሚያምን እንጂ (አንድም) የለም፤ በትንሣኤም ቀን በነሱ ላይ መስካሪ ይሆናል።" (ሱራ 4፡159)

ሙስሊም መሪዎች *ከመሞቱ በፊት* የሚለው ኢየሱስ በዳግም ምፅዓቱ ጊዜ ይሞታል በሚል ይፈቱታል። ነገር ግን ከመሞት በፊት ማመን የሚለው በቁርኣን ውስጥ ትልቅ ቦታ የተሰጠው መሪ ሐሳብ በመሆኑ ይህ ትክክለኛ ፍቺ አይመስልም።[93] በቁርኣን መሠረት እምነታቸው ተቀባይነት እንዲኖረው ከመሞታችሁ በፊት ማመን ግድ ነው። ይህ ጥቅስ አብዛኞቹ አይሁድ ኢየሱስ ከመሞቱ በፊት እንደማይቀበሉት ነው የሚናገረው። ኢየሱስን ስላልተቀበሉት አይሁድ ሞት እንጂ ስለ ኢየሱስ ሞት አይናገርም።

ሱራ 43፡61ን በተመለከተ

> "እርሱም (ዒሳ) ለሰዓቲቱ (ማወቂያ) በእርግጥ ምልክት ነው። በርሷም አትጠራጠሩ። ተከተሉኝም፤ ይህ ቀጥተኛ መንገድ ነው (በላቸው)።" (ሱራ 43፡61)

በሙስሊም መሪዎች መሠረት በቃሉ መጀመርያ ላይ የሚገኘው "እርሱ" የሚለው ተውላጠ ስም ኢየሱስን የሚያመለክት በመሆኑ ኢየሱስ ኢየሱስ የሰዓቱ ምልክት በመሆን ከፍርድ ቀን በፊት ተመልሶ በመምጣት ድርሻውን መወጣቱ ግድ ነው ይላሉ። ሆኖም የአማርኛ ቁርኣን ተርጓሚዎች ኢየሱስ መሆኑን እርግጠኛ ሆነው በቅንፍ ቢጨምሩም ጥቅሱ ግን በግልፅ ኢየሱስ ተመልሶ ይመጣል አይልም። "እርሱ" የሚለው ተውላጠ ስም ከኢየሱስ ይልቅ ቁርኣንን አመላካች ነው። ምልክት ወይም ዕውቀት፣ ጥርጥር የሌለውና ቀጥተኛው ተብሎ በቁርኣን ውስጥ በተደጋጋሚ የተነገረለት ቁርኣን ራሱ ነው።

> ይህ ጥቅስም ሆነ ሌሎች ኢየሱስ በመጨረሻው ቀን ተመልሶ እንደሚመጣ በግልፅ አይናገሩም። ሁሉም በናንተ አፈታት ላይ የተደገፉ ናቸው። ስለዚህ ቁርኣን በዚህ ጉዳይ ላይ ግልፅ ነው ማለት አይቻልም። ከቁርኣን ውጪ የሚገኙትን ሐዲሶች የማይቀበሉት አንዳንድ ዘመንኛ ተርጓሚዎች የኢየሱስ ዳግም ምፅዓት ከክርስትና የተቀዳ አፈ ታሪክ እንደሆነ መናገራቸው ብዙም አይደንቅም።[94]

[93] ቁርኣን 2:132, 217, 3:91, 102, 193, 4:18, 6:158, 7:32, 9:55, 85, 10:90-91, 15:99, 26:102, 36:70, 39:58, 40:11, 47:34, 56:83-96, 63:10.
[94] Akyol, p. 186.

ስለዚህ የኢየሱስ ዳግም ምፅዓት በቁርኣን ውስጥ በግልፅ ስላልተነገረ በቁርኣን መሠረት ኢየሱስ በመስቀል ላይ ሰማዕት የመሆኑን ጉዳይ በዚህ መነሻነት ውድቅ ማድረግ አይቻልም።

## መደምደምያ

በዚህ ክፍል የተቀረው የቁርኣን ክፍል ስለ ኢየሱስ ምን እንደሚናገርና በመስቀል ላይ የመሰቀሉ ጉዳይ ከዚህ ጋር አብሮ የሚሄድ መሆን አለመሆኑን ተመልክተናል። አብሮ እንደሚሄድም አረጋግጠናል። ስለዚህ በቁርኣን መሠረት ይህንን ሐሳብ ለመቃወም የሚያበቃ ምንም ነገር የለም። ይልቅ ቁርኣን ራሱን በራሱ እንዲያብራራ ከፈቀድን ተመራጩ አመለካከት እርሱ ይመስላል። ይህ ማለት አንድ ሙስሊም መጽሐፍ ቅዱስን አልሰማ ብሎ ኢየሱስ አለመሞቱ የሙጥኝ የሚል ከሆነ የተሻለውን ትርጓሜ ከቁርኣን ከራሱ ልታሳዩት ትችላላችሁ ማለት ነው። ይህ አካሄድ ታሪክና መጽሐፍ ቅዱስ የሚሰጡትን ምስክርነት ለማገናዘብ ልቡን እንዲከፍት ይረዳዋል፤ እናም በማስከተል ይህንን እናደርጋለን።

## የኢየሱስ መሞትና መጽሐፍ ቅዱስ

መጽሐፍ ቅዱስ ኢየሱስ ስለመሞቱ በግልፅ ይናገራል፤ ይህንንም ለሙስሊም ወዳጃችሁ ማሳየት በጣም ጠቃሚ ነው።

1. ኢየሱስ ስለ ሞቱ በተደጋጋሚ ተናግሯል።
   “ከዚያን ቀን ጀምሮ ኢየሱስ ወደ ኢየሩሳሌም ይሄድ ዘንድ ከሽማግሌዎችና ከካህናት አለቆች ከጻፎችም ብዙ መከራ ይቀበልና ይገደል ዘንድ በሦስተኛውም ቀን ይነሣ ዘንድ እንዲገባው ለደቀ መዛሙርቱ ይገልጥላቸው ጀመር።” (ማቴ. 16፡21)
   “እንዲሁም የሰው ልጅ ሊያገለግል ነፍሱንም ለብዙዎች ቤዛ ሊሰጥ እንጂ እንዲያገለግሉት አልመጣም።” (ማቴ. 20፡28)

   “ጽዋንም አንሥቶ አመስግኖም ሰጣቸው እንዲህም አለ፦ ሁላችሁ ከእርሱ ጠጡ፤ ስለ ብዙዎች ለኃጢአት ይቅርታ የሚፈስ የአዲስ ኪዳን ደሜ ይህ ነው።” (ማቴ. 26፡27-28)
2. ሁሉም ወንጌል ዘገባዎች ኢየሱስ በመስቀል ላይ መሞቱን ጽፈዋል።
3. የኢየሱስ ሐዋርያት ስለ ሞቱ ተናግረዋል።
   “ኢየሱስ ክርስቶስ ከሙታን በመነሣቱ ለሕያው ተስፋና ለማይጠፋ፥ እድፈትም ለሌለበት፥ ለማያልፍም ርስት እንደ ምሕረቱ ብዛት ሁለተኛ የወለደን የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አምላክና አባት ይባረክ።” (1ጴጥ. 1፡3)
   “ገና ደካሞች ሳለን ክርስቶስ ዘመኑ ሲደርስ ስለ ኃጢአተኞች ሞቶአልና።” (ሮሜ 5፡6)
4. ከኢየሱስ በፊት የነበሩት ነቢያት ስለ ሞቱ አስቀድመው ተንብየዋል። ይህ በጣም ጥሩ ነጥብ ነው ምክንያቱም ሙሊሞች የኢየሱስ ሞት በክርስቲያኖች

እንዳልተፈጠረና በነቢያት አስቀድሞ እንደተነገረ ይገነዘባሉና። ነቢዩ ኢሳይያስ ማን እንደሆነና መች እንደኖረ ከነገራችሁ በኋላ ኢሳይያስ 53ን አብራችሁ በማንበብ ምን እየተነበየ እንዳለ ጠይቋቸው። ስለ ኢሳይያስ 53 ጥያቄ ካላችሁ ምዕራፍ 6 ተመልከቱ።

*መጽሐፍ ቅዱስ ራሱ ይናገር...*

## የኢየሱስ ሞትና ታሪክ

ብሉይ ኪዳን የኢየሱስን መሞት እንደሚነግረን ሁሉ ታሪክም ይህንኑ ያረጋግጣል። ስለዚህ ሙስሊም መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ኢየሲስ መሞት የተናገረውን አልቀበልም የሚል ከሆነ ከመጽሐፍ ቅዱስ ውጪ የሚገኝ የታሪክ ማስረጃ መሞቱን እንደሚናገር ልትነግሩት ትችላላችሁ። ብዙ ሊቃውንት በዚህ ረገድ አስደናቂ መጻሕፍትን ጽፈዋል።[95]

- ታሉስ (55 ዓ.ም.)
- ማራ በር ሴራፒዮን (70 ዓ.ም.)
- ታሲተስ (64 ዓ.ም.)
- ፐሊኒ (110 ዓ.ም.)
- የሰሞሳታው ሉሺያን (115-200 ዓ.ም.)
- ዮሴፍ ወልደ ኮርዮን (c. 90 ዓ.ም.)
- ታልሙድ (> 200AD)
- ሱቶኒየስ (c. 49 ዓ.ም.)

ጠቂት ምሳሌዎች እነሆ። ታሲተስ የኢየሱስን ሞት የዘገበ ሮማዊ ባለ ሥልጣን ነው።

> “ይህንን ስም (ክርስቲያን የሚለውን) ያስገኘው ክርስቶስ; ጢባሪዮስ ቄሣር ንጉሥ በነበረበት ዘመን ወኪል አስተዳዳሪ በነበረው በጳንጢዮስ ጲላጦስ ትእዛዝ ተገድሏል። ይህ መርዛማ አምልኮት ለጊዜው በቁጥጥር ስር ቢውልም ነገር ግን ይህ ክፋት በተጀመረባት በይሁዳ ብቻ ሳይሆን ከዓለም ዙርያ ሁሉ ቆሻሻና አስቀያሚ የሆኑ አስተሳሰቦች ሁሉ በሚጠራቀሙባት በሮምም ውስጥ እንደ ወረርሺኝ ተስፋፍቷል።” (Tacitus, *Annals* 15:44)

የአይሁድ ታልሙድም እንዲህ ይላል፡-

> “በፋሲካ ዋዜማ ዬሹዋ (ኢየሱስ) ተሰቀለ። ከመገደሉ በፊት 40 ቀናት ቀደም ብሎ አዋጅ ነጋሪ በመውጣት ‘አስማትን በመለማመድ እሥራኤልን ወደ ክህደት ስለመራ ይወገራል። እርሱን በመደገፍ የሆነ ነገር መናገር የሚችል ፊት ለፊት ይውጣና ስለ

[95] Paul Barnett, *Is the New Testament History?* F.F. Bruce, *The New Testament Documents - Are The Reliable?* John Dickson, *The Christ Files*. Book and DVD, www.thechristfiles.com.au

እርሱ ይሚገት' በማለት ጮኸ ነበር። እርሱን የሚደግፍ ምንም ነገር ባለመቅረቡ በፋሲካ ዋዜማ ተሰቀለ።" (Babylonian Talmud, Sanhedrin 43a)

ከመጽሐፍ ቅዱስ ውጪ የሚገኘው ታሪክ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሚገኘውን ታሪክ ያረጋግጣል። ስለዚህ የኢየሱስን በመስቀል ላይ መሞት ለመጠራጠር የሚያበቃ ምንም ምክንያት የለም። የታሪክ ሊቃውንት በዚህ ረገድ ምንም ዓይነት ጥርጣሬ የላቸውም፤ ቀደም ሲል እንዳየነው ደግሞ ይህንን የሚቀበሉ አንዳንድ ሙስሊም ሊቃውንት አሉ።[96] [97]

## ማጠቃለያ

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ኢየሱስ በመስቀል ላይ መሞቱን ለሙስሊሞች እዴት ማሳየት እንደምንችል ተመልክተናል። ሙስሊሞች በአብዛኛው የሚያምኑት ኢየሱስ አለመሰቀሉንና እርሱን የሚመስል ምትክ በመስቀል ላይ መሰቀሉን ነው። ይህ ወንጌልን እንዳይቀበሉ ትልቅ እቅፋት ሆኖባቸዋል። ከመጽሐፍ ቅዱስ ወይንም ከታሪክ የኢየሱስን መሞት ከማስረዳት ይልቅ በቁርኣን መሠረት የኢየሱስን ሰማዕትነት መቀበል ይበልጥ ትርጉም እንደሚሰጥ በማስረዳት መጀመር የተሻለ መሆኑን ተመልክተናል። ይህ ማብራርያ ቁርኣን ራሱን በራሱ ሲያብራራ የምናገኘው ሲሆን ቁርኣንን በውጫዊ ምንጮች ከማብራራት የተሻለ ነው። ይህ ማብራርያ ከተቀረው የቁርኣን ክፍል ጋር ፍፁም የተስማማ መሆኑን በሰፋት ተመልክተናል። አዲስ ኪዳን ኢየሱስ በመስቀል ላይ መሞቱን በግልፅ እንደሚናገር ተመልክተናል፤ ብሉይ ኪዳንም ክስተቱን ይተነብያል፤ ታሪክም ይህንኑ ያረጋግጣል። ስለዚህ ክርስቲያኖችና ሙስሊሞች የኢየሱስን ስቅለት የሚጠራጠሩበት ምንም ምክንያት ባለመኖሩ ለምን እንደሞተ ወደ መወያየት መሸጋገር ያስፈልጋቸዋል።

## ትግበራና ማጠቃለያ

1. ለሙስሊሞች ወንጌልን ስታካፍሉ ስለ ኢየሱስ ስቅለት ምን እንደሚያምኑ መጠየቅ አስፈላጊ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ የሚለውን ካልተቀበሉ፡-
2. ሱራ 4፡1576-158 እንዴት እንደሚያብራሩት በመጠየቅ ሙስሊሞች የተለያዩ አቋሞች እንዳሏቸው አስረዷቸው። ለአመለካከታቸውም ያላቸው ማስረጃ ምን እንደሆነ ጠይቋቸው።
3. የኢየሱስ ሰማዕትነት የቁርኣንን ሐሳብ ለመተርጎም የተሻለው መንገድ መሆኑን አስረዷቸው። ሱራ 8:17, 2:154, 3:169 ጥቀሱላቸው። ቁርኣን ስለምትክ ምንም ነገር እንደማይል አሳዩዋቸው።

---

[96] Prof. Masud ul Hasan, History of Islam, Delhi, India: Adam Publishers & Distributors, 2002, vol. 1, p. 29.

[97] Reza Aslan, Zealot - The Life and Times of Jesus of Nazareth, New York, U.S.A.: Random House, 2013 p. xxviii

4. ኢየሱስ በመስቀል ላይ ስለመሞቱ መጽሐፍ ቅዱስ ግልፅ መሆኑን አሳዩዋቸው።
5. ከኢየሱስ በፊት የነበሩት ነቢያት ሞቱን አስቀድመው መተንበያቸውን አሳዩዋቸው።
6. ታሪክ ኢየሱስ በመስቀል ላይ መሞቱን እንደሚናገር አሳዩዋቸው።

በመጨረሻም ከሙስሊም ወዳጃችሁ ጋር ልትወያዩበት የምትችሉት ቡክሌት ድረገፅ ላይ የገኛል።

## የሚደጋገሙ ጥያቄዎች

1. *ሙስሊም* ፡ ኢየሱስ እንደ ዮናስ እንደሚሆን ተናግሯል። ዮናስ በዓሣው ሆድ ውስጥ ሕያው ነበር ስለዚህ ኢየሱስ በመስቀል ላይ ሕያው ነበር።

   > ዮናስ በዓሣ አንባሪ ሆድ ሦስት ቀንና ሦስት ሌሊት እንደ ነበረ፥ እንዲሁ የሰው ልጅ በምድር ልብ ሦስት ቀንና ሦስት ሌሊት ይኖራል።” (ማቴ. 12፡40)

   *ክርስቲያን* ፡ ኢየሱስ እንደ ዮናስ ሕያው ወይም ሙት እንደሚሆን አልተናገረም። ንፅፅሩ ከሦስት ቀናት ጋር ነው። ኢየሱስ ያላለውን ነገር ወደ ክፍሉ እየጨመርክ ነው። ለአይሁድ *ሦስት ቀንና ሦስት ለሊት* የሚለው የትኛውንም የቀን ክፍል የተመለከተ ንግግር ነው።[98]

   ዮናስ በዓሣው ሆድ ውስጥ በነበረ ጊዜ መቃብር መግባቱን ተናግሯል[99] (በእብራይስጥ ሺዖል ማለት መቃብር ማለት ነው)። ስለዚህ ሞቶ የመቃብርን ሁኔታ እያጣጣመ ሊሆን ይችላል። እስልምና እንደሚያስተምረው ሰዎች በመቃብር ውስጥ ንቁዎች ናቸው ስለዚህ ምናልባትም በዚያ ሁኔታ ውስጥ እያለፈ ሊሆን ይችላል።

2. *ሙስሊም* ፡ ኢየሱስ በመስቀል ላይ መሞቱን ከተቀበልኩ አንድ ችግር አለ፤ ኢየሱስ አምላክ ነው ትላላችሁ። ኢየሱስ አምላክ ከሆነ አምላክ እንዴት ሊሞት ይችላል? ፍጥረት ፈጣሪውን ሊገድል አይችልም።

   *ክርስቲያን* ፡ ይህ ጥሩ ጥያቄ ነው። መልሱ ሁለት ገፅታ አለው። የመጀመርያው ሞት ማለት ሕልውና ማጣት ማለት አይደለም። ሁለተኛው ኢየሱስ በአንድ ማንነት ሁለት ባሕርያት አሉት። የሞተው በሰብዓዊ ባሕርዩ ነው።

3. *ሙስሊም* ፡ ደቀ መዛሙርት ለስቅለት የዓይን እማኞች አልነበሩም።

   > ከምስክሮቹ መካከል አንዱ የሆነው ማርቆስ በምዕራፍ 14 ቁጥር 50 ላይ በጣም ወሳኝ በሆነው የኢየሱስ የሕይወት መስቀለኛ ጊዜ ላይ ሁሉም ደቀ መዛሙርቱ ጥለውት እንደሸሹ ስለሚናገር ነው። ክርስቲያን ጎረቤታችሁን “ሁሉም ማለት በናንተ ቋንቋ ሁሉም ማለት ነውን?” ብላች ጠይቁት። …

[98] አስቴር 4:16-5:1
[99] ዮናስ 2፡2

ለዚህ ምክንያቱ የኢየሱስ ደቀ መዛሙርት መምህራቸው በመስቀል ላይ መሰቀሉን በወሬ ወሬ መስማታቸው ነው። ነፍሱን መስጠቱን በወሬ ወሬ ስለሰሙ ነው። በሌላ አባባል፡- ነፍሱ ወጥታለች፤ ሞቷል። መሞቱንና ለሦስት ቀናት መቀበሩን በወሬ ወሬ ነው የሰሙት። የነበራቸው መረጃ ሁሉ የወሬ ወሬ ነው።[100]

*ክርስቲያን* ፡ በአጭሩ ይህ ሐሰት ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ሐዋርያቱና ተከታዮቹ የስቅለቱን ሒደት በዓይናቸው እንደተመለከቱ ይናገራል (ሉቃ. 23፡49፣ ዮሐ. 19፡ 25-27)።

4. *ሙስሊም* ፡ የኢየሱስ ሞት በትክክል እንዳልተከሰተና እንደተመሳሰለ የሚናገሩ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሌሉ ሌሎች ወንጌሎች አሉ።
*ክርስቲያን* ፡ አዎ አሉ ነገር ግን እነዚያው ወንጌል ያልካቸው የእግዚአብሔርን ፈጣሪነት ይክዳሉ። በነዚያ ሰዎች መሠረት ፈጣሪ ከፍጥረት የተነጠለ በመሆኑ በምንም መንገድ ከፍጥረት ጋር ግንኙነት ሊኖረው አይችልም። ኢየሱስ አምላክ መሆኑን ያምናሉ ስለዚህ አምላክ ከሆነ ደግሞ ተመስሎ እንጂ ሥጋዊ አካል የለውም ይላሉ። በዚህ ሁኔታ የተሰቀለ መሰለ ይላሉ። በፈጣሪ የምታምን ከሆነ ይህንን አመለካከት መቃወም ያስፈልግሃል። የቀደሙት ክርስቲያኖች እነዚህን ወንጌላት ያልተቀበሏቸው በምክንያት ነው። *የበርናባስ ወንጌልና የእስልምና ወንጌል* የተሰኙት መጻሕፍት ደግሞ ተመሳስለው በሙስሊሞች የተጻፉ በመሆናቸው አንቀበላቸውም።

5. *ሙስሊም* ፡ ኢየሱስ በመስቀል ላይ አልሞተም ምክንያቱም አላህ ነቢያቱ እንዲገደሉ አይፈቅድምና።
*ክርስቲያን* ፡ መጽሐፍ ቅዱስም ሆነ ቁርኣን ነቢያት በሰዎች እጅ ስለመገደላቸው ይናገራሉ፣ 2፡61፣ 3፡21፣ 4፡155

---

100 Ahmed Deedat, Crucifixion or Cruci-Fiction?, ch. 3, pp. 7-8 & ch. 13, p. 55

# ምዕራፍ 9

## ሙሐመድ ማን ነበር?

ሙሐመድ (570-632 ዓ.ም.) በእስልምና ሃይማኖት ውስጥ ዋናው ሰው ነው። ከነቢያት ሁሉ ታላቁ እንደሆነ ይታሰባል። በዛሬይቱ ሳዑዲ አረብያ ውስጥ በሚገኙ መካና መዲና በተሰኙ ከተሞች ውስጥ ይኖር የነበረ ሲሆን የአረብ ቁረይሽ ጎሣ ተወላጅ ነበር። የእስልምና ሃይማኖት ሙሉ በሙሉ በእርሱ ላይ የተመሠረተ ነው። ቁርኣን እርሱ ከፈጣሪ ዘንድ የተቀበለው መልእክት እንደሆነ ይነገርለታል። የእርሱ ልምምድ (ሱና) የሙስሊሞች ሁሉ ልምምድ እንዲሆን ይፈለጋል። እርሱ የመጀመርያው እስላማዊ ምንግሥት መሥራች ነበር።

### ክርስቲያኖች ማሰብ ያለባቸው ምንድነው?

ሙሐመድ ከእግዚአብሔር ዘንድ የመጣ ነቢይእንደሆነ ያስብ ነበር። ክርስቲያኖች ለዚህ እንዴት መመለስ ይኖርባቸዋል? መጽሐፍ ቅዱስ ነቢይ ነኝ የሚሉትን ሰዎች ዝም ብለን መግፋት ሳይሆን እንድንፈትናቸው ያሳስበናል።

> መንፈስን አታጥፉ፤ ትንቢትን አትናቁ፤ ሁሉን ፈትኑ መልካሙንም ያዙ። (1ተሰ. 5፡ 19-20)

> “የበግ ለምድ ለብሰው ከሚመጡባችሁ በውሥጣቸው ግን ነጣቂዎች ተኵላዎች ከሆኑ ከሐሰተኞች ነቢያት ተጠንቀቁ።ከፍሬያቸው ታውቋቸዋላችሁ። ከእሾህ ወይን ከኲርንችትስ በለስ ይለቀማልን?” (ማቴ. 7፡15-16)

> “ወዳጆች ሆይ፥ መንፈስን ሁሉ አትመኑ፥ ነገር ግን መናፍስት ከእግዚአብሔር ሆነው እንደ ሆነ መርምሩ፤ ብዙዎች ሐሰተኞች ነቢያት ወደ ዓለም ወጥተዋልና።” (1ዮሐ. 4፡1)

ታድያ ሙሐመድ ነብይ መሆን አለመሆኑን እንዴት ነው የምንመረምረው? በዚህ ምዕራፍ ሦስት ማስረጃዎችን እናጤናለን፤ የመጀመርያው ቁርኣን ለሙሐመድ እውነተኛ ነቢይነት የሚሰጠውን ማስረጃ ነው። ይህ ማለት ሙሐመድን በገዛ ቃሉ በመፈተን የሚያቀርብልንን ማስረጃ ማጤን ማለት ነው።[101] ሁለተኛ በመጽሐፍ ቅዱስ መስፈርቶች መሠረት ሙሐመድን እንመዝነዋለን። ከዚህም አልፎ ሌሎች ኢስላማዊ ምንጮችን በጥልቀት እንመለከታለን።

---

101 ሙስሊሞች ሒሳባዊ ግጥምጥሞሾችና ሳይንሳዊ ትንቢያዎችን የመሳሰሉ ሌሎች ማስረጃዎችን ለሙሐመድ ነቢይነት ያቀርባሉ። ቁርኣን እነዚህን ሙግቶች ስለማይጠቀም አሁን እዚህ አንመለከታቸውም። ይህንን ምዕራፍ ቁርኣን ራሱ በሚያቀርባቸው ሙግቶች ገድቤያለሁ።

## ክፍል ፲፡ ሙሐመድን በገዛ ቃሉ መመዘን

ሙሐመድ በ7ኛው ክ.ዘ በመካ ስብከቱን ሲጀምር አድማጮቹ ምልክት እንዲያሳያቸው ይጠይቁ ነበር። ሙሴና ኢየሱስ ምልክቶችን ማቅረባቸውን ሰምተው ስለነበር ሙሐመድንም ጠየቁት። ነገር ግን በቁርኣን ውስጥ እንደተነገረው ሙሐመድ ምንም ምልክት አልሰጠም። ከዚያ ይልቅ አስፈራሪ ብቻ እንደነበረ ነው የመለሰላቸው።

> «ከጌታውም በኾነ ተዓምር አይመጣንምን» አሉ በመጀመሪያዎቹ ጽሑፎች ውስጥ ያለችው ማስረጃ አልመጣቻቸውምን (ሱራ 20፡133)
>
> እውነቱም ከእኛ ዘንድ በመጣላቸው ጊዜ «ለሙሳ የተሰጠው ብጤ አይሰሰጠውም ኖሯልን» አሉ። «ከዚህ በፊት ሙሳ በተሰጠው አልካዱምን የተረዳዱ ሁለት ድግምቶች ናቸው» አሉ። «እኛ በሁሉም ከሓዲዎች ነንም» አሉ። (ሱራ 28፡48)
>
> «በእርሱ ላይም ከጌታህ ዘንድ ተዓምራቶች ለምን አልተወረዱም» አሉ። «ተዓምራቶች አላህ ዘንድ ብቻ ናቸው። እኔም ግልጽ አስፈራሪ ብቻ ነኝ» በላቸው። (ሱራ 29፡50)

ቁርኣን በእስልምና ውስጥ ዋና መጽሐፍ ነው። ሐዲስ የሚባሉ ሌሎች አስፈላጊ መጻሕፍትም አሉ። እነዚህ የሐዲስ መጻሕፍት ሙሐመድ ተዓምራትን ማድረጉን ቢናገሩም ከብዙ ክፍለ ዘመናት በኋላ የተጻፉና ከቁርኣን ጋር የሚጣረሱ በመሆናቸው ተዓማኒ አድርጎ መቁጠር አይቻልም። እኔ የተቀበልኩት የቁርኣንን ዘገባ በመሆኑ በቁርኣን መሠረት ሙሐመድ ምንም ዓይነት ተዓምር አላደረገም። ቁርኣን እንደ ሙሴና እንደ ኢየሱስ ያሉ ተዓምራትን ለሙሐመድ ነቢይነት እንደ ማረጋገጫ አለማቅረቡን እርግጠኛ መሆን ይቻላል።

አሁን ደግሞ ቁርኣን ለሙሐመድ ነቢይነት ያቀረባቸውን ማስረጃዎች እንመለከታለን።

## ምክንያት ፩፡ ሙሐመድ እውነተኛ ነቢይ ካልሆነ ፈጣሪ ይገድለዋል።

> "በኛ ላይም ከፊልን ቃላት (ያላልነውን) በቀጠፈ ኖሮ፤ በኀይል በያዝነው ነበር። ከዚያም ከርሱ የልቡን ስር (የተንጠለጠለበትን ጂማት) በቆረጥን ነበር።" (ቁርኣን 69፡44-46)

በዚህ ጥቅስ መሠረት ሙሐመድ እውነተኛ መልእክተኛ ባይሆን ኖሮ ፈጣሪ የልቡን ስር (ደም ቅዳ) በመቁረጥ ይገድለው ነበር። ሆኖም ይህ ትክክለኛ መስፈርት አይደለም፤ ምንም የሚያረጋግጠው ነገርም የለም። ለዚህ ምክንያቱ ሁለት ነው፤ የመጀመርያው ብዙ ሰዎች በእግዚአብሔር ስም ሐሰትን ቢናገሩም እግዚአብሔር ወድያውኑ ሲገድላቸው አለመታየቱ ነው። እግዚአብሔር ስላልገደላቸው ከእርሱ ዘንድ ናቸው ማለት ነውን? በፍፁም። ይልቁኑ እግዚአብሔር ከሐሰተኛ ነቢያት እንድንጠነቀቅና እንድንመረምራቸው ይፈልጋል። ስለዚህ

ይህ በቁርአን ውስጥ የቀረበው ምክንያት ስለ ሙሐመድ የሚነግረን ምንም ነገር የለም። ኢ-አመክንዮአዊ ነው።

በመጨረሻ ይህ ምክንያት የማይሠራና ኢ-አመክንዮአዊ ቢሆንም ትክክለኛነቱን ከተቀበልን በሚገርም ሁኔታ ሙሐመድ ሐሰተኛ ነቢይ መሆኑን ያረጋግጥልናል። ለዚህም ምክንያቱ ሙሐመድ ሊሞት ሲቃረብ የልቡ ስር እንደተቆረጠ ተሰምቶት ነበር።

> አይሻ እንዳወራችው፡- ነቢዩ በሞቱበት ህመም ሲታመሙ ሳሉ እንዲህ ብለው ይናገሩ ነበር፤ "አይሻ ሆይ! በኸይበር ከበላሁት ምግብ የተነሳ እስከ አሁን ህመም ይሰማኛል፣ በዚህ ሰዓት ግን ከመርዙ የተነሳ የልቤ ስር እንደተቆረጠ እየተሰማኝ ነው።" (ሳሂህ አል-ቡኻሪ ቅፅ 5፣ መጽሐፍ 59፣ ቁጥር 713፣ 4428)

## ምክንያት 2፡ ቁርአን በጠራ አረብኛ በመሆኑ ሙሐመድ እውነተኛ ነቢይ ነው

> እነሱም እርሱን (ቁርአንን) የሚያስተምረው ሰው ብቻ ነው፣ ማለታቸውን በእርግጥ እናውቃለን፤ የዚያ ወደርሱ የሚያስጠጉበት ሰው ቋንቋ ዐጀም ነው፤ ይህ (ቁርአን) ግን ግልጽ ዐረብኛ ቋንቋ ነው።[102]

የዚህ አውድ እንደሚያመለክተው የሙሐመድ ተቃዋሚዎች ሌላ ቋንቋ ከሚናገር ሰው ጋር ሲነጋገር ስለተመለከቱት ሙሐመድ መገለጡን ከፈጣሪ ዘንድ ሳይሆን ከዚያ ሰው እንደተቀበለ ተናገሩ። በምላሹም ቁርአን ሙሐመድ የሌላ ቋንቋ ተናጋሪ ከሆነ ሰው ጋር መነጋገሩን ሳይክድ ቁርአን በጠራ አረብኛ መሆኑንና ያ ሰው በሚናገረው መንገድ አለመሆኑን እንደ ምክንያት በማቅረብ ሙሐመድ ነቢይ ነኝ ማለቱ ትክክል ነው ይላል።

አሁንም ይህ ሙግት ስህተትና ምንም ነገር የማያረጋግጥ ከንቱ ሙግት ነው። ኢ-አመክንዮአዊ ነው። ከሌላ ባሕል ከመጣ አንድ ሰው ጋር ተነጋግራችሁ የእርሱን ሐሳብ ወደ ባሕላችሁ ማምጣት በጣም ይቻላል። እንዲህ ያለው የሐሳብ ተውሶ ሁል ጊዜ የሚደረግ ነው። አንዱ መንገድ የትርጉም ሥራ ነው። ብዙ መጻሕፍት ከአንዱ ወደ ሌላው ቋንቋ ተተርጉመዋል፤ እነዚህም ትርጉሞች ውበት ያላቸውና ተፅዕኖ ፈጣሪ ናቸው። ስለዚህ ሙሐመድ ስለ ፈጣሪ ሐሳቦችን ከሌላ ቋንቋ ተናጋሪ በመውሰድ ወደ አረብኛ ቋንቋ ለውጦ ማቅረብ ይችላል። ሙሐመድ በዙርያው ከነበሩት ባሕሎች ሐሳቦችን ይወስድ እንደነበር ስለተነገረ ይህ ሃቅ ነው።

> ኢብን አባስ እንዳወራው ነቢዩ ከአላህ ዘንድ ትዕዛዝ በሌለባቸው ጉዳዮች ላይ የመጽሐፉን ሰዎች (አይሁድና ክርስቲያኖች) የሚያደርጉትን ቀድቶ ያደርግ ነበር... (ሳሂህ አል-ቡኻሪ ቅፅ 7፣ መጽሐፍ 72፣ ቁጥር 799)

---

102 እንዲሁም ቁርአን 44፡14

አል-በራ እንዳወራው ለአሥራ ስድስት ወይንም አሥራ ሰባት ዓመታት ያህል ቀወደ ኢየሩሳሌም ዞረን እንሰግድ ነበር። ከዚያም አላህ ፊቱን ወደ ቂብላ (መካ) እንዲያዞር ነገረው። (ሳሂህ አል-ቡኻሪ ቅፅ 6፣ መጽሐፍ 60፣ ቁጥር 19)

አነስ እንዳወራው እስልምናን የተቀበለ አንድ ክርስቲያን ነበረ፤ ይህ ሰው ምዕራፍ 2 እና 3ን ያነብ የነበረ ሲሆን ለነቢዩ (ቁርአንን) ጸሐፊ በመሆን ያገለግል ነበር። ኋላ ላይም ወደ ክርስትናው በመመለስ እንዲህ ሲል አወራ፡- "ሙሐመድ እኔ ከጻፍኩለት ነገር ውጪ ምንም ነገር አያውቅም።" ከዚያም አላህ ገደለው... (ሳሂህ አል-ቡኻሪ ቅፅ 4፣ መጽሐፍ 56፣ ቁጥር 814)

የቁርአንን ቃላት ስንመለከት ይህ ይበልጥ ይረጋገጣል። ለምሳሌ ያህል *ወንጌል* የሚለውን ቃል ተመልከቱ። ቁርአን ብዙ ቦታዎች ላይ ስለ ወንጌል የሚናገር ሲሆን የሚጠቀመው ቃል ኢንጂል የሚል ነው። ነገር ግን ይህ የግሪክ ቃል ነው። የግሪኩ ቃል ኢዋንጌልዮን የሚል ሲሆን ወደ አረብኛ ሲወሰድ ኢንጂል ይሆናል። ሦስቱን ተመሳሳይ ተነባቢዎች መመልከት ትችላላችሁ (ኢንግል)። ልክ ሚስዮን እንሚለው የአማርኛ ቃል ማለት ነው። መነሻው ሚሽን የሚል የእንግሊዘኛ ቃል ነው። በቁርአን ውስጥ ብዙ የውጪ ቃላት ያሉ ሲሆን ከሌሎች ባሕሎች ሃይማኖታት ጋር አብረው የተጠቀሱ ናቸው።[103]

## ምክንያት 3፡ በቁርአን ውስጥ ተቃርኖ የለም

"ቁርአንን አያስተነትኑምን? ከአላህ ሌላ ዘንድ በነበረ ኖሮ፣ በርሱ ውስጥ ብዙ መለያየት ባገኙ ነበር።" (ቁርአን 4፡82)

በዚህ ጥቅስ መሠረት በቁርአን ውስጥ ተቃርኖ ስለሌለ ቁርአን ከፈጣሪ ዘንድ መሆኑን እናውቃለን፤ እናም ሙሐመድ እውነተኛ ነቢይ ነው።

አሁንም ይህ ሙግት ውኃ አይቋጥርም። እንደ መማርያ መጻሕፍት፣ ልበ ወለዶች፣ መድብለ ቃላትና የመሳሰሉት መጻሕፍት ተቃርኖ በውስጣቸው ላይኖር ይችላል። በሺህዎች የሚቆጠሩ ተቃርኖ በውስጣቸው የሌለ መጻሕፍት አሉ። ይህ ትክክለኛ የፈጣሪ ቃል አያደርጋቸውም ወይንም ጸሐፊያኑን ነቢያት አያደርጋቸውም። የቁርአኑ ሙግት ምንም ነገር የማያረጋግጥ ኢ-አመክንዮአዊ ነው።

ይህ ሙግት ምንም ነገር የማያረጋግጥ ኢ-አመክንዮአዊ ቢሆንም ቁርአንን ስንፈትሽ ግን በውስጡ ተቃርኖዎችን እናገኛለን። የተወሰኑ ግጭቶች እነሆ፡-

---

103 Arthur Jeffery, The Foreign Vocabulary of the Qur'an, Oriental Institute Baroda,
1938;
answering-islam.org/Books/Jeffery/Vocabulary/index.htm

1. በፍርድ ቀን የእስልምናው አምላክ መልካም ሥራችሁን እጥፍ ያደርገዋል ወይስ አሥር እጥፍ ያባዛዋል?
   “አላህ የብናኝን ክብደት ያህል አይበደልም፤ መልካም ሥራ ብትኾንም ይደራርባታል፤ ከርሱም ዘንድ ታላቅን ምንዳ ይሰጣል።” (4፡40)
   “በመልካም ሥራ የመጣ ሰው ለእርሱ ዐሥር ብጤዎችዋ አሉት። በክፉ ሥራም የመጣ ሰው ብጤዋን እንጅ አይመነዳም። እነርሱም አይበደሉም።” (6፡160)
2. የእስልምናው አምላክ ሰማይና ምድርን በምን ቅደም ተከተል ነው የፈጠረው? ምድርን ከሰማይበፊት ወይንስ በኋላ ነው የፈጠረው?
   “እርሱ ያ በምድር ያለውን ሁሉ ለእናንተ የፈጠረ ነው። ከዚያም ወደ ሰማይ አሰበ፤ ሰባት ሰማያትም አደረጋቸው። እርሱም በነገሩ ሁሉ ዐዋቂ ነው።” (2፡29)
   ባፈጣጠር እናንተ ይበልጥ የበረታችሁ ናችሁን? ወይንስ ሰማይ? (አላህ) ገነባት። ከፍታዋን አጓነ፤ አስተካከላትም። ሌሊቷንም አጨለመ። ቀንዋንም ገለጸ። ምድርንም ከዚህ በኋላ ዘረጋት። (79፡27-30)
3. ቁር አን በሁለት ቦታዎች ላይ በመካ ያሉ ሰዎች አባቶቻቸው እንዲያምኑበት መጽሐፍና ነብይ እንዳልተላከላቸው ይነግረናል።

የሚያጠኑዋቸው የኾኑ መጽሐፍቶችንም ምንም አልሰጠናቸውም። ከአንተ በፊትም አስፈራሪ ነቢይን ወደእነርሱ አልላክንም። (ሱራ 34፡44)

አባቶቻቸው ያልተስፈራሩትን ሕዝቦች ልታስጠነቅቅበት (ተወረደ)። እነርሱ ዘንጊዎች ናቸውና። (ሱራ 36፡6)

በሌላ ቦታ ግን ቁርኣን ኢብራሂም እና እስማዒል የመካ ሰዎች ቅድመ አያቶች እንደነበሩ ሲናገር ካዕባን የገነቡ፣ የጸሎት ቦታን ያቋቋሙ፣ ስለ ህዝባቸው የጸለዩ እና ሁለቱም በቅዱሳት መጻሕፍት የተላኩ ነቢያት ናቸው ይላል። ( ቁርኣን 2፡127፣ 136፣ 87፡18-19)። ይህ ጉልህ የሆነ ተቃርኖ ነው።

በሃይማኖት ማስገደድ አለ ወይስ የለም?

“በሃይማኖት ማስገደድ የለም።” (2፡256)

“ከነዚያ መጽሐፍን ከተሰጡት ሰዎች፣ እነዚያን በአላህ በመጨረሻዉ ቀን የማያምኑትን፣ አላህና መልክተኛዉ እርም ያደረጉትንም እርም የማያደርጉትንና እዉነተኛዉንም ሃይማኖት የማይቀበሉትን እነርሱ የተዋረዱ ሆነዉ ግብርን በእጆቻቸው እስከሚሰጡ ድረስ ተዋጉዋቸው።” (9፡29)

በሙሐመድ ባለማመናቸው ምክንያት ሰዎችን መዋጋት ማስገደድ ነው። ሌላ የማስገደድ ዓይነት የሆነውን የእስልምናን የክህደት ሕግ መመልከት እንችላለን።[104] ስለዚህ አንዳንድ የቁርኣን ጥቅሶች ማስገደድ እንደሌለ ይናገራሉ ሌሎች ደግሞ ማስገደድን ያዛሉ። የተለያዩ ሙስሊሞች የተለያዩ ትዕዛዛትን በመከተላቸው ምክንያት በዓለም ላይ የተለያዩ ተፅዕኖዎችን እያመጡ የሚገኙ ትቅሶች አሉ። ይህ የግጭት ባሕርይ ከቁርኣን ከራሱ የመጣ ነው።

*ፈጣሪን ልዩ በሚያደርገው በዚያው መንገድ ኢየሱስ የመፍጠርን ተግባር ፈፅሟል፡-*

## ምክንያት 4፡ እርሱን የሚመስል ሱራ አምጡ

> "በእውነትም «(ሙሐመድ) ቀጣጠፈው» ይላሉን «ይህ ከሆነ መሰሉን (አንዲት) ሱራ አምጡ። ከአላህም ሌላ የቻላችሁትን ሁሉ (ረዳት) ጥሩ። እውነተኞች እንደሆናችሁ (ተጋግዛችሁ አምጡ)» በላቸው።" (10፡38)[105]

የዚህ ጥቅስ አውድ የመካ ሰዎች ሙሐመድ ቁርኣንን ራሱ ነው የፈጠረው ብለው አለመቀበላቸው ነው። ለዚህም ቁርኣን ተከታዩን ምላሽ ሰጥቷል፤ ማንም እርሱን የሚመስል ሱራ ወይም ምዕራፍ መፍጠር አይችልም። ይህ ቁርኣን ልዩ በመሆኑ ምክንያት ፈጣሪ ብቻ ነው ሊያመነጨው የሚችለው።[106] ስለዚህም ሙሐመድ ነቢይ ነው ይሉናል። በመጀመሪያ ሊታወቅ የሚገባው ነገር ይህ የነቢይነት ሀሳብ ቁርኣንን ብቻ መሰረት ያደረገ ሳይሆን ከአሪትም ጭምር መሰረት የሚያደርግ ነው። ይህ ማለት ቁርኣን ልዩ የሆነ መጽሐፍ አይደለም ማለት ነው። ይህንን ለሙስሊሞች ማሳየት ይጠቅማል። ሆኖም ግን በብዙሃኑ እስላማዊ አስተሳሰብ ቁርኣንን የሚመስል ማምጣት የማይቻል ነው ተብሎ ይታሰባል።አቡ አማር ያሲር ቃዲ የትክክለኛውን እስልምና መረዳት እንዲህ ያስቀምጣል፡-

> *በነቢዩ ዘመን አረቦች የንግግር ክህሎታቸው በጣም አድጎ ስለነበር ይህ ከጥበብ ሥራዎቻቸው ትልቅ ቦታ የተሰጠው ነበር። ግጥም ዋጋ የሚሰጡት ታላቅ ነገር ስለነበር እያንዳንዱ ጎሣ ይበልጥ የተዋበ ግጥም ማን ይፈጥራል በሚል እርስ በርሳቸው ይፎካከሩ ነበር። ዑካዝ በተባለ ዓመታዊ ክብረ በዓል ወቅት ከመላው አረብያ የተውጣጡ ገጣሚያን ለግጥሞቻቸው ታላቁን ክብር ለማግኘት አንድ ላይ*

---

104 አብዱላህ እንደዘገበው የአላህ መልእክተኛ እንዲህ ብለዋል "ከአላህ በስተቀር አምላክ እንደሌለና እኔም የአላህ መልእክተኛ መሆኔን የመሰከረ ሙስሊም ደም በሦስት ምክንያቶች እንጂ አይፈስም፡ ለግድያ ቂሳስ፣ ሕገ ወጥ ወሲብ የፈፀመ ያገባ ሰውና እስልምናን በመክዳት ከሙስሊሞች የተለየ ሰው።" *(ሳሂህ አል-ቡኻሪ ቅፅ 9፣ መጽሐፍ 83፣ ቁጥር 17)* እንዲሁም ቁርኣን 4፡89፤ Ahmad ibn Naqib al-Misri, Reliance of the Traveller – A Classic Manual of Islamic Sacred Law. f1.0-f1.5, pp. 108-110, o8.0-o87,
pp. 595-598.

105 በተጨማሪም 2:23, 11:13, 17:88, 52:33-34

106 ይህንን ብሂል ቁርኣን ለተውራትም ተናግሮታል።

ይሰበሰቡ ነበር። አሸናፊ ግጥምም እስከሚቀጥለው ውድድር ድረስ በካዕባ በር ላይ ይለጠፋል።

ከዚህ በወቅቱ ከነበረው ክብር የተነሳ ለነቢዩ የተሰጠው ተዓምር ተመሳሳይ ሁኔታ ነበረው፤ አላህ ቁርአኑን የገለጠው በአረብኛ እግጅግ ውብና ማራኪ ንግግር በማድረግ ሲሆን አረቦቹ ከፈጣሪያቸው ዘንድ የመጣ ንግግር እንደሆነ እርግጠኞች እንዲሆኑ ነው።[107]

ይህ ማለት ቁርኣን አረብኛ ቋንቋን ውብ በሆነ መንገድ ስለተጠቀመው ከፈጣሪ ዘንድ ነው የሚል ሙግት ቀርቧል። እንደገና ይህ ሙግት ኢ-አመክንዮአዊና ምንም ነገር ማረጋገጥ የማይችል ነው። በመጀመርያ ደረጃ አንድ ነገር በተዋበ ንግግር መቅረቡ የፈጣሪ ቃል እንዲሆን አያደርገውም። ዶ/ር አኒስ ሾሮሽ እንደተናገሩት ሁሉ የወንድ ጉልበቱ ጥበበኛነቱን አያሳይም የሴት ውበቷም ክብሯን አያመለክትም።[108] ሁሉም ባሕሎች ውብ የሚሏቸው ሥራዎች አሏቸው። የቻይና ውብ የሆኑ ግጥሞች አሉ፣ የዊልያም ሼክስፒር ጽሑፎች አሉ፣ ጥንታውያን ውብ አፈታሪኮች፣ ወዘተ.። እነዚህ ሁሉ ለየት ያሉ፣ ውብና ማራኪ ናቸው። ሙስሊሞች ለቁርኣን እንደሚያደርጉት ሁሉ ሰዎችም እነርሱን ለመሸምደድ ጊዜ ያጠፋሉ። ነገር ግን ይህ ውበት የፈጣሪ ቃል አያደርጋቸውም። ስለዚህ ልዩና ውብ መሆን አንድ ነገር ከፈጣሪ ዘንድ ለመሆኑ ማስረጃ ሊሆን አይችልም።

ሁለተኛ ይህ በጣም ግላዊ የሆነ መመዘኛ ነው። መለኮታዊ ውበት ያለውን ንግግር ለይቶ የሚወስነው ማን ነው? ሙስሊሞች ቁርኣን ተዓምራዊ ውበት እንዳለው ያምኑ ይሆናል ነገር ግን ሁሉም ሰው እንደርሱ አያምንም።

ሦስተኛ ሊቃውንት ቁር አን ልዩ የሆነ መጽሐፍ ነው ብለው አያምኑም።

ቁርኣን ያልተሟሉና የተቆራረጡ ያለ ማብራርያ ልንረዳቸው የማንችላቸውን ዓረፍተ ነገሮች በውስጡ ይዟል። የውጪ ቃላት፣ ያልተለመዱ የአረብኛ ቃላት፣ እንዲሁም ከተለመሰው አጠቃቀም ውጪ የሆኑ ቃላትን ሸክፏል። ቁጥርንና ፆታን ያላገናዘቡ የተሳቢዎችና ግሦች አጠቃቀም፣ አንዳንዴ ማጣቀሻ አልባና ኢ-አመክንዮአዊ የሆኑ የሰዋሰው ሕግጋትን ያልጠበቁ የተውላጠ ስሞች፣ በግጥሙ ውስጥ ከሚገኙ ሐሳቦች የራቁ ቤት ለመምታት ብቻ ታስበው የገቡ ሐሳቦችን በውስጡ እናገኛለን። እነዚህና የመሳሰሉት የቋንቋ ግድፈቶች የቁርኣንን ውብ ንግግር ለማይቀበሉ ተቺዎች በር ከፍተዋል። ችግሩ የጥሩ ሙስሊሞችን አእምሮም ጭምር የሚያስጨንቅ ነው። ሐታቾች ማብራርያዎችን እንዲፈልጉ ያደረገ ሲሆን

---

107 Abu Ammaar Yasir Qadhi, An Introduction to the Sciences of the Qur'aan, AlHidaayah Publishing: U.K., 1999, p. 267

108 Anis A. Shorrosh, Islam Revealed - A Christian Arab's View of Islam, Nashville, U.S.A.: Thomas Nelson Publishers, 1988, p. 192.

ምናልባትም የንባብ ልዩነቶች እንዲፈጠሩ ካደረጉ ምክንያቶች መካከል አንዱ ነው።
[109]

አራተኛ ሙሐመድን ሲቃወሙ የነበሩ የመካ ሰዎች ቁርኣንን ማስመሰል እንደሚችሉ ተናግረዋል።

> "አንቀጾቻችንም በነሱ ላይ በተነበቡ ጊዜ ፡- በእርግጥ ሰምተናል፤ በሻን ኖሮ የዚህን ብጤ ባልን ነበር፤ ይህ የመጀመሪያዎቹ ሰዎች ጽሁፍ ተረቶች እንጂ ሌላ አይደለም ይላሉ።" (8፡31)

የመካ ሰዎች በቁርኣን ልዕለ ተፈጥሯዊ ውበት ምክንያት አልተቀበሉትም። 10,000 ሠራዊት ይዞ ስለመጣባቸው ነበር የተቀበሉት። የቁርኣን ውበት ሳይሆን የሙሐመድ ወታደራዊ ኃይል ነበር እንዲቀበሉት ያስገደዳቸው።

አምስተኛ ሙሰይለማ የተባለ በሙሐመድ ዘመን ነቢይ ነኝ ብሎ ተነስቶ የነበረ ሰው የራሱን አንቀፆች በቁርኣን ስልት ሲናገራቸው ነበር።

> ከዚያም ግጥሞችን በሰጅዕ በመናገር ቁርኣንን ማስመሰል ጀመረ።[110]

ስለዚህ ሌሎች ሰዎች ቁርኣንን የሚመስል ነገር ፈጥረዋል።

> እንዲሁም አብደላህ ኢብኑ ሰዕድ ኢብኑ አቢ ሰርህ በሰዎች አፈጣጠር ድንቅነት መገረሙን "ከፈጣሪዎች ሁሉ የላቀ የሆነው አላህ የተባረከ ይሁን" በማለት ተናገረ። የአላህ መልእክተኛ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) እንዲህ ብለዋል፡- "ይህ [የአብዱላህ የመጨረሻ ቃል] ወደኔ የተወረደው ነው።

ስድስተኛ ሙስሊሞች ቁርኣንን የሚመስል ለማምጣት አይሞክሩም፣ የሚሞክሩትንም ይቀጣሉ። ሙስሊሞች እነዚህን መመዘኛዎች ከልባቸው ከሆነ የሚያቀርቡት ሰዎች ቁርኣንን የሚመስል ለማምጣት እንዲሞክሩ ማበረታታት እናየከሽልማት ገንዘብ አዘጋጅተው ውድድሮች ይኖሩ ነበር። በዚህ መንገድ ማንም ቁርኣንን ሊያስመስለው እንደማይችል ይረጋገጥ ነበር። ሆኖም ግን ሙስሊምሞች ተቃራኒውን ያደርጉታል እና የሚሞክሩትን ይቀጣሉ።

በመጨረሻም አንዳንድ ጊዜ ሙስሊሞች ሙሐመድ ፊደል ያልቆጠረ ስለነበረ ቁርኣንን የመሰለ ውብ ንግግር ሊፈጥር አይችልም ብለው ሲናገሩ ይደመጣሉ። ነገር ግን ፊደል አለመቁጠር አንድ ሰው ችሎታ እንዳይኖረው አያደርግም። አብዛኞቹ ጥንታውያን ባሕሎች የሥነ ቃል ባሕሎች ቢሆኑም ሰዎች ግን ትልልቅ ችሎታ ነበራቸው። ሙሐመድ የሚጽፉለት

---

109 Ali Dashti, 23 Years - A Study of the Prophetic Career of Mohammad, Mazda Publishers, California, 1994, pp. 48-49.
110 Ibn Ishaq, Sirat Rasul Allah, p. 637

ጸሐፊያን ስለነበሩት ተሰጥዖ የነበረው ጸሐፍቱ ንግግሩን ይመዘግቡለት የነበረ ገጣሚ ሊሆን ይችላል።

## ምክንያት 5፡ ቁርአን የቀደሙትን መገለጦች ያረጋግጣል

> "እላንተ መጽሐፉ የተሰጣችሁ ሆይ! ፊቶችን ሳናብስና በጀርባዎች ላይ ሳንመልሳቸው፣ ወይም የሰንበትን ባለቤቶች (ያፈረሱትን) እንደረገምን ሳንረግማቸው በፊት ከናንተ ጋር ያለውን የሚያረጋግጥ ኾኖ ባወረድነው (ቁርአን) እመኑ፣ የአላህም ትዕዛዝ ተፈፃሚ ነው።" (ቁርአን 4፡47)[111]

በዚህ ጥቅስ ውስጥ ቁርአን መጽሐፍ ቅዱስን የበላይ አድርጎ ይቀበለዋል። ክርስቲያኖችንና አይሁድን የመጽሐፉ ሰዎች በማለት በመጥራት ቁርአን መጽሐፍ ቅዱስን ስለሚያረጋግጥ እንዲቀበሉት ያበረታታቸዋል። ይህ ማለት በቁርአን መሠረት ክርስቲያኖች የሙሐመድን ነቢይነት የሚያውቁበት አንዱ መንገድ እርሱ የሚናገረው የመጽሐፍ ቅዱስን ትምሕርት የሚያጸድቅ በመሆኑ ነው።

ከቀደሙት አራት ሙግቶች በተለየ ሁኔታ ይህ ሙግት ምክንያታዊና በትክክል ሊመዘን የሚችል መሆኑን እንቀበላለን። ሙሐመድ የቀደሙትን ነቢያት መልእክት አረጋግጦ ከነበረ እርሱን ለመቀበል ትክክለኛ መነሻ ነው። ሙሐመድ የጽሐፍ ቅዱስን መልእክት ማረጋገጥ አለማረጋገጡን ለማየት ሦስት ጉዳዮችን እንመለከታለን።

### 1. ሙሐመድና ነቢያት

መጽሐፍ ቅዱስ የአንድ ሰው ሥራ ሳይሆን የብዙ ነቢያት መጻሕፍት ስብስብ፣ ከተለያዩ ቦታዎች፣ በተለያዩ ቋንቋዎች፣ በ1500 ዓመታት ውስጥ የተዘጋጀ ነው። እንዲህ ብዝሐነት የሚታይበት መጽሐፍ ቢሆንም በምስሉ ላይ እንደሚታየው አስደናቂ አንድነት አለው።

ይህ ምስል የነቢያትን ዋና አስተምሕሮዎች የሚያሳይ ነው። እነዚህ መሠረታዊ አስተምሕሮዎች ናቸው። ሆኖም እንደምትመለከቱት ሙሐመድ ሁሉንም ክዷቸዋል። ስለዚህ በአጠቃላይ መልእክት ረገድ ሙሐመድ መጽሐፍ ቅዱስን አላረጋገጠም።

### 2. ሙሐመድ ስለ ኢየሱስ ያስተማረው

ሙሐመድ በቁርአን ውስጥ ብዙ ጊዜ ስለ ኢየሱስ አስተምሯል። ሆኖም መልእክቱ በምንም መንገድ የመጽሐፍ ቅዱስን የሚያረጋግጥ አይደለም። እነዚህ ሦስት ምሳሌዎች ውሰዱ።

---

111 እንዲሁም ቁርአን 46፡12

### ሀ. በቁርኣን ውስጥ የኢየሱስ እናት የአሮን እህት የኢምራን ልጅ ማርያም ናት።

ኢምራን የኢንበረም የአረብኛ አጠራር ሲሆን በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የጌታ እናት ማርያም የሙሴና የአሮን እህት የእንበረን ልጅ ነቢይቱ ማርያም በተጠራችበት ስም ተጠርታለች።

> "የእንበረም ሚስት ስም ዮካብድ ነበረ። እርስዋ በግብፅ ከሌዊ የተወለደች የሌዊ ልጅ ነበረች፤ ለእንበረምም አሮንንና ሙሴን እኅታቸውንም ማርያምን ወለደችለት። " (ዘኍ. 26፡59)

ነገር ግን በቁርኣን ውስጥ የአሮን እህት ማርያምና የኢሱስ እናት ማርያም አንድ ሰው ናቸው።[112]

> በርሱም የተሸከመቺዉ ኾና ወደ ዘመዶችዋ መጣች ፡- መርየም ሆይ ከባድን ነገር በእርግጥ ሠራሽ አሏት። የሃሩን እኅት ሆይ አባትሽ መጥፎ ሰዉ አልነበረም፤ እናትሽም አመንዝራ አልነበረችም አሉዋት ... ይህ የመርየም ልጅ ዒሳ ነው፤ ያ በርሱ የሚጠራጠሩበት እዉነተኛ ቃል ነዉ።" (19፡27-34)
>
> "ከችሮታችንም ወንድሙን ሃሩንን ነቢይ አድርገን ሰጠነዉ።" (19፡53)
>
> "የዒምራንን[113] ልጅ መርየምንም ያቺን ብልቷን የጠበቀችውን (ምሳሌ አደረገ)፤ በርሱም ውስጥ ከመንፈሳችን ነፍፉን እጌታዋ ቃላትና በመጽሐፍቱም አረጋገጠች፤ ከታዛዦቹም ነበረች።" (66፡12)

ሁለቱ ማርያሞች በ1500 ዓመታት ልዩነት የኖሩ ናቸው። ሁለቱም ተመሳሳይ ስም ስላላቸው ሙሐመድ ደባለቃቸው። ስለዚህ ይህ ሙሐመድ የመጽሐፍ ቅዱስን ታሪክም ሆነ የጊዜ ቅደም ተከተል አለማወቁን ስለሚያሳይ መጽሐፍ ቅዱስን ላለማረጋገጡ ማሳያ ነው።[114]

---

112 ሙሉ ታሪኩን ለማንበብ ቁርኣን 3፡35-51 ተመልከቱ

113 ኢምራን የኢንበረም የአረብኛ አጠራር ነው።

114 ይህ ስህተት ከባድ ከመሆኑ የተነሳ ሙስሊሞች ለምን ስህተት መስሎ እንደታየ ለማብራራት ሦስት ማብራርያዎችን ሰጥተዋል።

ሀ. "የአሮን እህት" ቃል በቃል መወሰድ የሌለበት የአረብኛ ዘይቤ ነው። ይህ አያስኬድም ምክንያቱም በዚያን ዘመን የነበሩት አረቦች ቃል በቃል ነበር የተረዱት (ሳሂህ ሙስሊም መጽሐፍ 25፣ ቁጥር 5326)። እንዲሁም ይህ ማብራርያ ለምን የኢምራን ልጅ ተብላ እንደተጠራች አያብራራም።

ለ. "የአሮን እህት" ነቢያት ሁሉ ወንድማማቾችና እህትማማቾች መሆናቸውን የሚያመለክት ዘይቤያዊ ንግግር ነው። አሁንም ይህ ማብራርያ ውድቅ ነው ምክንያቱም በቁርኣን ውስጥ የተጠቀሰው ቤተሰባዊ ትስስር ግልፅ ነውና (ቁርኣን 3፡33)፤ እህትና ልጅ ተብላ በሁለት ቤተሰባዊ ትስስር ተገልፃለች።

ሐ. የኢየሱስ እናት ማርያምና የአሮን እህት ማርያም በ1500 ዓመታት የተለያዩ ቤተሰብ አባላት ናቸው። ስለዚህ በኢምራን ስም የሚጠራ አንድ ቤተሰብ ሳይሆን ሁለት ቤተሰብ ነው ያለው። ይህ የሚቻል ቢሆንም ችግሩን ግን ሊፈታ አይችልም ምክንያቱም በመጽሐፍ ቅዱስም ሆነ ጥንታውያን በሆኑት የአይሁድ ድርሳናት መሠረት

### ለ. ኢየሱስ ጂሃዳዊ ነበር

ቁርኣን ኢየሱስ ወንጌልን[115] እንዳስተማረ ይናገርና አንዳንድ የወንጌል ዘቶችን እንደሚከተለው ያብራራል፡-

> “አላህ ከምእምናን፣ ነፍሶቻቸዉንና ገንዘቦቻቸዉን፣ ገነት ለነሱ ብቻ ያላቸው በመሆን ገዛቸው፤ በአላህ መንገድ ላይ ይጋደላሉ፤ ይገድላሉም፤ ይገደላሉም፤ በተዉራት፣ በኢንጅልና በቁርኣንም፣ (የተነገረውን) ተስፋ በርሱ ላይ አረጋገጠ፤ ከአላህም የበለጠ በኪዳኑ የሚሞላ ማነዉ? በዚያም በርሱ በተሻሻጣችሁበት ሽያጫችሁ ተደሰቱ፤ ይህም እርሱ ታላቅ ዕድል ነው።” (ቁርኣን 9፡111)

ይህ ጥቅስ እንደሚናገረው በውጊያ ውስጥ የሚሞቱትን ሰዎች ፈጣሪ ይክሳቸዋል፤ ይህ መልእክት ደግሞ የቶራህ፣ የወንጌልና የቁርኣን መልእክት ነው። ይህ ማለት ኢየሱስ እንደ ሙሐመድ ሁሉ ጂሃድን አስተምሯል ማለት ነው። ይህ በቀላሉ ሐሰትና ትርጉም አልባ ሊባል የሚችል ነው። ኢየሱስ ሰይፍን መጠቀምን ታቃውሟ፤[116] ደቀ መዛሙርቱም እንደ ወራሪ ሠራዊት አልተሰራጩም። መጽሐፍ ቅዱስ ኢየሱስን የእግዚአብሔር ልጅ ብሎ የሚጠራውን እንዴት እንደሆነ ልንመለከት እንችላለን ነገር ግን ሙሐመድ ይህን ይክዳል ነገር ግን ነጥቡ ግልጽ ነው። ሙሐመድ በምንም መንገድ የመጽሐፍ ቅዱስን መልእክት አላረጋገጠም።

## ምክንያት 6፡ ሙሐመድ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ተተንዮአል

> “ለነዚያ ያንን እነሱ ዘንድ በተውራትና በኢንጂል ተጽፎ የሚያገኙትን የማይጽፍና የማያነብ ነብይ የሆነውን መልክተኛ የሚከተሉ ለሆኑት (በእርግጥ እጽፋታለሁ)፤ በበጎ ሥራ ያዛቸዋል፤ ከክፉም ነገር ይከለክላቸዋል፤ መልካም ነገሮችንም ለነርሱ ይፈቅድላቸዋል፤ መጥፎ ነገሮችም በርሱ ላይ እርም ያደርግባቸዋል። ከነርሱም ላይ ሸክማቸውንና እነዚያንም በነሱ ላይ የነበሩትን እንዛዝላዎች (ከባድ ሕግጋቶች) በርሱ ያመኑ ያከበሩትም የረዱትም ያንንም ከርሱ ጋር የተወረደውን ብርሃን የተከተሉ እነዚያ እነሱ የሚድኑ ናቸው።” (ቁርኣን 7፡157)

> “የመርየም ልጅ ዒሳም የ እሥራኤል ልጆች ሆይ እኔ ከተውራት በፊቴ ያለውን የማረጋግጥና ከኔ በኋላ በሚመጣው መልክተኛ ስሙ አሕመድ በሆነው የማበስር

---

እንበረም (ኢምራን) የሚባል አባትና አሮን (ሀሩን) የሚባል ወንድም እንደነበራት የተነገረላት ብቸኛ ሴት ነቢይቱ ማርያም ናት። ከብዙ ዘመናት በኋላ አንድ ሰው በመምጣት “የእንበረም ልጅና የአሮን እህት” ስለሆነችው ማርያም ቢናገር የጠቀሳት ማርያም በነዚህ ምንጮች ውስጥ ከተጠቀሰችው የተለየች እንደሆነች ማሰብ የማይመስል ነው።

115 ቁርኣን 5፡46

116 ማቴ. 26:52፣ ዮሐ. 18:36

ስሆን ወደናንተ (የተላክሁ) የአላህ መልክተኛ ነኝ ባለ ጊዜ (አስታውስ)፤በግልጽ ታምራቶች በመጣቸውም ጊዜ ይህ ግልፅ ድግምት ነው አሉ።" (ቁርኣን 61፡6)

እነዚህ ጥቅሶች በድጋሜ መጽሐፍ ቅዱስን እንደ የበላይ ሥልጣን ይጠቅሳሉ። ሙሐመድ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ስለተጠቀሰ አይሁድና ክርስቲያኖች እውነተኛ ነቢይ መሆኑን ያውቃሉ ይላሉ። አባባሉ አመክንዮአዊና ሊመዘኑ የሚችሉ ናቸው። ሙሐመድ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከተተነበየ ክርስቲያኖች ሊቀበሉት ይገባል። ካልተተነበየ ግን ይህ ሙግት ሐሰት በመሆኑ ሙሐመድ የሐሰት ነቢይ ነው።

ሙሐመድ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ተተንብዮአል መባሉ ክርስቲያኖችን ሊያስገርም ይችላል ነገር ግን ቁርኣንና ሙስሊሞች የሚሉት ይህንን ነው። ቁርኣን የትኛው የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ ይህንን እንደሚል ስለማይጠቅስ ሙስሊም መሪዎች መጽሐፍ ቅዱስን በማንበብ ማግኘት አስፈልጓቸዋል። ሙሐመድ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እንደተተነበየ ለማመልከት ብዙ ጥቅሶችንም ይጠቅሳሉ። ትልቅ ቦታ የሚሰጧቸውን ሁለቱን እንመለከታለን።[117]

## ዘዳግም 18፡18 - ሙሴን የሚመስለው ነቢይ

"ከወንድሞቻቸው መካከል እንደ አንተ ያለ ነቢይ አስነሣላቸዋለሁ ቃሌንም በአፉ አደርጋለሁ፥ ያዘዝሁትንም ቃል ሁሉ ይነግራቸዋል።" (ዘዳ. 18፡18)

ሙስሊሞች ይህ ጥቅስ ሙሐመድን እንደሚያመለክት ይናገራሉ። ሙሐመድ የእስማኤል ዘር በመሆኑ በዚህ ቦታ *ወንድሞች* የተባሉት እስማኤላውያን ናቸው ይላሉ። ስለዚህ ዘዳግም 18፡18 እንደ ሙሴ ላለ የአረብ ነቢይ የተነገረ ነው። ሆኖም ይህ ጥቅስ በሚከተሉት ምክንያቶች ለሙሐመድ የተነገረ አይደለም፡-

መጀመርያ እነዚህን ጥቅሶች በአውድ ውስጥ ማንበብ ያስፈልገናል። ዘዳግም 17-18 ስለ እሥራኤል መሪዎች ይናገራል። ምዕራፉ ካህናትን፣ ፈራጆችን፣ ነገሥታትንና ነቢያትን የሚጠቅስ ሲሆን ከወንድሞቻቸው ይወጣሉ ይላል።[118] ወንድሞች የሚለው ቃል ወንድማማች የሆኑትን የእሥራኤል ነገዶች ለማመልከት የዋለ ነው፤ አውዱ የሚያሳየው ያንን ነው። ስለዚህ ዘዳግም 18፡18 የሚናገረው ስለ እሥራኤላዊ ነቢይ እንጂ ከሌላ ሕዝብ ስለሆነ ነቢይ አይደለም።

ሁለተኛ እንደ ሙሴ ያለ ነቢይ ለመሆን በመሠረታዊ አስተምህሮዎች ላይ ከሙሴ ጋር መስማማት ያስፈልጋል። ሙሐመድ ከሙሴ ጋር እንዳይስማማ ለማመልከት ሳጥን 1ን ማየት እንችላለን ነገር ግን በአምልኮ ላይ ማተኮር እፈልጋለሁ። ሙሴ በአምልኮተ እግዚአብሔር

---

117 ሌሎች ጥቅሶች እዚህ ተብራርተዋል answering-islam.org/Green/mhd_bible.htm

118 ዘዳ. 17:15, 17:20, 18:2

ወቅት የተለዩ ድንጋዮችን መጠቀምን አጥብቆ ከልክሏል። የአምልኮተ ጣዖት መገለጫ ናቸውና፡-

ሦስተኛ እንደ ሙሴ ያለ ነቢይ በእግዚአብሔር ስም ሐሰተኛ የሆነ ነገር መናገር የለበትም።

> "ነገር ግን ይናገር ዘንድ ያላዘዝሁትን በስሜ በድፍረት የሚናገር ወይም በሌላ አማልክት ስም የሚናገር ነቢይ፥ እርሱ ይገደል።" (ዘዳግም 18፡20)

ሙሐመድ ግን ይህንን አድርጓል።

> አላህ ያልተናገረውን እንደተናገረ አስመስዬ ተናግሬያለሁ።[119]

> አላህ ያልተናገረውን ፈጥሬ በመናገር የእርሱ ያልሆነውን ቃል የእርሱ በማስመሰል ተናግሬያለሁ።[120]

ስለዚህ ሙሐመድ እንደ ሙሴ ያለ ነቢይ አይደለም።

አራተኛ እግዚአብሔር ሙሴን በብዙ ተዓምራት አረጋግጦለታል። ሙሐመድ ግን ምንም አይነት ተዓምራት አላደረገም።

> እውነቱም ከእኛ ዘንድ በመጣላቸው ጊዜ «ለሙሳ የተሰጠው ብጤ አይስሰጠውም ኖሯልን» አሉ። «ከዚህ በፊት ሙሳ በተሰጠው አልካዱምን የተረዳዱ ሁለት ድግምቶች ናቸው» አሉ። «እኛ በሁሉም ከሓዲዎች ነንም» አሉ። (ሱራ 28፡48)

አምስተኛ አሁንም በዘዳግም 18፡20 መሠረት እንደ ሙሴ ያለ ነቢይ በያሕዌ ስም እንጂ በሌሎች አማልክት ስም መናገር የለበትም። ሙሐመድ በያሕዌ ስም አልተናገረም ነገር ግን በአላህ ስም ነው የተናገረው። *አላህ* የሚለው ቃል በአረብኛ አምላክ ለሚለው አቻ አይደለም። አምላክ ለሚለው የአረብኛ አቻ *ኢላህ* ነው። ያህዌ በመጽሐፍ ቅዱስ የአምላክ የተፀውዖ ስም እንደሆነው ሁሉ አላህም በእስልምና የአምላክ የተፀውዖ ስም እንደሆነ ይታሰባል። ስለዚህ ሙሐመድ በሌላ አምላክ ስም ስለተናገረ እውነተና የፈጣሪ ነቢይ ሊሆን አይችልም።

---

119 Ibn Sa'd, Kitab Al-Tabaqat Al-Kabir, (translator: S. Moinul Haq) New Delhi: Kitab
Bhavan, vol. 1, p. 237

120 Al-Tabari, The History of al-Tabari, vol. 6, "Muhammad at Mecca" (trans. W. Montgomery Watt & M.V. McDonald), Albany, N.Y.: State University of New York Press,
1988, p. 111

## ዮሐንስ 14፡16 - አፅናኙ

> “ብትወዱኝ ትእዛዜን ጠብቁ። እኔም አብን እለምናለሁ ለዘላለምም ከእናንተ ጋር እንዲኖር ሌላ አጽናኝ ይሰጣችኋል” (ዮሐንስ 14፡16)

ቁርአን ይህንን ጥቅስ በመጥቀስ ስለ ሙሐመድ የተነገረ ነው አይልም ነገር ግን ሙስሊም መሪዎች ኢየሱስ ስለ አፅናኙ ሲናገር ስለ ኢየሱስ መናገሩ ነው ይላሉ። ይህ ጥቅስ ሙሐመድን ያመለክታልን? በፍፁም። ምክንያቶቹ ደግሞ የሚከተሉት ናቸው፤ አንደኛ ጥቅስ መነበብ ያለበት በአውድ ውስጥ ነው። ይህንን ጥቅስ በአውድ ውስጥ ካነበብን ኢየሱስ አፅናኙን መንፈስ ቅዱስ ብሎታል።

> “ከእናንተ ዘንድ ስኖር ይህን ነግሬአችኋለሁ፤ አብ በስሜ የሚልከው ግን መንፈስ ቅዱስ የሆነው አጽናኝ እርሱ ሁሉን ያስተምራችኋል እኔም የነገርኋችሁን ሁሉ ያሳስባችኋል።” (ዮሐ. 14፡25-26)

ስለዚህ ኢየሱስ ዮሐንስ 14፡16 ላይ ስለ ሙሐመድ ሳይሆን ስለ መንፈስ ቅዱስ ነው እየተናገረ ያለው።

ሁለተኛ ዮሐንስ 14፡16-17 ኢየሱስ እየተናገራቸው የነበሩት ሐዋርያቱ መንፈስ ቅዱስን ይቀበላሉ፤ ይህ ደግሞ በትክክል ሆኗል። መጥምቁ ዮሐንስም ኢየሱስ ሲመጣ መንፈስ ቅዱስን እንደሚሰት ተናግሯል።

> “ኢየሱስም ዳግመኛ፦ ሰላም ለእናንተ ይሁን፤ አብ እንደ ላከኝ እኔ ደግሞ እልካችኋለሁ አላቸው። ይህንም ብሎ እፍ አለባቸውና፦ መንፈስ ቅዱስን ተቀበሉ። ኃጢአታቸውን ይቅር ያላችኋቸው ሁሉ ይቀርላቸዋል፤ የያዛችሁባቸው ተይዞባቸዋል አላቸው።” (ዮሐ. 20፡21-22)

መንፈስ ቅዱስም አስተምሯቸዋል፣ ኃይልን ሰጥቷቸዋል፣ ሞልቷቸዋል።[121] ኢየሱስ መንፈስ ቅዱስን ሲሰጥ የእግዚአብሔር ነቢያት አስቀድመው የተናገሩትን እየፈፀመ ነበር፦

> “መንፈሴንም በውስጣችሁ አኖራለሁ በትእዛዜም አስሄዳችኋለሁ፥ ፍርዴንም ትጠብቃላችሁ ታደርጉትማላችሁ።” (ሕዝ. 36፡27)

> “ከዚህም በኋላ እንዲህ ይሆናል፤ መንፈሴን በሥጋ ለባሽ ሁሉ ላይ አፈስሳለሁ፤ ወንዶችና ሴቶች ልጆቻችሁም ትንቢት ይናገራሉ፥ ሽማግሌዎቻችሁም ሕልምን ያልማሉ፥ ጐበዞቻችሁም ራእይ ያያሉ፤ ደግሞም በዚያ ወራት በወንዶችና በሴቶች ባሪያዎች ላይ መንፈሴን አፈስሳለሁ።” (ኢዩ. 2፡28-29)

---

121 ሐዋ. 1:2, 8, 2:1-33, 4:31

| የአፅናኙ ገለፃ በዮሐንስ 14-16 | የቅዱሱ መንፈስ ገለፃ በቁርኣን | የሙሐመድ ገለፃ በቁርኣን |
|---|---|---|
| መንፈስ ቅዱስ ተብሏል ዮሐ. 14፡26 | ቅዱሱ መንፈስ ተብሏል 2፡87፣ 2፡253፣ 5፡110፣ 16፡102 | አይ |
| የእውነት መንፈስ ዮሐ. 14፡17፣ 16፡13 | የእውነት መንፈስ ነው 1፡102፣ 26፡193 | አይ |
| ለሐዋርያቱ መገለጥን ያመጣላቸዋል ዮሐ. 16፡13 | ለሐዋርያቱ መገለጥን ያመጣላቸዋል 16፡102፣ 26፡193፣ 97፡4 | አይ |
| በውስጣችሁ ይኖራል ዮሐ. 14፡17 | በውስጣችሁ ሊሆን ይችላል 15፡29፣ 58፡22 | አይ |
| የሰዎችን ልብ ለእግዚአብሔር ይከፍታል ዮሐ. 16፡8-11 | የሰዎችን ልብ ለእግዚአብሔር ይከፍታል 58፡22 | አይ |
| በእግዚአብሔርና በኢየሱስ ተልኳል ዮሐ. 14፡26፣ 15፡26፣ 16፡7 | በአላህና በኢየሱስ ተልኳል 16፡102፣ 15፡29፣ 5፡110 | አይ |

ኢየሱስ መንፈስ ቅዱስን በመስጠት የነቢያትን ትንቢት እየፈፀመ ነበር። ይህ የሙሐመድን መምጣት እንደሚያመለክት መናገር ትርጉም አይሰጥም።

በመጨረሻም ቁርኣን ስለ መንፈስ ቅዱስ የሚናገር ሲሆን አስገራሚው ነገር አገላለፁ ዮሐንስ 14-16 ላይ ከሚገኘው ጋር ተመሳሳይ ነው። ሳጥን 2ን ተመልከቱ።

ቁርኣን ሙሐመድን መንፈስ ቅዱስ ብሎ አይገልፀውም። መንፈስ ቅዱስ ብሎም አልጠራውም። በቁርኣን መሠረት መንፈስ ቅዱስ ከሙሐመድ የተለየ ማንነት ያለው አካል ነው። ይህ ማለት በቁርኣን መሠረት እንኳ ኢየሱስ እየተናገረ የነበረው ስለ መንፈስ ቅዱስ ነበር ማለት ነው። ከቁርኣን በመነሳት ኢየሱስ ስለ ሙሐመድ እየተናገረ እንዳለ ለማሰብ የሚያበቃ ምክንያት የለም።

በዚህ ክፍል ሙሐመድ በመጽሐፍ ቅዱስ ተተንብዮአል የሚለውን ሙግት ተመልክተናል። ሙስሊም መሪዎች በተደጋጋሚ የሚያነሷቸውን ሁለት ጥቅሶች መርምረን ስለ ሙሐመድ

ምንም ነገር እንማይናገሩ አረጋግጠናል። ስለዚህ መጽሐፍ ቅዱስ የሙሐመድን እንደ እውነተኛ ነቢይ መምጣት አስመልክቶ ምንም ነገር አይናገርም።

## ክፍል 2 በሙስሊሞች የሚቀርቡ ሌሎች ማስረጃዎች

ባለፈው ክፍል ቁር አን ሙሐመድ ነቢይ ነው ለሚለው ትምህርቱ የሚያቀርባቸውን ማስረጃዎች ተመልክተን ነበር። በዚህ ክፍል ደግሞ በቁር አን የማይገኙ ነገር ግን ሙስሊሞች ለሙሐመድ ነብይነይ የሚያቀርቧቸርውን ማስረጃዎች እንመለከታለን።

የመጀመሪያው "ቁርአን በሙሐመድ ዘመን ሊታወቁ የማይችሉ ሳይንሳዊ ተዓምራትን በውስጡ ይዟል፡ ይህም ከፈጣሪ መሆኑን ያረጋግጣል" የሚል ሙግት ነው። ከእነዚህ ሙግቶች ይበልጥ ታዋቂው ስነ-ጽንስን በተመለከተ ቁርአን የሚናገረው ነው።

> ቁር አን ስለ ሰው ልጅ የጽንስ እድገት በጥልቀት ይናገራል። እነዚህ ጠለቅ ያሉ እውነታዎች በሙሐመድ ዘመን የማይታወቁ ነበሩ።[122]

ይህ ሙግት እጅግ አሳፋሪ ሙግት ነው። ቁርአን በቀላሉ ሊታወቅ የሚችልና በዘመኑ ይታመን የነበረን ነገር ነው የያዘው። ጽንስን በተመለከተ በውርጃ፣ በእንሣት እርድ ጊዜና በተለያዩ ምክንያቶች ሰዎች ተመልክተው ሊገነዘቡት የሚችሉት ነገር ነው።

> እኛ ጠየቅነው "የአላህ መልእክተኛ ሆይ ግመልን፣ ላምንና በግን ስናርድ በማህፀኗ ውስጥ ፅንስ ብናገኝ እንጣለው ወይስ እንብላው?" እርሱም "ከፈለጋችሁ ብሉት" አለ። (ሱነን አቡ-ዳውድ 2827፤ መጽሐፍ 15፣ ቁጥር 2821)

ቁርአን ደግሞ የፅንስ እድገትን ሲገልጽ አጥንቶች በጽንሱ ውስጥ እንደሚበቅሉ ሳይሆን ሥጋ እንደሚለብሱ የተሳሳተ ነገር ይናገራል።

> ከዚያም ጠብታዋን (በአርባ ቀን) የረጋ ደም አድርገን ፈጠርን። የረጋውንም ደም ቁራጭ ሥጋ አድርገን ፈጠርን። ቁራጯንም ሥጋ አጥንቶች አድርገን ፈጠርን። አጥንቶቹንም ሥጋን አለበስናቸው። ከዚያም (ነፍስን በመዝራት) ሌላ ፍጥረትን አድርገን አስገኘነው። ከሰዓሊዎችም ሁሉ በላጭ የሆነው አላህ ላቀ። (ሱራ 23፡14)

ሌላው የሚጠቀሰው ማስረጃ ቁርአን አሃዛዊ ተአምራት አለው የሚል ሲሆን ይህም ከፈጣሪ መሆኑን ያረጋግጣል ይላሉ። ለምሳሌ 19 ቁጥር በተደጋጋሚ የሚጠቀስ የተዓምር አይነት ነው። ሱራ 96 በውስጡ 304 የአረብኛ ፊደላትን የያዘ ሲሆን 304 ደግሞ 19 x 16.24 ብዜት ነው። ይህ ሁሉ ሙከራ ቁርአን ከፈጣሪ ዘንድ መሆኑን ለማረጋገጥ ነው።

---

[122] 23. The Qur'an - The Final Revelation to Mankind, Learn the Basics, islamicpamphlets.com/the-quran-the-final-revelation-to-mankind (Accessed 19 March, 2024)

እነዚህ አሃዛዊ ክርክሮች በጣም የተመረጡ ናቸው። ሁልጊዜ ሲፈተሹ የተሳሳቱ ናቸው። ነገር ግን ሰዎች ሙስሊሞች በእነሱ ያምኑባቸዋል። በቁርአን ውስጥ የ 19 ተአምራዊ ብዜቶች ቢኖሩም እንኳን ይህ ከፈጣሪ የመጣ መሆኑን አያረጋግጥም። ከዲያብሎስም ሊመጣ ይችላል። በአጠቃላይ 'የቁርዓን አሃዛዊ ተአምራት' ምንም አያረጋግጡም።

## ክፍል 2፡ ሙሐመድን በመጽሐፍ ቅዱስ መሠረት መመዘን

በመጀመርያው ክፍል የሙሐመድን ቃል በመውሰድ ለእውነተኛ ነቢይነቱ የሚያቀርባቸውን ማስረጃዎች አጢነናል። በዚህ ክፍል ደግሞ በመጽሐፍ ቅዱሳዊ መስፈርቶች መሠረት እንመዝነዋለን። መጽሐፍ ቅዱስ ነቢይ ነኝ የሚሉትን ሰዎች በተመለተ ዝንጉዎች እንዳንሆን ያሳስበናል። እንድንፈትናቸው ያዝዘናል። በዚህ የምዕራፉ ክፍል እነዚህን ትዕዛዛት በመመልከት በሙሐመድ ላይ እንተገብራቸዋለን።

### ፈተና 1፡ ፍሬያቸው ምንድነው?

> "የበግ ለምድ ለብሰው ከሚመጡባችሁ በውሥጣቸው ግን ነጣቂዎች ተኵላዎች ከሆኑ ከሐሰተኞች ነቢያት ተጠንቀቁ።ከፍሬያቸው ታውቋቸዋላችሁ። ከእሾህ ወይን ከኵርንችትስ በለስ ይለቀማልን?" (ማቴ. 7፡15-16)

ኢየሱስ ነቢያት ነን የሚሉትን ሰዎች ፍሬ እንድንፈትን ነግሮናል። ሙሐመድን በተመለከተ ግልፅ የሆነ መፈተን የምንችለው ፍሬ አለ።

### ሙሐመድና ዘይነብ

ሙሐመድ ዘይድ የተሰኘ የማደጎ ልጅ ነበረው። ዘይድ ዘይነብ የተሰኘች መልከ መልካም ሴት አግብቶ ነበር። አንድ ቀን ሙሐመድ ወደ ዘይድ ቤት ሲሄድ ዘይነብን ልብሷን ስትቀይር እርቃኗን ተመለከታት።፡

> ከዕለታት በአንዱ የአላህ መልእክተኛ ዘይድን ፍለጋ ሄደ። በመግቢያ በሩ ላይ ሻሽ ተጋርዶ ነበር ነገር ግን ንፋስ ሲገልበው በሩ በግልፅ ታየ። ዘይነብ በክፍሏ ውስጥ እርቃኗን ነበረች በዚህም ምክንያት የእርሷ አድናቆት የነቢዩ ልብ ውስጥ ገባ።[123]

ሙሐመድ በልቡ ውስጥ ከአድናቆት ያለፈ ነገር ስለተሰማው ዘይድ ዘይነብን በመፍታት ሙሐመድ እንዲያገባት የሚል ሐሳብ አቀረበ። ነገር ግን የማደጎ ልጃችሁን ሚስት ማግባት ዛሬም በብዙ ባሕሎች ውስጥ እንደሆነው በዚያን ዘመን በነበሩት አረቦች ዘንድ እንደ ነውር ይቆጠር ስለነበር ሙሐመድ ዘይነብን ሚስቱ አድርጎ መውሰድ አልቻለም ነበር። ከዚያም አላህ ለሙሐመድ ተናገረው። መጀመርያ አላህ ማደጎዎችን በሙሉ ሻረ፡-

---

123 Al-Tabari, The History of al-Tabari, vol. viii, p. 4

> “አላህ ለአንድ ሰው በሆዱ ውስጥ ሁለትን ልቦች አላደረገም፤ ሚስቶቻችሁንም እነዚያን ከነርሱ እንደናቶቻችሁ ጀርባዎች ይኹኑብን የምትሏቸውን እናቶቻችሁ አላደረገም።[124] ልጅ በማድረግ የምታስጠጓቸውንም ልጆቻችሁ አላደረገም፤ ይሃችሁ በአፎቻችሁ የምትሉት ነው፤ አላህም እውነቱን ይናገራል፤ እርሱም ትክክለኛዉን መንገድ ይመራል።” (ቁርኣን 33፡4)

ስለዚህ በእስልምና የማደጎ ልጅን እንደ ልጅ መቁጠር አይቻልም። ማደጎ ስለተሻረ ዘይድ የሙሐመድ ልጅ አይደለም ዘይነብን የልጁ ሚስት አይደለችም። ከዚያም ሌላ ቃል ከአላህ ዘንድ መጣ፡-

> “…ዘይድንም ከርሷ ጉዳይን በፈጸመ ጊዜ በምእምናኖች ላይ፣ ልጅ አድርገው ባስጠጉዋቸው (ሰዎች) ሚስቶች፥ ከነሱ ጉዳይን በፈጸሙ ጊዜ (በማግባት) ችግር እንዳይኖርባቸው፥ እርሷን አጋባንህ፤ የአላህም ትእዛዝ ተፈጻሚ ነው።” (ቁርኣን 33፡37)

መጽሐፍ ቅዱስ ስለዚህ ሁኔታ ምን ይላል? ይህ ሁኔታ አንድ ሰው የሌላውን ሰው የመመኘቱ ምሳሌ ነው። አሥርቱ ትዕዛዛት በዚህ ላይ ግልፅ ናቸው፡-

> “የባልንጀራህን ቤት አትመኝ፤ የባልንጀራህን ሚስት ሎሌውንም ገረዱንም በሬውንም አህያውንም ከባልንጀራህ ገንዘብ ሁሉ ማናቸውንም አትመኝ።” (ዘጸ. 20፡17)

እውነተኛው አምላክ የሌላን ሰው ሚስት መመኘትን ያመቻቻል ብሎ ማሰብ የማይሆን ነው። ይህ የሙሐመድ ታሪክ ከዳዊትና ቤርሳቤህ ታሪክ ጋር ይመሳሰላል[125] - ነገር ግን የተገላቢጦሽ ነው። ወደ ቤታችሁ በመምጣት ሚስታችሁ ልብሷን ስታወልቅ ካየሁ በኋላ እግዚአብሔር የኔ ሚስት እንድትሆን ሰጥቶኛል ብዬ ብላችሁ እስኪ አስቡት። ከገዛ ምናቤ የምናገር ሐሰተኛ ነቢይ እንጂ የእግዚአብሔር ነቢይ ልሆን እንደማልችል እንደምትደመድሙ ተስፋ አደርጋለሁ።

---

124 በልማዱ መሠረት አንዲትን ሴት ከፊታችሁ እናታችሁ ትሆናለች የሚል ነበር። ይህም ማለት ልታገቧት አትችሉም ማለት ነው። ሙሐመድ ይህንን በመሻር ከፍቺ በኋላ መልሶ ዳግመኛ ማግባትን ፈቅዷል። ቁርኣን 2፡ 2230 ተመልከቱ።

125 2ሳሙኤል 11-12

## የፍትወት አድሎ

ቁርአን አንድ ሙስሊም ወንድ ከአራት ሚስቶችና ከሴት ባርያዎች ጋር ፍትወት መፈፀም እንደሚችል ናገራል።[126] ሆኖም ሙሐመድ ከአንድ ተራ ሙስሊም ወንድ ከበዙ ሴቶች ጋር ወሲብ እንዲፈፅም እንደተፈቀደለት ተናግሯል።

> "አንተ ነቢዩ ሆይ! እኛ እነዚያን መህሮቻቸውን (3) የሰጠሃቸውን ሚስቶችህን፣ አላህ ባንተ ላይ ከመለሰልህም እነዚያን እጅህ የጨበጠቻቸውን ምርኮኞች፣ እነዚያንም ከአንተ ጋር፣ የተሰደዱትን የአንጎትህን ሴቶች ልጆች፣ የአክስቶችህንም ልጆች፣ የየሹማህንም ሴቶች ልጆች ፣ የየሹሜዎችሕንም ሴቶች ልጆች (ማግባትን) ለአንተ ፈቅደንልሃል፤ የአመነችንም ሴት ነፍሷን (ራሷን) ለነቢዩ ብትሰጥ ነቢዩ ሊያገባት የፈለገ እንደ ሆነ፣ ከምእምናን ሌላ ላንተ ብቻ የጠራች ስትሆን፣ (ፈቀድንልህ)፤ በነርሱ (በምእምናን) ላይ በሚስቶቻቸውና እጆቻቸውም በጨበጧቸው (ባሮች ነገር) ግዴታ ያደረግንባቸው በእርግጥ አውቀናል፤ ባንተ ላይ ችግር እንዳይኖር፣ (ያለፉትን ፈቀድንልህ)፤ አላህም መሐሪ አዛኝ ነው።" (ቁርአን 33፡50)

ይህ ጥቅስ እነዚህ ሴቶች ለሙሐመድ የተፈቀዱት በፖለቲካዊ አጋርነት ወይንም እርሱ እንዲጠብቃቸው አስገዳጅ ሁኔታ በመኖሩ ምክንያት ነው አይልም። እርሱ ስለፈለጋቸው ብቻ ነው። መመለስ ያለበት ጥያቄ፡ ለነቢይ በዚህ መንገድ ወሲባዊ አድሎን ማድረግ የእግዚአብሔር ባሕርይ ስለሆነ ነው ወይንስ የግለሰቡ ምኞት ነው? የሚል ነው።

## ወሲብ ከምትፈልጋት ሴት ጋር

ብዙ ሚስቶች ካሏችሁ ከእነርሱ ጋር እንዴት እንደምታሳልፉ ጊዜን መከፋፈል ያስፈልጋችኋል። ትክክለኛው ሁኔታ ባል ለሚስቶቹ ጊዜውን በእኩል ሁኔታ ያከፋፍላል የሚል ነው። ይህ ደግሞ የሴቶቹ መብት ነው። ነገር ግን ሙሐመድ የወሲብ ጊዜውን እንደወደደ ለሚስቶቹ እንዲያከፋፍል ፈጣሪ እንደነገረው ተናገረ።

> "ከነሱ የምትሻትን ታቆያለህ፤ ይምንሻትንም ወደ አንተ ታስጠጋለህ፤ (በመፍታት) ከአራቅሃትም የፈለግሃትን፥ (በመመለስ ብታስጠጋ)፥ በአንተ ላይ ሐጢያት የለብህም፤ ይህ ዓይኖቻቸው ወደ መርጋት፣ ወደ አለማዘናቸውም፥ ለሁሉም በሰጠሃቸው ነገር ወደ መውደዳቸውም በጣም የቀረበ ነው፤ አላህም በልቦቻችሁ ውስጥ ያለውን ሁሉ ያውቃል፤ አላህም ዐዋቂ ታጋሽ ነው።" (ቁርአን 33፡51)

በጣም የሚደንቀው ሙሐመድ ይህንን መገለጥ ከተናገረ በኋላ ከሚስቶቹ መካከል አንዷ የሰጠችው አስተያየት ነው፡-

---

[126] ቁርአን 4:3, 70:29-30

> አይሻ እንዲህ አለች፡- (ቁርአን 33፡51) ከጠቀሰች በኋላ … ለነቢዩ እንዲህ አልኩት "ጌታህ ምኞትህንና ፍላጎትህን ለመሙላት የተጣደፈ ይመስለኛል።" (ሳሂህ አል-ቡኻሪ ቅፅ 6፣ መጽሐፍ 60፣ ቁጥር 311)

ከአይሻ ጋር እስማማለሁ። ቁርአን የሙሐመድን ምኞት ለማፅደቅ የተጻፈ የግል ሰነዱ ነው።

ኢየሱስ ክርስቲያኖች ነቢያትን በፍሬያቸው ፈትነው እንዲለዩዋቸው አዟቸዋል። በዚህ ክፍል ሙሐመድ የሰው ሚስት በመመኘት ለመውሰድ፣ ከሌሎች ሙስሊም ወንዶች በላይ ወሲባዊ ሙብቶችን ለማግኘት እንዲሁም ከሚስቶቹ ጋር ፍትሃዊነት በሌለው በፈቀደው መንገድ ወሲብ ለመፈፀም የፈጣሪን ስም ተጠቅሟል። ይህ የእውነተኛ ነቢይ ፍሬ አይደለም።

## ፈተና 2፡ ምን ዓይነት ወንጌል ነው የሚሰብኩት?

> "በክርስቶስ ጸጋ እናንተን ከጠራችሁ ከእርሱ ወደ ልዩ ወንጌል እንዲህ ፈጥናችሁ እንዴት እንዳለፋችሁ እደነቃለሁ፤ እርሱ ግን ሌላ ወንጌል አይደለም፤ የሚያናውጡአችሁ የክርስቶስንም ወንጌል ሊያጣምሙ የሚወዱ አንዳንዶች አሉ እንጂ። ነገር ግን እኛ ብንሆን ወይም ከሰማይ መልአክ፥ ከሰበክንላችሁ ወንጌል የሚለይ ወንጌልን ቢሰብክላችሁ፥ የተረገመ ይሁን። አስቀድመን እንዳልን እንዲሁ አሁን ሁለተኛ እላለሁ፥ ከተቀበላችሁት የተለየውን ማንም ቢሰብክላችሁ የተረገመ ይሁን።" (ገላ. 1፡6-9)

በነዚህ ጥቅሶች ውስጥ ሐዋርያው ጳውሎስ የተለየ ወንጌል መስበክ ከባድ ችግር መሆኑን ይናገራል። ክርስቲያኖችም የወንጌሉን ዓይነት ለይተው መወሰን ያስፈልጋቸዋል። ይህ ክርስቲያኖች ነቢይ ነን የሚሉትን ሰዎች የሚፈትኑበት አንዱ መንገድ ነው፤ ምን ዓይነት ወንጌል ነው የሚሰብኩት?

ሙሐመድ መልአክ ወደ እርሱ መጥቶች እግዚአብሔር አባታችን እንዳልሆነ እንደነገረው ተናገረ፤[127] ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ አይደለም፤[128] ኢየሱስም በመስቀል አልተሰቀለም አለ።[129] የሙሐመድ ወንጌል ይህ ሲሆን ሙሉ በሙሉ ሐሰተኛ ወንጌል ነው። ስለዚህ ሙሐመድን በሰበከው ወንጌል መሠረት ስንፈትነው እውነተኛ ነቢይ እንዳልሆነ እንገነዘባለን።

## ማጠቃለያ

ሙሐመድ በክርስቲያኖች ላይ ሥልጣን ያለው ነቢይ መሆኑን ተናግሯል። ክርስቲያኖች ነቢይ ነን የሚሉ ሰዎችን ዝም ብለው መቃወም ሳይሆን መፈተንና ማየት ያስፈልጋቸዋል።

---

127 ቁርአን 5:18

128 ቁርአን 19:92-93

129 ቁርአን 4:157

በዚህ ምዕራፍ ሙሐመድን ፈትነነዋል። መጀመርያ ቁርኣን ለሙሐመድ ነቢይነት በማስረጃነት የሚያቀርባቸውን 6 ምክንያቶች ተመልክተናል። ይህም ማለት ሙሐመድን በገዛ ቃሉ ፈትነነዋል ማለት ነው። የመጀመርያዎቹ አራት ምክንያቶች ኢ-አመክንዮአዊና ምንም ነገር የማያረጋግጡ ባዶ ሙግቶች መሆናቸውን ይልቁኑ ሐሰተኛ ነቢይ መሆኑን እንደሚያሳዩ አይተናል። አምስተኛውና ስድስተኛው ሙግቶች ሙሐመድ መጽሐፍ ቅዱስን አረጋግጧል እንዲሁም በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ትንቢት ተነግሮለታል የሚሉ ናቸው። እነዚህን ሙግቶች በማጤን ሐሰት ሆነው አግኝተናቸዋል። ስለዚህ ሙሐመድ እውነተኛ የእግዚአብሔር ነቢይ መሆኑን የሚያሳይ ማስረጃ የለም።

ከዚያ ሙሐመድን በመጽሐፍ ቅዱስ መስፈርቶች መሰረት ገመገምነው። የሙሐመድ ፍሬዎች እንደሚያመለክቱት ከራሱ ፍላጎትና ምኞት እንጂ ከእግዚአብሔር እንዳልተናገረ አየን። ሐሰተኛ ወንጌል ማስተማሩንም ተመለከትን። ስለዚህ ሙሐመድ ኢየሱስና ሐዋርያቱ እንድንጠነቀቃቸው ከነገሩን ሐሰተኛ ነቢያት መካከል አንዱ ነው። ክርስቲያኖች ከሆናችሁ ስለዚህ ነገር ግልፅ መሆንና እዚህ ድምዳሜ ላይ ለምን እንደደረሳችሁ በግልፅ ማስቀመጥ ያስፈልጋችኋል።

## ትግበራና ማጠቃለያ

*ሙስሊም* ፡ ክርስቲያኖች ሙሐመድን እንደ ነቢይ ሊቀበሉት ይገባል።

*ክርስቲያን* ፡ ከሙሐመድ በኋላ ነቢይ ነኝ ያለውን ሁሉ ትቀበላለህ?

*ሙስሊም* ፡ አይ። ሐሰተኛ ነቢያት ናቸው።

*ክርስቲያን* ፡ አንተ ከሙሐመድ በኋላ የሚመጡትን ላለመቀበል የራስህ ምክንያቶች እንዳሉህ ሁሉ እኛም ሙሐመድን ላለመቀበል የራሳችን ምክንያቶች አሉን። ጥያቄው አንድ ነቢይ ከእግዚአብሔር መሆን አለመሆኑን የምናውቀው እንዴት ነው? የሚል ነው። የሆነ ማስረጃ መኖር አለበት። ሙሐመድ እውነተና ነቢይ ስለመሆኑ የቀረቡትን ማስረጃዎች እስኪ እናጧናቸው።

ሙስሊም፡ ማንም ሰው ቁርኣንን የሚመስል ሊያመጣ አይችልም። ይህም ከእግዚአብሔር ዘንድ እንደመጣ ያረጋግጣል።

ክርስቲያን፡- ቁርኣን ስለ ኦሪትም ተመሳሳይ ነገር ይናገራል (ቁርኣን 28፡49) ስለዚህ ይህ አባባል ምንም የተለየ አይደለም። እንደ ኦሪት ያለ ማንም ሊሠራ አይችልም ትላላችሁ? በሁለተኛ ደረጃ፣ በ7ኛው ክፍለ ዘመን በሰሜን ምዕራብ አረብኛ አቀላጥፈህ ትናገራለህ? ካልሆነ ታዲያ ዓረብኛው ድንቅ መሆኑን እንዴት ማወቅ ይቻላል? በሶስተኛ ደረጃ ሰዎች ቁርኣንን የሚመስል ነገር ሠርተዋል። ያን በማድረጋቸው ግን ይቀጣሉ፣ ስለዚህ አንተ መቼስ ቁር አንን የሚመስል ነገር ማምጣት አትችል ስትል ከልብህ አይደለም። በአራተኛ ደረጃ ፣ አንድ የሚያምር ትርኢት አንድ ነገር ከእግዚአብሔር መሆኑን ያረጋግጣል?

# ምዕራፍ 10

## ሙስሊሞችና መጽሐፍ ቅዱስ

ሙስሊሞች መጽሐፍ ቅዱስ መበረዙንና ሊታመን እንደማይችል ተምረዋል። ለእነርሱ ብቸኛው ከፈጣሪ ዘንድ የሆነ መጽሐፍ ቁርአን ነው። ይህ አስተምሕሮ ሙስሊሞች መጽሐፍ ቅዱስን ከጅምሩ እንዲቃወሙ ስለሚያደርጋቸው አብራችሁ ለማንበብ የምትሞክሩ ከሆነ እንቅፋት ሊሆንባችሁ ይችላል። በዚህ ምዕራፍ ከየት መጀመርና እንዴት መሄድ እንዳለብን እንመለከታለን።

### መጽሐፍ ቅዱስና ቁርአን

ሙስሊም ጓደኞቻችሁን ወደ መጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ከጋበዛችሁ ፈቃደኛ በመሆን የጌታን መልካምነት ቀምሰው እንደሚያዩ ተስፋ አደርጋለሁ! ኢየሱስን በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ሲያገኙትና የቅዱሳት መጻሕፍትን ተግባቦት ሲመለከቱ እንዲሁም ነቢያት በሙሉ በኢየሱስ ፍፃሜን እንዳገኙ ሲገነዘቡ በእግዚአብሔር ፈቃድ እምነትን ያገኛሉ። ለሙስሊም ወዳጆቻችን ጸሎታችን ይህ ነው። ነገር ግን ስለተማሩት ነገርና እንዴት ተፅዕኖን እንደሚያሳድርባቸውም ማወቅ ያስፈልገናል።

መጽሐፍ ቅዱስን ለማጣጣልና መበረዙን ለማረጋገጥ የሚሞክሩ ስፍር ቁጥር የሌላቸው የሙስሊም ቪድዮዎችና መጻሕፍት አሉ። ሙስሊሞች ስለ ክርስትና የሚማሩት የዘውትር ትምሕርት አካል የሆነ ትምሕርት አለ። እነዚህ መጻሕፍትና ቪድዮዎች መጽሐፍ ቅዱስ ተለውጧል የሚል ክስ ያቀርባሉ፤ ከታሪክና ከሳይንስ አኳያ ሊታመን እንደማይችል ለማሳመን ጥረት ያደርጋሉ። በግጭት እንደተሞላ፣ ብዙ ቅጂዎች እንዳሉት፣ የንባብ ልዩነቶች እንዳሉት፣ በማይታወቁ ጸሐፊያን እንደተጻፈና ሌሎች ወንጌላትን እንዳገለለ ይለፍፋሉ። ከነዚህ ክሶች በተጨማሪ ሙስሊሞች ቁርአን ራሱ መጽሐፍ ቅዱስ እንደማታመን እንደሚናገር ይማራሉ። ሙስሊሞች እነዚህን ክሶች በሰሙ ቁጥር መጽሐፍ ቅዱስን በመቃወም ይጸናሉ። ክርስቲያኖች እነዚህን በሚገባ የተጠኑ ተቃውሞዎች ለመጀመርያ ጊዜ ሲሰሙ ግራ ሊገባቸውና አልፎም እውነት ሊመስላቸው ይችላል።

እነዚህ ክሶች ሲቀርቡ አብዛኞቹ ክርስቲያኖች በተቻለ መጠን መልስ ለመስጠት ይሞክራሉ። መልሱን ሙሉ በሙሉ ካላወቁ ደግሞ ጥናት አድርገው በሌላ ጊዜ ምላሽ ሊሰጡ ይችላሉ። ይሁንና መጽሐፍ ቅዱስን ለመከላከል ጥሩ የጅማሬ ቦታ እንዳልሆነ ምክሬን እሰጣለሁ። ከልምድ እንደተረዳሁት ሙስሊሞች ስለ መጽሐፍ ቅዱስ ያላቸውን ጥያቄ በሙሉ ከመለሳችሁ በኋላ እንኳ ላታሳምኗቸው ትችላላችሁ። የዚህ ምክንያቱ የጉዳዩን ግማሽ ችግር ብቻ ስለምትነኩ ነው - ይህ ግማሽ ደግሞ አስፈላጊነቱ ዝቅ ያለው ግማሽ ነው። የሙስሊሞች

*ሙግት ጉለት ገፅታ አለው፤ መጽሐፍ ቅዱስ የተበረዘ ነው ቁርኣን ግን በትክክል የተጠበቀ ነው።*

> ቁርኣን በቀደመው መልኩ፣ በተሟላ ሁኔታ፣ ከአሥራ አራት ክፍለ ዘመናት በፊት ለነቢዩ በተገለጠው ሁኔታ፣ አንድ ቃል ሳጨመርበትና ከላዩ ላይ ሳይቀነስ ተጠብቆ የሚገኝ ብቸኛው መጽሐፍ ነው። ይህ ምንም የማያከራክር ታሪካዊ ሃቅ ነው። ጥበቃውን ፈጣሪ ራሱ አረጋግጦልናል (ቁርኣን 15፡9)። ስለዚህ ከነቢዩ ዘመን ጀምሮ በዘመናት ሁሉ በመላው ዓለም አንድ ዓነት የቁርኣን ቅጂ ብቻ ነው ያለው።[130]

> ከቁርኣን ጋር ሊመጣጠን የሚችል ሌላ መጽሐፍ በዓለም ላይ የለም ... ስለዚህ የአላህ መጽሐፍ አስደናቂው ነገር ላለፉት አሥራ አራት ክፍለ ዘመናት አንድ ነጥብ እንኳ ሳይለወጥ መቆየቱ ነው። ምንም ዓይነት የጽሑፍ ልዩነት በመካከሉ የለም። ይህንን ደግሞ ከተለያዩ የዓለም ክፍሎች የሙስሊም ንባባትን በማዳመጥ ማረጋገጥ ትችላላችሁ።[131]

ይህ ስለ ቁርኣን ያላቸው እምነት ለሙስሊሞች በእጅጉ ወሳኝ ነው። የሚኮሩበት ነገርም ነው። እስልምና እውነተኛ ሃይማኖት ለመሆኑ ማረጋገጫቸው ነው። የመጽሐፍ ቅዱስን ተዓማኒነት ለማጣጣል በራስ መተማመንንና አልፎም ትዕቢትን እንዲሞሉ ያደርጋቸዋል። ለዚህ ነው ይህንን እምነት ከመመርመር ውይይታችሁን እንድትጀምሩ የማበረታታው።

ይህም ማለት ሙስሊሞች መጽሐፍ ቅዱስን ለመቀበል ፈፅሞ እንዳያስቡ የሚያደርጋቸው ቅድመ ግንዛቤ ስላላቸው መጽሐፍ ቅዱስን ከመከላከላችሁ በፊት ይህንን ልትወያዩ ይገባል። ሁለት ዋና ዋና ቅድመ ግንዛቤዎች አሉ፤ የመጀመርያው አንድ ቁርኣን ብቻ አለ እርሱም በትክክል ተጠብቋል የሚል ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ቁርኣን መጽሐፍ ቅዱስ ተዓማኒነት የለውም ይላል የሚል ነው። እነዚህን መሠረታዊ ቅድመ ግንዛቤዎች ከተወያያችሁ እናንተና ሙስሊም ወዳጃችሁ የመጽሐፍ ቅዱስን ተዓማኒነት ለመወያየት የተሻለ መግባባት ላይ ትደርሳላችሁ። ምናልባትም መወያየት ላያስፈልጋችሁ ሁሉ ይችላል።

በተቀረው የምዕራፉ ክፍል ተከታዮቹን ነጥቦች እንዳስሳለን፡-

- የቁርኣንን ታሪክና የአሁን ሁኔታ
- ቁርኣን ስለ መጽሐፍ ቅዱስ ምን ይላል?
- የመጽሐፍ ቅዱስ ተዓማኒነት

---

130 Al-Ahsa Islamic Center, Before you start reading the Qur'an, Hofus, no date, p
131 Basic Principles of Islam, Abu Dhabi, UAE: The Zayed Bin Sultan Al Nahayan Charitable Humanitarian Foundation, 1996, p. 4

## የቁርኣንን ታሪክና የአሁን ሁኔታ

ሙስሊም መሪዎች ስለ ቁርኣን የሚከተሉትን ይላሉ፡-

- ሙሐመድ ቁርኣንን በትክክል ሸምድዶት ነበር።
- በትውስታቸው ለያዙትና ለጻፉት ተከታዮቹ ያለ ምንም ተጨማሪ ማስተካከያ አስተምሯቸዋል። ሙሐመድ የተጻፈውን በማየት አጽድቋል።
- ከመጀመርያው አንድ ዓይነት የቁርኣን ቅጂ ብቻ ነበር።
- ሁሉም ቁርአኖች ያለምንም ልዩነት ተመሳሳይ ናቸው።
- ቁርኣን በትክክል ተጠቋል።
- እነዚህ ሙግቶች በታሪክ የተረጋገጡ ናቸው።
- ቁርኣን በጥበቃው ከሌሎች መጻሕፍት የላቀ በመሆኑ የፈጣሪ ቃል ነው።

እነዚህን ንግግሮች ከሙስሊም ጓደኞችሁ ልትሰሙ ትችላላችሁ ወይንም የማይነገር ቅድመ ግንዛቤ ሊሆን ይችላል።  ስለ ቁርኣን የተማሩትና የሚያምኑት ይህንን ነው። ከዚህ እምነት በመነሳት ነው ሙስሊሞች ቁርኣንን ለመጽሐፍ ቅዱስ አማራጭ አድርገው የሚያቀርቡላችሁ። አብዛኞቹም መጽሐፍ ቅዱስ እንደማያስፈልጋቸው የሚያስቡት ከዚህ የተነሳ ነው። ሆኖም እነዚህ ሙግቶች እውነት ናቸውን? በፍፁም! እውነታው በእስልምና ጅማሬ ላይ ብዙ የቁርኣን ዓይነቶች የነበሩ ሲሆን ዛሬም በብዛት በዓለም ዙርያ መኖራቸው ነው።

እስልምናን ለማስፋፋት ካላቸው ጉጉት የተነሳና ለተራው ሙስሊም ጉዳዩን ለማቅለል በማሰብ እንዲሁም ለቁርኣን ካላቸው አክብሮት የተነሳ ሙስሊም መሪዎች ታሪካዊም ሆነ ምሑራዊ ተቀባይነት የሌላቸውን ሐሰተኛ ቢሂሎች አዳብረዋል። እነዚህ እምነቶች ሐሰት ናቸው፤ ለሙስሊም ወዳጆችሁ ደግሞ ይህንን ማሳየት መጽሐፍ ቅዱስን ዝም ብለው ማጣጣል እንደሚችሉ እንዳያስቡ ይረዳቸዋል።

በተቀረው የዚህ ምዕራፍ ክፍል የእስልምና ታሪክ፣ ሙስሊም ሊቃውንትና የእጅ ጽሑፎች ስለ ቁርኣን የሚያሳዩትን እናያለን። ስለ ቁርኣን አመጣጥ የሚነገረውን ዘመናዊ የጥናት አካሄድ አልጠቅስም።

## ሙሐመድና ጥቅሶቹ

ቁርኣን እንደ መጽሐፍ ሳይሆን ሙሐመድ ለማሕበረሰቡ ሲናገራቸው ከነበራቸው ቁርጥራጭ ጥቅሶች ይጀምራል። እነዚህ ጥቅሶች ክርስቲያኖች የጌታን ጸሎት በመሸምደድ ለጸሎት እንደሚጠቀሙበት ሁሉ ሙስሊሞችም በመሸምደድ ለጸሎት ይጠቀሙበታል። ጥቅሶች

ደግሞ በገዎች፣ አጥንቶችና ድንጋዮች ላይ ይጻፉ ነበር።[132] አንዳንዴ ሙሐመድ ጥቅሶችን ይረሳ ስለነበር አስታዋሽ ያሻው ነበር፡-

> (ቁርኣንን) በእርግጥ እናስነብብሃለን፤ አትረሳምም። (ቁርኣንን) በእርግጥ እናስነብብሃለን፤ አትረሳምም። (ሱራ 87፡6-7

አንድ ሐዲስ ደግሞ ሙሐመድ ከሞተ በኋላ የቁር አን ክፍሎ እንደተረሱ ይናገራል።

> (ሱራ 9) ባራዓትን የሚመስል ሱራ እናነብ ነበር። እኔ ግን ከዚሁ "ሁለት ባለጠግነት ሸለቆዎች ቢኖሩ ለአዳም ልጅ ሦስተኛውን ሸለቆ በናፈቀ፣ ለአዳም ልጅ ግን አፈር በቀር ሆድንም የሚሞላ ምንም ነገር ባልነበረም ነበር።" ከሚለው በቀር የተቀረእውን ረሳሁት። ሳሂህ ሙስሊም 2286

አንዳንዴ አንቀፆችን እያረመ ቅርፅ ያስይዝ ነበር፡-

> "አል-በራ እንዳስተላለፉት፡- ‹ተቀማጮቹና በአላህ መንገድ በገንዘቦቻቸውና በነፍሶቻቸው የሚታገሉት አይተካከሉም› የሚል ሱራ ወርዶ ነበር (4፡95)። ነቢዩ እንዲህ አሉ፡- ‹እስኪ ዘይድን ጥሩልኝ መጻፍያ ሰሌዳ፣ የቀለም ገንቦና (እንደ ብዕር የሚያገለግል) አጥንት ያምጣልኝ...› ከዚያ፡- ‹ተቀማጮቹና በአላህ መንገድ በገንዘቦቻቸውና በነፍሶቻቸው የሚታገሉት አይተካከሉም... ብለህ ጻፍ› አሉት። በዚህ ጊዜ ዓይነ ስውሩ አምር ቢን ኡም መክቱም አጠገባቸው ተቀምጦ ነበር። እርሱም እንዲህ አለ፡- ‹የአላህ መልእክተኛ ሆይ! ለኔስ የሚሰጡት ትዕዛዝ ምንድነው? እኔ ዓይነ ስውር ሰው ነኝ።› ስለዚህ በዚህኛው አንቀፅ ፋንታ ተከታዩ አንቀፅ ወረደ፡- ‹ከምእመናን የጉዳት ባለቤት ከኾኑት በቀር ተቀማጮቹና በአላህ መንገድ በገንዘቦቻቸውና በነፍሶቻቸው የሚታገሉት አይተካከሉም።›" (ቁርኣን 4፡ 95) (ሳሂህ አል-ቡኻሪ ቅፅ 6፣ መጽሐፍ 61፣ ቁጥር 512)

እዚህ ጋ እንደምናየው የ 4፡95 ቀዳሚ ቅጂ ኤዲት ተደርጎ "የጉዳት ባለቤት ከኾኑት በቀር" የሚል ተጨምሮበታል። እንዲህ ያለው የእርማት ሥራ ከመብዛቱ የተነሳ የሙሐመድ ተቃዋሚዎች እርሱን ለመቃወም እንደ ምክንያት ይጠቀሙ ነበር፡-

ሙሐመድ እነዚህን አንቀፆች ያስተማረ ሲሆን ሌሎችም እንዲያስተምሩ አዟል።

> መዝሩቅ እንዳወራው ... ነቢዩ እንዲህ ሲሉ ሰማሁ "ቁርኣንን ከአራት ሰዎች ተማሩ እነርሱም አብዱላህ ኢብን መስዑድ፣ ሰሊም፣ ሙዓዝና ኡበይ ቢን ከዕብ ናቸው።" (ሳሂህ አል-ቡኻሪ ቅፅ 6፣ መጽሐፍ 61፣ ቁጥር 521)

---

132 Sahih al-Bukhari: vol. 6, bk. 61, no. 509; Qur'an 68:1, 80:11-15, 96:4

በአንቀጽም ስፍራ አንቀጽን በለወጥን ጊዜ አላህም የሚያወርደውን ነገር አዋቂ ነው። «አንተ ቀጣፊ እንጂ ሌላ አይደለህም» ይላሉ። በእውነቱ አብዛኞቻቸው አያውቁም። (ሱራ 16፡ 101)

## የሙሐመድ ተከታዮችና ተመሳሳዮቹ ቁርአኖች

ሙሐመድ የሞተው እነዚህን ጥቅሶች በአንድ ጥራዝ ሳይሰበስብ ነበር።[133] በተበታተነ ሁኔታ በተለያዩ ሰዎች እጅ በሙስሊሙ መሕበረሰብ መካከል ተሰራጭተው ነበር። ከእርሱ ሞት በኋላ አስተማሪዎች አድርጎ የሾማቸው ሰዎች እነዚህን ጥቅሶች በማሰባሰብ የየራሳቸውን ኮፒዎች አዘጋጁ። እነዚህ ቁርአኖች ተመሳሳይ ቢሆኑም ልዩነቶች ነበሯቸው። ተከታዮቹ ልዩነቶች በመካከላቸው ነበሩ፡-

1. *የተለያየ መጠን ሱራዎች* - በቁርአኖቹ ውስጥ የነበሩት ሱራዎች ወይም ምዕራፎች ብዛት ይለያያል። የአብደላህ ኢብን መስዑድ ቁርኣን ሱራ 1፣ 113 እና 114 አልነበሩትም። የኡበይ ቢን ካዕብ ቁርኣን ደግሞ ሁለት ተጨማሪ ሱራዎች ነበሩት። የአረብኛ ቤተ መዛግብት ሊቅ የነበረው ኢብን አቢ ያዕቁብ አል-ነዲም በ375 ከሒጅራ በኋላ ወይንም በ987 ዓ.ም. ታዋቂ ካታሎግ አዘጋጅቶ ነበር። የነዚህን ቁርአኖች ይዘት በጥልቀት ጽፏል።

   > በአብዱላህ ኢብን መስዑድ የእጅ ጽሑፍ ውስጥ የነበረውን የቁርኣን ቅደም ተከተል በተመለከተ አል-ፈድል ኢብን ሸዛን እንዲህ አለ “በአብዱላህ ኢብን መስዑድ ቁርኣን ውስጥ ያገኘኋቸው የቁርኣን ሱራዎች ቀጥሎ የሚገኘውን ቅደም ተከተል ይዘዋል... እነዚህ አንድ መቶ አሥር ሱራዎች ናቸው።”[134]

   > ከታማኝ ወዳጆቻችን መካከል አንዱ እንደነገረን በኡበይ ቢን ካዕብ ንባብ መሠረት የተዘጋጀ የሱራዎች ስብስብ ቃርያት አል-አንሳር በተሰኘች ከአል-በሥራ የሁለት ቀን መንገድ ላይ በምትገኝ መንደር ውስጥ ይገኛል። እዚያም ሙሐመድ ኢብን አብድ አል-ማሊክ አል-አንሳሪ በቤቱ የተቀመጠ “ከአባቶቻችን የተላለፈልን የኡበይ ኮፒ ይህ ነው” ተብሎ የተጻፈበትን ቁርኣን አሳየን። በማገላበጥም የሱራዎችን ርዕሶች፣ የመገለጦችን ፍፃሜ እንዲሁም የአንቀፆችን ብዛት በደንብ አየሁ። ... አንድ መቶ አሥራ ስድስት ሱራዎች ነበሩ።[135]

---

133 Sahih al-Bukhari: vol. 6, bk. 61, no. 509

134 Al-Nadim, *The Fihrist of al-Nadim - A Tenth Century survey of Muslim Culture*, New York: Columbia University Press, 1970, p. 53.

135 Al-Nadim, pp. 58-61

ሁለቱ ተጨማሪ የኡበይ ቢን ካዕብ ሶራዎች የሚከተሉት እንደሆኑ ተነግሯል፡-

ሱራ 115 አል-ኸል፡- አ አላህ፣ ያንተን እርዳታና ምህረት እንለምናለን፤ እናመሰግንሃለን አንክድህምም። ባንተ ላይ ከሚወነጅሉት እንለያለን እንርቃለንም።

ሱራ 116 አል-ሐፍድ፡- "አ አላህ እናመልክሃለን፣ ወደ አንተም እንጸልያለን፣ ላንተም እንሰግዳለን፣ አንተንም ለመገዛት እንጣደፋለን። ምህረትህን ተስፋ እናደርጋለን ቅጣትህንም እንፈራለን። ያንተ ቅጣት ያለጥርጥር ከሃዲያንን ያገኛቸዋል።[136]

2. *የሱራዎች ቅደም ተከተል የተለያየ ነበር* - የሙሐመድ ተከታዮች የየራሳቸውን ቁርአኖች ያዘጋጁ በነበረበት ጊዜ ሱራዎችን በተለያዩ ቅደም ተከተሎች አስቀምጠው ነበር።[137] ይህ የሚያሳየው ከሙሐመድ የተላለፈ የቁርአንን ሱራዎች አደራደር የሚያሳይ መመርያ አለመኖሩን ያመለክታል። እነዚህ የተለያዩ ቅደም ተከተሎች የተለያዩ ክፍሎች በተለያዩ ጊዜያት እንደመጡ ያደርጋሉ።
3. *ለአንድ ጥቅስ የተለያዩ ቃላት* - አንድ ጥቅስ በተለያዩ ቁርአኖች ውስጥ የተለያዩ ቃላትን እንደሚጠቀም የሚያሳዩ ሁለት ጥቅሶች እነሆ። ሱራ 92፡3 በአብዱላህ ኢብን መስዑድ ቁርአን ውስጥ እንዲህ ይነበባል፡-

   በወንድና በሴት (እምላለሁ)። (ቁርአን 92፡3)

   በዘይድ ቢን ሣቢት ቁርአን እንዲህ ይነበባል፡-

   ወንድና ሴትን በፈጠረውም (አምላክ እምላለሁ)። (ቁርአን 92፡3)[138]

   ሱራ 33፡6 በኡበይ ቢን ካዕብ ቁርአን ውስጥ እንዲህ ይነበባል፡-

   ነቢዩ፣ በምእምናን ከነፍሶቻቸው ይበልጥ ተገቢ ነው፤ እርሱ አባታቸው ነው፤ ሚስቶቹም እናቶቻቸው ናቸው... (ቁርአን 33፡6)[139]

   የዘይድ ኢብን ሣቢት ቁርአን እንዲህ ይላል፡-

   ነቢዩ፣ በምእምናን ከነፍሶቻቸው ይበልጥ ተገቢ ነው፤ ሚስቶቹም እናቶቻቸው ናቸው... (ቁርአን 33፡6)

---

136 Ahmed von Denffer, *`Ulum al Qur'an*, Leicester: The Islamic Foundation, 1985, p. 48.
137 Ahmed von Denffer, pp. 47-49
138 *Sahih al-Bukhari*: vol. 6, bk. 60, no. 468; *Sahih Muslim*: bk. 4, no. 1799-1802
139 Abdullah Yusuf Ali, *The Holy Qur'an: Text, Translation, and Commentary*, 4th ed.,
Brentwood, Md., U.S.A.: Amana Corp., 1989, footnote 3674.

ልዩነቶቹ የዘዬ ሳይሆን የቃላት ጭማሬና የትርጉም ናቸው። ስለዚህ የእስልምና ታሪክ በግልፅ የሚታይ ልዩነቶችን የያዙ የተለያዩ የቁርኣን ቅጂዎች እንደነበሩ ያሳያል። ከክርስትና ጋር ንፅፅር ማድረግ እንችላለን። የተለያዩ የኢየሱስ ተከታዮች ወንጌላትን እንደጻፉ ሁሉ (ማቴዎስ፣ ማርቆስ፣ ሉቃስ፣ ዮሐንስ) የተለያዩ የሙሐመድ ተከታዮችም የተለያዩ ቁርአኖችን ጽፈዋል። በቀደመው የእስልምና ታሪክ ተመሳሳይ (ሲኖፐቲክ)[140] ቁርአኖች ነበሩ። ቁርአኖቹ ተመሳሳዮች የነበሩ ቢሆኑም ልዩነቶች ነበሯቸው።

## የቁርኣን ዝግጅት

ሙስሊም ሠራዊቶች አዲስ ወደተወረሩት አካባቢዎች ሲሄዱ የየራሳቸውን የቁርኣን ቅጂዎች ማስተማር ጀመሩ። በዚህ ጊዜ እነዚህ የተለያዩ ቁርአኖች በሙስሊም ማሕበረሰቦች መካከል ጭቅጭቆችን ማስነሳት ጀመሩ።

*"ሦርያውያን ከኢራቃውያን ጋር እሰጥ አገባ ውስጥ መግባታቸውን ሰማን። የመጀመርያዎቹ የኡበይ ቢን ካዕብን ቁርኣን ይከተሉ የነበረ ሲሆን ሁለተኞቹ ደግሞ የአብዱላህ ኢብን መስዑድን ቁርኣን ይከተሉ ስለነበር አንዳቸው ሌላቸውን ከሃዲያን ናቸው ይሉ ነበር።"*[141]

*ሦስተኛው ኸሊፋ ኡሥማን የራሱን ስብስብ የሙስሊሞች ሁሉ መደበኛ ቅጂ በማድረግ ይህንን ፖለቲካዊ ችግር ፈታ። ሌሎች ቅጂዎችም እንዲወድሙ አደረገ።*

> *ኡሥማን ለያንዳንዱ የሙስሊም ግዛት አንድ አንድ ኮፒ ከላከ በኋላ ቁርጥራጭ ኪፒዎች ይሁኑ ሙሉ የቁርኣን ኮፒዎች ሁሉም እንዲቃጠሉ አዘዘ...* (ሳሂህ አል-ቡኻሪ ቅፅ 6፣ መጽሐፍ 61፣ ቁጥር 510)

በኡሥማን ድርጊት ደስተኛ የሆኑት ሁሉም የሙሐመድ ተከታዮች አልነበሩም። በተለይም አብዱላህ ኢብን መስዑድ ቁርኣንን በአደባባይ በመቅራት ከመጀመርያዎቹ አንዱ የነበረ ቢሆንም የኡሥማን ቅጂ ሲዘጋጅ የኮሚቴ አባል ተደርጎ ስላልተመረጠ በጣም ተቆጥቶ ነበር።[142] ቁርኣንን ለሙሐመድ ይቀራለት የነበረ ሲሆን[143] እንዲያስተምር በራሱ በሙሐመድ ተሹሞ ነበር።[144] ተማሪዎቹ ቁርአኖቻቸው በኡሥማን እንዳይቃጠሉ እንዲሸሽጉ ነግሯቸው ነበር፡-

---

140 Synoptic (ሲኖፐቲክ) ማለት *ተመሳሳይ ዕይታ* ማለት ነው። ማቴዎስ፣ ማርቆስና ሉቃስ በጣም ስለሚመሳሰሉ *synoptic gospels* ወይንም *ተመሳሳዮቹ ወንጌላት* ይባላሉ።

141 Labib as-Said, *The Recited Koran: A History of the First Recorded Version*, tr. B. Weis, et al., Princeton, New Jersey: The Darwin Press, 1975, p. 23

142 Ibn Ishaq, p. 141

143 *Sahih al-Bukhari*: vol. 6, bk. 61, no. 576

144 *Sahih al-Bukhari*: vol. 6, bk. 61, no. 521

“አዝ-ዙህሪ እንዳስተላለፈው፤ ኡበይ ቢን አብዱላህ ቢን ኡትባህ እንደነገረኝ አብደላህ ቢን መስዑድ ዘይድ ቢን ጣቢት *ሙሳሒፉን* በመጻፉ ደስተኛ ስላልነበረ እንዲህ ብሎ ነበር፡- ‹እናንተ የሙስሊም ሕዝቦች ሆይ! የዚህን ሰው *ሙሳሒፍ* እና የእርሱን ንባብ ከናንተ አስወግዱ። በአላህ እምላለሁ! እኔ እስልምናን ስቀበል በከሃዲ ሰው እርግብግቢት ውስጥ ነበር።› አብደላህ ኢብን መስዑድ አክሎም እንዲህ አለ፡- ‹እናንተ የኢራቅ ሕዝቦች ሆይ! ከናንተ ጋር ያሉትን *ሙሳሒፎች* ያዟቸው፤ ደግሞም ደብቋቸው። አላህ እንዲህ ብሏልና ‘የሆነ ነገር የሚሰውር ሰው በዕለተ ትንሣኤ የሰወረውን ነገር ይዞ አላህን ይገናኘዋል።’ ስለዚህ አላህን *ሙሳሒፉን* ይዛችሁ ተገናኙት።› አዝ-ዙህሪ እንደተናገረው ‹ከተከበሩ የአላህ መልእክተኛ ባልደረቦች መካከል አንዳንዶቹ ይህንን የኢብን መስዑድ አመለካከት አልወደዱትም ነበር።›” (ሱናን አል-ቲርሚዚ፡ 3105)[145]

የኡሥማን ጥረት አንድ ቁርኣን ለመላው ዓለም ሕዝበ ሙስሊም በማዘጋጀት ሌሎች ቅጂዎችን በሙሉ ማስወገድ ነበር። ቀላሉ ማነፃፀርያ ክርስቲያኖች የማርቆስ፣ ሉቃስና ዮሐንስ ወንጌላትን ቀዳሚያን ጽሑፎች በማውደም ማቴዎስን ብቻ ቢያስቀሩ እንደማለት ነው። ይህ ነገሮችን ለማቅለል ቢጠቅም ክርስትና ግን ሁሉንም ምስክርነቶች በማግኘቱ የመረጃ ባለጠጋ ሆኗል። እስልምና ግን ሌሎች የቁርኣን ምስክርነቶችን በማጥፋቱ የመረጃ ድኻ ሆኗል።


የስታንፎርድ 07 የእጅ ጽሑፍ፤ ከስር የሚገኘው

## ዕድሜ ጠገብት የቁርኣን የእጅ ጽሑፎች

ክርስቲያኖች ስለ ሙት ባሕር ጥቅልሎችና ሌሎች የመጽሐፍ ቅዱስ የእጅ ጽሑፎች ያውቁ ይሆናል። ቁርኣንም ታዋቂ የሆኑ ዕድሜ ጠገብት የእጅ ጽሑፎች አሉት። በ1972 በየመን ሰነዓ ይገኝ የነበረ አሮጌ መስጊድ ሲታደስ ብዙ የቁርኣን የእጅ ጽሑፎች ተገኙ። እነዚህም ቀዳሚያን የቁርኣን

[145]*Sunan Al-Tirmithi, Dar Al-Kotob Al-ilmiyah, 2008, vol. 4, no. 3105, p. 134; also Ibn Sa'd, Kitab Al-Tabaqat Al-Kabir, vol. 2, p. 444*

ቁርጥራጮች መሆናቸው ተረጋገጠ። እነዚህ ቁርጥራጮች በቁርኣን ውስጥ የጽሑፍ ልዩነቶች መኖራቸውን ያረጋግጣሉ።

> ሰነዓ 1 (ስታንፎርድ 7) በመባል የሚታወቀው የእጅ ጽሑፍ የታችኛው መልኩ ከተለመደው የኡሥማን ቁርኣን ትውፊት ጋር አይጣጣምም። ይህ ማለት "ኡሥማናዊ ያልሆነ" ቁርኣን ነው ማለት ነው። C – 1 ተብሎ የተሰየመ ሌላ የቁርኣን ትውፊት ዘር ተደርጎ ተመድቧል።[146]

የጽሑፍ ልዩነት ያላቸው የሰነዓ ቁርአኖች ብቻ አይደሉም ነገር ግን ሌሎች ዕውቅ የቁርኣን የእጅ ጽሑፎችም ልዩነቶች ይታዩባቸዋል።[147] ስለዚህ ጥንታውያን የቁርኣን ጽሑፎች ልዩነቶች አሏቸው።

## የዛሬዎቹ ቁርአኖች

ሙስሊሞች በዚህ ዘመን የሚገኙት ቁርአኖች በሙሉ ፍፁም አንድ መሆናቸውን ይነግሩናል። ይህ ውሸት ነው። ዛሬ በዓለም ዙርያ ጥቅም ላይ እየዋሉ የሚገኙ የተለያዩ የቁርኣን ቅጂዎች ይገኛሉ።

ሁለቱ ዕውቅ ቅጂዎች የኢማም ሐፍስና የኢማም ዋርሽ ቁርአኖች ናቸው። የልዩነት ሁለት ምሳሌዎች እነሆ፡-

| የኢማም ሐፍስ ቁርኣን | የኢማም ዋርሽ ቁርኣን |
|---|---|
| تَقُولُونَ<br>ተቁሉነ<br>...እናንተ ትላላችሁ... 2፡140 | يَقُولُونَ<br>ያቁሉነ<br>...እነርሱ ይላሉ... |
| በቃላቱ መጀመርያ ላይ የተለያዩ ፊደላት ናቸው የሚገኙት። ይህ ልዩነት ትርጉሙን ከእናንተ ወደ እነርሱ ይለውጣል። | |

146 Behnam Sadeghi and Uwe Bergmann, "The Codex of a Companion of the Prophet and the Qur'an of the Prophet", *Arabica* 57, 2010, p. 344.

147 See answering-islam.org/PQ/A1.htm#AppendA for a comprehensive comparison between the Samarkand manuscript and the modern Qur'an

<table>
<tr><td>የኢማም ሐፍስ ቁርኣን</td><td>የኢማም ዋርሽ ቁርኣን</td></tr>
<tr><td>قَالَ<br><br>ቃለ<br><br>እርሱ (ሙሐመድ) አለ፤ “ጌታዬ ያውቃል...” 21፡4</td><td>قُلْ<br><br>ቁል<br><br>በል፤ ጌታዬ ያውቃል...</td></tr>
<tr><td colspan="2">እዚህ ጋ ያለው ልዩነት የግሡን ባለቤት ይለውጣል። በሐፍስ ቁርኣን ባለቤቱ ሙሐመድ ሲሆን በዋርሽ ቁርኣን ባለቤቱ አላህ ነው። ተመሳሳይ ልዩነት በ 21፡112 ላይ እናገኛለን።</td></tr>
<tr><td>ٱللَّهَ هُوَ ٱلْغَنِيُّ<br><br>አላህ ሁወ አል-ገኒይ<br><br>አላህ እርሱ የተብቃቃ 57፡24</td><td>ٱللَّهَ ٱلْغَنِيُّ<br><br>አላህ አል-ገኒይ<br><br>አላህ የተብቃቃ</td></tr>
<tr><td colspan="2">የሐፍስ ቁር አን ሁወ የምትል ጭማሪ ቃል አለው። ይህም ሰዋሰውን የተለየ ያደርገዋል። የሐፍስ አረፍተ ነገር ሲሆን የዋርሽ ደግሞ ያላለቀ ሀረግ ይሆናል። ተመሳሳይ ሀሳብን የሚገልጡ ቢሆንም ግን የተለያየ መንገድ ተጠቅመዋል።</td></tr>
<tr><td>هُمْ عِبَدُ ٱلرَّحْمَنِ<br><br>ሁም ዒበዱ ረህማን<br><br>እንረሱ የመሃሪው ባርያ ናቸው። 43፡19</td><td>هُمْ عِندَ ٱلرَّحْمَنِ<br><br>ሁም ዒንደ ረህማን<br><br>እነርሱ ከመሃሪው ዘንድ ናቸው 43፡19</td></tr>
</table>

<table>
<tr><td colspan="2">በእነዚህ ጥቅሶች ውስጥ የመካከለኛው ቃል መካከለኛ ፊደል የተለየ ነው። ይህ የነዚህን ቃላት ትርጉም በእጅጉ ይለውጣል። በሃፍስ እትም ቃሉ ባሮች ማለት ሲሆን በዋርሽ እትም ቃሉ ቅድመ ሁኔታ ነው "ጋር" ማለት ነው። ስለዚህም ጥቅሶቹ የተለየ ትርጉም አላቸው።</td></tr>
<tr><td>رَبِّهَا وَكُتُبِهِ<br>ረቢሃ ወ ኩቱቢሂ<br>ጌታዋና መጽሐፎቹ 66፡12</td><td>رَبِّهَا وَكِتَبِهِ<br>ረቢሃ ወ ኪታቢሂ<br>ጌታዋና መጽሐፉ 66፡12</td></tr>
<tr><td colspan="2">ልዩነቱ የሐፍስ ብዙ ቁጥር መጻሕፍት ሲሆን የዋርሽ ደግሞ ነጠላ ቁጥር መጽሐፍ ነው</td></tr>
</table>

በነዚህ ሁለቱ ቁርአኖች መካከል ወደ 1354 የሚሆኑ መሰል ልዩነቶች ይገኛሉ።[148]

በስፋት ጥቅም ላይ እየዋለ የሚገኘው የቁርኣን ቅጂ የግብፅ መደበኛ ዕትም (Egyptian standard edition) ይሰኛል። ይህ በሐፍስ ቅጂ ላይ የተመሠረተ ሲሆን እርሱ ራሱ ብዙ ቅጂዎች አሉት።

> መጠነኛ ማስተካከያዎች ተከትለው በሚገኙት ህትመቶች ውስጥ ተደርገዋል። አንዱ በ1924 የታተመው ሲሆን ሌላኛው ደግሞ በ1936 የታተመው ነው።[149]

## የሙስሊሞች ተቃውሞ

ለአብዛኞቹ ሙስሊሞች እነዚህን ልዩነቶች ካሳያችኋቸው በቂ ነው። አንድ ዓይነት ቁርኣን ብቻ እንዳለ እየተማሩ ስላደጉ እነዚህን ልዩነቶች ማሳየት ለእነርሱ አስደንጋጭ ነው። ስለ ቁርኣን ያላቸውን አመለካከት እንደገና እንዲያዩት ስለሚያደርጋቸው በዚያው ስለ መጽሐፍ ቅዱስም ያላቸውን አመለካከት እንደገና የማየት ዕድል ያገኛሉ። ሆኖም ይህንን ታሪክ ያጠኑት ሙስሊሞች ተከታዮቹን ምላሾች ሊሰጡ ይችላሉ።

*ምላሽ 1* ፡ እነዚህ ሁሉ ልዩነቶች ምንም የሚያመጡት ለውጥ የለም ምክንያቱም ቁርኣን መጀመርያ በንግግር የተሸመደደና ከዚያም በሁለተኛነት በጽሑፍ የሰፈረ ነውና። በዓለም ላይ

148 ለበለጠ መረጃ answering-islam.org/Green/seven.htm ተመልከቱ

149 Gabriel Said Reynolds, *The Qur'an in its Historical Context*, London: Routledge, 2008, p. 2.

የሚገኙት ቁርአኖች በሙሉ ቢወድሙ ቁርኣን መጀመርያ ስለተሸመደደ ምንም ችግር አይፈጥርም።

ይህ ምላሽ አቅጣጫን የማስለወጥ ስልት ነው ምክንያቱም መጽሐፍ የሰፈሩት ቁርአኖች አስቀድመው የተሸመደዱት ናቸውና። ይህ ምላሽ የተለያዩ የቁርኣን ዓይነቶች መኖራቸውን ማስተባበል አይችልም።

*ምላሽ 2* ፡ ሙሐመድ የተለያዩ የቁርኣን ቅጂዎች እንዲኖሩ ስለፈቀደ እነዚህ ሁሉ ቁርአኖች እኩል ትክክል ናቸው።

> (ሙሐመድ እንዲህ አለ) "ይህ ቁርኣን በሰባት የተለያዩ መንገዶች እንዲቀራ ተደርጎ ነው የወረደው ስለዚህ ከሰባቱ በተመቻቻሁ መንገድ ቅሩት።" (ሳሂህ አል-ቡኻሪ ቅፅ 6፣ መጽሐፍ 61፣ ቁጥር 514

ለዚህ ምላሽ ክርስቲያኖች ተከታዮቹን ነጥቦች መጥቀስ ይችላሉ፡-

1. ሙሐመድ የተለያዩ የቁርኣን ዓይነቶች እንዳሉ ፈቅዶ ከነበረ ሙስሊሞች አንድ ቁርኣን ብቻ ነው ያለው የሚለውን በመተው እውነቱን መናገር መጀመር አለባችሁ።
2. ሙሐመድ የተለያዩ የቁርኣን ዓይነቶች እንዲኖሩ ፈቅዶ ከነበረ የመጀመርያዎቹ ሙስሊሞች ልዩነቶችን ለማስወገድ ሲሉ ሁሉንም የቁርኣን ቅጂዎች ስለምን አቃጠሉ?
3. ቁርኣን ስለ እነዚህ ሁሉ ልዩነቶች ለምን አልተናገረም?
4. ፈጣሪ ቁርአኖች ውስጥ ልዩነቶች እንዲኖሩ አድርጎ አውርዷል ማለት ትርጉም አይሰጥም። ልክ እንደሌሎቹ መጻሕፍት ሁሉ ከዘመን ዘመን ሲሸጋገሩ የተፈጠሩ ልዩነቶች ናቸው።

ይህንን መረጃ እንዴት ነው መጠቀም ያለባችሁ? አንድ ሙስሊም መጽሐፍ ቅዱስ ተበርዟል የሚላችሁ ከሆነ እንዲህ በሉት፡- *መጽሐፍ ቅዱስ ተበርዟል ቁርኣን ግን በትክክል ተጠብቋል እያልክ ነውን?* መልሱ አዎን የሚል ነው። *ነገር ግን ያ እውነት አይደለም። የቀደሙት ሙስሊሞች ልዩነት ያላቸውን ቁርአኖች አቃጥለዋል። ዛሬ እንኳ ልዩነት ያላቸው ብዙ ቁርአኖች አሉ።*

ይህንን ክፍል ስለ ሙስጠፋ ነግሬያችሁ አጠቃልላለሁ። ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ እንዳልሆነና በመስቀል ላይ እንዳልሞተ እየተነገረው ያደገ ሰው ነው። ወንጌልን እንዳይቀበል በሚገባ ሰልጥኗል። ለዚህ ደግሞ የተማረው ምክንያት መጽሐፍ ቅዱስ ተበርዟል ነገር ግን ያልተበረዘ አንድ የቁርኣን ቅጂ አለ የሚል ነበር። ከዕለታት በአንዱ የኔን የክርክር ቪድዮ ይመለከት ነበር። በዚያ ክርክር ወቅት የተለያዩ ቁርአኖችን ከፍ አድርጌ እያሳየሁ ልዩነታቸውን ሳብራራ እታያለሁ። የሙስጠፋ ዓለም ወዲያውኑ ተቀየረ። መሪዎቹ ሲዋሹት

እንደነበር ተገለጠለት። ወንጌልን የማይቀበልበት ምክንያት ስላልነበረው ተቀብሎ ክርስቲያን ሆነ፤ አሁን በአገልግሎቴ እያገዘኝ ይገኛል።

## ቁርኣን ስለ መጽሐፍ ቅዱስ ምን ይላል?

እስልምና ስለ ዓለም ታሪክ የሚያስተምረው ከመጽሐፍ ቅዱስ የተለየ ነው። የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ *የመዋጀት ታሪክ* ይሰኛል። ይህም እግዚአብሔር ዓለምን ሲዋጅ የሚያሳይ ታሪክ ነው። እግዚአብሔር ዓለምን ፈጠረ ነገር ግን የሰው ልጆች በእግዚአብሔር ላይ ኃጢአትን በመሥራት ፍርድና ሞትን በዓለም ላይ አመጡ። በኃጢአት ስለተበከልን ራሳችንን ከዚህ ሁኔታ ማዳን አንችልም። እግዚአብሔር ከዓለም አብረሃምን መርጦ፣ የእሥራኤልን ሕዝብ ካዘጋጀ በኋላ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ወደ ዓለም በመምጣት እኛን አዳነን። እግዚአብሔር ወደ ራሱ መልሶናል። በኢየሱስ በኩል ስላዳነን ፍጥረት ሁሉ በዚህ ማዳን ውስጥ ይካፈላል።

በእስልምና የዓለም ታሪክ የተለየ ነው። *የነቢይነት ታሪክ* ይሰኛል። በዚህ ታሪክ መሠረት ፈጣሪ ዓለምን ፈጥሮ ሰውን በውስጡ አስቀምጧል። ከዚያም ለሁሉም ሕዝቦች ነቢያትንና መልእክተኞችን አስነስቷል። ነቢያቱም ስለ ፈጣሪ ለሕዝባቸው መመርያን ሰጥተዋል። አዳም የመጀመርያው ነቢይ ነበር። እያንዳንዳቸው ነቢያት ለሕዝባቸው የሚያስተምሯቸው መጻሕፍት ተሰጥቷቸዋል። በጊዜ ሒደት እነዚህ መጻሕፍት "ጠፍተዋል፣ ተረስተዋ፤፣ ተጥለዋል ወይንም ተሸረዋል"።[150] ዓለም የነበረበት ችግርና ሁኔታ ይህንን ይመስላል። ከፈጣሪ ዘንድ የሆነ ንፁህ መጽሐፍ ያልነበረው ዓለም ነበር። ለዚህ ዓለም ነው ፈጣሪ ሙሐመድን በማስነሳት ቁርኣንን የሰጠው። እርሱ ደግሞ በትክክል ተጠብቋል። ፈጣሪ የሰጣቸው የመጨረሻዎቹ መጽሐፍና ሃይማኖት በመሆናቸው በዓለም ላይ ያለ ሰው ሁሉ ሊቀበላቸውና ሊከተላቸው ይገባል።

ሙስሊሞች ስለ ክርስትናና ስለ መጽፍ ቅዱስ የሚገነዘቡት ይህንን ሲሆን ቁርኣን ስለመጽሐፍ ቅዱስ ይህንን የሚያስተምር ይመስላቸዋል ነገር ግን ቁርኣን ስለ መጽሐፍ ቅዱስ የሚያስተምረው ይህንን አይደለም። ሙስሊም መሪዎች የቁርኣንን ታሪክ እንደሚያዛቡት ሁሉ ቁርኣን ስለ መጽሐፍ ቅዱስ የሚናገረውንም ያዛባሉ። ይህ ማለት ሙስሊም ጓደኛችሁ ቁርኣን መጽሐፍ ቅዱስ መበረዙን የሚያስተምር ይመስለዋል ማለት ነው። ቁርኣን ይህንን እንደማይል ለእነርሱ ማሳየት መጽሐፍ ቅዱስን ማንበብ እንዲጀምሩ ይረዳቸዋል። በዚህ ክፍል ቁርኣን ስለ መጽፍ ቅዱስ ምን እንደሚል እንመለከታለን።

## የፈጣሪ ቅዱሳት መጻሕፍት

---

150 Hammudah Abdulati, *Islam in Focus*, Riyadh, Saudi Arabia: International Islamic
Publishing House, 2001, p. 12.

ቁርኣን ከእርሱ በተጨማሪ ሌሎች የፈጣሪ ቅዱሳት መጻሕፍት መኖራቸውን ይናገራል። እነዚህ መጻሕፍት ሙሴ፣ ዳዊትና ኢየሱስን ከመሳሰሉት ከሙሐመድ በፊት ከነበሩት ነቢያት ጋር የመጡ ናቸው። ቁርኣን መጽሐፍ ቅዱስን ሲጠቅስ ጠቅለል ባለ መንገድ ነው።[151] ክርስቲያኖችና አይሁድ እጅ የሚገኝ *መጽሐፍ* ወይም *ጥቅልሎች*[152] ወይም አንዳንዴ ተውራት፣ ኢንጂልና ዘቡር በሚሉ ስሞች ተጠቅሷል።[153] ከነዚህ መጽሐፍ በቀጥታ የማይጠቅስ ሲሆን የውጪ ተመልካች ዕይታ ነው ያለው። ጥያቄው ሙስሊሞች ስለ መጽሐፍ ቅዱስ ምን ዓይነት አመለካከት ሊኖራቸው ይገባል? የሚል ነው።

በዚህ ላይ ቁርኣን በጣም ግልጽ ነው፤ ሙስሊሞች መጽሐፍ ቅዱስን ማክበርና በእርሱና በቁርኣን መካከል ምንም ዓይነት አድልዎ ማድረግ የለባቸውም።

> "እላንተ ያመናችሁ ሆይ! በአላህና በመልክተኛው በዚያም በመልክተኛው ላይ ባወረደው መጽሐፍ፣ በዚያም ከበፊቱ ባወረደው መጽሐፍ፣ እመኑ፤ በአላህና በመላክቱም፣ በመጽሐፎቹም፣ በመልክተኞቹም፣ በመጨረሻውም ቀን የካደ ሰው፣ (ከሰውነት) የራቀን መሳሳት በእርግጥ ተሳሳተ።" (ቁርኣን 4፡136)
>
> "የመጽሐፉን ባለቤቶችም በዚያች እርሷ መልካም በሆነችው ክርክር እንጂ አትከራከሩ፤ ከነሱ ነዚያን የበደሉትን ሲቀር በሉም ፡- በዚያ ወደኛ በተወረደው፣ ወደናንተም በተወረደው አመንን፤ አምላካችንም አምላካችሁም አንድ ነው፤ እኛም ለርሱ ታዛዦች ነን።" (ቁርኣን 29፡46)
>
> "«በአላህና ወደኛ በተወረደው (ቁርኣን) ወደ ኢብራሂምም ወደ ኢስማዒልና ወደ ኢስሐቅም ወደ ያዕቁብና ወደ ነገዶቹም በተወረደው በዚያም ሙሳና ዒሳ በተሰጡት በዚያም ነቢያት ሁሉ ከጌታቸው በተሰጡት ከነርሱ በአንድም መካከል የማንለይ ስንኾን አመንን፤ እኛም ለርሱ (ለአላህ) ታዛዦች ነን» በሉ።" (ቁርኣን 2፡ 136)

እነዚህ ጥቅሶች ሙስሊሞች ያለ ምንም አድልዎ ሁሉንም ቅዱሳት መጻሕፍት እንደ ቁርኣን ሁሉ እንዲቀበሉ የሚያዝዙ ሃይማኖታዊ መግለጫዎች ናቸው። ይህ ማለት ሙስሊሞች መጽሐፍ ቅዱስን መከተል አለባቸው ማለት አይደለም፤ መከተል ያለባቸው ቁርኣንን ነው፤ መጽሐፍ ቅዱስን ከቁርኣን እኩል መመልከት ይኖርባቸዋል፤ እኩል ሲመለከቱ ግን ለሌላ ሕዝብ እንደተሰጠ መጽሐፍ አድርገው ነው።

---

151 ሙሐመድ ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር ብዙ ትውውቅ ስላልነበረው ቁርኣን መጽሐፍ ቅዱስን ሲጠቅስ እንደ ውጪ ሰውና አሻሚ በሆነ መንገድ ነው። አዲስ ኪዳን ብሉይ ኪዳንን በሚጠቅስበት መንገድ ሲጠቅስ አይታይም፤ ከዚያ ይልቅ የራሱን ሕይወት በሚገልፅ መንገድ የመጽሐፍ ቅዱስንና ሌሎች የክርስቲያን እንዲሁም የአይሁድ ታሪኮች በእጃዙር ይጠቅሳል። በመጽሐፍ ቅዱስ መጻሕፍትና የአፖክሪፋ ታሪኮች መካከል ወይንም በክርስቲያንና አይሁድ ማብራርያዎች መካከል ልዩነት ሳያደርግ ሁሉንም አንድ አስመስሎ ያቀርባል።

152 ቁርኣን 53:36

153 ቁርኣን 3:3, 17:55

“ወደ አንተም መጽሐፉን ከበፊቱ ያለውን መጽሐፍ አረጋጋጭና በርሱ ላይ ተጠባባቂ ሲሆን በውነት አወረድን፤ በመካከላቸውም፣ አላህ ባወረደው ሕግ ፍረድ፤ እውነቱም ከመጣልህ በኋላ ዝንባሌዎቻቸውን አትከተል። ከናንተ ለሁሉም ሕግንና መንገድን አደረግን፤ አላህም በሻ ኖሮ አንድ ሕዝብ ባደረጋችሁ ነበር፤ ግን በሰጣችሁ ሕግጋት ሊሞክራችሁ፣ (ለያያችሁ)፤ በጎ ሥራዎችንም (ለመሥራት) ተሽቀዳደሙ፤ መመለሻችሁ በጠቅላላ ወደ አላህ ነው፤ በርሱም ትለያዩበት የነበራችሁትን ነገር ይነግራችኋል።” (ቁርኣን 5፡48)

## የመጽሐፍ ቅዱስ ሥልጣን በቁርኣን ውስጥ

ቁርኣን ብዙ ጊዜ መጽሐፍ ቅዱስን ሁሉም ሰው ሊመለከተው እንደሚገባ ሥልጣናዊ መጽሐፍ ይጠቅሰዋል። ስለዚህ አይሁድ የራሳቸውን ቶራህ እንዲታዘዙ ተነግሯቸዋል፡-

“እነርሱም ዘንድ ተውራት እያለች በውስጧ የአላህ ፍርድ ያለባት ስትሆን እንዴት ያስፈርዱሃል? … እኛ ተውራትን በውስጥዋ መምሪያና ብርሃን ያለባት ስትሆን አወረድን፤ እነዚያ ትእዛዝን የተቀበሉት ነቢያት በነዚያ ይሁዳውያን በሆኑት ላይ በርሷ ይፈርዳሉ፤ ሊቃውንቱና ዐዋቂዎቹም ከአላህ መጽሐፍ እንዲጠብቁ በተደረጉትና በርሱም ላይ መስካሪዎች በሆኑት (ይፈርዳሉ)፤ ሰዎችንም አትፍሩ፤ ፍሩኝም፤ በአንቀጾቼም አነስተኛን ዋጋ አትለውጡ፤ አላህም ባወረደው ነገር ያልፈረደ ሰው እነዚያ ከሐዲዎች እነርሱ ናቸው። … አላህም ባወረደው ነገር የማይፈርድ ሰው፤ እነዚያ በደለኞቹ እነርሱ ናቸው።” (ቁርኣን 5፡43-45)

ልክ እንደዚሁ ክርስቲያኖችም ወንጌልን እንዲታዘዙ ተነግሯቸዋል፡-

“የኢንጅልም ባለቤቶች በውስጡ አላህ ባወረደው ሕግ ይፍረዱ፤ አላህም ባወረደው የማይፈርድ ሰው፣ እነዚያ አመጠኞች እነርሱ ናቸው።” (ቁርኣን 5፡47)

ለአይሁድና ለክርስቲያኖች ቁርኣን እንዲህ ይላል፡-

“እላንተ የመጽሐፉ ባለቤቶች ሆይ! ተውራትንና ኢንጅልን፣ ከጌታችሁም ወደናንተ የተወረደውን እስከምታቆሙ (እስከምትሠሩባቸው) ድረስ በምንም ላይ አይደላችሁም በላቸው፤ ከጌታህም ወደ አንተ የተወረደው ቁርኣን ከነሱ ብዙዎቹን ትዕቢትንና ክሕደትን በእርግጥ ይጨምርባቸዋል፤ በከሐዲያን ሕዝቦችም ላይ አትዘን።” (ቁርኣን 5፡68)

ስለዚህ መጽሐፍ ቅዱስ በቁርኣን ውስጥ የተጠቀሰው አይሁድና ክርስቲያኖች የእግዚአብሔርን ፈቃድ የሚያውቁበት ሥልጣናዊ መጽሐፍ ተደርጎ ነው። ሆኖም መጽሐፍ ቅዱስን መጥቀስ ያለባቸው አይሁድና ክርስቲያኖች ብቻ አይደሉም። ሙሐመድና ሙስሊሞች የቁርኣንን እውነተኛነት ከተጠራጠሩ ሊያጣቅሱት ይችላሉ፡-

> "ወደ አንተም ካወረድነው በመጠራጠር ውስጥ ብትሆን እነዚያን ከአንተ በፊት መጽሐፉን የሚያነቡትን ጠይቅ። እውነቱ ከጌታህ ዘንድ በእርግጥ መጥቶልሃል። ከተጠራጣሪዎቹም አትሁን።" (ቁርኣን 10፡94)[154]

መጽሐፍ ቅዱስ ቁርኣን ከፈጣሪ ዘንድ መሆኑን የሚያረጋግጥ ባለ ሥልጣን ነው፡-

> "እላንተ መጽሐፉ የተሰጣችሁ ሆይ! ፊቶችን ሳናብስና በጀርባዎች ላይ ሳንመልሳቸው፣ ወይም የሰንበትን ባለቤቶች (ያፈረሱትን) እንደረገምን ሳንረግማቸው በፊት ከናንተ ጋር ያለውን የሚያረጋግጥ ኾኖ ባወረድነው (ቁርኣን) እመኑ፣ የአላህም ትዕዛዝ ተፈፃሚ ነው።" (ቁርኣን 4፡47)

በመጨረሻም ሙሐመድ በመጽሐፍ ቅዱስ እንደተነገረ ቁርኣን ይናገራል፡-

> "ለነዚያ ያንን እነሱ ዘንድ በተውራትና በኢንጂል ተጽፎ የሚያገኙትን የማይጽፍና የማያነብ ነብይ የሆነውን መልክተኛ የሚከተሉ ለሆኑት (በእርግጥ እጽፋታለሁ) ..." (ቁርኣን 7፡157)[155]

ቁርኣን መጽሐፍ ቅዱስን ተዓማኒነት የሌለው አድርጎ የሚቆጥር ቢሆን ኖሮ ከላይ ከተጠቀሱት ሐሳቦች መካከል አንዱንም ባልተናገረ ነበር። ቁርኣን መጽሐፍ ቅዱስን እንደ ተዓማኒ ቅዱስ መጽሐፍ ያቀርባል፤ በዚያ መንገድም ጥቅም ላይ መዋል እንዳለበት ያሳስባል።

## ሙሐመድና መጽሐፍ ቅዱስ

ሙሐመድ መጽሐፍ ቅዱስን ልክ ቁርኣን በተናገረው መንገድ እንዳከበረው እስላማዊ ታሪክ ይናገራል።

> አብዱላህ ኢብን ዑመር እንዳወራው አይሁድ የአላህን መልእክተኛ እንዲጎበኛቸው ወደ ቁፍ ጠሩት። እርሱም በትምሕርት ቤታቸው ጎበኛቸው። ... ለአላህ መልእክተኛ ወንበር አመጡለት እርሱም ተቀመጠበት ከዚያም ተውራትን አምጡልኝ አለ። እነርሱም አመጡለት። ከዚያም ከወንበሩ ላይ በመነሳት ተውራትን አስቀምጦበት እንዲህ አለ፡- በአንተና አንተን በገለጠው (አምላክ) አምናለሁ። (ሱናን አቡ ዳውድ 4449፣ መጽሐፍ 38፣ ቁጥር 4434)

ሙሐመድ መጽሐፍ ቅዱስ እንደተበረዘና ተቀባይነት እንደሌለው ቢያምን ኖሮ ይህንን ባላደረገ ነበር፤ ሙስሊሞችም መሰል ታሪኮች ከሚያምኑት ነገር ጋር ስለሚጣረስ እንዲህ ያለ ታሪክ ፈጥረው ሊናገሩ አይችሉም።

## ሙስሊሞች መጽሐፍ ቅዱስን በተመለከተ የሚያቀርቡት የተቃውሞ ሙግት

---

154 ቁርአብ 2:111, 3:93, 21:7

155 ቁርኣን 20:133, 26:196-197

ቁርኣን ሙስሊሞች ያለ ምንም ልዩነት ቅዱሳት መጻሕፍትን በሙሉ እንዲቀበሉ እንደሚያዛቸው ተመልክተናል። ሙሐመድም ያደረገው ይህንኑ ነበር። ክርስቲያኖችና አይሁድ መጽሐፍ ቅዱስን እንዲታዘዙ ያዛቸዋል፤ የቁርኣንንና የሙሐመድን እውነተኛነት ለማረጋገጥ መጽሐፍ ቅዱስን ይጠቀማል። ይሁን እንጂ የተለመደው የሙስሊሞች ምላሽ ቁርኣን በሁለት ምክያቶች ይህንን ሊያስተምር አይችልም የሚለው ነው፡-

*ምክንያት 1* ፡ ቁርኣን ተውራት፣ ዘቡርና እንጂል ሲል *ኦሪጅናሉን* ለማለት እንጂ ዛሬ በክርስቲያኖችና በአይሁድ እጅ የሚገኘውን የተበረዘውን ለማለት አይደለም። ሙሰሊሞች በኦሪጅናል መጽሐፍ ቅዱስ ያምናሉ፡-

> እኛ ሙስሊሞች የምናምነው ተውራት የአይሁድና ክርስቲያኖች "ቶራ" አይደለም ... እንዲሁም ዘቡር (መዝሙር) ከፈጣሪ ዘንድ ለዳዊት እንደተገለጠ እናምናለን ነገር ግን ዛሬ የሚገኘው ከስሙ ጋር የተያያዘው መዝሙር ግን ያ መገለጥ አይደለም ... እንጂልስ? በሕይወት ዘመኑ ኢየሱስ አንድ ቃል እንኳ አልጻፈም፤ ማንንም እንዲጽፍ አላዘዘም። ዛሬ ወንጌል ተብለው የተላለፉት የማይታወቁ ሰዎች ሥራዎች ናቸው![156]

ስለዚህ በእስልምና መሪዎች መሠረት ሙስሊሞች ሊያምኗቸው የሚገቡት ቅዱሳት መጻሕፍት የጠፉት ኦሪጅናሎች እንጂ ዛሬ በአይሁድና በክርስቲያኖች እጅ የሚገኙት የተበረዙት መጻሕፍት አይደለም።

ይህ ትምሕርት ሐሰትና ቁርኣንን የሚጻረር ነው። ቁርኣን በሐሳባዊ ኦሪጅናሎችና ዛሬ በአይሁድና በክርስቲያኖች እጅ በሚገኙት መጻሕፍት መካከል ልዩነት አያደርግም ይልቅ እውነታው የዚያ ተቃራኒ ነው። ለኢየሱስ ተሰጠ የተባለው ወንጌል ክርስቲያኖች እጅ የሚገኘውና ሊታዘዙት የተገባው ነው፡-

> "በፈለጎቻቸውም (በነቢያቶቹ ፈለግ) ላይ የመርየምን ልጅ ዒሳን ከተውራት በስተፊቱ ያለውን አረጋጋጭ ሲሆን፣ አስከተልን፤ ኢንጂልንም በውስጡ ቀጥታና ብርሃን ያለበት በስተፊቱ ያለችውን ተውራትንም የሚያረጋግጥ ለጥንቁቆችም መሪና ገሣጭ ሲሆን ሰጠነው። የኢንጅልም ባለቤቶች በውስጡ አላህ ባወረደው ሕግ ይፍረዱ፤ አላህም ባወረደው የማይፈርድ ሰው፣ እነዚያ አመጠኞች እነርሱ ናቸው።" (ቁርኣን 5፡46-47)

ክርስቲያኖች *የወንጌል ሰዎች* ተብለው ተጠርተዋል፣ በተደጋጋሚም የአይሁድንና የክርስቲያኖችን ቅዱሳት መጻሕፍት በእጃቸው የሚገኙት ቅዱሳት መጻሕፍት እንደሆኑ ይገልጻል።

---

156 Ahmed Deedat, *Is the Bible God's Word?*, ch. 3, pp. 7-8

> "እላንተ መጽሐፉ የተሰጣችሁ ሆይ! ፊቶችን ሳናብስና በጀርባዎች ላይ ሳንመልሳቸው፣ ወይም የሰንበትን ባለቤቶች (ያፈረሱትን) እንደረገምን ሳንረግማቸው በፊት ከናንተ ጋር ያለውን የሚያረጋግጥ ኾኖ ባወረድነው (ቁርኣን) እመኑ፣ የአላህም ትዕዛዝ ተፈፃሚ ነው።" (ቁርኣን 4፡47)

> "ለነዚያ ያንን እነሱ ዘንድ በተውራትና በኢንጂል ተጽፎ የሚያገኙትን የማይጽፍና የማያነብ ነብይ የሆነውን መልክተኛ የሚከተሉ ለሆኑት (በእርግጥ እጽፋታለሁ)፤ በበጎ ሥራ ያዛቸዋል፤ ከክፉም ነገር ይከለክላቸዋል..." (7፡157)

> "ከነሱም ጋር ያለውን (መጽሐፍ) አረጋጋጭ የኾነ መጽሐፍ ከአላህ ዘንድ በመጣላቸው ጊዜ (ከመምጣቱ) በፊት በነዚያ በካዱት ላይ ይረዱበት የነበሩ ሲኾኑ ያወቁት ነገር በመጣላቸው ጊዜ በርሱ ካዱ። የአላህም ርግማን በከሓዲዎች ላይ ይኹን።" (2፡89)

ስለዚህ ቁርኣን በቅዱሳት መጻሕፍት መካከል ልዩነት እንደማያደርግ ሲናገር ዛሬ በአይሁድና በክርስቲያኖች እጅ የሚገኙትን ቅዱሳት መጻሕፍት በተመለከተ ነው።

*ምክንያት 2* ፡ ቁርኣን አይሁድ መጽሐፍ ቅዱስን በርዘውታል ይላል።

> "ለነዚያም መጽሐፉን በእጆቻቸው ለሚጽፉና ከዚያም በርሱ ጥቂትን ዋጋ ሊገዙበት «ይህ ከአላህ ዘንድ ነው» ለሚሉ ወዮላቸው። ለነርሱም ከዚያ እጆቻቸው ከጻፉት ወዮላቸው። ለነሱም ከዚያ ከሚያፈሩት (ኃጢኣት) ወዮላቸው።" (ቁርኣን 2፡79)

ሙስሊም መሪዎች መጽሐፍ ቅዱስ መበረዙን ለማመልከት በተደጋጋሚ የሚጠቅሱት ጥቅስ ይህንን ነው። ይሁን እንጂ ጥቅሱ መጽሐፍ ቅዱስ እንደተበረዘ አይናገርም። አንዳንድ አይሁድ ቅዱሳት መጻሕፍትን ለራሳቸው ትርፍ ሲሉ እንደሚጽፉ ነው የሚናገረው። ከዚህ ጥቅስ በኋላ ዘግየት ብሎ ስለ መጽሐፍ ቅዱስ ያለውን እሳቤ እንዲህ ያስቀምጣል፡-

> "«በአላህና ወደኛ በተወረደው (ቁርኣን) ወደ ኢብራሂምም ወደ ኢስማዒልና ወደ ኢስሐቅም ወደ ያዕቁብና ወደ ነገዶቹም በተወረደው በዚያም ሙሳና ዒሳ በተሰጡት በዚያም ነቢያት ሁሉ ከጌታቸው በተሰጡት ከነርሱ በአንድም መካከል የማንለይ ስንኾን አመንን፤ እኛም ለርሱ (ለአላህ) ታዛዦች ነን» በሉ።" (ቁርኣን 2፡ 136)

ስለዚህ ሱራ 2፡79 መጽሐፍ ቅዱስ እንደተበረዘ እንደሚናገር በማስመሰል የሚተረጉሙ ሰዎች ከቁርኣን በተቃራኒ እየተረጎሙ ነው። ቁርኣን ራሱን በራሱ እንዲተረጉም መፍቀድ ይኖርብናል።

በመጨረሻም ቁርኣን እንዲህ ይላል፡-

“እርሱ ያ መጽሐፉን የተብራራ ኾኖ ወደእናንተ ያወረደ ሲኾን «ከአላህ ሌላ ዳኛን እፈልጋለሁን» (በላቸው)። እነዚያም መጽሐፍን የሰጠናቸው እርሱ ከጌታህ ዘንድ በእውነት የተወረደ መኾኑን ያውቃሉ። ከተጠራጣሪዎቹም አትኹን። የጌታህም ቃላት እውነተኛና ትክክለኛ ስትኾን ተፈጸመች። ለቃላቱ ለዋጭ የለም። እርሱም ሰሚው ዐዋቂው ነው።” (ቁርአን 6፡114-115)

ስለዚህ ከቁርኣን አኳያ መጽሐፍ ቅዱስን ላለመቀበል ወይንም ተዓማኒ አይደለም ለማለት የሚያበቃ ምንም ነገር የለም። አንዳንድ ሙስሊም ሊቃውንት ይህንን ሃቅ አምኖ ለመቀበል ዝግጁዎች ናቸው፡-

> የአይሁድና የክርስቲያኖች ቅዱሳት መጻሕፍት በነቢዩ ዘመን ከነበረው ጋር አንድ በሆነ መንገድ ተጠብቀው ስለሚገኙ ቁርኣን የጠቀሳቸው ተውራትና ኢንጂል በሙሴና በኢየሱስ ዘመን የነበሩት “ንፁህ” ተውራትና ኢንጂል ናቸው ብሎ መሟገት ከባድ ነው። ጽሑፎቹ ይብዛም ይነስም በሰባተኛው ክፍለ ዘመን በነበረው መልካቸው ዛሬም የሚገኙ ከሆነ ቁርኣን በዚያን ዘመን ያሳያቸው ክብር ዛሬም ተመሳሳይ መሆን አለበት። ጠበሪ፣ ራዚ፣ ኢብን ተይሚያና አልፎም ቁጥብን የመሳሰሉት ብዙ የቁርኣን ሐታቾች ይህንን አመለካከት ወደ መጋራት ያዘነበሉ ናቸው። የአይሁድና የክርስቲያኖችን ቅዱሳት መጻሕፍት የማጣጣል አመለካከት በሙሉ የቁርኣንና የዋና ዋና ተፍሲሮች ድጋፍ ያለው አይመስልም።[157]

## የሙስሊሞች አጣብቂኝ

እስልምና አጣብቂኝ ውስጥ ነው። እርሱም ቁርኣን ሙስሊሞች በመጽሐፍ ቅዱስና በቁርኣን መካከል ልዩነት እንዳያደርጉ ማዘዙና መጽሐፍ ቅዱስ ሙሐመድንም ሆነ ቁርኣንን የሚያረጋግጥ ባለ ሥልጣን መሆኑን መናገሩ ነው። ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስን ስናነብ ሁለቱንም አያደርግም።

ሙስሊም መሪዎች ለዚህ አጣብቂኝ ምላሽ የሰጡት ሙሐመድን በመጠራጠር ሳይሆን አይሁድና ክርስቲያኖችን ተወቃሽ በማድረግ ነው። ምላሻቸው መጽሐፍ ቅዱስ የቁርኣንን ትምሕርት የማያጸድቀው ክርስቲያኖች ስለለወጡት ነው የሚል ነው። የክርስቲያኖች ስህተት ነው። ክርስቲያኖች መጽሐፍታቸውን የመለወጥ ወንጀል ፈፅዋል። የእስልምና ነገረ መለኮት የእስልምና ብሒል ሐሰት መስሎ የመታየቱን ሁኔታ ለማብራራት ይህንን መሰል ማብራርያ አዳብሯል። ለዚህ ነው ሙስሊሞች መጽሐፍ ቅዱስን ሲተቹ የሚታዩት። ነገር ግን ይህ ፈር የለቀቀ አመክንዮ ነው። ለራስህ ችግር ሌላውን ተጠያቂ ማድረግ ይባላል። ለሙሐመድ ስህተት ክርስቲያኖችን ተጠያቂ ማድረግ ነው።

157 Abdullah Saeed, “The Charge of Distortion of Jewish and Christian Scriptures” *Muslim World*, Fall 2002, vol. 92, issue 3/4, p. 419.

ለክርስቲያኖች መልካሙ ዜና ሙስሊሞች መጽሐፍ ቅዱስ ላይ ጥቃት በሚሰነዝሩበት መንገድ ብሉይ ኪዳንን ማጥቃት የማያስፈልገን መሆኑ ነው። ኢየሱስ የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ለእርሱና ለትልዕኮው ምስክር መሆናቸውን ተናግሯል፡-

> "እርሱም፡- ከእናንተ ጋር ሳለሁ በሙሴ ሕግና በነቢያት በመዝሙራትም ስለ እኔ የተጻፈው ሁሉ ይፈጸም ዘንድ ይገባል ብዬ የነገርኋችሁ ቃሌ ይህ ነው አላቸው።" (ሉቃስ 24፡44)

እውነት ነው ምስክሮች ናቸው። እርሱ ቃል የተገባው መሲህ ነው። የመዋጀትን ትራኬ ከግብ አድርሷል። የቤተ መቅደሱ፣ የክህነትና የመሥዋዕት ፍፃሜ ነው። እውነተኛው የእግዚአብሔር ምስል፣ እውነተኛው ሰው ነው። ለዚህ ነው መጽሐፍ ቅዱስ ብሉይና አዲስ ኪዳናትን የያዘው። የኢየሱስ ብሒሎች ሁሉ እውነት በመሆናቸው ክርስቲያኖች ሁሉንም ቅዱሳት መጻሕፍት ያነባሉ። የእስልምና ብሒል ግን ሐሰት በመሆኑ ሙስሊሞች ቅዱሳት መጻሕፍትን ያጣጥላሉ።

የዚህ ትግበራ ግልፅ ነው፤ ሙስሊሞች መጽሐፍ ቅዱስን ሲክዱና ሲያጠቁ እምነታቸውን እየካዱ ነው። ሙስሊም ወዳጆቻችሁ ይህንን የሚያደርጉ ከሆነ ይህንን እውነታ ልታስገነዝቧቸው ትችላላችሁ። በዚህ ክፍል የተጠቀሱትን ማጣቀሻዎች ለዚህ ዓላማ ተጠቀሙ።


## የመጽሐፍ ቅዱስ ተዓማኒነት

ይህ ምዕራፍ የሚጀምረው ሙስሊሞች መጽሐፍ ቅዱስን የሚያጠቁ ከሆነ ምላሽ ለመስጠት ትክክለኛው የጅማሬ ቦታ መጽሐፍ ቅዱስን መከላከል ሳይሆን ቅድም ግንዛቤዎቻቸውን ማስተካከል መሆኑን በመግለፅ ነው። እነዚህ ቅድመ ግንዛቤዎች አንድ ያልተለዋወጠ ቁርኣን ብቻ አለ እንዲሁም ቁርኣን መጽሐፍ ቅዱስ መበረዙን ይናገራል የሚሉት ናቸው። እነዚህን ቅድመ ግንዛቤዎች ከመለስንና እውነታው ግልፅ ከሆነ በኋላ ክርስቲያኖችና ሙስሊሞች ስለ መጽሐፍ ቅዱስ ቅንነትን የተሞላ ውይይት ለማድረግ ዝግጁዎች ይሆናሉ። እንዲያውም ሙስሊሞች የተለያዩ የቁርኣን ቅጂዎችንና ቁርኣን ስለ መጽሐፍ ቅዱስ ምን እንደሚል አንዴ ካሳያችኋቸው ሌላ ሥራ ሳያስፈልጋችሁ መጽሐፍ ቅዱስን ከናንተ ጋር ማንበብ ሊጀምሩ ይችላሉ። ሆኖም መጽሐፍ ቅዱስ ላይ የሚያቀርቧቸውን ተቃውሞዎችና እንዴት ምላሽ እንደምትሰጡ ማወቅ ያስፈልጋችኋል። አሁን የምንመለከተው እርሱን ይሆናል።

የመጽሐፍ ቅዱስ ተዓማኒነት ሰፊ ርዕስ ሲሆን የጽሑፍ አስተላለፍ፣ የቀኖና አመጣጥ፣ ታሪክ፣ የጸሐፊያን ማንነት፣ ውስጣዊ ተግባቦትና ነገረ መለኮትን ያጠቃልላል። በዚህ ክፍል እነዚህ ሁሉ በጥልቀት ማየት ያዳግታል። በዚህያ ፋንታ ከየት መጀመር እንዳለባችሁ ለማሳየት ያህል ዋና ጉዳዮችን በተመለከተ አጠር ያለ ማውጫ መሰል አቀርባለሁ። ለበለጠ መረጃ ተከታዮቹን መጻሕፍት ተመልከቱ፡-

# የመጽሐፍ ቅዱስ ጽሑፎች

የመጽሐፍ ቅዱስ ጽሑፍ መለወጥ አለመለወጡን እንዴት ነው ማወቅ የምንችለው? ማስረጃዎችን በማጤን ይህንን የሚያረጋግጥ ነገር መኖር አለመኖሩን ማየት ያስፈልገናል። ነገር ግን ማስረጃው ምንድነው? ከቦታ አንፃር አዲስ ኪዳንን ብቻ የምንመለከት ሲሆን ማስረጃዎቹ ሁለት ናቸው፤ የመጀመርያው በኦሪጅናል ቋንቋዎቹ የተጻፉ *ጥንታውያን የእጅ ጽሑፎች* አሉ። ከተለያዩ ቦታዎች የተገኙ በቀደምት የቤተ ክርስቲያን ክፍለ ዘመናት የተጻፉ በርካታ ጽሑፎች አሉ። ሁለተኛ *ጥንታዊያን ትርጉሞች* ይገኛሉ። እነዚህ ትርጉሞችም በቀደምት የክርስትና ክፍለ ዘመናት የተዘጋጁ በመሆናቸው የአዲስ ኪዳንን ትክክለኛነት ያስረዳሉ። ሦስተኛ *ጥንታውያን ጥቅሶች* ይገኛሉ። ከክርስትና ጅማሬ አንስቶ የቤተ ክርስቲያን አበው ተብለው የሚታወቁ ክርስቲያን መምህራን አዲስ ኪዳንን በጽሑፎቻቸው ውስጥ ጠቅሰዋል። እነዚህም ለአዲስ ኪዳን ጥንታዊ ጽሑፎች ሌላ ምስክር ናቸው። እነዚህ ሦስትዮሻዊ ማስረጃዎች ጥንታዊ ለሆነው የመጽሐፍ ቅዱስ መልክ ማስረጃና ምስክሮች ናቸው።




ይህ ማስረጃ አዲስ ኪዳን በትክክል የተጠበቀ መሆኑን ያረጋግጣል። ወንጌላት ከእንደገና የተጻፉ መሆናቸውን የሚያመለክት ምንም ዓይነት ማስረጃ የለም። የመሲሁ ኢየሱስ ትምሕርቶች፣ የእግዚአብሔር ልጅ፣ ለኃጢአታችን ስል የተሰቀለ፣ ከሞት ተነሣ፣ የእግዚአብሔርን መንግሥት በምድር ላይ መሠረተ፣ ለፍርድ ተመልሶ ይመጣል የሚሉት ወጥና ያልተለወጡ መልእክቶች ናቸው። ክርስቲያኖች ስለዚህ ጉዳይ እርግጠኞች መሆን ይችላሉ። ይህ ማለት ግን በእጅ በተጻፉት ጽሑፎች መካከል ጥቃቅን ልዩነቶች የሉም ማለት አይደለም። ትልቅ መጠን ያላቸው ጽሑፎች በእጅ ሲገለበጡ ግድፈቶች ይፈጠራሉ። እነዚህ ግድፈቶች ሆነ ብለው የተደረጉ ወይንም ድንገቴ ሊሆኑ ይችላሉ ነገር ግን ሌሎች ጽሑፎችን ጎን ለጎን በማስተያየት ሃቀኝነታቸው ስለሚጣራ የመጨረሻ አይደሉም። ምስሉ ይህንን ሒደት ያሳያል።

ለምሳሌ ያህል ክልል ሀ ላይ በነጥብ በተመለከተው ቦታ ስህተት ተሠራ እንበል። ይህ ለውጥ በዚያ ክልል በሚገኙት ተከትለው በሚመጡት ኮፒዎች ላይ ተፅዕኖ ቢኖረውም በሌሎች ክልሎች ላይ ያለው ተፅዕኖ አነስተኛ ነው። የሌሎች ክልሎችን ጽሑፎች በማነፃፀር ለውጡ የት ጋ እንደተደረገ ታውቆ ኦሪጅናሉን መመለስ ይቻላል። የንባብ ሐያሲያን ሥራቸውን እንዴት እንደሚሠሩ ለማሳየት ይህ ቀለል ያለ ምሳሌ ነው። ሒደቱን በመጽሐፍ ቅዱስ

ትርጉሞቻችሁ የግርጌ ማስታወሻዎች ላይ ማየት ትችላላችሁ።

የእጅ ጽሑፎች፣ ትርጉሞችና ጥቅሶች በብዛት የሚኖራችሁ ከሆነ የሥራችሁም ጥራት በዚያው መጠን ይሆናል። ለአዲስ ኪዳን ከየትኛውም ጥንታዊ ጽሑፍ የላቀ የማስረጃ ብዛት አለን። ወደ 5,700 የሚሆኑ ከመጀመርያዎቹ የክርስትና ክፍለ ዘመናት ጀምሮ የተጻፉ የእጅ ጽሑፎች አሉን።[158] ወደ ስምንት የሚሆኑ ቀዳሚያን ትርጉሞች አሉን።[159] ወደ 36,000 የሚሆኑ የአበው ጥቅሶች አሉን።[160] ይህ እጅግ ብዙ ሰነድ ሲሆን በእጃችን ባለው የአዲስ ኪዳን ጽሑፍ እንድንተማመን ያደርገናል። የተለያዩ የንባብ ሕየሳ ሊቃውንት የአዲስ ኪዳንን ተዓማኒነት 99 ከመቶ አድርገው አስልተውታል።[161] ይህ ለየትኛውም መጽሐፍ ሊባል ከሚችለው በላይ የታማኝነት ደረጃ ነው።

እንደተመለከትነው ቁርአንም የጽሑፍ ልዩነቶች አሉት። አብዛኞቹ ኡሥማን ጽሑፉን መደበኛ ባደረገበት ጊዜ ተቃጥለው ጠፍተዋል። ይሁን እንጂ ዛሬም ድረስ ልዩነቶች በመኖራቸው ምክንያት ሙስሊም ተርጓሚዎች ይበልጥ አስተማማኝ የሆነውን ትርጉም ለማግኘት የትኛውን መምረጥ እንዳለባቸው ይወስናሉ።[162] ሙስሊም ሙፈሲሮች በተፍሲሮቻቸው ውስጥ ያብራሯቸዋል።[163] ኦሪጅናል ቁርአን ምን እንደሚል ለማወቅ ከእነርሱ ጋር አብረው የሚሠሩና ፍለጋ የሚያደርጉ የንባብ ሒየሳ ሊቃውንት አሉ።[164] ልዩነቶቹ ጉልህ ባይባሉም ነገር ግን በሺህዎች የሚቆጠሩ ናቸው። ማስረጃዎች እንደሚያሳዩት የኡሥማን ቁርአን በጥሩ ሁኔታ ተጠብቋል ነገር ግን ልዩነቶች ይታዩበታል።

---

158 Bruce M. Metzger and Bart D. Ehrman, *The Text of the New Testament*, (4th ed.),
Oxford, England: OUP, 2005, pp. 505-51.
159 Bruce M. Metzger and Bart D. Ehrman, p. 94ff
160 Norman L. Gelsler and William E. Nix, *A General Introduction to the Bible*, Chicago, U.S.A.: Moody Press, 1986, p. 431
161 Norman L. Gelsler and William E. Nix, p. 473
162 Abdullah Yusuf Ali, *The Holy Qur'an: Text, Translation, and Commentary*, 4th ed.,
Brentwood, Md., U.S.A.: Amana Corp., 1989, footnote 2767 for sura 21:112. Also, Alan
Jones, *The Qur'an*, U.K.: Gibb Memorial Trust, 2007, p. 19.
163 Seyyed Hossein Nasr, *The Study Qur'an*, sura 1, fn. 4, p. 7.
164 Behnam Sadeghi, “Criteria for Emending the Text of the Qur'an” in Michael Cook,
et al., (eds.) *Law and Tradition in Classical Islamic Thought*, New York, U.S.A.: Palgrave
Macmillan, 2013, chap. 2, pp. 21-41.

ይህ ማለት ቁርአንም ሆነ መጽሐፍ ቅዱስ በጥሩ ሁኔታ ተጠብቀዋል። ሁለቱም በጽሑፎቻቸው ውስጥ መጠነኛ ልዩነቶችን ቢያሳዩም ሊቃውንት ትክክለኞቹን ለመለየት በቂ ሰነዶች አሏቸው። ስለዚህ ሙስሊሞች ስለ መጽሐፍ ቅዱስም ሆነ ስለ ቁርአን የተጋነኑ ነገሮችን መናገር በማቆም የመጻሕፍቱን ጽሑፎች ባሉበት ሁኔታ መቀበል ይኖርባቸዋል።

## ቀኖና

ካነን የሚለው የግሪኩ ቃል *መለኪያ* ወይም *ደረጃ* ወይም *ደንብ* ማለት ነው ሲሆን በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ መጠቃለል ያለባቸው መጻሕፍት የትኞቹ እንደሆኑ ያሳያል።

መጽሐፍ ቅዱስ የብዙ መጻሕፍት ስብስብ በመሆኑ ምክንያት እነዚህ መጻሕፍት የተሰባሰቡበትና የተደለደሉበት ሒደት መኖሩ ግድ ነው። ይህ የሆነው አይሁድና ክርስቲያኖች የትኞቹ ቅዱሳት መጻሕፍት በቀኖና ዝርዝር ውስጥ መካተት እንዳለባቸውና እንደሌለባቸው ይወያዩ በነበሩባቸው በቀደሙት የክርስትና ዘመናት የተከናወኑ ናቸው። ከሙስሊም ክሶች መካከል አንዱ ይህ ሒደት የተቀላቀለ በመሆኑ መጽሐፍ ቅዱስም የተበረዘ ነው የሚል ነው። ሁለት ዋና ዋና ሙግቶች አሏቸው፤ የመጀመርያው ክርስቲያኖች የተለያዩ ቀኖናዎች አሏቸው የሚል ሲሆን[165] ሁለተኛው ደግሞ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያልተካተቱ ሌሎች ወንጌላት አሉ የሚል ነው። ከዚህም በመነሳት እውነተኛው የኢየሱስ ትምሕርት በቤተክርስቲያን ተደብቋል የሚል የሤራ ትወራ ያቀርባሉ።[166]

ክርስቲያኖች የተለያዩ ቀኖናዎች እንዳሏቸውና ቤተክርስቲያንም የተወሰኑ መጻሕፍትን ከአዲስ ኪዳን ማግለሏ እውነት ነው። ነገር ግን የቀደሙት ሙስሊሞችም ተመሳሳይ ነገር እንደነበራቸውና መፈፀማቸውም እውነት ነው። በዚህ ክፍል ጅማሬ ላይ እንደተመለከትነው የተለያዩ የቁርአን ቀኖናዎች ነበሩ። አንዳንዶች 116፣ አንዳንዶች 110፣ ሌሎች ደግሞ 114 ሱራዎች ነበሯቸው። ልዩነቱ ኡሥማን አንዱን ቀኖና ብቻ መርጦ ሌሎቹን ሕገ ወጥ ማድረጉና ክርስቲያኖች ግን ያንን ማድረግ አለመቻላቸው ነው። ይህ ማለት ቀኖና ለክርስቲያኖች ጥያቄ የሆነውን ያህል የሙስሊሞችም ጥያቄ ነው ስለዚህ ሙስሊሞች ምንም ዓይነት ህፀፅ እንደሌለባቸው በማስመሰል ነገሮችን ማጋነን ማቆም ያስፈልጋቸዋል። ሁለታችንም ይህንን ጉዳይ ለመፍታት ጥረት ማድረግ ግዴታ ሆኖብናል።

በተጨማሪም የሙስሊሞች የቀኖና ችግር ቁርአን ብቻ ሳይሆን ቁርአንና ሐዲስ ናቸው። የሐዲስ መጻሕፍት ሃይማኖታዊና ሌሎች ጉዳዮችን ለመወሰን የሚያስችሉ የሙሐመድ ታሪኮች ሲሆኑ በእስልምና በጣም ወሳኝ ናቸው። የቀኖና አካል ናቸው። ሆኖም የትኛው

---

165 The Roman Catholic and Orthodox Churches have more Old Testament books than
does Judaism or Protestant Christians.

166 Muhammad `Ata ur-Rahim, *Jesus: A Prophet of Islam*, Karachi: Begun Aisha Bawany Waqf, 1981, ch. 3, p. 41.

ሐዲስ መካተት እንዳለበት በሙስሊሞች መካከል ትልቅ አለመግባባት አለ። ሱኒና ሺኣ የተለያዩ ሐዲሳት ያሏቸው ሲሆን ጭራሹኑ ሐዲስ የማይቀበሉ ሙስሊሞች አሉ። ስለዚህ የሙስሊም ቀኖና ክፍትና ተለዋዋጭ ነው። በድጋሜ ሙስሊሞች በራሳቸው ቀኖና እስከ ዛሬ ስላልተስማሙ ነገሮችን ማጋነን ማቆም አለባቸው።

| የክርስቲያን ቀኖና | የሙስሊም ቀኖና |
|---|---|
| መጽሐፍ ቅዱስ- በርካታ ነቢያት<br>የትኞቹ መጽሐፍት?<br>• ካቶሊክ እና ኦርቶዶክስ<br>• የፕሮቴስታንት ቀኖና<br>• የአይሁድ ቀኖና | ቁር አንና ሐዲስ- አንድ ግለሰብ<br>የትኞቹ ሐዲሳት?<br>• የሱኒ ሐዲሳት<br>• የሺዓ ሐዲሳት<br>• ሐዲስ የለሽ<br>የትኛው ቁርአን<br>• በሙሐመድ ያልተጻፈ ቁር አን<br>• ከተመሳሳይ ቁር አኖች የተመረጠ<br>• የትኛው ቂርአት እስከ 10 የሚጠጉ ቂር አቶች ነበሩ በ4ኛ ኢስላማዊ ክፍለ ዘመን |

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያልተካተቱ ሌሎች ወንጌላትን በተመለከተስ? ሌሎች ወንጌላት መኖራቸው እውነት ነው ነገር ግን አለመካተታቸው በቂ ምክንያት ነበረው።

አንድ መጽሐፍ እንዚህን መስፈርቶች ካላሟላ ተቀባይነት የለውም። ከትቂቶች በስተቀር ለአብዛኞቹ የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት ውይይት እንዳልተደረገ መጠቆም በጣም አስፈላጊ ነው። እነዚህ መጻሕፍት በጣም የሚታወቁና በስፋት ጥቅም ላይ የዋሉ በመሆናቸው ያለ ምንም ውይይት ቀኖናዊነታቸውን አረጋግጠው ነበር። ነገር ግን ውይይት ያስፈለጋቸውና ትክክለኛነታቸው ለሰዎች ሁሉ በግልፅ ይታይ ዘንድ ማመሳከር ያስፈለጋቸው ትቂት መዛሕፍት ነበሩ። እነዚህም ዕብራውያን፣ ያዕቆብ፣ 2ጴጥሮስ፣ 2ና3 ዮሐንስ፣ ይሁዳና ራዕይ ነበሩ። በከፊል ችግር ሆኖ የነበረው እነዚህ መጻሕፍት ወደ ተወሰነ ቦታ ተልከው[167] ከዚያ ቦታ ለዓለም አቀፏ ቤተክርስቲያን መሰራጨት ስለነበረባቸው ነበር። ይህ ሁኔታ ጊዜ መውሰዱና አመኔታን ለማግኘት በሒደት ውስጥ ማለፉ ግድ ስለነበር ውይይት እንደ ችግር ሊታይ የሚገባው ሳይሆን ጽሑፎች ከቤታ ቦታ ሲሰራጩ የሚፈጠረው የተለመደ ሒደት አካል መሆኑን ማወቅ ያስፈልጋል። የተጠቀሱት መጻሕፍት በቂ ማስረጃዎች ስለቀረቡ እንደ ቅዱሳት መጻሕፍት ተቀባይነትን አግኝተዋል።[168]

167 አብዛኞቹ መልእክታት ወደ የትኛው ክልል እንደተላኩ በመግቢያዎቻቸው ላይ ያትታሉ።

168 ለበለጠ መረጃ “Adoption into the Canon” section for each book in Carson, Moo, Morris, *An Introduction to the New Testament*. ይመልከቱ።

ለሙስሊም የዚህን ሒደት ምሳሌ መስጠት አስፈላጊ ነው። ለምሳሌ ያህል *የበርናባስ ወንጌል* (14ኛው ክ.ዘ.) ወይም *ወንጌል እንደ እስልምና* (1979 ዓ.ም.) የተሰኙትን መጻሕፍት እንደ ምሳሌ መጥቀስ ይቻላል።[169] እስልምና እነዚህን ወንጌላት እንደ እውነተኛ ቅዱሳት መጻሕፍት ለክርስቲያኖች አቅርቧል። ክርስቲያኖች በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ሊያካትቷቸው ይገባልን? በፍፁም! ምክንያቱም ሙስሊም ሊቃውን እንኳ እንደሚያምኑት ተመሳስለው የተሠሩ ሐሰተኛ መጻሕፍት ናቸውና።

## ጸሐፊያን

አዲስ ኪዳን የኢየሱስ ሕይወትና የሐዋርያቱ ትምሕርቶች የዓይን ምስክሮች ዘገባ ነው። ምናልባትም የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት ባልታወቁ ሰዎች እንጂ በሐዋርያት እንዳልተጻፈ በመናገር ተዓማኒነታቸውን እንድትጠራጠሩ ሊያደርጋችሁ የሚሞክር ሙስሊም ሊገጥማችሁ ይችላል።

የወንጌላትን ጸሐፊያን በተመለከተ[170] በ185 ዓ.ም. ኢሬኔዮስ[171] ማቴዎስ፣ ማርቆስ፣ ሉቃስ፣ ዮሐንስ ብሎ እስከጻፈበት ጊዜ ድረስ ማንነታቸው አይታወቅም ነበር የሚል ነው። ሆኖም ይህ በሁለት ምክንያቶች ስሁት ሙግት ነው። አንደኛ ነገር ለመጀመርያ ጊዜ የተገኘ የጽሑፍ ቅሪት በነዚያ ስሞች መጠራት የጀመሩት በዚያን ወቅት መሆኑን አያመለክትም። የመጀመርያው በእጃችን የሚገኝ ማጣቀሻ ብቻ ነው። ከዚያ ቀደም የተጻፉ ነገር ግን የጠፉ ብዙ መጻሕፍት ስለነበሩ ወንጌላት በነዚያ መጻሕፍት ውስጥ ማቴዎስ፣ ማርቆስ፣ ሉቃስ፣ ዮሐንስ ተብለው ተጠርተው ሊሆን ይችላል። አልነበሩም ብሎ ማለት ከዝምታ በመነሳት የቀረበ ሙግት በመሆኑ ተቀባይነት የለውም። ሁለተኛ ከ185 ዓ.ም. በፊት "የማቴዎስ ወንጌል 16፡5" ወዘተ. በማለት የጠቀሱ አባቶች ጽሑፎች አለመኖራቸው እውነት ቢሆንም ከዚያ በኋላም ቢሆን ዝም ብለው የሚጠቅሱና የወንጌሉን ስም የማይጠሩ ብዙ አባቶች ስለነበሩ የወንጌላቱ ጸሐፊያን አይታወቁም ማለት አይደለም። ለምሳሌ ያህል አትናቴዎስ በ4ኛው ክ.ዘ. "ስለ ተሠግዎ" በሚል ርዕስ በጻፈው መጽሐፉ ውስጥ ከማቴዎስ፣ ማርቆስ፣ ሉቃስና ዮሐንስ ወንጌላት ሁሉ ጠቅሶ ቢጽፍም አንዴ ብቻ ዮሐንስን ጠቅሶታል። የቤተክርስቲያን አበው ቅዱሳት መጻሕፍትን ሲጠቅሱ እኛ በምናደርገው መንገድ ስላልነበረ ስሞቻቸውን ስላልጠቀሱ የጸሐፊያኑ ማንነት አይታወቅም ልንል አንችልም።

ጸሐፊው በማይታወቅበት ጊዜ ቤተ ክርስቲያን የመጻሕፍት ስም እንዳልፈለሰፈች ማስረጃ አለን። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሚገኘውን የዕብራውያንን መጽሐፍ ተመልከት። ማን እንደፃፈው አናውቅም እስካሁን ምንም ስም አልተፈለሰፈም እና አልተጨመረበትም።

---

169 ምዕራፍ 2 ይመልከቱ።

170 ሙስሊሞች እነዚህን ሙግቶች አልፈጠሩም ነገር ግን ባርት አህርማንን ከመሳሰሉ ጸሐፊያን ነው የቀዱት።

171 St. Irenaeus, *Against Heresies*

የጥንቷ ቤተ ክርስቲያን ጸሀፊያን ባልታወቁ ጊዜ ስለ መጻሕፍት ደራሲያን ተወያይታ ነበር፣ ይሁን እንጂ ስለወንጌላቱ ጸሐፊያን ግን ፈጽሞ አልተወያየችም።

የቤተክርስቲያን አበው የወንጌላት ጸሐፊያን ማንነት እንደማይታወቅ ወይንም ከስሞቻቸው ጋር ከተያያዙት ሰዎች በተለዩ ግለሰቦች እንደተጻፉ ስላልገለጹ እነዚህ ስሞች በኋለኞቹ ዘመናት የተጨመሩ ናቸው ልንል አንችልም። በመጨረሻም ጥንታውያን የእጅ ጽሑፎች ወይንም የሽፋን ገፆች በሙሉ የጸሐፊያኑን ስም ይዘዋል።[172] ስለዚህ ወንጌላት ባልታወቁ ሰዎች እንደተጻፉና በተባሉት ሰዎች እንዳልተጻፉ ለማሳሰብ የሚያበቃ ምንም ምክንያት የለም።

የአዲስ ኪዳንን መልእክታት በተመለከተ ብዙዎቹ ስሞቻቸው በሰፈሩባቸው ጸሐፊያን ስላልተጻፉ መጽሐፍ ቅዱስ ተዓማኒ አይደለም የሚል ሙግት ይቀርባል። ይሁንና የሚቀርቡት ምክንያት ወሳኝ የሆኑ መረጃዎችን ችላ ይላሉ አለበለዚያም ምክንያታዊ ባልሆኑ የተጋነኑ ጥርጣሬዎች ላይ የተመሠረቱ ናቸው። አንድ ምሳሌ እንደ ማሳያ እናነሳለን።

2ጴጥሮስ በጴጥሮስ አልተጻፈም ምክንያቱም የተጠቀመው የግሪክ አጻጻፍ ከ 1ጴጥሮስ የተለየ ነውና የሚል ሙግት አለ። እውነት ነው የአጻጻፍ ስልቱ ይለያል ለዚህ ደግሞ ጥሩ ምክንያት አለ፤ ጴጥሮስ መልእክታቱን ሲጽፍ የነበረው በጸሐፊያን እርዳታ ነበር።

> "... የታመነ ወንድም እንደ ሆነ በቈጠርሁት በስልዋኖስ እጅ በአጭሩ ጽፌላችኋለሁ።" (1ጴጥ. 5፡12)

ሲልዋኖስ ጴጥሮስ መልእክቱን እንዲጽፍ የረዳው ሲሆን ነቢይ ነበር።[173] ነገር ግን ሲልዋኖስ 2ጴጥሮስን እንዲጽፍ የረዳው አይመስልም ስለዚህ አጻጻፉ የተለየ ሊሆን ችሏል። እዚህ ጋ ምንም ችግር የለም።

ሁለተኛው፣ 2ጴጥሮስ ከጴጥሮስ ሞት በኋላ የነበረን ነገረ መለኮት ስለያዘ በጴጥሮስ የተጻፈ ሊሆን አይችልም ይላሉ። ነገረ መለኮቱ ደግሞ የኢየሱስ ምፅዓት ከብዙ ዘመናት በኋላ ወደፊት የሚሆን ነው የሚል ነው።

> "እናንተ ግን ወዳጆች ሆይ፥ በጌታ ዘንድ አንድ ቀን እንደ ሺህ ዓመት፥ ሺህ ዓመትም እንደ አንድ ቀን እንደ ሆነ ይህን አንድ ነገር አትርሱ። ለአንዳንዶች የሚዘገይ እንደሚመስላቸው ጌታ ስለ ተስፋ ቃሉ አይዘገይም፥ ነገር ግን ሁሉ ወደ ንስሐ እንዲደርሱ እንጂ ማንም እንዳይጠፉ ወዶ ስለ እናንተ ይታገሣል።" (2ጴጥ. 3፡8-9)

---

172 Simon J. Gathercole, "The Titles of the Gospels in the Earliest New Testament Manuscripts," ZNW 104 (2012), pp. 33–76.
173 ሐዋ. 15፡32

ሙግቱ ሲቀጥል ኢየሱስ በሐዋርያቱ የሕይወት ዘመን ወደ ምድር እንደሚመለስ ተናግሯል ይላል፤ ለዚህም በማስረጃነት ማቴዎስ 24፡34 ይጠቀሳል።[174] ኢየሱስ ስላልተመለሰ የኋለኞቹ ክርስቲያኖች የእርሱ መመለስ ወደፊት የሚፈፀም እንደሆነ ማስተማር ጀመሩ ይላሉ። 2ጴጥሮስ ይህንን የኋለኛ ዘመን አስተምሕሮ ስለሚያንጸባርቅ ቀደም ሲል በሞተው በጴጥሮስ የተጻፈ ሊሆን አይችልም በማለት ሙግታቸውን ያጠቃልላሉ። የዚህ ሙግት ችግር ኢየሱስ የተናገረውን ችላ ማለቱ ነው ምክንያቱም ኢየሱስ የመምጫውን ቀን እንደማያውቅ ተናግሯልና።[175] ቀኑን ካላወቀ መቼ እንደሚመጣ አልተናገረም ማለት ነው። አጠቃላይ ሙግቱ መሠረተ ቢስ ቢሆንም መሰል የጥርጣሬ ሙግቶች በተደጋጋሚ ሊያጋጥሟችሁ ይችላሉ።

እስልምናም ለቁርኣን የጸሐፊ ማንነት ጥያቄ አለው። ቀደም ሲል እንደተባለው በዓለም ላይ ጥቅም ላይ እየዋሉ የሚገኙ የተለያዩ ዓይነት የቁርኣን ቅጂዎች ይገኛሉ። ሆኖም እነዚህ ብቸኛ ቅጂዎች አይደሉም፤ እነዚህ *ተቀባይነትን ያገኙ* ቅጂዎች ናቸው። የእስልምና ታሪክ እንደሚነግረን በመጀመርያዎቹ ጥቂት የእስልምና ክፍለ ዘመናት ቢያንስ 50 የሚሆኑ ቅጂዎች ተፈጥረው ነበር።[176] ከነዚያም መካል ሰባቱ እንደ ተዓማኒ ተቆጥረዋል። ከዚያም ሌሎች ሦስት ተጨምረው አሥር ተቀባይነት ያላቸው ቅጂዎች ተፈጥረዋል።[177] የትኛው ቅጂ ትክክል እንደሆነ መምረጥ የእስልምና የጸሐፊያን ማንነት ጥያቄ ነው።

ይህ ማለት ቁርኣንም ሆነ መጽሐፍ ቅዱስ የጸሐፊያን ማንነት ጥያቄ ያላቸው ሲሆን ክርስቲያኖችና ሙስሊሞች የጸሐፊያኑን ማንነት የመለያ ዘዴዎችን አበጅተዋል። ይህ እንደ ችግር የሚታይ ሳይሆን መጻሕፍት ከተጻፉ በኋላ የሚከሰት የተለመደ ጉዳይ ነው። ችግሩ ሙስሊሞች እንዲህ ያለውን ጥያቄ መመለስ የሌለባቸው ይመስል በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ ጥርጣሬን ለመፍጠር ሲሞክሩ ነው።\

---

174 1ተሰ. 4፡15 ላይ ጳውሎስ ኢየሱስ በእርሱ የሕይወት ዘመን ወደ ምድር እንደሚመለስ ያምን እንደነበር እንደሚያሳይ ቢነገርም 5፡10 ላይ ነገሩ እንደርሱ እንዳልሆነ አስረድቷል።

175 ማቴ. 24:36

176 Al-Nadim, *The Fihrist of al-Nadim* - A Tenth Century survey of Muslim Culture, New York: Columbia University Press, 1970, pp. 63-71. Intisar A. Rabb, "Non-Canonical Readings of the Qur'an: Recognitition and Authenticity (the Himsi Reading)", *Journal of Qur'anic Studies*, 2006, vol. 8, no. 2, p. 124, footnote 114.

177 Abu Ammaar Yasir Qadhi, *An Introduction to the Sciences of the Qur'an*, chap. 11.

## ውስጣዊ ተግባቦት - ግጭቶች

ሙስሊም የመጽሐፍ ቅዱስ ተቺዎች መጽሐፍ ቅዱስን ለማጣጣል ግጭቶችን ማሳየት እንደ ዋና ነጥብ ይዘዋል። አሕመድ ዲዳትና[178] ሻቢር አሊ[179] ብዙ ጥቅሶችን ያሰባሰቡ ሲሆን ሙስሊሞች የባርት ኤህርማንንም[180] ሐሳቦች ይጠቀማሉ። ስለዚህ ሙስሊሞች በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ብዙ ግጭቶች አሉ የሚል ትምሕርት የሃይማኖታቸው አካል ሆኗል ማለት ይቻላል። ለነዚህ ክሶች የተዘጋጁ ምላሾች አንላይን ይገኛሉ።[181]

በአንድ ወቅት አንድ ሙስሊም የዩኒቨርሲቲ ተማሪ እነዚህን ግጭት ተብዬዎች ከኢንተርኔት በማውረድ ይዞልኝ መጣ። እነዚህን ነጥቦች ሲያሳየኝ በትችት መልክ ሳይሆን ምላሾቻቸውን ከማወቅ አንፃር ነበር። የተወሰኑትን አብረን ከመለስን በኋላ የተቀሩትን የማወቅ ፍላጎቱ ጠፋ። ስለዚህ መጽሐፍ ቅዱስ በግጭቶች የተሞላ ነው ስለሚለው ክስ አንዳንድ ነገሮችን ማወቅ አስፈላጊ ነው።

የመጀመርያው ሁለት ነገሮች ግጭት ቢመስሉም ላይሆኑ ይችላሉ የሚል ነው። ግጭት መስለው የሚታዩት ሁለቱም እውነት መሆናቸውን ለማወቅ የሚያስችል በቂ መረጃ ስለሌላችሁ ሊሆን ይችላል። ለምሳሌ ያህል ሙስሊሞች በተደጋጋሚ ከሚጠቅሷቸው መካከል በመጽሐፈ ሳሙኤል፣ ነገሥት፣ ዜና፣ ዕዝራና ነህምያ ውስጥ የሚገኙትን የቁጥር ልዩነቶች ነው። አንዳንዴ ነገሥታቱ የነገሡባቸው የዘመናት ርዝማኔ ይለያያል፤ የወታደሮች ቁጥር የተለያየ ሊሆን ይችላል፤ ወይንም ከስደት ተመላሾች ቁጥር እኩል ላይሆን ይችላል። እንዲሁ ሲታዩ ግጭቶች ይመስላሉ ነገር ግን የበለጠ መረጃ ስናገኝ ምንም ዓይነት ግጭት አይኖርም። ለምሳሌ ያህል የንጉሥ ሰለሞንን የንግሥና ዘመን ውሰዱ፡-

> “በዚያም ቀን በታላቅ ደስታ በእግዚአብሔር ፊት በሉ ጠጡም። የዳዊትንም ልጅ ሰሎሞንን ሁለተኛ ጊዜ አነገሡት፤ እርሱንም አለቃ ይሆን ዘንድ ለእግዚአብሔር ቀቡት፥ ሳዶቅንም ካህን ይሆን ዘንድ ቀቡት።” (1ዜና 29፡22)

ይህ ማለት ሰለሞን ሁለት ጊዜ ለንግሥና ተቀብቷል ማለት ነው፤ በሁለት የተለያዩ ዘመናት ለንግሥና ተቀብቷል። ይህ ቆጠራ ከምትጀምሩበት የመቀባት ጊዜ ላይ ተመሥርቶ ሁለት የተለያዩ ዘመናትን ይሰጣችኋል። ነገር ግን የተሟላ መረጃ ካገኛችሁ ግጭት አለመኖሩ ይገባችኋል። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሚገኙት ቁጥሮች ምናልባትም እናንተ ልትገነዘቡ

---

178 Ahmed Deedat, *Is the Bible God's Word*, Saudi Arabia: Abdul-Qasim Publishing House, not date.
179 Shabir Ally, *101 Clear Contradictions in the Bible*, Toronto, Canada: Al Attique Publishers Inc, 2001.
180 Bart D. Ehrman, *Jesus, Interrupted*, New York, U.S.A, HarperOne, 2010.
181 Jay Smith et al, *101 'Cleared-Up' Contradictions In The Bible*, debate.org.uk/debate-topics/apologetic/contrads/ accessed 19 July, 2018.

ከምትችሉት በላይ በጣም ትክክል ሊሆኑ ይችላሉ። በተቃርኖነት ከመፈረጃችሁ በፊት በጣም ልትጠነቀቁ ይገባችኋል።

ወንጌላትም ተቃርኖ በውስጣቸው እንደሚገኝ ተነግሯል። ወንጌላት አንዱን ክስተት መጠነኛ ልዩነቶች በሚታዩባቸው መንገዶች መዘገባቸው እውነት ቢሆንም ግጭቶች ግን አይደሉም። ወንጌላት የኢየሱስ ሕይወት የዐይን ምስክሮች ዘገባዎች በመሆናቸው ምክንያት ስለ አንዱ ክስተት የተለያዩ ነጥቦች ላይ በማተኮር ሊጽፉ ይችላሉ። እነዚህ ልዩነቶች ግጭቶች ሳይሆኑ ስብጥርን የሚፈጥሩ ናቸው። ለምሳሌ ያህል በኢየሱስ መቃብር ቦታ ስለተገኙት ሴቶች ውሰዱ። ባርት ኤህርማን ወንጌላት ይጋጫሉ የሚል ክስ ያቀርባል፡-

ወደ መቃብር ቦታ የሄደው ማን ነው? ማርያም ብቻ (ዮሐ. 20፡1)? ማርያምና ሌላ ማርያም (ማቴ. 28፡1)? መግደላዊት ማርያም፣ የያዕቆብ እናት ማርያምና ሰሎሜ (ማር. 16፡1)?[182]

ሆኖም እዚህ ጋ ምንም ዓይነት ግጭት የለም። የተለያየ ደረጃ ያለው ዝርዝር መረጃ ብቻ ነው። ኤህርማን ቁጥሮቹን በጥንቃቄ አላነበባቸውም ማለት ይቻላል። “ማርያም ብቻ (ዮሐ. 20፡1)?” ብሎ ጠይቋል ነገር ግን ጥቅሱን በአውድ ውስጥ አንብቡት እስኪ፡-

> “ከሳምንቱም በፊተኛው ቀን መግደላዊት ማርያም ገና ጨለማ ሳለ ማለዳ ወደ መቃብር መጣች ድንጋዩም ከመቃብሩ ተፈንቅሎ አየች። እየሮጠችም ወደ ስምዖን ጴጥሮስና ኢየሱስ ይወደው ወደ ነበረው ወደ ሌላው ደቀ መዝሙር መጥታ፡- ጌታን ከመቃብር ወስደውታል ወዴትም እንዳኖሩት አናውቅም አለቻቸው።” (ዮሐ. 20፡1-2)

ማርያም “አናውቅም” በማለት ብዙ መሆናቸውን ትገልፃለች። ይህ ማለት ከእርሷ ጋር ሌሎች መኖራቸውንና ብቻዋን እንዳልነበረች ይገልፃል። ይህ ከሌሎች የወንጌላት ዘገባዎች ጋር ሙሉ በሙሉ ይስማማል። ወንጌላት ተሰባጣሪ ዘገባዎችን እንጂ የሚጋጩ ዘገባዎችን አያቀርቡም።

ሁሉንም በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ የሚነሱ የግጭት ክሶች ለመመለስ በቂ ቦታ የለንም። አብዛኞቹ መጽሐፍ ቅዱስን በጥንቃቄ በማንበብ ብቻ የሚመለሱ ናቸው። መመለስ ያልቻላችኋቸው ጥያቄዎች ካሉ ቀደም ሲል በሰጠነው የኢንተርኔት አድራሻ ወይንም ኦንላይን ፍለጋ በማድረግ ተመልከቱ።

በመጨረሻ የምንመለከተው ክስ ወንጌላት እያንዳንዳቸው ኢየሱስን በተለያዩ የሚጋጩ መንገዶች ስለውታል ወይንም የተለያየ ነገረ ክርስቶስ ያስተምራሉ የሚለውን ነው። ሙግቱ እንደሚለው ማርቆስ የቀደመው ወይንም ቀዳሚው ወንጌል ነው፤ ኢየሱስን እንደ ሰው ያቀርበዋል፤ ማቴዎስና ሉቃስ ይህንን የተወሰነ ያህል ያዳብሩታል፤ ዮሐንስ ደግሞ ኢየሱስን አምላክ አድርጎ ያቀርበዋል የሚል ነው። ለዚህ ማስረጃ ተደርጎ የሚቀርበው የተወሰኑ

---

182 Bart Ehrman, *Jesus, Interrupted*, p. 48

የወንጌላቱን ተመሳሳይ ዘገባዎች በማነፃፀር ነገረ መለኮታዊ ይዘታቸው አድጓል የሚል ነው። ለምሳሌ ያህል ማርቆስ እንዲህ ሲል ጻፈ፡-

> “ብርቱ ዐውሎ ነፋስም ተነሣና ውኃ በታንኳይቱ እስኪሞላ ድረስ ማዕበሉ በታንኳይቱ ይገባ ነበር። እርሱም በስተኋላዋ ትራስ ተንተርሶ ተኝቶ ነበር፤ አንቅተውም፡- መምህር ሆይ፥ ስንጠፋ አይገድህምን? አሉት። ነቅቶም ነፋሱን ገሠጸው ባሕሩንም፡- ዝም በል፥ ፀጥ በል አለው። ነፋሱም ተወ ታላቅ ፀጥታም ሆነ።” (ማር. 4፡37-39)

ማቴዎስ ደግሞ እንዲህ ሲል ጻፈ፡-

> “እነሆም፥ ማዕበሉ ታንኳይቱን እስኪደፍናት ድረስ በባሕር ታላቅ መናወጥ ሆነ፤ እርሱ ግን ተኝቶ ነበር። ደቀ መዛሙርቱም ቀርበው፡- ጌታ ሆይ፥ አድነን፥ ጠፋን እያሉ አስነሡት። እርሱም፡- እናንተ እምነት የጎደላችሁ፥ ስለ ምን ትፈራላችሁ? አላቸው፤ ከዚህ በኋላ ተነሥቶ ነፋሱንና ባሕሩን ገሠጸ፥ ታላቅ ጸጥታም ሆነ።” (ማቴ. 8፡24-26)

እንደምትመለከቱት ማርቆስ ደቀ መዛሙርቱ ኢየሱስን *መምህር* እንዳሉት የጻፈ ሲሆን ማቴዎስ ደግሞ *ጌታ ሆይ* እንዳሉት ጽፏል። ይህ ልዩነት ስለ ኢየሱስ የነበረው መረዳት እየተለወጠ መምጣቱን አመላካች በመሆኑ አዳጊ ነገረ ክርስቶስ ይታያል የሚል ሙግት ይቀርባል። ይህ ትክክለኛ ድምዳሜ ነውን? በሚከተሉት ምክንያቶች አይደለም፡-

የመጀመርያው ደቀ መዛሙርት ኢየሱስን መምህርና ጌታ ብለው መጥራታቸው ነው። በጊዜ ሒደት ከአንዱ ወደ ሌላው የተደረገ ዕድገት የለም።

> “እናንተ መምህርና ጌታ ትሉኛላችሁ፤ እንዲሁ ነኝና መልካም ትላላችሁ።” (ዮሐ. 13፡13)

ሁለተኛ በሁለቱም ዘገባዎች ውስጥ ኢየሱስ እንደ እግዚአብሔር ማዕበሉን በቃሉ ብቻ ፀጥ አድርጓል።[183] በማርቆስ ውስጥ ኢየሱስ ማዕበሉን ፀጥ ለማድረግ ወደ እግዚአብሔር ጸልዮ ቢሆን ኖሮና በማቴዎስ ውስጥ ደግሞ እንደ እግዚአብሔር በቃሉ ብቻ ፀጥ አድርጎ ቢሆን ኖሮ ዕድገት መኖሩን መደምደም ይቻል ነበር። ነገር ግን የሆነው ይህ አልነበረም። በሁለቱም ዘገባዎች ውስጥ ኢየሱስ እንደ አምላክ በሥልጣን ሲናገር ይታያል። ዕድገት የለም።

እንዲያውም በአንዳንድ ሁኔታዎች ማስረጃው ማርቆስ ጥንታዊ ወንጌል ነው ከሚለው ተቃራኒ ነው። ለምሳሌ በማርቆስ 2፡7 ላይ ኢየሱስ ሰውየውን ኃጢአቱን ይቅር ሲለው የሕግ መምህራን ይህን ማድረግ የሚችለው እግዚአብሔር ብቻ ነው ብለው ተቃውመውት ነበር። በዚህ ክፍል ኢየሱስም አምላክነቱን እያሳየ ነበር። ነገር ግን፣ ይኸው ክስተት በማቴዎስ 9

---

183 መዝሙር 89:9-10, 104:7, 107:23-30

ላይ ሲመዘገብ ይሄ መለኮታዊ መገለጫነቱ የለም። አሁን ይህ የሚያሳየው ማቴዎስ ከማርቆስ የበለጠ ጥንታዊ መሆኑን ነው?

ሦስተኛ ነጥባችሁን ለማረጋገጥ ጥቂት ጥቅሶችን ብቻ የምትመርጡ ከሆነ ይህ ጉዳይ አሳሳች ይሆናል። በዚህ ፋንታ ግን ወንጌላትን በሞላ ማነፃፀር ያሻናል። እንደርሱ ካደረግን የምናገኘው ምስል የተለየ ነው። ሰጥኑን ተመልከቱ፡-

| **አንድ ኢየሱስ የተለያየ አፅንዖት** | **ማቴዎስ** | **ማርቆስ** | **ሉቃስ** | **ዮሐንስ** |
|---|---|---|---|---|
| ተሰቅሏል፣ ሞቷል፣ ከሞት ተነስቷል | 16:21, 17:22-23, 20:17-19, 27:45-28:10 | 8:31, 10:32-34, 15:1-16:8 | 9:20-22, 18:31-34, 23:44-24:12 | 3:14, 10:11-18, 12:24, 19:17-20:23 |
| የእግዚአብሔር ልጅ | 3:17, 4:3-6, 8:29, 11:27, 14:33, 16:16, 17:5, 21:37, 22:2, 24:36, 26:63-64, 27:40, 43, 54, 28:19 | 1:1? 1:11, 3:11, 5:7, 9:7, 12:6, 13:32, 14:60-62, 15:39 | 1:32, 1:35, 3:22, 4:3-9, 4:41, 8:28, 9:35, 20:13, 22:70-71 | 1:34, 1:49, 3:16-18, 3:35-36, 5:16-30, 6:40, 8:35-36, 10:36, 11:4, 11:27, 13:32, 14:13, 17:1, 19:7, 20:31 |
| የሰው ልጅ | 8:20, 9:6, 10:23, 11:19, 12:8, 12:32, 12:40, 13:37, 13:41, 16:13, 16:27-28, 17:9, 17:12-14, 17:22, 19:22, 20:18, 20:28, 24:27, 24:30, 24:37-39, 24:44, 25:31, 26:2, 26:24, 26:45, 26:64 | 2:10, 2:28, 8:31, 8:38, 9:9, 9:12, 9:31, 10:33, 10:45, 13:26, 14:21, 14:41, 14:62 | 5:24, 6:5, 6:22, 7:34, 9:22, 9:26, 9:44, 9:58, 11:30, 12:8-10, 12:40, 17:22-30, 18:8, 18:31, 19:10, 21:27, 21:36, 22:22, 22:48, 22:69, 24:7 | 1:51, 3:13-14, 5:16-30, 6:27, 6:53, 6:62, 8:28, 9:35, 12:23, 12:34, 13:31 |
| የዳዊት ልጅ | 1:1, 9:27, 12:23, 15:22, 20:30-31, 21:9- 15, 22:41-46 | 10:47-48, 11:10, 12:35-37 | 1:27, 1:32, 1:69, 2:4, 2:11, 3:31, 18:38-39, 20:41-44 | 7:42? |
| መምህር | 8:19, 9:11, 10:24-25, 12:38, 17:24, 19:16, 22:16, 22:24, 22:36, 26:18 | 4:38, 5:35, 9:17, 9:38, 10:17, 10:20, 10:35, 12:14, 12:19, 12:32, 13:1, 14:14 | 6:40, 7:40, 8:49, 9:38, 10:25, 11:45, 12:13, 18:18, 19:39, 20:21, 20:28, 21:7, 22:11 | 1:38, 3:2, 8:4, 11:28, 13:13-14, 20:16 |
| ረቢ | 26:25, 26:49 | 9:5, 11:21, 14:45 | 1:38, 1:49, 3:2, 4:31, 6:25, 9:2, 11:8 | 26:25, 26:49 |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ጌታ | 3:3, 7:21-22, 8:2, 8:6, 8:21, 8:25, 9:28, 12:8, 14:28-30, 15:22, 15:25- 27, 16:22, 17:4, 17:15, 18:21, 20:30-33, 21:3, 22:43-45, 24:42, 25:37, 25:44, 26:22 | 1:3, 2:28, 5:19, 7:28, 11:3, 12:36-37 | 2:11, 3:4, 5:8, 5:12, 6:5, 6:46, 7:6, 7:13, 7:19, 9:54, 9:59-61, 10:1-2, 10:17, 10:39-41, 11:1, 11:39, 12:41-42, 13:15, 13:23- 25, 17:5-6, 17:37, 18:6, 18:41, 19:8, 19:31, 19:34, 20:42-44, 22:33, 22:38, 22:49, 22:61, 24:3, 24:34 | 1:23, 6:23, 6:68, 8:11, 9:38, 11:2-3, 11:12, 11:21, 11:27, 11:32-34, 11:39, 13:6, 13:9, 13:13-14, 13:25, 13:36-37, 14:5-8, 14:22, 20:2, 20:13, 20:18-20, 20:25-28, 21:7, 21:12, 21:15-21 |
| መሲህ/ክርስቶስ | 1:1, 1:16-18, 11:2, 16:16, 16:20, 22:42, 23:10, 26:63, 27:17, 27:22 | 1:1, 8:29, 9:41, 12:35, 14:61, 15:32 | 2:11, 2:26, 4:41, 9:20, 20:41, 22:67, 23:2, 23:35, 23:39, 24:26, 24:46 | 1:17, 1:41, 3:28, 4:25-26, 7:25-44, 9:22, 10:24-25, 11:27, 17:3, 20:31 |
| ለኃጢአታችን መሥዋዕት | 20:26-28, 26:26-28, 27:51 | 10:45, 14:22-24, 15:38 | 22:17-20, 23:45 | 1:29, 1:35-36 |
| ተዓምራት | አዎ | አዎ | አዎ | አዎ |
| እግዚአብሔር አባቱ ነው | አዎ | አዎ | አዎ | አዎ |
| ከመወለዱ በፊት የነበረ | Matthew 3:11- 12 | Mark 1:7-8 | Luke 3:16, 5:8[184] | John 1:1-3 |
| ሰዓቲቱ አላወቀም ወይም መማር አስፈልጎታል | 24:36 | 13:32 | 2:52 | 5:30 |

ዋና የወንጌል መልእክታት ሲስተያዩ የገዘፈ ታሪካዊና ነገረ መለኮታዊ መመሳሰል እንዳላቸው መረዳት ይቻላል። አንድ ቋሚ የወንጌል መልእክት አለ። ሆኖም እያንዳንዱ ወንጌል ሌላውን ዝም ብሎ የሚደግም ሳይሆን የተወሰኑ ነጥቦች ላይ አፅንዖት የሚሰጡ ናቸው። እነዚህ የተለያዩ አፅንዖታት ግጭቶች ሳይሆኑ የዓይን መስክሮች ዘገባዎች ተፈጥሯዊ ገፅታዎች ናቸው።

184 ለምሳሌ ኢሳ. 6, ኢዩ. 2:28, 3:12 ተመልከቱ።

## ትግበራና ማጠቃለያ

1. ሙስሊም መጽሐፍ ቅዱስ ተለውጧል የሚል ከሆነ መጽሐፍ ቅዱስ መለወጡንና አንድ ቁርኣን ብቻ መኖሩን በአንደበታቸው እንዲያረጋግጡላችሁ ጠይቋቸው። ከዚያም ስለ ቁርኣን የመቃጠልና አንድ መልክ የማስያዝ ታሪክ እንዲሁም ዛሬ ስላሉት የተለያዩ የቁርኣን ቅጂዎች አሳዩዋቸው።
2. ቁርኣን ስለ መጽሐፍ ቅዱስ ምን እንደሚል ካሳያችሁ በኋላ መጽሐፍ ቅዱስን ቁርኣን በሚናገረው መንገድ እንዲመለከቱ ጠይቋቸው።

## የሚደጋገሙ ጥያቄዎች

1. *ሙስሊም*፡ መጽሐፍ ቅዱስ ራሱ ስለመበረዙ ይናገራል።

   "እናንተስ፡- ጥበበኞች ነን የእግዚአብሔርም ሕግ ከእኛ ጋር ነው እንዴት ትላላችሁ? እነሆ፥ የጸሐፊ ብርዕ ሐሰተኛ ነው በሐሰትም አድርጎአል።" (ኤር. 8፡8)

*ክርስቲያን*፡ በመጀመርያ ጥቅሱ የሚናገረው ስለ ተወሰኑ ጸሐፍት ተግባር እንጂ ስለ ሁሉም አይደለም። የኤርምያስ ጸሐፊ የነበረውን ባሮክን የመሳሰሉ ጸሐፍትን ምን ልናደርጋቸው ነው (ኤር. 36፡26)? አንድን አጋጣሚ ወስደህ በሁሉም ሁኔታዎች ላይ ተግባራዊ በማድረግ ነገሮችን እያጋነንክ ነው። ያንተ አባባል ሙስሊም አሸባሪዎች ስላሉ ሁሉም ሙስሊሞች አሸባሪዎች ናቸው ብሎ የሙስሊሞችን ሁሉ ስም እንደማጥፋት ነው።

ሁለተኛ ጥቅሱ አንተ በምትለው መንገድ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ጥቅም ላይ አልዋለም። ኋላ ላይ ኤርምያስ ሕጉን ተከተሉ ይላል (26፡4)። ሕዝቅኤል 44፡15 እንዲሁም ዕዝራ 7፡1-6 ይህንኑ ይላል። ሕጉ ከተበረዘ እንዴት እንዲህ ሊባል ይችላል?

አራተኛ ቁርኣን በሰይጣናዊ ጥቅሶች የተበረዘ ቢሆንም አንተ ግን ተበርዟል ብለህ አታምንም።

2. *ሙስሊም* ፡ በዘመናዊ የመጽሐፍ ቅዱስ ሕትመቶች ውስጥ ማርቆስ 16፡9-11፣ ዮሐንስ 8፡1-11 እንዲሁም ዮሐንስ 5፡7-8 (ኪንግ ጀምስ ትርጉም ውስጥ በተጠቀሰው መሠረት) በጥንታውያን የእጅ ጽሑፎች ውስጥ እንደሌሉ ተነግሯል። ይህ መጽሐፍ ቅዱስ ስለመበረዙ ማስረጃ ነው።

*ክርስቲያን* ፡ ይህ የሚያሳየው ተቃራኒውን ነው፤ ምክንያቱም እንዲህ ያሉ ችግሮች አነስተኛ (ሦስት ብቻ) መሆናቸውን ያመለክታልና። እነዚህ ልዩነቶች የተለዩና አጠቃላዩን መጽሐፍ ቅዱስ የማይወክሉ ናቸው። ጥቂት ጠቅሶ ሁሉንም በአንድ መፈረጅ ትክክል አይደለም።

3. ሙስሊም፡- ቁር አን ስለ አንድ ወንጌል ብቻ ነው የሚናገረው። እናንተ ጋር ግን አራት ወንጌላት አሉ። ማቴዎስ ማርቆስ ሉቃስና ዮሐንስ። ስለዚህ ቁር አን ስለናንተ ወንጌል እያወራ አይደለም።

ክርስቲያን፡ ቁርኣን ስለ "የመጽሐፉ ሰዎች" ይናገራል። ግን ስለ መጽሐፍቱን ሲዘረዝር ኦሪትን፣ የነቢያት መጻሕፍትን፣ መዝሙረ ዳዊትን እና ወንጌልን ይጠቅሳል። ስለዚህ አንድ ነጠላ መጽሐፍ የተለያዩ ክፍሎች ሊኖሩት ይችላል። በተመለከተ ቁርኣን ማቴዎስን፣ ማርቆስን፣ ሉቃስን እና ዮሐንስን አይጠቅስም። ይህ እውነት ነው ነገር ግን ሰባቱን አህሩፍ ወይም አስር ቂራአቶችን አይጠቅስም ማለትም አጠቃላይ መረጃን ብቻ ይሰጣል።

4. የአዲስ ኪዳን ወንጌላት በግሪክ ነው የተጻፉት ነበር። የኢየሱስ ቋንቋ ምን ነበር?

ክርስቲያን፡ በመጀመሪያ ደረጃ ቁር አን የግሪክ ቃል የሆነውን ኢንጂልን ይጠቀማል። በመቀጠል ወንጌላቱ ኢየሱስ ግሪክኛ ተናጋሪ ሰዎችን እንዳነጋገረ ዘግበዋል። ይህ ማለት ግሪክኛ በወቅቱ ዓለም አቀፍ ቋንቋ ነበር ማለት ነው።

5. ሙስሊም፡- ክርስቲያኖች እስከ 4ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ድረስ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያሉትን መጻሕፍት ቀኖና አልያዙም። ይህ መጽሐፍ ቅዱስ የቱ እንደሆነ ለማወቅ በጣም ዘግይቷል.

ክርስቲያን፡- እነዚህ መጻሕፍት ከዚህ ቀን በፊት እንደ ቅዱሳት መጻሕፍት ይታወቃሉ፣ ነገር ግን ቀኖናዊውን የመጻሕፍት ዝርዝር የማዘጋጀቱ ሂደት ጊዜ ይወስዳል። ከቁርኣን ጋር ተመሳሳይ ነው። ሙስሊሞች ተቀባይነት ያላቸውን አስር የቁርኣን ቅጂዎች እስከ 4ኛው ኢስላማዊ ክፍለ ዘመን ድረስ አልቀዱም። እነዚህ ነገሮች ጊዜ የሚወስዱ ሲሆን በዚህ ውስጥ ምንም ስህተት የለበትም። ሐዲሱን ብንመረምርም በሙስሊሞች መካከል ቀኖናዊ ሐዲስ ምን እንደሆነ አሁንም መግባባት እንደሌለ እናያለን።

6. ሙስሊም፡ አላህ ራሱ ቁርኣንን ፤ለመጠበቅ ቃል ገብቷል።

ክርስቲያን፡ ቁር አንና ሐዲሳት አንዳንድ የቁርአን ክፍሎች እንደጠፉ ይናገራሉ። የትኛውን ነው ትክክል?

# ምዕራፍ 11

## ታሪክ

እስልምና ፍልስፍና ሳይሆን በታሪካዊ ክስተቶች ላይ የተመሠረተ ሃይማኖትና ሥልጣኔ ነው። በሙስሊሞች እምነት መሠረት በታሪክ የሆነ ክፍል ላይ ፈጣሪ ሙሐመድን ነቢይ አድርጎ በማስነሳት እስልምናን ዓለም አቀፋዊ ግዛተ መንግሥትና ሃይማኖት አድርጎ አቆመ። ስለዚህ ታሪኩን መማር የእስልምና ትምሕርት ወሳኝ ክፍል ነው። ሙስሊም መሪዎች ነገረ መለኮታዊ ብቻ ሳይሆን ታሪካዊ ሙግትም ያቀርባሉ ማለት ነው። ይህ ስለ ሙሐመድና ስለ ሙስሊሞች ሕዝቦች ወይንም እስልምና ለዓለም ያደረገውን አበርክቶት ወይንም ሙስሊሞች ሌሎችን እንዴት እንደተንከባከቡና በሌሎች ምን እንደተደረገባቸው የመሳሰሉትን ታሪኮች ሊሆን ይችላል። ስለዚህ ክርስቲያኖች ከሙስሊሞች ጋር ሲነጋገሩ ታሪክን መወያየት ሊያስፈልጋቸው ይችላል። በዚህ የመጨረሻ ምዕራፍ እስልምናና ታሪክን በተመለከተ ከየት መጀመር እንዳለብን እናያለን።

ስለ እስልምና ታሪክ ማወቅ ከፈለጋችሁ ከየት ነው መጀመር ያለባችሁ? ብዙ ያገኟቸው ሰዎች ምንም የሚያዉቁት ነገር የለም። አንዳንዶች ስለ ክሩሴዶች ወይንም በዓለም የንግድ ማዕከላት ላይ ስለደረሰው ጥቃት ወይንም ስለ ምዕራባውያን የውጪ ፖሊሲዎች በማጥናት መጀመር መልካም መስሎ ይታያቸዋል። የምሥራቅ ኦርቶዶክስ ክርስቲያን ከሆናችሁ ከቁስጥንጥንያ መረራ መጀመር ትፈላጋላችሁ። ከሌላ ዓለም ከሆናችሁ ደግሞ እስልምና ወደ እናንተ ከመጣበት ዘመን መጀመር ትፈልጉ ይሆናል። እነዚህ ወሳኝ የታሪክ ክስተቶች ቢሆኑም የእስልምና አንቀሳቃሹ ኃይል በእነዚህ ላይ የተመሠረተ አይደለም። የሙሐመድ የሕይወት ታሪክና እስልምና አብዛኛውን ዓለም የገዛባቸው ዘመናት ናቸው። አሁን እነዚህንና እስልምና ወደ ፊት ምን ተስፋ እንደሚያደርግ እንመለከታለን። በሙስሊም ክርስቲያን ውይይት ወቅት በሚነሱ ነጥቦች ላይ ይበልጥ እናተኩራለን።

### የሙሐመድ ዓለም

ሙሐመድ 570 ዓ.ም. አካባቢ ነበር የተወለደው። አረብና የቁረይሽ ጎሣ አባል ነበር። አብዛኛውን ሕይወቱን ያሳለፈው መካና መዲና በተባሉ ሒጃዝ በተሰኘ የአረብያ ክፍል ውስጥ በሚገኙ ከተሞች ውስጥ ነበር።

በዚያን ወቅት ሁለት ዋና ዋና ግዛተ መንግሥታት ነበሩ። የፋርስ ግዛተ መንግሥት በሰሜን ምሥራቅ ነበር። ይህ ግዛተ ምንግሥት የዞራስትራኒዝም ሲሆን ብዙ ክርስቲያኖችና አይሁድ ይኖሩ ነበር። ሌላኛው ደግሞ ቢዛንቲን ወይም የምሥራቃዊ ሮማ ግዛተ መንግሥት ሲሆን በሰሜን ምዕራብ አቅጣጫ ይገኝ ነበር። ይህ የክርስቲያን ግዛተ መንግሥት የነበረ ሲሆን ሮማውያን ሦርያውያን፣ ቅብጦችን እንዲሁም አረብ ክርስቲያኖችንና አይሁድን ይገዙ ነበር። በነዚህ ግዛተ መንግሥታት መካከል የነበረው ድንበር ቋሚ አልነበረም። በ616 ዓ.ም. ፋርሳውያን




ፍልስጥኤምን የወረሩ ሲሆን በ618 ደግሞ ግብፅን ያዙ። ሮማውያን በ628 ዓ.ም. ማለትም ሙስሊሞች በእነርሱ ላይ ውጊያዎችን ከመከፈታቸው ከ8 ዓመታት በፊት የተወሰዱባቸውን ምድሮች መቆጣጠር ቻሉ።



በነዚህ ግዛተ መንግሥታትና በአረብያ መካከል የአረብ ጥቃቅን መንግሥታት ነበሩ። እነዚህ መንግሥታት በፋርሳውያንና በሮማውያን መካከል እንደ ነፃ ቦታና በሮማውያንና በአረብ ጥቃት አድራሾች መካከልም እንደ ድንበር ያገለግሉ ነበር። እነዚህ መንግሥታት ከተለያዩ ግዛተ መንግሥታት ጋር በማበር ገንዘብን ተቀብለው እንደ ነፃ ቀጠና ሰላምን ያስጠብቁ ነበር። ነገር ግን በዓለም መድረክ ላይ አስነስተኛ ተዋንያን አልነበሩም። ድንገተኛ የዝርፍያ ጥቃቶችን ያደርሱ ነበር፣ ትልልቅና አነስተኛ አውደ ግንባሮች ላይ ይሳተፉ ነበር፣ በሦስተኛው ክፍለ ዘመን በንግሥት ዜኖብያ መሪነት ብዙ የሮም ግዛተ መንግሥትን ተቆጣጥረው ነበር።[185]

ሰሜናዊ አረብያ ብዙ ክርስቲያን መነኮሳትና መናንያን በገዳማትና በተለዩ ዋሻዎች ውስጥ የሚኖሩበት አካባቢ ነበር።

በምዕራብ በኩል አፍሪካዊት ክርስቲያን መንግሥት አቢሲንያ ትገኛለች። በቀይ ባሕር ማዶ የሚገኙ ሲሆን ከየመንና ከሮማ ግዛተ መንግሥት ጋር የሰነበተ ግንኙነት ነበራቸው። በወቅቱ ደግሞ በክርስቲያኖች ላይ ለደረሰ ጭፍጨፋ ምላሽ የመንን ድል በመንሳት በመካ ላይ ዘምተዋል።

በደቡብ የአረብ መንግሥታት የነበሩ ሲሆን ፋርሳውያንና ሮማውያን ቦታ ለመያዝ ይሽቀዳደማሉ። ከእነዚህ መካከል በየመን የሚገኝ አንዱ ይሁዲን ተቀብሏል። አረቦች

185 Robert G. Hoyland, Arabia and the Arabs, U.K., London: Routledge, 2001, pp. 75-76.

አነስተኛ መንግሥታት ቢኖራቸውም ትልቅ ግዛተ መንግሥት ግን አልነበራቸውም። የአነስተኛ መንግሥታት ስብስቦች፣ በጎሣ ተከፋፍለው የሚኖሩና ዘላኖች ነበሩ። ብዙዎቹ ነጋዴዎች ነበሩ። የመካ ነጋዴዎች በሦርያ ውስጥ እንደ ማረፍያ የሚያገለግላቸው ቦታ ነበራቸው።

ባሕላዊው የአረቦች ሃይማኖት እንደ ድንጋይ፣ ዛፍ፣ ፀሐይና ጨረቃን የመሳሰሉትን ፍጥረታት ማምለክ ነበር። ጣዖት አምልኮ፣ በመንፈስ የሚመሩ ገጣሚያንና ጠንቋዮች ነበሩ። ብዙ አማልክት ይመለኩ የነበሩ ሲሆን ከነዚያ መካከል አላህ አንዱ ነበር። አንዳንዶች ሕይወት ማለት በምድር የሚከትምና ከሞት በኋላ የሌለ ነው።[186] ሆኖም የአረቦች ሃይማኖት የተደራጀ ነበር። የተቀደሱ ወራትን፣ የፆምና የበዓል ቀናትን የሚያሳይ የቀን አቆጣጠር፣ ተጓዥ ወደ ተቀደሱ ቦታዎች ተጉዞ ሃይማኖታዊ ሥርዓቶችን መፈፀም እንዲችል ውጊያ የማፈፀምባቸው ወራት ነበሩ።

አንዳንድ የአረብ ጎሣዎች ክርስትናን ተቀብለው ነበር።

> ከአራተኛው እስከ ስድስተኛው ክፍለ ዘመናት ክርስትና ወደ አረብያ ገብቶ ነበር። የሰሰናውያን (ፋርሳውያን) ቤተክርስቲያን በጣም ጠንካራ ስለነበረች በምሥራቃዊ አረብያ በሚገኙት ጠረፋማ አካባቢዎችና ደሴቶች ላይ በርካታ አብያተ ክርስቲያናት ነበሩ። ከአምስተኛው ክፍለ ዘመን አጋማሽ አንስቶ ቢዛንቲን ክርስትናን በደቡባዊ አረብያ ውስጥ ለማስፋፋት ትሠራ ነበር፤ ይህንን ደግሞ በወዳጇ በኢትዮጵያ አማካይነት ትሠራ የነበረ ሲሆን ይህ ሁኔታ ከይሁዲ አቀንቃኞች ጋር ግጭትን ፈጥሮ ነበር። በዚያን ወቅት በብዛት ክርስትናን የተቀበሉት የሰሜን አረብያ ነዋሪዎች ነበሩ። ብዙ ጊዜ ከክርስትና አምላክ ሃያልነት የተነሳ ክርስትናን እንደተቀበሉ የሚነገርላቸው ሲሆን ተዓምራት አድራጊ ቅዱሳን ሰዎች እንደነበሩ ይነገራል።[187]

እነዚህ ክርስቲያን ሚስዮናውያን የሐዋርያት ዓይነት ስብዕናዎች ነበሩ። ጣዖታትን ይቃወማሉ፣ ሰዎች ክርስትናን እንዲቀበሉ ይጠይቃሉ፣ ሰዎችም ወደ እነርሱ ይሳባሉ። ግብርና፣ ንግድና የራሳቸው ሃይማኖታዊ መዋቅሮች የነበሯቸው የአይሁድ ማሕበረሰቦችም ነበሩ። በብዙ መንገድ አረብያ ለክርስቲያኖችና ለአይሁድ የስብከት ምድር ነበር። የመስበክ ነፃነት የነበረ ሲሆን ክርስቲያኖችና አይሁድ ቅዱሳት መጻሕፍታቸውን ወደ አካባቢው በማምጣት ታሪኮችን ይናገሩ ነበር። ለዚህ ነው ቁርአን የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪኮችን ሲጠቅስ ሰዎች ቀደም ሲል ዕውቀት እንደነበራቸው ቅድመ ግንዛቤን በመያዝ የሚተርከው። አሓዳዊነት በአረብ ባሕረ ሰላጤ ሕያውና አዳጊ ነበር።

---

186 ቁርአን 45:24

187 Robert G. Hoyland, *Arabia and the Arabs*, U.K., London: Routledge, 2001, p. 147.

ይህ ትምሕርት በሙሐመድ ቤተሰብ ላይ እንኳ ተፅዕኖ ነበረው። አጎቱ (የሚስቱ አጎት) ወረቃ ክርስትናን መቀበሉንና በመካ ውስጥ የወንጌል ጽሑፎችን ይዞ ያገለግል እንደነበር እናነባለን።

> ወረቃ … ከእስልምና ዘመን በፊት ክርስትናን ተቀብሎ የነበረ ሲሆን ቅዱሳት መጻሕፍትን በእብራይስጥ ፊደላት ይጽፍ ነበር። አላህ የፈቀደለትን ያህል ከወንጌል በእብራይስጥ ይጽፍ ነበር። (ሳሂህ አል-ቡኻሪ ቅፅ 1፣ መጽፍ 1፣ ቁጥር 3)
>
> ወረቃ ቅዱሳት መጻሕፍትን ያጠና ሊቅ ነበር።[188] ወረቃ ከክርስትና ጋር ራሱን በማቆራኘት ቅዱሳት መጻሕፍትን በጥልቀት እስኪያውቅ ድረስ ያጠና ነበር።[189]

## ስለ ሙሐመድ ሕይወት ከየት ነው የምንማረው?

ስለ ሙሐመድ ሕይወት ሲነሳ የሕይወት ታሪኩን ከቁርአን መማር እንደማንችል መታወቅ አለበት። ቁርአን በሕይወቱ ውስጥ ላጋጠሙት ሁኔታዎች በንግግር የሰጠው ምላሽ ሲሆን እነዚያ ሁኔታዎች ምን እንደሆኑ አልጻፈም። የሙሐመድን የሕይወት ታሪክ ለማወቅ ሌሎች እስላማዊ መጻሕፍትን ማንበብ ወሳኝ ነው። እነዚህም የመጀመርያዎቹ ሲራ የተሰኙ መጻሕፍት ናቸው። ቀዳሚያን የሚባሉት የሚከተሉት ናቸው።

- ኢብን ኢሳቅ (773 ዓ.ም.) *ሲራት ረሱል አላህ*
- አል-ወቂዲ (822 ዓ.ም.) *ኪታብ አል-መግሐዚ*
- ኢብን ሰዓድ (852 ዓ.ም.) *ኪታብ አል-ጠበቃት አል-ከቢር*

ሁለተኛ ሐዲስ የሚባሉ አሉ። እነዚህ ስለ ሙሐመድና ስለ ተከታዮቹ ግዙፍ የሆኑ የንግግሮች ስብስብ ናቸው። ዋና ዋናዎቹ የሱኒ ስብስቦች፡-

- አል-ቡኻሪ (870 ዓ.ም.)
- ሙስሊም (875 ዓ.ም.)
- አቡ ዳውድ (875 ዓ.ም.)
- አል-ቲርሚዚ (892 ዓ.ም.)
- አል-ነሳዒ (915 ዓ.ም.)
- ኢብን ማጃህ (886 ዓ.ም.)

የሺአዎች ደግሞ፡-

- ሙሐመድ ኢብን ያቁብ አል-ኩሉኒ (939 ዓ.ም.)

---

188 Ishaq, p. 83
189 Ishaq, p. 99

- ሙሐመድ አል-ሁሚ (991 ዓ.ም.)
- ጣሒር አል-ሸሪፍ አል-ሙርተዘ (1004 ዓ.ም.)
- ሙሐመድ አል-ቱሲ (1067 ዓ.ም.)

ሙሐመድ የሞተው በ632 ዓ.ም. ሲሆን እነዚህ ሁሉ መጻሕፍት ከእርሶ ህልፈት ከብዙ ዓመታት በኋላ እንደተጻፉ ማየት ትችላላችሁ። ከሁሉ በላይ ቀዳሚና ተፅዕኖ ፈጣሪ የሆነው የኢብን ኢስሐቅ *ሲራት ረሱል አላህ* ነው። ሙስሊሞች ከሞላ ጎደል እነዚህን መጻሕፍት አላነበቧቸውም። በዚህ ፋንታ ስለ ሙሐመድ በመሪዎቻቸውን በኋለኞች ጸሐፍት ይነገራቸዋል።

የሙሐመድ ሕይወት በተለምዶ በሁለት ደረጃዎች ይከፈላል፤ በመካና በመዲና ያሳለፋቸው ጊዜያት። አሁን እነዚህን እንመለከታለን።

## ሙሐመድ በመካ ውስጥ 610-622 ዓ.ም.

ሙሐመድ በመካ በ570 ዓ.ም. አካባቢ ተወለደ። አረብ የነበረ ሲሆን የቁረይሽ ጎሣ አባል ነበር። አባቱ አብደላ ከእርሱ መወለድ በፊት የሞተ ሲሆን በመዲና ተቀብሯል። ከተወሰኑ ዓመታት በኋላ እናቱም በበሞቷ ምክንያት ከሌሎች ዘመዶቹ ጋር ለመኖር ተገድዶ ነበር፤ የመጨረሻ የኖረው ከአጎቱ አቡ-ጧሊብ ጋር ነበር። ሙሐመድ ዕድሜው 12 በነበረ ጊዜ አጎቱ አቡ ጧሊብ ወደ ሦርያ እንደወሰደውና እዚያም ባሕሬ የተሰኘ መነኩሴ ከሙሐመድ ጋር ስለ ፈጣሪ እንዳወራ ግለ ታሪኩ ይናገራል።

## ሕልሞችና ራዕዮች

ወጣት በነበረ ጊዜ ከዲጃ ለተሰኘች ሴት ተቀጥሮ መነገድ ጀመረ። በ15 ዓመታት ብትበልጠውም እርሱ የ25 ዓመት ወጣት ሳለ ተጋብተው ብዙ ልጆችን ወልደዋል። ይህ ደግሞ በመካ ውስጥ ኃብትና ከበሬታን አትርፎለታል። ሃይማኖታዊ እንደነበረና በታማኝነቱ እንደሚታወቅ ተነግሮናል። የመጀመርያው መገለጡ ልክ እንደ መልካም ሕልም ነበር ተብሎለታል።[190] ደግሞም፡-

> ብዙ ጊዜ በመካ አቅራቢያ ወደሚገኘው የሒራ ዋሻ በመሄድ በፅሞና ያሰላስልና ከፈጣሪ ዘንድ አብርሆትን ይፈልግ ነበር።[191]

ዕድሜው አርባ ሲሞላው በዋሻ ውስጥ በነበረበት ሰዓት ሙሐመድ የአካላዊ ጥቃት[192] ዓይነት ሁኔታ የገጠመው ሲሆን በዚያ ሁኔታ ውስጥ ሳለ "አንብብ" የሚል ድፅ ሰማ፤

---

[190] Sahih al-Bukhari: 3; vol. 1, bk. 1, no. 3

[191] Prof. Masud ul Hasan, vol. 1, p. 52

[192] ይህ ሁኔታ ከባድ ከመሆኑ የተነሳ በጆሮው ውስጥ የደውል ዓይነት ድምፆችን ይሰማ ነበር (*Sahih Muslim*: bk. 30, no. 5765)። ራሱን በመሳት ይወድቅ ነበር (Al-Tabari, *The History of al-Tabari*, vol.

እንዲያነበንብም ቃላት ተገለጡለት።[193] መጀመርያ ላይ ይህ ልምምድ ግራ አጋብቶት ነበር። መጀመርያ ላይ ክፉ መንፈስ የያዘው መስሎት ወይም ጋኔን የያዘው ገጣሚ ሊሆን እንደሆነ በማሰብ ራሱን ለማጥፋት ይመኝ ነበር።[194] ሚስቱ ነገሩ እሱ እንዳሰበው አለመሆኑን ካስረዳችው በኋላ ወረቃ ወደተሰኘው ክርስቲያን አጎቱ ዘንድ ወሰደችው። ከዚያም ወረቃ የሙሐመድን ልምምድ ከተረጎመ በኋላ መልአኩ ገብርኤል እንዳገኘውና ለሕዝቡ ነቢይ እንዲሆን እንደተመረጠ ነገረው።[195] ሙሐመድን የተናገረው አምላክ ስም *አላህ* ሲሆን ሙሐመድ ስለ አላህ በመካ ከተማ ማስተማር ጀመረ።

በመጀመርያዎቹ ሦስት ዓመታት በግልና ለቤተሰቡ አባላት ብቻ አስተማረ። አንዳንዶች ነቢይነቱን አምነው የተቀበሉ ሲሆን ሌሎች ተጠራጥረውታል። ከዚህ በኋላ በአደባባይ ማስተማር ጀመረ። በመካ ከተማ ውስጥ ስለ ሃይማኖት ከሚያስተምሩ ሰዎች መካከል አንዱ የሆነ ሲሆን ጣዖታትን እየተቃወመ ማስተማር እስከጀመረበት ጊዜ ድረስ በድብልቅ ስሜት ነበር የተስተናገደው፤ ኋላ ላይ ግን ተቃውሞ ሲነሳበት አጎቱ ከጉዳት ተከላክሎታል።[196] በጊዜ ሒደት ብዙ ሰዎች የተከተሉት ሲሆን አንዳንዶች ትልቅ ስም የነበራቸው የመካ ነዋሪዎች ነበሩ። ሙሐመድ በገዛ ቤቱ፣ በገበያ ቦታ፣ በከተማ ውስጥና ሰዎች ለሃይማኖታዊ ጉዞ በሚሄዱባቸው ጎዳናዎች ላይ ይሰብክ ነበር። አንዳንድ የሌላ ከተማ ሰዎች በተለይም በመካ የሚኖሩት እስልምናን ተቀበሉ። በአጠቃላይ ሲታይ ግን በዚያን ወቅት የተከታዮቹ ቁጥር አነስተኛ ነበር።

## ተቃውሞ

የመካ ነዋሪዎች ሙሐመድንና ተከታዮቹን በማሽሟጠጥ፣ በአካላዊ ጥቃት እንዲሁም ለተወሰነ ጊዜ በጎሣው ላይ አድማ በመምታት ዝም ሊያሰኟቸው ሞክረው ነበር። ነገር ግን አልቻሉም። በዚህ ወቅት ሙሐመድ በሃይል እርምጃ ምላሽ አልሰጠም። በዚህ ፋንታ ግን ከመካ ውጪ ከነበሩ ጎሣዎች ጋር ግንኙነቱን ማጠናከር ተያያዘ።

> ቁረይሾች ከጎሣቸው ያልሆኑ በሌላ ቦታ የሚኖሩ የነቢዩ ተከታዮች መኖራቸውን ባወቁና ሌሎች ተከታዮቹ ከእነርሱ ጋር ተቀላቅለው አዲስ ቦታ ላይ ኑሮ ጀምረው

---

viii,
pp. 2-3)። በቀዝቃዛ ቀን እንኳ ያልበው ነበር (*Sahih al-Bukhari*: vol. 5, bk. 59, no. 462)። ፊቱ ይቀላ ነበር በከባድ ሁኔታም ይተነፍስ ነበር (*Sahih al-Bukhari*: vol. 6, bk. 61, no. 508)። እንደ ግመል ያንኮራፋና አረፋ ይደፍቅ ነበር (*Sahih al-Bukhari*: vol. 3, bk. 27, no. 17)። አፉና ከናፍርቱ ይንቀጠቀጡ ነበር (*Sahih al-Bukhari*: vol. 6, bk. 61, no. 564)።

193 Ibn Ishaq, pp. 104-107; *Sahih al-Bukhari*: vol. 1, bk. 1, no. 3

194 Ibn Ishaq, p. 106; *Sahih al-Bukhari*: vol. 9, bk. 87, no. 111

195 ምናልባትም ወረቃ ሙሐመድን ጎብኝቶ ይሆናል።

196 Ibn Ishaq, p. 118

> አዲስ ጠባቂዎችን እንዳገኙ ባወቁ ጊዜ ነቢዩ ወደ እነርሱ እንዳይሄድ ፍርሃት አደረባቸው ምክንያቱም ሊዋጋቸው ወስኖ እንደነበር አውቀዋልና።[197]

በዚህ ጊዜ ስለ ፈጣሪ ያስተምርና ወደ እርሱ የሚመጡትን ጥቅሶች ያነበንብ ነበር። ይህ የቁርኣን ጅማሬ ነበር። በወቅቱ የስብከቱና የቁርኣን ይዘት፦

- ሙሐመድ እውነተኛ ነቢይ ነው።
- አንድ አምላክ ብቻ አለ።
- ጣዖታት ዋጋ የላቸውም።
- የፍርድ ቀን፣ ገነትና ገሃነም አሉ።

## ሙሐመድ ማን ነበር?

ከጻፍኳቸው ነገሮች አብዛኞቹን በዚህ ዘመን በሚገኙት እስላማዊ የሕትመት ውጤቶች ውስጥ ታገኟቸዋላችሁ። ነገር ግን ሙስሊም መሪዎች ሊነግሩን የማይፈልጓቸው ሙሐመድ ያደረጋቸው ነገሮች አሉ። ሙስሊም መሪዎች ስለ ሙሐመድ ሲነግሩን እስልምናን በማስፋፋት ስሜት ስለሆነ የሚናገሩትን ነገር መርጠው ይናገራሉ። ይህን መሰል መረጣ መኖሩን በእነዚህ እስላማዊ መሪዎች በግልፅ ሲነገር እናያለን።

> በፈጣሪ ፈቃድ ይህንን የነቢዩን ግለታሪክ የምጀምረው ኢብን ኢስሐቅ በመጽሐፉ ውስጥ የጻፋቸውን አንዳንድ ነገሮች በማስወገድ ነው ... እነዚህም ለመነጋገር አሳፋሪ የሆኑ ነገሮችና አንዳንድ ሰዎችን ሊያስጨንቁ የሚችሉ ናቸው።[198]
>
> ከነቢዩ የነቢይነት ተልዕኮ ጋር የማይጣጣሙ ወይንም ለእርሱ የማይመቹ የሚመስሉ ትውፊቶች በሙሉ ተቀባይነት ማግኘት የለባቸውም።[199]

ይህ ማለት ስለ ሙሐመድ ሕይወት የተጻፈ ታሪክ ምንም ያህል አስተማማኝ ቢሆን አስጨናቂ፣ አሳፋሪ ወይንም እርሱን የማያከብር ከሆነ መነገር የለበትም ማለት ነው። ስለዚህ ሙስሊሞች የሙሐመድን ታሪክ የያዙ ጽሑፎችን ወይንም ዲቪዲዎችን የሚያድሉ ከሆነ ይዘታቸው በጣም የተመረጠና የሙሐመድን ማንነት በትክክል እንደማይወክል መታወቅ አለበት። በጣም በስፋት የተዘገቡ ነገር ግን ለሙስሊሙ ማሕበረሰብም ሆነ ለሌላው ሕዝብ የማይነገሩ ሁለት ምሳሌዎችን እጠቅሳለሁ። የመጀመርያው *ሰይጣናዊ ጥቅሶች* የተሰኘ ክስተት ነው፦

---

197 Ibn Ishaq, p. 221

198 "Ibn Hisham's Notes" in Ibn Ishaq, p. 691

199 Muhammad Zubayr Siddiqi, *Hadith Literature - Its Origin, Development & Special Features*, 2008, p. 114.

> የሰይጣናዊ ጥቅሶች ክስተት በመጀመርያዎቹ 150 ዓመታት ውስጥ የሙስሊም ማሕበረ ሰቦችን የታሪክ ትውስታ ተቆጣጥሮ የነበረ ሲሆን በተፍሲርና ሲራህ-መግሐዚ ዘርፍ በሚሠሩ ከሞላ ጎደል ሁሉም ሊቃውንት የተመዘገበ ነው።[200]

ሙሐመድ በመካ በነበረ ጊዜ ከመካውያን በአጎቱ ጥበቃ ይደረግለት ነበር። ሆኖም አብዛኞቹ ተከታዮቹ እንዲህ ያለ ጥበቃ ያልነበራቸው ሲሆን ከዚህ የተነሳም ተሰደዱ። ስደተኙቹም ክርስቲያናዊት መንግስት ወደነበረችው አቢሲንያ መጡ። ይህ ሁኔታ አመቺ ባለመሆኑ ከመካውያን (ቁረይሾች) ጋር እርቅን ለማውረድ ሲል ስለ መካ አማልክት ተከታዮን ጥቅስ ተናገረ፡-

> “አል-ላትንና አል-ዑዛን አያችሁን? ሦስተኛይቱንም መናትን አያችሁን? እነዚህ ከፍ ያሉ ግሃራኒቅ (በራሪዎች) ናቸው። ምልጃቸውም ተስፋ ይደረጋል።” ቁረይሾች ይህንን በሰሙ ጊዜ አማልክታቸውን በማሞጋገሱ ደስተኛ በመሆን ያደምጡት ጀመር ... ከዚያም ሰዎች ሁሉ ወደየመጡበት ተበተኑ፣ ቁረይሾችም ስለ አማልክቶቻቸው በተናገረው ነገር ሀሴት አድርገው “ሙሐመድ ስለ አማልክታችን እያደናነቀ ተናገረ” አሉ።[201]

ሙሐመድ የመካ አማልክት ምልጃ ተቀባይነት እንዳለው በመናገሩ ተቀብሏቸዋል። ከዚህም የተነሳ መካውያን ከእርሱ ጋር ሰላምን ስለፈጠሩ ተከታዮቹ ከአቢሲንያ መመለስ ጀመሩ።

> ከዚም መልአኩ ገብርኤል ወደ ሙሐመድ በመምጣት “ሙሐመድ ሆይ ምን ያደረከው ምንድነው?” አለው። “እኔ ከፈጣሪ ዘንድ ያላመጣሁልህን ነገር ለዚህ ሕዝብ አንብበሃል፤ እርሱ ያልተናገረውንም ተናግረሃል።” ... አላህ ሰይጣን የሚጥለውን ያስወግዳል።[202]

ስለዚህ በእስላማዊ ምንጮች መሠረት ሙሐመድ የሰይጣንን ቃል በመናገር አሓዳዊነቱን አመቻምቿል። ይህ በጣም ከባድ ጉዳይ ቢሆንም ሙስሊሞች የማይማሩት ለሌላውም ሕዝብ የማይነግሩት ጉዳይ ነው።

በሙሐመድ ሕይወት የመጀመሪያዎቹ እስላማዊ የሕይወት ታሪኮች (ሲራ) ውስጥ፣ የሰይጣን ጥቅሶች ታሪክ ለመድገም ሦስት ገጾችን የሚፈጅ ረጅም ታሪክ ነበር። ነገር ግን፣ በሐዲስ ውስጥ፣ ታሪኩ ወደ አንድ አጭር አረፍተ ነገር ተስተካክሏል፣ በታሪኩ ውስጥ ያሉ ሁሉም አፀያፊ ነገሮች ተወግደዋል።

---

200 Shahab Ahmed, *The Satanic Verses Incident in the Memory of the Early Muslim Community*, Princeton University PhD thesis, 1999, p. i. Also, "Ibn Taymiyyah and the Satanic Verses", *Studia Islamica*, no. 87, 1998, p. 70 & 122.
201 Ibn Ishaq, pp. 165-166
202 Ibn Ishaq, p. 166

ኢብን አባስ እንዳስተላለፈው ነቢዩ ሱረቱ ነጅምን እይቀራ ሰገደ ሙስሊሞችም ጣዖት አምላኪያንም አጋንንቶችም ሁሉም አብረውት ሰገዱ። ሳሂህ አል-ቡኻሪ 1071፣ ቅጽ 2 መጽሐፍ 19 ቁጥር 177

ሐዲሱ ከሙሐመድ ከ200-300 ዓመታት ገደማ በኋላ ነው የተዘጋጀው። ይህ እንግዲህ የሙሐመድ ሕይወት ምን ያህል እየተሻሻለ እንደመጣ ያሳየናል።

ሁለተኛው ምሳሌ ሙሐመድ እንዴት በሌሎች ሰዎች አስተሳሰብ ይመራ እንደነበር ነው።

ኢብን አባስ እንዳወራው ነቢዩ ከአላህ ዘንድ ትዕዛዝ በሌለባቸው ጉዳዮች ላይ የመጽሐፉን ሰዎች (አይሁድና ክርስቲያኖች) የሚያደርጉትን ቀድቶ ያደርግ ነበር... (ሳሂህ አል-ቡኻሪ ቅፅ 7፣ መጽሐፍ 72፣ ቁጥር 799)

አል-በራ እንዳወራው ለአሥራ ስድስት ወይንም አሥራ ሰባት ዓመታት ያህል ቀወደ ኢየሩሳሌም ዞረን እንሰግድ ነበር። ከዚያም አላህ ፊቱን ወደ ቂብላ (መካ) እንዲያዞር ነገረው። (ሳሂህ አል-ቡኻሪ ቅፅ 6፣ መጽሐፍ 60፣ ቁጥር 19)

አነስ እንዳወራው እስልምናን የተቀበለ አንድ ክርስቲያን ነበረ፤ ይህ ሰው ምዕራፍ 2 እና 3ን ያነብ የነበረ ሲሆን ለነቢዩ (ቁርአንን) ጸሐፊ በመሆን ያገለግል ነበር። ኋላ ላይም ወደ ክርስትናው በመመለስ እንዲህ ሲል አወራ፡- "ሙሐመድ እኔ ከጻፍኩለት ነገር ውጪ ምንም ነገር አያውቅም።" ከዚያም አላህ ገደለው... (ሳሂህ አል-ቡኻሪ ቅፅ 4፣ መጽሐፍ 56፣ ቁጥር 814)

እነዚህ ሐዲሳት ሙሐመድ ምን ያህል በአይሁዳዊያንና በክርስቲያኖች ተፅእኖ እንደተደረገበት ያሳያል። ይሁን እንጂ ሙስሊም ሰባኪያን ይህንን ለመእመኑ ሙስሊም አይነግሯቸውም።

እስልምናና ክርስትና በጣም የሚለያዩት እዚህ ጋ ነው። እንደ ክርስቲያኖች ስለ ኢየሱስ ሁሉንም ነገር እንናገራለን፤ ሰዎችም ቀዳሚያን የሆኑትን ስለ እርሱ የተጻፉትን ዘገባዎችን እንዲያነቡ እናበረታታለን። ነገር ግን በእስልምና ስለ ሙሐመድ የሚነገረን የተወሰነ ነገር ነው፤ ቀዳሚያን የሕይወት ታሪኮቹንም እንድናነብ አንበረታታም።

## ሙሐመድ በመዲና 622-632 ዓ.ም.

## የመጀመርያው እስላማዊ መንግሥት

አጎቱ ሲሞት ሙሐመድ በመካ የነበረውን ጥበቃ በማጣት ወደ መዲና ገበያ ተንቀሳቀሰ። ይህ ጉዞ ሒጅራ በመባል የሚታወቅ ሲሆን በሕይወቱ ውስጥ ወሳኝ ነጥብ ነበር። በመዲና ውስጥ ሙስሊሞች ስለነበሩ ሙሐመድ እዚያ ሲደርስ ድጋፍን አግኝቷል። ዳኛ በመሆን ከከተማዋ ጋር የሰላም ውል ገባ። ወታደሮችን ማዘጋጀት የጀመረው እዚያ ሲሆን የእስልምና ዘመን

አቆጣጠርም የሚጀምረው ከዚያን ዘመን ነው፤ በልደቱ ወይንም ነቢይ መሆኑን ከተናገረበት ጊዜ ሳይሆን የመጀመርያው እስላማ መንግሥት ከተመሠረተበት ጊዜ ይጀምራል።

ስለ ጦርነት፣ ስለ ሕግጋት፣ የሌሎች እምነት ተከታዮችን አያያዝ እንዲሁም በውጊያ ላይ ለተሳተፉ ሰዎች ስለተሰጠው የገነት ተስፋ የሚናገሩ የቁርኣን ጥቅሶችን መስተላለፍ ተያያዘ። ይህ *የመደራጀት ጊዜ* በመባል ይታወቃል።

## ዝነኛ አውደ ውጊያዎች

አሁን ሙሐመድ የጦር ሠራዊት ስላደራጀ መጠቀም ጀመረ። በዙርያው የነበሩትን ማጥቃት ወይንም የሰላም ስምምነት ማድረግ ጀመረ።[203] በተቀናጀ ሁኔታ ያደረጋቸው በርካታ ውጊያዎች ቢኖሩም በጣም ታዋቂዎቹ ሦስት ነበሩ። የመጀመርያው *የበድር ጦርነት* ይሰኛል።

> ከዚያም አቡ ሱፊያን ቢን ሐርብ ከሦርያ ብዙ የቁረይሽ ነጋዴዎችን አስከትሎ እየመጣ እንደሆነ ነቢዩ ሰማ። እነርሱም ገንዘባቸውንና ሸቀጦቻቸውን ይዘው ሠላሳ በሚሆኑ ሰዎች ታጅበው እየመጡ ነበር … ከዚያም ለሙስሊሞች እንዲህ የሚል ትዕዛዝ ሰጠ፣ "እነኚህ ንብረታቸውን ይዘው እየሄዱ ያሉ የቁረይሽ ነጋዴዎች ናቸው፤ ውጡና አጥቋቸው።"[204]

መካውያን የሙሐመድን ዕቅድ ስለሰሙ የራሳቸውን ወታደሮች አዘጋጁ። ሁለቱ ሠራዊቶች ገጥመው ሙስሊሞች አሸነፉ።

ሁለተኛው ታዋቂ ውጊያ *የኡሑድ* ጦርነት ነበር። ይህ መካውያን በበድር ለገጠማቸው ሽንፈት ለመበቀል የመጡበት ሲሆን ሙስሊሞች ተሸንፈዋል።

ቀጣዩ *የምሽጎች ጦርነት* ይሰኛል። ይህ ብዙ የአረብ ጎሣዎች ሙሐመድን ለማስቆም ለመጨረሻ ሙከራ የተሰባሰቡበት ነበር። መዲናን ለማጥቃት ቢመጡም ሙስሊሞች ምሽጎችን በመቆፈር አስቁመዋቸዋል። ረዘም ያለ ከበባ የነበረ ሲሆን መካውያን በስተመጨረሻ ሳይሳካላቸው ተመልሰዋል፤ ሙሐመድን አቅሙን ማሳደቅ ቀጥሏል።

## የአረብ አይሁድና ክርስቲያኖች

በመዲና ውስጥ ሦስት የአይሁድ ጎሣዎች ነበሩ። ሙሐመድ በመጣ ጊዜ አይሁድ እንደ ነቢይ ባይቀበሉትም ከእርሱ ጋር በመተባበር እንደ ከተማይቱ ነዋሪ በሰላም ለመኖር ጥረት አድርገዋል። ይሁንና በዚህ መንገድ ለረጅም ጊዜ አልቀጠለም። በአይሁድና በሙስሊሞች መካከል የተፈጠረ መጠነኛ ግጭት የነበረ ሲሆን ወደ ከባድ ግጭት አድጎ የቀይኑቃዕ ጎሣ የሆኑት አይሁድ ከመዲና ተባርረዋል። ከዚያም ከኡሑድ ጦርነት በኋላ የነዲር ጎሣ አይሁድ

---

[203] Ibn Ishaq, pp. 281-289

[204] Ibn Ishaq, p. 289

መካውያንን ረድተዋል በሚል ተጠረጠሩ፤ ከዚያም ከበባ ከተደረገባቸው በኋላ ከመካ ተባረሩ። በመጨረሻም በምሽጎች ጦርነት ወቅት የቁረይዟ ጎሣ አይሁድ መዲናን ለከበቡት መረጃ ሰጥተዋል ተባለ። በዚህም ምክንያት ወንዶቻቸው የታረዱ ሲሆን ሴቶችና ህፃናት ለባርነት ተከፋፍለዋል።

ከአይሁድ በተፃራሪ የአረብያ ክርስቲያን ጎሣዎች ከማንም ጋር ሳይወግኑ ገለልተኛ ሆነው ቆይተዋል።[205] ለሙሐመድ ግብር የመክፈል ግዴታ የነበረባቸው ሲሆን በዚያን ወቅት በተወሰነ ደረጃ ከጥቃት ነፃ ነበሩ።

ሙስሊም ወሪዎች ሙሐመድ ለዓለም ችግሮች ሁሉ መፍትሄ መሆን የሚችል ምሳሌያዊ መሪ መሆኑን ይናገራሉ፤[206] ሆኖም ከአይሁድ ጎሣዎች ጋር የነበረው ግንኙነት ተፃራሪውን ያሳያል። በጎሣና ሃይማኖታት መካከል ሊነሱ የሚችሉ ተራ ግጭቶችን እንኳ በትክክል መፍታት አልቻለም። በመጠነኛ የግለሰቦች ግጭት ነገሮች ሲካረሩ በሰላም መፍታት ተስኖታል። በዚህ ፋንታ መላውን ጎሣ ከከተማ አባሯል። ይህ ሁኔታ አለመተማመንን በመፍጠሩ ምክንያት ሌላ ጎሣ የተባረረ ሲሆን ሦስተኛ ጎሣ ደግሞ ለጭፍጨፋና ለባርነት ተዳርጓል። ሙሐመድ የመሠረታት "ምሳሌያዊት" ከተማ መዲና ሰዎችን ማኖር የቻለችው ሁሉም ሙስሊሞች ሲሆኑ ብቻ ነበር፤ ይህም ሆኖ ኋላ ላይ ችግሮች ተፈጥረው ሰላም ደፍርሷል። ይህንን ወደ በኋላ እናያለን።

## አረብያን መጠቅለል

ከምሽጎች ጦርነት በኋላ ሙሐመድ ከመካውያን ጋር የሰላም ውል ተፈራረመ። ሙስሊሞች ለሃይማኖታዊ ጉዞ መካን መጎብኘት ይችሉ የነበረ ሲሆን አንዱ ሌላውን ወገን አያጠቃም ነበር። ይህ የሰላም ውል ወሳኝ ነበር ምክንያቱም ሙሐመድ የተቀረውን የአረብያ ክፍል ለማስገበር ጊዜ ገዝቶለታልና። ይህንን በተለያዩ መንገዶች ፈፅሟል። መጀመርያ እስላምናን በማስተማር አንዳንድ ጎሣዎች በሰላም እንዲሰልሙ አድርጓል። ሁለተኛ ጦር በመምዘዝ። ሙሐመድ ደከም ያሉትን የአረብ ጎሣዎች እስልምናን እንዲቀበሉ ይጋብዝና ጥሪውን ካልሰሙ ይዋጋቸዋል።

> ሙሐመድ ከአንድ ጎሣ እስላማዊ የጸሎት ጥሪ ከሰማ ይታቀባል፤ ካልሰማ ግን ያጠቃቸዋል።[207]
>
> የአላህ መልእክተኛ ካሊድ ቢን ዋሊድን ከ አራት መቶ ሙስሊሞች ጋር ወደ በኑ አል-ሐሪሥ ላከ … ከመዋጋቱ በፊት ሦስት ጊዜ ወደ እስልምና እንዲጠራቸው

---

205 Prof. Masud ul Hasan, vol. 1, p. 68.
206 Prof. Masud ul Hason, vol. 1, pp. 76-77. This is also a common theme in the leaflets used to promote Islam.
207 Ibn Ishaq, p. 511

ነገረው … ጥሪውንም ተቀበሉ። እስልምናን፣ ሥርዓቶቹን፣ የአላህን መጽሐፍና የነቢዩን ሱና ሊያስተምራቸው ከእነርሱ ጋር ኖረ።[208]

“ኢብን ዑመር እንዳስተላለፈው የአላህ መልእክተኛ እንዲህ ብለዋል፤ ሰዎች ከአላህ በስተቀር ሊመለክ የሚገባው እንደሌለና ሙሐመድም ደግሞ መልእክተኛው መሆኑን እስኪመሰክሩ ድረስ እንዲሁም ሶላትን ደንቡን ጠብቀው እስኪሰግዱ ድረስና ዘካትን እስኪሰጡ ድረስ እንድዋጋቸው (በአላህ) ታዝዣለሁ…”[209]

ሦስተኛ ጠንካራና ታላላቅ ጎሣዎችን ነቢይነቱን እንዲቀበሉ ጥሪ ቢያደርግላቸውም ራስ ገዝነታቸውን አልተቀናቀነም። አንዳንድ ታላላቅ ጎሣዎች ተቀብለውታል ነገር ግን ያልተቀበሉት ባልተቋረጠ የጠላትነት ስሜት ውስጥ ኖረዋል። በዚህ ሁኔታ ጎሣው እስልምናን እስኪቀበል ድረስ መሪዎቻቸውን ነፍሰ ገዳዮችን እየላከ ያስገድል ነበር። የኸትማ ጎሣ ታዋቂ ሰዎች የነበሩትን አቡ አፋክ እና አስማ ቢንት ማርዋንን በዚህ ሁኔታ አስገድሏል። [210]

አራተኛ ሙሐመድ ገንዘብን በመጠቀም ሰዎች እስልምናን እንዲቀበሉ ያደረገባቸው ጊዜያት ነበሩ።

ነቢዩም ለመሊክ ሙስሊም ሆኖ ወደ እርሱ ቢመጣ ንብረቱን በሙሉ እንደሚመልስለትና አንድ መቶ ግመሎችን እንደሚሰጠው እንዲነግሩት ነገራቸው። ይህንን በሰማ ጊዜ መሊክ ወደ ነቢዩ መጣ … ነቢዩም ቤተሰቡንና ንብረቱን እንዲሁም መቶ ግመሎችን ሰጠው። ጥሩ ሙስሊምም ሆነ።[211]

በመጨረሻም ሙሐመድ ሌሎች የሃይማኖት ማዕከላትን፣ ማለትም ሌሎች ካዕባዎችን አጥፍቷል። እነዚህም ሌሎች የሃይማኖታዊ ጉብኝት ማዕከላት ነበሩ። ከዚያም መካ ብቸኛዋ ማዕከል ሆነች።

ጃቢር ቢን አብዱላህ እንዳወራው በቅድመ እስልምና ዘመን ዙል-ኸለሳ ወይም አል-ካዕባ አል-የመንያ ወይም አል-ካዕባ አሽ-ሻሚያ በመባል የሚታወቅ ቤት ነበር። የአላህ መልእክተኛ እንዲህ አለኝ “ከዙል ኸለሳ ልታሳርፈኝ ትችላለህ?” ስለዚህ 150 ሰዎች ሆነን ወደዚያ በመሄድ አጠፋነው፤ በቦታው የነበሩትንም ሰዎች ሁሉ

---

208 Ibn Sa'd, *Kitab Al-Tabaqat Al-Kabir*, vol. 1, p. 399

209 Sahih Al-Bukhari; Vol. 1 Book 2, Number 24

210 Ibn Ishaq, pp. 675-676

211 Ibn Ishaq, p. 593

ገደልን። ከዚያም ወደ ነቢዩ በመምጣት ነገርነው። እኛንና የአህማስ ጎሣ አባላትን ባረከ። (ሳሂህ አል-ቡኻሪ ቅፅ 5፣ መጽሐፍ 58፣ ቁጥር 160)።[212]

ቁርኣን በሃይማኖት ማስገደድ እንደሌለ መናገሩ እውነት ቢሆንም[213] ይህ ማለት ግን እስልምናን አለመቀበልና የወደድከውን ነገር ማድረግ ትችላለህ ማለት አይደለም። እስልምና የበላይ ሆኖ መግዛት አለበት፤ እርሱን የምትቃወም ከሆነ ቅጣት አለው።

> አቡ በክር እንዲህ አለ፡- "ምርጥ ምክር እንድሰጥህ በጠየከኝ መሠረት እሰጥሃለሁ። አላህ ሙሐመድን ከዚህ ሃይማኖት ጋር የላከው ሲሆን ሰዎች በውድም ሆነ በግድ እስኪቀበሉ ድረስ ታግሏል።"[214]

## ረሱል፣ ሰሃባና ታሊባን

በአረብኛ ሙሐመድ *ረሱል* ወይም መልእክተኛ ተብሏል። ከእርሱ ጋር የነበሩት ወዳጆቹ *ሰሃባ* በመባል የሚታወቁ ሲሆን የእነርሱ ተማሪዎች ደግሞ *ታሊባን* በመባል ይታወቃሉ። ሙሐመድ ተከታዮቹን ለወረራ እየላከ ያሰለጥን ነበር። ኢየሱስ ተከታዮቹን ለስብከት እየላከ ያሰለጥናቸው እንደነበረ ሁሉ[215] ሙሐመድም ተከታዮቹን ለውጊያና ለወረራ እየላከ ያሰለጥን ነበር። አንዳንድ ተከታዮቹ ግን መዋጋትን አይፈልጉም ነበር።[216] ሙሐመድ ለእርሱ መዋጋት በፈጣሪ ዘንድ ከፍተኛውን መንፈሳዊ ደረጃ እንደሚያስገኝ በግልፅ ተናግሯል። ሙሐመድ የጦርነትን ባሕል የፈጠረ ሲሆን ልምድ ያላቸውን ልበ ደንዳና ወታደሮችንም አፍርቷል።[217]

## የሙሐመድ ሚስቶች

የሙሐመድ ሚስቶች በሕይወት ታሪኩ ውስጥ ወሳኝ ሚና አላቸው። በቁርኣን ውስጥ ለእነርሱ የተነገሩና ስለ እነርሱ የሚናገሩ ብዙ ጥቅሶች ያሉ ሲሆን የሙስሊሞች ሁሉ እናቶችና የሴቶች ሁሉ ምሳሌዎች ተደርገው ይቆጠራሉ።[218] ሙስሊሞች ስለ ሙሐመድ እንደሚማሩት ሁሉ ስለ ሚስቶቹም ይማራሉ።

የሙሐመድ የመጀመርያዋ ሚስት ከዲጃ ትሰኛለች። ነቢይ መሆኑን ከማወጁ በፊት ያገባት ሲሆን በ15 ዓመታት ትበልጠዋለች። በእርሱ ለማመን የመጀመርያዋ ሰው እርሷ ስትሆን በዚህ ጋብቻ ወቅት ተደራቢ ሌላ ሴት አላገባም ነበር። ከእርሷ ሞት በኋላ ብዙ ሚስቶችን

---

212 Also Arabian temples Ibn Ishaq, p. 565.
213 ቁርኣን 2:256
214 Ibn Ishaq, pp. 668-669
215 Matthew 10, Mark 6:6-13, Luke 9:1-9, 10:1-24, John 15:17
216 2:216
217 ቁርኣን 4:95-96
218 ቁርኣን 33፡6

ያገባ ሲሆን ስለ እነርሱ የሚታወቁ ብዙ ታሪኮች አሉ። ለእርሱ አጋዥ የነበሩ ቢሆንም አንዳንዴ ሲያስቸግሩት ሁላቸውንም ለመፍታት ይዝት ነበር።[219]

በምዕራፍ 8 እንዳየነው የማደጎ ልጁ ዘይድን አግብታ የነበረች ዘይነብ የተባለች ሚስቱ ነበረች። ሙሐመድ ዘይነብን እርቃኗን በማየቱ ምክንያት ተመኛት።[220] ዘይድ ዘይነብን ለመፍታት ፈቃደኛ ቢሆንም የማደጎ ልጅን ሚስት ማግባት በዚያን ዘመን ነውር በመሆኑ ምክንያት ችግር ተፈጠረ። በዚህም ምክንያት የሙሐመድ አምላክ የማደጎ ልጅነትን የሚሽር ጥቅስ በማውረድ ዘይድ የሙሐመድ ልጅ እንዳይሆን ያደረገ ሲሆን[221] ይህ አምላክ ዘይነብን ለሙሐመድ የሚሰጥ ሌላ ጥቅስ አወረደ።[222]

በሌላ አጋጣሚ ደግሞ ሙሐመድ ሙሐመድ ለሚስቱ ለሐፍሳ ከባርያዋ ከግብፃዊቷ መርየም ጋር ወሲብ እንደማይፈፅም ቃል ገባላት። ሐፍሳ ሙሐመድ ከመርየም ጋር ሲማግጥ እጅ ከፍንጅ ይዛው ስለነበር ሁኔታውን ለሌሎች ሚስቶቹ በማውራቷ ምክንያት ችግር ተፈጥሮ ነበር።[223] ይህ ሁኔታ ተከታዩ የቁርኣን ጥቅስ እንዲወርድ በማድረግ ሙሐመድን ከመሃላው ነፃ አደረገው፡-

> “አንተ ነቢዩ ሆይ አላህ ለአንተ የፈቀደልህን ነገር ሚስቶችህን ማስወደድን የምትፈልግ ስትሆን (ባንተ ላይ) ለምን እርም ታደርጋለህ፤ አላህ እጅግ መሐሪ አዛኝ ነው። አላህ ለናንተ የመሐሎቻችሁን መፍቻ ደነገገላችሁ፤ አላህም ረዳታችሁ ነው፤ እርሱም ዐዋቂው ጥበበኛው ነው።” (ቁርኣን 66፡1-2)

ሙሐመድ አይሻን እንዲያገባ ሕልም ያየ ሲሆን በ6 ዓመቷ አጭቷት በ9 ዓመታ ጋብቻውን ፈፅሟል።[224]

ሙስሊም ወንዶች እስከ 4 ሚስቶች ብቻ እንዲያገቡ የተፈቀደላቸው ሲሆን ሙሐመድ ግን የፈለገውን ያህል እንዲያገባ ተፈቅዶለታል።[225] ሙሐመድ መድብለ ጋብቻን ከመፈፀሙም በላይ ለተከታዮቹ አስተምሯል፣ በገነትም ተመሳሳይ ነገር እንደሚጠብቃቸው ተስፋን ሰጥቷል።[226] ነገር ግን ሙሐመድ ሴት ልጁ መድብለ ጋብቻ ውስጥ እንድትገባ ፈቃደኛ አልነበረም፡-

---

219 ቁርኣን 66፡5
220 Al-Tabari, *The History of al-Tabari*, vol. viii, p. 4
221 ቁርኣን 33፡4
222 ቁርኣን 33፡37
223 Seyyed Hossein Nasr, *The Study Qur’an*, Sura 66: 1, fn. 1, p. 1389
224 *Sahih al-Bukhari*: vol. 5, bk. 58, no. 235-236
225 ቁርኣን 4:3, 33:50
226 ቁርኣን 44:51-54, 56:34-35, 78:31-33


አል ሚስዋር ቢን መኽረማ እንዳወራው የአላህ መልእክተኛ ምስባክ ላይ ቆሞ እንዲህ ሲል ሰምቼዋለሁ “በኑ ሒሻም አል-ሙግሂራ ሴት ልጃቸውን ለአሊ ቢን አቡ ጧሊብ እንዲድሩለት እንድፈቅድ ጠይቀውኛል። ነገር ግን ፈቃደኛ አልሆንኩም። አሊ ቢን አቡጧሊብ ልጃቸውን እንዲያገባ የምፈቅደው ልጄን ከፈታት ብቻ ነው። ምክንያቱም ፋጢማ የኔ አካል ናትና፤ እርሷ ለማየት የምትጠላውን እኔም እጠላለሁ፤ እርሷን የሚጎዳት ነገር ሁሉ ይጎዳኛል።” (ሳሂህ አል-ቡኻሪ ቅፅ 7፣ መጽሐፍ 62፣ ቁጥር 157)

## የአረብያ ነቢያት

ሙሐመድ በምድረ አረብያ ነቢይ ነኝ ለማለት ብቸኛው ሰው አይደለም። ከሌሎች ጎሣዎች የሆኑ ሌሎች ነቢያት ነበሩ። እነዚህ ጎሣዎች ሙሐመድን ሲቀበሉት ሁለት ነቢያት ይኖሯቸዋል። በአረብያ ውስጥ የነቢይነት እንቅስቃሴ በስፋት የነበረ ይመስላል። የምናውቃቸው ሌሎች ነቢያት የሚከተሉት ናቸው፡-[227]

- ጣልሀ ቢን ኹዋኢሊድ አል-አሰዲ
- ማሊክ ቢን ኑዋኢራህ
- አል-ሙንዚር ቢን አኒን-ኑማን
- አል-ያማመማህ ሙሰይለማህ
- ዙህ ኧት-ታጅ
- ሙሐመድ ቢን አብዱላህ
- ለቂት ቢን ማሊክ አል-አዝዲ
- ኢያስ ቢን አብዱላህ ቢን አብድ የሊል
- ኧል-አሻሥ ቢን ቃይስ አል-ኪንዲ
- ቀይስ ቢን መክሹህ
- ኧል-አስዋድ ኧል-አንሲ

ትኩረት የሚስበው ከየማማህ አካባቢ የነበረው ሙሰይለማህ ነበር። ሕዝቡ እንደ ነቢይ ተቀብለውት ነበር።[228] ስለ




[227] Dr. Shawqi Abu Khalil, *Atlas on the Prophet’s Biography*, Riyadh, KSA: Darussalem, 2003, p. 254.
[228] Ibn Ishaq, p. 134

ፈጣሪ ሲናገር አልረህማን እያለ ነበር። ኋላ ላይ ሙሐመድም እንደዚያ ማለት ጀምሯል።[229] የራሱ የሆነ የሃይማኖት መመርያ ነበረው፣ ብዙ ሠራዊትም ያዝዝ ነበር፣ መገለጡንም ቁርኣንን በሚመስል መንገድ ይናገር ነበር።[230] ከሙሐመድ ጋር ፉክክር ውስጥ የነበረ ትኩረት ሳቢ ሰው ነበር። እነዚህ ነቢያት ተብዬዎች አንዳቸው በሌላቸው ላይ የነበራቸውን ተፅዕኖ በበቂ ሁኔታ ማወቅ ቢያዳግትም ሙሐመድ ነቢይ መሆኑን የተናገረና ተቀባይነት ያገኘ ብቸኛ ሰው እንዳልነበረ መረዳት ይቻላል።

## ለሕዝቦች መልእክተኞች

ሙሐመድ አረብያን የበለጠ በተቆጣጠረ ቁጥር በዙርያው የነበሩትን ሕዝቦች የመቆጣጠር ፍላጎት አደረበት። ይህንንም መጀመርያ መልእክተኞችን በመላክ ለማስፈፀም ሞከረ። መልእክተኞች የሮም ንጉሥ ለነበረው ለሔራክሊዮስ፣ የኢራኑ ኪሥራ፣ ለአቢሲንያው ንጉሥ፣ ለገሰነዳውያን ነገሥታት እንደሁም ለየማማ አለቆች ተልከዋል።[231] የሙሐመድ መልእክት፤ “እኔ የአላህ መልእክተኛ ነኝ፣ ስለሙ፣ እስልምናን ተቀበሉ፣ ይህንን ካደረጋችሁ ከሙስሊም ሠራዊት ወረራ ነፃ ትሆናላችሁ” የሚል ነበር።

... ከሙሐመድ፣ የአላህ መልእክተኛ፣ ለሔራክሊዮስ፣ የሮማውያን ንጉሥ። መመርያውን በተከተለው ላይ ሰላም ይሁን። ከዚህ በኋላ እስልምናን እንድትቀበል ጥሪ አቀርብልሀለሁ። እስልምናን ተቀበል ደህንነትህ የተጠበቀ ይሆናል... (*Sahih Muslim*: bk. 19, no. 4380)

ከዚህ በኋላ ከመዲና ወደ ሰሜን መንቀሳቀስ ጀመረ። ትልቁን ድንገተኛ ጥቃት የፈፀመው በኸይባር በሚገኙት የአይሁድ ከተሞች ላይ ነበር። ጦርነት ማለት ሁለት ሠራዊቶች ሲዋጉ ሲሆን በዚህ ሁኔታ አንዱ ቦታ ሊለቅና ሌላው ሊይዝ ይችላል። ድንቀተኛ ጥቃት ማለት ግን ጥቂት የተዘጋጁ ወራሪዎች በሰላም በሚቀመጡ ሕዝቦች ላይ ድንገተኛ ጥቃት በማድረስ ሰዎችን መግደል፣ ባርያ ማድረግና መዝረፍ ማለት ነው። ሙሐመድ ኸይባርን ከወረረ በኋላ ግዛቱን በማስፋፋት በሰሜን በሚገኙት በገሳኒድ ጎሣ ኃላፊት ስር በሮማ ግዛት ውስጥ ይኖሩ በነበሩት አረቦች ላይ ጥቃቶችን መፈፀም ቻለ። በነዚህ ድንገተኛ ጥቃቶች ሳብያ የተወሰኑ የአረብ ጎሣዎች ከጥቃቶቹ ለማምለጥ ግብር መክፈል የጀመሩ ሲሆን ሌሎቹ ሰልመዋል። እነዚህ ጎሣዎች ጥበቃን ለማግኘት ወደ ሰሜን ወደ ሮማውያን ሳሆን ወደ ደቡብ መመልከት ጀመሩ። ይህንን የወዳጅነት አቅጣጫ የለወጠውን ሙሐመድን ለማስቆምና የግብር ፍሰት አቅጣጫን ለመቀልበስ የአረብ ገሳኒድ ጎሣ ቢዘምቱም በሙስሊም ተዋጊዎች ተግዳሮት ገጠማቸው። ሙስሊሞች የሮምን ግዛት መውረር ባይችሉም የጦርነት እሳት ተለኩሷል።

---

229 F.E. Peters, *Muhammad and the Origins of Islam*, New York, U.S.A: SUNY Press, 1994, pp. 156-159.

230 Ibn Ishaq, p. 637

231 Prof. Masud ul-Hasan, vol. 1, p. 69

## የመካ ድል መደረግ

ከመካውያን ጋር የነበረው የሰላም ስምምነት እየተናደ ቢሆንም ለሙሐመድ ግን አረብያን ለማስገበር ሠራዊቱን ለማደራጀት ጊዜ መግዣ ሆኖታል። በ630 ዓ.ም. ሙሐመድ 10,000 ወታደሮችን ይዞ በመካ ላ ዘመተ። መካውያን ሁኔታው ተስፋ አስቆራጭ መሆኑን ስለተመለከቱ እጅ በመስጠት ሰለሙ። ሙሐመድ እስልምናን ስለተቀበሉ ይቅር ብሏቸው ከሠራዊቱ ጋር ቀላቀላቸው።

ሙሐመድ በመካ ካደረጋቸው የመጀመርያ ነገሮች መካከል አንዱ ወደ ካዕባ በመሄድ በውስጡ የነበሩትን ጣዖታት መሰባበር ነበር። መካ ለእስላዊ አምልኮ ብቻ የተለየች ቢሆንም ትቁሩ ድንጋይ ግን በቦታው አለ። አረቦች ድንጋዮችን ለአምልኮ ይጠቀሙ ነበር።[232] ጥቁሩ ድንጋይ ደግሞ ዋና ድንጋይ ነበር።[233] ሙሐመድ ይህንን ድንጋይ በቦታው ስለተወ ሙስሊሞች ዛሬም ድረስ ይስሙታል፣ ይተሻሹታል። እስልምና ዛሬም ድረስ በውስጡ ጣዖታዊነት አለ። ሙሐመድ አብዛኞቹን የአረብ ጣዖታውያን ልማድ ሳያጠፋ እስላማዊ ትርጉም አግኝተው እንዲቀጥሉ አድርጓል። ነገር ግን ጥቁሩን ድንጋይ በቦታው መተውና ሌሎች የቅድመ እድልምና ልማዶች የእስልምና አምልኮ አካል መሆናቸው አንዳንድ የሙሐመድን ወዳጆች ግራ ማጋባቱ አልቀረም። ሆኖም የሙሐመድ ምሳሌነት አሸናፊ ሆኖ በመውጣቱ ሳብያ እነዚህ ነገሮች ዛሬም ቀጥለዋል።[234]

መካ አንዴ ድል ተነስታ ነዋሪዎቿ ከሰለሙ በኋላ ሙሐመድን መቋቋም ፋይዳ እንደሌለው ሌሎች የአረብ ጎሣዎች ተገነዘቡ።

> የአረብ ጎሣዎች መካ መሸነፏንና የመካ ቁረይሾች እስልምናን መቀበላቸውን ሲሰሙ እጣቸውን ከአዲሱ ኃይል ጋር መጣል እንደሚገባቸው ተገነዘቡ። 631 ዓ.ም. የመቀላቀል ዓመት ተብሎ የሚታወቅ ሲሆን የተለያዩ የአረብ ጎሣዎች ለነቢዩ ታማኝነታቸውን ለመግለፅና እስልምናን ለመቀበል ወደ መዲና ይጎርፉ ነበር። ሁሉም የአረብያ ፓጋን ጎሣዎች እስልምናን ተቀበሉ።[235]

እጅ ያልሰጡት ጎሣዎች ተደጋጋሚ ጥቃት ይደርስባቸው ነበር። መላዋ አረብያ እጅ ከሰጠች በኋላ ሙሐመድ በዙርያው ወደ ነበሩት ሕዝቦች ፊቱን አዞረ። የመጀመርያዎቹ ደግሞ ክርስቲያን ሮማውያን ነበሩ።

---

232 Clement of Alexandria, "Exhortation to the Heathen", *Ante-Nicene Fathers*, ed. Alexander Roberts & James Donaldson; Massachusetts: Hendrickson, 1995, vol. 2, p. 184; Arnobius, "The Seven Books of Arnobius Against the Heathen," *Ante-Nicene Fathers*, vol. 6, p. 510; *Sahih al-Bukhari*: vol. 5, bk. 59, no. 661.
233 Ibn Ishaq, p. 99
234 *Sahih al-Bukhari*: 1605 or vol. 2, bk. 26, no. 675
235 Prof. Masud ul-Hasan, vol. 1, p. 74

## ታላቁ ተልዕኮ

ሙሐመድ እንደገና 30,000 ወታደሮችን አስከትሎ ወደ ሰሜን አቅጣጫ ወደ ተቡክ ከተማ ሄደ።[236] ከተቡክ በዙርያው ላሉት የአረብ ጎሣዎች በሮማውያን ላይ ለመዝመት እንዲረዱት መልእክተኞችን ላከ። አንዳንዶች ከእርሱ ጋር ለመዋጋት ተቀላቀሉት ሌሎች ደግሞ ገበሩለት። ሮማውያን ከሦርያ ሠራዊት ማደራጀት እንደጀመሩ ተነግሮናል። ሙሐመድ የውጊያ ጊዜ እንዳልሆነ በማስተዋል የውጊያ መስመሩን ለወደፊት ውጊያ ዝግጁ ካደረገ በኋላ ወደ መዲና ተመልሷል። በዚህ ጊዜ አካባቢ ነበር ሙሐመድ ሱራ 9ን የተናገረው። የመጨረሻው ዋና ሱራ ሲሆን ሙሐመድ ለተከታዮቹ ታላቁን ተልዕኮ ሰጥቷል፡-

> "ከነዚያ መጽሐፍን ከተሰጡት ሰዎች፣ እነዚያን በአላህ በመጨረሻዉ ቀን የማያምኑትን፣ አላህና መልክተኛዉ እርም ያደረጉትንም እርም የማያደርጉትንና እዉነተኛዉንም ሃይማኖት የማይቀበሉትን እነርሱ የተዋረዱ ሆነዉ ግብርን በእጆቻቸው እስከሚሰጡ ድረስ ተዋጉዋቸው። አይሁድ ዑዘይር የአላህ ልጅ ነዉ፣ አላችሁ፤ ክርስቲያኖችም አልመሲሕ የአላህ ልጅ ነዉ አሉ፤ ይህ በአፎቻቸዉ (የሚናገሩት) ቃላቸው ነው፤ የነዚያን ከነሱ በፊት የካዱትን ሰዎች ቃል ያመሳስላሉ፤ አላህ ያጥፋቸዉ (ከእዉነት) እንዴት ይመለሳሉ! ከርሱ በቀር ሌላ አምላክ የሌለዉን አንድን አምላክ ሊገዙ እንጂ ያልታዘዙ ሲሆኑ ሊቃውንቶቻቸውንና መነኮሳታቸዉን የመርየምን ልጅ አልመሲሕንም ከአላህ ሌላ አማልክት አድርገው ያዙ፤ ከሚያጋሩት ሁሉ የጠራ ነው።" (ቁርኣን 9፡29-31)

ሙሐመድ ለተከታዮቹ ያስተላለፈው ታላቁ ተልዕኮ አምላኩን፣ ትምሕርቱንና ነቢይነቱን ያልተቀበሉ ሰዎችን በመዋጋት እንዲያስገዙ ነው። በተለይም ክርስቲያኖችና አይሁድ በእግዚአብሔር ልጅ ስለሚያምኑ በልዩ ሁኔታ የጥቃት ዒላማ ሆነዋል። ለሙስሊም ማሕበረሰብ የሰጠው ራዕይ በእስልምና ቁጥጥር ስር የወደቀች ዓለምን ነው። ዓለምን መግዛት የእስልምና ግብ ነው፡-

> እርሱ ያ አጋሪዎቹ ቢጠሉም መልክተኛዉን (ሙሐመድን) በቅን መንገድና በእውነተኛ ሃይማኖት ላይ ከሃይማኖት ሁሉ በላይ ይፋ ያደርገው ዘንድ የላከው ነዉ።" (ቁርኣን 9፡33፣ 48፡28-29፣ 61፡9)

ሙስሊም ጂሃዳውያን ሙስሊም ያልሆኑትን ሲያገኙ ሦስት ምርጫዎችን ይሰጧቸዋል፤ መስለም፣ ግብር መክፈል ወይንም መገደል።[237] እንደምንመለከተው የሙሐመድ ተከታዮች

---

[236] Prof. Masud ul-Hasan, vol. 1, p. 74
[237] *Sahih Muslim*: bk. 19, no. 4294

በቀጣይ 1000 ዓመታት ይህንን ተልዕኮ የተገበሩ ሲሆን የሁሉም እስላማዊ መደቦች አስተምሕሮ ነው።[238]

ሙሐመድ ለማድረግ ሲሞክር የነበረው ምን ነበር? ሌላ መንግሥት፣ ሌላ ኢምፓየር እየገነባ ነበርን? አይደለም፣ ይልቁኑ የአላህ መንግሥት፣ አምላክ በነቢዩ በኩል የሚያስተዳድርበት መለኮታዊ አገዛዝ፣ ተምሳሌታዊ ማሕበረሰብ ነው። አዲስ ዘመን መጥቷል፣ እናም ሙስሊሞች እስላማዊውን መንግሥት በዓለም ላይ ለመጫን መዋጋት ይኖርባቸዋል። ሙሐመድ ለዓለም ታሪክ ያበረከተው ሌጋሲ ይህ ነው።

የነገሩን አስኳል ለማግኘት የሙሐመድን ታላቁን ተልዕኮ ከጌታችን ከኢየሱስ ታላቁ ተልዕኮ ጋር ማነፃፀር ያስፈልገናል። ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ የሰጠው ተልዕኮ ንስሐ፣ እንምነትና የመዳን መልዕክት ነው።[239] የሙሐመድ ታላቁ ተልዕኮ ሠራዊት በማሰማራት የእስልምናን አገዛዝ ማንሰራፋት ነው። ኢየሱስና ሙሐመድ ለምን በጣም የተለያዩ ሆኑ? ጉዳዩ ከነቢያት ጋር የተያያዘ ነው።

ከኢየሱስ በፊት የነበሩት ነቢያት የሰው ልጆች በኃጢአት ስለተበከሉ የእግዚአብሔርን መንግሥት ማምጣት እንደማይችሉ ግልፅ አድርገዋል። እግዚአብሔር መንግሥቱን ሲመሠርት የሰው ልጆች በኃጢአትና በሞት ይበልክሉታል። ይህንን በብሉይ ኪዳን ውስጥ በእሥራኤል ታሪክ የምንመለት ሲሆን ለእሥራኤል እውነት የሆነው ሁሉ ለኛም እውነት ነው፤ ይወክለናል። ስለዚህ ተስፋ የተገባው የእግዚአብሔር መንግሥት በትሣኤ ወቅት የሚመጣ፤[240] ኃጢአትና ሞት ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ የሚወገዱበት ሲሆን እርሱን የሚያመጣው ደግሞ መሲሁ ነው።[241] እኛ ማድረግ ያልቻልነውን ለማድረግ እግዚአብሔር ቃል ገብቷል። ብሉይ ኪዳን የተጠናቀቀው እግዚአብሔር የትንሣኤውን መንግሥት በመሲሁ አማካይነት እንደሚያመጣ ተስፋን በመስጠት ነው። ይህ መንግሥት ኢየሱስ በትንሣኤው አማካይነት ያመጣው መንግሥት ሲሆን እርሱ በሠራልን ሥራ በማመንና በንስሐ ወደ መንግሥቱ እንገባለን። ለዚህ ነው ኢየሱስ ወንጌልን ይሰብኩ ዘንድ ሐዋርያቱን የላከው።

ሙሐመድ ይህንን የነቢያትን መልእክት ተቃውሟል። በእርሱ እምነት መሠረት የሰው ልጆች በኃጢአት አልተበከሉም፤ የሚያስፈልገን መመርያ ብቻ ሲሆን የእግዚአብሔርን አገዛዝ በራሳችን በምድር ላይ መመሥረት እንችላለን። ለዚህ ነው ሙሐመድ የአላህን አገዛዝ ያሰፍኑ ዘንድ ጂሃዳውያንን ሰይፍ አስታጥቆ የላከው። የሙሐመድ ዕቅድ በጎ ቢመስልም ከእግዚአብሔር ዕቅድ ጋር የሚጋጭና የማይሠራ ነው።

---

238 Ahmad ibn Naqib al-Misri, *Reliance of the Traveller - A Classic Manual of Islamic Sacred Law*, (translated: Nuh Ha Mim Keller), Maryland, U.S.A.: Amana Publication, 1994, o9.8-o9.9, pp. 602-603.

239 ማቴ. 28:16-20, ሉቃ. 24:45-49, ዮሐ. 15:27

240 ኢሳ. 65:17-18, ዳን. 12:13

241 ኢሳ. 11

## ኑዛዜና ህልፈት

ሙሐመድ ወደ ተቡክ ከዘመተ ከጥቂት ጊዜ በኋላ ሞተ። ወደ መዲና ተመልሶ ሙስሊሞች ሁሉ ለሐጅ ወደ መካ ጠራ። ይህ የመጨረሻው የሐጅ ጉዞ ነበር። በዚያም ሳለ የመጨረሻ ንግግሩን አድርጎ ወደ መዲና ከተመለሰ በኋላ ሞተ። የሞቱ ትክክለኛው ምክንያት አይተወቅም። ብዙዎች የሚስማሙበት በኸይበር ወረራ ወቅት አንዲት አይሁዳዊት ሴት መርዝ አብልታው ነበር የሚል ነው።

> እውነተኛ ሙስሊሞች የሙሐመድን ሕይወት የመኖርን ትርጉም የሚያሳይ ተምሳሌታዊ የሃይማኖት ሕይወት አድርገው ይቆጥሩታል ነገር ግን ሃይማኖቱ ከነቢዩ ጋር አልሞተም። ረሺዱም ወይም "በትክክል የተመሩት" ተብለው በሚታወቁት በአራቱ ተተኪዎቹ ዘመን፣ በአቡበክር፣ ዑመር፣ ኡሥማንና አሊይ ዘመናት ቀጥሏል። ከዋሻው መገለጥ ጀምሮ እስከ ነቢዩ አራተኛው ተተኪ ድረስ የነበረው የአርባ ዓመታት ድራማ የእስልምናን ማዕከላዊ ሃይማኖታዊ አስተምሕሮ ፈጥሯል። ይህም በክርስትና ውስጥ ከሚገኘው የክርስቶስ የመጨረሻው እራት፣ ስቅለትና ትንሣኤ ጋር በተነፃፃሪነት ሊታይ ይችላል።[242]

በተቀረው የዚህ ምዕራፍ ክፍል ከዚያ ቀጥሎ በነበረው የእስልምና ታሪክ ላይ አጭር ሐተታ አቀርባለሁ።

## በትክክል የተመሩት ኸሊፎች

ሙሐመድ እንደሞተ ወዲያው የተነሳው ጥያቄ ሕዝበ ሙስሊሙን ማን ይምራ የሚል ነበር። የሙሐመድ ቅርብ ወዳጆች መመረጥ እንዳለባቸው ግልፅ ነው ነገር ግን ማን? ኮሚቴ ተቋቁሞ አቡበክር ተመረጠ። የሙሐመድ ወዳጅና የአጎቱ ልጅ የነበረውና ለሥልጣኑ ቀዳሚ ዕጩ የነበረው አሊይ በኮሚቴው ውስጥ አልተካተተም።

ሽማግሌዎቹ ሲሰበሰቡ አሊይ የነቢዩን አስከሬን እያጠበ ነበር። ስለ ውይይቱ ምንም ነገር ከመስማቱ በፊት ውሳኔ ተወሰነ።[243]

ይህ በሙሐመድ ቤተሰብና በሌሎች የእስልምና መሪዎች መካከል የአለመግባባት ጅማሮ ነበር። አሊይ የአቡበክርን ሹመት ተቀብሎ እስልምናን በታማኝነት አገልግሏል።

አቡበክር መሪ ሲሆን እንደ ሙሐመድ የነበረ ነቢይ ሳይሆን ኸሊፍ የተሰኘ ሌላ ዓይነት መሪ ነበር። በርሱ ዙርያ የመዲና ሙስሊሞችና ሌሎች ጎሣዎች የተሰባሰቡ ቢሆንም ብዙ ጎሣዎች እምቢተኞች ሆነው ነበር። ሙሐመድ ከሞተ በኋላ፡-

---

242 Tamim Ansary, *Destiny Disrupted - A History of the World Through Islamic Eyes*, New York, U.S.A.: Public Affairs, 2009, p. 33.
243 Tamim Ansary, p. 36.

> ብዙ ጎሣዎች እስልምናን በመከዳት *ዘካት* አንከፍልም አሉ። ብዙ ሐሰተኛ ነቢያት በመላው አረብያ ስለተነሱ ብዙ ሕዝቦች እነርሱን መከተል ጀምረው ነበር። የቀረበው ሙግትን ከሞተ ነቢይ ይልቅ በሕይወት ያለ ይሻላል የሚል ነበር።[244]

እነዚህ ሕዝቦች በሙሐመድ ዘመን እስልምናን የተቀበሉት ለይስሙላ ይመስላል። ሌሎች ጎሣዎች ደግሞ ጭራሹኑም እስልምናን አልተቀበሉም ነበር። የአቡበክር የመጀመርያው ተግባር አረብያን እንደገና ማስገበር ነበር። እነዚያ ጎሣዎች አንድ በአንድ ጥቃት ተፈፀባቸው፣ ነቢያቶቻቸው ተገድለው ወደ እስልምና እንዲመለሱ ተደርጓል። አረብያን ካረጋጋ በኋላ አቡበክር ሌሎች ሕዝቦችን ወደ ማጥቃት ፊቱን አዞረ። ጂሃዳውያን ስኬታማ ጥቃት እየፈፀሙ ወደ ኢራቅና ሦርያ ገሠገሡ። ለሚገጥሟቸው ሕዝቦች ደግሞ ሦስት ምርጫዎችን ይሰጡ ነበር።

ቀጣዩ ኸሊፍ ዑመር ነበር። ለሙስሊሞች ሕግን እያሰፈነ ሌሎች ሕዝቦችን መውጋት ቀጠለ። በእርሱ አገዛዝ ዘመን ኢራቅ፣ ሦርያና ግብፅ ድል ተነስተው በሙስሊሞች ቅኝ ተያዙ። ሮማውያንና ፋርሳውያን በእስላም ሠራዊት ፊት መቆም አልቻሉም፤ በመቶ ሺህዎች የሚቆጠሩ ተዋጊዎችም ተገደሉባቸው። ለሮማውያንና ፋርሳውያን ነገሩን ያከበደው በመካከላቸው እንደ ድንበር ያገለግሉ የነበሩ የአረብ ጎሣዎችና አንዳንድ አርመናውያን እንዲሁም ሌሎች ሕዝቦች አሰላለፋቸውን ከሙስሊሞች ጋር አድርገው እነርሱን መዋጋታቸው ነው።[245] እነዚህ ሕዝቦች ከአረቦችና ፋርሳውያን ጋር የራሳቸው ቅሬታ ስላላቸው ምቹ አጋጣሚ ይጠብቁ ነበር። ሌሎች ቅብጦችን የመሳሰሉት የግብፅ ክርስቲያኖች ጭራሹኑም እርምጃ አልወሰዱም። ሙስሊሞች ወደ ግብፅ ሲነጡ ቅብጦች ገለልተኛ በመሆን ሮማውያንና ሙስሊሞች እንዲዋጣላቸው በዝምታ ይመለከቱ ነበር። የግብፅ ቅብጦች በሮማውያን ከፍተኛ ስደት ደርሱባቸው ስለነበር ለእነርሱ ታማኞች የመሆን ፍላጎት አልነበራቸውም።

> ዑመር (ረዐ) ሙስሊሞች ጣዖት አምላኪያንን እንዲወጓቸው ወደ ታላላቅ አገሮች ላካቸው። አል-ሁርሙዛን እስልምናን በተቀበለ ጊዜ ዑመር (ረዐ) እንዲህ አላቸው። "እነዚህን ለመውረር ስላሰብኳቸው አገሮች ላማክርህ እፈልጋለሁ።" ለአሕዛብም "ነብያችን የጌታችን መልእክተኛ አላህን በብቸኝነት እስክትገዙ ወይም ጂዝያን (ግብርን) እስክትሰጡ ድረስ እንድንዋጋችሁ አዘዙን" እንላለን። (ሳሂህ አል-ቡኻሪ 3159፣ 3160፣ ቅጽ 4፣ መጽሐፍ 53፣ ቁጥር 386)

ሌላው ለሙስሊሞች ስኬት እንደ ምክንያት የሚቆጠረው ሙሐመድ እነርሱን በጥሩ ሁኔታ ማሰልጠኑ ነው። ልምድ ያላቸው ጦርነት ያደነደናቸው ወታደሮች ነበሩ። የድል ወይንም

---

[244] Prof. Masud al-Hasan, vol. 1, p. 97.

[245] Bat Ye'or, *The Decline of Eastern Christianity Under Islam - From Jihad to Dhimmitude*, London, England: Associated University Presses, 1996, p. 144

የገነት ተስፋን ይዘው ነበር የሚዋጉት። “የአላህ ሰይፍ” ተብሎ የሚታወቀው ኻሊድ ቢን ዋሊድን የመሳሰሉ የጦር መሪዎች ነበሯቸው። በተጨማሪም ዑመር ክርስቲያኖችንና አይሁድን ከአረብያ አባሯል።[246]




ቀጣዩ ኸሊፍ ኡሥማን ሲሆን በእርሱ ዘመን እስልምና መንገራገጭ ጀመረ። ወረራው ቀጥሎ ሰሜን አፍሪካ የተወሰደ ሲሆን ነገር ግን ሙስሊሞች ከሮማውያንና ፋርሳውያን የዘረፉት የማይነገር ኃብት የቅንጦት ኑሮ እንዲኖሩ ስላደረጋቸው ማጉረምረም ጀመሩ፤ ኡሥማንም ሁኔታውን መቆጣጠር አልቻለም። ቁርኣን የተስተካከለውና መደበኛ ንባብ እንዲኖረው የተደረገው በእርሱ ዘመን ሲሆን ይህም ሌላው ያለመግባባት ምክንያት ነበር። በመጨረሻም ኸሊፍ ኡሥማን በ656 ዓ.ም. በአንድ ሙስሊም ተገደለ፤ የአንድነት ዘመንም አከተመለት።

ቀጣዩ ኸሊፋ አሊ ነው። የሙሐመድ ቤተሰብ አባል ሲሆን ለብዙ ዓመታት ችላ ተብሏል። በኡሥማን ዘመን የነበረውን መጥፎ ሁኔታ ለማፅዳት ቢሞክርም ተባብሶ ወደ አመፅ አደገ። አንዳንዶች ከአሊና የሙሐመድ ቤተሰብ ጋር የወገኑ ሲሆን የሺአ እስልምና ጅማሬ ነው። ሌሎች ደግሞ ከሙሐመድ ሚስት ከአይሻ ጋር የወገኑ ሲሆን ይህ የሱኒ እስልምና ጅማሬ ሆነ። *የግመል ጦርነት* የተሰኘ ውጊያ በሙስሊሞች መካከል ከተደረገ በኋላ እስልምና ሺአና ሱኒ ተብሎ እስከ ወዲያኛው ተከፈለ። አሊ ዋና ከተማውን ከመዲና ወደ ኢራቅ ኩፋ ካዛወረ በኋላ በሙስሊም ወገኑ ተገደለ።

ሙሐመድ የፈጣሪን መልካም ዘመን እንደሚያመጣ ቢናገርም እስልምና እንደ ማንኛውም የሰው ግዛተ መንግሥት ተበክሎ ራሱን በራሱ ከፋፈለ። ይህ የእስልምና ታሪክ *አል-ጠበሪን* ጨምሮ በብዙ ሙስሊም ታሪክ ጸሐፍት ተዘግቧል። አል-ጠበሪ አርባ ቅፅ የዓለምና የእስልምና የታሪክ መጽሐፍትን ጽፏል።[247] ይህ ታሪክ በሙስሊሞች ብቻ ሳይሆን በእስልምና ተፅዕኖ በደረሰባቸው ሌሎች ጸሐፍትም ተጽፏል። በቅብጥኛ፣ በግሪክ፣ በአርመንኛ፣ በላቲን፣ በሦርያኛ፣ በቻይንኛ፣ በእብራይስጥና በአረብኛ የተጻፉ የክርስቲያን፣

---

246 *Sahih Muslim*: bk. 19, no. 4366

247 Al-Tabari, *The History of al-Tabari*, U.S.A., New York: SUNY, volumes 1-40, 1989.

የአይሁድና የዞራስትሪያን (ዛቱስትራ) ምንጮች ይገኛሉ።[248] እነዚህ በቀደሙት የእስልምና ዘመናት የነበሩ ሲሆን እስከ ዘመናችን ቀጥለዋል።

## *ሥረወ መንግሥታት*

በኡመያድ *ሥረወ መንግሥት* ዘመን የእስልምናው ዓለም ዋና ከተማ ደማስቆ ሆናለች። ካሊፌት የነበረ ሲሆን ኡመያድ ግን በአመዛኙ ዓለማዊ ነበር። በመካ ሙሐመድን ሲቃወም ከነበረው ጎሣ የተገኙ ነበሩ። በነርሱ ዘመን የጂሃድ ወረራ የቀጠለ ሲሆን በምዕራብ በኩል እስከ ፈረንሳይ በምሥራቅ በኩል ደግሞ እስከ ምዕራብ ቻይና ድረስ ዘልቋል። አረብኛ ዋነኛ መግባቢያ እንዲሆን የተደረገ ሲሆን ለእስልምና ጠቃሚ የሆኑት የቀደሙት ጽሑፎች ወደ አረብኛ እንዲተረጎሙ ተደርገዋል። ሙስሊሞች ከግሪክና ከፋርስ ፍልስፍናዎች ጋር የተጋፈጡት በዚያን ዘመን ሲሆን የሙስሊሙ ዓለምም በአመክንዮአዊ አስተሳሰብና በእስላማዊ ሃይማኖተኝነት መካከል ግራ ተጋብቶ ነበር። ይህንን ሁኔታ ክርስቲያኖችም ተጋፍጠውት ነበር። በሱኒና በሺአ መካከል የነበረው ጦርነት እጅግ ተካርሮ የሙሐመድ ልጅ ልጆች በሱኒ ሙስሊሞች ተገድለዋል።

ኡመያዶች በምሥራቅ በአባሲዶች በግብፅ ደግሞ በፋጥሚዶች ተተኩ። አባሲዶች ባልተወረሩት አገራት ላይ የሚፈፅሙትን ጂሃድ ቀጠሉ። ከአውሮፓ እስከ ቻይና የተዘረጋ የተረጋጋ ግዛተ መንግሥት ከመሠረቱ በኋላ በዓለም ላይ የሚገኙትን ጥበቦች ወደ ዋና ከተማቸው ወደ ባግዳድ መሰብሰብ ጀመሩ። ብዙ የፍልስፍናና የቴክኒክ ዕድገቶች የታዩት በዚያን ዘመን ነበር። የቱርክ ሱልጁኮች እስልምናን ከተቀበሉ በኋላ ዋነኛ ወታደሮች ሆኑ። ከጊዜ በኋላ ገዢ መሆን ስለፈለጉ ሦስት እስላማዊ *መንግሥታት* ተመሠረቱ፤ እነርሱም አባሲድ፣ ፋጥሚድና ሱልጁክ ሲሆኑ ሁላቸውም እርስ በርሳቸው ይዋጉ ነበር። እንዲሁም ያ ዘመን የነፍሰ ገዳዮች ዘመን ስለነበር እስላማዊው ዓለም በሽብር ይታመስ ነበር።

የመጀመርያውን ክሩሴድ የቀሰቀሰው የሱልጁኮች ተግባር ነበር። ምዕራባውያን ክርስቲያን ተጓዦች ወደ ኢየሩሳሌም ሲሄዱ ጥቃት ይደርስባቸውና ባርያዎች ይደረጉ ነበር። በቁስጥንጢንያ ላይ ይደረግ የነበረው እስላማዊ ጂሃድም እየበረታ መጣ። ከዚህ የተነሳ የመስቀል ጦረኞች ወደ ተከፋፈለው የእስልምናው ዓለም በመምጣት የራሳቸውን ግዛት መሠረቱ። ይህ በሙስሊሞች መካከል የነበረው ክፍፍል የበረታ ስለነበረ አንዳንድ ሙስሊሞች ከመስቀል ጦረኞች ጋር በማበር ሙስሊም ወገናቸውን ይዋጉ ነበር።[249] በእስልምና ታሪክ የመስቀል ጦርነት ለአጭር ጊዜ የቆየ፣ በትንሽ ቦታ የተገደበና ያልተሳካ

---

248 Robert G. Hoyland, *Seeing Islam as Others Saw It,* Princeton, New Jersey: The Darwin Press, 1997.

249 Tamim Ansary, p. 139. Prof. Masud al-Hasan, vol. 1, p. 456

ተደርጎ ቀርቧል። ለእስልምና ትልቅ ችግር የፈጠረው በሙስሊሞች ዘንድ የጭፍጨፋ ዘመን ተብሎ የሚታወቀው የሞንጎሎች ወረራ ነው።[250]

## የጭፍጨፋ ዘመን

አላኡዲን ሙሐመድ የተሰኘ አንድ ትዕቢተኛና ሞኝ የአባሲድ ንጉሥ የሞንጎል ሲራራ ነጋዴዎችን ሸምቆ በመጠበቅ 450 ነጋዴዎችን ገደለ። የሞንጎል ንጉሥ ጄንግስ ኻን ካሳ ጥየቃ ሦስት ልዑካንን ላከ። አላኡዲን አንዱን በመግደል ሌሎቹን ጢማቸውን ቆርጦ መለሳቸው። ከዚያም በ1219 ጄንግስ ኻን ሠራዊቱን አስከትሎ በመምጣት ታይቶ በማይታወቅ ሁኔታ ሙስሊሞችን በመጨፍጨፍ በሙስሊሙ ዓለም ላይ መአት አወረደ። ይህ ለእስልምና ታላቅ ኪሣራ ነበር። ብዙ ከተሞች ፈራረሱ፣ ሚሊዮኖች ተገደሉ፣ የሙስሊሙ ዓለም ሊጠፉ ምንም አልቀረው ነበር። ከዘመናት በኋላ ሞንጎሎች እስልምናን ቢቀበሉም የእስልምና የመማርያ ማዕከላት መውደማቸው፣ ንግድ መረበሹ፣ መሠረተ ልማቶች መውደማቸውና ሕዝቦች ማለቃቸው የእስልምናው ዓለም መፈራረሱን ያሳያል። ቀስ በቀስ አረብ ሙስሊሞች፣ ፋርሳውያን፣ ቱርኮችና አይሁድ እንዲሁም ክርስቲያን ገባሮቻቸው የገዛ ዓለማቸውን መጠገን ጀመሩ።

በእስልምናው ዓለም ውስጥ የተነሳው ጥያቄ ይህ ሊሆን እንዴት ቻለ? የሚል ነበር። እስልምና ትክክል መሆኑ የታመነው ስኬታማ ስለሆነ ነው፤ እስከዚህ ነጥብ ደግሞ በስኬት ነበር የመጣው። አብዛኛውን የዓለም ክፍል በመውረር፣ ቅኝ ገዝቷል፣ ሰዎችን ባርያ አድርጓል፣ የዓለም መልከ መልካም ሴቶች በሙስሊም ወንዶች ጉያ ወድቀዋል፣ ያለፈውን ሥልጣኔ በማስወገድ የራሱን አቁሟል። የዓለም ዋና ሃይማኖት ለመሆን በቅቷል፤ ቁርአንም ቃል የገባው ይህንኑ ነው፤ ስለዚህ ይህ ሁሉ ውድመት እንዴት ሊሆን ቻለ? አንዳንዶች ችግሩ ከሃይማኖቱ እንደሆነና ሙስሊሞች እስላማዊ ላልሆኑ ሐሳቦች ክፍት ባለመሆናቸው ምክንያት ይህ እንደተፈጠረ ደመደሙ። የበለጠ በራቸውን ክፍት ቢያደርጉ ኖሮ የበለጠ ስኬታሞች ይሆኑ ነበር። ነገር ግን ኢብን ተይሚያን ለመሳሰሉት ሊቃውንት ጉዳዩ የተገላቢጦሽ ነበር። ሙስሊሞች ቁርአንን በትክክል አልታዘዙትም፤ እውነተኛ ሙስሊሞች ሆነው አልተገኙም። ሙስሊሞች ስኬታማ ለመሆን ልባቸውን ሙሉ በሙሉ ወደ ቁርአን መመለስ ያስፈልጋቸዋል።

## የአውሮፓ ግርዶሽ

የእስልምናው ዓለም እንደገና ማገገም ሲጀምር አዳዲስ ግዛተ መንግሥታት ተፈጠሩ፤ አረብ፣ ቱርክ፣ ፋርስና ሞግሃል። እነዚህም ጂሃድን እንደገና በማፋፋም ወደ አፍሪካ፣ ኢስያና አውሮፓ መግፋት ተያያዙ። በተለይም ኦቶማን ቱርኮች የጂሃድን ሰንደቅ በማንሳት የክርስቲያኑን ዓለም የወረሩ ሲሆን የኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ማዕከል የነበረችው

[250] Tamin Ansary, p. 149

ቁስጥንጢንያ በ1453 ዓ.ም. በቱርክ ጂሃዳውያን እጅ ወድቃለች። ነጋዴዎችም እስልምናን ወደ አፍሪካና ኢስያ አዳዲስ አካባቢዎች አስፋፍተዋል።

ይሁን እንጂ አውሮፓም እያደገች ነበር። የመስቀል ጦርነትና የሞንጎሎች ወረራ ሙስሊም ላልሆነው ዓለም ትንፋሽ የመሰብሰብያ ጊዜን ሰጥቷል። መጀመርያ ላይ አውሮፓውያን የምሥራቅ ሸቀጦችን ወደ ምዕራብ ለመውሰድ መጥቷል። ሙስሊም መሪዎች በንግድ መስመሮች ላይ የአውሮፓ ነጋዴያን ቢሮዎችን እንዲከፍቱ የፈቀዱ ሲሆን ከጊዜ በኋላ ሸቀጥ ከምሥራቅ ወደ ምዕራብ ማመላለስ ብቻ ሳይሆን የአውሮፓንም ቴክኖሎጂ ለሙስሊሞች መሸጥ ጀምረዋል። ቱርኮች በምሥራቅ አውሮፓ አገራት ላይ ጂሃድ ለማድረግ ከምዕራብ አውሮፓ አገራት ጠብመንጃዎችን ይገዙ እንደነበር ከታሪክ እናነባለን።

ሙስሊሞች የምሥራቁን የንግድ መስመር ተቆጣጥረውት ስለነበር ወደ ሕንድ የሚወስድ አማራጭ መንገድ ፍለጋ ሲያደርግ ክርስቶፈር ኮሎምበስ በ1492 ዓ.ም. አሜሪካን አገኘ። ከአሜሪካዎች ያገኙትን እጅግ ብዙ ወርቅ በመጠቀም አውሮፓውያን የራሳቸውን ግዛተ መንግሥት በመገንባት ከሙስሊሙ ዓለም እየላቁ ሄዱ። ሳይንስሳዊው አብዮት የጤክኖሎጂ ዕድገትን ስላመጣ ሙስሊሞች የአውሮፓን መሣሪያዎች ከመግዛት አልፈው ወታደሮቻቸውን እንዲያሰለጥኑላቸውና እንዲያስታጥቁላቸው መጠየቅ ጀመሩ። ሙስሊም ወታደሮች ከሌሎች ሙስሊሞች ጋር ሲዋጉ የአውሮፓውያንን ዩኒፎርም በመልበስና በአውሮፓውያን አማካሪዎች ሐሳብ መሠረት ነበር። የአውሮፓውያን ካማፓኒዎች ከገዢ መደብ የነበሩ ሙስሊሞችን ይቀጥሩ ነበር። ሙስሊሞች ለሐጅ ወደ መካ ሲሄዱ በአውሮፓውያን መጓጓዣዎች ነበር። የገዛ ማዕድኖቻቸውን ማውጣት ሲፈልጉ አውሮፓውያን መሐንዲሶችን ይጠሩ ነበር። የሙስሊሙ ዓለም በአውሮፓ ላይ ጥገኛ ሆነ። የአውሮፓ ወረራ አልነበረም[251] ነገር ግን በንግድ፣ በሳይንሳዊና ወታደራዊ የበላይነት፣ እንዲሁም በግብዣ አውሮፓውያን በመካከለኛው ምሥራቅ ትልቅ ፖለቲካዊና ወታደራዊ ኃይል ሆነው ነበር። እስላማዊው ኢምፔርያሊዝም በአውሮፓውያን ኢምፔርያሊዝም እየተተካ ነበር።

በርግጥ አውሮፓ አንድነት አልነበራትም። ብሪትሽ፣ ፈረንሳይ፣ ጀርመንና እስፔን በተደጋጋሚ እርስ በርሳቸው ይዋጉ ነበር፤ ሁላቸውም ደግሞ የሩሲያና የምሥራቅ አውሮፓ ባላንጣዎች ነበሩ። እነዚህ ልዩነቶች በሙስሊሙ ዓለም ውስጥም የፖለቲካዊ ክፍፍል ሰበብ ሆኗል። ስለዚህ ግሪክና ሩሲያ በትብብር እስልምና የወሰዳቸውን ምድሮች የማስመለስ ዘመቻ ሲጀምሩ እስፔን፣ ፈረንሳይና ብሪቴን ከቱርክ ጋር በመተባበር ተዋግተዋቸዋል።[252] የመካከለኛው ምሥራቅ ዓለም በአውሮፓውያን ጥቅም መሠረት ይደገፋ ወይንም ደግሞ ይጠመዘዛል።

---

251 Tamim Ansary, p. 230, 246
252 Bat Ye'or, pp. 93-95

የፈረንሳይ አብዮት፣ ግላዊነት፣ የሃይማኖት እኩልነት፣ እንዱስትሪያዊነት፣ ብሔርተኝነት፣ ኮሚዩኒዝም፣ ዲሞክራሲ፣ ዓለማዊነት፣ ትምሕርት፣ ሙዚቃ፣ የባቡር ሐዲዶች፣ ክርስቲያን ሚስዮናውያን እና ኢንተርኔትን የመሳሰኩት የአውሮፓ ሐሳቦችም ወደ ሙስሊሙ ዓለም ገቡ። እነዚህ ሐሳቦች በተለያዩ ቡድኖች የተለያዩ አቀባበሎች ነበሯቸው። የተጨቆኑት የምሥራቃዊ አውሮፓና የመካከለኛው ምሥራቅ ክርስቲያኖች እኩልነትን ወይንም ከእስልምና ነፃነትን እንደ ማግኛ መንገዶች የተቀበሏቸው ሲሆን ብዙ ጊዜ ግን በውጤቱ የከፋ ግፍ ይከተላቸው ነበር።[253] ብዙ ሙስሊሞችም ተቀብለው ነበር። ነገር ግን በአጠቃላይ ብዙዎች ይህንን ለእስልምና ችግር የተሰጠ ምዕራባዊ ችግር አድርገው የቆጠሩት ሲሆን ከራሱ ከእስልምና ውስጥ መፍትሄ እንዲመጣ ይሹ ነበር።

## ቀጣይ አቅጣጫ ምንድነው?

ሙሐመድና የመጀመርያዎቹ ጂሃዳውያን የእስልምናን ኢምፓየር ሲመሠርቱ በፊታቸው ያጋጠማቸው ሕዝብ ሁሉ በመውረር ባርያ አድርገዋል። እስልምና በምድር ላይ እየተንቀሳቀሰ ያለ የፈጣሪ እጅ ተደርጎም ታስቦ ነበር። የሞንጎል ጭፍጨፋ የሆነ ችግር መኖሩን አመላከተ። ከሞንጎሎች በኋላ የአውሮፓውያን ክንድ ሲፈረጥም ሙስሊሞች ከአንዱ ውድቀት ወደ ሌላው እየተሸጋገሩ እዚህ ደረሱ። ያ ገናናነት አክትሞለታል። ሙስሊሞች ዛሬ ለታሪክ ያላቸው መረዳት ይህ ሲሆን ጥያቄን ያጭርበቸዋል፤ ቀጣይ አቅጣጫ ምንድነው? አንዳንዶች ወደ ቁርኣንና ወደ ሙሐመድ ምሳሌነት መመለስ ይገልጋሉ፤ ሌሎች የዓለም ዜጎች በመሆን የምዕራባውያን ሐሳቦችን ብቻ ሳይሆን ሁሉንም ዓይነት ሐሳብ መቀበል ይገልጋሉ፤ ሁለቱን መቀላቀል የሚፈልጉ ሰዎች ደግሞ አሉ።

ለክርስቲያኖች ቢያንስ ሁለት ተግባራዊ መንገዶች አሉ፤ የመጀመርያው የእስልምናና የሙስሊሙ ዓለም መፃዒ ጊዜ ምን ሊሆን እንደሚችል መጠየቅ ነው። ሁለተኛው ሙሐመድ የመሠረተው ግዛተ መንግሥት እንደ ማንኛውም ሰው ሠራሽ መንግሥት መፈራረሱን ማሳየት ነው። የእግዚአብሔር የትንሣኤ መንግሥት ብቻ ነው ዘላለማዊ ሆኖ የሚኖረው። ይህ ነው የነቢያት መልእክት።

## መደምደሚያ

በዚህ ምዕራፍ የእስልምናንና የታሪክን ጉዳይ ተመልክተናል። ታሪክ ለሙስሊሞች ጠቃሚ እንደሆነ አይተናል የሙሐመድ እና የባልደረቦቻቸው ህይወት ለታሪካቸው መነሻ ነው። እስልምና ድል የተቀዳጀበት፣ ቅኝ የገዛበት፣ የተገዛበት ወርቃማ ጊዜ እንደነበረው አይተናል።

---

253 ለምሳሌ ያህል ቱርኮች በአርመኖች ላይ የፈፀሙት የዘር ማጥፋት ጭፍጨፋ

# በተደጋጋሚ ለውይይት የሚቀርብ ታሪክ

1. *ሙሐመድ ራስን ለመከላከል ብቻ ነበር የተዋጋው። ጂሃድ ራስን መከላከል ነው።* ይህ ሐሳብ ገለባ ነው። የሙሐመድን የሕይወት ታሪክ፣ የእስልምናን አምፓየር ታሪክ እንዲሁም የቁርኣንንና የእስልምና ሕግጋትን ትምሕርቶች የሚክድ ነው።

   ብዙ ጊዜ በአሜሪካ የሚኖሩ ሙስሊሞች ጂሃድ ማለት መልካም ሰው ለመሆን ጥረት ማድረግ ነው ሲሉ ይደመጣሉ። ነውጠኝነት እንደሆነ የሚያስቡት ፀረ ሙስሊም አመለካከት ያላቸው በጥላቻ ቸተሞሉ ሰዎች ብቻ ናቸው ይላሉ። ነገር ግን ከሙሐመድ ዘመን ጀምሮ ለነበሩት ሙስሊሞች ጂሃድ የነበረውን ታሪካዊ ትርጉም ችላ ይላሉ። ጂሃድ ከጦርነት ጋር ግንኙነት እንደሌለው የሚያስብ ሰው ከሙሐመድ ዘመን ጀምሪ ጂሃድ ተብሎ የተጠራውን የጦርነት ታሪክ ዞር ብሎ መመልከት ያስፈልገዋል።[254]

2. *ሙስሊሞች ሮማውያንና ፋርሳውያንን በወረሩ ጊዜ በሮማውያንና ፋርሳውያን ስር የተጨቆኑትን ነፃ ለማውጣት ነበር የተዋጉት።* ይህ ሐሰት ነው ምክንያቱም ሙስሊሞች የሮማውያንና ፋርሳውያንን አገዛዝ በራሳቸው አገዛዝ ተክተዋልና። ቅብጦች፣ አረቦች፣ ሦርያውያን፣ አይሁድ፣ አርመናውያን፣ ከለዳውያንና አሦራውያን አዲስ ገዢዎች ናቸው የመጡባቸው፤ በነዚህ አዲስ ገዢዎች ስር ብዙ ጭቆናና ሥቃይ ደርሶባቸዋል፤ ጠይቋቸው።

3. *ዘመናዊው ዓለም ለደረሰበት ሳይንሳዊ ዕድገት የእስልምና ውለታ አለበት።*

   ብዙ እስላማውያን ዘመናዊው ሳይንስ የእስልምና ሥልጣኔ ባለ ዕዳ እንደሆነ ቢናገሩም እስልምና *ጃህሊያ* ብሎ ከሚጠራው ከእርሱ ዘመን በፊት ከነበሩት ሥልጣኔዎች ስለወሰዳቸው ሳይንሳዊ ጉዳዮች መናገር አይፈልጉም። የእስላማዊ ሳይንስ ምንጭ ምን እንደሆነ ሊነግረን የሚችል ሙስሊም ይኖራል? ከቁርኣን፣ ከሐዲስ ወይንስ በቀጥታ ከሰማይ በመላእክት አማካይነት መጣ? የአረብ ሥልጣኔ እስከ ስምንተኛው ክፍለ ዘመን አጋማሽ ድረስ ሳይንስ የሚባል ነገር አላየም። በሙሐመድ ዘመንም ሆነ ኹላፋ ኢ ረሽዲን (በትክክል የተመሩ ኸሊፎች) ዘመን ሳይንስ ነበር ለማለት የሚያስደፍር ምንም ነገር አልነበረም። በእስልምና ውስጥ ሳይንስ ያበበው በለዘብተኛው የአባሲድና የኦቶማን ቱርኮች ዘመን ነበር። ይህ የሆነው ደግሞ አበሲዶች ግሪኮችን፣ ሕንዶችን፣ ቻይናዎችንና ሌሎች ሳይንሳዊ እሳቤ የነበራቸውን ሕዝቦች መበመቀበላቸውና ሥራዎቻቸውን ወደ አረብኛ በማስተርጎማቸው ምክንያት ነው። አብዛኞቹ እነዚያ

---

[254] Tamim Ansary, p. 354

ሳይንቲስቶች በባግዳድ የተሰባሰቡ ክርስቲያኖች፣ አይሁድ፣ ሙስሊሞችና አልፎም ቡዲህስቶች እንዲሁም ከሕንድ የመጡ ሒንዱዎች ነበሩ።[255]

ይህ ማለት ሙስሊሞች ሳይንስን የተማሩት ከወረሯቸው ሕዝቦች እንጂ ከሙሐመድ አይደለም ማለት ነው። ሙሐመድ ስለ ሳይንስ የነበረው መረዳት ዋጋ ቢስ ነበር።

> አቡ ሁረይራ እንዳወራው ነቢዩ እንዲህ አሉ "በማናችሁም መጠጥ ውስጥ ዝንብ ብትወድቅ ወደ ውስጥ አጥልቃችሁ ድፈቋት ምክንያቱም በአንድ ክንፏ ላይ በሽታ በሌላው ላይ ፈውስ ይዛለችና"። (ሳሂህ አል-ቡኻሪ ቅፅ 4፣ መጽሐፍ 54 ቁጥር 537)

ሳይንስን ከሌሎች በመማር ለሳይንስ ዕድገት አስተዋፅዖ ማበርከታቸው እሙን ነው።

4. *ሙስሊሞች የጥንት ዕውቀቶችን በሙሉ ወደ አረብኛ በመተርጎም አቆይተዋል።*[256]
   ይህ በብዙ ምክንያቶች ሐሰት ነው። የመጀመርያው እነዚህ ሥራዎች መጀመርያ በተጻፉበት ቋንቋ በግሪኮችና በፋርሳውያን ተጠብቀዋል። ሁለተኛው ሙስሊሞች ጠብቀው ያቆዩት ለእስልምና መስፋፋት ጠቃሚ የነበሩትን ሥራዎች ብቻ ነበር። በእስልምና ወረራ ምክንያት የጠፉ ጥንታውያን ሥራዎች አሉ። የትኛውንም ጥንታዊ ግጥም፣ ድራማና ታሪክ ጠብቀው አላቆዩም።[257]
5. *ክርስትና፣ እስልምናና ባርነት*
   የክርስትናው ዓለም በባርነት ውስጥ የተሳተፈበት ዘመን ነበር። ይህ በአትላንቲክ ላይ ሲደረግ በነበረው የባርያ ንግድ ሊገለፅ ይችላል። ይሁንና የክርስቲያኑ ዓለም ይህንን ወንጀል በማመን የባርያ ንግድን አስቀርቷል። የእስልምናው ዓለም ግን ሰፊ የባርነት ንግድ ታሪክ ያለው ሲሆን ንግዱ እንዳይወገድም ተቃውሞ አሰምቷል።
   ባርነት አብሶም የጥቁር ባርነት በእስልምና ዋና ተቋማት ተቀባይነት ያለውና በተማሩ ሙስሊሞችና የሕግ ሊቃውንት እንዲሁም መልካም በተባሉት አማኞች ዘንድ ዕውቅናና የተቸረው ነው። ግብፅ በአረቦች ከተወረረች በኋላ በ639 እና 642 ዓ.ም. ቢላድ አል-ሱዳን ወይም "የጥቁሮች ምድር" ለሙስሊሙ ዓለም የባርያ ምንጭ ሆኖ ነበር። የባርያ ፈንጋዮች ዋና ዋና ምንጮች ጦርነት (ጂሃድ)፣ ድንገተኛ ጥቃት፣ ገባርነት፣ ግዢ እና ጠለፋ ነበሩ።[258]

---

255 S. Irfan Habib, *Jihad or Ijtihad*, India: HarperCollins, 2012, p. 55
256 Prof. Masud ul-Hasan, vol. 1, p. 596
257 Bernard Lewis, *What Went Wrong? Western Impact and Middle Eastern Response*, England: Oxford University Press, 2002, p. 139.
258 John Alembillah Azumah, *The Legacy of Arab-Islam in Africa*, Oxford, England: One World, 2001, p. 141.

የሙስሊም አፍሪካን አብዛኛውን ክፍል በተመለከተ ግን አውሮፓውያን ከመምጣታቸው ከብዙ ክፍለ ዘመናት በፊት የባርያ ንግድ የተቀናጀና ተቋማዊ ይዘት የነበረው ነው።[259]

የእስልምና ቅድስት ከተማ የሆነችው መካ "የዓለም የባርያ ንግድ ማዕከል" ሆና እስከ ሃያኛው ክፍለ ዘመን ድረስ ያገለገለች ሲሆን ከምሥራቅ አፍሪካና ከሱዳን የመጡ ባርያዎች ወደ መላው አረብያና የሙስሊም ዓለም ይሰራጩ ነበር።[260]

የእስልምናው ዓለም ድል የነሳቸውንና በግዛቱ ወሰን ላይ የሚገኙትን ብዙ ሕዝቦች[261] ለ1000 ዓመታት ያህል ባርያ አድርጓል።[262] የባርያ ንግድ እንዲቀር ሲወሰን የተቃወመ ሲሆን መጨረሻ ላይ በምዕራባውያን ተፅዕኖ ምክንያት ለመተው ተገድዷል፤ ሆኖም ይህ ታሪክ እምብዛም አይታወቅም።

6. *እስልምና ክርስቲያንና አይሁድን ያከብራል፤ እነርሱ "የመጽሐፉ ሰዎች" ናቸው።* ቁርኣን ክርስቲያኖችና አይሁድን ማስገበር አስፈላጊ መሆኑን ስለሚናገርና እስልምና የበላይ በሆነባቸው ከአንድ ሺህ ለሚልቁ ዘመናት ሁሉ ተግባራዊ ስለተደረገ ይህ አባባል ሐሰት ነው። ክርስቲያኖች የእስልምናውን ኢምፓየር ለማስተዳደር ማገልገላቸው እውነት ነው። ይህ የሆነበት ምክንያት ተፈላጊዎች በመሆናቸው ነው። እነዚያ አካባቢዎች ከመወረራቸው በፊት የሮምንና የፋርስን ግዛተ መንግሥታት ሲያስተዳድሩ ስለነበር ነገሮችን ለማስኬድ ሙስሊሞች እነርሱ የግድ ያስፈልጓቸው ነበር። በሙስሊሞች መካከል ባለጠጋ የነበሩ ክርስቲያኖች መኖራቸው እውነት ቢሆንም እነርሱም ተፈላጊዎች ስለነበሩ ነው። ዘኪዎስ ለሮማውያን አስፈላጊ እንደነበረው ሁሉ[263] ክርስቲያኖችም ለሙስሊሞች አስፈላጊዎች ነበሩ። ከክርስቲያኑ ማሕበረሰብ ግብርን በመሰብሰብ ለእነርሱ እንዲገዙ የሚያደርጉት እነርሱ ናቸውና። እነዚህ ተመሳጣሪዎች ባለጠጎች መሆናቸው እስልምና የክርስቲያኖችን መብት ስለማክበሩ ምሳሌ መሆን አይችሉም። ሙስሊሞች ከግዛታቸው ውጪ ከሚገኙት ክርስቲያን መንግሥታት ጋር ለመነገድ ክርስቲያን ነጋዴዎች ያስፈልጓቸው ነበር። ይህም እስልምና ክርስቲያኖችን ችሎ ስለማኖሩ ምሳሌ ሊሆን አይችልምለ። ለአብዛኞቹ ክርስቲያኖች እስላማዊ አገዛዝ ማለት ለብዙ አድልዎና ጥቃት የተጋለጠ ትጥቅ አልባ ሁለተኛ ዜጋ ሆኖ መኖር ነው። ሆኖም እስልምና ለክርስቲያኖች ያለውን አመለካከት በትክክል የሚያሳየው ክርስትናን የሚቀበል ሙስሊም መገደሉ ነው።

---

259 Azumah, p. 117

260 Azumah, p. 146

261 Hugh Kennedy, *The Great Arab Conquests*, U.S.A: Da Capo Press, 2007, pp. 222-223, 323, 367.

262 Bernard Lewis, pp. 11, 26, 85-89

263 ሉቃስ 19

7. *ክሩሴዶች ያለ ምንም ምክንያት የተቀሰቀሱ የወረራ ጥቃቶች ናቸው።* ይህ አባባል ሐሰት ነው ምክንያቱም በክርስቲያን ዓለም ላይ የተፈፀመውን የጂሃድ ታሪክ ይዘነጋልና።
8. *እስልምናና የእግዚአብሔር ዕቅድ።* ከእስልምና የወረራ ዘመናት አንስቶ ክርስቲያኖች እስልምና እግዚአብሔር ለዓለም ካለው ዕቅድ አኳያ እንዴት መታየት እንዳለበት ለመረዳት ሲጥሩ ነበር። ብዙ ምላሾችም ነበሩ፤ ለአንዳንዶች በከሃዲዋ ቤተክርስቲያን ላይ የመጣ የእግዚአብሔር ፍርድ ነው፣ ለአንዳንዶች ሙሐመድ በራዕይ መጽሐፍ ላይ የተነገረው የክርስቶስ ተቃዋሚ ነው፣ ለሌሎች ደግሞ እስልምና የተለየ ሃይማኖት ሳይሆን የክርስትና ኑፋቄ ነው። ምናልባትም እነዚህ ሁሉ ሐሳቦች ስለ እስልምና የተወሰነ እውነት የሚገልጡ ሊሆኑ ይችላሉ። ሆኖም ከመጽሐፍ ቅዱስ ግልፅ የሆነው ነገር ክርስቲያኖች ሙስሊሞችን መውደድ፣ ወንጌልን ከእስላማዊ ሐሰቶች መመከት፣ ሙስሊሞች ደግሞ የማዳኑን ወንጌል መስማት እንደሚገባቸው ነው። እነዚህ ለተመለከትናቸው ታሪኮች በሙሉ ቁልፍና መቋጫ ሊሆኑ ይገባቸዋል።

## ትግበራና ማጠቃለያ

1. ሙስሊም ወዳጃችሁን የእስልምናና የሙስሊሞች መፃዒ ጊዜ ምን ሊሆን እንደሚችል ጠይቁት።
2. ሙሐመድ የመሠረተው ግዛተ መንግሥት እንደ ማንኛውም ሰው ሠራሽ መንግሥት መፈራረሱን ጠቁሙ። የእግዚአብሔር የትንሣኤ መንግሥት ብቻ ነው ዘላለማዊ ሆኖ የሚኖረው። ይህ ነው የነቢያት መልእክት።

## ማጠቃለያ

በዚህ ምዕራፍ እስልምናንና ታሪክን ተመልክተናል። ታሪክ ለሙስሊሞች ወሳኝ መሆኑንና የሙሐመድና የተባባሪዎቹ ታሪክ ለዚህ ታሪክ ጅማሬ መሆኑን ተመልክተናል። እስልምና አብዛኛውን ዓለም የወረረበት፣ ቅኝ የገዛበትና ባርያ ያደረገበት ወርቃማ ዘመን እንደነበረው ተመልክተናል። ይህ ዘመን በሞንጎሎች ቢጠፋም ከሙስሊሞች ትውስታ ግን አልጠፋም። የእስልምና ክብር ቀለሙ እየፈዘዘ ሲሄድ የአውሮፓውያን ኢምፓየር ተነስቶ ሙስሊሞች በሁሉም ረገድ ተበልጠዋል፤ ዕጣ ፈንታቸውም በሌሎች የሚወሰንላቸው ሆነዋል። ለዚህ ደግሞ ከእስልምና ዘንድ የመፍትሄ ሐሳብ እስከ አሁን አልተገኘም። በመጨረሻም ሙስሊሞች በሚናገሩት ሐሰተኛ ታሪክ እንዳይታለሉ ክርስቲያኖች ይህንን ታሪክ ማወቅ እንደሚገባቸውና ለሙስሊሞች የተሻለ ተስፋ ያለው መፃዒ ዘመን ማሳየት እንደሚያስፈልጋቸው ተመልክተናል።

# ምዕራፍ 12

## የስብከት ምሳሌዎች እና እስልምና

ይህ የመጨረሻው ምዕራፍ በስብከቶቻችሁ፣ በመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ቡድኖቻችሁና በሌሎችም ክርስቲያናዊ አገልግሎት ውስጥ እስልምናን እንዴት እንደምትገልፁት ይዳስሳል። በዚህ ዘመናዊው ዓለም በሚከተሉት ምክንያቶች ይህንን ማድረግ እጅግ አስፈላጊ ነው።

- እስልምና ከዋናዎቹ የዓለማችን ንጽረተ ዓለማት መካከል አንዱ ሲሆን የሕዝበ ሙስሊሙ ብዛትና ተጽእኖም በአብዛኞቹ አገራት እያደገ ነው።
- በቤተክርስቲያንህ ጉባኤ አባላት የሆኑ ምዕመናን ሙስሊም ጓደኞች ወይም የሥራ ባልደረቦች ሊኖራቸው ይችላል።
- ለብዙ ክርስቲያኖች እስልምና እንቆቅልሽ በመሆኑ ለጥያቄዎቹ እንዴት ምላሽ እንደሚሰጡ አያውቁም። እንዲሁም በትምህርት ቤትም ሆነ በማህበራዊ ድረ-ገፅ ሙስሊም ጓደኞች ላሏቸው ልጆቻቸው ስለ እስልምና ምን ማለት እንዳለባቸውም አያውቁም።
- በአካልና በማህበራዊ መገናኛ ዘዴዎች እስልምና የሐሰት ወንጌልን በአደባባይ በስፋት በማስተማር ላይ ይገኛል፤ ስለዚህ ሐሳዊ ትምህርት ክርስቲያኖችን ማሳወቅ፣ ማስጠንቀቅና መጠበቅም አለብን።
- እስልምና ስለ ምስጢረ ሥላሴ፣ ምስጢረ ሥጋዌ፣ ስለ መጽሐፍ ቅዱስ እና የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ግልጽ እንድንሆን ያስገድደናል፤ ይህም ጥሩ ነገር ነው።
- ሙስሊሞች ቤተ ክርስቲያንን ይጎበኛሉ።
- እስልምና በክርስቲያን ወንድሞችና እህቶች ላይ ለደረሰባቸው ከፍተኛ ጭቆናና ስቃይ ምክንያት የነበረ፤ አሁንም እየሆነ ያለ እምነት ነው።

ስለ እስልምና በምናስተምርበት ጊዜ ተከታዮቹን ምሳሌዎች እንደ መግባቢያ መጠቀም እንችላለን፦ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ስለ ተሰጠን ድነት ስታስተምሩ፣ አምላክ እናንተን ለማዳን የሚሠራ ሆኖ በሁሉም ሃይማኖቶች አለመገለጡን ለማስረዳት እነዚህን ማጣቀሻዎች ከቁርኣንና ከሀዲስ መጥቀስ ትችላላችሁ።

> «ከመልክተኞች ብጤ የሌለኝ አይደለሁም። በእኔም በእናንተም ምን እንደሚሠራም አላውቅም። ወደእኔ የሚወረደውን እንጅ ሌላን አልከተልም። እኔም ግልጽ አስፈራሪ እንጅ ሌላ አይደለሁም» በላቸው። (ቁርኣን 46፡9)
>
> እሳቸውም [ሙሐመድ] እንዲህ አሉ፦ "እርሱ እንደሆን በአላህ ይሁንብኝ ሞት አሸንፎታል፤ መልካሙንም እመኝለታለሁ። በአላህ ይሁንብኝ እኔ የአላህ

መልእክተኛ ብሆንም አላህ ምን እንደሚያደርግብኝ አላውቅም።" በአላህ ይሁንብኝ ከሱ ወዲያ ማንንም ጻድቋል ብዬ መናገር አልችልም… (ሳሂህ አል-ቡኻሪ፣ ቅፅ 5፣ መጽሐፍ 58፣ ቁጥር 266)

ሙሐመድ ምን እንደሚገጥመው ካላወቀ ማንም ሙስሊም አላህ በእርሱ ላይ ሊያመጣ ያለውን ነገር ማወቅ አይችልም (ከጂሃዲስት ሰማዕት በስተቀር)። በእስልምና አላህ እናተን ለማዳን ምንም አላደረገም። ሆኖም ክርስቲያኖች በተፈጸመው የኢየሱስ ክርስቶስ ዓለምን በማዳን ሥራ (በመስቀል ላይ በከፈለው መሥዋዕት) ምክንያት ከእግዚአብሔር ጋር እንደሆኑና የት ቦታ እንደ ሚቆሙ ማወቅ ይችላሉ።

ይህ ምእራፍ ኢየሱስና መጽሐፍ ቅዱስ የተለዩ መሆናቸውን እንዴት ማሳየት እንደምትችሉ አዳዲስ ሐሳቦችን እንደሚሰጣችሁ ተስፋ አደርጋለሁ፤ ደግሞም በጉባኤያቶቻችሁ ያሉ ሰዎችን ለሙስሊም ጓደኞቻቸው ወንጌል እንዲሳተፉ አበረታቷቸው።

## በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ያሉ ርዕሶች

- አጠቃላይ ንፅርተ ዓለም መጽሐፍ ቅዱስን እና ቁርኣንን ማድረግ
- ስለ ኢየሱስ እና ሙሐመድ
- ስለ ያህዌ እና አላህ
- ስለ መቅደስ
- ስለ አምልኮ
- ስለ ሥላሴ
- ስለ ሥጋዌ
- ስለ ኃጢአት እና የሰው ተፈጥሮ
- ስለ ፍርድ
- ስለ መዳናችን
- ዳዊት እና ቤርሳቤህ፣ ሙሐመድ እና ዘይነብ
- ስለ ሐሳዊው ነብይ
- ስለ ማርያም/መርየም
- ስለ ጣዖት አምልኮ - ጥቁር ድንጋይ(ካዕባ)

## አጠቃላይ ንፅርተ ዓለም መጽሐፍ ቅዱስን እና ቁርኣንን ማድረግ

በመጽሐፍ ቅዱስና በቁርኣን መካከል ያለውን ልዩነት በማነፃፀር ማሳየት መጽሐፍ ቅዱስ ምን ያህል አስደናቂ እንደሆነ የምናረጋግጥበት ትልቅ መንገድ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ አንድ መጽሐፍ ሳይሆን የበርካታ ነቢያት መጽሐፍ ስብስብ ነው። ነገር ግን ከዚህ በተቃራኒ በቁርኣን ያለው ሙሐመድ የተናገረውን ቃል ብቻ ነው። ዘፍጥረትን ወይም ኢሳያስን ወይም

የነቢያትን አንዱንም መጻሕፍትን ቁርአን አልያዘም፤ ይልቅ ሙሐመድ የተናገረው የሙሐመድን ቃል ብቻ ነው የተሸከመው። ሙስሊሞች በነቢያት አያምኑም፣ ሙሐመድ ስለ ነቢያት የተናገረውን ግን ያምናሉ። እስልምና ለክርስቲያኖች "ነብያትን ራሳችሁ በግላችሁ አታንብቡ፤ ሙሐመድ ምን ለማለት እንደፈለጉ ያስረዳችኋል" በማለት ያስተምራል። እስኪ አንድ ሰው ወደ ቤተ ክርስቲያን መጥቶ "መጽሐፍ ቅዱስን አታንብብ ምን ማለት እንደፈለገ እኔ እነግርሃለሁ" አላችሁ እንበል። ምን አይነት ምላሽ ትሰጣላችሁ? ሙሐመድ ያደርገው ይህንኑ ተግባር ነው። ሁሉንም ነቢያት ብናነብ ጥሩ አይደለምን?!

## ኢየሱስ እና ሙሐመድ

ስለ ጌታችን ኢየሱስ ኃጢአት አልባነት ሕይወት ስታስተምሩ፤ ሙሐመድ ይህንን ለራሱ እንደማይናገር፤ ከእስላማዊ ምንጮች አጣቅሳችሁ ማሳየት ትችላላችሁ። ኢየሱስ ፍፁም ሰው እንዲሁም እንከን አልባ ሲሆን፤ ሙሐመድን ግን በእስላማዊ ምንጮች መሠረት ከኃጢአት የጸዳ አይደለም። ቁርአን ይህን ሐሳብ በተመለከተ እንዲህ ይላል፦

> እነሆ ከአላህ ሌላ አምላክ አለመኖሩንም ዕወቅ። ስለ ስህተትህም ለምእመናንም ምሕረትን ለምን። አላህም መዘዋወሪያችሁን፣ መርጊያችሁንም ያውቃል። (ቁርአን 47፡19)

ኢየሱስ ርኩሳን መናፍስት ይገዙለት ነበር፤ በዚህ ምክንያት ክርስቲያኖች መንፈሳዊውን ዓለም ፈፅሞ መፍራት የለባቸውም። በተቃራኒው ግን ሙሐመድ ለክፉ መናፍስት ተገዢ ነበር፤ እናም ዛሬ ሙስሊሞች መንፈሳዊውን ዓለም አጥብቀው እንዲፈሯቸው ግድ ሆኖባቸዋል። ምክንያቱም ሙሐመድን ሊነካ ከቻለ በሙስሊሙ ላይ ምን ያህል ሊሆን እንደሚችል በማሰብ ነው።

> አይሻ እንዳወራችው፦ በአላህ መልእክተኛ ላይ አስማቱ ሰርቶባቸው ከሚስታቸው ጋር የግብረስጋ ግንኙነት ሳያደርጉ  የሚያደርጉ ይመስላቸው ነበር። (ሳሂህ አል-ቡኻሪ 3268፣ ቅጽ 4፣ መጽሐፍ 54፣ ቁጥር 490)
>
> አነስ እንደተረከው፦ ነብዩ ወደ መጸዳጃ ቤት በሄዱ ቁጥር፦ "አላህ ሆይ! ከክፉ እና ከመጥፎ ነገሮች ሁሉ (ከክፉ ሥራ እና ከመጥፎ መናፍስት) በአንተ እጠበቃለሁ" ይሉ ነበር። (ሳሂህ አል-ቡኻሪ 142፤ ቅጽ 1፣ መጽሐፍ 4፣ ቁጥር 144)

ኢየሱስ እግዚአብሔርን አባት ብሎ ሲጠራው፤ በተቃራኒው ሙሐመድ ግን ባሪያ ብቻ ነው መሆን የምንችለው ስላለ ሙሐመድን ጨምሮ ተከታዮቹን ሙስሊሞች አምላካቸውን እስከዛሬ አባት ብለው ጠርተው አያቁም።

> ለአልረሕማን ልጅን መያዝ አይገባውም። በሰማያትና በምድር ያለው ሁሉ (በትንሣኤ ቀን) ለአልራሕማን ባሪያ ኾነው የሚመጡ እንጂ ሌላ አይደሉም። (ቁርአን 19፡92-93 እና 5፡18 )

ኢየሱስ ወዴት እንደሚሄድ ያውቅ ነበር ሙሐመድ ግን ቀደም ሲል እንደተመለከትነው አያውቅም።

> “ኢየሱስ መለሰ አላቸውም፦ እኔ ስለ ራሴ ምንም እንኳ ብመሰክር ከወዴት እንደመጣሁ ወዴትም እንድሄድ አውቃለሁና ምስክርነቴ እውነት ነው፤ እናንተ ግን ከወዴት እንደ መጣሁ ወዴትም እንድሄድ አታውቁም።” (ዮሐንስ 8፥14)

ነገረ መስቀልን በተመለከትን ጊዜ በተለምዶ በብዙዎቹ ዘንድ ቁርኣን የኢየሱስን መሰቀል ይክዳል ተብሎ እንዲያው በደፈናው ይታመናል። በምዕራፍ 7 ላይ እንደገለጽኩት እኔ ይህ አይነቱ አመለካከት የለኝም።

የኢየሱስ ታላቅ ተልእኮ በተመለከትን ጊዜ ዓላማው ወንጌልን መስበክና አሕዛብን ሁሉ የራሱ ደቀ መዝሙር ማድረግ ነው። በተፃራሪው የሙሐመድ ታላቅ ተልዕኮ ዓላማ እርሱን እንደ ነብይ አድርገው እንዲቀበሉና ያልተቀበሉትን በጂሃዳዊ አገዛዝ ድል ማድረግ ነው። ኢየሱስ ደቀመዛሙርቱን አገልጋዮች አድርጎ ወደ ዓለም ሲልክ፤ ሙሐመድ ግን ጂሃዲስቶችን ነበር የላከው።

> ከእነዚያ መጽሐፍን ከተሰጡት ሰዎች እነዚያን በአላህና በመጨረሻው ቀን የማያምኑትን፣ አላህና መልክተኛው እርም ያደረጉትንም እርም የማያደርጉትንና እውነተኛውንም ሃይማኖት የማይቀበሉትን እነርሱ የተዋረዱ ኾነው ግብርን በእጆቻቸው እስከሚሰጡ ድረስ ተዋጉዋቸው። አይሁድ ዑዘይር የአላህ ልጅ ነው አለች። ክርስቲያኖችም አልመሲሕ የአላህ ልጅ ነው አሉ። ይህ በአፎቻቸው (የሚናገሩት) ቃላቸው ነው። የእነዚያን ከነሱ በፊት የካዱትን ሰዎች ቃል ያመሳስላሉ። አላህ ያጥፋቸው። (ከእውነት) እንዴት ይመለሳሉ!... እርሱ ያ አጋሪዎቹ ቢጠሉም መልክተኛውን (ሙሐመድን) በቅን መንገድና በእውነተኛ ሃይማኖት ላይ ከሃይማኖት ሁሉ በላይ ይፋ ያደርገው ዘንድ የላከው ነው። (ቁርኣን 9፡29-33)
>
> ጁበይር ቢን ሀይያ እንደተረከው፡- ዑመር ሙስሊሞችን ወደ ታላላቆቹ አገሮች ጣኦታዊያንን እንዲዋጉ ላካቸው። አል-ሁርሙዛን እስልምናን በተቀበለ ጊዜ ዑመር (ረዐ) እንዲህ አለው፡- "እነዚህን ለመውረር ስላሰብኳቸው አገሮች ላማክርህ እፈልጋለሁ።" ... [ለነዚህ ሀገራት እንዲህ እንላለን] ነብያችን የጌታችን መልእክተኛ አላህን በብቸኝነት እስክትገዙ ወይም ጂዝያን እስክትሰጡ ድረስ እንድንዋጋችሁ ታዝዘናል። (ሳሂህ አል ቡኻሪ 3159፣ 3160፣ ቅጽ 4፣ መጽሐፍ 53፣ ቁጥር 386)

## ያህዌ እና አላህ

ዘዳግም 18:20 በአምላክ ትክክለኛ ስም መናገር ምን ያህል አስፈላጊ እንደሆነ ያሳየናል። በብሉይ ኪዳን አምላክ የሚለው ቃል ኤሎሂም ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥም ያለው የእግዚአብሔር ስም ያህዌ ነው። በቁርአን ውስጥ አምላክ የሚለው ቃል ኢላህ ነው። በቁርአን ውስጥ ያለው የአላህ ስም አላህ ነው። እስልምና ያህዌ የሚለውን ስም በአላህ ተክቷል። ሙሐመድ በአላህ እንጂ አንድም ቦታ በያህዌ ስም እንዳልተናገረ በዚህ እንረዳለን።

## መቅደስ

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ለመገናኛው ድንኳን/ቤተመቅደስ ትኩረት ተሰጥቶ ሲነገር፣ በተቃራኒ ቁርአን ግን የቤተመቅደስ ሥርዓት ሥነ-መለኮትን ፈፅሞ አያቀውም። ማለትም፣ እግዚአብሔር ከፈጠረው ሕዝቡ ጋር እንደሚኖር ምንም አይነት ፅንሰ-ሐሳብ በውስጡ አላስቀመጠም፤ በቅዱሱ አምላክና በኃጢአተኛ ሕዝብ መካከል የሚያስታርቅ የክህነት ሥልጣን፣ የእግዚአብሔርን ቁጣ ለመቀልበስ የስርየት መስዋዕትነት ሐሳብ በቁርአን ውስጥ ለሽታ ያህል እንኳ አናገኝም። ሙስሊሞች ቁርአን ስለ ገነት ሲገልጽ የቤተመቅደስን ቋንቋ ወይም ፅንሰ-ሐሳቦችን በመያዝ ነው ይላሉ፤ ይህ ግን በፍጹም ሐሰት ነው፤ መጽሐፍ ቅዱስ በሚገልፅበት መንገድ ቁርአን ፈፅሞ አይጠቀምም። ስለ መቅደስ ሥርዓት እነዚህን ልዩነቶች በማነፃፀር በቁርአን ውስጥ አለመኖሩን ማድመቅ ቤተ መቅደሱ ምን ያህል ውብ እንደሆነ ያሳያል።

## አምልኮ

በክርስትና አስተምህሮ መሠረት በኃጢአታችን ሙታን የነበርን፤ ከዚህም የተነሳ እኛ እግዚአብሔርን ማምለክ አንችልም ነበር። ለዚያም እግዚአብሔር እኛን ከዚህ አሮጌው ማንነት [ከኃጢአት ዝንባሌ] አንጽቶ አዲስ ፍጥረት አድርጎ ሲሠራን እርሱን ለዘላለም ማምለክ (ራዕይ 7፡9-12፣ ወዘተ) እንድንችል አድርጎን ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ፣ አዲሱ ፍጥረት በቤተመቅደስ ቋንቋና ለእግዚአብሔር አምልኮነት ተገልጧል። በእስልምና ግን ተቃራኒው ነው። አሁን አምላክን የማምለክ አቅም አለህ፣ ይሄን ካደረግክ ደግሞ አምልኮ በማይፈለግበት ገነት ውስጥ ሽልማት ታገኛለህ። ይሄም ሽልማት በቁርአን ውስጥ እንደተነገረው ደናግላንን ያካትታል (ቁርአን 56: 36)። ነገር ግን ከሁሉም በላይ፤ በእስላማዊ ገነት ውስጥ ምንም አምልኮ የለም። ምክንያቱም ጀነት የሽልማት ቦታ ናት (ቁርአን 56፡1-56)። እዚህ ጋር ይሄን የምትጠቀሙት አንድ ሙስሊም በኢስላማዊው ገነት ውስጥ ስለ አምልኮ ሲወያያችሁ ነው። ስለዚህ ስለ አምልኮ በምታስተምሩበት ጊዜ ሁሉም ሃይማኖታት አምልኮን አንድ ዓይነት አድርገው እንደማይመለከቱት ማስገንዘብ ትችላላችሁ።

## ክርስቲያኖች እና ሙስሊሞች አንድ አምላክ ያመልካሉን?

በኃጢአታችን ምክንያት ሙታን ስለሆንን፤ እግዚአብሔርን በእውነተኛ አምልኮ የሚያመልክ ማንም ሰው አልነበረም [ሮሜ3:11]። ምክንያቱም ሁላችን ኃጢአተኞች ነበርንና። ለአብ ፍጹም የሆነውን አምልኮ እንድንሰጥ ያደረገው ሥጋን በመልበስ የተገለጠው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ነው። አምልኮታችንንም የሚቀበለውም በእርሱ በኩል ብቻ ነው።

## ሥላሴ

እንደ የይሖዋ ምሥክሮች ሁሉ ሙስሊሞችም ሥላሴን አይቀበሉም። ነገር ግን፣ ሥላሴን ከተቃወሙ አሁንም አብን፣ ወልድንና መንፈስ ቅዱስን በትክክል ማስረዳት ይኖርባችኋል። ለይሖዋ ምስክሮች፣ አብ አምላክ ነው፣ ወልድ መልአክ ሚካኤል ነው፣ መንፈስ ቅዱስ ደግሞ ኃይል ብቻ ነው። ይህ ትርጓሜ በፍፁም አይሠራም። ዕብራውያን ምዕራፍ 1 እና ቆላስይስ 2፡ 18 ላይ ኢየሱስ መልአክ አይደለም፣ መንፈስ ቅዱስም ወደ አብ ስለ እኛ ይማልዳል ተብሏል፤ ስለዚህ ይሄ ማለት ኃይል አይደለም ማለት ነው። ለእስልምና ደግሞ እግዚአብሔር አብ (አባት) አይደለም፣ ኢየሱስ ሰው ብቻ ነው፣ መንፈስ ቅዱስ ደግሞ መልአኩ ገብርኤል ነው። በድጋሚ ይሄ ትርጓሜ አይሠራም። ምክንያቱም በቁርአን ውስጥ አላህ መንፈሱን በአዳምና በማርያም እፍ እንዳለ እናነባለን (21፡91)፤ ይህ ማለት አላህ ወደ አዳምና ማርያም መልአክን እፍ አለባቸው እንደ ማለት ነው። ስለዚህ ገብርኤል የሕይወት እስትንፋስ ይሆናል። ስለዚህ፣ ስለ ሥላሴ በምስታስተምሩበት ጊዜ ለቅዱሳት መጻሕፍት እውነት የሆነው ሥላሴ መሆኑንና ብቸኛው መፍትሔ እርሱ እንደሆነ በማሳየት ጉባኤያችሁን ማበረታታት ትችላላችሁ።

በሁለተኛ ደረጃ፡- በሥላሴ አስተምህሮ ውስጥ ምንም ችግር የለም፤ ስለዚህ ምስጢር ነው በሚል መዝጋት አያስፈልግም። እግዚአብሔር ከእኛ አእምሮ የላቀ ነው። እግዚአብሔር በባህርዩ ከእኛ በእጅጉ የተለየ በመሆኑ ምንነቱም ይሁን ማንነቱ በጊዜና በቦታ የተገደቡ አይደሉም። ሙስሊሞች ስለ ሥላሴ ለመረዳት የተቸገሩበት ምክንያት ከራሳቸው የመኖር ልምድ የመነጨ ሥነ አመክንዮ በመጠቀም ስለ እግዚአብሔር ምክንያታዊ የሆነውን ትርጓሜ ለመወሰን ማሰባቸው ነው። ጨርሰን ካወቅነውማ እርሱ እግዚአብሔር አይደለም ማለት ነው። ስለ እርሱ ጥቂት ዕውቀት ማግኘት መታደል ነው፤ ከዚያ ውጪ ሙሉ በሙሉ ልናውቀው አንችልም።ምክንያቱም እግዚአብሔር ከእኛ አእምሮ በላይ ነውና።

## ነገረ ሥጋዌ

ትሥጉትን ስናስተምር የምናምንበትን ነገር ለማብራራት እስልምናን መጥቀስ ጠቃሚ ነው። ምክንያቱም ሙስሊሞች ትሥጉት ማለት እግዚአብሔር ተፈጥሮውን ለውጦ ሰው ሆነ ማለት እንደሆነ ተምረዋልና። እኛ ግን የምናምነው ይህ አይደለም። መለኮት የሆነው ወልድ ሥጋን ገንዘቡ እንዳደረገ እናምናለን። ኢየሱስ ሁለት ባህሪያት አሉት፤ እርሱ ፍፁም አምላክ ፍፁም ሰው ነው። ይህ ሲሆን ግን ለአፍታም መለኮታዊ ኑባሬው አልተለወጠም። ወልድ በግዳጅ

ሳይሆን እንደ ጸጋ የሰውን ልጅ ወደ አባቱ ፍቅር ለማምጣት የሰውን ባሕርይ ገንዘቡ አደረገ። ስለዚህ የእስልምናን ስሁት መረዳትን ግልፅ አድርጎ ማብራራት የጌታችንን የማዳን ሥራው ግልጽ ለማድረግ ይረዳል።

የኢስላማዊ ሥነ-መለኮት ፀረ-ትሥጉት (አምላክ በሥጋ አይገለጥም) የሚለው አቋም ፈጣሪን ከፍጥረቱ ውስጥ እንዳይገባ ዘግቶታል። ይህም ቁርኣንና ሐዲስ የማይሉትን በማለት ነው።

> ወደ ጌታቸው ተመልካቾች ናቸው። (ቁርኣን 75: 23-24)
>
> መላእክትም ሰልፍ ሰልፍ ኾነው ጌታህ (ትዕዛዙ)[264] በመጣ ጊዜ... (ቁርኣን 89:22, 2:210)
>
> አቡ ሰዒድ አል-ኩድሪ እንደተረከው፡- "የአላህ መልእክተኛ ሆይ! የትንሣኤ ቀን ጌታችንን እናየዋለንን? እርሱም እንዲህ አለው፡- «ሰማዩ በጠራ ጊዜ ፀሐይንና ጨረቃን ለማየት ይከብዳችኋልን? አይደለም አልን። ፀሐይንና ጨረቃን (በጠራራ ሰማይ ውስጥ) ለማየትም እንደማትቸገር በዚያ ቀን ጌታችሁን ለማየት አትቸገሩም አላቸው።[...] ኃያሉ ጌታ በመጀመሪያ ጊዜ ካዩት ቅርጽ ሌላ መልክ ይመጣባቸዋል። «እኔም ጌታችሁ ነኝ» ይላቸዋል። (ሳሂህ አል ቡኻሪ 7439፣ ቅጽ 9፣ መጽሐፍ 93፣ ቁጥር 5328)

## ኃጢአት፣ ሰው እና ተፈጥሮ

በእስላማዊ ሥነ-መለኮት ሁሉም ሰው ንፁህ ሆኖ የተወለደ ሲሆን የሕይወት ዓላማ የተወሰነው የንጽሕና ደረጃን ለመጠበቅ ወይም መልሶ ለማግኘት ነው። የተለያዩ ሙስሊሞች የተለያዩ የጽድቅ ደረጃዎችን ያገኛሉ፤ ልክ መሰላል ላይ እንደመሆን ማለት ነው። ኃጢአት ከመሰላል እንድትወርድ ያደርግሃል፤ መልካም ሥራ ያወጣሃል። የተለያዩ ወደ አላህ የመቅረብ ደረጃዎች አሉ።

> ካዕባን ጎብኝዎችን ማጠጣትንና የተከበረውን መስጊድ መሥራትን በአላህና በመጨረሻው ቀን እንዳመነና በአላህ መንገድ እንደታገለ ሰው (እምነትና ትግል) አደረጋችሁን አላህ ዘንድ አይተካከሉም። አላህም በዳዮች ሕዝቦችን አይመራም። እነዚያ ያመኑት፣ ከአገራቸውም የተሰደዱት፣ በገንዘቦቻቸውና በነፍሶቻቸውም በአላህ መንገድ ላይ የታገሉት አላህ ዘንድ በደረጃ በጣም የላቁ ናቸው። እነዚያም እነሱ ፍላጎታቸውን ያገኙ ናቸው።(ቁርኣን 9፡19-20)
>
> ከምእመናን የጉዳት ባለቤት ከኾኑት በቀር ተቀማጮቹና በአላህ መንገድ በገንዘቦቻቸውና በነፍሶቻቸው የሚታገሉት አይተካከሉም። በገንዘቦቻቸውና በነፍሶቻቸው የሚታገሉትን አላህ በተቀማጮቹ ላይ በደረጃ አበለጠ። ለሁሉም

---

264 አረብኛው አላህ እንደ መጣ እንጂ ትዕዛዙ የሚል ቃል የለውም።

አላህ መልካሚቱን (ገነት) ተስፋ ሰጠ። ታጋዮቹንም በተቀማጮቹ ላይ አላህ በታላቅ ምንዳ አበለጠ። ከእርሱ ዘንድ በኾኑ ደረጃዎች (አበለጠ)። ምሕረትንም አደረገ። እዝነትም አዘነላቸው። አላህም መሓሪ አዛኝ ነው።(ቁርኣን 4:95-96)

ከፊላቸውን በከፊሉ ላይ እንዴት እንዳበለጥን ተመልከት። የመጨረሻያቱም አገር በማዕረጎች በጣም የከበረችና በመብለጥም የተለቀች ናት።(ቁርኣን 17:21)

በክርስትና አስተምህሮ ውስጥ ግን ሁሉም ሰው በእኩል ደረጃ በኢየሱስ በኩል ወደ አብ መምጣት ይችላል። በንፅህና ስለምንበላለጥ ሳይሆን ንፁህ በሆነው በክርስቶስ በኩል። ኢስላማዊው ግንዛቤና ድርጊት ግን እራስህን ከሌሎች ጋር ወደ ማወዳደር ማምራቱ አይቀሬ ነው።

ሁለተኛ፡- እንደ እስልምና እምነት ችግሩ በሰው ተፈጥሮ ላይ ሳይሆን በስርአቱ ላይ ነው። እስልምና ስርዓቱን መለወጥ ይፈልጋል። በእስልምና መሠረት የተፈጥሮ ለውጥ ሳይሆን የሥርዓት ለውጥ ያስፈልገናል። እስልምና ደግሞ ፍጹም ሃይማኖታዊ ሥርዓት ነው። ሁሉም ሌሎች ሃይማኖታዊ ሥርዓቶች ተበላሽተዋል ይላል።

ሦስተኛ፡ ይህ ሐዲስ እንደሚያሳየው ከሆነ ኃጢአት በእግዚአብሔር ፊት ትልቅ ችግር አይደለም።

"አቡ አዩብ አንሷሪ እንድዘገቡት የአላህ መልዕክተኛ እንዲህ አሉ "እናንተ ወንጀል (ኃጢአት) ባትሰሩ አላህም ከምድረገፅ ያስወግዳችሁ ነበር። በሌሎችም ወንጀል ሰርተው ምህረት (ይቅርታ) በሚጠይቁ ሕዝቦች ይተካችሁ ነበር። እርሱም ይቅር ይላቸው ነበር።" (ሳሂህ ሙስሊም 2748-2749; መጽ. 37, ቁ. 6621-6622)

## ፍርድ

እስልምና የኢየሱስን የመስቀል ላይ የማዳን ሥራ አጥብቆ ይቃወማል። ነገር ግን አሁንም እግዚአብሔር ኃጢአትን እንዴት እንደሚመዘግብ ማብራሪያ መስጠት አለበት። ቁርኣን በቂያማ ቀን ጥሩና መጥፎ ሥራችን በሚዛን እንደሚመዘን ያስተምራል።

ሚዛኖቹም የከበዱለት ሰው እነዚያ እነርሱ ፍላጎታቸውን ያገኙ ናቸው። ሚዛኖቹም የቀለሉበት ሰው እነዚያ እነርሱ ነፍሶቻቸውን ያከሰሩ ናቸው። በገሀነም ውስጥ ዘመውታሪዎች ናቸው። (ቁርኣን 23:102-103)

አላህ ሙስሊሞችን መጥፎ ሥራቸውንና መልካም ሥራቸውን በመመልከት፤ በዘፈቀደ መጠን በማባዛት ሚዛኖቻቸው የበለጠ መልካም ሥራ እንዲኖራቸው በማድረግ ይረዳቸው።

አላህ የብናኝን ክብደት ያህል አይበድልም። መልካም ሥራ ብትኾንም ይደራርባታል። ከእርሱም ዘንድ ታላቅን ምንዳ ይሰጣል።(ቁርኣን 4: 40)

በመልካም ሥራ የመጣ ሰው ለእርሱ ዐሥር ብጤዎችዋ አሉት። በክፉ ሥራም የመጣ ሰው ብጤዋን እንጅ አይመነዳም። እነርሱም አይበደሉም።(ቁርኣን 6:160)

እነዚህ (ይህንን ባዮች) በገነት ጓዶች ውስጥ ሲኾኑ እነዚያ ከሠሩት ሥራ መልካሙን ከነሱ የምንቀበላቸውና ከኅጢአቶቻቸውም የምናልፋቸው ናቸው። ያንን ተስፋ ይሰሰጡት የነበሩትን እውነተኛ ቀጠሮ (እንሞላላቸዋለን)።(ቁርኣን 46:16)

ስለዚህ በቁርኣን አስተምህሮ መሠረት አላህ ዝም ብሎ የእኛን ኃጢአት ይቅር ይላል የሚል ነገር አናገኝም። ይልቁንም ለፍርድ ቀን ለሙስሊሞች አድልዎ እንደሚያደርግ ይናገራል። መልካም ሥራቸውን ያበዛል መጥፎ ሥራቸውንም ይተዋቸዋል። ያለ ፍትሃዊነት ይምራቸዋል። በመስቀሉ ላይ ግን ከዚህ የተለየ ነገር እናያለን፤ ይኸውም የእግዚአብሔር ምሕረትና ፍትህ በእኩል ሁኔታ ይታያሉ።

## ድነት

ሙሐመድ ጂሃዲስቶችን የላካቸው የድነት መልእክት ሳይሆን ለእስልምና የመገዛት የመጨረሻ ማስጠንቀቂያ አድርጎ ነበር። መዳን በእስልምና አስፈላጊ ነው፤ ዋናው ማዕከላዊ መልእክት ግን እርሱ አይደለም። በኢስላም መዳንህ የሚወሰነው በምትሠራው ሥራ ላይ በመመርኮዝ ነው። በጂሃድ የሚሞቱ ሙስሊሞች በቀጥታ ወደ ጀነት እንደሚገቡ ቃል ኪዳን አላቸው። እነዚህ ሙስሊሞች የመዳን ዋስትና አላቸው።

በአላህም መንገድ ብትገደሉ ወይም፤ ብትሞቱ ከአላህ የኾነው ምሕረትና እዝነት (እነርሱ) ከሚሰበስቡት ሀብት በእርግጥ በላጭ ነው። ብትሞቱም ወይም ብትገደሉ በእርግጥ ወደ አላህ ብቻ ትሰበሰባላችሁ።(ቁርኣን 3:157-158)

ጃቢር ቢን አብደላህ እንደተረከው፡- በኡሁድ ጦርነት ቀን አንድ ሰው ወደ ነብዩ (ሶ.ዐ.ወ) ዘንድ መጣና፡- “ሸሂድ ብሆን የት እንደምሆን (ሲያል ወይስ ጀነት) ንገሩኝ?” አላቸው። ነቢዩም “በጀነት ውስጥ” ሲሉ መለሱ። ሰውዬው በእጁ የተሸከመውን ቴምር ጥሎ እስከ ሰማዕትነት ድረስ ተዋጋ።(ሳሂህ አል ቡኻሪ 4046; ቅጽ 5, መጽሐፍ 59, ቁጥር 377)

አንድ ሙስሊም ሸሂድ [ሰማእት] ካልሆነ ምን እንደሚደርስበት ማወቅ አይችልም። ይህ ብቻ አይደለም ሙሐመድ ራሱ እንኳን ምን እንደሚገጥመው አያውቅም ነበር (ቁርኣን 46:9፣ ሳሂህ አል-ቡኻሪ 7003፣ ቅጽ 9፣ መጽሃፍ 87፣ ቁጥር 131)

አብዛኞቹ ሙስሊሞች ወደ መቃብር እና ከዚያም በኋላ ወደ ጀነት መግባትን ተስፋ ያደርጋሉ። በእስልምና እንደ ክርስትና ለመዳን ተስፋ የሚደረግ የእግዚአብሔር የማዳን ተግባር የለም። በዓለም ላይ እንደ ክርስትና እግዚአብሔር እኛን ለማዳን ሲል የሠራውን ፍቅር የሚነግረን የለም አንድም ትምህርት የለም።

## ዳዊት እና ቤርሳቤህ፣ ሙሐመድ እና ዘይናብ

ዳዊት የሌላ ሰውን ሚስት (የኦርዮንን ሚስት) ተመኘ፤ እግዚአብሔርም በታላቅ ቁጣ ተቆጣ፣ ቀጣውም (2ሳሙ 11) ሙሐመድ ግን የሌላ ሰው ሚስት ተመኘ አላህም ሕጉን ሽሮት (ለልቡ ምኞት ሲል) ሰጠው።

> ከእለታት አንድ ቀን የአላህ መልእክተኛ ዛይድን ፍለጋ ወጡ። በበሩም ላይ የፀጉር ጨርቅ ተሸፍኖ ነበር፤ ነገር ግን ነፋሱ የበሩን መጋረጃ አንሥቶ እስኪገለጥ ድረስ ነፈሰ፤ የተጋረደው ተከፈተ። ዘይነብ በጓዳዋ ውስጥ ነበረች፣ ልብስ ሳትለብስ፣ ለእሷ ያለው አድናቆት [ፍላጎት] ወደ ነብዩ ልብ ውስጥ ገባ። (Al-Tabari, The History of al-Tabari, U.S.A.,New York: SUNY, vol. viii, p. 4)

ሙሐመድ ለዘይነብ ያለው ፍላጎት ግልጽ ነበር፤ ስለዚህም የማደጎ ልጁ ዘይድ ሙሐመድ ሚስቱን እንዲያገባትና እርሱ እንዲፈታት ጥያቄ አቀረበ። ይሁን እንጂ ይህን ጥያቄ ሲያቀርብ ምራትን (የልጅን ሚስት) ማግባት በአረብ ባሕል ፈፅሞ የተከለከለ ነበር። ከዚያም ሙሐመድ ሁሉም የማደጎ ልጆች እንደተሰረዙ አምላክ ነገረኝ አለ። (ከዚያ ወዲህ በእስልምና የማደጎ ልጅ አባት ተብሎ የመጠራት ሥርዓት የለም፤ ነገር ግን አባት ተብለው ሳይጠሩ ማሳደግን ብቻ ይለማመዳሉ)።

> አላህ ለአንድ ሰው በሆዱ ውስጥ ሁለትን ልቦች አላደረገም። ሚስቶቻችሁንም እነዚያን ከእነርሱ እንደናቶቻችሁ ጀርባዎች ይሁኑብን የምትሏቸውን እናቶቻችሁ አላደረገም። ልጅ በማድረግ የምታስጠጓቸውንም ልጆቻችሁ አላደረገም። ይህ በአፎቻችሁ የምትሉት ነው። አላህም እውነቱን ይናገራል። እርሱም ትክክለኛውን መንገድ ይመራል። (ቁርአን 33:4)

የማደጎ ልጅ አባት የመባል ሕግ አሁን ስለተሻረ ዘይድ የሙሐመድ ልጅ አልነበረምና ዘይነብም ምራትነቷ (የማደጎ ልጅ ሚስት መባል) ቀርቷል። ከዚያም ሙሐመድ አላህ እንዲህ ሲል እንደተናገረው ተናግሯል፡-

> ለእዚያም አላህ በእርሱ ላይ ለለገሰለትና (አንተም ነጻ በማውጣት) በእርሱ ላይ ለለገስክለት ሰው (ለዘይድ) አላህ ገላጩ የሆነን ነገር በነፍስህ ውስጥ የምትደብቅና አላህ ልትፈራው ይልቅ የተገባው ሲሆን ሰዎችን የምትፈራ ሆነህ «ሚስትህን ባንተ ዘንድ ያዝ፤ (ከመፍታት) አላህንም ፍራ» በምትል ጊዜ (አስታውስ)። ዘይድም ከእርሷ ጉዳይን በፈጸመ ጊዜ በምእምናኖች ላይ ልጅ አድርገው ባስጠጉዋቸው (ሰዎች) ሚስቶች ከእነርሱ ጉዳይን በፈጸሙ ጊዜ (በማግባት) ችግር እንዳይኖርባቸው እርሷን አጋባንህ። የአላህም ትእዛዝ ተፈጻሚ ነው።(ቁርአን 33:37)

ሙሐመድ የማደጎ ልጁን ሚስት ተመኘ፤ ከዚያም አላህ እርሷ ከእርሱ ጋር ጋብቻ እንዳትፈፅም የሚከለክለውን የአባትነትና የልጅነት ሕግ እንደለወጠው ተገለጠልኝ በማለት ተናገረ። ይህ ክስተት እንደ ዳዊትና ቤርሳቤህ ታሪክ ነው፤ ነገር ግን በተቃራኒው ነው። ሙሐመድ በሕይወት ሳለ ኢየሱስ እንዳደረገው ለእግዚአብሔር ታዛዥ ሆኖ አልተገኘም። በሙሐመድ ጉዳይ አምላኩ የልቡ ምኞት የሚሻውን ሁሉ [የተከለከሉትንም ጨምሮ] እንዲያገኝ ሥርዓቱንና ሕግጋቱን ይሽርለታል።

> አይሻ [ከነብዩ ሚስቶች እንዷ የሆነችው] እንዲህ አለች፦ "እኔ እንደሚመስለኝ ጌታህ (አላህ) ያንተን ፍላጎት ለሟሟላት ይፈጥናል።" (ሳሂህ አል ቡኻሪ 4788; ቅጽ 6, መጽሐፍ 60, ቁጥር 311)

## ሐሳዊው ነብይ

መጽሐፍ ቅዱስ በብዙ ሥፍራዎች ደጋግሞ ስለ ሐሰተኛ ነቢያትና ከእነርሱ እንድንጠበቅ ያስጠነቅቀናል። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የሕይወታቸውን ፍሬ በማየት በቀላሉ መለየት እንደምንችል እንዲህ በማለት ገልጾልናል፦

> የበግ ለምድ ለብሰው ከሚመጡባችሁ በውሥጣቸው ግን ነጣቂዎች ተኵላዎች ከሆኑ ከሐሰተኞች ነቢያት ተጠንቀቁ። ከፍሬያቸው ታውቋቸዋላችሁ። ከእሾህ ወይን ከኵርንችትስ በለስ ይለቀማልን? እንዲሁ መልካም ዛፍ ሁሉ መልካም ፍሬ ያደርጋል፥ ክፉም ዛፍ ክፉ ፍሬ ያደርጋል። (ማቴዎስ 7፡5-7)

1. ቀደም ባለው ክፍል እንደዳሰስነው ከሆነ ሙሐመድ የሌላውን ሰው ሚስት [የማደጎ ልጁን ሚስት ጨምሮ] እንዴት እንደሚመኝና ከዚያም አምላኩን ለገዛ ልቡ ምኞት በማስገዛት ሊወስዳት እንደሚችል እንደነገረው አይተናል። ይህ ተግባር ደግሞ የእግዚአብሔርን ቀጥተኛ ትእዛዛት የሚጻረር ስለሆነ አምላክ እንዲህ ዓይነት ነገር በፍጹም አይናገርም። በዚህ ሚዛን መሠረት ደግሞ ይህ የእውነተኛ ነቢይ ተግባርና የሕይወት ፍሬ ፈፅሞ አይደለም።

2. ሙሐመድ ተከታዮቹ እስከ አራት ሚስቶች እንዲያገቡ ፈቅዶላቸዋል (ቁርአን 4፡3፣ 70፡ 29-30)፣ ነገር ግን ለራሱ የፈለገውን ያህል ሴቶችን መድረስ [ወሲብ ማድረግን] አላህ እንደፈቀደለትና ከተከታዮቹ በተሻለ ልዩ እድል እንደሰጠው ተናግሯል።

> አንተ ነቢዩ ሆይ! እኛ እነዚያን መህሮቻቸውን የሰጠሃቸውን ሚስቶችህን፣ አላህ ባንተ ላይ ከመለሰልህም እነዚያን እጅህ የጨበጠቻቸውን ምርኮኞች፣ እነዚያንም ከአንተ ጋር የተሰደዱትን የአጎትህን ሴቶች ልጆች፣ የአክስቶችህንም ሴቶች ልጆች፣ የየሹማህንም ሴቶች ልጆች፣ የየሹሜዎችህንም ሴቶች ልጆች (ማግባትን) ለአንተ ፈቅደንልሃል። የአመነችንም ሴት ነፍሷን (ራሷን) ለነቢዩ ብትሰጥ ነቢዩ ሊያገባት የፈለገ እንደ ኾነ ከምእምናን ሌላ ላንተ ብቻ የጠራች ስትኾን (ፈቀድንልህ)። በእነርሱ (በምእምናን) ላይ በሚስቶቻቸውና እጆቻቸው በጨበጧቸው (ባሮች

ነገር) ግዴታ ያደረግንባቸውን በእርግጥ ዐውቀናል። ባንተ ላይ ችግር እንዳይኖር (ያለፉትን ፈቀድንልህ)። አላህም መሓሪ አዛኝ ነው። (ቁርኣን 33:50)

የሙሐመድ ሚስቶች እነማን እንደሆኑ በእስላማዊ ምንጮች መሠረት እናውቃቸዋለን። ሚስቶቹ የፖለቲካ ጥምረት ውጤቶችም አልነበሩም፤ ካላው ከልብ ፍላጎት የተነሳ ዝም ብሎ ይመኛቸዋል። ሙሐመድ ለሌሎች ሰሃባዎቹ [ተከታዮቹ] የሰበከውን በተግባር በመሻር ሲጠመድ እንመለከታለን።

3. በመድብለ ጋብቻ ውስጥ ሚስቶች ከባል ጋር እኩል ጊዜና የውርስ ድርሻ የማግኘት መብት አላቸው። ነገር ግን ሙሐመድ አምላኩ አላህ ላገባቸው ለሚስቶቹ የጋብቻ መብት የመጠየቅ ፍቃድ እንደማይሰጥና ክብር እንደሌለው፤ ይልቁንም ለሊት [ለወሲብ] የፈለጋትን ሚስት ማግባት እንደሚችል ተናግሯል ያለው።

> ከእነርሱ የምትሻትን ታቆያለህ። የምትሻውንም ወደ አንተ ታስጠጋለህ። (በመፍታት) ከአራቅሃትም የፈለግሃትን (በመመለስ ብታስጠጋ) በአንተ ላይ ኀጢአት የለብህም። ይህ ዓይኖቻቸው ወደ መርጋት፣ ወደ አለማዘናቸውም፣ ለሁሉም በሰጠሃቸው ነገር ወደ መውደዳቸውም በጣም የቀረበ ነው። አላህም በልቦቻችሁ ውስጥ ያለውን ሁሉ ያውቃል። አላህም ዐዋቂ ታጋሽ ነው። (ቁርኣን 33:51)

ይህንን ታሪክ ከሙሐመድ ሚስቶች መካከል አንዷ በምሬት ማስታወሷ ምንም አያስደንቅም። አይሻ በዘገበችው ሐዲስ ላይ እንዲህ እናነባለን፦

> አይሻ እንዳስተላለፈችው፦ ለአላህ መልእክተኛ እራሳቸውን እየመጡ አሳልፈው በሚሰጡ ሴቶች ቅናት ተሰማኝ፤ አላህ ሱብሃነሁ ወተኣላ ይህንን አያ አወረደ (ቁርኣን 33:51)፦ ከእነርሱ (ከሴቶቹ) መካከል የምትፈልጋትን ታቆያለህ። የመረጥሃትንም ሴት ለራስህ ትወስዳለህ ። የትውካትንም ሴት መልሰህ ብትፈልጋት ወደራስህ ብታስጠጋት በአንተ ላይ ኀጢአት የለብህም። አይሻ እንዲህ አለች "እኔ እንደሚመስለኝ ጌታህ (አሏህ) ያንተን ፍላጎት ለሚሟላት ይፈጥናል።" (ሳሂህ ሙስሊም መጽሐፍ 17፣ ሐዲስ 64፣ ሳሂህ አል-ቡኻሪ ሐዲስ 4788, እና ቅጽ 6, መጽሐፍ 60, ሐዲስ 311)ስ

እንግዲህ ሙሐመድ ተአማኒ በሆኑ በእስላማዊ ምንጮች መሠረት በግልጽ እንደምናነበው ከራሱ የልብ ምኞት አንጻር የአምላክን ሕግና ሥርዓት ጥሷል፤ በዚህም ምክንያት ሐሰተኛ ነቢይ ነው። ሐዋርያው ጳውሎስ እንዲህ ላሉና ለገዛ ጥቅማቸው ሲሉ ወንጌልን ስለሚቀይሩ ሰዎች እንዲህ ሲል በመልእክቱ አስጠንቅቆናል፦

> በክርስቶስ ጸጋ እናንተን ከጠራችሁ ከእርሱ ወደ ልዩ ወንጌል እንዲህ ፈጥናችሁ እንዴት እንዳለፋችሁ እደነቃለሁ፤ እርሱ ግን ሌላ ወንጌል አይደለም፤

የሚያናውጡአችሁ የክርስቶስንም ወንጌል ሊያጣምሙ የሚወዱ አንዳንዶች አሉ እንጂ። ነገር ግን እኛ ብንሆን ወይም ከሰማይ መልአክ፥ ከሰበክንላችሁ ወንጌል የሚለይ ወንጌልን ቢሰብክላችሁ፥ የተረገመ ይሁን። አስቀድመን እንዳልን እንዲሁ አሁን ሁለተኛ እላለሁ፥ ከተቀበላችሁት የተለየውን ማንም ቢሰብክላችሁ የተረገመ ይሁን። (ገላትያ 1፡6-9)

ሙሐመድ መልአክ ወደ እርሱ መጥቶ አላህ አባታችን አይደለም፣ ኢየሱስም የአላህ ልጅ አይደለም (ቁርኣን 5፡18፣ 19፡92-93)፣ መንፈስ ቅዱስ ደግሞ መልአኩ ገብርኤል ነው ብሎ እንደተናገረው አስተማረ። ይህ የሐሰት ወንጌል ነው፤ ሲከፋም ኑፋቄ ነው። ስለ ጌታችን መሰቀል በተመለከተ ሙሐመድ እርግጥ የሆነ መፍትሔ ከመስጠት ይልቅ ሙስሊሞችን ግራ በማጋባት፤ ሙስሊሙም ማሕበረሰብ ወደ ጌታችን የማዳን መንገድ ከመመልከት ይልቅ በራሳቸው የጽድቅ ሥራ ራሳቸውን ለማዳን እንዲሞክሩ አድርጓል። በእነዚህ ሁሉ ምክንያቶች ሙሐመድ የሐሰተኛ ነቢይ እውነተኛ ምሳሌ ነው ብንል ማጋነን አይሆንም።

## ማርያም/መርየም

ማርያምና መርየም በአጠራራቸው የተለያዩ ቢሆኑም የአንድ ሴት ስም ናቸው። በቁርኣን አዘጋገብ መሠረት  የኢየሱስ እናት የነበረችው የአሮንና የሙሴ እህት ነች።

> በእርሱም የተሸከመቺው ሆና ወደ ዘመዶቿ መጣች። «መርየም ሆይ! ከባድን ነገር በእርግጥ ሠራሽ» አሏት። የሃሩን እኅት ሆይ! አባትሽ መጥፎ ሰው አልነበረም»። እናትሽም አመንዝራ አልነበረችም» አሏት።[....] ይህ የመርየም ልጅ ዒሳ ነው። ያ በርሱ የሚጠራጠሩበት እውነተኛ ቃል ነው። (ቁርኣን 19:27-34)

ከችሮታችንም ወንድሙን ሃሩንን ነቢይ አድርገን ሰጠነው። (ቁርኣን 19:53)

ሙሐመድ የኢየሱስን እናት የኢምራን ልጅ እንደሆነች ገልጿል። ኢምራን የአረብኛ አጠራር ሲሆን እምበረም ማለት ነው።

> የዒምራንን ልጅ መርየምንም... (ቁርኣን 66:12)
>
> “የእንበረም ሚስት ስም ዮካብድ ነበረ። እርስዋ በግብፅ ከሌዊ የተወለደች የሌዊ ልጅ ነበረች፤ ለእንበረምም አሮንንና ሙሴን እኅታቸውንም ማርያምን ወለደችለት። ”(ዘኍልቁ 26፥59)

ሙሐመድ ሁለቱን ሴቶች ማለትም የአሮንና የሙሴ እህት ማርያምና የኢየሱስን እናት ማርያምን ቀላቅሎዋቸዋል። ይሄ የሚያሳየው  ስለ ታሪካዊው አቀማመጥ [የጊዜ ሰሌዳ] ምንም ግንዛቤ እንደሌለው ነው።

## ጣኦት አምልኮ - ጥቁር ድንጋይ

“እኔ እግዚአብሔር አምላካችሁ ነኝና ለእናንተ ጣዖት አታድርጉ፥ የተቀረጸም ምስል ወይም ሐውልት አታቁሙ፤ ትሰግዱለትም ዘንድ በምድራችሁ ላይ የተቀረጸ ድንጋይ አታኑሩ።” ዘሌዋውያን 26፥1

በተጨማሪም እነዚህን ምስሎች ብወስድና በፊታችሁ ባስቀምጣቸው፣ እናንተም ብትመረምሯቸው ያደጋችሁበት ይህ ልማድ፤ የሰውን አይረቤ የእጅ ሥራዎች ማምለክ ምን ያህል ከንቱ እንደሆነ ታረጋግጣላችሁ። በጥንት ዘመን እስኩቴሶች የእስኩቴስን ሰይፍ፣ አረቦች ድንጋዮችን፣ ፋርሳውያንም ወንዞቻቸውን ያመልኩ ነበር። (Clement of Alexandria, c. 215, `Exhortation to the Heathen: Chapter 4', Ante-Nicene Fathers. ed. Alexander Roberts & James Donaldson; Massachusetts: Hendrickson, 1995. vol. 2, p. 184)

“አቡ ራጃ አል-ዑታሪደ እንዳወሳው:- ከዚህ ቀደም ድንጋይ እናመልክ ነበር። እናመልክ ከነበረው የተሻለ ድንጋይ ካገኘን የመጀመሪያውን ትተን አዲሱን እናመልክ ነበር። ነገር ግን ድንጋይ ካላገኘን ከመሬት አፈር እንሰበስብና በበግ ወተት ለውሰን እንዞረው ነበር። …” (ሳሂህ አል-ቡኻሪ ቅፅ 5 መጽሐፍ 59 ሐዲስ 661)

እስልምና ግን ንፁህ የፈጣሪ አምልኮ ነው ብሎ ይኩራራል። የእስልምና እምብርት ግን የጣዖት አምልኮ ተግባር ነው።

ቡኻሪ፣ ሙስሊምና አቡ ዳውኡድ በዘገቡት መሠረት:- "ዑመር ወደ ጥቁሩ ድንጋይ ቀረበና ሳመው፤ ከዚያም “አንተ ምንም የማትጠቅምና የማትጎዳ ድንጋይ ብቻ መሆንህ ምንም ጥርጥር የለውም። የአላህ መልእክተኛ ሲስምህ ባላይ ኖሮ አልስምህም ነበር” አለ።” አል-ኸታቢይ እንዲህ ብለዋል:- “ይህ የሚያሳየው የነቢዩን (ሰ.ዐ.ወ) ሱና መከተል አስገዳጅ መሆኑን ነው፤ ምክንያቱን ብንረዳውም ሆነ ባንረዳው ወይም ከጀርባው ያለው ጥበብ ቢገባንም ባይገባንም።” የዚህን መረጃ ትርጉም ሙሉ በሙሉ ባይረዱትም በሚሰሙት ሁሉ ላይ ግዴታን የሚጥል ነው። ይሁን እንጂ ጥቁሩን ድንጋይ መሳማችን ለድንጋዩ አክብሮት እንዳለን፣ ለእርሱ ያለንን ግዴታ መገንዘባችንና የአላህን በረከት ለማግኘት መንገድ እንደሚሆነን የሚያመለክት መሆኑ ይታወቃል።። (Sayyid Sabiq, Fiqh-us-Sunnah, Indiana, U.S.S አሜሪካን Trust Publications, 1991, vol. 5, p.75)

የISIS አባል አቡ ቱራብ አል ሙጋዳሲ በመካ ውስጥ ያለውን ካዓባን እንደሚያጠፉ ተናግረዋል - «አላህ የሻ ከሆነ በመካ ድንጋዮችን የሚያመልኩትን እንገድላቸዋለን፤ ካዕባንም እናጠፋለን።» ሰዎች ወደ መካ የሚሄዱት ድንጋዮቹን ለመንካት እንጂ ለአላህ አይደለም።"

(Reported ISIS Member Says They Will Destroy The Kaaba In Mecca, 'Kill Those Who Worship Stones')

ሙስሊሞች እስልምና ንጹሑን አምልኮ ያቀርባል ብላችሁ እንድታስቡ በማድረግ እንዲያታልሏችሁ አትፍቀዱ። ከእስልምና በፊት የነበረው ጣዖት አሁንም ድረስ እዚያው አለ።

## ማጠቃለያ

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ የሚገኙት ምሳሌዎች በአስተምህሮአችሁ ውስጥ በማካተት ስለ እስልምና ታስተምሩ ዘንድ ጉባኤያችሁን እንድታስታጥቁ እንደሚያበረታቱ ተስፋ እናደርጋለን ።

## የነገሩ ፍጻሜ

የዚህ መጽሐፍ ዓላማ ለሙስሊም ወዳጆችሁ ወንጌልን ስታካፍሉና ክርስቲያናዊ አስተምሕሮዎችን ስታብራሩ ከትክክለኛው ነጥብ መጀመር ትችሉ ዘንድ መርዳት ነው። እስልምናን ይበልጥ እንድትረዱ እንዳገዛችሁና ይልቁኑ የክርስትናን አስተምሕሮዎች ጥልቀት እንዲሁም የነቢያትን መልእክት መሰናሰልና በክርስቶስ ፍፃሜን ማግኘት በማሳየት እምነታችሁ በጠንካራ መሠረት ላይ የቆመ መሆን እንድትገነዘቡ እንደረዳችሁ ተስፋ አደርጋለሁ። ክርስትና እውነት መሆኑን አጥርታችሁ እንዳያችሁና ለሙስሊም ወዳጆችሁ ወንጌልን ለማካፈል ይበልጥ እንደተበረታታችሁ አምናለሁ።

ሙስሊሞች ሁሉ የተለያዩ መሆናቸውና ሳታናግሯቸው በፊት ቅድመ ግንዛቤ መያዝ እንደሌለባችሁ አስታውሱ። ማንነታቸውን ጠይቃችሁ ተረዱ። ውደዷቸው፤ ጸልዩላቸው።

ለሙስሊሞች ወንጌልን ማካፈል ለማንኛውም ሰው እንደማካፈል ነው፤ ልምድ በማዳበር እየተሻሻላችሁ ትሄዳላችሁ። ስለዚህ እነዚህን ነገሮች ማሰባችሁን እንድትቀጥሉ አበረታታችኋለሁ። እንድትናገሩ እግዚአብሔር የሚሰጣችሁን ዕድል ተጠቀሙ፣ በድረ ገፆች ላይ የሚገኙትን ወንጌልን ለማድረስ የሚያግዙ ጽሑፎችን ተጠቀሙ።

# መጽሐፍ ቅዱስ ምንድነው?

## በሳሙኤል ግሪን



## መጽሐፍ ቅዱስ ምንድነው?

መጽሐፍ ቅዱስ የክርስቲያኖች ቅዱስ መጽሐፍ ነው። በእንግሊዝኛ ባይብል የሚለው “ቢብሊያ” ከሚል የግሪክ ቃል የመጣ ሲሆን “መጻሕፍት” ማለት ነው።

መጽሐፍ ቅዱስ መጽሐፍ ብቻ ሳይሆን በተለያዩ ነቢያት፣ በተለያዩ ቦታዎችና በተለያዩ ቋንቋዎች በ1500 ዓመታት ውስጥ የተጻፉ የተለያዩ መጻሕፍት ስብስብ ነው። የሙሴን ሕግ (ቶራ)፣ የዳዊትን መዝሙር፣ የሰለሞንን መጻሕፍት፣ ኢሳይያስ፣ ኤርምያስ፣ ሕዝቅኤል፣ ዳንኤል፣ ሆሴዕ፣ ኢዩኤል፣ አሞፅ፣ አብድዩ፣ ዮናስ፣ ኢዮብ፣ ሚክያስ፣ ናሆም፣ ዕንባቆም፣ ሶፎንያስ፣ ሐጌ፣ ዘካርያስ፣ ሚልክያስና የመሳሰሉትን ነቢያት መጻሕፍት አካቷል። በማቴዎስ፣ ማርቆስ፣ ሉቃስና ዮሐንስ የተጻፈውን የኢየሱስን ወንጌል ይዟል። የሐዋርያትም ጽሑፎች በውስጡ ይገኛሉ።

| መጽሐፍ ቅዱስ | | | |
|---|---|---|---|
| **የሙሴ ሕግ (ቶራ)** | **የነቢያት መጻሕፍት** | **መዝሙራት** | **ወንጌል** |
| ‹‹---------------------- 1500 ዓመታት ----------------------›› | | | |

ቁርኣን ስለ ተውራትና ወንጌል (ኢንጂል) (ቁርኣን 3፡3)፣ የነቢያት መጻሕፍት (ቁርኣን 3፡84)፣ እና መዝሙራት (ዘቡር) (ቁርኣን 4፡163 ይናገራል፤ ክርስቲያኖችንም “የመጽሐፉ ሰዎች” በማለት ይጠራቸዋል (ቁርኣን 5፡68)።

**ክርስቲያኖች እነዚህ ሁሉ መጽሐፍ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ለምን ኖራቸው?**

ክርስቲያኖች ሁሉንም ነቢያት ስለሚቀበሉና በመካከላቸው አድልዎን ስለማያደርጉ ሁሉም መጽሐፍ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አሏቸው፤ ያነቧቸዋልም።

ሁለተኛ እግዚአብሔር በብዙ ነቢያት በኩል ተናግሮናል። መጻሕፍታቸው አንዳቸው በሌላቸው ላይ የተገነቡ ሲሆኑ በጋራ እንዲነበቡ የታሰቡ ናቸው። በጋራ በመሆንም የተሟላውን አምላካዊ መመርያ ይሰጡናል።

ክርስቲያኖች ስለ እግዚአብሔር የሚያምኑት ሁሉ አጠቃላዩን የነቢያት መጽሐፍት ያገናዘበ ነው።

የኢየሱስ ሐዋርያት ወንጌልን የተቀበሉ የነበሩ ቢሆኑም ከሙሴ ሕግ፣ ከነቢያትና ከመዝሙራት እየጠቀሱ ያስተምሩ ነበር፤ መጻሕፍቱንም ያነብቡ ነበር።

ከተለያዩ አገራት የሆኑ ብዙ ሕዝቦች ክርስትናን ሲቀበሉ እንደ ሐዋርያት ሁሉ የሙሴን ሕግ፣ ነቢያትን፣ መዝሙራትንና ወንጌልን ተቀብለው ማንበባቸውን ቀጠሉ። ዛሬም ቢሆን አንድ ሰው ክርስቲያን ሲሆን ወንጌልን ብቻ ሳይሆን የነቢያትን መጻሕፍት ሁሉ ይማራል። በክርስቲያን አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ ሁሉም የነቢያት መጻሕፍት በአደባባይ ይነበባሉ፣ ይሰበካሉ።

ክርስትና ሰዎች የሙሴን ሕግ፣ ነቢያትንና መዝሙራትን ከወንጌል ጋር በማጣመር እንዲያነብቡና እንዲቀበሉ በማስተማር ነው የተስፋፋው። የነቢያት ሁሉ መጻሕፍት በሰው ልጆች ሁሉ ይታወቁ ዘንድ ክርስቲያኖች እነዚህን መጻሕፍት ወደ አብዛኞቹ ቋንቋዎች ተርጉመዋል።

**እርስዎና ነቢያት**

ነቢያትን በሙሉ ማክበር ይፈልጋሉን? ትክክለኛው ነቢያትን የማክበርያ መንገድ እነርሱን መስማትና መጻሕፍታቸውን ማንበብ ነው። የእግዚአብሔርን ሁሉንም መልእክቶች ማወቅ ይፈልጋሉን? አንዱን ብቻ ሳይሆን ሁሉንም የነቢያት መጻሕፍት ማንበብ ይጠበቅቦታል።

እነዚህ ነቢያት በገዛ ቋንቋዎ ተተርጉመዋል። ክርስቲያኖች ቅዱሱን መጽሐፍ እንዲሰጡዎ ይጠይቁ፤ ወይንም ኦንላይን ፍለጋ ያድርጉ። የእግዚአብሔርን ነቢያት መጻሕፍት እንዳያነብቡ ማንም ሰው እንዲያሳስትዎት ወይንም እንቅፋት እንዲሆንብዎት አይፍቀዱ።

ይህንን ጸሎት መጸለይ ይሻሉን?

ሁሉን ቻዩ አምላካችን በነቢያቶችህ ልትናገረን ፈቃድህ ስለሆነ አመሰግንሃለሁ። ሁላቸውንም ማድመጥ እችል ዘንድ እርዳኝ። አሜን።

የምስራቹን

# ለሙስሊሞች ለማድረስ ከየት እንጀምር?

የዚህ መጽሐፍ ዓላማ ለሙስሊም ወዳጆችሁ ወንጌልን ስታካፍሉና ክርስቲያናዊ አስተምሕሮዎችን ስታብራሩ ከትክክለኛው ነጥብ መጀመር ትችሉ ዘንድ መርዳት ነው። እስልምናን ይበልጥ እንድታውቁ እንደሚያግዛችሁና ይልቁኑ የክርስትናን አስተምሕሮዎች ጥልቀት እንዲሁም የነቢያትን መልእክት መሰናሰልና በክርስቶስ ፍፃሜን ማግኘት በማሳየት እምነታችሁ በጠንካራ መሠረት ላይ የቆመ መሆኑን እንድትገነዘቡ እንደሚረዳችሁ እተማመናለሁ። ክርስትና እውነት መሆኑን አጥርታችሁ እንድታዩና ለሙስሊም ወዳጆችሁ ወንጌልን ለማካፈል ይበልጥ እንድትበረታቱ እንደሚያግዛችሁ ተስፋ አደርጋለሁ።

ለሙስሊሞች ወንጌልን ማካፈል ለማንኛውም ሰው እንደማካፈል ነው፤ ልምድ በማዳበር እየተሻሻላችሁ ትሄዳላችሁ። እንድትናገሩ እግዚአብሔር የሚሰጣችሁን ዕድል ሁሉ ተጠቀሙ።

**ሳሙኤል ግሪን**

ቄስ ሳሙኤል ግሪን አውስትራሊያዊ ዐቃቤ እምነት፣ ደራሲና የቤተክርስቲያን አገልጋይ ናቸው። ከሙስሊሞች ጋር ውይይቶችን በማድረግ በዓለም ዙርያ ይታወቃሉ።